የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ

አራተኛ መጽሐፍ

ከዶ/ር ላጵሶ ጌ· ድሌቦ
ረዳት የታሪክ ፕሮፌሰርና ደራሲ

1999

የመጽሐፉ የፊት ሽፋን

የመጽሐፉ የፊት ሽፋን በሰነድ፥ በትውፊት፥ በአርኪኦሎጂ፥ በሊንጉዊስቲክስና በፖሌአንቶሎጂ መረጃዎች ላይ በዘመናዊ የጥናት ሜቶዶሎጂ በአገርኛ ቋንቋ ያዘጋጀሁትና ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት በስሜን ምሥራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የተካሄደውን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገር፥ ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት በሥፍራና በጊዜ ሚዛን የሚያሳይ የአገሪቱ የመጀመሪያ የታሪክ ጎብረ ቀለም ካርታ ነው። መጽሐፉ በካርታው ላይ በመስመርና በቀለም ምልክቶች በአጭርና በጥቅል የቀረበ የኢትዮጵያ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ ዝርዝር መግለጫና ማብራሪያ ነው።

ይህ ካርታ በኢትዮጵያ ረጅምና በህውርታዊ የጥንት፥ የመካከለኛና የዘመናዊ ታሪክ ላይ አዘጋጅቼ ካቀረብኩት ሰፊ ጥናት ጋር፥ በኢትዮጵያ የካርታ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በ1988 በተዘጋጀው ብሔራዊ አትላስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕትመት ወጥቷል። ባለሥልጣኑ የካርታውን ቅጅ ስለሰጠኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

በ1999 ታተመ።

Typesetting by M. A. Allam

መታሰቢያ

ይህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገለጫዎች የኢትዮጵያን ጥንታዊ የእስላም ሥልጣኔና የአገሪቱን ሕዝቦች የመሰተጋብር እና የመወራረስ ታሪክ ከጊዜና ከዘመን ጨለማ ወደ ብርሃን አውጥተው ለትውልድና ለዓለም ላሳወቁ የሕዝብና የአገር ባለውለታዎች፥ ማለትም፦

1. በሐረር ከተሜ ኤሚሬት ስነድ የኢትዮጵያን የሸዋ ሱልጣኔት (896-1285) ታሪክ ላቆየው የሐረሩ ጸሐፊI
2. የሐርላና የሀዲያ እስላም ሕዝቦችንና መንግሥታትን ታሪክ በአጼ አምደ ጽዮን (1314-1344) ዜና መዋዕል ለጻፈውና ስሙ ለማይታወቅ ኢትዮጵያዊ ጸሐፊI
3. በ1330ዎቹ የይፋት፥ የሀዲያ፥ የደዋሮ፥ የአርባቢኒ፥ የሸርካ፥ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶችን ታሪክ ለግብፁ ጸሐፊ አልዑመሪ ላስተማረው ኢትዮጵያዊ የሕግ ምሁርና ዲፕሎማት ሼክ ጀማሉዲን አብደላህI
4. የይፋት፥ የሀዲያ፥ የደዋሮ፥ የአርባቢኒ፥ የሸርካ፥ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶችን ታሪክ ከሼክ ጀማሉዲን አብደላህ ተምሮ በመጽሐፍ ለትውልድና ለዓለም ላቆየውና በ1348 ለሞተው ግብፃዊ ጸሐፊ ለፈድለአላህ አልዑመሪI
5. የኢትዮጵያ የሰለሞናዊ ክርስቲያን ዓጼዎችንና የሃሸማይት ዋላስማ እስላም ሱልጣኖችን የጦርነት ታሪክ ከስባቱ የይፋት፥ የሀዲያ፥ የደዋሮ፥ የአርባቢኒ፥ የሸርካ፥ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶች ታሪክ ጋር መዝግቦ ላቆየው ግብፃዊ ጸሐፊ አህመድ ማከሪዚ (1364-1442)I
6. የኢማም አሕመድን የአመጽ ጦርነት (1524-1543) ታሪክ ፉቱሕ አል ሐበሻ በተሰኘ መጽሐፍ ጽፎ ለትውልድና ለዓለም ላቆየው ለኢትዮ/የመኑ የሕግ ምሁር ሸሃበዲን ቢን አብዱልቃድር (1506-1543)I
7. የኢትዮጵያን የ1520-1620 ታላቁን የሕዝቦች እንቅስቃሴ ታሪክ በቅደም ተከተል በዜና ዘጋላ፥ በሥረጸ ድንግል ዜና መዋዕል፥ በሱሰንዮስ ዜና መዋዕልና በጋላ ታሪክ ጽፈው ላቆዩት ለኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ባሕሪይ፥ ወልደሃይማኖት፥ ተክለሥላሴና አጽመ ጊዮርጊስ፥
8 ዘረኛ የውጭ አስተማሪዎች የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማች-አክሱም ሥልጣኔ ፈጣሪዎች ከአስያ መጤ ሴማውያን ናቸው ብለው ለረጅም ዘመን ለዓለም ያስተማሩትን ተረት ውድቅ በማድረግ የሥልጣኔው ፈጣሪ ባለቤት ነባርና ሉአላዊ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሆናቸውን በአርኪኦሎጂ መረጃና ትምህርት በቅደም ተከተል Inscriptions de l'Ethiopie Antique እና "Les Debuts de l'Histoire Ethiopienne" በተሰኙ ተከታታይ ጥናቶች ለዓለምና ለትውልድ ላረጋገጡ የኢፒግራፊ ምሁራን፥ የደቹ ፕሮፌሰር አብራሃም ጀሃን ድሬዊስና የሉክሰምበርጉ ፕሮፌሰር ሮገር ሸናይደር መታሰቢያ ነው።

የደራሲው የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናትና ግንዛቤ

ለዚህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገሪያዎች ትምህርትና ምርት ባለፉት አምስት የትምህርትና የሥራ አሠርታት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የዓለማት የመነሻት የይዘትት የዕውቀትት የሙያት የቴክኒክት የሥልትት የተግባር፥ የማቴሪያልና የሞራል፥ የህሳብና የእምነት ድጋፍ እርዳታና ግፊት የሰጡኝ ባለውለታ አስተማሪዎች፥ የትምህርትና የባህል ተቋማት፥ መጻሕፍት፥ የሃይማኖት፥ የታሪክና የፍልስፍና ምሁራንና ፈላስፋዎች፥ ድርጅቶችና ማኅበራት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፥ ግለሰቦችና ወዳጆች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። በዚህ ወቅትና ኢጋጣሚ ጥቅቶችን ብቻ ከሕይወት፥ ከትምህርትና ከሥራ ገጠመኝ አኳያ እንደሚከተለው አስታውሳለሁ።

በሕፃንቴ ዘመን ወላጆቼ በ1951* በአንድ ሳምንት ውስጥ በሞት ከተለዩኝ በኋላ በድምሩ ከ1953 እስከ 1964 ድረስ በትውልድ አገሬ በቦቢኾ የሱዳን ኢንተርየር ሚሲዮን ትምህርት ቤት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል፥ በሆሣዕና የራስ አባተ ቧያለው 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ7 እስከ 8ኛ ክፍል፥ በናዝሬት የአፄ ገላውድዎስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል፥ በናዝሬት ባይብል አካዳሚ ከ10ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ብዙ ሚሲዮናውያንና የኢትዮጵያ አስተማሪዎች በነፃ ያስተማሩኝ የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ጠንካራ የሕይወት፥ የእምነትና የእውቀት መነሻ፥ መሠረትና መገሪያ ሆኖኛል።

ከ1960 እስከ 1966 ድረስ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች በናዝሬት ከተማና በአካባቢው በነበርኩበት ዘመን ለወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች አንድ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያንና የግል ትምህርት ቤት አቋቁሜ በአስተዳዳሪነትና በአስተማሪነት ለስድስት ዓመታት ጎብረተሰቡን አገልግየዋለሁ።

ከ1953 እስከ 1966 ድረስ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች በቦቢኾ፥ በሆሣዕናና በወንጂ ሸዋ በነበርኩበት ዘመን በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ጎብረተሰብ የነበረውን የመሬት፥ የብሔረሰብ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥ የባህል፥ የፍትህ፥ የሥርዓት፥ የትምህርት፥ የመደብ፥ የአስተዳደር፥ የፖለቲካ፥ የአርሶአደርና የሠራተኛ ችግር፥ ብዝበዛና ጭቆና በሕይወትና ልምድ ከመስኩና ከመድረኩ ለማየትና ለማወቅ ችያለሁ። ይህም ገጠመኝ የኢትዮጵያን ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ

* እንደ እውሮፓ አቆጣጠር፤

ሕዝቦች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ከሥር መሠረቱ እንዳጠና ወሳኝ መነሻና መሣሪያ ሆኖኛል።

ከ1966 እስከ 1974 ድረስ በአሜሪካ አገር በቨርጂኒያ እስቴት በኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅና በዋሽንግተን ዲሲ ኩመን በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ በሃይማኖት፥ በፍልስፍናና በታሪክ መስኮችና ጥናቶች የባችለርስ፥ የማስትሬትና የፒኤችዲ ዲግሪዎችን አገኘሁ። በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ የትምህርት ውጤትና የውድድር ሚዛን የፎርድ ፋውንዴሽን ፌሎውሽፕ ሽልማት ከማሸነፍ በፒኤችዲ ዲግሪ ጥናት ፕሮግራምና ሥራ ግራጁዌት ፌሎው ተማሪ ነበርኩ።

በፒኤችዲ ዲግሪ ጥናትና ዲሰርቴሽን የኢትዮጵያ የዘመኑ ሁለት ብሔራዊ የሕዝብ፥ የአገርና የሥርዓት ችግሮች በደቡብ ተዛማጅ የመሬት፥ የብሔረሰብ፥ የጎሳ፥ የቋንቋ፥ የባህል፥ የሃይማኖትና የሥልጣን ችግር በሰሜን ደግሞ የኤርትራ የፖለቲካ ችግር እንደሆኑ በዩኒቨርሲቲ ጥናትና በሕትመት ሥራ በግልጽና በይፋ አረጋግጫለሁ።

በአሜሪካ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች ከ1966 እስከ 1976 ድረስ በቆየሁበት ዘመን የአገሪቱን ወቅታዊ የሥርዓትና የፖለቲካ ጉዳዮችን በሚመለከት በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባል ነበርኩ። ከትምህርት አኳያ በፍልስፍና መሠረታዊ የሰው፥ የጎብረተሰብ፥ የተፈጥሮ፥ የሕይወት፥ የእውቀት፥ የንብረት፥ የሕግ፥ የሃይማኖት፥ የኤቲክስ፥ የርዕዮተ ዓለም፥ የፖለቲካ፥ የሥርዓትና የመንግሥት ጉዳዮችን በሚመለከት ከምዕራብ ታላላቅ ፈላስፋ ዎችና ምሁራን በተለይም ከፍራንሲስ ቤከን፥ ከሬኔ ደካርት፥ ከጆርጅ በርክሌ፥ ከባሩክ እስፕኖዛ፥ ከቶማስ ሆብስ፥ ከጆን ላክ፥ ከዴቭድ ሁም፥ ከኤማኑኤል ካንት፥ ከጆርጅ ሄግል፥ ከሰረን ኪርከጋርድና ከካርል ማርክስ እንዲሁም የታሪክ ትርጉምና ትምህርት በሚመለከት ከሄግልና ከማርክስ ታላቅ ትምህርታዊ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። በተጨማሪም በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ታዋቂ አፍሮ አሜሪካዊ የታሪክ ምሁርና ጸሐፊ ፕሮፌሰር ቻንስለር ዊሊያምስ በአፍሪካ ታሪክ የጂኦ-ፖለቲካና የውጭ ኃይሎች የተጽዕኖ ሚና በሚመለከት መሠረታዊ ትምህርት አስተምረውኛል።

ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ባለፉት 700 ዓመታት የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋ፥ የሥነ ጽሑፍ፥ የንገሥታት ዜና መዋዕልና የቅዱሳን ገድል አስተማሪዎች ተርጓሚዎችና ጸሐፊዎች ካሳደሩበት ተጽዕኖ ነፃ ተደርጎ

ከሥልጣኔ ምርትና ከሥርዓት ማህበር አኳያ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች አገራዊ አንድነትና ዲሞክራሲያዊ እኩልነት አኳያ እንደገና በአዲስ የጥናት ዘዴ መጠናትና መጻፍ እንዳለበት ከራሴ ጥናት ተረዳሁ። በዚሁ መሠረት በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ለፒኤችዲ ዲግሪ ባቀረብኩት ዲሰርቴሽን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ የጥናት ሥልትና ሚዛን ማጥናትና መጻፍ ጀመርኩ።

ከ1974 እስከ 1976 በአሜሪካ በቨርጂኒያ እስቴት በሪችሞንድ ኩመን በቨርጂኒያ ዩኒየን ዩኒቨርሲቲ በረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ የአፍሪካ ጥናት ፕሮግራም ኃላፊና የታሪክ አስተማሪ ሆኜ ሠርቻለሁ። በግንቦት 1976 በእናት አገር ጥሪ የቨርጂኒያ ዩኒየን ዩኒቨርሲቲ ሥራዬን በፈቃዴ ለቅቄ ከውጭ ወደ አገሬ ተመለስኩ።

ከውጭ አገር ወደ አገሬ ከተመለስኩ በኋላ ከ1976 እስከ 1997 በኢትዮጵያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር፥ በኢትዮጵያ ባህል ሚኒስቴር፥ በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ (ኢፌድሪ) ሕገ መንግሥት ኮሚሽንና በኢፌድሪ ፓርላመንት ዋና የታሪክ ኤክስፐርት በመሆን በድምሩ ለሀያ አንድ ዓመታት በዚህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ጥናት በስፋትና በዝርዝር የቀረበውን የራሴን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ግንዛቤ ትምህርትና ትርጉም በሚመለከት የስድስት ጥናታዊ መጻሕፍት ሕትመትና ስርጭት ጨምሮ በልዩ ልዩ የትምህርት የባህልና የመገናኛ መንገዶች መድረኮችና መሣሪያዎች ማለትም በሕትመት ሥራ፥ በስብሰባ፥ በመጽሔቶችና ቢጋዜጦች፥ በሕዝባዊና በመንግሥታዊ ጉባኤዎች በብሔራዊ አትላስ፥ በራዲዮና ቡቴሌቭዥን ሚዲያ በድምሩ በመቶ አምሳ የሚቆጠሩ ጥናታዊ ጽሑፎችንና ንግግሮችን በማቅረብ የራሴን አዲስ የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርትና ትርጉም ለጎብረተሰቡ በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል አቅርቤአለሁ።

በዚህ ረገድና ተግባር በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ብሔራዊ አትላስ (*National Atlas of Ethiopia*) በኢትዮጵያ የካርታ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በሳይንሳዊ ቴክኒክና አሠራር የተዘጋጀው በ1988 ነው። የካርታ ባለሥልጣን ለአትላሱ የታሪክ ምዕራፍ የሚያስፈልገውን በኢትዮጵያ የጥንት፥ የመካከለኛውና የዘመናዊ ታሪክ ላይ ከተሰማሚ ካርታዎች ጋር የተዘጋጁ ጥናታዊ የሽልማት

ጽሑፎችን ለምርጫ የሚያቀርቡ የታሪክ ምሁራንን አወዳድሮ ለመምረጥ በጋዜጣ ዓለማቀፋዊ ማስታወቂያ አወጣ።

ከተወዳዳሪ የውጭና የአገር ውስጥ ምሁራን ለምርጫ ከቀረቡ የታሪክ ጽሁፎችና ካርታዎች በካርታ ባለሥልጣን ተመርጠ በስሜ ለአትላሱ አገልግሎት የዋለው በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት በአገሪቱ የጥንት፥ የመካከለኛውና የዘመናዊ ታሪክ ላይ ከዘጠኝ ካርታዎች ጋር አዘጋጅቼ ያቀርብኩት የኢትዮጵያ ረጅም፥ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች የአምስት ሺህ ዓመታት ታሪክ ጥናትና ትምህርት ነው።

በተጨማሪም የአትላሱ የታሪክ ጥናት ከዘጠኙ ካርታዎች ጋር በ1988፥ Ethiopia: A Cradle of History በሚል ርዕስ በልዩ እትም በኢትዮጵያ የማስታወቂያ ሚኒስቴር በብዙ ሺህ ኮፒዎች በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰራጨ። እንዲሁም በ1989፥ ኢትዮጵያ፥ የታሪክ መነሻ በሚል ርዕስና የአማርኛ ትርጉም በኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስቴር በ40,000 ኮፒዎች ታትሞ በአገሪቱ የትምህርት ቤቶች የትምህርት ማስተማሪያ መጽሐፍ እንዲሆን ተሰራጭቷል።

በዚህ መጽሐፍ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት (ኢብጥኢ) ከ1983 እስከ 1993 ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ብሔራዊ የመሬት ክልልና የሕዝብ ቁጥር በሚመለከት በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ የጥናት ዘዴና ሚዛን የተሳካ ጥናት ያካሄደው ልዩ የትምህርት ተቋም ነው።

በዚህ ልዩ የጥናትና ምርምር ተቋም በተጠቀሰው ዘመን (1983-1993) ከላይ ከተመለከተው ጥናት ሌላ (1) *የምርትና የባህል ዕድገት በከምባታ-ሀዲያ* (1983)፥ (2) *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* (1990)፥ (3) *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም* (1991) እና (4) *የኢትዮጵያ የመሰረታዊ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ* (1993) በተሰኙ ርዕሰ ጉዳዮች በኢትዮጵያ ረጅም፥ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ላይ እነዚህን ጥናታዊ መጻሕፍት በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል ጽሑና አሳትሜ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዛትና በስፋት አሰራጭቻለሁ። በተጨማሪም በ1993-1994 የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት ኮሚሽን የታሪክ ጥናት ቡድን ሰብሳቢ ኤክስፐርት በመሆን በሕገ መንግሥቱ ለአገሪቱ ታሪክ የተሰጠውን ከፍተኛ ግምትና ሥፍራ በእርካታ አረጋግጫለሁ። የራሴንም አስተዋጽኦ አድርጌዋለሁ።

ከእነዚህ መጻሕፍት፥ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* በመጀመሪያ 18 ወራት ሶስት ጊዜ ታትሞ ተሰራጭቷል። የኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስቴር ከሁለቱ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* እና *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም* ብዙ ሺህ ኮፒዎችን የትምህርት መረጃ ምንጮች እንዲሆኑ ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤተ መጻህፍት አስፋፍሏል።

በአጭርና በጥቅል አነጋገር በ1983-1993 አሥርት ከላይ የተጠቀሱ ጥናታዊ መጻሕፍት ሕትመትና ሰፊ ስርጭት የኢትዮጵያን ረጅም፥ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪካዊ መነሻ፥ ዕድገት፥ ይዘትና ተግባር በሚመለከት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ጎብረተሰብ አዲስ ትምህርታዊ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ችያለሁ የሚል እምነት አለኝ። ይህም ትምህርታዊ ግምትና ግንዛቤ ይህን ቀጣይ *የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች* ማለትም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ማብራሪያ ጥናት እንዲካሄድ የመንፈስ ግፊት፥ ብርታትና ትጋት ሰጥቶኛል።

በእነዚህ ጥናቶች ብሎም በመጽሐፉ ይዘትና ግኝት በሰፋት እና በዝርዝር እንደተገለጸው፥ የግብጽና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖትና የቋንቋ አስተማሪዎች ከተከታዮቻቸው ጋር በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ሕብረተሰብና ታሪክ ላይ እስከ የኢትዮጵያ የ1974 ሕዝባዊ አብዮት ድረስ ለረጅም ዘመን በፈጠሩ የይዘት፥ የቅርጽ፥ የስልትና የትርጉም ግድፈቶች የአገሪቱ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በትክክል ከሥልተ ምርትና ከሥርዓተ ማህበር አኳያ ሳይጠና፥ ሳይገለጽና ሳይታወቅ ዝክረ ተረት ሆኖ ኖሯል።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከታወቀ በኋላ በአንድ በኩል ለተጠቀሰው የፖለቲካ ተረትና ትውፊት መሠረትና መሣሪያ ሆኖ የኖረው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዘውድ ሥርዓት ከገዥው መደብ ጋር በአብዮቱ ፍንዳታና ሂደት ተወግዷል። በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ የተገኙ ሳይንሳዊ የጂኦፖለቲካ፥ የሰነድ፥ የሊንጉስቲክስ፥ የአርኪኦሎጂ፥ የፓለንቶሎጂና የኢቮሉሽን መረጃዎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ በውጭ አስተማሪዎች የተፈጠረውን የፖለቲካና የዘረኝነት ተረት ውግዘና ውድው አድርገውታል።

በመሆኑም ዛሬ በድህረ አብዮት በኢትዮጵያ በአንድ በኩል በአገሪቱ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ሕብረተሰብና ታሪክ ላይ በውጭ አገር አስተማሪዎች ትምህርት የተፈጠ

ረውን ግድፈት በባህላዊ ትምህርትና አብዮት ለማስወገድ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በሳይንሳዊ ሥልተ ጥናትና ትርጉም እንደገና ለማጥናትና ለመጻፍ በሙያውና በመስኩ በተሰማሩ የአገሪቱ ምሁራን ፊት የማይታጠፍና የማይታለፍ ትውልዳዊ ግዴታና ኃላፊነት ተደቅኗል።

ባጭሩ ከዚህ በላይና በታች ከደራሲው የቀረበው ጅምር የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ጥናት የተካሄደው ይህንን ሰብአዊና ትውልዳዊ ግዴታና ኃላፊነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው። በመጨረሻም በምንም ሥፍራና ጊዜ ማንም ግለሰብ በደራሲው ጅምር የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ላይ ሊኖር የሚችለውን የመረጃ፥ የሥልት፥ የግንዛቤና የትርጉም ግድፈት በተሻለ የትምህርት መሣሪያ፥ መንገድና አሰራር ቢያርምና ቢያሰተካክል ለደራሲውም ለሕብረተሰቡም የትምህርትና የእውቀት ግንዛቤ ሰለሚሰጥ ከወዲሁ ይመሰገናል።

ማውጫ

	ገጽ
መቅድምና መግቢያ	XVII
የኢትዮጵያ የብዙ ሕዝቦች ጎብረተሰብና መንግሥት ከስተትና ዕድገት	XVII
የሰሜን/ፈላሻና የሙስሊም ሕዝቦች ታሪክ ጥናትና ግንዛቤ	XXIV

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ትንተና	1
1. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን	1
2. የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ታሪክ መነሻና ዕድገት	5
የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻና የባለቤት ጥያቄ	5
የኢትዮጵያ ሕዝቦች መጤዎች አይደሉም	6
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሀገር በቀል ናቸው	8
የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጥንታዊ ነው	9
አውሮፓውያን የማንነት ችግር አለባቸው	10
የሰው ዘር መገኛ የአፍሪካ አህጉር ነው	12
የአፍሮ-እስያ ቋንቋዎች መነሻና ትምህርት	13
የኢትዮጵያ ወንዞች የአፍሪካ ሥልጣኔ ምንጮች ናቸው	16
የተማከለ ቋንቋ ወጣት ነው	16
የጉራጌ አመጣጥ ታሪክ	18
ነጮች የአፍሪካን ሥልጣኔ ከደዋል	20
ለኢትዮጵያ ታሪክ በቂ ሰፍራ አልተሰጠም	21
3. የኢትዮጵያ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ ግንዛቤ	22
የኢትዮጵያና የአረቦች ግንኙነት ታሪክ	22
የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ዕድገትና ዓለማቀፋዊ ይዘት	22
የኢትዮጵያ የ550-1300 የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት 'ጨለማ ዘመን'	23
የኢትዮጵያና የአረቦች የጂኦፖለቲካ ታሪክ	25
በዘመነ እስልምና ዋዜማ በአካባቢው የዓለም ኃያላን መንግሥታት አሰላለፍ	27
የኢትዮጵያ የአረቢያ ግዛት ታሪካዊ መነሻ	28
የኢትዮጵያ ነገሥታትና ወታደሮች በአረቢያ	30

የአይሁዶች ጦርነትና የኢትዮጵያ ግዛት በየመን አረቢያ ... 33
የኢትዮጵያውያኑ የ577-610 የሂጃዝ አረቢያ ሰፈራና
የእስልምና ክስተት በመካ ... 35
የ615-631 የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በኢትዮጵያ ... 36
ኢትዮጵያና እስልምና ... 37
4. የጦርነት ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ... 39
የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ጎብረተሰብ ግንኙነት ... 39
የመንግሥትና የሃይማኖት ግኙኙነት ... 44
የሕዝቦች እንቅስቃሴና ባህላዊ መወራረስ በኢትዮጵያ ... 50
5. የሰብአዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ-በኢትዮጵያ ታሪክ ... 58
የጦርነትና የሰብአዊ መብት ቅራኔ ... 58
የሰብአዊ መብትና ነፃነት ትምህርት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት 61
የሰብአዊ መብትና የነፃነት ሞዴሎች ... 61
1. የተፈጥሮ ሕግ ሞዴል ... 61
2. የማህበራዊ ሥርዓት ሞዴል ... 62
3. የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሞዴል ... 63
የ1948 የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶችና
ነፃነቶች ቻርተር ምሥረታ ... 64
የተመድ የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ታሪክ ... 66
6. የኢትዮጵያ ታሪክ ድልና ትንሣኤ ... 68
የሕዝብ የመብት ትግልና ድል ... 68
የታሪክ ትንሣኤና ትምህርት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ... 70
የእስልምና መነሻና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ ... 73

ክፍል ሁለት

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ ... 79
1. የታሪክ መረጃ ትርጉምና ትምህርት ... 79
የቅድመ-ታሪክና የዘመን-ታሪክ ልዩነትና ግንኙነት ... 79
የታሪክ መረጃ ዓይነቶች ... 80
የኢትዮጵያ የፖሌአንቶሎጂ መረጃ ... 80
የኢትዮጵያ ታሪክ የሰነድ መረጃ ... 81
የፑንት-ኢትዮጵያ ታሪካዊ ክስተትና ዕድገት ... 81
የኢትዮጵያ ረጅም የሰነድ መረጃ ታሪክ ... 83

የአርኪኦሎጂ ሳይንስና የኢትዮጵያ ታሪክ ግኝት ... 85
2. የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ ... 87
3. የጎብረተሰብና የሃይማኖት ግንኙነት ... 90
የሃይማኖት ማኅበራዊ ትምህርትና ተግባር ... 90
የሃይማኖት ድርጅትና ተግባር በጥንቱ አዋማዊ ግብፅ ... 91
የሃይማኖት ምሥጢራዊ ባሕሪውና ግልጽ ማኅበራዊ ፋይዳ ... 92

ክፍል ሦስት

የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት ... 93
1. የአዋማዊ ሃይማኖት ቀዳሚ መነሻና ሚና ... 93
አሰቢነሰ የትሮጅሎዳውያን የፀሐይ አምላክ ... 93
የደአማታውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት ... 95
የአክሱማውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት ... 95
የደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊ ሃይማኖቶችና የታሪክ መረጃዎች 96
2. የክርስትና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት ... 100
የክብረ ነገሥቱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ትምህርት ... 100
በኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የአሪት መገኘት ጥያቄ ... 102
በአለቃ ታዬ የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የቀረበ ሂስ ... 103
የክርስትና ታሪካዊ መነሻና ትምህርት ... 106
በኢትዮጵያ የክርስትና አባት አስተማሪዎች ... 110
የኢትዮጵያ የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን ... 111
የክርስትና የዕድገትና የመስፋፋት ዘመን 1270-1524 ... 112
3. የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻ፥ ዕድገትና
ውድቀት ... 115
የሰሜን/ፈላሻ የጂኦፖለቲካ ታሪካዊ ፋይዳ ... 115
አሪታዊ የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት
የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት ... 119
የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀትና የመንግሥቱ የመስፋፋት
ታሪክ ... 119
የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ትምህርት መነሻና ሚና
በኢትዮጵያ ታሪክ ... 121
በአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት የሰሜን/ፈላሻ ሚና ጥያቄ ... 123
የጉዲት ተረትና የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ቅጣት ... 125

የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአግራ ሕዝቦች
የጋራ መነሻና ዕድገት ... 126
የሥርዓተ አረት ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ ... 129
የኢትዮጵያ መምህራን ተግባር በሰሜን/ፈላሻ አገር ... 129
የእዮስጣጤዎሳውያኑ የ1337-1450 የአረት አመፅና ድል ... 131
የ1332-1632 የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት ጦርነቶች 135
የደቡብ ኢትዮጵያውያን ኢስመፅ ተፅዕኖ በሰሜን/ፈላሻ
ታሪክ ላይ ... 135
በሰሜን/ፈላሻ አገር የጎንደር መንግሥት ታሪካዊ
መነሻና ውጤት ... 139
የሠርፀድንግልና የሰሜን/ፈላሻ ጦርነቶች (1580-1595) ... 143
የቱርክ ኑፍጠኞችና መድፎች በሰሜን/ፈላሻ ተራሮች ... 143
የ1580 የካሌፍ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት ... 144
የ1580 የረድኤት አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት ... 146
የ1587 የጉሸን ወርቅ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት ... 147
የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ውድቀት ... 148
የ1603-1632 የሃይማኖት ጦርነት ... 148
የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ተግባር በኢትዮጵያ ... 148
የ1609-1624 የዳግማዊ ጌዲኦን አመፅና የሰሜን/ፈላሻ
መንግሥት ፍፃሜ ... 151
የጦርነቱ ታሪካዊ መነሻና ውጤት ... 152
የ1629-1632 የአገው አመፅና የኢትዮጵያ የካቶሊክ
መንግሥት ውድቀት ... 156
የቤተ እሥራኤል/ፈላሻ ሥቃይና የስደት ፍጻሜ ... 157
4. የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት ... 161
ከእስልምና በፊት የኢትዮጵያና የአረቦች ታሪካዊ ግንኙነት 161
የኢትዮጵያና የሮማውያን የፖሊሲ ስምምነት በአረቢያ ... 161
ኢትዮጵያ በአረቢያ ላይ የነበራት ፖሊሲ ታሪካዊ
መነሻና ዕድገት ... 162
የ517-525 የይሁዳውያኑ አመፅ በአረቢያ ... 168
በአረቢያ የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች ጦርነትና ውድቀት 168
የ517-525 የአረብ ስደተኞች በኢትዮጵያ ... 170
የይሁዳውያኑ የአረቢያ አመፅና ውድቀት ... 171

የኢትዮጵያ የ525-577 የደቡብ አረቢያ መንግሥት
ዕድገትና ውድቀት ... 172
የኢትዮጵያና የቁረይሽ አረብ ግንኙነት መነሻና
ዕድገት (577-610) ... 177
የኢትዮጵያውያኑ የሂጃዝ አረቢያ ስደትና ሰፈራ ... 177
በእስልምና ከስተት ዋዜማ በሂጃዝ፥ የኢትዮጵያና
የቁረይሽ አረቦች ግንኙነት ... 179
በእስልምና ምሥረታና ግምባታ የኢትዮጵያውያን ...
ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ ... 184
የታሪክ መረጃ ምንጮች ... 184
የእስልምና ዓለም አቀፋዊ ክስተትና ዕድገት (610-661) ... 185
የኢትዮጵያውያን ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ
በእስልምና ምሥረታ ... 188
በቁረይሽ አረቦች ጦርነት የኢትዮጵያ ሀበሾች ማንነትና ሚና 196
የሀበሻ መንግሥት መነሻና ውድቀት
በየመን አረቢያ (1021-1159) ... 202
በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሙስሊሙ ዓለም ሚና ... 205

ክፍል አራት

የእስልምና ሃይማኖትና መንግሥት መነሻና ዕድገት
በኢትዮጵያ 615-1300 ... 209
በዘመነ እስልምና የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር በሮችና መንገዶች 209
የኢትዮጵያ እስላማዊ ሥልጣኔ ክስተትና ዕድገት (896-1300) 211
የታሪክ መረጃ ምንጮች ... 211
የኢትዮጵያ የማኸዙማይትና የሃሽማይት-ዋላስማ ሥርወ
መንግሥታት ታሪካዊ መነሻ ... 215
የኢትዮጵያ የሸዋ ቀዳሚ ሱልጣኔት ረጅም የጂሐ-ፖለቲካ
ታሪክ (896-1991) ... 218

ክፍል አምስት

የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ረጅም የስያሜ ታሪክ ... 221
የሀበሻና የአጋዓዚያን ነገዶች ጥያቄ በኢትዮጵያ ታሪክ ... 221
የሀበሻ ታሪካዊ መነሻና ትርጉም በአረቡ ዓለም ... 221
በኢትዮጵያ ታሪክ የሀበሻና የአጋዓዚያን ጥያቄ ማብራሪያ .. 223

የአረቦቹ የአፍሪካውያን ግንዛቤና ስያሜ 226
የኢትዮጵያ የአገርና የመንግሥት ስያሜ ረጅም ታሪክ 227

መደምደሚያ

የውጭ አገር አስተማሪዎች ትምህርት ተጽዕኖ
በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ 235
የመረጃ ምንጮች 247

የመረጃና የማስረጃ ምንጮች

ካርታና ቻርት

1) የዓለም ቋንቋዎች የመነሻና የሥርጭት ካርታና ቻርት 3
2) የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የ5000 ዓመታት ታሪክ ካርታ 38
3) በ1855 ዘውዳዊ ምዕክልና በተጀመረ ጊዜ የኢትዮጵያ የነጻ
ሕዝቦችና መንግሥታት ካርታ 54
4) የኢትዮጵያ የ1524 – 1543 የኢማም አህመድ ጦርነት ካርታ 99
5) የኢትዮጵያ የ1520 – 1660 ታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ካርታ 208
6) የኢትዮጵያ የ1855 – 1900 ታላቁ ምዕክልና ታሪክ ካርታ 220
7) የውጭ ኃይሎች ግፊት ፡ የኢትዮጵያ የትግልና የድል ካርታ ... 252

ሠንጠረዥ

1) የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ዝርዝር 55
2) በ1984 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከ20,000 በላይ የሰው ቁጥር
ያላቸው የኢትዮጵያ የ56 ብሔረሰቦች ዝርዝር 56
3) በ1994–97 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች
ዓይነትና ብዛት 57
4) የኢትዮጵያ የፖሌአንቶሎጂና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች ግኝት ... 81
5) በ522–1981 የኢትዮጵያን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ያገኙ ምሁራን 85
6) በ1893–1981 የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን
የተረጎሙ ምሁራን 86
7) በ14ኛው ምዕተ ዓመት በጀ.ሜ.ለዲን–ዑማሪ ግምት የኢትዮጵያ
የሰባት ሡልጣኔቶች የመሬት ስፋትና የሠራዊት ብዛት 214

የዘር ሐረግ

የኢትዮጵያ የማኅበራማይትና የሃሽማይት ዋላስማ ሥርወ
መንግሥታት የነገደ ቁረይሽ ሐረግ 217

መቅድምና መግቢያ

የኢትዮጵያ የብዙ ሕዝቦች ኅብረተሰብና መንግሥት ክስተትና ዕድገት

የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የተሰኘው ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ጥናት ነው። መጽሐፉ በአዲስ ሳይንሳዊና ዘመናዊ የጥናት መረጃ፥ ሥልትና ሚዛን በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል እስከ ዛሬ ድረስ ቡኮፐፍና በታወቁ የጂኦ-ፖለቲካ፥ የትውፊት፥ የሰነድ፥ የሊንጉዊስቲክስ (የቋንቋ ሳይንስ)፥ የአርኪኦሎጂ (ከከርሰ ምድር የሚገኙ ጥንታዊ ጽሑፎች)፥ የፓሌአንቶሎጂ (ከከርስ ምድር የሚገኙ የቅድመ ታሪክ የአጥንትና የድንጋይ መሣሪያዎች) እና የኢቮሉሽን (ሂደታዊ የተፈጥሮ የሕይወትና የሰው ክስተትና ዕድገት ትምህርት) መረጃዎች፥ ማስረጃዎች፥ ግኝቶችና ግብራሪያዎች ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ አዲስ ትምህርትና ትርጉም ነው።

ይህ *የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች* ከይዘትና ከትምህርት ከሥልትና ቴክኒክ ከድርጅትና ከዝግጅት አኳያ በአምስት ርዕሰ ክፍሎችና በብዙ ምዕራፎች የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው። በመጽሐፉ የመጀመርያ ክፍል «የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ትንተና» በሚል ርዕስ ሥር በአንድ በኩል በግምትና በድምር ከ1270 እስከ 1974* ድረስ በ700 ዓመታት የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ የሃይማኖት፥ የቋንቋ፥ የሥነ ጽሑፍ፥ የነገሥታት ዜና መዋዕልና የቅዱሳን ገድል ጸሐፊዎች፥ ተርጓሚዎች እና አስተማሪዎች ተዛምጅ የመረጃ፥ የሥልትና የትርጉም ትምህርት በሥልተ ሂስ ተገምግሟል። በሌላ በኩል ግን በግምት በዓሙተ ዓለም ከ500 እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በአሥር ምዕተ ዓመታት በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግሪክና የግዕዝ ቋንቋዎችና ፊደሎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው በዘመናችን የተገኙ የአቀማዊ ደአማት-አክሱም ጽሑፎችና ጥንታዊ የአጎራብች አረብ ሰነዶች ከዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስና የፓሌአንቶሎጂ

*ሌላ ግብራሪያ ካልተሰጠ በስተቀር በዚህ ጥናት የጊዜ ቀመር እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ነው።

መረጃዎች ጋር የተጠቀሱ የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ክርስቲያን ጸሐፊዎችንና አስተማሪዎችን ወገናዊ ትምህርት ሰማሪም ብሎም የኢትዮጵያን ጥንታዊና በሠውርታዊ የብዙ ሕዝቦች ታሪክ በአዲስ መንገድና መሣሪያ ለማጥናት፥ ለማወቅና ለማስተማር የሚያስችሉ ቁልፍ የትምህርትና የባህል መሣሪያዎች ሆነው ተገኝተዋል።

በተጠቀሱ ጥንታዊ የደአማት-አክሱም ጽሑፎች፥ የአረብ ሰነዶችና በዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስና የፓሌአንቶሎጂ መረጃዎች መሠረት፥ (1) የኢትዮጵያ ምጅር ከሁሉ በፊት የሰው ዘር፥ ቋንቋና ሥልጣኔ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተበት የሰውና የሥልጣኔ ምንጭና መነሻ ነው። (2) የኢትዮጵያ ሁሉም ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ናይሎቲካዊና አሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የአገሪቱ ጥንታዊ፥ ነባርና ተወላጅ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ናቸው። (3) የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጨምሮ የኢትዮጵያ ጥንታዊና አዋጣዊ የደአማት-አክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በግብፅ፥ በአውሮፓና በኢትዮጵያ ክርስቲያን ጸሐፊዎችና አስተማሪዎች እንደ ተገመተው ከኢየሩሳሌምና ከአረቢያ የገቡ ሴማዊ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ፈጠራ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ጥንታዊና ነባር ሕዝቦች ምርት እንደሆኑ በታሪክ መረጃና ትምህርት በትክክል ተረጋግጧል።

(4) እንዲሁም በ330 የክርስትና ሃይማኖትን ቀጥሎም በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን ግሪኮ-ሮማውያን ክርስቲያኖች ወደ አክሱም ከማስገባታቸው በፊት በኢትዮጵያ ጥንታዊና አዋጣዊ ምድርና ታሪክ የአይሁዳውያኑ መሰከታዊ የአሪት ሃይማኖትና ሕግ በፍጹም አልተገኙም። (5) በመጨረሻ በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በረጅም የፖለቲካ ትግልና ድል የአገሪቱን ታሪክና ባህል ከተጠቀሱ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ጸሐፊዎችና አስተማሪዎች ተጽዕኖ ነፃ አድርገዋል።

በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል «የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ማንዛቤ» በሚል ርዕስ ከፍልስፍና አኳያ ከሁሉ በፊት የተፈጥሮ፥ የሰው፥ የአእምሮ፥ የተገዛር፥ የእውቀት፥ የምርት፥ የሥርዓት፥ የባህልና የታሪክ መነሻ፥ መስተጋብርና መወራረስ ጥያቄ በሚመለከት የማንዛቤ ሀሳብና ትምህርት በከፊል እንደሚከተለው ቀርቧል። በዚህ የማንዛቤ ሀሳብና ትምህርት መሠረት የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን በራሱ ማኅበራዊ የአእምሮ መሣሪያ በተወሰነ የሥፍራና የጊዜ ቀመር የሚያውቅና የሚለውጥ በማኅበራዊ ሥፍራው ራሱንና ባህሉን የሚፈጥር አንድ ልዩ አካል ነው።

የአእምሮና የዕውቀት ባለቤትና ጌታ የሆነው የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን በሥፍራና በጊዜ ወሰን የሚያውቀውና የሚለወጠው ግን በታሪክ መሣሪያና እውቀት ነው። በዚህ ረገድና ተግባር የሰው ልጅ ህልውናና ሕይወት መኖርና መሆን በተግባራዊ ልምድ የሚከሰተው፥ የሚገለጸውና የሚታወቀው በተወሰነ የሥፍራና የጊዜ ገደብና ወሰን በራሱ የሥራ እንቅስቃሴና የቋንቋ መሣሪያ ነው። በዚህ አጭርና አጠቃላይ የተፈጥሮ፥ የሰው፥ የአእምሮ፥ የዕውቀት፥ የህሳብ፥ የተግባር፥ የቋንቋ፥ የድርጅት፥ የባህል፥ የሥርዓትና የታሪክ ማንዛቤ፥ ትምህርትና ትርጉም መሠረት የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሠውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረ ተሰብና መንግሥት ምንጭና መነሻ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነው። በዚህ በተወሰነ የመሬት ክልል ላይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ህልውናዊ መሠረቶች፥ መለያዎች፥ መግለጫዎችና መሣሪያዎች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች በሙሉ በመካከላቸው የጎይነትና የደረጃ የእምነትና የባህል ልዩነትና ምርጫ ሳይደረግ የዚህ ሁለአቀፍ ሕዝባዊና አገራዊ ጥናትና ትምህርት ማዕከላዊ ርዕሰ ጉዳዮች ሆነው ቀርበዋል።

በመጽሐፉ ሶስተኛ ክፍል «የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት» በሚል ርዕስ ሥር በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ የተነሱ የአማኝ፥ የክርስትና፥ የሰሜን/ፈላሻ አሪትና የእስላምና ሃይማኖቶች በተከታታይ ምዕራፎች በቅደም ተከተል ተገልጿል።

በዚህ ረገድና ተግባር ከ330 እስከ 615 ድረስ በ285 ዓመታት ሶስቱ መለከታዊና አህዳዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ከሶስቱ ሰማያዊ የጽላተ ሙሴ፥ የወንጌልና የቁርአን ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በቅደም ተከተል ከመካከለኛው ምስራቅና ከምድረ አረቢያ በግሪኮ-ሮማውያንና በአረብ ስደተኞች፥ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገቡ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ሁሉ በተጨባጭ የታሪክ መረጃና ትምህርት በዝርዝር ተገልጿል።

የሃይማኖቶቹን ዕድገትና መስፋፋት በሚመለከት በግምት በሁለተኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት (1000-1600) ሶስቱ መለከታዊና አህዳዊ ሃይማኖቶች ማለትም ክርስትና በመህል ሰሜኑ ደጋአምባ፥ በአክሱም-ትግሬ፥ በአገውና በአማራ አጎራባች ምድር፤ አሪት በሰሜን ምዕራብ በሰሜን/ፈላሻ ምድር፤ እስላምና በመህል ደቡብ ምስራቅ በሐርላና በሀዲያ አጎራባች ምድር

በአንድ ዘመን በየአካባቢያቸው የአገሪቱ ሶስት ተቋማዊ የሕዝብና የመንግሥት ሃይማኖቶች ሆነው ተከለቱ። አደጉ። ተስፋፉ። ተጋጩ። ተዋጉ። በመጨረሻ ደግሞ ታጠፉ።

በዚህ እኳያ በግምት ከ1270 እስከ 1600 ድረስ ለሶስት ምዕተ ዓመታት የመሬት የሥልጣንና የኃብት ባላንጣ ኃይሎች የነበሩ የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ፥ አሪታዊና እስላማዊ መንግሥታትና ባለሥልጣኖች በቮአ-ፖለቲካ፥ በመሬትና ቧንቧድ ጉዳዮችና ምክንያቶች ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርን የዘውትር ጦርነት አውድማ አደረጉ። በመንግሥታቱ የመሬት፥ የኃብትና የንግድ ጦርነት ሃይማኖቶቹ በየአካባቢያቸው የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም መሣሪያዎችና አገልጋዮች ተደረጉ።

በመጨረሻ በ16ኛው ምዕተ ዓመት ከውጭ በፖርቱጋልና በቱርክ ተባራሪ ኃይሎች ግፊት በአገር ውስጥ ደግሞ በተዛማጅ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ የእመጽ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴ ግፊት የኢትዮጵያ ሶስቱ የክርስቲያን፥ የአሪትና የእስላም መንግሥታት በአንድ ዘመን በየፊናቸው ፈረሱ። በመንግሥታቱ ውድቀት ደግሞ ሃይማኖቶቹ በየአካባቢያቸው ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃ ሆኑ። ከመንግሥታዊ ሞግዚትነትና ተጽዕኖ ነፃ ሆነው የሕዝብ ሃይማኖቶች መሆን ጀመሩ።

በዚህ ሁኔታና ወቅት በግምት ከ1559 እስከ 1855 ድረስ ለ3 ምዕተ ዓመታት በክፍለ አህጉሩ ነባር ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ አሞአዊና ናይሎቲካዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች መካከል በሥፍራ፥ በቋንቋ፥ በሃይማኖትና በባህል ታላቅ የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታ፥ ሂደት እና ሥርዓት ተፈጠረ። በሌላ ቃል፥ በክፍለ አህጉሩ መንግሥታት ሲዳከሙና ሲወድቁ በሕዝቦች መካከል ነፃና ዘላቂ የሆነ የመስተ ጋብርና የመወራረስ እንቅስቃሴ የበለጠ ጠነከረ። አደገ። ተስፋፉ።

ከታሪክ አኳያ የዚህ የ1559-1855 የክፍለ አህጉሩ ነባርና አጎራባች ሕዝቦች የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታ፥ ሂደትና ውጤት ለኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረተሰብና ታሪክ ዕድገት አንድ ታላቅ መሻና መሠረት እንደሆነ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል። የዚህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪካዊ ግንኙነት ሁኔታና ሂደት አንዱና ዋናው ምሳሌና መገለጫ የአሞማዊ አሮሞ ማኅበረሰብ ታሪካዊ ክስተት፥ ዕድገትና መስፋፋት ነው።

በዚህ እኳያ በ16ኛ ምዕተ ዓመት በ1520ዎቹ ገዳማ ዛሬ

የኢትዮጵያ በቁጥርና በሥፍራ ትልቁ የሆነ ኩሻዊ የኦሮሞ ሕዝብ በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በግምት በዓቢያ ሐይቅና በገናሌ ወንዝ መካከል በሚገኘው ክልል "ገዳ" ተብሎ በሚታወቅ በራሱ ልዩ ባህላዊና ማኅበራዊ ሥርዓት እየተመራ በእንሰሳት እርባታ ተሰማርቶ በዘላንነት የሚኖር አንድ አናሳ ማኅበረሰብ እንደነበር የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል። በዘመኑ የኦሮሞ ዘላን ማኅበረሰብ "ባዕዳን" የአካባቢ ሕዝቦችን በመብትና ግዴታ የራሱ ወገን ማለትም አንድና እኩል አድርጎ የሚቀልባቸው "ጉዲፈቻ" እና "ሞጋሳ" የተሰኙ የራሱ ማኅበራዊ ሕጎችና ሥርዓቶች ነበሩት።

ይህ በሕዝባዊ የገዳ፥ የጉዲፈቻና የሞጋሳ ድርጅቶች፥ ተቋማትና ሥርዓቶች የሚመራ የኦሮሞ አሞማዊ ሕዝብ በግምት ከ1520ዎቹ እስከ 1620ዎቹ ድረስ በአንድ ምዕተ ዓመት ዘመን ውስጥ በርቱግና ቦረና በተባሉ ሁለት ኃላዎችና ከረዩ፥ ወሎ፥ ቱላማና ሚጫ በተባሉ አራት ቅርንጫፍ ማኅበረሰቦች ተከፍሎ በፍለሳ እንቅስቃሴ በደቡብ ምስራቅ ከገናሌ ወንዝ አካባቢ በመነሣትና በአብዛኛው የዛሬ ደቡብ፥ ምስራቅ፥ መሀልና ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ላይ በመስፋፋት ብሎም በተጠቀሱ አካባቢዎች ከጥንቱ ነባር ኩሻዊ፥ ሴማዊና አሞአዊ የባሌ፥ የደዋሮ፥ የአዳል፥ የሀዲያ፥ የፈጠጋር፥ የወርጅ፥ የሀርላ፥ የሶማሌ፥ የአፋር፥ የአርጎባ፥ የይፋት፥ የአማራ፥ የአገው፥ የትግሬ፥ የጋፋት፥ የአይመላል፥ የጉራጌ፥ የዳሞት፥ የበሻ፥ የእናሪያ፥ የቢዛሞ ... ሕዝቦች አገሮችና መንግሥታት ጋር በሥፍራና በጊዜ፥ በጦርነት፥ በጋብቻ፥ በቋንቋ፥ በኅላ፥ በባህል፥ በሃይማኖትና በሥርዓት በመወራረስ በአጭር የታሪክ ዘመን ውስጥ ከሥፍራና ክቱጥር አኳያ የኢትዮጵያ ትልቁ ማኅበረሰብ ለመሆን በቃ። በአገሪቱ የተለያዩ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች መካከል ዘላቂ መስተጋ ብርና መወራረስ ፈጠረ።

በዚህ መሠረታዊና ዘላቂ በሆነ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረ ሰቦች የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ብዛትና አንድነት ጉዳይ በሚመለከት በአገሪቱ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በአንድ ምዕተ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ (1520-1620) የአሞማዊ አሮሞ የገዳ ሕዝባዊ ሥርዓትና እንቅስቃሴ ያደረገውን ታላቅ አስተዋጽዖ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በ1000 ዓመታት፥ የክርስትና ሃይማኖት በ1670 ዓመታት፥ የእስልምና ሃይማ ኖት በ1300 ዓመታት እንዲሁም ሰለሞናዊ የአማራ ሥርወ መንግሥት በ700 (1270-1974) ዓመታት ዘመን አላደረገም። ምክንያቱም ለምሳሌ በኢትዮጵያ የ1994 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገሪቱ

ሕዝብ አንድ ሶስተኛ የኦሮሞ ቋንቋ ማኅበረሰብ አባል ነው። ከዚህም ሕዝብ በሃይማኖት ግማሹ ክርስቲያን ግማሹ ደግሞ እስላም እንደሆነ የቆጠራው ውጤት ጨምሮል ያሳያል።

በኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረተሰብና መንግሥት በቀድሞ ዘውዳዊ ሥርዓት (1855-1974) ማዕከላዊ ርዕሰ ጉዳይ ሁለአቀፍ የመሬት፥ የብሔረሰብ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥ የባህል፥ የትምህርትና የመንግሥት ሥልጣን ችግር ነው።ኢየችግሩ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት በ16ኛው ምዕተ ዓመት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከሁለቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ተዛማጅና ተከታታይ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመጽ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴ ጥምር ታሪክ ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዘ የጭቆና ሥርዓት ነው።

በዚህ አኳያ በማምት ከ1270 እስከ 1543 ድረስ ከመህል ሰሜኑ ደጋአምባ ክርስትቲያን ነገሥታትና የሃይማኖት መምህራን ከግብፅ አቡኖች ጋር የመላ ደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊና እስላማዊ ነባርና ጥንታዊ ሕዝቦችንና መንግሥታትን በሰፋሪ ወታደሮችና ቄሶች አማካይነት በክርስትና ሃይማኖት ለመገዛት ለሶስት ምዕተ ዓመታት ያካሄዱት ወታደራዊና ወንጌላዊ ዘመቻዎች ሁሉ በመጨረሻ በሁለቱ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመጽ ጦርነትና የ1520-1620 የሕዝቦች የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴ ግፊት በሽንፈትና በውድቀት ተደመደሙ።

በሌላ በኩል ግን በሁለቱ የክርስቲያንና የእስላም ተጣራሪ መንግሥታት የጋራ ሽንፈትና ውድቀት በማምት ከ1559 እስከ 1855 ድረስ ከደቡብ ምስራቅ ቆላማ አካባቢ በተሳካ የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴ የተሳኑ የኦሮሞ አራቱ የከረዩ፥ የወሎ፥ የቱለማና የሜጫ ማኅበረሰቦች በየፊናቸው በአብዝኛ የምስራቅ፥ የደቡብ፥ የመህል፥ የምዕራብና የሰሜን ኢትዮጵያ ለሰውና ለእንሰሳት ኑሮ ምቹ በሆኑ ሰፊ፥ ለም፥ ደጋማና ጤናማ አካባቢዎች በነዋሪነት ሰፈሩ።

በአንጻሩ በ16ኛው ምዕተ ዓመት ሁለቱ የክርስቲያንና የእስላም መንግሥታትና ሥርዓቶች በውስጥና በውጭ ተጣራሪ ሁኔታዎችና ኃይሎች ግፊት ከፈረሱ በኋላ በማምት ከ1600 እስከ 1855 ድረስ በሰ ሜኑ ደጋአምባዎች ሶስቱ ክርስቲያናዊ የጎንደር፥ የትግራይና የሸዋ የፖለቲካ ኃይሎች፥ ማዕከላትና አካባቢዎች በአዋማዊ፥ በኦሪታዊና በእስላማዊ ሕዝቦች ዙሪያና መካከል ተከሰቱ።

የሶስቱ የጎንደር፥ የትግራይና የሸዋ ክርስቲያናዊ የመሳ ፍንት፥ የካህናት፥ የባላባትና የጠር ኃይሎች የጋራ ዓላማ፥ ፖሊሲ፥

ፖሊቲካና ተግባር በአንድ በኩል በየአካባቢያቸው አዋማዊ፥ ኦሪታ ዊና እስላማዊ ነባር ሕዝቦችን በጦርና በገባር ሥርዓት ማስገበርና መግዛት በሌላ በኩል ደግሞ በ16ኛው ምዕተ ዓመት በእስላሙ ጭግራኝ ወረራ" እና በአዋማዊ "የጋላ ወረራ" ፈረሰ፥ ጠፋ፥ የሚሉ ችን ዘውዳዊ የአፄ መንግሥት «መልሶ» በተጠቀሱ «ጠላት» ሕዝቦች ላይ መገንባት ነበር።

ይህ የጎንደር፥ የትግራይና የሸዋ ክርስቲያናዊ ኃይሎች ዘውዳዊ የክርስቲያን ጎብረተሰብ፥ መንግሥትና ሥርዓት የመገንባት ቋሚ ፖሊሲና ፕሮግራም በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ (1855-1900) ከሶስቱ አካባቢዎች በተከታታይ በተሳኩ አፄ ነገሥታት ቴዎድሮስ፥ ዮሐንስና ምኒልክ አመራርና በውጭ ኃይሎች የመሣሪያ እና የፖለቲካ ድጋፍ እንደሚከተለው ተግባራዊ ሆነ። መጀመሪያ በመህል ሰሜኑ ደጋአምባ ከጎንደርና ከትግራይ በተከታታይ የተሳኩ አፄ ነገሥታት ቴዎድሮስና ዮሐንስ በአካባቢው ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ለረጅም ዘመን በነበረው ተዛማጅ የጂኦ-ፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የፀጥታና የማኅበራዊ ችግር ምክንያት በዘውዳዊ ምዕከ ልና ፖሊሲና ፕሮግራም በክፍለ አህጉሩ እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦ ችና መንግሥታት ላይ የክርስቲያን መንግሥት ለመገንባት የጀመሩ ትን ዘመቻ ከግቡ ሳያደርሱ በ1868 እና በ1889 በቅደም ተከተል በመቅደላና በመተማ ጦርነቶች ሞቱ።

በመህል ሰሜኑ ደጋአምባ በሁለቱ ነገሥታት የተጀመረው የክርስቲያን መንግሥት ማጠቃለያ ፖሊሲና ፕሮግራም ከፈረሰ በኋላ አፄ ምኒልክ (1889-1913) ከሸዋ እስትራቴጂያዊ ክልል በመነሳት በአንድ በኩል የደቡብ ኢትዮጵያን ታላቅ የሰውና የተፈጥሮ ሀብት በመቆጣጠር በሌላ በኩል ደግሞ ከአውሮፓውያን ከፍተኛ የጦር መሣሪያና የፖለቲካ ድጋፍ በማግኘት በክፍለ አህጉሩ አዋማዊና እስላማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ዘውዳዊ የክርስቲያን መንግ ሥት፥ ሃይማኖትና ጦር በጠንካራ የገባር ኢኮኖሚ መሠረት በሰፋሪ ነፍጠኞችና ቄሶች ኃይል በደቡብ ኢትዮጵያ ማዕከልነት መርተው ሞቱ።

ነገር ግን በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋ ዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብ በተጠቀሱ የጎንደር፥ የትግ ራይና የሸዋ ክርስቲያን ነገሥታትና የጦር ኃይሎች ፖሊሲና ተግባር በጎብረተሰቡ ላይ የተማከለው ዘውዳዊ መንግሥትና ሥርዓት በአገሪቱ ለተዛማጅና ሁለአቀፍ የመሬት፥ የብሔረሰብ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥ የባህል፥ የሥርዓት፥ የትምህርትና የመንግሥት ሥልጣን ችግሮች

ታሪካዊ መነሻና ምክንያት በመሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ በአንድ በኩል የራሱን የዘውዳዊ መንግሥትና የገዥ መደብ ውድቀት በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ነፃነትና እርኒት እንዴት እንዳስከተለ ይህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የታሪክ ዕውነታ፥ እውቀትና እውነት ያስተምራል።

በመጽሐፉ አራተኛ ክፍል «የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት መነሻና ዕድገት በኢትዮጵያ 615-1300» በሚል ርዕስ፥ በአምስተኛ እና በመጨረሻ ክፍል ደግሞ «የኢትዮጵያ የሕዝቦችና የመንግሥት ረጅም የስያሜ ታሪክ» በሚል ርዕስ በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ተገቢ አገራዊና ሕዝባዊ ትኩረትና ግንዛቤ ያላገኙ ሁለት መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳዮች ለመነሻ ያህል በአጭርና በጥቅል መልኩ ተገልጸዋል።

የሰሜን/ፈላሻና የሙስሊም ሕዝቦች ታሪክ ጥናትና ግንዛቤ

በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት በዝርዝር እንደሚታየው፥ ባለፉት 700 (1270-1974) ዓመታት የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ጸሐፊዎች፥ አስተማሪዎችና ተርጓሚዎች ከኢትዮጵያ ስለሞናውያን ተከታዮቻቸውና ተማሪዎቻቸው ጋር ባሳደሩት የተረት፥ የሃይማኖትና የፖለቲካ ተጽዕኖ ምክንያቶች የአገሪቱ አሪታዊ የሰሜን/ፈላሻና ጥንታዊ የሙስሊም ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ታሪክ በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ከሞላ ጎደል ሳይታወቅ ኖሯል። በመሆኑም አሁን የሁለቱም ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ረጅም የመነሻ፥ የማንነትና የጭቆና ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ታሪክ ከተቀረው የአገሪቱ አጠቃላይ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ጋር በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል ከብዙ ጥንታዊና ዘመናዊ የስነድ መረጃዎች ተጠንቶ ለጎብረተሰቡ ትምህርታዊ ግምገማ፥ ግንዛቤና አገልግሎት ከሥር ከመሠረቱ ቀርቧል።

ከእውነትና ከእውቀት አኳያ፥ የሁለቱ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ታሪክ በዚህ ጥናት እንደቀረበው ለአንባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ታሪክ መስሎ ባይታይ አያስገርምም። ታሪኩ ግን እውነተኛ ነገር ብቻ ሳይሆን ባለፉት 700 ዓመታት በቀድሞ ዘውዳዊ ሥርዓት የተቀሩ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ታሪክ ዓይነተኛ ምሳሌ፥ ማስረጃና መግለጫ እንደሆነ ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በሰፋትና በዝርዝር ይታያል።

የታሪኩን ግኝትና ትምህርት በሚመለከት፥ አሪታዊ የሰሜን/ፈላሻ ረጅም (300-1990) የጠርነትና የስደት ታሪክ የተገኘው ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችና ከሰለሞናዊ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች ሲሆንት የሙስሊሞቹ ታሪክ ደግሞ ከአረብ ምንጮች፥ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የሐረር ከተሜ መንግሥት ሰነዶችና ከሰለሞና ዊያን ነገሥታት ዜና መዋዕሎች ነው።

የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በግምት ከ300 እስከ 1632 ድረስ ለ1300 ዓመታት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ቡተከዜና በዓባይ መንዞች መካከል ባለው ለምና እስትራቴጂያዊ አገር ላይ ከአካባቢው ተከታታይ የአክሱም፥ የአገውና የአማራ መንግሥታትና ነገሥታት ጋር እየተዋጋ በሉአላዊ ነፃት እንደኖረ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል። ነገር ግን በመጨረሻ በ1580-1632 የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት በጠላቶቹ እጅ በዘመናዊ የጉጥጥና የመድፍ መሣሪያዎች ሲደመሰስ፥ ሕዝቡ ከመሬቱ ተነቅሎ በ1980ዎቹ ከአገሪቱ እስኪሰደድ ድረስ ለአራት ምዕተ ዓመታት እንዴት ለአጎራባች ሕዝቦች የዕደ ጥበብ አገልጋይ ማኅበረሰብ እንደሆነ በጥናቱ በዝርዝር ተገልጿል።

በዚህ ጥናት የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ታሪክ ከሥር ከመሠረቱ በሰፋት እንዳጠና ብርቱ ግፊትና ንቃት የሰጠኝ፥ ባለፉት አሥርታት የኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ መነሻ ከስተትና ዕድገት በማስረዳት በልዩ ልዩ መንገዶች፥ መድረኮችና መሣሪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ያስተማርኩትን ትምህርት በሚመለከት ከአገሪቱ የሙስሊም ጎብረተሰብ በአጠቃላይ፥ በደቡብ ኢትዮጵያ ከጥንታዊ የሀዲያ፥ የስልጤ፥ የአላባ፥ የቀቤና፥ የሐረሪ፥ የአርጳ፥ የወርጅ፥ የአፋርና የሱማሌ ሙስሊም ማኅበረሰቦችና ተወላጆች ቡተለይ የተገኘ ከፍተኛ የሞራል ድጋፍና ትብብር ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር ከ896 ማለትም ገና ከዘመነ አክሱም ጀምሮ እስከ 1600 ድረስ በደቡብ ኢትዮጵያ በአዋሽ፥ በከሰም፥ በሙገር፥ በዓባይ፥ በጊቤ፥ በብላቴ፥ በዋቤና በገናሌ መንዞች ተፋሰስና ወይናደጋ ክልል በጥንታዊ አጎራባች የሐርላና የሀዲያ ሴማዊና ኩሻዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ምድር በአረቡ የሙስሊም ዓለም፥ የዜይላ ሕብረት መንግሥታት ተብለው የሚታወቁ እስላማዊ የሸዋ፥ የሀዲያ፥ የይፋት፥ የወርጅ፥ የግዛል፥ የአዳል፥ የሞራ፥ የለበከላ፥ የሀገራ፥ የፈድሳ፥ የግዳድ፥ የጎንብ፥ የዚባ፥ የሐርላ፥ የህበት፥ የተርሳ፥ የእይም፥ የእልብር፥ የዜይላ፥ የእስቴ፥ የደዋሮ፥ የመንዝ፥ የዜጋ፥ የኩልጎራ፥ የገደያ፥ የቀድሴ፥ የሀርጋይ፥ የበቁልዘር፥ የፈጢጋር፥

የአርኅባ፥ የሸርካ፥ የአረባኒኒ፥ የባሌ፥ የደራ፥ የሐረር፥ የጉራጌ፥ የስልጤ፥ የአውላ ... ሕዝቦች፥ አገሮች፥ መንግሥታትና ከተሞች እንደነበሩ ከታሪክ መረጃና ትምህርት በሥፍራና በጊዜ ቀመር በትክክል ታውቋል።

ከ896 እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ የሙስሊም መንግሥትና ሥልጣኔ ታሪክ ግንዛቤና ትምህርት በሚመለከት፥ በአካባቢው በተለይ በጥንታዊ የሐርላ ለም፥ ደጋማና ጤናማ ምድር ላይ፦

1ኛ፥ በ896-1285 ከአረቢያ በዚይላ የወደብ በር በገባው መኸዝማዊ የቁረይሽ አረብ ሥርወ መንግሥት የተገነባው የሸዋ ሱልጣኔት I

2ኛ፥ በ1285-1415 ከአረቢያ በዚይላ የወደብ በር በገባው የሃይሺማይት፥ ዋላስማ የቁረይሽ አረብ ሥርወ መንግሥት የተገነባው የይፋት ሱልጣኔት I

3ኛ፥ በ1415-1577 የሃይሺማይት፥ ዋላስማ ሥርወ መንግሥት የተገነባው የአዳል ሱልጣኔት፥ በ1524-1543 በሐረርና በደምቢያ ማዕከላት የኢማም አሕመድ ክፍለ አህጉራዊ የአዳል ሱልጣኔት፥ በ1544-1567 የኤሚሪ ኑር የሐረር ኤሚሬትና ጀጎል ግምብ I

4ኛ፥ በ1577-1647 በኢማም አሕመድ ተወላጅና ወራሽ ኢማም መሐመድ ጃሳ የተገነባው የአውላ ኢማሜት I

5ኛ፥ በ1577-1887 በኢማም አሕመድ ተወላጅና ወራሽ ኢማም መሐመድ ጃሳ የተመሠረተው የሐረር ኤሚሬት I

በ1647-1662 በሐረር ኤሚሬት የኤሚር ዓሊ ዳውድ አመፅ በአውላ ኢማሜት ላይ ብሎም የነፃ ሐረር ኤሚሬት (ከተሜ መንግሥት) ክስተትና ዕድገት (1647-1887) I

6ኛ፥ በ1887-1994 የሐረር ኤሚሬት (ከተሜ መንግሥት) ውድቀት በኢትዮጵያ ግዛተ አፄ I

7ኛ፥ በ1994 በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሥር የሐረሪ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ክስተት በቅደም ተከተል የሚቀርቡ ታላላቅ ታሪካዊ ምዕራፎች፥ ኃይሎች፥ እንቅስቃሴዎችና ዘመናት ናቸው።

ባጭሩ ከ896 ጀምሮ ለአራት ምዕተ ዓመታት በደቡብ ኢትዮጵያ በአጎራባች የሐርላና የሀዲያ አገሮች የእስላም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ሥርዓት ካደገና ከተስፋፋ በኋላ በ1270 በሰሜኑ ደጋአምባ ማለትም በላስታ የአገውን የክርስቲያን መንግሥት በአመፅ ገልብጠ የተነሳውና ራሱን በኢትዮጵያ ሰለሞናዊ ዘር ነኝ ብሎ የሰየመው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት በተጠቀሱ የእስላም ሕዝቦችና

መንግሥታት ላይ እስከ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመፅ ጦርነት ድረስ ለሶስት ምዕተ ዓመታት የሚቆየውን ሁሉአቀፍ የመሬት፥ የንግድና የሃይማኖት ጦርነት ጀመሩ።

ነገር ግን በ16ኛው ምዕተ ዓሙት የኢትዮጵያ ሁለቱም የክርስቲያንና የእስላም ተፋላሚ መንግሥታት፥ ነገሥታትና የጦር አበጋዞች በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ከአሪታዊው የሰሜን/ፈላሻ ጥንታዊ መንግሥት ጋር በሁለቱ ተዛማጅና ተከታታይ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመፅ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ ግፊት በየአካባቢያቸው ተሸንፈው እንዴት እንደወደቁ ብሎም በሂደቱ የእስልምና ሃይማኖት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ደረጃ እንዴት የበለጠ እንደተስፋፋ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ይዘትና ሂደትና ትምህርት ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በስፋትና በዝርዝር ያሳያል።

በመጨረሻም በዚህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች፥ የኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖት ጥናትና ትምህርት በሚመለከት፥ ከአረቢያና ከሐረር ከተሜ መንግሥት ከተገኙ የመረጃ ምንጮች ቀጥሎ ለጥናቱ ፍሬና ምርት የማንዛቤ፥ የትምህርት፥ የመረጃ፥ የሙያ፥ የቴክኒክ፥ የምክርና የሞራል እገዛና አስተዋጽኦ ያደረጉ የኢትዮጵያ ድርጅቶችና ዜጎች ብዙ ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በተለይ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ፍዕርዳታና ልማት ማኅበር በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ህዝቦችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ውስጥ የሙስሊም ኅብረተሰብ ሃይማኖትና ታሪክ ጥናቴን ሰምተውና አይተው በየበኩላቸው ላሳዩኝ መልካም አመለካከትና ለሰጡኝ የትምህርትና የሞራል ድጋፍ ምስጋና ናዱ የላቀ ነው። ወዳጄ አቶ ወሂብ መሐመድ ቱሬ በኢትዮጵያ ሪጅም የሙስሊም ሥልጣኔና ታሪክ ታላቅ ማዕከላዊ ሥፍራና ሚና ያለውን የሐረሪ ከተሜ መንግሥትና ኅብረተሰብ ሕያው ታሪክ ከጀጎል ምንጩና መስኩ ለማጥናትና ለማወቅ ባደረግኩት ጥረት በመልካም አስተያየቱና ተግባሩ ታላቅ ትምህርታዊ ግፊትና ግንዛቤ እንደሰጠኝ ሶገልፅ በታላቅ ደስታ ነው። እንዲሁም ይህን መጽሐፍ በታላቅ ትግሥትና ትጋት በኮምፕዩተር በማቀነባበር አቶ ሙክታር አሕመድ ዓላም ለጥናቱ መሳካትና አገልግሎት የራሱን ልዩ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ከታላቅ ምስጋና ጋር አገልፃለሁ። ከሁሉም በላይና በፊት በዚህ ረጅምና አስጨናቂ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት የባለቤቴ ሽቶ ግርማና የልጆቼ ፀጋነሽ፥ ትዕግሥትና ዝናሽ የቤተሰብ

ተሳትፎና ወላኝ አስተዋጽኦ ሳይገለጽና ሳይታወቅ የማይታለፍ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በዚህ መጽሐፍ የቀረበው የኢትዮጵያ ታሪክ የጥናት ሥልት ሆነ ትምህርትና ትርጉም የኔ የራሴ ብቻ ነው።

ላ. ጌ. ድ.
ሴፕተምበር 1998
አዲስ አበባ

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ትንተና

1. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

ከእንቅስቃሴና ከሀልውና አኳያ፥ ሥፍራና ጊዜ የመኖርና የመሆን ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በዚህ ረገድና ተግባር፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የሚዋሰነው እስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ተዛማጅ ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ናይሎቲካዊና አሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የመኖሻ ምድር ነው። ይህ የክፍለ አህጉሩ መሰን በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ የሚለው የአገር ስያሜ ሰፋ ያለ አካባቢን የያዘ መሆኑን የሚገልጽ ታሪካዊ ማብራሪያ ነው።

የኢትዮጵያ በህውርታዊ (multinational) ሕዝብ ታሪካዊ መኖሻና ግንኙት በሚመለከት ደግሞ፥ ዘመናዊ ሥነልሳን (የሊንጉዊስ ቲክስ ሳይንስ) እንደሚያስተምረው፥ የሦስቱ ጥንታዊና አጎራባች የአፍሪካ፥ የእስያና የአውሮፓ አህጉራት ነባር ሕዝቦች ዛሬ የአፍሮ-እስያ እና የኢንዶ-አውሮፓ የቋንቋ ቤተሰቦች ተብለው በሁለት ታላላቅ የቋንቋ ግንዶችና ምንጮች ይከፈላሉ።[1]

ከሁለቱ የዓለም የቋንቋ ግንዶችና ምንጮች፥ የአፍሮ-እስያ የቋንቋ ቤተሰብ ራሱ የቻድ፥ የበርበር፥ የግብፅ፥ የኩሽ፥ የሴም፥ የኦሞና የናይሎሳሃራ በተሰኙ ንኡስ የቋንቋ ዘርፎች ይከፈላል። ከተጠቀሱት ቅርንጫፍ የቋንቋ ዘርፎች፥ ኩሻዊና ሴማዊ ቋንቋዎች በአመዛኙ፥ አሞአዊ ቋንቋዎች በሙሉ፥ ናይሎሰሃራዊ ቋንቋዎች በከፊል የሚገኙት በኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ ምድር ነው። በሊንጉዊስቲክስ ሳይንስ መሠረት፥ የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በህውርታዊ ብዛትና ግንኙነት ሁኔታ ለቋንቋዎቹ አካባቢያዊ መኖሻና ጥንታዊነት ታሪካዊ ማስረጃና መግለጫ ነው።[2]

[1] Martin Bernal, Black Athena - The Afroasiatic Roots of Classical Civilization: Volume I: The Fabrication of Ancient Greece 1785-1985 (Rutgers, 1987), Maps and Charts, pp. XXIV-XXVII, 11-14; J. H. Greenberg, African Linguistic Classification, UNESCO, General African History, 8 Vols. (1981), I, pp. 92-308; M. L. Bender, The Ethiopian Nilo-Saharans, (1975).

[2] Martin Bernal, "ጉራጊኛ የግዕዝ አያት ነው"፥ እርይታ፥ ቅ 5 ቁ 40 (1989)፥ ገፅ 11።

በተጨማሪም፥ በቅርቡ በአካባቢው በተገኙ የአርኪኦሎጂና የፓሌአንቶሎጂ (archaeology and paleontology) መረጃዎች የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች በሀውርታዊነትና ጥንታዊነት የበለጠ ተረጋግጧል። ከዚህ አኳያ ባለፉት 200 ዓመታት በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ አጎራባች አገሮች፥ በአምሳ ከሚቆጠሩ ታሪካዊ ሥፍራዎች፥ በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በ500 የሚቆጠሩና በድንጋይ ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ከከርሰ ምድር በአርኪኦሎጂ ጥናትና ምርምር ተገኝተዋል። በነዚህ ጽሑፎች መሠረት፥ የግዕዝን ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጨምሮ፥ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማት-አክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩት፥ በቅርቡ ዘመን የአውሮፓ ምሁራን እንደገመቱት ከእስያ ከፍለ አህጉር ወደ ኢትዮጵያ ገቡ የተባሉት የውጭ ኃይሎች ሳይሆኑ፥ የአገሪቱ ነባርና ጥንታዊ የአፍሪካ ሕዝቦች ናቸው።[3]


ይህም ብቻ አይደለም። በቅርቡም በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አሥርታት ውስጥ፥ በአርኪኦሎጂ ቁፋሮ በተገኙ የፓሌአንቶሎጂ መረጃዎች (ጥንታዊ የቅድመ ታሪክ የአጥንትና የድንጋይ መሣሪያዎች) በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደተረጋገጠው፥ የሰው ልጅ ራሱ በሀልውናዊ እካሉና አእምሮው እድጎና ዳብሮ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው ከዛሬ ብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር፥ በታላቁ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በኢትዮጵያ የአዋሽ-አሞ ወንዞች ምድር ነው።[4] ከዚህ ከኢትዮጵያ የስምጥ ሸለቆ፥ የሰው ልጅ መነሻው ምድር፥ የዓለም የአፍሮ-እስያና የኢንዶ-አውሮፓ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች፥ በግምት ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት በፍለሳና በስፈራ እንቅስቃሴ በአፍሪካና በእስያ አጎራባች አህጉራት ላይ እንዴት እንደተሰራጩ የሊንጉዊስቲክ ሳይንስ ምሁራን እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፥ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) አሁን በይፋ ያስተምራሉ።[5]

[3] A. J. Drewes, Inscriptions de L'Ethiopie Antique (1962); R. Schneider, "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne" Documents Histoire Civilisation Ehiopienne, RCP. 230, CNRS, FASC. 7 (1976); E. Bernand; J. A. Drewes, R. Schneider et F. Anfray, trs. and eds., Recueil des Inscriptions de L'Ethiopie des Periodes Pre-Axoumite et Axoumite (Forthcoming).

4 Bernal, Black Athena, pp. 11; UNESCO, History of Africa, I. pp. 300-301.

[5] Ibid., Black Athena, pp. 11-14; G. Hudson, "Language Classification and the Semitic Pre-History of Ethiopia", Folia Orientalia, Vol. 18 (1977), pp. 119-166; Ibid., "Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Pre-History", Abbay, No. 9 (1978), pp. 71-85.

የዓለም ቋንቋዎች መነሻና ስርጭት



Source:- Bernal, Black Athena (1987) by Adoption.

Source: M. Bernal, Black Athena (1987) Vol. 1, p. XXVI.

በዘመነ-ታሪክ፥ ባለፉት ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት ውስጥ፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በሜዲትራኒያን ባሕር፥ በመካከለኛው ምስራቅና በአረቢያ ጥንታዊና አጎራባች አካባቢዎች፥ በየዘመናቸውና በየአካባቢያቸው የተነሱት ጥንታዊ የግብፅ፥ የይሁዲ፥ የግሪክ፥ የሮም፥ የፋርስና የአረብ ተከታታይ ሕዝቦችና መንግሥታት በተለይ በንግድ፥ በሃይማኖትና በባህል መንገዶችና መስኮች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ታሪካዊና እስትራቴጂያዊ ክፍለ አህጉር ከኢትዮጵያ ነባር ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታዎች፥ እንቅስቃሴዎችና ሂደቶች እንደነበሩዋቸው በየወቅቱ በጥንታዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፥ የዕብራይስጥ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክ፥ የላቲን፥ የኮፕቲክ እና የአረብ ቋንቋዎች ተጽፈው የተገኙ የታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ።

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ መነሻና ስያሜ በሚመለከት፥ ከተጠቀሱት ጥንታዊ የአካባቢው ሕዝቦች በተለይም ሁለቱ ግብፃውያንና ይሁዳውያን- «ፑንት»፥ ግሪኮች- «ኢትዮጵያ»፥ አጎራባች አረቦች ደግሞ «ሀበሻ» በተሰኙ የአገርና የሕዝብ ስሞች እንደሚጠሩ ከታሪክ መረጃና ትምህርት ታውቋል።

ከዚህ አኳያ ከ330 እስከ 615 ድረስ በ285 ዓመታት ውስጥ በግሪክ-ሮማውያንና በአረብ አስተማሪዎች አማካይነት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ጋር ወደ አክሱም አገርና ቤተ መንግሥት የገቡት ሦስቱ የዓለም መለኮታዊና አህዳዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች በአንድ ላይ ባለፉት 1700 ዓመታት ውስጥ በየፊናቸውና በየአካባቢያቸው የእምነት፥ የድርጅትና የትምህርት መሠረቶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች በመሆን ለኢትዮጵያ ጥንታዊ እና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገር፥ ጎብረተሰብና መንግሥት ህልውናዊ ክስተትና ዕድገት ድምር አስተዋፅኦ እንዳደረጉ በዚህ ጥናት፥ ይዘትና ሂድት በስፋት ይታያል።

2. የኢትዮጵያ በህውርታዊ ታሪክ መነሻና ዕድገት

የኢትዮጵያ ታሪክ የመነሻና የባለቤት ጥያቄ

እንግሊዛዊው ታዋቂ የታሪክ፥ የቋንቋና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል፥ *Black Athena: The Afroasiatic Roots of Classical Civilization (1897)* በተሰኘው ጥናቱ እንዲሁም በቅርቡ በአዲስ አበባ ተገኝቶ «የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ አፍሪካ ናት» በሚል ርዕስ ከአፎይታ መጽሔት ጋር ባካሄደው ትምህርታዊ ቃለ ምልልስ፥ በ18-20ኛ ምዕተ ዓመታት የምዕራቡ ክርስቲያን ምሁራን፥ በጀርመኑ የቋንቋ፥ የታሪክና የሃይማኖት ፈላስፋዎች አመራር፥ በአፍሪካና በእስያ ጥንታዊ ሕዝቦች ላይ የጭው አውሮፓውያንን የዘርና የባህል በላይነት ለመገንባት ባካሄዱት ትግል የዘረኝነት እምነትና ትምህርት ፈጥረው፥ በአውሮፓና በአሜሪካ እንዳስፋፉት፥ ብሎም በሂትለሩ ጀርመን በይሁዳውያን ላይ ለተካሄደው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዴት የፖለቲካ መሠረት፥ መንገድና ምክንያት እንደፈጠሩ አሳይቷል።

ከፕሮፌሰሩ ጋር የተካሄደውን የቃለ ምልልስ ይዘትና ትምህርት አስመልክቶ የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል እንደገለጸው፥

«በዚህ እትማችን ለየት ያለ ታሪክ ይዘን ቀርበናል። እውቁ እንግሊዛዊ ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል ያልተለመደ የታሪክ ምልከታ አድርገዋል። አዲስ የታሪክ ሃሳብም አቅርበዋል። «የኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎች አባት ግዕዝ ነው» የሚለውን ሽረውታል። «ጉራግኛ የግዕዝ ሉዮት ነው» ብለውታል። ያልተለመደ ነው። የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች ከደቡብ አረቢያ መጡ ሲባል ነበር። ይህ አስተሳሰብ እስካሁን ድረስ ተቀባይነት አግኝቶ ቢቆይም በፕሮፌሰሩ ዘንድ ግን ሥፍራ ያለው አይደለም። እስካሁን ሲታመንበት የቆየውን የሴም ቋንቋዎች ከደቡብ ኢትዮጵያ ካሉ ቋንቋዎች ቀደምትነት አላቸው የሚለውን ሙሉ በሙሉ ያናጋል። ለዘመናችን በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠውን የታሪክ ትምህርትም የሚገለባብጥ በመሆኑ የክርክር እሳት ለኩሰዋል ፕሮፌሰሩ - ጥልቅ ንባብን ይጠይቃል።»[6]

በመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል አስቀድሞ እንደተገመተውም የፕሮፌሰሩ ትምህርት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ክርክር ማስነሳቱ አልቀረም። ይህንንም በሚመለከት አፎይታ መጽሔት በሐምሌ 1989

[6] አፎይታ፥ ቅ. 5 ቁ. 10 (ሐምሌ 1989) ገፅ 2።

እትሙ፥ «ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል የተባሉ ምሁር ሁለት አከራካሪ ሐሳቦች አቅርበው ነበር። አንደኛው ሐሳብ የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ አፍሪካ ናት የሚል ሲሆን፥ ሁለተኛው ሐሳብ ደግሞ የጉራማኛ ቋንቋ ከግዕዝ ቋንቋ ቀደምትነት አለው የሚል ነው። ሁለተኛው ሀሳብ በተለይ ከፍተኛ ክርክር አስነስቷል። ሀሳቡ ደጋፊዎችም ተቋሚዎችም አሉት። በሁለቱም ሀሳቦች ላይ ያላቸውን ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡን በታሪክ ምሁር የሆኑትን ዶክተር ላጵሶ ጌ. ድሌቦን ጋብዘናል»[7] በማለት የግንዛቤ ጥያቄ አቅርቧል።

ይህን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ ታሪክ መነሻና ባለቤት በተመለከተ ከእርይታ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በቀረበው ጥያቄ መሠረት የሰጠሁት ማብራሪያ የዚህ <u>ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች</u> ጥናት አካል ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች መጤዎች አይደሉም

ጉዳዩ አንገብጋቢና ወቅታዊ ነው። ጥያቄውም የማንነት ጥያቄ ነው። አንድ ሕዝብ፥ አንድ ሀገር፥ አንድ ባህል የራሱ የሆነ ሕይወት አለው። መነሻ አለው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሕዝብነታቸው፥ ዜጎችም በዜግነታቸው የማንነት ጥያቄ አንስተዋል። የሀገርን ምልክት፥ የሀገርን ማንነት፥ የሀገርን መሠረት ማንሳት የአንድ ሕዝብ የዕድገትና የማንነት መነሻ ነው። እስከዛሬ ድረስ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተሳሰረ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸው ሰው ሁሉ ከመካከለኛው ምስራቅ እንደ ተገኘ ነው። ምዕራቡ አለምም ያንን እምነት ተቀብሎ ያስተጋባል። ምዕራባውያን ምሁራን የሚያስተምሩት በክርስትና፥ በእስልምና እና በአሪት እምነቶች ላይ የተመሰረተውን ታሪክ ነው።

ኢትዮጵያ ሶስቱን ታላላቅ መለኮታዊ እምነቶች ተቀብላ የኖረች ሀገር ነች። ከሃይማኖት፥ በተለይም ከዘፍጥረትና ከሴም ቋንቋዎች ጋር በማያያዝ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደቡብ አረቢያ የመጣ ሕዝብ ነው የሚሉት። እንደመጽሐፍ ቅዱስ አባባል አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ ነው። በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ያሉ ሕዝቦች ሴማውያን ስለሆኑ የሴም ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ሕዝብ ሁሉ ከመካከለኛው ምስራቅ የፈለሰ ነው ብለው ለ300 ዓመታት ነጭ ምሁራን ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ይህ እምነት ነው፥ የሚያስፈልገው ግን እምነት ሳይሆን እውቀት ነው። እውቀት የሚጨበጥ፥ የሚዳሰስ፥ ክርክር የማያስነሳ የመረጃ፥ የሕዝብና የስፍራ ጥያቄ

[7] እርይታ፥ ቅ.6 ቁ.2 (ጎንር 1990)፥ ገፅ 16-22።

ስለሆነ ማስረጃ ያስፈልገዋል። ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያውያን ማን ናቸው? ተብሎ ይጠየቃል። ይህ ዘወትር የሚነሳ ጥያቄ ነው።

ከፍተኛ ጥንታዊ ስልጣኔ በኢትዮጵያ መገኘቱ ሐቅ ነው። ፊደልና ዘውድ ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝተዋል። ይህ የሥልጣኔ ምልክት ነው። ከዚህ አኳያ በ1681 ጀርመናዊው የቋንቋ ምሁር ኢዮብ ሉዶልፍ የኢትዮጵያ ታሪክን በሚመለከት አንድ መጽሐፍ ጽፏል። ይህ ምሁር የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ሲመረምር ስምንት ሕያው የሆኑ የሴም ቋንቋዎችን ማለትም ግዕዝ፥ ትግሪኛ፥ ትግርኛ፥ አርጎባ፥ አማርኛ፥ ጉራግኛ፥ ሐረሪኛና ጋፋትኛ አገኘ። ከዚህ ግኝት ተነስቶ ቋንቋዎቹ ከደቡብ አረቢያ የመጡ ናቸው ብሎ ደመደመ። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያውያን ከደቡብ አረቢያ የመጡ ሕዝቦች ናቸው ብሎ አስተማረ ፡፡ለት ነው። ለምን? ከሁሉ አስቀድሞ፥ ኢዮብ ሉዶልፍ ክርስቲያን ነው። ስለዚህም ሥራውን የመሰረተው በክርስትና እምነት ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሉዶልፍ ዘመን የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ ሀሳብ (evolution theory) አልነበረም። የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ ሀሳብ የመጣው በ19ኛው ምዕተ ዓመት ነው። ስለዚህም የሉዶልፍ ሥራ የተመሰረተው በክርስትና አስተምህሮ ላይ ነው። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእስራኤልና የአረብ ወገን ነው ተብሎ ተፈረጀ።

ከሉዶልፍ ቀጥሎ የተነሱ ምዕራባውያንና የአይሁድ የቋንቋና የስነጽሑፍ ሊቃውንት በተለይም የጀርመን፥ የኢጣሊያና የይሁዲ ሊቃውንት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሴማዊ ሕዝብ ነው ብለው በስፋት አስተማሩ። እኛንም ጭምር ያስተማሩን ይህንኑ ታሪክ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ምርጥ የሆነ ሴማዊ ሕዝብ ከምድረ አረቢያ ተነስቶ ኋላቀር የነበረውን የአፍሪካን «ኩሻዊ ሕዝብ» አሰልጠነ እንደማለት ነው። ይህ ግን በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ እውቀት ሳይሆን ሃይማኖታዊ ቀኖና ነው። እኛ ከታሪክ አኳያ መመርመር ያለብን ደግሞ በቀኖና ላይ የተመሠረተ ሃይማኖትን ሳይሆን ተጨባጭ መረጃዎችን ነው። መረጃ ከሌለ ታሪክ የለም። ታሪክ የሚኖረውም መረጃ ሲኖር ነው። ታሪክ ማለትም ባለፉት ዘመናት የሰው ልጅ የሰራቸው ተግባሮች ናቸው። የሰዎች ሥራዎች የሚሞኑት ግን ከእውቀት እንጂ ከእምነት አይደለም።

በመሠረቱ የኢትዮጵያን ታሪክ ከሶስቱ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ጋር እያያያዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመካከለኛው ምስራቅ የመጣ ነው ማለት ሚዛን አይደፋም። የኢትዮጵያ ታሪክ ከመካከለኛው ምስራቅ ታሪክ ቅድሚያ አለው። ምክንያቱም የአይሁድ ታሪክ «ከአብረሃም ኩሎሳን» ያለው እድሜ 4000 ዓመት ነው። የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ ግን

ከአይሁድ፥ ከሙሴና ከኖህ በፊት ነበር። ሕዝቡም እዚሁ ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ነበር። ሙሴ ራሱ ሲጽፍ በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ሕዝብ ፕንት፥ በሱዳን ያለውን ሕዝብ ኩሽ፥ በግብፅ የነበረውን ሕዝብ ግብፃዊ ብሏል። ስለዚህም እነዚህ ወንድማማች የሆኑ ነገርና ጥንታዊያን ሕዝቦች በአካባቢው መኖራቸውን እንጂ ከአረቢያ መምጣታቸውን የሙሴ ዘገባ አያመለክትም።

ይህንን ሐቅ ከተቀበልን በሶስቱም አካባቢዎች ማለትም በግብፅ፥ በኑቢያና በኢትዮጵያ ታላላቅ ሥልጣኔዎች ነበሩ። ነገር ግን ምዕራባዊያን ምሁራን ይህንን እውነታ በመካድ አፍሪካዊ ሥልጣኔ አልነበረም አሉ። ጥቁር ሕዝብ አይሰራም፥ የግብፅ፥ የኑቢያና የኢትዮጵያ ሥልጣኔዎች መጤዎች ናቸው ብለው አስተማሩ። ሥልጣኔዎቹ የጥቁር ሥልጣኔዎች ሊሆኑ አይችሉም ብለው ደመደሙ። ሌላውንም ሕዝብ አሳመኑ። አሁን ግን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከማደጉ የተነሳ የእውቀት አብዮት ተካሄደ፥ ምርምር ተጠናከረ። አርኪዮሎጂ እንደገና ተመረመረ። በምድር ውስጥ ተቀብሮ የነበረው ጽሑፍ ተጠና። የአርኪዮሎጂው መረጃ አውሮፓውያን ታሪክ ብለው ያስተማሩትን ተረት የሚያፈርስ ሆኖ ተገኘ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሀገር በቀል ናቸው

ከ1955 ጀምሮ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የአርኪዮሎጂ ጥናት ተካሄዷል። በዚህም መሠረት በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግእዝና የግሪክ ቋንቋዎች የተፃፉ ወደ 500 የሚጠጉ ሰነዶች በኢትዮጵያ ተገኝ ተዋል። ደአማት ለግእዝ መነሻ የሆነ ጥንታዊ ቋንቋ መሆኑ ተረጋግጧል። ሰነዶቹ የሚያስረዱት የሴም ቋንቋዎች የአፍሪካ ቋንቋዎች መሆናቸውን ነው። አውሮፓውያኑ ግን ሴማዊ ፊደልና ስምንት የሴም ቋንቋ ማኅበረሰቦች ስለተገኙ ሕዝቦቹ ከባሕር ማዶ ነው የመጡት ብለው አስተማሩ። እምነታዊ ተጽእኖም አሳደሩ።

ዳሩ ግን በኢትዮጵያ ከአክሱም ሥልጣኔ በፊት በነበረው የደአማት ሥልጣኔ ዘመን ሁለት ፊደሎች እንደነበሩ በአርኪዮሎጂ ጥናትና ምሁራን አሁን ተረጋግጧል። ከሁለቱ አንዱ የሳባ ጽሑፍ ሲሆን ይህም ጽሑፍ ሐውልታዊ የቁም ጽሑፍ ነው። ሆኖም ይህ ጽሑፍ አንድ መቶ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ጠፍቷል። በምን ምክንያት እንደጠፋ ግን አይታወቅም። ከሳባ ፊደል ሌላ ስድ (cursive) የሆነ ፊደልም ተገኝቷል። ጽሑፉ ተራ ጽሑፍ ሲሆን የዚህ ጽሑፍ ምስጢር የተገኘው ከ20 ዓመት በፊት ነው። የዚህን ጽሑፍ ምስጢር ታላላቅ ምሁራን የተባሉት ኤኖ ሊትማንና ኮንቲ ሮሲኒ እንኳ ሊያውቁት

አልቻሉም ነበር። እንዳውም ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጣ በኋላ ኢትዮጵያውያን ያበላሹት የሳባ ፊደል ነው ብለው ደምድመዋል። አሁን ግን የጥንት ጽሑፍ ኤክስፐርቶች (epigraphists) ሲመረምሩት ራሱን የቻለ የደአማት ፊደል ሆኖ ተገኘ። ይህ ፊደል በኋላ ለመጣው ለግእዝ ፊደልና ጽሕፈት መሠረት እንደሆነ በአርኪዮሎጂ ጥናት ተረጋግጧል። ይህንንም ምስጢር የደረሱበት የደቹ ተወላጅ አብርሃም ጆሃን ድሬዌስና የሉክሰምበርጉ ተወላጅ ሮዝር ሽናይደር ናችው። እነዚህ ምሁራን በመጀመሪያ ሌሎች አውሮፓ ውያን የፃፉዋቸውን ድርሳናት በሙሉ ከመረመሩ በኋላ አያሌ ጥያቄዎችን ደረደሩ። ቀጥሎም የኢትዮጵያ ፊደል ከውጭ ለመምጣቱ ማስረጃው ምንድነው? ብለውም ጠየቁ። በኋላም ድሬዌስ በ1962 እኤአ እስካሁን በአውሮፓውያን የተፃፈው ታሪክ ስሕተት ያለበት መሆኑን በሚገባ አጋለጡ። በመጨረሻም ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘው ደአማታዊ ፊደል ሀገር በቀል እንጂ ከውጭ የመጣ አለመሆኑን ፕሮፌሰር ሽናይደር ጨምረው አረጋገጡ።

ሁለቱ ምሁራን የደረሱበት ግኝት ትክክለኛ መሆኑንን አለምን አሳመኑ። እርግጥ የሳባ ፊደል ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝቷል። ነገር ግን ከርሱ በፊት ለዛሬ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥልጣኔ መሠረት የሆነው የደአማት ፊደል የተገኘው በኢትዮጵያ ምድር ነው። ፊደሉ ከኢትዮጵያ ውጭ በሌላ አለም አልተገኘም። አለመገኘቱንም የቋንቋ ሳይንስና የአርኪዮሎጂ መረጃዎች አረጋግጠዋል።

በቋንቋ ሳይንስ ማስረጃዎች እውነታ መሠረት ፊደሉ በታዳጊነት ደረጃ ላይ የነበረ ቢሆንም የግዕዝ ቋንቋ ፊደልና ጽሕፈት የተገኘው ከዚሁ ከደአማት ቋንቋ ፊደልና ጽሕፈት መሆኑ ተረጋግጧል። በኋላ ግን እያደገ በመሄድና አናባቢዎችን በመጨመር የግእዝ ፊደል ሆኗል። በዚህም መሠረት እስከ አሁን ቀኖናዊ ምሁራን እንደሚነግሩን ሳይሆን የኢትዮጵያ የአክሱም ሥልጣኔ የሚጀምረው ከአክሱም ሥልጣኔ 500 አመታት በፊት ከነበረው የደአማት መንግሥት ነው።

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጥንታዊ ነው

የደአማት ሥልጣኔ ከመጀመሩ በፊትም በአፍሪካ ቀንድ የፑንት ሥልጣኔ ነበር። የፑንት መንግሥት ከግብፆች ጋር ከ2800-1000 ዓመተ ዓለም ድረስ ለ1800 ዓመታት ያህል የጠበቀ የንግድ ግንኙነት ነበረው። በዚያን ወቅት ተስሎ የተገኘው ስዕል የዛሬ ሱማሌዎችን፥ ትግሬዎችን፥ አሮሞችን፥ አፋሮችን መዘተ የሚመስል ገፅታ አለው። ሥዕሉ እነዚህ ሕዝቦች በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚኖሩ ጥንታውያን ሕዝቦች መሆናቸውን ያሳያል። ይህ ከዛሬ 7,000 ዓመታት በፊት የነበረ ሥዕል

ኢትዮጵያ ከጥንት ግብፃውያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደ ነበራት ያሳያል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ያልተቋረጠ ዘመናዊ መንግሥት የጀመረው ከደአማት ዘመን ሲሆን ከዚያ በኋላ የአክሱም መንግሥት፥ ከአክሱም መንግሥት ቀጥሎ የአገው መንግሥት፥ ከአገው መንግሥት በኋላ የአማራ መንግሥት ይከተላል። በደቡብም እንደዚሁ ሐርላና ሀዲያ የሚባሉ ሕዝቦችና መንግሥታት ነበሩ። እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ደግሞ አያሌ መንግሥታት ተስፋፍተዋል። በዚህም መሠረት ለመንግሥታት መበራከት የአሪት፥ የክርስትናና የእስልምና እምነቶች ምክንያት ሆነዋል። እነዚህም ሃይማኖቶች ከጥንት ጀምሮ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደ ነበረን ያሳያሉ። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የንግድ መስተጋብሮች የነበሩዋት ሲሆን በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ የነበሩ ሉአላዊ መንግሥታትና የኢትዮጵያ መንግሥት ግንኙነት ነበራቸው። የአርኪዮሎጂ መረጃም የሚመሰክረው ይህንን ሐቅ ነው። ሐቁ ይህ ከሆነ ደግሞ ከ50 ዓመት በፊት ስለኢትዮጵያ የተፃፉት ታሪኮች ተረቶች ነበሩ ማለት ይቻላል። መነሻቸውም ቁጥር የሥልጣኔ ፈጣሪ ሊሆን አይችልም የሚል መላምት ነው። የሚገርመው ግን ያንን ተረት ተቀብለን ማስተጋባታችን ነው። ነገሩ ሞኝን አንድ ጊዜ ስደበው ራሱን ሲሰድብ ይኖራል እንደሚባለው መሆኑ ነው። ያም ሆነ ይህ እውቀት በሰፈነበት ዘመን ፈረንጆቹ ያሉትን ተቀብሎ ማስተ ጋባቱ የሚያዋጣ ነገር አይደለም። የአርኪዮሎጂ መረጃ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ምንጭም፥ መነሻም፥ ባለቤትም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ነው።

አውሮፓውያን የማንነት ችግር አለባቸው

በቋንቋ ሳይንስ በኩል ያለውን ደግሞ እንመርምር። ይህ የቋንቋ ሳይንስ የአንድን ቋንቋ አገባብ፥ ግስ፥ እድሜና ዘርፉን የሚነግረን ነው። የቋንቋ ሳይንስ ሊንጉዊስቲክስ ይባላል። የሥነ ልሳን ሳይንስ የተስፋፋው ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ሲሆን አዲስ ሳይንስ ነው። ከዚያ በፊት ግን ከዚህ ቀድም ስለኛ ሲነግሩን የነበሩ አውሮፓውያን ማንነትን በግልፅ እንመርምር። ከሁሉ አስቀደሞ አውሮፓ የማንነት (identity) ችግር ያለበት አህጉር ነው። በዚህም ረገድ ግብፆች የዓለም መንግሥት በነበሩበት ወቅት፥ ፊኒቃውያን የዓለም አስተማሪዎች በነበሩበት ወቅት፥ ባቢሎናውያን የዓለም ሕግ አስተማሪዎች በነበሩበት ወቅት የአውሮፓ ውያን ሥልጣኔ አልነበረም። ከዘመናት በኋላ ግን ግሪኮች ተነሱ።

ግሪኮችም ወደ ግብፅ ተጉዘው ሃይማኖትንና የሃይማኖት ሥርዓትን፥ ጂአሜትሪንና ኪነጥበብን ከግብፅ ሊቃውንት ተማሩ።

ከፊኒቃውያንም እንደዚሁ የተለያዩ ጥበቦችን ተምረዋል። ከዚያ ምክንያት ግሪካውያን ሰለጠኑ። ሮማውያንም ለጠቁ። እስልምና ሲነሳ ግን ታጠፉ። ከዚያ በኋላ ምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ከማእከላዊ አውሮፓ የመጡ ባርቤሪያንስ የተባሉ ወራሪ ዘላኖች የግሪክንና የሮማውያን ሥልጣኔ አጥፍተው በኋላ አዲስ ክርስቲያናዊ ሥልጣኔ መሰረቱ። ከዚያም መስፋፋት ጀመሩ። ነገር ግን የእስልምናን እንቅስቃሴ መቋቋም አልቻሉም። የመስቀል ጦርነት የሚባል ዘመቻ አውጀው ለ300 ዓመታት ተዋግተው ተሸንፈዋል። ከዚህም የተነሳ የጥቁር ዘር እኩይ ነው፥ የአረብ ዘር እርጉም ነው፥ እስልምና ማለት ባርነት ነው ብለው ሰበኩ፥ አስተማሩ። በመሠረቱ ይህ ትምህርት ሚዳቋን አባሮ መያዝ ሲያቅት ስጋዋ መጥፎ ነው ከማለት የተለየ አይደለም።

ከዘመናት በኋላ ግን አውሮፓውያን ሳይንስና ቴክኖሎጂን አስፋፍተው በየብስ ያቃታቸውን በባሕር ተጉዘው ዓለምን በቅኝ ግዛትነት ያዙ። አፍሪካን የባሪያ ገበያ፥ የምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ አህጉራትን፥ አውስትራሊያንና ኒውዚላንድንም መኖሪያቸው አደረጉ። ከዚህ በኋላ የማንነት ጥያቄ ተነሳ። ጀርመኖች፥ አንግሎ-ሳክሰኖችና ፍራንኩች ባርቤሪያንስ ስለነበሩ ከዚያ የተገኘ ሥልጣኔ ስላልነበር ፈታቸውን ወደ ግሪክ ሥልጣኔ አዞሩ። ይህንን ያደረጉት የማንነትን ጥያቄ ለመመለስ ነው። ከሮማውያን ሕግን፥ ከግሪኮች ዴሞክራሲን ወሰዱ! ያም ስላልበቃቸው ክርስትናን አጠናከሩ።

የግሪክን ሥልጣኔ ሲመረምሩ ከግብፅ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ሆኖ አገኙት ግን አምኖ ለመቀበል አልፈቀዱም። ምክንያቱም ባሪያ አድርገው የገዙትን አፍሪካዊ፥ የሰው ዘር አይደለም ብለው የካዱትን ሕዝብ የሥልጣኔ ምንጭ ነው ብለው መቀበል አዳገታቸው። ሆኖም ሶስት የጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔዎችን አግኝተዋል። የግብፅ፥ የኑቢያና የአክሱም ሥልጣኔዎች ናቸው። እነዚህን ሥልጣኔዎች አፍሪካዊ ሥልጣኔዎች ናቸው ብለው ለመቀበል አልፈለጉም። ይህን ያልተቀበሉት የሚያካሂዱትን የባሪያ ንግድ የሚቃረን በመሆኑ ነው። ስለዚህም አውሮፓውያን ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። በመጣታቸውም ኢትዮጵያ የሚለውን ስም በመፋቅ አቢሲኒያ በሚል ስያሜ ተኩት። የአንድን ነገር ሕልውና ለማጥፋት መጀመሪያ መጠሪያውን መቀየር የተለመደ አካሄድ መሆኑን ካርል ማርክስ በአጽንኦት መግለጹን እዚህ ላይ ማስታወስ ይጠቅማል።

ይሆንን ከአደረጉ በኋላ አውሮፓውያኑ የፈጠራ ታሪካቸውን አስተማሩን፥ የነፃ ትምህርት እድል ሰጡን። እኛም ያስተማሩንን አጠናን። ያንን ለሌሎችም ማስተማር ጀመርን። የአርኪዮሎጂ ዕውቀት እየሰፋ ሲሄድ ግን የተማርነው ትምህርት ስህተት ሆኖ ተገኘ። ስነልሳን በበኩሉ የሴም ቋንቋዎች በአረቢያ፥ በባቢሎን ከመነገራቸው በፊት፥ ፊኒቃውያንና አይሁዳውያን ከመገኘታቸው በፊት ቢያንስ ከ10 ሽህ ዓመታት በፊት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ይነገሩ እንደነበር አረጋገጠ። ቋንቋዎቹ ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሄዱት ከአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ተነስተው እንደሆነም አሳየ። በዚህም መሠረት ማስረጃዎች የሚያረጋግጡት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሀገር በቀል መሆናቸውን ነው። ስለሆነም ሴማዊ፥ ኩሻዊ፥ ናይሎቲካዊና አሞአዊ ቋንቋዎች በሙሉ ኢትዮጵያውያን ቋንቋዎች ናቸው። ከውጭ የመጣ አንድም የኢትዮጵያ ቋንቋ የለም። ሕዝቡም የዚሁ ሀገር ተወላጅ፥ ነባር ነው። መጤ የሚባል ሕዝብ የለም። የጠፋ ዘርም የለም። የሚያስገርመው ነገር በሌላው ዓለም ዘር ሲጠፋ፥ በባእዳን ሲገዛ፥ በአፍሪካ ቀንድ ግን የጥንቱ ፔንታውያን ደአማታውያን ሆኑ፥ ደአማ ታውያን ደግሞ አክሱማውያን ሆኑ እንጂ አልጠፉም። ፈረንጆቹ ያስተማሩት ግን የዚህን ተቃራኒ ነው። ለመሆኑ በመካከለኛው ምስ ራቅ ውስጥ ያልነበረ ቋንቋ እንዴት ወደዚህ ሊመጣ ይችላል?

የሰው ዘር መገኛ የአፍሪካ አህጉር ነው

በፓሌአንቶሎጂ መረጃና ትምህርት መሰረት፥ የሰው ዘር መገኛ ምንጭ ባቢሎንና መካከለኛው ምስራቅ ሳይሆኑ የአፍሪካ አህጉር ነው። ከዚህ አኳያ የድንቅነሽ ቅሪት አካል በኢትዮጵያ መገኘት የዓለምን ታሪክ ገለባብጦታል። የሰው ዘር መገኛ በአፍሪካ አህጉር የኢትዮጵያ ምድር መሆኑን ድንቅነሽ አስመስክራለች። እንደ ይሁዳውያኑና እንደ አውሮፓውያኑ የሃይማኖት ትምህርት ከሆነ የዓለም ታሪክ ከ6000 ዓመታት አይበልጥም። ምክንያቱም ትምህርታቸው በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የምድርን እድሜ ከ8000 ዓመታት በታች ያደረገዋል። የድንቅነሽ እድሜ ግን ከ3 ሚልዮን ዓመት በላይ ነው። የሰው ልጅ የተገኘው በአዋሽ አካባቢ ነው። አዋሽ ደግሞ የኢትዮጵያ ወንዝ ነው። አፍሪካ የሰው ዘር መገኛ መሆንዋን ዩኔስኮ ተቀብሎታል። ዩኔስኮ ስለአፍሪካ ታሪክ በስምንት ተከታታይ ቅፆች ባሳተማቸው ዕሁፎች የሰው ዘር መገኛ አፍሪካ እንደሆነች በሚገባ ገልጿል። ጆርመኖችና ኢጣሊያውያን ምሁራንም አሁን የአፍሪካን የሰው ዘር ምንጭነት ይቀበላሉ።

በእርግጥም በእምነት ግፊት ሳይሆን በተጨባጭ እውቀት የምናምን ከሆነ መቀበል ያለብን ሰው የተገኘው በአፍሪካ ቀንድ መሆኑን ነው። የአሁኑ ዘመን የምዕራብ ሊቃውንት የአፍሪካን የሰው ዘር ምንጭነት ተቀብለዋል። ይህንን ሐቅ ፖሌአንቶሎጂ አረጋግጧል። በተጨማሪም የሁለት ሚሊዮን ዓመት እድሜ ያለው ድንጋይ መሳሪያ ከአዲስ አበባ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በመልካ ቁንጥሬ ተገኝቷል። በአፋር ምድር የተገኘውም የድንጋይ መሳሪያ ደግሞ የአራት ሚልዮን ዓመት እድሜ አለው። ይህም የቤት እንስሳትን፥ እፅዋትን አዝርዕትንና አራዊትን ያሰለጠነ ሕዝብ የተገኘው በዚህ ሀገር ነው። የተከዜ፥ የቀይ ባሕር፥ የአዋሽ፥ የዓባይ፥ የኦሞ፥ የዋቢሸበሌ፥ የዳቡስ ወንዞች ወዘተ የሚገኙትም በዚህ አካባቢ ነው። በዚህ አካባቢ የሚገኘው ሕዝብ በሚደረገው እንቅስቃሴ፥ በጦርነት፥ በጋብቻ እርስ በርስ የተወራረሰ ነው። ከሥልጣኔም ትልቁ ነገር የመንግሥት ምስረታ ነው። በዚህ ረገድ የአካባቢው የቱንት መንግሥት ከየትኛውም ሀገር በፊት መንግሥት ከመሰረተው ከጥንቱ የግብፅ መንግሥት ጋር ለ1800 ዓመታት ያህል የጠበቀ ግንኙነት ነበረው።

ነገር ግን ይህን የአገር ታሪክ እውነታና እውቀት ከማወቅና ከማስተማር አኳያ፥ ከሃይማኖት ተፅእኖ የተነሳ ኢትዮጵያዊው ምሁርና ባለሙያ ፈሪና ተጠራጣሪ ሆኗል። እምኑ ስለተጫነው ወይም የውጭ አስተማሪ፥ ምሁር ስለተናገረ፥ አሱም የኔ መምህር ስለሆነ ያንን መቀበል አለብኝ የሚልም ይመስላል። ነገር ግን ያንን ተረት ዘመናዊና ሳይንሳዊ የታሪክ መረጃና ትምህርት ሽሮታል።

የአፍሮ-እስያ ቋንቋዎች መነሻና ትምህርት

የአፍሮ-እስያ ቋንቋዎች መገኛ አብዮታዊ አስተሳሰብን አምጥቷል። የዚህ ግኝት ባለቤት አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ጆሴፍ ግሪን በርግ ናቸው። አፍሮ-እስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ የቅብጥን (ግብፅ)፥ የበርበር (የሰሜን አፍሪካ)፥ ቻዳዊ (ምዕራብ አፍሪካ)፥ ኩሻዊ፥ ናይሎቲካዊ፥ አሞአዊና ሴማዊ የተባሉ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ያጠቃልላል። እነዚህ ቋንቋዎች የአፍሪካና የእስያ ጥንታዊና ተዛማጅ ቋንቋዎች ናቸው። ከነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ የሴም ቋንቋዎች በኢትዮጵያ፥ በደቡብ አረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ ይገኛሉ። ሃያ አራት የሚሆኑ ኩሻዊ ቋንቋዎች የሚገኙት በኢትዮጵያ ሲሆን ሌሎች የኩሽ ቋንቋዎችም በጎረቤት ሀገሮች ይገኛሉ። የአሞአዊ ቋንቋዎች የሚገኙት በኢትዮጵያ ብቻ ነው። ናይሎቲካዊ ቋንቋዎችም በኢትዮጵያና በጎረቤት ሀገሮች ይገኛሉ። እነዚህን ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦች ጥንታውያንና

ተዛማጆች ናቸው። ሕዝቦቹ በዘር፥ በሥፍራና በጊዜ ተወራርሰዋል። ነባር የአካባቢው ነዋሪዎችም ናቸው። ኩሻዊ ቋንቋ የሚወክለው ሶስት ጥንታዊ ሕዝቦችን ሲሆን ይኸውም በአፍሪካ ቀንድ ጉንታውያንን፥ በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ኑቢያውያንን፥ በታችኛው ዓባይ ሸለቆ ግብፃውያንን ነው። ከነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ የኑቢያ ቋንቋ ጠፍቷል። ሀገሩም የአረቦች ሀገር ሆኗል። ግብፅም እንዲሁ የአረቦች ሀገር ሆኗል።

ዛሬ እነዚህን ሶስት ጥንታዊ የኩሽ ቋንቋዎችን የምትወክል ኢትዮጵያ ናት። የጉንት፥ የግብፅና የኑቢያ ወራሽ የሆነ ያልጠፋ ሀገርና ሕዝብ የሚገኘው በአፍሪካ ቀንድ ነው። ቋንቋ በኢትዮጵያ የዘር መሊያና የማንነት መግለጫ ነው። በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ሰውጥ እየተካሄደ ነው። አዲስ የፖለቲካ ስልት፥ አዲስ የኢኮኖሚ ሥርዓት እየተመሰረተ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ባሕር ነው። እስካሁን የተፃፈው ግን ዜና መዋእልና ገድል ነው። መፃፍ ያለበት ግን የኅብረተሰብ ታሪክ ነው። ያንን ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎች ተገኝተዋል። አዲሰ የታሪክ አጠናን ስነዘዴም (methedology) ተፈጥሯል። ቋንቋን ብንወስድ የሀገር፥ የብሔር፥ የብሔረሰብና የማኅበረሰብ መለያ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት 50 ዓመታት የብሔር ብሔረሰቦች አብዮት እየተካሄደ ነው። የብሔር ብሔረሰቦች አብዮት ማለት የቋንቋ፥ የታሪክ፥ የባህል፥ የሃይማኖት እንቀስቃሴ መግለጫ ማለት ነው። ይህ በሚደረግበት ዘመን የአርኪዮሎጂ፥ የሥነ ልሳንና የፖሌዮንቶሎጂ መረጃዎች ከእኛ ጋር ተሰልፈዋል። የአፍሮ-እስያዊ ቋንቋ ቤተሰብ መገኘት ከዚህ ቀደም የነበረውን ታሪክ ሽሮታል። ከዚህ ቀደም የነበረው ታሪክ ጥንታዊ የአይሁድ አስተማሪ ዎችና ጸሐፊዎች በፃፉት ድረሰናት ላይ የተመሰረተ ነው። ታሪኩም ከእምነት ጋር የተቆራኘ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ነው። የአውሮፓ ታሪክ ጸሐፊዎች ያስተጋቡት የነበረው ያንን ታሪክ ነው። በዚህም የተሳሳ ነው የሴም ቋንቋዎች መነሻ መካከለኛው ምስራቅ ነው የተባለው።

አውሮፓውያን በበኩላቸው የኢንዶ-አውሮፓ፥ ግሪክና ላቲን ቋንቋዎችን አቅፈው ተነሱ። በዚያም ምርጥ ዘር ነንና ዓለምን መግ ዛት አሰብን አሉ። ከሰው ዘሮች ሁሉ ምርጥ የሆነው የአርያን ዘር ነው የሚል ፍልስፍና አመጡ። አፍሪካን ባሪያ አድርገው መግዛት ያዙ። የአፍሪካ ሕዝቦችን ሥልጣኔ ካዱ። ይህም ለባሪያ ንግድ እንዲ መቻቸው ነው። የግብፅን ሥልጣኔ መካድ ሲችግራቸው ደግሞ ግብፅ ጥቁር አይደ ለም፥ ኔግ ነው አሉ። ኑቢያም ኔግ እንጂ ጥቁር ሕዝብ አይደለም አሉ። የኢትዮጵያን ሥልጣኔ አፍሪካዊነት ለመካድ የኢትዮጵያ ሕዝብ

ኔግ እንጂ ጥቁር አይደለም አሉ። አውሮፓውያን በመውናበድ ላይ ሳሉም ዘረኝነት መጣ። ይህም ሒትለርና መሶሊኒን አስነሳ። ሒትለር የሰውን ዘር ሰማጥፋት ታጥቆ ተነሳ። አውሮፓ ነደደ። አውሮፓውያን ተርበደበዱ! አፈሩ። ይህን ሁሉ ጣጣ ያመጡት የሰው ዘር ጥላቻንና ንቀትን ሲሰብኩ የነበሩ ፈላስፋዎቻቸው ናቸው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት መከራን ተጋቱ። ጥቁር ሕዝብ ሰብአዊ ፍጡር አይደለም ብለው ሲሰብኩ የነበሩት ጀርመኖች በተለይ ራቁታቸውን ቀሩ። የዘረ ኝነት ፍልስፍናቸው ራሳቸውን መልሶ ሲያቃጥላቸው ጊዜ ዛሬ የሰው ልጅ ሁሉ እኩልነትና ሰብአዊ መብት ይከበር እያሉ ማስተማር ጀመሩ። ከአውሮፓ ዘር ውጭ ያሰው ሕዝብ ሰብአዊ ፍጡር አይደለም እንዳላሉ ሁሉ ዛሬ ለሰው ዘር ዴሞክራሲያዊ መብት ተሟጋች ሆኑ። ይህ ያለፈ በደላቸውን ለማካካስ ሲሉ የፈጠሩት ዘዴ ነው።

በቋንቋም ረገድ የነበረው መላምት ውድቅ ሆኖባቸዋል። የኢትዮጵያን ቋንቋዎች በኢንዶ-አውሮፓዊና በአይሁድ ቋንቋዎች ውስጥ ማስቀመጥ አልቻሉም። የአሜሪካ ፕሮፌሰሮች የደረሱበት ጭብጥ የእስያና የአፍሪካ ቋንቋዎች ተዛማጆች መሆናቸውን ነው። ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ቋንቋዎች ሀገር በቀል እንጂ ከውጭ ያልመጡ ቋንቋዎች መሆናቸው ታውቋል። ይህ ደግሞ አሁን ለተያያዝነው የሀገር ግምባታ በጣም ጠቃሚ ነው። ሴማዊ፥ ኩሻዊ፥ ናይሎቲካዊና ኦሞያዊ ሕዝቦች ነባር ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች ናቸው። በእውቀት መንገድ የምንጓዝ ከሆነ ሐቁ ይህ ነው። በእምነት ዓለም የምንጓዝ ከሆነ ሌላ ጉዳይ ነው። ማስረጃዎች የሚያረጋግጡት ግን አንድም መጤ የሆነ ሕዝብ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌለ ነው። እኛ መመራት ያለብን በሳይንስ መረጃ ነው እንጂ በእምነት ብቻ አይደ ለም። ታሪክን የምናውቀው በመዳሰስ ነው። ዘመኑን፥ ሕዝቡንና ስፍራውን ማወቅ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ የሚያግዙን ደግሞ የፖሌአንቶሎጂና የስነልሳን መረጃዎች ናቸው። በነዚህ መረጃዎች እማካይነት የኢትዮጵያውያን መነሻና ማንነት ማወቅ እንችላለን። ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ አሉ። ታላላቅ የነበሩትን፥ የሮማንና የፋርስ ሥልጣኔዎችን የደመሰሰው የአረብ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ጋር ተወዳጀ እንጂ ኢትዮጵያን አላጠፋም። ቱርኮችና ፖርቱጋሎች ኢትዮጵያን ለማጥቃት ሞክረው ነበር። ግን ተሸነፉ! ቅኝ ገዢዎችም ሞክረው ነበር ግን አድዋ ላይ ድል ተነሱ። ፋሽዝም ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ጠርነት ገጥሞ ተሸነፈ። ኢትዮጵያውያንም ያካሄዱት የ50 ዓመት አብዮት የሕዝብን አንድነት የበለጠ አጠናክረው እንጂ አላፈረሰውም። ይህ አካባቢ ሕልውናውን ጠብቆ የሚኖር ልዩ ችሎታ

ያለው ስፍራ ነው። ሕዝቡ ጥንታዊ ነው። ኋላቀር መሆኑም ታሪኩን የሚያዛባ ነገር አይደለም። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝቦች በፈጣን ዕድገት ጎዳና በመገስገስ ላይ ናቸው።

የኢትዮጵያ ወንዞች የአፍሪካ ሥልጣኔ ምንጮች ናቸው

የኢትዮጵያ ጂኦ-ፖለቲካዊ ስፍራ እስትራቴጂካዊ ነው። ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ጋን ናት። የኢትዮጵያ ውሃ የኑቢያንና የግብፅን ሥልጣኔ አፍርቷል። እኛንም አኑሮናል። ወንዞቹን በሚገባ አልተጠቀምንባቸው ይሆናል። ነገር ግን የወንዞቹ መኖር ራሱ ትልቅ ፀጋ ነው። የኢትዮጵያ ተራሮችም ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው። የታላላቅ ወንዞች መፍለቂያዎች ናቸው። ከዚህም ሌላ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ አላቸው። ለወራሪ ኃይሎች አይመቹም። ለሀገሬው ተወላጅ ግን ተስማሚ ናቸው።

ኢትዮጵያ በያይነቱ ሀብት አላት። የደጋ፣ የወይና ደጋ፣ የቆላና የበረሃ የአየር ንብረትዋ እጅግ ተስማሚ ነው። በያይነቱ እፅዋት፣ አዝርእት፣ አራዊትና እንሰሳት ይገኛሉ። ደገኛው ወደ ቆላ ይወርዳል፣ ቆለኛው ወደ ደጋ ይወጣል። ሕዝቡ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ውስጣዊ ፍልሰትንና ውህደትን ማለትም የሕዝቦችን መስተጋብርና መወራረስ ፈጥሯል።

የተማከለ ቋንቋ ወጣት ነው

የኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎችን በተመለከተ ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል ወዳጎላው ጥያቄ እንምጣ። ፕሮፌሰሩ የሚለው የተማከለ ቋንቋ ወጣትና ዘመናዊ እንደሆነ እንገንዘብ ነው። እንግሊዘኛን ብንወስድ በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በኒውዚላንድ የተማከለ ... ነው። ቋንቋው በተፈጠረበት በእንግሊዝ ግን በሀውርታዊ ነው። ይህም ብዙ ልዩነት ያሳያል ማለት ነው። በሀውርታዊ የሆነ ቋንቋ ጥንታዊነትን ማመልከቱ እርግጥ ነው። የተደራጀና የተማከለ ቋንቋ ደግሞ ዘመናዊ መሆኑ እርግጥ ነው የሚል አስተያየት ነው የሰነዘረው። ፕሮፌሰሩ የሰጠው የግንዛቤ ሐሳብ ነው። ውሳኔ አይደለም።

በጋዜጣና በመጽሔት ላይ የወጡትን አስተያየቶች ተመልክቻለሁ። አንዱ ሐሳብ የኢትዮጵያ ታሪክ በውጭ ሀገር ምሁራን መፃፍ የለበትም የሚል ነው። እውነቱ ግን ሌላ ነው። እስከዛሬ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ የፃፉት ፈረንጆችና አረቦች ናቸው። ኢትዮጵያዊ ታሪክ ፀሐፊ ነበር ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ያስቸግራል። ሁላችንም ባእዳን የፃፉትን ወስደን ነው የምናስተጋባው። በዛሬው ዘመን ታሪክ

ለመፃፍ አርኪዮሎጂ፣ ፖሌአንቶሎጂ፣ ኢፒግራፊና የተለያዩ የትም ሀገሮች ዘዴዎችና ቋንቋዎች ማወቅ ያስፈልጋል። እስካሁን የነበረው «የኢትዮጵያ ታሪክ» ዜና መዋእል፣ ገድለ ቅዱሳንና ገድለ ሰማእታት ነው። የፃፉትም የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ባለሟሎች ናቸው። የተጻፈውም የመሳፍንትና የነገሥታት ታሪክ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ገና አልተፃፈም። የሕዝቦችን እውነተኛ ታሪክ ለመፃፍ ገና ሙከራ እየተደረገ ነው።

ፕሮፌሰር ቤርናል ጉራማኛ የግእዝ አያት ነው ያለው የሥነ ልሳንን ጥናት ስነዘዴ ተመርኩዞ ነው። ስለዚህም እኛ ማድረግ ያለብን የእጠናንን ስነዘዴ ማወቅ ነው። ፕሮፌሰሩ ኢንፎርሜሽን ሰጥቶናል። በአሁኑ ጊዜ እየታመነ የመጣ ነገርም አለ። ይህም የኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎች ከደቡብ አረቢያ የመጡ አይደሉም፣ ቋንቋዎቹ ነባርና ሀገር በቀል ናቸው የሚል ነው።

ፕሮፌሰር ቤርናል ታላቅ ምሁር ነው። የኢትዮጵያ ሴማውያን ቋንቋዎች ከደቡብ አረቢያ አልመጡም ብሎ እውነቱን ስለነገረን ማኅረምረም የለብንም። ፕሮፌሰሩ ያቀረበው ሐሳብ እንደግእዝና አማርኛ ያሉ ቋንቋዎች የተማከሉና ዘመናዊ ቋንቋዎች ናቸው። ይህም በእድሜ ወጣት መሆናቸውን ያመለክታል የሚል ነው። ይህንን ሐሳብ በጥልቀት መመርመር እንጂ «ሰውዬውን እወደዋለሁ ወይም እጠለዋለሁ» ማለት ብቻ ፋይዳ የለውም። እውቀት፣ ሙያ እንጂ ስሜት አይደለም።

በእፎይታ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 10/89 ላይ ትምህርታዊ ጽሑፍ ወጥቷል። እስከዛሬ ድረስ እንደዚህ ያለጽሑፍ በአማርኛ ቋንቋ ተጽፎ አያውቅም። እኔ ከ40 ዓመት በላይ ስለኢትዮጵያ አንብቤ ያለሁ። የኢትዮጵያ ታሪክና ማንነት በሚመለከት ያነበብኳቸው መፃሕፍት የሚያወሩት ሐቁን ሳይሆን መላምት ነው። በእፎይታ መጽሔት የቀረበው ጽሑፍ አንኳር ሀሳብ ግን አፍሪካ የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ ናት፣ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ምንጭም፣ ባለቤትም ኢትዮጵያ ናት የሚል ነው። ቋንቋም በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ ለእኔ ያንን ያህል አንገብጋቢ መስሎ አይታየኝም። ማን አያት? ማን አባት? ማን ልጅ ነው የሚለው ጥያቄም ቢሆን ይህን ያህል የሚያስጨንቅን አይደለም። ዋናው ቁም ነገር ስምንቱም የሴም ቋንቋዎች ነባርና ሀገር-በቀል መሆናቸው መታወቁ ነው። ማን ከማን ይቀድማል የሚለውን ለመመለስ ያለን መረጃ አነስተኛ ነው። ያም ሆኖ ግን ፕሮፌሰር ቤርናል «የተማከለ ቋንቋ ዘመናዊና ወጣት ነው፣ በሀውርታዊ የሆነና ያልተማከለ ቋንቋ ደግሞ ጥንታዊ ነው» ያለው መንደርደሪያ ምሁራዊ አባባል

ነው። ለዚህ አባባል የሚረዳን አያሌ ሕዝብ የሚናገረውን ኦሮምኛን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል። ኦሮምኛ ኩሻዊ ቋንቋ ነው። የተማከለና የተስፋፋም ቋንቋ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ 24 ገደማ የሚሆኑ ኩሻዊ ቋንቋዎች አሉ። ከዚህ ውስጥ ስምንቱ በጣም ይቀራረባሉ። ከስምንቱ ቋንቋዎች አንዱ ኦሮምኛ ነው። የተቀሩት ሰባቱ ቋንቋዎች ያሉት በደቡብ ኢትዮጵያ ሲሆን በጣም ጥቂት ተናጋሪዎች አሏቸው። እንድ ምሁር ይህ ሁኔታ ሲያጋጥመው «የትኛው ነው ምንጭ፥ የትኛው ነው ቅርንጫፍ» ብሎ ይጠይቃል። ከዚህ በመነሳት ከስምንቱ ቋንቋዎች መካከል ኦሮምኛ ወጣት ነው ብሎ ግምት መስጠት ይቻላል። ፕሮፌሰር ቤርናልም ጉራግኛ የግእዝ አያት ይመስላል ያለው ከዚህ በመነሳት ነው። የጉራጌ ምድር ሜዳ ነው፥ ተራራማ አይደለም ያለውን አንድ ፀሐፊ በመቃወም የጉራጌ ምድር ተራራማ ነው ብሏል። ይህ ትክክለኛ አባባል አይደለም። ፕሮፌሰሩ ተራራ ሲል እንደራስ ዳሽን፥ ሐማሊያና ኤቨርስት ያሉ ተራሮች ማለቱ እንጂ ኮረብታ ማለቱ አይደለም። በጉራጌ ምድር ያሉ ኮረብታዎችን የተጫኑ በቅሎዎች፥ ፈረሶችና መኪናዎች የሚወጧቸው ናቸው። ቢያንስ ኮረብታና ተራራን መለየት መቻል አለብን። አንድን ሀሳብ ለመተቸትና ስሕተት ነው ለማለት ማስረጃ ያስፈልጋል። በተለይም የሰነድ፥ የሥነ ልሳንና የትውፊት መረጃዎች ያስፈልጋሉ። እነዚህ ሲሟሉ ነው አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻለው። ባለሙያ መሆን ያስፈልጋል። የእውቀት ባለቤት መሆን ያሻል። አሁን ባለን መረጃ መሠረት ስምንቱ የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋ ዎች የአንድ ቋንቋ ቤተሰብ በመሆናቸው ይዛመዳሉ። ፕሮፌሰር ቤርናል ጉራግኛ ከግእዝ ቀደምትነት አለው የሚል ሀሳብ ሰንዝሯል። በቂ መረጃም ሰጥቷል። መቀበል የፈለገ ይቀበላል። መቀበል ያልፈለገ ደግሞ ያለመቀበል መብት አለው። የምሁር ድርሻ ማሳወቅ ነው። ምሁር የማስገደድ ሥልጣን የለውም። የምሁር ግዴታ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። ፕሮፌሰር ቤርናል ያደረገውም ይህንኑ ነው። የሱን ሀሳብ ለማፍረስ የፈለገ ደግሞ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ስሜታዊ ተቃውሞ ማሳየት ምሁራዊ ባሕርይ አይደለም። በስሜት መነዳት የለብንም።

የጉራጌ አመጣጥ ታሪክ

ስለጉራጌ ሕዝብ አመጣጥ ፕሮፌሰር ቤርናል አንድ ሀሳብ ሰንዝሯል። ጉራግኛና ሌሎቹ የሴም ቋንቋዎች እድሚአቸው በጣም ረጅም ነው። ከዚህ ቀደም ታሪክ ፀሐፊዎች የመሰላቸውን ፅፈዋል። ኮንቲ ሮሲኒ ግእዝ ከባሕር ማዶ መጥቶ ሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎችን ወለደ ብሎ ጽፏል። ያ ሀሳቡ አሁን በትምህርትና በእውቀት ተሽሯል። ቀርቷል።

ተረት ሆኗል። የጉራጌን ቋንቋ ስንመለከት የ700 ዓመት እድሜ ያለው ቋንቋ ነው ለማለት የሚቻል አይመስለኝም። ጉራጌ የአምደ ፅዮን የጦር አበጋዝ ከሆነው አዝማች ስብሐት ጋር መጣ የሚል አፈታሪክ አለ። ይህንን የፃፉት አለቃ ታዬ ናቸው። አለቃ ታዬ የታሪክ ምሁር አይደሉም። ታሪክ ለመፃፍ የሞከሩ ሀገር ወዳድ ናቸው። አለቃ ታዬ ከሚሲዮኖች ጋር ጥቂት ቆዩ፥ ጀርመንን ጎበኙ፥ ከዚያም የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍኩ አሉ። አሁን እሳቸው የጻፉትን መፅሐፍ ስናነብ ፈጠዋታ ነው የሚመስለን።

የአለቃ ታዬ መጽሐፍ ጥሩ የተረት መጽሐፍ ነው። እኛ ስለ ሳይንስ ስለ ስነልሳን፥ ስለ ሰነድ መረጃና ስለ ስነዘዴ ነው የምንናገረው። እነዚህን መረጃዎች ለማሳጠርና ምርቱን ከግርዱ ለመለየት የሚችለው ደግሞ በመስኩ የተካነ ባለሙያ ነው። ዜና መዋዕል እኮ ጥሬ መረጃ ማለት ነው። ያንን ጥሬ መረጃ የሚተረጉም ባለሙያ ያስፈልጋል። እዚህ አገር ታሪክ ሲፃፍ የነበረው ሙያው ሳይኖር በድፍረት ነው። ታሪክ ለመፃፍ ግን የታሪክ ጥልቅ ሙያና እውቀት ያስፈልጋል።

የጉራጌን ሕዝብ በተመለከተ የአምደ ፅዮንን ጦር ከወጉት አያሌ የድቡብ ሕዝቦች መካከል አንዱ የጉራጌ ሕዝብ ነው። የጉራጌ ሕዝብ የአምደፅዮን ሰራዊት አካል ቢሆን ኖሮ አምደ ፅዮንን መልሶ አይወጋም ነበር። ጉራጌዎች ከአምደፅዮን ሰራዊት ጋር መዋጋታቸው ዘራሱ በአምደ ፅዮን ዜና መዋዕል ተገልጿል። የጉራጌ ሕዝብ በደቡብ እንዳሉት ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ነባርና ጥንታዊ ሕዝብ ነው። የጉራጌ ሕዝብ በአምደፅዮን ዘመን ከሰሜን ኢትዮጵያ መጣ የሚለው አፈታሪክ ጥሩ ተረት ነው። እኛ የምንፈልገው ግን እውነተኛ ታሪክና እውቀት ነው። የጉራጌ ሕዝብ በአካባቢው ለብዙ ሺህ ዓመታት መኖሩ የሚካድ ጉዳይ አይደለም። ፕሮፌሰር ቤርናል ለማረጋገጥ የፈለገው ይህንን እውነታ ነው። ሕዝቡ ነባርና ጥንታዊ ሕዝብ ነው። ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ በአኃዝ ለማስቀመጥ ቢያቅተንም ለብዙ ሺህ አመታት ሕዝቡ በአካባቢው ይኖር እንደነበር ማወቅ አያዳግትም። ሁኔታዎችን በሚገባ ሳይመረምሩ ያይሆናል ግምት ሕዝብን ማሳሳት ግን ተገቢ አይደለም። ዛሬ ያልታወቀ ነገር ነገ ይታወቃል። ሽግግሌ ዎች የጉራጌ ሕዝብ ከቅርብ ዘመናት በፊት ከሰሜን ኢትዮጵያ ነው የመጣው ስላሉ ብቻ እንደበቂ የታሪክ መረጃ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። መመርመር አለበት። ያንን ለማጥናት ስነዘዴ ያስፈልጋል። ጊዜው በውል መታወቅ አለበት። ከዚያ በኋላ እውቀት ይሆናል። እውቀትን ሸሽተን በእምነት መንገድ እንጓዝ ከተባለ ሰው የፈለገውን ማመን ይችላል። ታሪክ ከሆነ ደግሞ በጠንካራ ማስረጃ ማስደገፍ

ያስፈልጋል። ከሰሜን የመጡ ወራሪ ነገሥታት ጉራጌዎችን ወግተው አስገብረዋቸዋል። ከአምደ ጽዮን ጀምሮ የሰሜን ኢትዮጵያ ነገሥታት የጉራጌን ሕዝብ በተከታታይ ወግተውታል። በዚያን ወቅት የጉራጌ ሕዝብ የራሱ ቋንቋ፥ የራሱ ባህል፥ የራሱ ሃይማኖት ነበረው። ከወረራ በኋላ ጉራጌዎች ክርስትናንና እስልምናን ተቀብለዋል። የጥንቱን እምነታቸውን የያዙም አሉ። እነዚህ ሕዝቦች አሁን በአሉበት ቦታ ለብዙ ዘመናት ኖረዋል። ከሰሜን ኢትዮጵያ የመጡት ከ700 ዓመታት በፊት ነው የሚለው ሀሳብ ሚዛን አይደፋም። የሚያቀጣው ፕሮፌሰር ቤርናል ያቀረበውን ፈተና ለማለፍ ጥልቅ የታሪክ ምርምር ማድረግ ነው። ለዚህም በርትቶ ታሪክን ማጥናት ነው። አንድ ሰው ከመሬት ተነስቶ ጥሩ ብሔራዊ ስሜት ስላለኝ ታሪክ እጽፋለሁ ወይም አስተምራለሁ ቢል አያዋጣም። ብሔራዊ ስሜቱን በኪነትና በመዝሙር መግለጽ ይችላል። ስሜት ግን እውቀት አይሆንም። የታሪክ ባለሙያም አያደርግም።

ነጮች የአፍሪካን ሥልጣኔ ከደዋል

ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ አፍሪካ ናት በማለቱ ነጭ ምሁራን እንደሚጠምዱት የታወቀ ነው። ጀርመኖች ሲያቀነቅኑት የነበረውን ሀሳብ ሽሮባቸዋል። የነጮን የሥልጣኔ ምንጭነት በመሸከማቸው ጀርመኖች ተሳስተዋል በማለቱ ፕሮፌሰሩ ላይ ጠላቶች መሳሳታቸው ግልጽ ነው። ፕሮፌሰሩ ግን የሚለው ነጮቹ የአውሮፓን ሥልጣኔ ወጥ (የመጀመሪያ) ነው ለማለት የአፍሪካን የሥልጣኔ ምንጭነት ከደዋል ነው። ለምሳሌ፥ ታላቁ የጀርመን ፈላስፋ ሔግል አፍሪካዊ ሰው ሰብአዊ ገጽታ የለውም ብሏል። ይህንን ሀሳብ የሰነዘረው በባሪያ ንግድ ዘመን ነው። ነጮች የባሪያ ንግድ ተጠቃሚዎች ስለነበሩ ጥቁር ሰብአዊ ፍጡር ነው ብለው ለመቀበል አዳግቷቸዋል። ሆኖም የዘረኝነት ውጤት ፋሽዝም መሆኑን ቤሒትለርና በሙሶሊኒ እብሪት ተረድተውታል። ነገር ግን ጥቅማቸው የተነካባቸው ሽማግሌ የታሪክ ምሁራን አዲሱን ሀሳብ ይቃወማሉ። በኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ የጥናት ጉባኤዎች ላይ በየጊዜው የሚቀርቡ አዳዲስ ሀሳቦችና ግኝቶች ናቸው። ፕሮፌሰሩም ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነገር ሕዝብ ነው። መጤ አይደለም ነው። ሽማግሌዎቹ ነጭ ምሁራን የአፍሪካ የሥልጣኔ ምንጭነት መካዱን ይቀጥሉበታል። አባቴ ባሪያ ነጋዴ ነበር፥ ሀሰት የሚያስተምር መምህር ነበር ብለው ለማመን አይፈልጉም። እነዚህ ሽማግሌ ምሁራን የዩኒቨርሲቲያቸውን ክብር ይጠብቃሉ።

ፕሮፌሰር ቤርናል ተራማጅና ስርዓቀል የሆነ አስተሳሰብ ያለው ምሁር በመሆኑ እውነቱን ተናገረ። ዘረኛ የሆኑ ነጭ ምሁራን ደግሞ ተቃወሙት። በመሰረቱ አንድ አዲስ ሀሳብ የነባር ፕሮፌሰሮችን ጥቅም የሚፃረር ሆኖ ከተገኘ ትምህርቱ በዩኒቨርሲቲ እንዳይሰጥ ያደርጋሉ። ፕሮፌሰሩ የተከተለው የታሪክ አጠናን ስህዘዴ ግን የማያፈናፍን ጠንካራ ስለሆነ ሀሳቡን በቀላሉ ሚፍረስ ያዳግታል። በማውናበድ ሀሳቡን በማረሳሳትም ሆነ በዲፕሎማሲ ዘዴ በመጠቀም ፕሮፌሰሩ የደረሰበትን እውነታ ለመቅበር አይቻልም። የፕሮፌሰሩ ሀሳብ በመላው ዓለም ታውቋል። ከእንግዲህም የሀሳቡን መስፋፋት ለመገደብ መሞከሩ አያዋጣም።

አፍሪካውያን የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር ስህዘዴን መማርና እውቀትን መፈልፈል ነው። የታሪክ፥ የፍልስፍና፥ የሶሺዮሎጂና የአንትሮፖሎጂ ባለሙያ ለመሆን ደግሞ ጠንክሮ መማር ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ በተለይ በኢትዮጵያ አውሮፓውያን እንደሚያደርጉት የ«ሊበራል አርትስ» እሳቤን መቀበል ተገቢ ይመስለኛል። ይህም ማለት የታሪክ፥ የቋንቋ፥ የፍልስፍናና የስነጽሑፍ ጠቅላላ እውቀት ማስተማር ይገባል ማለት ነው። ይህን ጠቅላላ እውቀት ከገበየን በኋላ በፈለግነው ሙያ ለመካን እንችላለን። ባለሙያ ለመሆን መማር፥ እውቀት መስብ ሰብና መመራመር ያስፈልጋል። የባህርይ ለውጥ ማምጣትም ያሻል።

ለኢትዮጵያ ታሪክ በቂ ስፍራ አልተሰጠም

ኢትዮጵያ ከጎብፅ፥ ከግሪኮች፥ ከሮማውያንና ከአረቦች ጋር የረጅም ዘመን ግንኙነት እንደነበራት የተረጋገጠ ነው። የክርስትናን፥ የአሪትንና የእስልምናን እምነት ተቀብለናል፥ አስተናግደናል። ለእነዚህም እምነቶች ከፍተኛ ቦታ ሰንሰጥ ለኢትዮጵያ ታሪክ ግን ስፍራ አልሰ ጠንም። ስለሆነም የአምላክን ነገር ለቤተ ክርስቲያንና ለመስጊድ ትተን የታሪክን ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት፥ ወደ ግለሰብ፥ ወደ ጎብረተሰብ እንውሰድ። ንጉሥ እገሌ ከእገሌ ተወለደ። ከእገሌ ጋር ተዋጋ፥ በጦር ሜዳ ሞተ የሚል ዜና መዋዕል የሚፈይደው ነገር የለም። የተወለደ ሁሉ ይሞታል። ይህ ምን አዲስ ነገር አለው? እኛ ማስተማር ያለብን ስለነበረው ሥርዓት፥ ተቋም፥ ላዕላይ መዋቅር፥ ታሕታይ መዋቅር፥ የአስተዳደር ድቺጅትና የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። ይህንን ግን ዛሬ ፈትፍቶ የሚያስተምር የለም። ምክንያቱ ለብለብ፥ ትምህርታችንም ለብ ለብ ስለሆነ ችግር አለብን። የሰከነ ሥራ ለመሥራት የጠበቀ እውቀት ያስፈልጋል። የታሪክ ትምህርትና እውቀት ያገርና የጎብረተሰብ ማንባታ መሰረትና መሳሪያ ነውና።

3. የኢትዮጵያ የጂኦፖለቲካ ታሪክ ግንዛቤ

የኢትዮጵያና የአረቦች ግንኙነት ታሪክ

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ዕድገትና ዓለማቀፋዊ ይዘት

የዓይነት፥ የቅርፅ፥ የመጠንና የዕድገት ደረጃ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ፥ በእንግሊዝኛ ዘእስቴት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች በዘልማድ መንግሥት ተብሎ የሚታወቀው ድርጅታዊ ሥርዓት፥ የአንድ በሥፍራና በጊዜ የተወሰነ ምድር፥ ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ሕጋዊ ቅንጅትና ታሪካዊ ትስስር ነው። ይህ በአንድ ቦተወሰነ የምድር፥ የሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ድርጅታዊ ቅንጅትና ትስስር የሚፈጠረው የመንግሥት ሥርዓት ከባህል መስፈርት አኳያ ሲታይ የሰለጠነም ያልሰለጠነም ሊሆን ይችላል። በሌላ ቃል የመንግሥት ሥርዓት ማዕከላዊ ባህርይና መገለጫ የፖለቲካ ሥልጣን ነው። በመሆኑም ሥልጣኔ ማለትም የተወሰነ የባህል ዓይነትና የዕድገት ደረጃ የመንግሥት ሥርዓት ዓይነተኛው ሚዛንና መገለጫ አይደለም ማለት ነው።

ከትርጉም ሆነ ከተግባር አኳያ ሥልጣኔ ግን የከተማና የገጠር ተግባራት ክፍፍልና ዕድገት፥ የእርሻና የንግድ ሥራዎች፥ የግል መሬት ይዞታ፥ የጽሕፈትና የገንዘብ አገልግሎት የመታወቂያ ገፅታዎችና መገለጫዎች የሆኑበት አንድ ባህላዊ የኅብረተሰብ ሥርዓት ወይም አንድ ማኅበራዊ የዕድገት ደረጃ ነው። በዚህ አጭር ትርጉም መሠረት መንግሥት የሥልጣኔ ቅድመ ሁኔታ ነው፤ ሥልጣኔ ግን የመንግሥት ቅድመ ሁኔታም ገላጭ ባህርይም አይደለም። ሕዝብ ያለ መንግሥት ሊኖር ይችላል። መንግሥት ግን ያለ ሕዝብ አይኖርም።

በዚህ መሠረት፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአክሱም የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብ አንድ በተወሰነ ሥፍራና ታሪካዊ ወቅት የአንድ የተወሰነ መሬት ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ሕጋዊ ቅንጅትና ድርጅት በመሆኑ አንድ ሉአላዊ መንግሥት ነው። እንዲሁም አንድ ባህላዊ የእርሻ፥ የከተማ፥ የንግድ፥ የዕደጥበብ፥ የግል ሀብት፥ የሕግ፥ የጽሕፈትና የገንዘብ ሥራዎች፥ ድርጅቶችና አገልግሎቶች ያሉት ማኅበረሰብ በመሆኑ አንድ ሥልጣኔ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የሚለው አባባል ትክክለኛ ግንዛቤና አባባል ነው።

የኢትዮጵያና የአረቦችን ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት፥ በመቀሌ ከተማ ጎዳር 27 እና 28 ቀን 1990 (1998) በተካሄደው «እስሐማ ነጃሺ ሲምፖዚየም» ላይ ከደራሲው በተሰጠው የጂኦ-ፖለቲካና የታሪክ

ሌክቸር እንደተገለጸው፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በአራቱ አኅጉራት አካባቢዎች የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አስትራቴጂያዊ አካባቢዎች በሥፍራና በጊዜ አድጎና ተስፋፍቶ በሁለቱ ጥንታዊና አኅጉራት የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በሥፍራ፥ በጊዜ፥ በንግድ፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በፖለቲካ፥ በሃይማኖትና በታሪክ የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት እንዴት እንደፈጠረ ብሎም ከ610-661 ባሉት አምሳ ዓመታት በተፃራሪ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ላይ ለአረቦቹ አስላማዊ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ዓለም አቀፋዊ ትግልና ድል በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የተደረገው ታሪካዊ የድል አስተዋፅኦ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የኢትዮጵያ የ550-1300 የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት 'ሠላሳ' ዘመን

በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ፥ ለሰባንት ምዕተ ዓመታት በቤተ መንግሥትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የተፃፈ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። በሌላ በኩል በዚህ ከፍለ ዘመን በኢትዮጵያ፦ (1) የአክሱም ሥልጣኔ ፈርሷል። (2) የክርስትና ሃይማኖት በቀይ ባሕርና በዓባይ ወንዝ መካከል በኃይል ተስፋፍቷል። (3) የአገው (ዘአገው) የክርስቲያን መንግሥትና የገዥ መደብ (1100-1270) ተጎስቶ ወድቋል። (4) በአክሱማውያኑ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በግምት በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል፥ «ሰሜን» እና «ወልቃይት» ተብለው በሚታወቁ ጥንታዊና አዋማዊ ሕዝቦች አገር፥ በአንድ በኩል ሃይማኖተ አሪትን የሚከተል ብሎም ራሱን «ሰለሞናዊ አይሁድ» ነኝ እያለ የሚጠራ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በአጎራባች ሕዝቦች «ፈላሻ» (መጤ፥ ባዕድ) ተብሎ የተሰየመ አንድ አዲስ አገርና መንግሥት ተከስቷል። (5) እንደ ሰሜን/ፈላሻም ራሱን «ሰለሞናዊ አይሁድ» ነኝ ብሎ የሚጠራ አዲሱ የአማራ መንግሥትና የገዥ መደብ ተከስቷል። (6) በተጨማሪም ከአገር ውጭ በአረቢያ የአክሱም መንግሥት የባሕር ማዶ ግዛትና ገበያ ተደምስሷል። (7) ከአጎራባቹ የአረቢያ ምድር አዲሱ ዓለማቀፋዊ የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት ተጎስቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቷል። (8) በደቡብ ኢትዮጵያ እስላማዊ ሃይማኖትና መንግሥት በኃይል ተስፋፍቷል።

በተጠቀሰው ረጅም የታሪክ መረጃ ባልተገኘበት ዘመን እነዚህና ሌሎችም ታላላቅ አገርና ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች፥ ኃይሎች፥ ክስተቶችና እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት

በሰነድ ተጽፈው አልተገኙም። ወይም ከጊዜ በኋላ ማለትም ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች በተረት መልክ ተቀርፀው ተገኝተዋል። በዚህ ረገድና ተግባር እንዲያውም ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344) በ1320 ገደማ በግዕዝ ትርጉም በክብረ ነገሥት መጽሐፍ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የገባው አዲሱ የታሪክ ትምህርት ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ ጨምሮ የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል በሙሉ ወደ ዝክረ ተረት ለውጠታል። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ራሳቸው «ሕዝብ» እና «አሕዛብ» ተብለው በሁለት ተግራሪ ሠፈሮችና ፊር ጆች ተከፍለዋል።

እጅግ በጣም የሚገርመው ነገር በዚህ «ኢትዮጵያውያን ዓለምን እረስተውና በዓለምም ተረስተው በረጅሙ ተኙ» ተብሎ በተገጠመለት ዘመን መጀመሪያ ላይ አጎራባች አረቦች፥ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ፥ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በራሳቸው ፈቃድ፥ ስንቅና ትጥቅ ከጎናቸው ተሰልፈው በነቢዩ ሙሐመድና በካሊፋዎቹ ማለትም በአቡበክር፥ በዑመር፥ በዑትማንና በዓሊ ተከታታይ አመራርና ዘመን ለአምሳ ዓመታት (610-661) ሊታሳቁ የእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ በተግራሪ ኃይሎች ላይ በተካሄደው ትግል ከፍተኛ ተሳትፎና የድል አስተውጽአ ያደረጉ ባለውለታ ሕዝብና መንግሥት ናቸው ብለው የምስክርነት ቃላቸውን ለዓለምና ለትውልድ በይፋ ሰጥተዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ አሁን ከጊዜና ከታሪክ አኳያ ከአንድ ወገን ብቻ የተሰጠው የአረቦች የምስክርነት ቃል ታሪካዊ መነሻና ፋይዳ በምን ተጨባጭ መንገድና ሚዛን ማወቅና መግለጽ ይቻላል? የሚለው መሠረታዊ የይዘትና የግንዛቤ ጥያቄ ነው። ለዚህ ተገቢና ወቅታዊ ጥያቄ አሳማኝ መልስ ለማግኘት ደግሞ የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦችን ጥንታዊ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ ማጥናትና ማወቅ እማራጭ የሌለው ቁልፍ ነገር ይሆናል።

በአጭርና በጥቅል አነጋገር የኢትዮጵያውያንና የአረቦች ረጅም ግንኙነት በዓባይ፥ በቀይ ባሕር፥ በአክሱም ሥልጣኔ፥ በጥንታዊ የሳባ የግዕዝና የአረብ ቋንቋዎች፥ በቅዱስ ቁርአን፥ በእስልምና ሃይማኖትና በጥንታዊ የአረብ ጸሓፊዎች ትምህርት መሠረቶችና መሣሪያዎች የተገ ነባ የሁለቱ አጎራባች ሕዝቦች ሕልውናዊ አንድነትና ትስስር እንደ ሆነ የሚከተለው ረጅም የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

የኢትዮጵያና የአረቦች የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ

ኢትዮጵያውያንና አረቦች፥ ከጥንት ከቅድመ ታሪክ ጀምሮ፥ ለብዙ ሺህ ዓመታት በቀይ ባሕር ጂኦ-ፖለቲካ ተሳስረው የሚኖሩ አጎራባች ሕዝቦች ናቸው። ጂኦ-ፖለቲካ በአንድ አገር፥ በአንድ አካባቢ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ እንደአካባቢውና እንደዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረታዊ የዕድገት አስተዋፅኦ ሊያደርግ ወይም አፍራሽ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል የጂኦግራፊ፥ የአስትራቴጂ፥ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች መግለጫና መስተጋብር ነው። በዚህ ረገድና ተግባር የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ጂኦ-ፖለቲካ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በአካባቢው ሕዝቦች ሕይወትና ዓለማቀፋዊ ሁኔታና ሂደት ላይ መሠረታዊ የልማት አስተዋጽያና የአፍራሽ ተጽዕኖ መፈራረቅ ሊያስከትል እንደኖረ ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።

ቡጉንት ዘመን፥ ቦምት ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 615 ዓመተ ምህረት ድረስ ለ3430 ዓመታት በቀይ ባሕርና በዓባይ ሸለቆ ጠረፎችና የንግድ መስመሮች ጥንታዊ ግብፃውያን፥ ሳባውያን፥ ግሪኮች፥ ሮማውያንና ኦረቦች በየዘመናቸው በንግድ፥ በሃይማኖትና በባህል ከለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ጋር ለረጅም ዘመን የነበራቸው ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነት ለኢትዮጵያ ጥንታዊ የቡንታው ያን፥ የደአማታውያንና የአክሱማውያን ሕዝቦችና መንግሥታት የዕድገት አስተዋፅኦ እንዳደረገ ከታሪክ መረጃና ጥናት ይታወቃል። በመሆኑም በ615-661 በአረብ ሙስሊሞችና በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች መካከል የተከሰተው ታሪካዊ ግንኙነት ራሱ በሁለቱ አጎራባች ሕዝቦች መካከል ለረጅም ዘመን የነበረው የጂኦ-ፖለቲካ ግንኙነት አንድ ማስረጃና ምሳሌ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት የኖረው የአይሁድ አስተማሪና ጸሐፊ ነቢዩ ሙሴ በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 10፣ ቁጥር 6-20 ላይ በታችኛው ዓባይ ሸለቆ፥ በላይኛው ዓባይ ሸለቆ፥ በሰ ሜን ምስራቅ አፍሪካና በአረቢያ ሞዝሩ ሕዝቦችን በቅደም ተከተል ግብፅ፥ ኩሽ፥ ፑንትና ሳባ በተሰኙ ስሞች ገልጿል። ዛሬ በዘመናችን ግለትም ከ1800 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ከዘርሰ ምድር በአርኪኦሎጂ ጥናት የተገኙ ጥንታዊ የግብፅ የሃይሮግላ ፊክስ ጽሑፎች የእነዚህ ሕዝቦችን ታሪክ በሚመለከት ብዙ ተጨማሪ መረጃዎችን ሰጥተዋል።

ከዚህ አኳያ፥ በጥንታዊ ግብፅና ፑንት መካከል በንግድ፥ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና መንገዶች ከ2800 እስከ 1000 ዓመተ ዓለም ድረስ ለ1800 ዓመታት የቆየ የንግድ ግንኙነት እንደነበር

ከተጠቀሱት የሃይሮግላፊክስ መረጃዎች በትክክል ታውቋል።

በግምት ከ1000 ዓመተ ዓለም ገደማ ጀምሮ የተጠቀሰው የግብፅና የቱንት ጥንታዊ የዕጣን፥ የከርቤ፥ የሙጫና የቀረፋ ቅመማ ቅመም ንግድ በትክክል ባልታወቁ ምክንያቶች ከተቋረጠ በኋላ በ1000-500 ዓመተ ዓለም ባለው ዘመን ውስጥ በአንድ በኩል በሰሜን መህል ደጋ በሚገኘውና «የሀ» ተብሎ በሚጠራው አገር የኢትዮጵያ አዲሱ የደአማት ዘውዳዊ መንግሥት፥ በሌላ በኩል ደግሞ በአጎራባቹ ደቡብ አረቢያ እንዲሁም በዕጣን፥ በሙጫ፥ በከርቤና በቀረፋ ምርትና ንግድ የተሰማሩ ሚና፥ ሳባ፥ ቀጣጠንና ሃድራማዊ የተባሉ የአረብ አናሳ መንግሥታት ተከስተዋል።

በኢትዮጵያውያንና በተጠቀሱት አረቦች መካከል የመጀመሪያው ታሪካዊ ግንኙነት በደአማትና በሳባ ሉአላዊ መንግሥታት መካከል በዓመተ ዓለም በ4ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ለአጭር ዘመን ተጀምሮ እንደነበር የሚያሳዩ ሰነዳዊ መረጃዎች ተገኝተዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በአንድ በኩል በኋላ ለአክሱማውያኑ የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት መነሻ በሆነው የደአማት ጥንታዊ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጎን የሳባ ሐውልታዊ የቁም ጽሕፈት ተገኝቶ ባልታወቀ ምክንያትና መንገድ በአንድ ምዕተ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጠፍቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከደአማት ነገሥታት አንዱ ማለትም «ድል አድራጊው ንጉሥ ለመነ» በዜና መዋዕሉ ራሱን «የደአማታውያንን፥ የሳባውያንን፥ የአበራውያንን፥ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ»፥ አገሩን ደግሞ «ከምስራቅ እስከ ምዕራብ» በማለት እንዲሁም «አስቴር፥ ሀበስ፥ አለመቀህ፥ ደተህመ፥ ደተብአደአነ» የተሰኙ አዋማዊ አማልክቱን ዘርዝሮ በማሳወቅ በዘመኑ የነበረ የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥትን የሕዝቦች፥ የቋንቋዎች፥ የባህሎችና፥ የሃይማኖቶች ብዛትና አንድነት ባጭርና በጥልቅ አስረድቷል።

በኢትዮጵያ የደአማት መንግሥትና ሥልጣኔ፥ እንዲሁም በደቡብ አረቢያ በዕጣን፥ በሙጫ፥ በከርቤና በቀረፋ ምርትና ንግድ የተሰማሩ የአረብ አናሳ መንግሥታት በየአገራቸው በዕድገት እንቅስቃሴ ላይ እንዳሉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በዓመተ ዓለም ከ6ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በላይኛው የዓባይ ሸለቆ፥ በጥንቱ የኩሽ/ኑቢያ አገር አዲሱ የሚሮዌ መንግሥት ተከስቶ። ከ525-405 ዓመተ ዓለም በታች ኛው የዓባይ ሸለቆ ግብፅ የፋርሳውያን ግዛት ሆነ። ቀጥሎም በ332-30 ዓመተ ዓለም ግብፅ የግሪኮች ግዛት ሆነ። በመጨረሻ ከ30 ዓመተ

ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት የሮማውያን ግዛት ሆነ።

ባጭርና በጥቅል አነጋገር በግብፅ የግሪኮ-ሮማውያን ተከታታይ ግዛቶች በአንድ በኩል በላይኛው ዓባይ ሸለቆ በሚሮዌ ላይ እንዲሁም በደቡብ አረቢያ በአረብ መንግሥታት ላይ የውድቀት ተፅእኖ አስከ ተሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለኢትዮጵያ ተከታታይ የደአማት-አክሱም መንግሥታት የዕድገትና የመስፋፋት አስተዋፅኦ እንዳደረጉ የታሪክ መረጃና ጥናት ያሳያል።

ከዚህ አኳያ፥ በ332 ዓመተ ዓለም በታላቁ እስክንድር መሪነት የግሪክ ጦር ግብፅን ከፋርሶች ከያዘና በታላቁ እስክንድር ስም የእስክንድርያ መዲና ከተቆረቆረች በኋላ በሚቀጥሉት 300 ዓመታት ውስጥ በግብፅ ምድር ላይ ቶለማውያን የተባሉ የግሪክ ነገሥታት ተነሱ። በግብፅ ቶለማውያን ነገሥታት በዘመኑ በዕጣን ምርትና ንግድ በዓለም ታዋቂ የነበረውን ደቡብ አረቢያን ከጎን በመተው ለንግድና ለአደን ተግባራት ትኩረታቸውን በአፍሪካ ምድር በቀይ ባሕርና በኤደን ባሕረሰላጤ ጠረፎች ላይ አደረጉ።

በዚሁ ሁኔታና ወቅት፥ በቀይ ባሕር ዳርቻ፥ የኢትዮጵያ የአዱሊስ ወደብ በሜድትራኒያን ባሕርና በሕንድ መካከል የተስፋፋው ዓለማቀፋዊ የግሪክ ንግድ፥ ቋንቋ፥ ባህልና ሥልጣኔ ኬላ፥ ማዕከልና መናኸሪያ ሆኖ አደገ። ማለትም የአዱሊስ ወደብ ለአክሱም መንግሥት እና ሥልጣኔ የመካከለኛው ምስራቅና የሜዲትራኒያን ሥልጣኔዎች የመግቢያ በርና መንገድ ሆነ።

በመጨረሻ በ30 ዓመተ ዓለም ማለትም በዘመነ-ክርስትና መባቻ ሮማውያን ግብፅን ከግሪኮች ያዙ። በዚህ በግሪኮ-ሮማውያን ዓለማቀፋዊ ሽግግር ዘመን በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ጥንታዊው የኑቢያ-ሚሮዌ መንግሥትና ሥልጣኔ እንዲሁም በአጎራባቹ አረቢያ የሚና፥ የሳባ፥ የቀጣጠን፥ የሃድራማዊ፥ የሚሚያሪትና የሃምዳና አረብ መንግሥታት በየበኩላቸው በራሳቸው ውስጣዊና አካባቢያዊ ምክንያቶችና ግፊቶች ሁሉም ባፋጣኝ የውድቀት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ነበሩ።

በዘመነ አስልምና ዋዜማ በአካባቢው የዓለም ኃያላን መንግሥታት አሰላለፍ

ከላይ የተዘረዘሩት የዘመኑ ታላላቅ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ክስተቶች፥ ሁኔታዎችና ሂደቶች የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕር፥ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ አስትራቴጂያዊ አገሮችን ለሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን አዜ መንግሥታት ቅርብና ነፍጉት የገቢያ የግዛትና የተፅእኖ አካባቢዎችና መስኮች አደረጉዋቸው።

የኢትዮጵያ ነገሥታትና ወታደሮች በአረቢያ

በግምት ከ175 እስከ 225 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በአረቢያ እርስ በርሳቸው የማትና የሥልጣን ጠላት በሆኑ የሃምዳና፥ የሳባ፥ የሂሚያሪት፥ የቀጣባንና የሃድራማዊ አረብ መንግሥታትና የጦር አበጋዞች መካከል በተካሄደው ረጅም ጦርነት አገሮቹ በኅሳና በሥልጣን አንጃዎች ተለያይተው ሲዋጉ «የሀበሾችና የአክሱማውያን ነገሥታት» ከሚሉዋቸው ገደረት፥ ዋዜባና አድባ አንድ ጊዜ የፖለቲካና የመሣሪያ እርዳታ ሲፈልጉ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጊዜያዊ የአረብ ጎብረት ፈጥረው ከኢትዮጵያ ጋር ሲዋጉ ይታያሉ።

በመጨረሻም በ220ዎቹ የሂሚያሪታውያኑ አናሳ መንግሥት የተቀሩ ባላንጣ መንግሥታትን በውልም በውጊያም ተቆጣጥሮ ከዛፋሩ መዲናው በኢትዮጵያውያኑ የማት ተፅዕኖ ሥር አንድ ጠንካራ የሂሚያሪት-ሳባ ጥምር የአረብ ኃይል መሠረተ።

በሌላ በኩል «የሀበሾችና የአክሱማውያን» መንግሥት በአረቢያ የቀይ ባሕርን ምሥራቃዊ የጠረፍ ክልል በለሜን ምዕራብ ከሂጃዝ፥ ከአሲርና ከቲሃማት ክልል ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ ኤደን ወደብ ድረስ ማለትም የሂጃዝ-የመን ጠረፎችን በሙሉ በመቆጣጠር በምድርም በባሕርም ላይ ለሚቀጥሉት ምዕተ ዓመታት የደቡብ አረቢያ የበላይ ኃይልና ሥርዓት ሆነ።

በተጠቀሰው ዘመን የአክሱሙ የአጼ መንግሥት የአራቱ የለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አኅራባች ሕዝቦችና አገሮች የበላይ ኃይል ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ታሪክ ላይ የታወቀው በታላቁ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ነው። የዚህ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ የጸሐፊው ስም ሆነ ጽሑፉ የተጻፈበት ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል አልተረጋገጠም።

ይሁን እንጂ ጽሑፉ የተጻፈበት ዘመን በሁለተኛው ምዕተ ዓመት «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» አረቢያን ከገዛበት ጊዜ በኋላና በ4ኛው ምዕተ ዓመት በ330 ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን በፊት እንደሚሆን በኢትዮጵያ የዘመኑ ታሪክ ታዋቂ ምሁራን ይገመታሉ።

የዚህ የአዱሊስ ጽሑፍ ግኝትና ቅጅ አስመልክቶ የግሪክ-ግብፅ ጸሐፊ ኮስማስ ከ525 የአዱሊስና የአክሱም ከተሞች ጉብኝቱ መልስ እንደጻፈው፥ በተጠቀሰው ዓመት አጼ ካሌብ የጽሑፉን ቅጅ አስገልብጠ እንዲልክለት አባስ ለተባለ የአዱሊስ ገዥ ትእዛዝ ይሰጣል። በታሪክ አጋጣሚ በዚህ ጊዜ ጸሐፊው ኮስማስ ሚናስ ከተሰኘ ጓደኛው ጋር በንግድ ሥራ ምክንያት በአዱሊስ ከተማ ነበር። በመሆኑም አገረ

ገዢው አባስ ግሪክ-ግብፅ ጸሐፊዎቹን ከሐውልቱ ጽሑፍ ለአጼ ካሌብ የሚልከውን ቅጅ እንዲያዘጋጁለት ጠየቃቸው። ጸሐፊዎቹም የጽሑፉን ለስት ቅጂዎች አዘጋጅተው አንዱን ለአገረገዢው ሰጡ። የተቀሩትን ለራሳቸው አንዳንድ ወሰዱ። ኮስማስ የራሱን ቅጅ *የክርስቲያን ቶፖግራፊ* በተሰኘ መጽሐፉ ገልብጦ ለትውልድና ለታሪክ መረጃ አስተላለፈ። ነገር ግን ኮስማስ የጽሑፉን ደራሲ ስም ሆነ የተጻፈበትን ዘመን ባለመጻፉ መቼና በማን ተጻፈ የሚለው ቁልፍ የታሪክና የጊዜ ጥያቄ እስከ ዛሬ ድረስ አልተመለሰም።

ባጭሩ የታላቁ የአዱሊስ ጽሑፍ ርዕሰ ነገሮች በጽሑፉ ገፅ ሆነ ያዛት በማይታወቅ ዘመን በአንድ በስሙ በማይታወቅ የአክሱም ንጉሥ በአራቱ የለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አካባቢዎች በ30 በሚቆጠሩ አገሮች ላይ በምድርና በመርከብ ያካሄዳቸው ጦርነቶች ናቸው። ከዚህ አኳያ፥ በመጀመሪያ ዘመቻ በለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋአምባ ክልል በግምት በመረብ ወንዝና በጣና ሐይቅ መካከል በሚገኘው ምድር ንጉሡ ግዕዝ፥ አጋሜ፥ ስሜ፥ አድዋ፥ ቲአሞ፥ ጋምቤላ፥ ዘንጋበኔ፥ አንገበ፥ ትአማ፥ አገው (አታገው)፥ ከለና ሰሜን የሚላቸውን አሥራ ሁለት አዋማዊ አገሮችንና መንግሥታትን አስገበራቸው።

በሁለተኛው ዘመቻ በግምት በቀይ ባሕር፥ በአትበራ ወንዝ፥ በኑቢያ-ሚሮዌና በግብፅ መካከል ለዘንፉ፥ ዘአ፥ ዝለ፥ አታለሞ፥ ቤጃና ተንገናይቴ (ታካ) የሚላቸውን ስድስት የተለያዩ የቤጃ አገሮችንና ማኅበረሰቦችን በማስገበር የመንግሥቱን የለሜን ምዕራብ ወሰን በላይኛው የዓባይ ሸለቆ እስከ የሚሮዌና የግብፅ ጠረፎች ድረስ አስፋፋ።

በሦስተኛው ዘመቻ ጠረኛው ንጉሥ በክፍለ አህጉሩ ከትግራይ ደጋአምባ በደቡብ ምስራቅ በግምት ከአዋሽ ሸለቆ እስከ ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ድረስ ባለው ቆላማና በጥንቱ ዓለም በዕጣን ምርትና ንግድ በታወቀ የትሮጅሎዳውያንና የበርበራውያን ምድር አነን፥ ምጣን፥ ሰለአ፥ ሮሳይና ሶላቴ የተሰኙ አምስት የቆላ ሕዝቦችንና አገሮችን አስገበራቸው።

በአራተኛውና በመጨረሻው ዘመቻ የንጉሡ ጦር በእግርና በመርከብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ወደአረቢያ ረጅም ምዕራባዊ ጠረፍ ዳርቻ ላይ በለሜን ምዕራብ ክልል በሚገኘው በሂጃዝ-አሲር አገር በዘመኑ የሮማውያን ይዞታ ከነበረ ከለኡከመ ወደብ ጀምሮ በመሀል፥ በምስራቅና በደቡብ አረቢያ እስከ ሳባ-ሂሚያሪት ጠረፎች እስከ ባቤልመንደብ ለርጥ አካባቢ ድረስ ሙሉ ዘመቻ በማካሄድ በዘመኑ በሂጃዝ-አሲር ጠረፍ ኪናይዶኮልፕቴና በሂሚያሪት ጠረፍ አራቡቱ

የተለዩ ሁለት አስተራቴጂያዊ አገሮችን የመንግሥቱ የባሕር ማዶ ግዛቶች አድርጎ በቀጥታ ያዘ። በዚህ ረገድና ተግባር ከዚህ በፊት «በህበሾችና በአክሱማውያን ነገሥታት» ገደረት፥ ዋዜባና አድባ ዘመን በደቡብ አረቢያ በየመን ጠረፍ ህበሻ የተባለ የኢትዮጵያውያን ግዛት እንደነበር አይዘነጋም።

የአዱሊሱን ታሪካዊ ጽሑፍ ከጻፈው ንጉሥ ቀጥሎ በለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አጎራባች አካባቢዎች የኢትዮጵያ መንግሥትን በቅደም ተከተል በ4ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመታት በኢኮኖሚ፥ በድርጅት፥ በባህል፥ ብሄያይማኖት፥ በዲፕሎማሲና በትጥቅ ከጥንቱ ኩሻዊ የግብፅና የኑቢያ መንግሥታት በኋላ የአፍሪካ ታላቁ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት አድርገው የገነቡት ሁለት አጼ ነገሥታት ኢዛና (320-344) እና ካሌብ (493-534) ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር የኢትዮጵያ የመጨረሻው አዋማዊና የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሥ የሆነው አጼ ኢዛና በኢትዮጵያና በአረቢያ በግሪክ፥ በግዕዝና በሳባ ጥንታዊ ቋንቋዎች በተጻፉ ዜና መዋዕሎች (1) «ሰዎቼ» እያለ የሚጠራቸው መሀራ፥ ሀራ፥ ደመወ፥ ፊልሀ፥ ፅራእ፥ ህሌን፥ ምጤን፥ ጳኬን፥ ለኬንና ሰብራት የተባሉ የጦር ድርጅቶች፥ (2) «አባቶቼ» የሚላቸው አርስ፥ መሕርም፥ አስ ተር፥ ብሔር፥ ምድር፥ የሶማይ አምላክ፥ ክርስቶስ፥ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ተብለው በልዩ ልዩ ስሞችና ቋንቋዎች የሚታወቁ የውጭና የአገር ውስጥ አማልክት እንደነበሩት፥ (3) እንዲሁም «ግዕዝ»፥ «ካዕብ»፥ «ሳልስ»፥ «ራብዕ»፥ «ሐምስ»፥ «ሳድስ»፥ና «ሳብዕ»፥ የተሰኙ የኢትዮጵያ የቋንቋ ድምፅ ንግግርና ንባብ ሥዕላዊ ምልክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመነ መንግሥቱ እንደተገኙ የሰንዶች ጥናት ያሳያል።

በተጨማሪም በተጠቀሱት የድንጋይ ላይ ጽሑፎች «የእክሱም፥ የሂሚያር፥ የረይዳን፥ የኢትዮጵያ፥ የህበሻ፥ የሰልሄን፥ የፅያሞ፥ የቤጃ፥ የካሱ፥ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ» የሚለው የአጼ ኢዛና የአገርና የመንግሥት ስም ንጉሡ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በ330ዎቹ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የአራቱ አጎራባች የለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አገሮች ሉአላዊ የበላይ ኃይልና ሥርዓት እንደሆነ ያመለክታል።

ከእነዚህ ከኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ግዛቶች ሂሚያር፥ ረይዳን፥ ህበሻ፥ ሳባና ሰልሄን የመንግሥቱ አምስት የአረቢያ ግዛቶች፥ እንዲሁም ፅያሞ፥ ቤጃና ካሱ የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ

ግዛቶች፥ አክሱምና ኢትዮጵያ ደግሞ በለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በለሜኑ ደጋአምባ ላይ የአጼው መንግሥት የማዕከላዊው ከተማና አገር ስሞች ናቸው።

ከአጼ ኢዛና ዘመን 200 ዓመታት በኋላ በ530ዎቹ «የአክሱም፥ የካሱ፥ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሄን፥ የትአሞ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የራባም፥ የቤጃ፥ የኖባ፥ የአራባት፥ ንጉሥ» የሚለው የአጼ ካሌብ የአገርና የመንግሥት ስም በሁለቱም የአፍሪካና የእስያ አጎራባች አህጉራት የኢትዮጵያ መንግሥት ከአጼ ኢዛና ዘመን የበለጠ እንደተስፋፋ በግልጽ ያሳያል።

በአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ከተጠቀሱ ግዛቶች ረይዳን፥ ሳባ፥ ሰልሄን፥ የመን፥ ቲሃማት፥ ራባምና አራባት ለባት የኢትዮጵያ መንግሥት የአረብ ግዛቶች ናቸው። በዘመኑ ቲሃማት በለሜን ምዕራብ ጠረፍ ከሂጃዝ በደቡብ ምስራቅ ጠረፍ እስከ የመንና ከዚያም ባሻገር ያለው ረጅም የደቡብ አረቢያ ምዕራባዊ ጠረፍ አጠቃላይ ሲያሚ ነው። ካሱ፥ ትአሞ፥ ቤጃና ኖባ ደግሞ፥ ከሥስቱ ተከታታይ የአዱሊስ ሐውልት፥ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንደሚታወቀው፥ በቤጃና በሚሮዌ ሕዝቦችና አገሮች ላይ እየሰፉ የመጡ የኢትዮጵያ መንግሥት የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ግዛቶች ናቸው።

የአይሁዶች ጠርነትና የኢትዮጵያ ግዛት በየመን አረቢያ

የኢትዮጵያን ጥንታዊ የታሪክ መረጃ ዓይነትና ብዛት በሚመለከት፥ በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ ባለው በ1000 ዓመታት ዘመን ውስጥ በአራቱ ጥንታዊ የደለማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ የተጻፉና በ500 የሚቆጠሩ ጥንታዊ ጽሑፎች ከ1804 እስከ 1981 ድረስ በሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ በድምሩ ከ50 በሚበልጡ የተለያዩ ታሪካዊ ሥፍራዎች በ30 በሚቆጠሩ ምሁራን እና ተመራማሪዎች ተገኝተው ለጥናትና ምርምር አገልግሎት መዋላቸውን በ1982 በኢትዮጵያ ባህል ሚኒስቴር የጥንታዊ ጽሑፎች ተመራማሪ ምሁር ፕሮፌሰር ሮዜ ሽናይደር ለዚህ ጸሐፊ በለጡት ማስታወሻ አስታውቀዋል።

በእነዚህ ቁልፍና ወሳኝ የታሪክ መረጃዎች መሠረት፥ በ330 ዓመተ ምህረት በሁለት የሶሪያ ስደተኞች ፍሬምናጦስና አዲስዮስ እማኝነት የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ አዋማዊ ቤተ መንግሥት ከመግባቱ በፊት በአገሪቱ ምድርና ታሪክ የይሁዳውያኑ የአሪት ሃይማኖት አልተገኘንም። ቀጥሎም በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ

(470-550) ዘጠኙ ግሪኮ-ሮማውያን ስደተኛ ቅዱሳን አረጋዊ፥ ጰንጠሌዎን፥ ገሪማ፥ ሊቃኖስ፥ ይምአታ፥ ፅሕማ፥ ጉባ፥ አፍጼና አሌፍ በአክሱም ከተማ በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተረጎሙ። በሌላ በኩል ደግሞ የጎዳም ተቋምና ሥርዓት መሠረቱ። የጸድቃኑ የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስና ሥጎ ጽሑፍ ከገዳም ሥርዓት ጋር በኢትዮጵያ ለሁለቱም የክርስትናና የአሪት ሥርዓቶች የመነሻ መሠረት ይሆኗሉ። ከሰባት አሥርታት በኋላ በ615 የአረብ ስደተኞች ደግሞ እስልምናውን ማለትም ሦስተኛውን መለኮታዊ ሃይማኖት ወደ አክሱም ያስገባሉ።

ከዚያ በፊት አክሱማውያንና ሮማውያን ክርስትናን በየበኩላቸው በየመን አረቢያ በማስተማር አስፋፉት። ይሁን እንጂ በ517 በየመን አረቢያ የነበሩት ተግራሪ የአይሁድ ኃይሎች በማዝሩቅ ዙ ኑዋስ መሪነት በኢትዮጵያ፥ በአረብ፥ በሮማዊያንና በሌላም አገር ክርስትያኖች ላይ የማጥፋት ጦርነት ከፈቱ። በመሆኑም በ517 እና በ525 የአክሱሙ ንጉሥ አጼ ካሌብ በሁለት ተከታታይ ዘመቻዎች የአይሁዶችን አመጽ ደምስሶ በየመን የአክሱም መንግሥትን የባሕር ማዶ አስተዳደር (525-577) መሠረተ።

በ517-525 የአይሁዶች ጦርነት ጊዜ ከአረቢያ ብዙ ሕዝቦች ሱማፋ አሸዋን የተባለ አዋማዊ የሚሚያር መስፍን ጨምሮ በስደት ወደ አክሱም እንደሄዱ ታውቋል። በ525 አጼ ካሌብ የአይሁዶችን አመጽ ከደመሰሰ በኋላ ሱማፋ አሸዋንን የክርስትና ልጁና በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ንጉሥ እንደራሴ (525-535) አድርጎ አነገ ሠው። በተጨማሪም ከንጉሥ ሱማፋ አሸዋን ጎን የአገሩን ጸጥታና ሃሎት እንዲጠብቅ በአንድ የጦር አበጋዞች ጉባኤና ትእዛዝ የሚመራ የጦር ሠራዊት በየመን አሰፈረ።

በ535 በየመን አንድ አብረሃ የተባለ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት አዛዥ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋንን በኩዴታ ገልብጦ ራሱን «የሳባ፥ የዲሁ ረይዳን፥ የሃድራማዊ፥ የየመንና የቲሃማት፥ የደጋና ቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅና አዝማች» በማለት በ535-558 አነገሠ።

የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ የደቡብ አረቢያ መዲናን ከጥንቱ የሚሚያር-ሳባውያኑ የዛፋር ከተማ በስተሰሜን ከማሪብ የውሃ ግድብ ከተማ አጠገብ አዲሱን የሰንዓ ከተማ አሠርቶ ወደዚያ አዛወረ። በተጨማሪም የሰንዓ ካቴድራል ጨምሮ በየመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠራ። እንዲሁም የማሪብን ጥንታዊ የውሃ ግድብ በከፍተኛ ወጪ አድሶ ገሰ። የሰሜንና የምዕራብ አረቢያ አካባቢዎችንና ነገዶችን ከየመን አረቢያ ጋር አዋህዶ አንድ ጠንካራ

የአረብ አገርና መንግሥት ለመገንባት በፋርስና በባይዘንታይም ተግራሪ ኃይሎች ላይ ብዙ ያልተሳኩ ወታደ ራዊና ፖለቲካዊ ትግሎችን እንዳካሄደ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ፥ በ558 ንጉሥ አብርሃ ሞተ። በመሆኑም ከ558 እስከ 577 ድረስ በየመን አረቢያ በንጉሡ ልጆችና በተከታዮቹ መካከል ረጅም የሥልጣንና የእርስ በርስ ጦርነት ተካሄደ። በመጨረሻ በ577 የአረብ አማፅያን ከፋርሳውያን ባላንጣ ኃይሎች ወታደራዊና የፖለቲካ እርዳታ አግኝተው የኢትዮጵያ ሰፋሪ ኃይሎችን ከየመን አረቢያ አባረሩ። ነገር ግን ፋርሳውያን የኢትዮጵያ ጥንኛ የነበረውን የሚሚያር-ሳባውያኑን የአረብ መንግሥት ደምስሰው የመን አረቢያን በጦር በመያዝ በቀጥታ መግዛት ጀመሩ።

የኢትዮጵያውያኑ የ577-610 የሂጃዝ አረቢያ ሰፈራና የእስልምና ክስተት በመካ

በ577 የኢትዮጵያውያኑ የየመን አረቢያ ግዛት ውድቀት በሚ ቀጥሉት ሦስት አሥርታት ውስጥ በአንድ በኩል በየመን አረቢያ ላይ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ሕይወት ፈጣን ውድቀትን በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በቲሃማት ጠረፍ ክልልና በመካ የመሀል ሀገር ከተማ ፈጣን ልማትና ዕድገትን አስከተለ።

በዚህ ወቅት ከየመን አረቢያ የተፈናቀሉ ብዙ የኢትዮጵያ ሰፋሪ ነጋዴዎች፥ ወታደሮች፥ የዕደጥበባት ባለሙያዎች፥ ሠራተኞች እና ባሮች በሰሜን ምዕራብ አረቢያ የጠረፍና የመሀል ሀገር ከተሞች በተለይም በመካው የንግድና የ360 ጣኦታት ከተማ በብዛት እንደሰፈሩ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል። በዚህ ረገድና ተግባር የመካን የንግድና የሃይማኖት ከተማ ክፍለ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እንደገነቡ ከሚነገርላቸው ከአቢዩ ሙሐመድ አብደላህ (470-632) አራቱ እውቅ ጎሳዎች የአብድሸምስ ልጆችና ተወላጆች በምዕራብ አቅጣጫ ቀይ ባሕርን ተሻግረው ከኢትዮጵያ ጋር፥ የአል-ሙጠሊብ ልጆችና ተወላጆች በደቡብ አቅጣጫ ከየመን ጋር፥ የሀሺም ልጆችና ተወላጆች በሰሜን የባይዘንታይም ግዛት ከነበረው ሶሪያ ጋር፥ የነውፈል ልጆችና ተወላጆች በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ከኢራቅ-ፋርስ ጋር ድንበር ዘለል ንግድ ያካሄዱ እንደነበር ታውቋል።

በእነዚህ አገር አቋራጭ የሲራራ ንግድ መስመሮችና ገበያዎች የተሰማሩ የመካ ቁረይሽ አረብ ከበርቴዎችና ባለሥልጣኖች በ610ዎቹ ሦስቱ ኃያላን የባይዘንታይም፥ የፋርስና የአክሱም ተግራሪ መንግሥታት በየፊናቸው በሚቆጣጠሩት በአረቡ በርሃማ አገርና ዓለም አዲስ

የፖለቲካ ኃይልና የገዥው መደብ ሆነው ተከሰቱ። በ610ዎቹ ነቢዩ ሙሐመድ በዚህ አዲስ የአረብ የፖለቲካ ኃይል ላይ ታሳቁን እስላማዊ አመፅ አወጁ።

የ615-631 የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በኢትዮጵያ

በ615-616 የመካ ቁረይሽ ከበርቴዎችና ባለሥልጣኖች በነቢዩ ሙሐመድና በተከታዮቹ ላይ የቅጣት እርምጃ በወሰዱ ጊዜ ነቢዩ ተከታዮቹን በስደት ወደ አጎራባቹ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዛቸው። በመሆኑም ከ615 እስከ 661 ድረስ በአምስት አሥርታት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥትና ዜጎች በራሳቸው ስንቅና ትጥቅ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተግራሪ ኃይሎች ላይ በነቢዩ ሙሐመድና በካሊፋዎቹ አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ ጎን ተሰልፈው የአረቦቹን እስላማዊ የዓለም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ከጥፋት ለማዳን በተካሄደው ትግል ብርቱ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ እንዳደረጉ የታሪኩ ባለቤት የሆኑ የአረብ መሪዎች፥ ተከታዮችና ፀሐፊዎች ለዓለምና ለትውልድ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው አልፈዋል።

በኢትዮጵያ የ615-631 የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞችን የዘር ጥንቅር፥ ቁጥር፥ ሕይወትና ሥራ በሚመለከት፥ በመጋቢት 1904 በአዲስ አበባ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የቱርክን የመጀመሪያ ልዑካን ቡድን መርቶ የመጣው ሌ/ጄ ሳድቅ አልሙሊያድ አልአዝም በዓመቱ Habash Siyahetnameshi በሚል ርዕስ በቱርክኛ ቋንቋ ጽፎ በ1908 Rihlate al Habasha (The Ethiopian Voyage) ጉዞ በሚል ስም ወደ አረብኛ ቋንቋ በተተረጎመው ተወዳጅ መጽሐፍ የጥንት አረብ ሙስሊም ጸሐፊዎችን ሰነዶችበስፋትና በጥልቀት መርምሮ ብዙ አዲስና ጠቃሚ መረጃዎችን በማቅረብ በ615-661 የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከነቢዩና ከተከታይ ካሊፋዎቹ ጎን ተሰልፈው ለአረቦቹ እስላማዊ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ድልና ዕድገት ያደረጉትን ታሪካዊ አስተዋጽኦ በዝርዝር አስቀምጧል።

የቱርኩ ጄኔራል በአዲስ አበባ ቆይታው ወቅት ከሁሉ በላይ የአገራቸውን ታሪክ በወግ ለማያውቁ ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የአገራቸው የጥንቱ ክርስቲያን መንግሥትና ሕዝብ ነቢዩ ሙሐመድን በእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ተግባር እንዴት በልዩ ልዩ ሥራዎች፥ መንገዶችና መሣሪያዎች እንደረዱ ለመጀመሪያ ጊዜ በማሳወቅ በእጅጉ አስደነቃቸው።

ሁለተኛ የጄኔራል አልአዝም ጥናት በ615-631 በኢትዮጵያ ከነበሩና በድምሩ በ150 ከሚቆጠሩ ሙስሊም ስደተኞች ከበረካ ኡም አይማን የነቢዩ ኢትዮጵያዊት አሳዳጊ ሞግዚት ጋር አምስት ሴቶችን

ጨምሮ ሀያ አንድ በዘርና በትውልድ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ያሳያል። በተጨማሪም የተጠቀሱ ኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በኢትዮጵያ በቆዩበት ረጅም ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ወደ እስልምና ሃይማኖት እንደአስገቡ የጄኔራሉ ጥናት ጨምሮ ያመለክታል።

ሦስተኛ፥ በዚህ ረገድና ተግባር በ631 በነቢዩ ሙሐመድ ቤተ ዘመድ በጃዕፈር ሙጠሊብ መሪነት ስደተኞቹ ወደ አረቢያ በተመለሱ ጊዜ ከተጠቀሱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ነቢዩን በትጥቅ ለመርዳት 72 ወደዘማቾች በንጉሥ አስሓማ ወንድም ልጅ በዙ ማህጃር አልሀበሻ፥ በአረቢያ የቀድሞው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አብርሃ (535-558) የልጅ ልጅ አብርሃ ቢን ሰባህ አልሀበሻና በአንድ ዕውቅ የታሪክና የቅኔ ባለሙያ በዙ ማህጀር አልሀበሻ ጥምር አዝማችነት ከስደት ተመላሾቹ ጋር አብረው እንደሄዱ ተገልጿል።


ከእነዚህ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥትና የጦር ሹማምን ቶች አንዱ ዙ ማህጃም አልሀበሽ ለነቢዩ ሙሐመድ የኢትዮጵያና የአረብ ጥንታዊ የግንኙነት ታሪክን ያስተምር ነበር ተብሏል።

ኢትዮጵያና አሰልምና

ከታሪክ መረጃና ትምህርት አኳያ ሲደመደም፥ በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ የታሪክ ሰነዳዊ መረጃ ባልተገኘበት ዘመን ውስጥ ከአገር ውጭ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች የኢትዮጵያ የታሪክ መረጃ ብቸኛ ምንጭ እንደሆኑ ታውቋል። በዚህ ረገድና ተግባር በተጠቀሰው ዘመን በግምት ከ615 እስከ 661 ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥትና ዜጎች በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ከነቢዩ ሙሐመድና ከአራቱ ተከታይ ካሊፋዎች አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ ጎን ተሰልፈው በውስጥና በውጭ ተግራሪ ኃይሎች ላይ ለታላቁ የእስልምና ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ዕድገትና ዓለማቀፋዊ መስፋፋት የድል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ፥ ብሎም ነቢዩ ለሙስሊም ተከታዮቹ ከኢትዮጵያውያን ጋር በእስላማዊ ጉርብትና አብረውና ተከባብረው እንዲኖሩ ቋሚ የእምነት፥ የትምህርትና የፖሊሲ መመሪያ እንደሰጣቸው የዘመኑ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ለትውልድና ለዓለም የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል። ይህ አስገራሚ ታሪክ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ አምስትና ስድስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ በኢትዮጵያና በአረብ ሕዝቦች መካከል የነበረው መልካም የጂኦ-ፖለቲካ ግንኙነት ዓይነተኛ መገለጫ እንደሆነ በዚህ ጥናት በቀረበው የታሪክ መረጃና ትምህርት

ተረጋግጧል። ስለሆነም ለኢትዮጵያውያን እስልምና መለከ ታዊ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የታሪክ ቅርስና ውርስም ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የ5000 ዓመታት ታሪክ ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።

4. የጦርነት ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ

የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ግንኙነት

በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ኅብረተሰብ በ20ኛው ምዕተ ዓመት በአንድ በኩል የሰው ልጅን አጠቃላይ የመነሻ ታሪክ በሚመለከት ዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌአንቶሎጂ፥ የሊንጉስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስ የእውቀትና የትምህርት አብዮት አስገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በአገሪቱ የሥርዓት ለውጥ አስከትሏል። እንዲሁም በዓለም ላይ የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መሠረተ ሀሳብና ትምህርት እየተስፋፋ መጥቷል። የዘረኝነት እምነትና ትምህርት በዓለም ላይ ከኃይል ሥርዓት ጋር ውግዝና ውድቅ ተደር ጓል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ምሥረታና ግምባታ አመቺ ሁኔታና ዘመን ተፈጥረዋል ለማለት ይቻላል።

ስለሆነም በፖለቲካ ተረትና በዘረኝነት ትምህርት ለዘመናት የተቀመመውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ክስልተ ምርትና ከሥርዓተ ማኅበር አኳያ፥ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ግንኙነት አኳያ በአዲስ ሜቶዶሎጂ (ስልተ ጥናት) ከመነሻ አንስቶ እንደገና ለማጥናትና ለመገምገም አስገዳጅ የእውቀትና የትምህርት ሁኔታዎች፥ መንገ ዶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች ተፈጥረዋል። የኢንፎርሜሽን እና የእውቀት አብዮት ተካሂዷል። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ዘመን1


አንደኛ፥ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የጭቆና ሥርዓት በሕዝባዊ አብዮት ተወግዷል። የመንግሥት ሥልጣን ምን ጭና ባለቤት አምራቹ ሕዝብ እንደሆነ አብዮታዊ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል።

ሁለተኛ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የእውቀትና የቴክኖሎጂ አብዮት ተካሂዷል። የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥያቄ የዘመኑ ትምህርትና ሥርዓት እየሆነ መጥቷል። በመንግሥትና በሥርዓት ላይ የግለሰብ የማኅበረሰብ የሕዝብና የኅብረተሰብ ሉአላዊ በላይነት ዓለማቀፋዊ እውቅና እያገኘ መጥቷል።

ሦስተኛ፥ ባለፉት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ታሪክ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው የውጭ ምሁራን ትምህርት በዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌአንቶሎጂ፥ የሊንጉዊስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስና እውቀት ውግዝና ውድቅ ተደርጓል። ባጭሩ ዛሬ በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ግምባታ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችና ሂደቶች አመቺ ሆነው ተገኝተዋል።

ተረጋግጧል። ስለሆነም ለኢትዮጵያውያን እስልምና መለኮ ታዊ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የታሪክ ቅርስና ውርስም ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የ5000 ዓመታት ታሪክ ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፣ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።

4. የጠረነት ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ

የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ግንኙነት

በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ኅብረተሰብ በ20ኛው ምዕተ ዓመት በአንድ በኩል የሰው ልጅን አጠቃላይ የመነሻ ታሪክ በሚመለከት ዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌአንቶሎጂ፥ የሊንጉስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስ የእውቀትና የትምህርት አብዮት አስገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በአገሪቱ የሥርዓት ለውጥ አስከትሏል። እንዲሁም በዓለም ላይ የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መሠረተ ሀሳብና ትምህርት እየተስፋፋ መጥቷል። የዘረኝነት እምነትና ትምህርት በዓለም ላይ ከኃይል ሥርዓት ጋር ውግዝና ውድቅ ተደር ጓል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ምሥረታና ግምባታ አመቺ ሁኔታና ዘመን ተፈጥረዋል ለማለት ይቻላል።

ስለሆነም በፖለቲካ ተረትና በዘረኝነት ትምህርት ለዘመናት የተቀመመውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ከስልተ ምርትና ከሥርዓተ ማኅበር አኳያ፥ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ግንኙነት አኳያ በአዲስ ሜቶዶሎጂ (ስልተ ጥናት) ከመነሻ አንስቶ እንደገና ለማጥናትና ለመገምገም አስገዳጅ የእውቀትና የትምህርት ሁኔታዎች፥ መንገ ዶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች ተፈጥረዋል። የኢንፎርሜሽን እና የእውቀት አብዮት ተካሄዷል። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ዘመን፤

አንደኛ፥ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የጭቆና ሥርዓት በሕዝባዊ አብዮት ተወግዷል። የመንግሥት ሥልጣን ምን ጭና ባለቤት አምራቹ ሕዝብ እንደሆነ አብዮታዊ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል።

ሁለተኛ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የእውቀትና የቴክኖሎጂ አብዮት ተካሄዷል። የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥያቄ የዘመኑ ትምህርትና ሥርዓት እየሆነ መጥቷል። በመንግሥትና በሥርዓት ላይ የግለሰብ የማኅበረሰብ የሕዝብና የኅብረተሰብ ሉአላዊ በላይነት ዓለማቀፋዊ እውቅና እያገኘ መጥቷል።

ሦስተኛ፥ ባለፉት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ታሪክ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው የውጭ ምሁራን ትምህርት በዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌአንቶሎጂ፥ የሊንጉዊስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስና እውቀት ውግዝና ውድቅ ተደርጓል። ባጭሩ ዛሬ በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ግምባታ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችና ሂደቶች አመቺ ሆነው ተገኝተዋል።

ከዚህ አኳያ በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ የማኅበራዊ ለውጥና ዕድገት መነሻ ነባር ማኅበራዊ ድርጅትና ሥርዓት ነው። ከላይ እንደ ተባለው፥ ለሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረ ተሰብና መንግሥት የመነሻ ምድር ነው። ይህ ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓት በመጨረሻ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ከፍለ አህጉሩን ከሞላ ጎደል ከሥሩ ያማከለውና ከጥንቱ አዋማዊ የደአማት-አክሱም ሥልጣኔና መን ግሥት በረጅም ታሪካዊ ሂደት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የኢትዮ ጵያ ዘውዳዊ ሥርዓት ነው።

ከዚህ አንፃር በከፍለ አህጉሩ ከየሀ-ደአማት እስከ አዲስ አበባ ዘመን ድረስ ባለፉት 2500 ዓመታት በደአማት፥ በሳባ፥ በግሪክ፥ በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋዎች ተጽፎ የተገኘው የኢትዮጵያ ታሪክ በጠባብ መልኩ ሲታይ የነገሥታትና የካህናት ጥምር የፖለቲካና የሃይ ማኖት ዘገባ ነው። ከሰፊው የኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረተሰብ ክስተትና ዕድገት አኳያ ሲታይ ደግሞ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ነው። የብዙ ሕዝቦች የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴዎች ታሪክ ነው። በመሆኑም የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች የመስተጋብርና የመወራረስ መግለጫ ነው።

ከሥርዓትና ከትምህርት አኳያ፥ የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ብዝትና አንድነት በአንድ በኩል የጎብረተሰቡን ጥንታዊነት ያሳያልI በሌላ በኩል ደግሞ ለረጅም ዘመን ዕድገትና ለውጥ ያልተካሄደበት ኋላቀር ጎብረተሰብ፥ መንግ ሥትና ሥርዓት መሆኑን በግልፅ ያስተምራል።

በተጨማሪም ይህ የኢትዮጵያ ጥንታዊ፥ በህውርታዊና ኋላቀር የፖለቲካ ሥርዓት የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ጎብረተሰብ ጥንቅር እና ቅንጅት እንደሆነ አሁንም ከታሪክ መረጃና ጥናት በግልፅ ይታያል። በዚህ ኋላቀር የፖለቲካ ሥርዓት መንግሥት የጎብረተሰቡን የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ ድርጅቶችንና መዋቅሮችን ከሃይማኖትና ከጦር ድርጅቶች ጋር በበላይነት የሚቆጣጠርና የሚገዛ ብቸኛው ኃይል ነው። በመሆኑም መንግሥት ወይም ንጉሥ በፍጹም ሥልጣኑ የሕዝቡን ሕይወትና ንብረት እንደፈለገ ይገዛል። ለወደደው ሹመት፥ መሬት፥ ማዕረግና ክብር ይሰጣል። ከጠላው ደግሞ ይወሰ ዳል። ሕዝቡ ግን በንጉሡ ላይ የሕይወቱንና የንብረቱን መብት የሚያ ስከብርበት ሕጋዊ መንገድና መሣሪያ የለውም። ምክንያቱም ንጉሡ በሕዝቡና በጎብረተሰቡ ላይ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት

ነውና። ለምሳሌ፥ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ በብሉቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ (ዝክረ ነገር) ቃል፦

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሚገዛው አገር ላይ ያለው ሥልጣን በማም የተሰፋፋ መሰን የሌለው ነው። በሥጋዊም በመንፈሳዊም ሥራ ሁሉ ይገባል። ከፍ ባለው ሥልጣኑም ይሸማል፥ ይሽራል፥ ይሰጣል፥ ይነሳል፥ ያሰራል፥ ይፈታል፥ ይቆርጣል፥ ይገድላል፥ ይምራል። ይህንንም የመሰለውን ሁሉ ይፈጽማል።[8]

በአጼ ሱሰንዮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊ እንደተባለው ደግሞ፥ ራሱን የኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ የሚጠራው፦

«ንጉሥ የወደደውን ያከብር ዘንድ የጠላውን ያዋርድ ዘንድ በሚገዛው ዓለም ላይ የእግዚአብሔር እንደራሴ ነው። ንጉሡ የወደደውን ይጠላል። የጠላውን መልሶ ይወዳል። በአመጻቸው የገደላቸው ሰዎችን ልጆች ወንድሞችና ዘመዶች እያመጣ ወዳጅ ያደርጋቸዋል»[9] ይላል።

ይህንን ጠንካራ የሆነ መንግሥታዊ የንጉሥ ኃይልና ሥልጣን የፈጠረው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓት ጠባዩ ምን እንደ ሆነ፥ ከምን ዓይነት የምርት ግንኙነት የወጣ እንደሆነ፥ መቼና በምንስ ሁኔታ እንደሚለወጥ ብሎም በጎብረተሰቡ ማኅበራዊ ሕይወትና ዕድገት ላይ ምንዓይነት ተፅዕኖ እንዳስከተለና እንደሚያስከትል ለማወቅ የሥርዓቱን የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ ድርጅቶችና መዋቅሮች ማጥናትና ማወቅ የግድ ይሆናል።

የተገለጸው ሥርዓት የጋርዮሽ ሥርዓት ነው እንዳይባል የተመ ለከተው ጎብረተሰብ በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና የግል ሀብት መሠረት ለዘመናት በመደብ የተደራጀ የገዥና የተገዥ ጎብረተሰብ ነው። የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ነው እንዳይባል ደግሞ የተጠቀሰው ጎብረተሰብ የምርት ግንኙነት የባሪያ ምርት ግንኙነት ሳይሆን የጎ ዜጎች፥ አገርና ጎብረተሰብ ነው። የፊውዳሊዝም ሥርዓት ነው እንዳይባልም መሠረታዊ የፊውዳሊዝም ገጽታዎች ማለትም ከመሬት ጋር ተያይዘው የመንቀሳቀስና የምርጫ ነፃነት የሌላቸው ገበሮች መደብ፥ በግል መሬትና ጠር ተደራጅተው መደባዊና ሕጋዊ ጥቅማቸውን በገዛሩና በመሳፍኑ ላይ ማስከበር የሚችሉ የመሬት ከበርቴዎች መደብ፥ በገጠርና በከተማ መካከል ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና ሥርዓታዊ ቅራኔ፥ እንዲሁም በከተማ የተደራጁ የንግድና የዕደጥበብ ማኅበረሰቦች መደብ ከላይ በተመለከተው የኢትዮጵያ ንጉሣዊ ጎብረ ተሰብ ዘንድ ማኅበራዊና መደባዊ ሀልዎና የለውም።[10]

[8] ማሀተም ሥላሴ፥ ዝክረ ነገር፥ (1962)፥ ገፅ 52።

[9] ተክለ ሥላሴ፥ የሱስንዮስ ታሪክ፥ ም 48፥ ቁ 223

[10] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ (1982)፥ ገፅ 291-92።

ይህን በጋርዮሽ ሆነ በባሪያ አሳዳሪው ወይም በፊውዳል ሥርዓት ሥልተ ምርትና ሥርዓተማኅበር መልክና ደረጃ የማይመደበውን ጥንታዊና ኋላቀር ጎብረተሰብ ካርል ማርክስ «እስያዊ» ወይም «ምሥራቃዊ»[11] ስልተ ምርትና ሥርዓተ ማኅበር ብሎ ይመድበዋል።

የዚህ የምሥራቃዊ ስልተ ምርትና ጎብረተሰብ ገላጭ ባህርያት ብዙና መሠረታዊ[12] ናቸው። ሰትምህርታዊ ግንዛቤ ያህል የጎብረተሰቡ መሬት የመንደርና የቤተሰብ ይዞታ ነው። በሥርዓቱ መሠረት መሬትም፥ መንደርም፥ ቤተሰብም፥ ሁሉም የመንግሥት ማለትም የንጉሡ ይዞታ ነው። የግል መሬት ይዞታ እንዲሁም የግል ሀብት ሕግ የለም። ጎብረተሰቡ ጥንታዊ የገጠር ጎብረተሰብ ነው። የገጠር መንደሮች በኢኮኖሚና በፖለቲካ ራስገዝ አካባቢዎች ናቸው። በገጠርና በከተማ መካከል የሥራ ክፍፍልና ሥርዓታዊ ቅራኔ ገና አልዳበረም። የጎብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት የመንደር እርሻና ዕደጥበብ ቅንጅት ነው። ዘመናዊ ሳይንስና የምርት ቴክኖሎጂ የለም። በመንግሥትና በሃይማኖት መካከል ልዩነት የለም። ሙያዊና ማህበራዊ የሥራ ብዝት፥ ልዩነትና ክፍፍል ገና ያልዳበረ በመሆኑ በጎብረተሰቡ ዘንድ የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ የለም። በፖለቲካ፥ በሃይማኖት፥ በአስተዳደር፥ በኢኮኖሚ፥ በገንዘብ፥ በመከላከያና በኮንስትራ ክሽን ሥራዎችና መስኮች በንጉሥ የሚገዛ መንግሥት የጎብረተሰቡ የበላይ ተቆጣጣሪ ጌታ[13] ነው።

ነገሥታትና ካህናት የጎብረተሰቡ ገዢዎችና አስተማሪዎች ናቸው። በጎብረተሰቡ ዘንድ በግል ሀብትና በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል የተመሠረተ መደባዊ ልዩነትና ሥርዓታዊ ቅራኔ ገና ያልዳበረ በመሆኑ በእስያዊ ወይም በምሥራቃዊ ኋላቀር ሥልተምርትና ሥርዓተማህበር በአንድ በኩል ጎብረተሰባዊ ዕድገትና ለውጥ ሰረጅም ዘመን አይታይም። ከፍተኛ የዕድገትና የለውጥ ቅራኔ የለበትም። በሌላ በኩል ግን የፖለቲካ፥ የመንግሥት፥ የነገሥታትና የሥርወ መንግሥት ዕድገት፥ ለውጥ፥ ውድቀት፥ ሽብር የዘወትር ክስተት ነው። በሌላ አባባል የፖለቲካና የመንግሥት ዕድገትና ለውጥ ማኅበራዊ የጎብረተሰብ ዕድገትና ለውጥ አይደለም ማለት ነው።

ካርል ማርክስ አንዳስቀመጠው፥ በእስያዊ ወይም በምሥራቃዊ ጎብረተሰብ ዘንድ ይህንን መንቲያ የሆነ ሥርዓታዊ ገፅታ የሚያስረዱ

[11] K. Marx, Capital, Vol. 1 Part 4, Chap. 15, Sec. 4; K. Marx, Pre-Capitalist Economic Formation, ed. E. J. Hobsbawm (1972), pp. 79-83.

[12] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገፅ 295-96።

[13] Marx, Capital, I, pp. 333-34.

ቁልፍ ነገሮች በተጠቀሰው ጎብረተሰብ በየመንደሩ ራስ ገዝ የሆኑና ሁልጊዜም ከጦርነትና ከሌላም አደጋ በኋላ በቶሎ ተመልሰው የሚያድጉ ትንንሽ የገጠር ማኅበረሰቦች ያላቸው፥ ነገር ግን በቅርፅ፥ በይዘትና በዕድገት ደረጃ የመሻሻል ለውጥ የማይታይባቸው፥ የምርት አደረጃጀት መንገዶችና መሣሪያዎች ናቸው። ባጭርና በጥቅል አነጋገር፥ በተጠቀሰው ጥንታዊ የምስራቅ ጎብረተሰብ ዘንድ ዘወትር የሚካሄድው የመንግሥት ለውጥ ሆነ የፖለቲካ ሽብር ወይም ጦርነት በጎብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረትና አደረጃጀት ላይ የዕድገት ለውጥ አያስከትልም።[14] በሌላ ቃል፥ ፖለቲካም ሆነ ጦርነት ወይም ሃይማኖት በጎብረተሰቡ ዘንድ በትምህርትና በምርት ቴክኖሎጂ ሥርዓት ላይ ለውጥ እና ዕድገት ለማምጣት እስካልቻለ ድረስ በመሠረታዊ የኢኮኖሚ፥ የህልና የማኅበራዊ ሥርዓቶችና መስኮች ላይ ለውጥና ዕድገት እንደማያስከትል የተጠቀሰው ስልተ ምርትና ሥርዓተ ማህበር በግልፅ ያሳያል።

በአንድ ሌላ የጀርመን ምሁር በፕሮፌሰር ማርክስ ዊትፎጌል ዝርዝር ጥናትና ግኝት መሠረት፥ የተጠቀሰው ምሥራቃዊ ስልተ ምርትና ሥርዓተማኅበር የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ጎብረተሰብ ቅንብርና ቅንጅት ነው።[15] በሥርዓተ ማህበሩ መንግሥት የጎብረተሰቡ ፍጹም ጌትና ጌታ ነው። ሃይማኖትና ጦር የመንግሥቱ ማለትም የንጉሡ የግል መሣሪያዎች ናቸው። ሰዎች የመንግሥት ገባሮችና እሽከሮች ናቸው። የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች ትምህርትና ጥያቄ ከሥርዓተ ማኅበሩ ጋር አብሮ አይሄድም። ሕዝብና ጎብረተሰብ የመንግሥትን ንጉሣዊ አስጨናቂና አፋኝ ኃይል የሚቆጣጠርበት ሕጋዊ መሠረት፥ መንገድ፥ መሣሪያ የለውም። በመሆኑም የፖለቲካ አመፅና ጦርነት የሥርዓቱ ዓይነተኛ ገፅታዎች ናቸው። ጎብረተሰቡ የሚገዛው በሕግና በስላም ሳይሆን በኃይልና በአመፅ ግፊት ነው።

በካርል ማርክስ ጥናትና ግኝት መሠረት፥ በማኅበራዊ ዕድገት ገና ሙሉ በሙሉ ወደ ፊውዳላዊ ደረጃ ያልደረሰው የዚህ ኋላቀር ምሥራቃዊ ሥልተ ምርትና ሥርዓተ ማኅበር ሁለት ዓይነተኛ ምሳሌዎች ጥንታዊ የሕንድና የቻይና መንግሥታትና ጎብረተሰቦች ናቸው። በእነዚህ ጥንታዊ ጎብረተሰቦች ዘንድ የውጭ ወረራም ሆነ የውስጥ ጦርነት ወይም ዘወትር የሚከሰቱ የረሃብና የተፈጥሮ አደጋዎች በጎብረተሰቡ ጥንታዊ የኢኮኖሚ መሠረትና አደረጃጀት ላይ፥ በራስገዝ የመንደር እርሻና ዕደጥበብ ቅንጅት ላይ፥ በአሮጌ የምርት ኃይሎችና

[14] Ibid., p. 358.

[15] K. A. Witfogel, Oriental Despotism: A Comparative Study of Total Power, (1959), p. 271.

የምርት ግንኙነት ላይ የዕድገት ለውጥና መሻሻል አያስከትሉም። በመሆኑም በተጠቀሱ ጥንታዊ የሕንድና የቻይና ጎብረተሰቦች ዘንድ ለዘመናት በአሮጌ የምርት ኃይሎች ሆነ የምርት ግንኙነቶች ላይ የለውጥና የዕድገት ሁኔታዎች፥ እንቅስቃሴዎችና ሂደቶች አልተ ገኙም።[16]

ነገር ግን በ19ኛው ምዕተ ዓመት የምዕራቡ ኢንዱስትሪያዊ ኮሎኒያልዝምና ኢምፔሪያሊዝም በሸቀጥ ንግድና በትምህርት መሣሪያ ዎች የሕንድ-ቻይና መንግሥታትንና ጎብረተሰቦችን ጥንታዊ የኢኮኖሚ መሠረትና የአደረጃጀት ስልት በማናጋትና በማጥፋት ለዘመናዊ ሳይንስ፥ የምርት ቴክኖሎጂ፥ የጦርና የመገናኛ መሳሪያዎች፥ የገንዘብ እና የሸቀጥ ገበያ መንገድና በር በመክፈት ለመሠረታዊ የስልተ ምርትና የሥርዓተ ማኅበር ለውጥና ዕድገት እንዴት አመቺ ሁኔታ እንደፈጠሩ ካርል ማርክስ ጨምሮ አሳይቷል።[17]

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓትና ንጉሣዊ ሥልጣን በይዘትም ሆነ በአደረጃጀት ስልት ወይም በተግባር በጀርመን ምሁራን ማርክስና ዊትፎጌል ከተገለጸው ጥንታዊ የምስራቅ ስልተ ምርት እና ሥርዓተ ማህበር በዓይነት ልዩ አይደለም። በዚህ የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ የዘውድ ሥርዓትና መንግሥት ሥር ነው ሦስቱ መለኮ ታዊና አሀዳዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ከመጽ ሐፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ጋር በስላማዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ በመግባትና መንግሥታዊ የእምነት፥ የትምህርትና የባህል ተቋማት፥ መሠረቶችና መሣሪያዎች በመሆን ባለፉት 1700 ዓመታት ውስጥ የተስፋፉት። የተጠቀሱ ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ የሥልተ-ምርትና የሥርዓተ-ማህበር ለውጥ አላስከተሉም። ነገር ግን በጎላ፥ በቋንቋ፥ በባህልና በዕድገት ደረጃ በተለያዩ የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች መካከል ለአገራዊና ለባህላዊ መስተጋብርና መወራረስ ድርጅታዊ ኃይሎችና መሣሪያዎች በመሆን ታሪካዊ ሚና እንደ ተጫወቱ የማይካድ ሀቅ ነው።

የመንግሥትና የሃይማኖት ግንኙነት

ከላይ እንደተባለው፥ በኢትዮጵያ ሦስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች የተስፋፉትና የኖሩት በጎብረተሰቡ ዘንድ የመንግሥት የፖለቲካ መሣሪያዎችና አገልጋዮች ሆነው ነው። በዚህ ረገድና ተግባር፥ በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥

[16] K. Marx and F. Engels, On Colonialism, (1974), pp. 19-44, 81-8.

[17] Ibid., pp. 40-41, 81-87.

የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች ተጽፈው ከክርስ ምድር በቅርቡ በአርኪኦ ሎጂ ጥናት በተገኙ ጽሑፎች መሠረት፥ በ330ዎቹ ዓመተ ምህረት መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና ሃይማኖት በግሪኮ-ሮማውያን አስተማ ሪዎች አማካይነት ወደ አገሪቱ እስኪገባ ድረስ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ምድር፥ ሕዝብ፥ መንግሥት፥ ሃይማኖትና ሥልጣኔ አዋማዊ እንደ ነበር ተረጋግጧል። በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጽሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ በዘጠኙ ግሪኮ-ሮማውያን ጻድቃን ወደ ግዕዝ ከተተረጎመ በኋላ ግን የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ አዋማዊ አገርና መንግሥት በአንድነት እንደተሰፋፉ በአጠቃላይ መልክና መንገድ ይታወቃል። ነገር ግን ከዚህ አኳያ፥ በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ በዘመኑ የተጻፈ የሰነድ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ በአገሪቱ ውስጥ ስላልተገኘ የሃይማኖቶቹ የዕድገትና የሰርጭት ዝርዝር ታሪክ በትክ ክል አይታወቅም።

በሌላ በኩል በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ ሦስተኛው መለኮታዊና አሀዳዊ የእስልምና ሃይማኖት ከአረቢያ በሙስሊም ስደተኞች አማካ ይነት በ615 በለሜን ኢትዮጵያ በአክሱም ቤተ መንግሥትና አገር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተሰበከ ቀጥሎም ከ896 እስከ 1270 ድረስ በአረብ አስተማሪዎችና ነጋዴዎች አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ገብቶ በደቡብ ኢትዮጵያ በፍጥነት እንደተስፋፋ ከታሪክ መረጃ ተረጋግጧል።[18] ባጭሩ በኢትዮጵያ፥ እንደ ጎብረተሰቡም፥ የዓይነትና የደርጃ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ፥ ሁሉም ሃይማኖቶች የመንግሥት አገልጋይ መሣሪያዎች ናቸው።

በ14ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአጼ አምደጽዮን (1314-44) ዘና መዋዕል በዝርዝር እንደተጻፈው፥ ሦስቱም የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች በቅድም ተከተል በለሜን፥ በለሜን ምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ሦስት የተለያዩ የመንግሥት ሃይማኖቶች ነበሩ። የዘመኑ የታሪክ መረጃና ትምህርት በስፋት እንደሚያመ ለክተው፥ ከትምህርትና ከተግባር አኳያ፥ ሃይማኖቶቹ በአንድ በኩል ስተጠቀሱት መንግሥታትና ነገሥታት ፍጹም የፖለቲካ መሣሪያዎች እና አገልጋዮች ነበሩ። በሌላ በኩል ደግሞ በሚያገለግሉዋቸው መንግ ሥታት ሥር ብዙ ተከታይ ጅዕመናን ነበሩዋቸው። በተጨማሪም መንግሥታቱ በየበኩላቸው በመሬት፥ በግዛትና በንግድ ጥያቄ እርስ በርሳቸው በዘውትር ጦርነት ውስጥ ነበሩ። የመንግሥታቱ ጦርነት በሕዝቦች መካከል ጥፋትና መለያየት ሲፈጥር ሶስቱ መለኮ ታዊ ሃይማኖቶች ግን በየአካባቢያቸው በኢትዮጵያ በሀውርታዊ አገርና

[18] J. Couq, L'Islam in Ethiopia, (1981).

ቋንቋ ወደ ግዕዝ እንደተረጎሙና እንዲሁም የገዳምና የምንኩስና ሥርዓት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደመሠረቱ አይረሳም።

ከዚያ በኋላ በ1337-1450 በተጠቀሱ ጻድቃን የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስና የገዳም ትምህርት መሠረትነት የኢትዮጵያ እምስጣጢዎሳውያን የተባሉ የገዳም መሰረትና መምህራን ለመጀመሪያ ጊዜ ከክርስትና ሃይማኖትና ትምህርት ጎን የአሪትን ሕግና ሃይማኖት በመላው የሰሜን ኢትዮጵያ ደጋአምባ ክልል በአራቱ የትግሬ፥ የአገው፥ የአማራና የሰሜን/ፈላሻ አጎራባችና ተዛማጅ ማኅበረሰቦች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ እንደገለጡ ተረጋግጧል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በመሬት፥ በሃብትና በሥልጣን ጥያቄ ባላንጣ የሆኑ ሰሜን/ፈላሾችና የክርስቲያን ኃይሎች በተከዜ ዓባይ እስትራቴጂያዊ ለምና ሰፊ ምድር ከ1316 እስከ 1632 ድረስ ለ316 ዓመታት ሲዋጉ እንደኖሩና በመጨረሻም አሪታዊ የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ሠርፀድንግልና ሱስንዮስ በተባሉ ክርስቲያን የአማራ ነገሥታት አመራር በዘመናዊ የጉጥጥና የመድፍ መሣሪያዎች እንደተደመሰሰ፥ ሕዝቡም ከመሬቱ ተነቅሎ በተወሰኑ መንደሮች ብቻ በዕደጥበብ ሙያው እንዲኖር እንደተደረገ የዘመኑ ታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

ከታሪክና ከጊዜ አኳያ፥ ከ1316 እስከ 1632 ድረስ በአሪታዊ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና በክርስቲያን የአማራ ነገሥታት አምደጽዮን፥ ዳዊት፥ ይስሐቅ፥ ዘርዓያዕቆብ፥ ባዕደማርያም፥ እስክንድር፥ ናኦድ፥ ልብነ ድንግል፥ ገላውዴዮስ፥ ሚናስ ሠርፀድንግልና ሱስንዮስ መካከል የተካሄዱ ጦርነቶች ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት በክፍለ አህጉሩ በኢትዮጵያ አዋማዊ፥ እስላማዊና አሪታዊ ሕዝቦችና በክርስቲ ያን ነገሥታት መካከል ከተካሄዱ ጦርነቶች ለዓይነት ብቻ የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ ረገድና ተግባር፥ የተጠቀሱት ነገሥታትና የጦር አበጋዞቻቸው፦

(1) በግምት ከ1270-1577 ድረስ ለ300 ዓመታት በኢትዮጵያ እስላማዊና አዋማዊ የሸዋ፥ የሀዲያ፥ የወርጅ፥ የይፋት፥ የዳዋሮ፥ የአራባቢኒ፥ የሻርካ፥ የባሌ፥ የደራ፥ የአዳል፥ የሞራ፥ የለበከላ፥ የሀገራ፥ የፊድሌ፥ የግደድ፥ የንብ፥ የዘባ፥ የሁብት፥ የተርላ፥ የእይም፥ የሐርላ፥ የእልብሮ፥ የዜይላ፥ የእስቴ፥ የአርጎባ፥ የፊጠጋር፥ የሐረር፥ የስልጤ፥ የጉራጌ፥ የአውሳ፥ የዶባ፥ የዋጅ፥ የሶማሌ፥ የከምባታ፥ የጋሞ፥ የወላይታ፥ የጋፋት፥ የጀንጀሮ (የም)፥ የዳሞት፥ የበሻ፥ የእናርያ፥ የቢዛሞ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ በሥፍራና በጊዜ ያልተዛመጡ ጦርነቶችን በማካሄድ የሕዝቦቹንና የመንግሥታቱን የኢኮኖሚ፥

የፖለቲካ፥ የመከላከያ፥ የሃይማኖት፥ የባህል ሥርዓቶችንና ድርጅቶችን እንዳጠፉ በነገሥታቱ ዜና መዋዕሎች[25] በዝርዝር ተመልክቷል።

(2) በ1524-1543 ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (ግራኝ) ባካሄደው የአመፅ ጦርነት አሪታዊ ሰሜን/ፈላሻን ጨምሮ የመላ ክፍለ አህጉሩን እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችን በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ አስተባብሮ፥ በ1543 ለክርስቲያኑ መንግሥት እርዳታ ከሕንድ በመጡ የፖርቱጋል ኑፍጥኞች እስኪገደል ድረስ፥ በክርስቲያኑ መንግሥትና ጦር ላይ ታላቅ የአጸፋ ጉዳት እንዳደረሰ ታውቋል።[26]

(3) የኢማም አሕመድ ግራኙ የአመፅ ጦርነት በክርስቲያን ኃይሎች ላይ ካደረሰው ውድቀት ሌላ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለአዋማዊ የኦሮሞ ማኅበረሰቦች ፍለሳና ሰፊራ ብሎም በክፍለ አህጉሩ ለታላቁ የ1520-1620 የሕዝቦች እንቅስቃሴ በር ና መንገድ ከፈተ።[27]

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በተለይ ከላይ የተጠቀሱ የ1270-1577 ጦርነቶች በደቡብ ኢትዮጵያ በሁለቱ ተፋላሚ የክርስቲያንና የእስላም ኃይሎች ላይ የጋራ ሽንፈትና ውድቀት ከደረሰባቸው ቡኋላ፥ ከክፍለ አህጉሩ የደቡብ ምስራቅ ቆላማ አካባቢ ቢታላቅ የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴ የተጀመሩና ገዳ በተሰኘ ልዩ የኦሳ ሥርዓት የሚመሩ የኦሮሞ ዘላን ማኅበረሰቦች ቢረጅም ጦርነት የተዳከሙ የክርስቲያንና የእስላም ባላንጣ ኃይሎችን በቀላሉ ተቆጣጥረው[28] በክፍለ አህጉሩ የደቡብ፥ የምስራቅ፥ የመሀል፥ የምዕራብና የሰሜን ለምና ሰፋፊ አካባቢዎች በሸዋሪነት በመስፈር ባጭር ጊዜ ውስጥ ለዛሬው የኢትዮጵያ በህውሪታዊ ሕዝቦች ጎብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ ዕድገት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ያደረጋሉ።[29]

(4) ሁለቱ ተከታታይና ተዛማጅ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ ግራኙ የአመፅ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴ በሰሜን ኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥትና ጎብረተሰብ

[25] Huntingford, Amda Seyon; J. Perruchon, tr. and ed., Les Chroniques de Zara Yaqob et de Baeda Maryam, (1893); Conti Rossini, Sarsa Dengil.

[26] Arab Faqih, Conquete.

[27] ላቋሶ ጌ ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገፅ 2159-17795-96

[28] Bahrey, History of the Gallas; Conti Rossini, Sarsa Dengil; ተክለ ሥላሴ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ።

[29] ለምሳሌ በ1994 የኢትዮጵያ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት፥ በ9 ክልሎች ከተቆጠረው ከአገሪቱ 49,000,000 ሕዝብ፥ 17,000,000 የኦሮሞ ቋንቋ ማኅበረሰብ ሲሆን፥ በ2ኛ ደረጃ 16,000,000 ደግሞ የአማራ ቋንቋ ማኅበረሰብ ነው። በሃይማኖት በኩልም በ16ኛው ምዕተ ዓመት ሙሉ በሙሉ አዋማዊ ከነበረው የኦሮሞ ሕዝብ፥ በ1994፥ 9,000,000 ክርስቲያን፥ 8,000,000 እስላም፥ 800,000 ደግሞ አዋማዊ እንደሆነ ተመልክቷል።

የፖለቲካ ጉዳይ ሆነ።

በተጠቀሱ የክርስቲያን ኃይሎች የኦሪታዊ፥ የእስላማዊና የአሞማዊ ሕዝቦች ፖሊሲና ፖለቲካ መሠረት፥ ከ1580 እስከ 1632 ድረስ የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት በፖርቱጋልና በቱርክ ኑፍጥና መድፍ በታጠቁ በአጼ ነገሥታት ሠርፀድንግልና ሱስንዮስ ሠራዊቶች ከ300 ዓመት ምህረት ጀምሮ ለ1300 ዓመታት በሰነድ ታውቆ በኖረባቸው በሰሜኑ አምባዎችና ሸለቆዎች «የአይሁድ» መንግሥት ነው ተብሎ በይፋ ተደመሰሰ። ሕዝቡም በሙሉ ከመራቡ ተነቅሎ በአገሩ ለአሸናፊው ኃይል ገባርና ባሪያ ተደረገ። ሃይማኖቱም በንጉሥ አዋጅ ተሰረዘ። እንዲሁም በጎንደር፥ በትግራይና በሸዋ የክርስቲያን አገሮች በዘልማድ «ጀበርቲ» ተብለው የሚታወቁ የአማራ፥ የአገውና የትግሬ ሙስሊሞች የመሬት ባለቤቶች እንዳይሆኑ፥ በመንግሥት ሥልጣንና ሥራ እንዳይሳተፉ የእምልኮ ቦታና ቤትም እንዳይኖራቸው ተደረጉ።

ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱ የኦሮሞ ማኅበረሰቦች በየአካባቢ ያቸው በቁጥርም፥ በሀብትም በጦር ኃይልም በጎንደር፥ በትግራይና በሸዋ በተጠቃሽ የክርስቲያን ኃይሎች ላይ ለረጅም ዘመን ከፍተኛ የኃይል ሚዛን ስለነበራቸው፥ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ የአውሮፓ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ፥ የንግድና የትምህርት ወኪሎች ከዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በተጠቀሰው የኃይል ሚዛን ጉዳይ ላይ መሠረታዊ ለውጥ እስኪያስከትሉ ድረስ፥ የክርስቲያን ኃይሎች ከሦስቱ አጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ፥ ዮሐንስና ምኒልክ በፊት፥ የመሬትና የሃይማኖት ፖሊሲያቸውን በፊረስ ጦር በታወቁ ኦሮሞዎች ላይ ለመተግበር በፍጹም አልቻሉም። በዚህ ረገድና ተግባር፥ አጼ ቴዎድሮስ በጎዳር 1862 ለእንግሊዝ ንግሥት በጻፉት ደብዳቤ I

«እስከ ዛሬ ድረስ አባቶቼ ነገሥታቱ ፈጣሪአችንን ቢበድሉት መንግሥታቸውን ለጋላና ለቱርክ አሳልፎ ስጥቶባቸው ነበር። ዛሬ ግን እኔ ከተወለድኩ ፈጣሪዬ ከአመድ አንስቶ ኃይል ስጥቶ ባባቶቼ መንግሥት አቆመኝ። በእግዚአብሔር ኃይል ጋሎችን አስለቅቄአቸው ቱርኮች ግን ያባቴን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአ ብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነኝ»[33] በማለት ባጭርና በግልፅ ያስቀመጡት ነገር የታሪኩን እውነታና ታላቅነት በትክክል ይገልጻል።

ባጭርና በጥቅል ለማስቀመጥ፥ ከጎንደር፥ ከትግራይና ከሸዋ ታሪካዊ የክርስቲያን ክልሎች ከላይ በተመለከተው የክርስቲያን ኃይሎች የፖለቲካ ትምህርት መሠረት፥ በተከታታይ በተነሱ በአጼ


[33] S. Rubenson, King Tewedros of Ethiopia (1966), p. 48.

ነገሥታት ቴዎድሮስ፥ ዮሐንስና ምኒልክ የዘውዳዊ ምዕክልና ፖሊሲና ፖለቲካ በተፈጠረው የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት የተከሰቱ የሥርዓት፥ የፖለቲካ፥ የአስተዳደር፥ የኢኮኖሚ፥ የባህል፥ የትምህርት፥ የብሔረ ሰብና የመደብ ሁኔታዎችና ኃይሎች፥ ቅራኔዎችና ግፊቶች በእንድነት ተደምረው ባጭር የታሪክ ዘመን ውስጥ የ1974 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮትን አስከተሉ።

አብዮቱ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ጎብረተሰብ ግንኙነት መሠረታዊ ችግር መሆኑን የበለጠ አስገነዘበ። በመሆኑም፥ መንግሥት የሕዝብና የጎብረ ተሰብ ተገዥና አገልጋይ የሚሆንበትን፥ ሕዝቡ የመንግሥት ሥልጣን ሉአላዊ ምንጭና ባለቤት የሚሆንበትን፥ እንዲሁም ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና አሠራር የሕይወቱና የንብረቱ ሉአላዊ ባለቤትና ጌታ የሚሆንበትን አዲስ የፖለቲካ ጎብረተሰብና ሥርዓት በጉልበቱና በእውቀቱ የመገንባት ረጅምና መራራ ትግሉን ጀምሯል።

ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገር ግምባታ ትግል ግቡን የሚመታው ግን ሕዝቡ ራሱን በራሱ ታሪክና ልምድ መሠረት ለማደራጀትና ለመምራት ሲችል ብቻ ይሆናል። ምክንያቱም የአንድ ሕዝብ ታሪክ ጎብረተሰቡን የሚያንቀሳቅስ የመንፈስ ሞተርና ግፊት ነውና። በመሆኑም እስከ አብዮቱ የነበረውና የኃይለኛው መንግሥትና የደካማው ጎብረተሰብ ግንኙነት መሠረትና መግለጫ የሆነው የኢትዮጵያ ታሪክ ከስልተምርትና ከሥርዓተማኅበር አኳያ፥ ከኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አኳያ ባዲስ ሳይንሳዊ ሜቶዶሎጂና ሚዛን እንደገና በትክክል ተጠንቶ መቅረብ አለበት። የዚህ ጥናት ዓላማና ተግባር በዚህ ረገድና አቅጣጫ ጅምር አስተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ይሆናል።

በ1855 ዘውዳዊ ምዕክልና በተጀመረ ጊዜ የኢትዮጵያ የነፃ ሕዝቦችና መንግሥታት ካርታ



ሠንጠረዥ 1
የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ዝርዝር

ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች	ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች	ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች	ናይሎዕቲካዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች
ቤኻ ቢለን አገው ወይጦ ፈላሻ ሶማሌ ረንዳል ጋቶ አርቦሬ ማኅሰዶ ባይላ ኮንሶ አሮሞ ዋራዚ ገሞዳ ፀማይ ደሳንች (ገለብ) አፋር ሳሆ ሲዳማ ከምባታ ሀዲያ ጥምባሮ አላባ ቀቤና ማረቆ ጌዲኦ ቡርጂ ትግረወርጅ	አሪ ሐመር በናግሌ ዘይሴ ቡላ አይዳ ዶርዜ ካፋ ጋሞ ማሎ ወላይታ ዲማ ናኦ ጫራ ኮንታ ኩሎ (ዳውሮ) ቦሻ የም ዲዚ ባስኬቶ ሻኮ ማኦ ኩፋ ሸኮቾ (ሞቻ) አንፊሎ ሺናሻ ኮራ ዘርጉላ ጋንዱላ ቃጫማ ጊዲቾ	ግዕዝ ትግረ ትግሬ አማራ አርኦባ ጋፋት ሐረሬና የጉራጌ ማኅበረሰቦች፥ ምሁር መስቃን ስልጤ እነሞር ቸሀ ጌቶ አገር አንዳጋኝ ወለኔ ኤነር አዘርንትብርበሬ ዝዋይ ሶዶ	ማዞንገር ሙርሌ ሙርሲ ከዋንጉ ቦዲ ትሸና ሱሪ ባሌ ቡሩን ኑዌር አኙዋክ ያንጋቶም በርታ ኮማ ጃብላዊ ናራ ጉሙዝ ኩናማ ፋዳሺ

ምንጭ ላቋሰ ጌ ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ(1985) ገጽ24

ሠንጠረዥ 2
በ1984 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከ20,000 በላይ የሰው ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ የ56 ብሔረሰቦች ዝርዝር

ተ ቁ	ብሔረ ሰቦች	የሕዝብ ብዛት		ተ ቁ	ብሔረ ሰቦች	የሕዝብ ብዛት	
		በቁጥር	ከመቶ			በቁጥር	ከመቶ
1	ኦሮሞ	13027875	30.57	29	ግሉ	58039	0.14
2	አማራ	12055250	28.29	30	ጥምባሮ	57938	0.14
3	ትግሬ	4249697	9.74	31	ሞቻ	57505	0.14
4	ጉራጌ	1855905	4.36	32	አርጎባ	51877	0.12
5	ሱማሌ	1613394	3.79	33	ሚኤን	50405	10.12
6	ሲዳማ	1261721	2.96	34	ናራ	49229	0.12
7	ወይታ	1092958	2.57	35	ባስኬቶ	45471	0.11
8	ትግሪ	683085	1.60	36	ቻብላዊ	44129	0.10
9	ሀዲያ	643512	1.51	37	ዶርዜ	43924	0.10
10	አፋር	583120	1.37	38	ቡርጂ	43259	0.10
11	አገው	489834	1.14	39	ኮንታ	39305	1.09
12	ጋሞ	463933	1.09	40	ሻንቅላ	38731	0.08
13	ጌዲኦ	455408	1.07	41	ፈላሻ	34056	0.08
14	ከፋ	443209	1.04	42	ጉሙዝ	33833	0.08
15	ከምባታ	432812	1.02	43	ደሳች	32629	0.08
16	ደመቱ (ደወሮ)	275552	0.65	44	ጊዶሌ	31048	0.07
17	ትግንት	169168	0.40	45	ግሌ	30887	0.07
18	ጎፋ	154041	0.36	46	ቪክ	30763	0.07
19	ሳሆ	144485	0.34	47	አኙዋክ	30499	0.07
20	ቤኻ	124342	0.29	48	አደሬ	29518	0.07
21	ቤንች	123034	0.29	49	ኑዌር	27827	0.07
22	የም	115906	0.27	50	ሐመር	26759	0.06
23	አሪ	109124	0.26	51	መሎ	26087	0.05
24	ኩናማ	99999	0.24	52	ዲዚ	22329	0.05
25	ኮንሶ	94719	0.22	53	ገሞዳ	20122	0.05
26	ቢለን	88453	0.21	54	ሺናሻ	20002	0.05
27	አላባ	83839	0.19	55	ሌሎች	727310	1.70
28	ኮይራ	69852	0.16	56	የውጭዜጎች	9041	0.02
					ድምር	42616876	100%

Source: The 1984 Population and Housing Census Commission of ethiopia (1991)

ሠንጠረዥ 3
በ1994-97 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት

ክልል	የሕዝብ ብዛት	ሃይማኖት					
		ኦርቶዶክስ	ፕሮቴስታንት	ካቶሊክ	ሙስሊም	ኦሮማዊ	
አዲስአበባ	2,121,737	1,732,374	81,759	16,448	267,693	385	
አርማጂያ	18,737,820	7,621,727	1,188,310	10,310	8,178,085	778,359	
ኦሮሬ	13,834,297	11,264,297	11,392	937	2,541,834	2,734	
ደቡብ ብሔሕ	10,371,192	2,862,734	3,611,583	307,604	1,735,214	594,374	
ትግራይ	3,136,267	2,992,305	1,136	12,489	727,657	53	
ሐረሪ	131,139	49,554	1,231	603	78,952	34	
ድሬዳዋ	151,864	86,777	2,668	1,818	158,871	11	
ቤንሻንጉል ጉሙዝ	460,459	160,079	26,917	2,532	202,970	60,346	
ጋምቤላ	162,397	39,187	71,478	5,205	8,362	16,699	
ሶማሌ	3,382,762	31,586	3,451	3,988	3,340,101	2,093	
አፋር	1,097,064	42,448	4,765	944	1,048,710		
ጠ/ ድምር	53,382,938	26,783,468	6,305,690	459,918	16,588,539	2,467,088	
	53,000,000	27,000,000	6,000,000	500,000	17,000,000	2,500,000	

ምንጭ በ1994-97 የቤትና ሕዝብ ቆጠራ ከ11 ብሔራዊ ክልሎች ዘጠ በለቀማ የተጠና

5. የሰብአዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ በኢትዮጵያ ታሪክ

የጦርነትና የሰብአዊ መብት ቅራኔ

የታሪክ እውቀትና እውነት በስልታዊ ሙያና ትምህርት ተመር ምሮ የሚታወቀው በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች በተፈጸመ የሥራ መረጃና ሚዛን ነው። በሌላ ቃል የታሪክ ትምህርት መነሻና መሠረት በተወሰነ ሥፍራ፥ ጊዜና ተግባር የተፈጸመ የሰዎች ሥራ ነው። በዚህ አጭር ትርጉም መሠረት ታሪክ ረቂቅ የተፈጥሮ ክስተት ወይም ምስጢራዊ የአማልክት ተአምር ሳይሆን በሥፍራና በጊዜ የሚገለጽ ሰብአዊ ተግባርና ማኅበራዊ ትምህርት ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ በተለይ ላለፉት 700 (1270-1974) ዓመታት ከአገር ውጭ የመጡና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖትና የቋንቋ አስተማሪዎች በአገር ውስጥ ከሰለሞ ናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎች ጋር በእምነትና ትምህርት ተሰማም ተው የኢትዮጵያን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖ ቶችና ባህሎች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ከይሁዳውያኑ የፍጥረትና የሃይማኖት ትምህርት ጋር በሥፍራና በጊዜ በማያያዝ የአገሪቱን ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ በዓመተ ዓለም በአንደኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ አጋማሽ (1000-500) የፈጠሩት ባለቤቶችና ጌቶች ከኢየሩ ሳሌምና ከምድረ አረቢያ የገቡ «ምርጥ» ሴማዊ የአይ ሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው ብለው አስተምረዋል።

በዚህ የግብፅና የአውሮፓ አስተማሪዎች ትምህርት መሠረት፥ የኢትዮጵያ የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎች መላ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አዋማዊ፥ እስላማዊና አሪታዊ ሕዝቦችን፥ ቋንቋዎችን፥ ሃይማኖቶችንና ባህሎችን በሙሉ ለመቆጣጠርና ኢትዮጵያ በሚል ስም የራሳቸውን አህጉራዊ ማኅበረሰብ፥ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ታሪክ ለመፍጠር ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ባከሄዱት የጦርነትና የጭቆና ፖሊሲ የሰሜን/ፈላሻ፥ የሸዋ፥ የህዲያ፥ የዳሞት፥ የይፋት፥ የደዋሮ፥ የአርባኒና፥ የሻርካ፥ የባሌ፥ የአዳል፥ የዜይላ፥ የፈጠጋር፥ የአውሳ፥ የእናርያ፥ የከምባታ፥ የአይመላል፥ የጉራጌ፥ የጋፋት፥ የበሻ፥ የጃንጀሮ/የም፥ የወላይታ፥ የጋሞ፥ የቀቤና፥ የጊቤ፥ የሐረሪ፥ የከፋ መንግሥታትን ጨምሮ ብዙ አገሮችንና ሕዝቦችን በባሪያ፥ በጉበር፥ በኦፍጠኛ፥ በጢስኛና በባላባት ሥርዓቶች እንደገዙና ቋንቋዎችን፥ ሃይማኖቶችንና ባህሎችን "ጨፍልቀው" ለማጥፋት ሁለአቀፍ የፖለቲካና የሕግ እርምጃዎችን እንደወሰዱ ራሳቸው በዜና መዋዕሎችና በቅዱሳን ጽሁፎች ቀርፀው ለትውልድና ለታሪክ በደፋ ቆመውቃዋል።

በዚህ የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና ታሪክ የጦርነትና የጥፋት ሥርዓ ታዊ ምንጭና መነሻ አህጉራዊ የመንግሥት ሥርዓት ነው። በዚህ ጥናት ተደጋግሞ እንደተገለጸው፥ የቅርጽና የአድገት ደረጃ ልዩነት ሳይደረግ በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ መንግሥት አንድ የተወሰነ የመሬት ክልል፥ የመሬቱ ባለቤት ሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ሕጋዊ መስተ ጋብር ነው። የዚህ የመንግሥት ዋናው መሠረትና መግለጫ የፖለቲካ ሥልጣን ነው። በምንም ሥፍራና ሥርዓት የፖለቲካ ዓይነት የግድ የመንግሥትና የጎብረተሰብ ዓይነትና የዕድገት ደረጃ ይወስናል። ባጭሩ የመንግሥት ሥልጣን በአንድ በተወሰነ መሬትና ሕዝብ ላይ በሕይወትና በንብረት ጉዳዮች ይግባኝ የማይኖረውን የመጨረሻ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚችል የበላይ ኃይል ነው። ይህ ወሳኙ የመንግሥት ሥልጣን በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ ከሶስቱ በአንዱ መንገድ ማለትም ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ትውፊታዊ የሥልጣን ውርስ ወይም በመሣሪያ ኃይል ወይም በዲሞክራሲያዊ የሕዝብ ውሳኔ ሊገኝ እንደሚችል ታሪክ ጨምሮ ያስተምራል።

የመንግሥት ሥልጣን የሚገኝበት መንገድና መሣሪያ ደግሞ ዘውዳዊ ይሁን ወታደራዊ ወይም ሕዝባዊ የአንድ መንግሥትን ዓይ ነት፥ ድርጅትና ተግባር ይወስናል። በዚህ ረገድና ተግባር የመን ግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነና የሚሆን ኃይል ራሱ በራሱ የመንግሥት ሥልጣን ሉአላዊ ምንጭም ባለቤትም ነው። በመሆኑም በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለ ቤት ያልሆነና የማይሆን ሕዝብ ነፃና የራሱ ጌታ የሆነ ሕዝብ ነው ሊባል አይችልም። የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት ያልሆነና የማይሆን ሕዝብ ደግሞ ሰብአዊ ክብሩንና መብቱን፥ ሕይወቱንና ንብረቱን የሚጠብቅበት የሚከላከልበት መንገድና መሣሪያ የለውም። የመንግሥትን ዓይነት፥ ድርጅትና ተግባር በሚመለከት ደግሞ ከፖለቲካ ሥርዓትና ሥልጣን አኳያ መንግሥት ሥልጣኑና ተግባሩ በተለያዩና ሉአላዊ በሆኑ ማለትም በመብትና በግዴታ እኩል በሆኑ የፖለቲካ አካላትና ኃይሎች መካከል የማይከፈል አህጉራዊ የተማከለ መንግሥት ወይም ሥልጣኑ በተለያዩ በመብትና በግዴታ እኩልና ሉአላዊ በሆኑ የፖለቲካ አካላትና ኃይሎች መካከል የሚከፈል ፌደራላዊ ጎብረመንግሥት ሊሆን ይችላል። መንግሥት አህጉራዊም ሆነ ፌደራላዊ የራሱ ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የሚከሰትና የሚከሰም ማኅበራዊ ሥርዓት ነው።

በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ ባለው በአንድ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረ ተሰብ ላይ የተማከለ አህዳዊ መንግሥት በጎብረተሰቡ ላይ በኃይል የተመሠረተ የጭቆና ኃይልና ሥርዓት እንደሆነና እንደሚሆን ታሪክ ያስተምራል።

ምክንያቱም የበህውርታዊ ጎብረትና የአሃዳዊ መንግሥት መስተጋብር ሁልጊዜ ራሱ በራሱ የቅራኔ የግጭትና የመከራ ሥርዓት ነው። በበህውርታዊ ጎብረተሰብና በአህዳዊ መንግሥት ቅንጅት በውርስ ሆነ በኃይል ወይም በምርጫ የሚገኘውን የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ይዘ የሚገዝው ኃይል ሊመጣ የሚችለው ከአንድ ከተወሰነ የጎብረተሰብ ክፍል፥ ወገን፥ መደብ ነው።

በመሆኑም በአንድ በህውርታዊ ጎብረተሰብ የገዥው መደብ ይግባኝ የሌላውን የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ይዘ በጎብረተሰቡ ዘንድ የሁሉን ወገኖች ሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮችንና ፍላጎቶችን በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እና አሠራር በእንድነትና በእኩልነት ለማከበርና ለማስከበር አይች ልም። አቅምም አይኖረውም።

ስለሆነም በአንድ በህውርታዊ ጎብረተሰብ አህዳዊ የተማከለ የመንግሥት ሥልጣን የሚይዘው ኃይል በፖለሲና በተግባር ወገኖችና አካባቢያዊ ይሆናልI ብሎም በፖለቲካ፥ በሥርዓት፥ በመብት፥ በጥ ቅም፥ በክብር፥ በታሪክ፥ በህብትና በኩል ጉዳዮች ምዕክልና ፖሊሲ ያካሄዳል። በሥርዓቱና ቁሁኔታው አስገዳጅነት ወገኖችና ጨቋኝ ኃይል ይሆናል። በይፋ የሚነገረውን በተዮሪና በቃለመፈክር የሚሰብከውን አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳይ በወገኖች ተግባሩ ያፈርሳል። በጎብረተሰቡ ዘንድ በአንድ በኩል ብሔራዊ የአንድነት፥ የፀጥታና የክብር ዓላማና ጉዳይ ይሰብክል። በሌላ በኩል ግን በጎብረተሰቡ ዘንድ ዲሞክራሲያዊ እኩልነትና ማኅበራዊ ፍትህ ተግባራዊ እንዳይሆን ያደርጋል። በመሆኑም በጎብረተሰቡ ዘንድ ማኅበራዊ ሰላምና ሕዝባዊ አንድነት አይገኝም። ማኅበራዊ ዕድገት፥ ፍትህና እኩልነት አይገኝም። ከዚህም የተነሳ በአህዳዊ ኃይሎች ላይ የሕዝቡ ጥላቻና አመጽ ይቀሰቅሳል። በዚህ ሁኔታ በበህውርታዊ ጎብረተሰብ የአህዳዊ መንግሥት ሕይወትና ተግባር የሚወሰነው በኃይል ብቻ ይሆናል።

ባጭሩ እንደ ኢትዮጵያ ባለው በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት የፖለቲካ ምዕክልና ፖሊሲና ተግባር ማለት የኃይልና የጭቆና ሥርዓት ስለሚሆን በጎብረተሰቡ ውስጥ የአመጽ ሁኔታዎችን ኃይሎችንና እንቅስቃሴዎችን

ይፈጥራል። በዚህ ወቅትና ሂደት ለገዥው መደብ በአመጽ ሀሳቦች፥ ኃይሎችና እንቅስቃሴዎች ላይ በአገርና በሕዝብ ስም፥ በአንድነት በሰላምና በፀጥታ ስም የኃይል ፖሊሲና ፖለቲካ መከተልና መጠቀም የሥርዓትና የሕይወት ጉዳይና ግዴታ ይሆናል። ባጭሩ በጎብረተሰቡ ዘንድ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ እስኪደረግ ድረስ ማለትም ለብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች እስኪከበሩ ድረስ የሕዝቡ ተሳማጅ የመከራና የአመጽ ሕይወት ይቀጥላል።

የሰብአዊ መብትና ነፃነት ትምህርት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

የሰብአዊ መብትና የነፃነት ምዴሎች

1.የተፈጥሮ ሕግ ሞዴል

ከሰው ልጅና ከሥልጣኔ ረጅም ታሪክ እንደሚታወቀው፥ በየ ትም ሥፍራና በምንም ጊዜ እንደሰብአዊ ነፃነትና እንደ ዲሞክራሲያዊ መብት ያለ የፍልስፍና መሠረተ-ሀሳብ፥ እምነትና ትምህርት ሁልጊዜ የአንድ በሥፍራና በጊዜ የተወሰነ ስልተምርትና ሥርዓተ ማኅበር መግለጫ ነው። መሠረተ-ሀሳቡም የሚፈጠረው በጎብረተሰቡ ዘንድ በአርሶና በአዲስ ማኅበራዊ ሥርዓቶች መካከል ግለትም በሁለት ተከታታይና ተቃራኒ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች መካከል በሚፈጠረው ሥርዓታዊ ቅራኔና ግጭት ምክንያት ነው።

በዚህ ረገድ የሰብአዊ መብትና ነፃነት መሠረተ ሀሳብ የፖለቲካ ፍልስፍና ሆኖ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው ከሰባት ምዕተ ዓመታት በፊት በአውሮፓ አገሮች በአሮጌው ዘውዳዊና ሃይማኖታዊ የፊውዳሊዝም ሥርዓትና በአዲሱ የቡርጂ ካፒታልዝም ሥርዓት መካከል በተፈጠረው የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ቅራኔና ግጭት ሂደት እንደሆነ ታሪክ ያስተምራል።

በዚህ ታሪካዊ የሽግግር ዘመን በተለይ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን የፊውዳልዝምን ሃይማኖታዊ መሠረተ-ትምህርትና ርዕዮተ ዓለም ውድቅ በማድረግ የሕይወትና የሕልውና መነሻና መሠረት የተፈጥሮ አካባቢና ሁኔታ ነው የሚል አብዮታዊ መሠረተ ሀሳብና ትምህርት አስተማሩ። የሰው እውቀት መነሻ በሰው አዕምሮና በተፈጥሮ አካባቢ መካከል የሚካሄደው ተግባራዊ መስተጋብርና ዕድገት ነው በማለት ሰውን፥ ተፈጥሮን፥ እውቀትን፥ ማህበራዊ ሥርዓትንና ንብረትን በሚመለከት ፀረ-ፊውዳልዝም የሆነ አብዮታዊ የግንዛቤ ሀሳብና ትምህርት አስፋፉ። ተፈጥሮ፥ ሰውና ማህበራዊ ሥርዓት ሁሉም ከመሬት ጋር በአንድ ላይ ሕያው፥ አዳጊና

ተንቀሳቃሽ፥ ብሎም ቋሚ የሕይወትና የኃይል ምንጭ በሆነው ፀሐይ ዙሪያ ዘውትር የሚንቀሳቀሱ ነገሮችና አካላት እንደሆኑ አስተማሩ። የሰው ልጅ ሲወለድ አዕምሮው ባዶ ጥቁር ሰሌዳ ብቻ እንደሆነ ብሎም በባዶ የአዕምሮ ሰሌዳ ላይ የሰው አሳብና ቋንቋ እውቀትና ትምህርት በተግባራዊ ሥራና ልምድ በሥፍራና በጊዜ ቀመር እንደሚፈጠርና እንደሚያድግ ገለጹ።

በዚህ የአውሮፓ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን ትምህርትና ግንዛቤ መሠረት፥ የሰው ልጆች የዘር፥ የጸታ፥ የቀለም፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም በተፈጥሮ ነፃ፥ እኩልና ወንድማማች ናቸው። ሰው ራሱንና አካባቢውን በአዕምሮ መሣሪያዊው የሚያውቅና የሚለወጥ ሕያው አካል ነው። በዚህ ሕያውና አዳጊ የተፈጥሮ ሀሳብ፥ ሕግና ትምህርት መሠረት የሰው ልጅ የግል ሕይወትና ንብረት ያለባለቤቱ ፈቃድና ፍላጎት በማንም ሌላ ሰው በምንም መንገድና ሥርዓት የማይደፈር ውድና ክቡር ሃብር ነው ተባለ። የሰው ልጅ የግል ሀብት የግለሰቡ ጥንካሬ፥ ትጋትና ብርታት ውጤት ነው። ጎብረተሰብ የግለሰቦች ስብስብ፥ ድርጅት ነው። በመሆኑም መንግሥት በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ ሊጋራ ደህንነትና አገልግሎት በሃዋሪ ዜጎች ሉአላዊ ፍላጎትና ፈቃድ የሚመሠረት የፖለቲካ ሥርዓት ነው። የሕዝቡ የግልና የጋራ ሕይወት፥ ንብረትና ክብር ከሕግ አኳያ የሚከበረ ውና የሚዳብረው በዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና አሠራር እንደሆነ፥ ዲሞክ ራሲ ራሱ የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣንና ሥርዓት እንደሆነ ተገለጸ።

ይህ በተፈጥሮ ሕግና ተግባር ሞዴል የተመሠረተው የቡርሂ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን ትምህርት በምዕራቡ ዓለም በአንድ በኩል በአሮጌው የፊውዳሊዝም ሥርዓት ላይ ለአዲሱ የካፒታሊ ዝም ሥርዓት ድል የፖለቲካና የርዕዮተዓለም መሠረትና መሣሪያ ሆነ። በሌላ በኩል ደግሞ የካፒታሊዝም ሥርዓት ራሱ በራሱ የቡርሂና የወዛ ደር መደቦች መካከል ቅራኔና ግጭት ፈጠረ። ቀጥሎም የኢምፔ ሪያሊዝምን ዓለማቀፋዊ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓትና ዘመን አስከተለ።

2.የማኅበራዊ ሥርዓት ሞዴል

በወዛደር ምሁራን ማርክስ፥ ኤንግልስና ሌኒን እመለካከት ጸረ-ፊውዳሊስት የቡርሂ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን እንደ ገመቱት የተፈጥሮ ሞዴልና ሚዛን የሰው ልጅ ማህበራዊ ሥርዓት፥ ሕይወት፥ ክብርና መብት የሚመዘንበት ታሪካዊ ሚዛን አይደለም። የሰው ልጅ ህልውና፥ ሕይወት፥ ክብርና መብት የሚመዘነው በተፈጥሮ ሞዴልና ሚዛን ሳይሆን በማህበራዊ ሥርዓት ተግባርና ፋይዳ ነው። የማህበራዊ ሥርዓት፥ መሻሻና መሠረት ደግሞ የሰው ልጅ ሥራ ነው።

የሰው ልጅ ህልውና፥ ሕይወት፥ ክብር፥ መብትና ሀብት መሠረቱና ምንጩ ማኅበራዊ ሥራ ነው። በመሆኑም በተፈጥሮ ሞዴልና በግል ንብረት የተመሠረተው የቡርሂው ካፒታሊስት ሥርዓት፥ ማኅብረሰብና መንግሥት ኢሰብአዊ የሆነ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት፥ ጎብረተሰብና መንግሥት ነው ተባለ።

ስለሆነም የካፒታሊዝም ሥርዓት ብሎም የቡርሂው ጎብረተሰብና መንግሥት በወዛደሩ አብዮታዊ አመጽ ተደምስሶ በምትኩ የዘር፥ የጸታ፥ የቀለም፥ የዕድሜና የሀብት ልዩነትና ምርጫ ሳይደረግ የሰው ልጅ መሠረታዊ አንድነትና እኩልነት፥ ክብርና መብት የሚከ በርበት አዲስ ወዛደራዊ ሶሻሊስት ሥርዓት፥ ጎብረተሰብ፥ መንግሥ ትና ርዕዮተዓለም በኃይል መገንባት አለበት አሉ እንግርክስ።

በዚሁ የወዛደር ምሁራን ትምህርት መሠረት በ1917 በሌኒን መሪነት ሶሻሊስት አብዮትና ሥርዓት በዛሩ ፊውዳል ሩሲያ ተካሄደ። በሚቀጥሉት 70 ዓመታት ዓለም በሁለት ተፃራሪ የካፒታልዝምና የሶሻልዝም ሠፈሮች ተከፈለ። በሶቭዬት ጎብረት የተመራው የሶሻል ዝም ሰፈር በወዛደራዊ ዓለማቀፋዊነት ትምህርት መሠረት ባካሄደው ርዕዮተ ዓለማዊ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ በምዝብር የዓለም ወዛደሮችና በምዕራቡ ካፒታሊስት መንግሥታት የኮሎኒያሊዝም-ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ሥር በአፍሪካ፥ በእስያና በላቲን አሜሪካ አህጉራት በጦር ኃይልና በፖለቲካ ተጽዕኖ ቦሚዝ ሕዝቦች ስም የሰው ልጅን መሠረታዊ ክብር፥ መብትና ነፃት በመሚመለከት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ታሪክ ያስተምራል።

3. የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሞዴል

በተጠቀሰው የካፒታሊዝምና የሶሻሊዝም ኃይሎች ቅራኔና ግጭት ዘመን በተለይም ከ1920ዎቹ እስከ 1940ዎቹ ድረስ በተዛማጅ የጦርነትና የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሥርዓታዊ ክስረትና ውድቀት የደረሰባቸው የቡርሂ ፋሽስቶች ማለትም የከሰሩ ከበርቴዎች የካፒታ ሊዝም ሥርዓትን ከወዛደራዊ አብዮትና ከኮሚኒዝም ሥርዓት እናድነ ዋሰን በሚል መነሻ በተለይም በጀርመንና በኢጣሊያ መንግሥታዊ አምባገነኖች መሪነት ባካሄዱ ጸሮወዛደርና ጸረ-ሶሻሊዝም ጦርነት በመላው ዓለም ላይ ስድስት ሚሊዮን የአውሮፓ አይሁዶችን ጨምሮ የብዙ ለላማዊ ሕዝቦችን ሕይወትና ንብረት በኢሰብአዊ መንገድና አሠራር አጠፉ። የለውን ልጅ ሕይወትና ንብረት በአረመኔአዊ ጭካኔ አጠፉ።

ከታሪክ አኳያ ይህ ኢሰብአዊና ኢዲሞክራሲያዊ የሆነ የፋሽዝም ሥርዓትና ተግባር ክስተትና ውድቀት ሰወደፊቱ በዓለም

ላይ ዳግም እንዳይነሳ ያደርጋል ተብሎ የታመነበትን የዓለም መንግ
ሥታት ድርጅትና የድርጅቱንም የ1948 ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ
መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር አስከተለ።

የ1948 የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶችና
ነፃነቶች ቻርተር ምሥረታ

በ1948 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የሰብአዊ
መብቶችና ነፃነቶች አዋጅ መሠረት፥ ሰዎች ሁሉ ሲወለዱ በተፈጥሮ
አቸው ነፃና እኩል ናቸው። እኩል ሰብአዊ ነፃነት፥ መብትና ክብር
አላቸው። ስለሆነም የዘር፥ የቀለም፥ የጸታ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥
የፖለቲካ አቋም፥ የብሔር፥ የመደብ፥ የንብረት፥ የልደት ወይም
የማዕረግ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም የሰው ልጆች በአዋጁ
የተዘረዘሩ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች እኩል
ባለቤቶችና ተጠቃሚዎች ናቸው። በመሆኑም ማንም ሰው የሕይ ወት፥
ሶፃ ነትና የደህንነት መብት አለው። ማንም ሰው በባርነትና በገባርነት
አይገዛም። ማንም ሰው ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ መሲቃየት፥ መዋረድና
መቀጣት የለበትም። ማንም ሰው በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ በሕግ
ፊት ሉአላዊ ክብሩ የመታወቅ መብት አለው። ሁሉም ሰዎች በሕግ
ፊት እኩል ናቸው። ሁሉም ሰዎች እኩል የሕግ ዋስትና አላቸው።
ማንም ሰው በሕግ የታወቁ መሠረታዊ፥ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ
መብቶቹና ነፃነቶቹ በማንም ሲጣሱና ሲደፈሩ ሥልጣንና መብት
ባላቸው ፍርድ ቤቶች የፍትህ ብይን መብት አለው። ማንም ሰው
በሕገወጥ መንገድ አይያዝም፥ አይታሰርም፥ አይከሰስም፥ አይሰ
ደድም። ማንም ሰው በነፃ ፍርድ ቤቶች የፍትሐዊ ዳኝነትና ብይን
መብት አለው። ማንም በወንጀል ተግባር የተጠረጠረ ሰው ከፍርድ
ቤት ውሳኔ በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት አለው። ማንም
ሰው በቅድሚያ በሕግ ጥፋት መሆኑ ያልታወቀ ድርጊት በመፈጸሙ
በሕግ ያለመቀጣት መብት አለው።

የማንም ሰው የግል፥ የቤት፥ የቤተሰብ፥ የመልእክት ምስጢር
እና የስም ክብር በሕግ የተጠበቀ ነው። ማንም ሰው በመንግሥቱ
ግዛት ውስጥ የመንቀሳቀስና የመኖር መብት አለው። ማንም ሰው
በፈቃዱ ከአገሩ የመውጣትና ከውጭም ወደ አገሩ የመመለስ መብት
አለው። ማንም ሰው ባገሩ ሆኖ ከሚደርስበት መከራ በሌላ አገሮች
የጥገኝነት መብት አለው። የፖለቲካ ስደተኞች ሳልሆኑትና የተመድን
ዓላማዎችና መርሆዎች ለማያከብሩ ሰዎች ግን የጥገኝነት መብት
አይፈቀድም። ማንም ሰው ዜግነት የማግኘት መብት አለው። ማንም
ሰው በሕጋዊው መንገድና ሥራ የዜግነት መብት አያጣም።

ለትዳር የደረሱ ወንዶችና ሴቶች ቢጋብቻ ጥያቄ የዘር፥ የዜግነት
ወይም የሃይማኖት ገደብ ሳይደረግ የመጋባት መብት አላቸው። ጋብቻ
በትዳር ጓደኞች ሙሉ ስምምነት ብቻ ይፈጸማል። ቤተሰብ የጎብረ
ተሰብ መሠረት በመሆኑ የመንግሥት ጥበቃ ይደረግ ለታል። ማንም
ሰው በግል ወይም በጋራ ሥራ ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብት
አለው። ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ ንብረቱን አያጣም። ማንም
ሰው የሀሳብ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ማንም ሰው
ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግል ወይም ከሌላ ሰዎች ጋር በይፋ
የመኩተልና በሰላማዊ መንገድ የማስተማር መብት አለው። ማንም ሰው
የራሱን አስተያየት የመያዝና የመግለጽ መብት አለው። ማንም ሰው
በሰላማዊ መንገድ ከሌላ ሰዎች ጋር የመሰብሰብና የመደራጀት መብት
አለው። ማንም ሰው የማንም ድርጅት አባል እንዲሆን አይገደድም።

ማንም ሰው በቀጥታ ወይም በነፃ ምርጫ በተመረጡ ወኪሎች
አማካይነት በአገሩ መንግሥት ጉዳይ የመሳተፍ መብት አለው።
ማንም ሰው በአገሩ በሕዝባዊ አገልግሎት በእኩልነት የመሳተፍ መብት
አለው። የመንግሥት ሥልጣን መሠረቱ የሕዝብ ፈቃድ ነው። ሉአላዊ
የሕዝብ ፈቃድ ወቅታዊ፥ ሀቀኛ፥ ምስጢራዊ፥ አጠቃላይ፥ እኩልና ነፃ
በሆነ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል። ማንም ሰው
የጎብረ ተሰቡ አባል በመሆኑ የማህበራዊ ዋስትና መብት አለው።
ማንም ሰው የመንግሥቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን ለክብሩ እና
ለነፃ ሰብአዊ ዕድገቱ የሚያስፈልጉ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊና የባህላዊ
ጥቅሞችንና አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለው።

ማንም ሰው ሥራ የማግኘት የሥራ ዓይነትን በነፃ የመምረጥ
ተስማሚ የሆነ የሥራ ሁኔታና የሥራ ዋስትና የማግኘት መብት
አለው። ማንም ሰው አለምንም አድሎ ለእኩል ሥራ እኩል የሥራ
ዋጋ የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት
ፍትሐዊና ተስማሚ በሆነ መንገድ ለራሱና ለቤተሰቡ ፍላጎትና ክብር
በቂ ዋጋ የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው ጥቅሙን ለማስከበር
በሙያ ማኅበር የመደራጀትና አባል የመሆን መብት አለው። ማንም
ሰው የማረፍ የመዝናናት የተወሰነ የሥራ ሰዓትና ወቅታዊ የበዓል ዕረ
ፍት መብት አለው። ማንም ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ፥ ለምግብ፥
ለልብስ፥ ለመኖሪያ ቤትና ለሕክምና በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት
መብት አለው። ለእናቶችና ለልጆች ልዩ ጥንቃቄና ዕርዳታ ይደረግላ
ቸዋል። ከጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች እኩል እንክ
ብካቤ ይደረግላቸዋል።

ማንም ሰው የመማር መብት አለው። የትምህርት አገልግሎት ለሰው ዕድገት በብሔር፥ በዘርና በሃይማኖት በተለያዩ ሕዝቦች መካከል የሰብአዊ መብቶችን ጉዳይና የተመድን የሰላም ፖሊሲ በሚያስፋፋ መንገድና አሠራር ይዘጋጃል። ወላጆች ለልጆች የትምህርት ዓይነት የመምረጥ ቀዳሚ መብት አላቸው። ማንም ሰው ከሳይንስ ዕድገትና ምርት ለመካፈል መብት አለው። ማንም ሰው የራሱ ሥራ በሆነ የሳይንስ፥ የሥነጽሑፍ፥ የሥነጥበብ ውጤት የሚገኙ ጥቅሞችን የማስጠበቅ መብት አለው።

ማንም ሰው በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብቶችና ነፃነቶች ሁሉ ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችሉበት ሥርዓት ውስጥ የመኖር መብት አለው። ማንም ሰው የራሱ ሰብዕና በነፃና በተሟላ መንገድና ሁኔታ ለሚያድግበት ጎብረተሰብ ተገዥ የመሆን ግዴታ አለበት። የራሱን መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ የሚያደርግ ማንም ሰው የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ማክበርና ለዲሞክራሲያዊ ጎብረተሰብ የሚያስፈልጉ የሞራል የሕዝባዊ ሰላምና የደህንነት ጉዳዮችንና ግዴታዎችን ማሟላት አለበት። እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የተመድን ዓላማዎችና መርሆዎች በሚቃረኑ መንገዶች ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም። ማንም መንግሥት፥ ቡድን ወይም ሰው እዚህ ከቀረቡ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች አንዱንም ለማጥፋት የሚያስችል መብት በዚህ አዋጅ እንደተሰጠው አድርጎ መተርጎም የለበትም።

የተመድ የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ታሪክ

የታኅሣሥ 1948 የተመድ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር አዋጅ በድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከድርጅቱ 56 አባል አገሮች በ48ቱ ጸደቀ። ስድስት በሶቭዬት ሩሲያ የሚመሩ ሶሻሊስት አገሮች ከሳውዲ አረቢያና ከደቡብ አፍሪካ ጋር በድምሩ ስምንት አገሮች ቻርተሩን አላጸደቁም።

የ1948 የተመድ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር አገልግሎት በሚመለከት በድርጅቱ መድረክ በፖለቲካ ሥርዓትና በርዕዮተዓለም ጉዳዮች ላይ በአሜሪካ በሚመሩ የምዕራብ ካፒታሊስትና በሶቪዬት ሩሲያ በሚመሩ የምስራቅ ሶሻሊስት መንግሥታት መካከል የተፈጠረው ልዩነትና ግጭት በ1980ዎቹ መጨረሻ የሶሻሊዝም ሥርዓት ከሶቭዬት ሩሲያ ኃይሎች ጋር እስኪወድቅ ድረስ በቻርተሩ ዓለማቀፋዊ ይዘትና ተግባራዊነት ላይ ከባድ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ታሪክ ያስተምራል።

በዚህ ረጅም የሽግግር ዘመን በአንድ በኩል በተግራቡ የካፒታሊስትና የሶሻሊስት መንግሥታት መካከል በተፈጠረ የሥርዓት እና

የርዕዮተዓለም ግጭት፥ በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ በኢምፔሪያሊዝም ተዕዕኖ ሥር በነበሩና ዛሬ «ሶስተኛ» ዓለም አገሮች ተብለው በሚታወቁ የአፍሪካ፥ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች በተካሄዱ የነፃነት፥ የአብዮትና የእርስ በእርስ ጦርነቶች በሰላም፥ በነፃነት፥ በአብዮትና በዲሞክራሲ፥ በአገር አንድነትና ክብር፥ በሕዝቦች እኩልነት በመሠረታዊ ዓለማቀፋዊነት ስምና ስብዕት፥ ለምሳሌ በካምቦዲያ ሽብርተኞች የተጨፈጨፉ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎችን እንዲሁም የረሃብ፥ የችግር፥ የበሽታ፥ የጦርነት፥ የፖለቲካ ሽብር፥ የእሥራትና የስደት ሰለባ የሆኑ ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ጨምሮ በዓለም ደረጃ ቁጥራቸውን በአሀዝ መገመት የማይቻል ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች ሰብአዊ መብትና ነፃነት አጥተው እንዳለቁ አይረሳም።

6. የኢትዮጵያ ታሪክ ድልና ትንሣኤ

የሕዝብ የመብት ትግልና ድል

በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ (1950-2000) በአንድ በኩል ብዙ የሰነድ፥ የአርኪኦሎጂ፥ የሊንጉዊስቲክስና የፖሊአንቶሎጂ መረጃዎች ግኝትና ትምህርት፥ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ አብዮት በአገሪቱ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና ታሪክ መሠረታዊ የሥልተምርት፥ የሥርዓተ ማኅበር፥ የፖለቲካ፥ የሥልጣን፥ የሕግ፥ የዕውቀት፥ የአመለካከት፥ የግንዛቤና ትምህርት ለውጥና ዕድገት እንዳስከተሉ በዚህ *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ታሪክ* በስፋትና በዝርዝር ተብራርቷል።

በጥናቱ ግኝትና ትምህርት መሠረት ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ምድር ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የሰው ልጅ ራሱ በአካልና በአእምሮ መሣሪያዎቹ አድጎና ዳብሮ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተበት ታሪካዊ ሥፍራ እንደሆነ በፓሌአንቶሎጂ መረጃና ትምህርት መሠረት ዓለማቀፋዊ እውቅና አግኝቷል። በዚህ ረገድ በቅድመ ታሪክ የሰው ልጆችና ቋንቋዎች ከኢትዮጵያ የመነሻ ምድር ቀይ ባሕርን በፍለሳና በሰፈራ እንቅስቃሴ ተሻግረው በእስያና በአውሮፓ አህጉራት እንደሰፈሩ የሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

በዚህ አካያ ሴማዊ የአፍሮ እስያ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች በቅርቡ ቅድመ-ታሪክ ማለትም ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ቀይ ባሕርን ተሻግረው በአረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ እንደሰፈሩ አሁንም የሊንጉዊስቲክስ ሳይንስ ጨምሮ ያስተምራል። በዚህ የሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት መሠረት የኢትዮጵያ አራቱ ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የክፍለ አህጉሩ ነባርና ጥንታዊ ሕዝቦች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ሰዎች በዓመተ ዓለም በአንደኛው ሚሊኒየም (1000-500) ከኢየሩሳሌምና ከአረቢያ የገቡ ሴማዊ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው ብለው የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች ባለፉት 700 (1270-1974) ዓመታት ያስተማሩት መላምት የፈጠራ ተረት ሆኖ ቀርቷል።

በሌላ በኩል እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙ የሰነድ፥ የአርኪኦሎጂና የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎች ጨምረው እንደሚያስተምሩ፥ በቅርቡ-ዘመነ-ታሪክ ማለትም ባለፉት ስድስትና ሰባት ሺህ ዓመታት የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነባር የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ከጥንቱ የግብፅ፥ የአረቢያ፥ የግሪክና የሮም ሕዝቦችና መንግሥታት

ጋር በንግድና በሃይማኖት በተለያዩ መንገዶችና ደረጃዎች ቢያንስ ለ5000 ዓመታት ሉአላዊ መስተጋብርና መወራረስ ነበራቸው።

ነገር ግን ከዛሬ የኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረተሰብና ታሪክ ከስተትና ዕድገት አኳያ በአጠቃላይ መንገድ ሲታይ፥ የዛሬ በሥፍራና በጊዜ ያልተቋረጠ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ሕዝቦች ዘመናዊ ታሪክ የተከሰተው ቢያንስ ከ2500 ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ሰሜን ደጋአምባ ምድር ላይ በየሀ-ደአማት ነው። በዚህ ጥናት ተደጋግሞ እንደተባለው፥ በክፍለ አህጉሩ ከየሀ-ደአማት እስከ ዘመነ አዲስ እበባ ድረስ ባለፉት 2500 ዓመታት በአምስቱ የደአማት፥ የሳባ፥ የግሪክ፥ የግዕዝና የአማርኛ ቋንቋዎች ተጽፎ የተገኘው የኢት ዮጵያ በህውርታዊ ታሪክ በጠባብ መልኩ ሲገመገም የነገሥታትና የካህናት ጥምር የፖለቲካና የሃይማኖት ዘገባ ነው።

ይሁን እንጂ ከሰፊው የኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረተሰብ ከስተትና ዕድገት አኳያ ሲገመገም ደግሞ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች የጋራ ታሪክ ነው። የብዙ ሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች ታሪክ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ረጅምና በህውርታዊ ታሪክ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች የመስተጋብርና የመወራረስ ታሪክ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር በተለይ ባለፉት 1700 ዓመታት ከብዙ ተከታታይ መንግሥታዊ ሥርዓቶችና ሕዝባዊ የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች ጋር ለኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና ታሪክ የዛሬውን ጎብረመልክ፥ ቅርጽና ይዘት የሰጡ ሶስት ማኅበራዊ ኃይሎች መለኮታዊና አህጉራዊ የሆኑ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ናቸው።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ጎብረተሰብ በግብፅና በአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች እምነትና ትምህርት የሚመሩ የቀድሞ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎች በግምት ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት የአገሪቱን አዋማዊ አስላማዊና አሪታዊ ሃይማኖቶችና ሕዝቦች በሙሉ ተቆጣጥረው የራሳቸውን አህጉራዊ የክርስቲያን ማኅበረሰብ፥ መንግሥት፥ ቋንቋ፥ ሃይማኖት፥ ባህልና ታሪክ ለመገንባት ባካሄዱት የጦርነትና የጭቆና ፖሊሲና ተግባር ሕዝቦችን በጥቂ አገራቸውና መሬታቸው ላይ በባሪያ፥ በገባር፥ በባላባት፥ በጪሰኛ፥ በጉልተኛና በአፍጠኛ ሕጎችና ሥርዓቶች ለምዕተ ዓመታት ሲገዙ እንደኖሩና ይህም ረጅም የመከራ ዘመንና ሥርዓት በመጨረሻ በ1974 ሕዝባዊ አብዮት ከዘውዳዊ መንግሥትና

ሥርዓት ጋር እንዴት እንደተወገደ ይታወሳል።

የታሪክ ትንሣኤና ትምህርት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ

ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥትንና ዘውድን ከገሸሹው መደብ ጋር በማስወገድ የኢትዮጵያ ብሔሮችን፥ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን በሙሉ የመሬት፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖትና የባህል ባለቤቶችና ጌቶች ያደረገው የኢትዮጵያ አብዮት እንዲሁም የዘር፥ የጎሳ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የሁሉንም ብሔሮች፥ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ በአገራዊ አንድነትና በዲሞክራሲያዊ እኩልነት ሚዛን አጥንቶ ለማወቅ፥ ለመጻፍና ለማሳወቅ አመራሪያዊ እኩልነት ሚዛን አጥንቶ ለማወቅ፥ ለመጻፍና ለማሳወቅ አመቺና አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን፥ መንገዶችን፥ መብቶችንና ነፃነቶችን አስገኝቷል።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል የዘር፥ የጎሳ፥ የቋንቋ፥ የፖለቲካ፥ የሃይማኖት፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የብሔሮችን፥ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪክ በአገራዊ አንድነትና በዲሞክራሲያዊ እኩልነት በአዲስ መልክና መንገድ እንደገና ለማጥናት፥ ለማወቅ፥ ለመጻፍና ለማሳወቅ በወደቀው ዘውዳዊ ሥርዓት በተፈጠሩ ብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶችና እንቅፋቶች የማይቻል ነገር ነው ባይባልም እጅግ በጣም አስቸጋሪና ውስብስብ ተግባር እንደ ሆነ በሚመለከተው ሁሉ ዘንድ በቅድሚያ በግልጽ መታወቅ አለበት።

በዚህ አኳያ አንደኛ፥ ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት በአንድ በኩል በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብ ላይ በጦር ኃይል የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት የሆኑ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በግብፅና በአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪ ዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ ሥር የነበሩ የቀደሞ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎችና ታሪክ ጸሐፊዎች ከራሳቸው አንድ ማኅበረሰብ፥ ቋንቋ፥ ሃይማኖት፥ ታሪክና ባህል በስተቀር የተቀሩ የሰሜን ምሰራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነባር አዋማዊ፥ ኦሪታዊና እስላማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን በሙሉ በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋዎች በተጻፉ ሰነዶች የእነርሱ ታሪካዊ ጠላቶች እንደሆኑ አድርገው በይፋ መዝግበዋል። በዚህ ሃይማኖታዊ እምነትና ትምህርት መሠረት በ1974 እብዮት እስኪወገዱ ድረስ ሰለሞናዊ ነገሥታትና ገዥዎች በጠላትነት የተፈረጁ ሕዝቦችን በጽ መሬታቸው ላይ በልዩ የባሪያ፥ የጉልበት፥ የጉል ተኛ፥ የመልከኛ፥ የኦፍጠኛ፥ የጢሰኛና የባላባት ሕጎችና ሥርዓቶች ሲገዙዋቸው እንደኖሩ ይታወሳል። ከዚህ ዓይነት መንግሥታዊ ፖሊሲ፥

ሥርዓትና ሰነድ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦችን፥ ቋንቋዎችን፥ ሃይማኖቶችንና ባህሎችን ታሪክ ማጥናትና ማወቅ ምን ያህል አስቸጋሪ ሥራ እንደሚሆን ለማንም አስተዋይ የታሪክ ጸሐፊ፥ አንባቢ፥ ተማሪና አስተማሪ ግልጽ ነገር ነው።

ሁለተኛ፥ በ17ኛው ምዕተ ዓመት የጀርመኑ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁር ዶክተር ሉዶልፍ በአገሩ ሆኖ በኢትዮጵያ አዋማዊ፥ ኦሪታዊና እስላማዊ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ጥላቻ ከታወቁና ኢየሱሳውያን ከተሰኙ የካቶሊክ ሚሲዮናውያንና ከአንድ ኢትዮጵያዊ መኳሴ ተከታያቸው ያገኛቸውን የፖለቲካ፥ የጦርነት፥ የሃይማኖት፥ የቋንቋ መረጃዎች አገናዝቦ በኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ስም የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎችን ተረትና ታሪክ አስመልክቶ ባካሄደው ጅምር ጥናት በኢትዮጵያ ነባር አዋማዊ፥ ኦሪታዊና እስላማዊ ሕዝቦችና በሰለሞናዊ ነገሥታት መካከል ለምዕተ ዓመታት የነበረውን የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የመሬት ጦርነት ከክርስቲያን ነገሥታቱ አኳያ በጎብረ ቀለም ቀርጾ በአውሮፓ የክርስቲያን ዓለም አሰራጨ።

በ1681 የኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ ብሎ ባዘጋጀው መጽሐፍ ዶክተር ሉዶልፍ የኢትዮጵያ አዋማዊ፥ ኦሪታዊና እስላማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን በገዛ አገራቸው ለሰለሞናውያን የክርስቲያን መንግሥትና ሃይማኖት ታሪካዊ ጠላቶች እንደሆኑ አድርጎ ይከሳቸዋል። በተጨማሪም የጀርመኑ ጸሐፊ በተጠቀሰው መጽሐፍ ለሰለሞናዊ ነገሥታት የኢትዮጵያ እስላሞችንና የኦሮሞ አዋማዊ ማኅበረሰቦችን በተለይ ለመዝት የአውሮፓ ክርስትያን መንግሥታት የጠብመንጃ፥ የፖለቲካና የትምህርት እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የዓለም ዝያና ዝት ለሚፈልጉ አውሮፓውያን ገና በዘመኑ አስተምሮዋቸዋል። ዶክተር ሉዶልፍ እንዳለውም በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሰለሞናዊ ነገሥታትና የጦር አበጋዞች በአውሮፓውያኑ ትምህርትና ጠብ መንጃ የኢትዮጵያ እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን እንደ ገዙዋቸው ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።

ሶስተኛ፥ በ19ኛውና በ20ኛው ምዕተ ዓመታት የአውሮፓ የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ ምሁራን በአህጉራቸው ታላላቅ የባህልና የትምህርት ከተሞች፥ ሚዕከላትና ተቋማት በኢትዮጵያ ስም ከአገሪቱ አራት የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ያንዱን ብቻ ማለትም የሴም ቋንቋዎችን ብቻ መርጠው የሚያስተምሩባቸውን የጥናት ክፍሎች መሥርተው የኢትዮጵያን ጥንታዊ መንግሥት፥ ሥልጣኔና ታሪክ በአፍሪካ ምድር ላይ የፈጠሩ ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ የገቡ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው የሚል መላምታቸውን እስከ 1974

የሰለሞናውያን ዘውድና የገዥ መደብ ውድቀት ድረስ ሙያቸው አድርገው ሲሰብኩ ኖሩ። በሌላ በኩል እነዚህ የምዕራቡ ሴሚቲስት የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁራን የአገሪቱን አዋማዊና እስላማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን ታሪክ ከኩሻዊ፥ ናይሎቲካዊና አሞአዊ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ጋር ወደ ተጠቀሱት የጥናት ክፍሎች እንዳይገባ አድርገዋል።

ስለሆነም አሁን በድህረ አብዮት በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በዘር፥ በጎሳ፥ በቋንቋ፥ በፖለቲካ፥ በሃይማኖት፥ በቀለም፥ በባህል፥ በሥፍራና በጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የአገሪቱን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪክ በአዲስና በሁለአቀፍ የጥናት ሥልትና ሚዛን ለጎብረተሰቡ በሚገባ መንገድና ቋንቋ እንደገና ማጥናት፥ መጻፍና ማስተማር ለሁሉም ያገር ዜጋ ባለሙያዎች መብትም ግዴታም ነው።

በዚህ የእውቀትና የእውነት ግንዛቤና ግዴታ ነው ይህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገለጫዎች የተሰኘ ሁለአቀፍ ጥናት ባገርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ የታሪኩ ሉአላዊ ባለቤት ሰሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገልግሎትና ጥቅም እንዲሆን የቀረበው።

በዚህ ረገድና ተግባር በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት በሰፋትና በዝርዝር ተደጋግሞ እንደተገለጸው፥ የኢትዮጵያን ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ከውጭና ከአገር ውስጥ ክርስቲያን አስተማሪዎችና ጸሐፊዎች ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ነፃ ያወጡት ከዘመናዊ የፓሌንቶሎጂና የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎች ጋር የደአማት-አክሱምና የአረብ ጥንታዊ ጸሐፊዎችና ሰነዶች ናቸው።

የተጠቀሱ የውጭና የአገር ውስጥ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች በኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ላይ ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ ያሳደሩት ታሪኩን በመጽሐፍ ቅዱስ ከይሁዳ ውያኑ የፍጥረትና የሰው ዘር መነሻና ስርጭት ትምህርት ጋር በቅርብና በጥብቅ በማያያዝ ነው።

ነገር ግን በሳይንሳዊ የኢቮሉሽን፥ የፓሌንቶሎጂና የሊንጉዊስቲክስ መረጃ ግኝትና ትምህርት መሠረት የሰው ልጅ ታሪካዊ መነሻ፥ ክስተትና ስርጭት የጀመረው ከዛሬ ሶስትና አራት ሚሊዮን ዓመታት በፊት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በኢትዮጵያ የአዋሽ-አሞ ወንዞች ክልል ነው። በሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት መሠረት ደግሞ፥ የዛሬ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ የዓለም ሕዝቦች በፍለሳና በሰፊራ

እንቅስቃሴ ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ቀይ ባሕር ተሻግረው በአረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ የተገኙ ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት በዘመነ-ታሪክ ዋዜማ ነው። በመሆኑም በዓሙተ ዓለም በመጀመሪያ ሚሊኒየም (1000-500) የኢትዮጵያን ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ የገቡ ሴማዊ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው የሚለው ተዛማጅ የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ክርስትያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አሰተማሪዎች ትምህርት ጥሩ ተረት ብቻ ነው።

በሌላ በኩል በዓሙተ ዓለም በማምት ከ500 እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1050 ዓመታት በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ አጎራባች አገሮች በደአማት፥ በሳባ፥ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው በተገኙና በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በደቹና በሉክሰበርጉ የጥንታዊ ጽሑፎችና ታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰሮች ድሬዊስና ሽናይደር በተተረጎሙ የደአማት-አክሱም ጽሑፎች መሠረት፥ የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጨምሮ የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ በደአማት-ዩህ ደጋአምባ ምድር የተፈጠረው በአገሪቱ ሉአላዊ የደአማት-አክሱም ሕዝብ ነው።

በተጠቀሱ የደአማት-አክሱም ጥንታዊ ጽሑፎች መረጃና ትምህርት መሠረት፥ በ330 ዓመተ ምህረት መለኮታዊና አህጉራዊ የክርስቲያን ሃይማኖት ወደ አክሱም ከመግባቱና ቀጥሎም በ5ኛው ምዓ በዘጠኙ ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ከመተርጎሙ በፊት በአዋማዊው የደአማት-አክሱም ምድርና ቤተ መንግሥት የአይሁዳውያኑ የአሪት ሃይማኖት አልተገኘም። በተጨማሪም ሰነዶቹ በዘመነ-ክርስትና በመጀመሪያ 6 ምዕተ ዓለም የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በአጎራባች የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አካባቢዎች ዓለም አቀፋዊ ኃይልና ሥርዓት ሆኖ እንደተስፋፋ ጨምረው ያሰተምራሉ።

የእስልምና መነሻና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ

ከህልውናውም ከባህልም አኳያ በአካባቢም በዓለምም ላይ የኢትዮጵያን በህውርታዊ ጎብረቴሰብና ታሪክ አንድ ልዩና አስገራሚ ሥርዓት ያደረጉት ሶስት ማኅበራዊ ኃይሎች ከ330 እስከ 615 ድረስ በ285 ዓመታት ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ በግሪክ ሮማውያንና በአረብ አስተማሪዎች አማካይነት ወደ አገር ውስጥ ገብ ተውበየፊናቸው የመንግሥትና የአገር ሃይማኖቶች የሆኑ መለኮታዊና አህጉራዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ናቸው። ከሶስቱ የዓለም ሃይማኖቶች የእስልምና ሃይማኖት በክስተቱም በእድገቱም በውጤቱም

ከኢትዮጵያ የአክሱም መንግሥት ሥልጣኔና ታሪክ ጋር የቀረበ ታሪካዊ ግንኙነት ያለው ማኅበራዊ ኃይልና እንቅስቃሴ ነው። ይህን የኢትዮጵያና የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ ግንኙነት በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት የሰነድ መረጃ ባልተገኘበት ዘመን (550-1300) ለትውልድና ለዓለም በአረብኛ ቋንቋ ጽፈው ያሳወቁ ባለውለታዎች የጥንቱ የአረብ ታሪክ ምሁራንና ጸሐፊዎች ናቸው።

በተጠቀሱ የአረብ ምሁራን ዘገባ መሠረት፥ የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በሁለት በተለያዩ ጊዜያት፥ በሮችና አካባቢዎች ነው። ከሁሉ በፊት ከእስልምና ክስተት ዋዜማ ጀምሮ በ575 ከየመን ደቡብ አረቢያ በፋርሳውያን የተባረሩ ብዙ የኢትዮጵያ ሰፋሪዎች ከ575 እስከ 661 ደረስ ለዘጠኝ አሥርታት በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በሂጃዝ መካ ማለትም በዛሬው ሳውዲ አረቢያ ከነባር አረቦች ጋር በሥፍራ፥ በቋንቋ፥ በኢኮኖሚና በባህል ተቀላቅለው ይኖሩ እንደነበር ከታሪክ መረጃና ትምህርት ተረጋግጧል።

በ610-615 ነቢዩ ሙሐመድ መለኮታዊና አህጉራዊ የእስልምናን ሃይማኖት በመካ ከተማ በሰበከ ጊዜ ለመጀመሪያ ትምህርቱን አምነው የተከተሉት በመካ ጥቂት የቁረይሽ አረብ ነገድና የኢትዮጵያ ተወላጆች እንደሆኑ የመጀመሪያ የአረብ ሙስሊም ታሪክ ጸሐፊዎች አረጋግጠዋል። በ615-616 በነቢዩ ሙሐመድ ትዕዛዝ ወደ አክሱም ከተሰደዱ የመጀመሪያ የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች አምስት ሴቶች ጨምሮ ሀያ አንድ ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ የተጠቀሱ የአረብ ጸሐፊዎች ጨምረው አስተውሰዋል።

በአክሱም አረቦቹ ነጃሺ ማለትም ንጉሥ ብለው በሚጠሩት በአፄ አስሓማ የሚመራ የኢትዮጵያ መንግሥት ለእስልምና ሃይማኖት በቁረይሽ ተባራሪ ኃይሎች ላይ በይፋ የመጀመሪያ ዓለማቀፋዊ እውቅናና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ሰጠ። ባጭሩ ከ610 እስከ 661 ድረስ የኢትዮጵያ ዜጎችና መንግሥት ከአምስቱ የቁረይሽ አረብ የእስልምና ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ መሥራች መሪዎች ነቢዩ ሙሐመድ፥ አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ ጎን በልዩ ልዩ መንገዶችና መሣሪያዎች ተሰልፈው በመካ፥ በአክሱም፥ በመዲና፥ በኢራቅ፥ በፋርስ፥ በፍልስጤም፥ በአርመን፥ በሶሪያና በግብፅ ለሃይማኖቱ ዓለማቀፋዊ ዕድገትና ስርጭት ታሪካዊ ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ለትውልድና ለታሪክ አስታውቀዋል።

በግምት ከ632 እስከ 700 ድረስ በሰባት አሥርታት እስላማዊ የአረብ ዓለማቀፋዊ ኃይልና እንቅስቃሴ በመካከለኛው ምስራቅ፥

በግብፅና በሰሜን አፍሪካ ጥንታዊ የፋርስና የሮም ዓለማቀፋዊ መንግሥታትንና ሥልጣኔዎችን በወታደራዊ የምድር ላይ ዘመቻ በሚቆጣጠሩበት ዘመን የቀይ ባሕር ደሴቶች፥ ወደቦችና ጠረፎች ገና በኢትዮጵያ መንግሥትና የባሕር ኃይል ቁጥጥር ሥር ነበሩ። ከእነዚህ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጠረፍ ሥፍራዎች በየጊዜው ከኢትዮጵያውያን የባሕር ላይ ወንበዴዎች በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ ላይ የሚሰነዘረውን የዘረፋና የጥቃት አደጋ ከሥር ከምንጩ ለማስቀረት ከደማስቆ ሶሪያ ማዕከላቸው የአረብ ኡመያድ ባለሥልጣኖች በ700ዎቹ አካባቢ በአንድ በኩል በቀይ ባሕር የዳህላክን ደሴት በሰፋሪ ጦር በቀጥታ ያዙ። በሌላ በኩል ደግሞ ባሕሩን ተሻግረው የኢትዮጵያን የአዱሊስ ወደብ ከተማን ደመሰሱ።

በዚህ አዲስ የቀይ ባሕር ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታና ሂደት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ጠረፎችና ደሴቶች ሱዋኪንን ዜይላን በርበራንና ሞቃዲሾን ጨምሮ የአረብና የፋርስ ሙስሊም ሰፋሪዎች ብዙ እስላማዊ የንግድ፥ የሃይማኖትና የባህል ማዕከላትን፥ ወደቦችንና ከተሞችን ቆረቆሩ። እነዚህ እስላማዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጠረፍ ወደቦችና ከተሞች ከውጭ የአረብ ሙስሊም ሃይማኖት፥ ባህልና ሥልጣኔ ወደ ክፍለ አህጉሩ መሀል አካባቢዎች የሚገቡባቸው ታሪካዊና ባህላዊ በሮችና መንገዶች ሆነው መላ ኢትዮጵያን ያገለግላሉ።

በዚህ ረገድና ተግባር ከሂጃዝ አረቢያ በአረብ ሙስሊም አስተማሪዎችና ነጋዴዎች አማካይነት በታላቁ የዜይላ ቤርና መንገድ የእስላም ሃይማኖት፥ ባህልና ሥልጣኔ በክፍለ አህጉሩ መሀል ደቡብ ወደ ጥንታዊና አጎራባች የሐርላና የሀዲያ ሴማዊና ኩሻዊ አገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገቡ ብሎም ከ896 ጀምሮ በሐርላ ሴማዊ ምድር "ሸዋ" የተሰኘው የኢትዮጵያ የመጀመሪያው እስላማዊ ሱልጣኔት (መንግሥት) እንደተነሳ በኢጣሊያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ በዶክተር ቼሩሊ በ1936 ከሐረር ከተማ ቡተሃኘው የአረብ ጥንታዊ ሰነድ ተገልጿል። ሁለቱም የሸዋ ቀዳሚ ሱልጣኔት (896-1285) እና ቀጣዩና ወራሹ የይፋት-ዋላስማ ሱልጣኔት (1285-1577) ቤሐርላ ምድርና አገር ከመካ ቁረይሽ ነገድ በቅደም ተከተል በማኅዙማዊና በሃሺማይት ጎሳ ተወላጅ ሰፋሪዎች እንደተመሰረቱ በዚህ ጥናት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ተገልጿል።

በደቡብ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ እስላም ሕዝቦችና መንግሥታት ታሪክ ላይ ከ896 እስከ 1543 ድረስ ማለትም ከሸዋ ሱልጣኔት ክስተት እስከ ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አል-ጋዚ (ግራኙ)

የ1524-1543 አመጽ ድረስ የተጻፉ አራት ቁልፍና ወሳኝ የአረብኛ ቋንቋ ሰነዶችI

(1) በ1936 ከሐረር ኩተማ የተገኘው የሸዋ ማኸዙማዊ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኔት ታሪክI (2) ከአንድ ኢትዮጵያዊ የዜይላ-ይፋቱ የሕግ ምሁር ሼክ ጀማሉዲን አብደላህ በግብፅ ቡተሰጠው ዝርዝር መረጃ መሠረት፥ የኢትዮጵያ ሰቡቱን የይፋት፥ የደዋሮ፥ የአርባቢኒ፥ የሀዲያ፥ የሸርካ፥ የባሌና የደራ ሕዝቦችና ሱልጣኔቶች ታሪክ በሚመለከት በ1330ዎቹ በግብፁ አስተዋይ ምሁር ኢብን ፋድል አልዑመሪ የተጻፈው ታሪካዊ መጽሐፍI (3) በ1430ዎቹ የይፋትን የሣሽማይት-ዋላስማ ሥርወ መንግሥትና ታሪክ፥ እንዲሁም የኢትዮጵያ ረጅም የክርስቲያን አፄዎች ንና የሙስሊም ሱልጣኖችን የመሬት፥ የንግድና የኃይል ሚዛን ጦርነት በሚመለከት "የሙስሊም ነገሥታት በህበሻ" በሚል ርዕስ በአንድ ሌላ የግብፅ ታሪክ ጽሐፊ ማክሪዚ የተጻፈው መጽሐፍና (4) በ1530ዎቹ በኢትዮጵያ ተወላጅና የሕግ ምሁር ሸሃበዲን አሕመድ ቢን አብድልቃድር (አረብ ፊቂህ) የተጻፈው ታላቁ የኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም ዜና መዋዕል ናቸው። ከእነዚህ ውድና ብርቅ የታሪክ ሰነዶች የሸዋ ሱልጣኔት ታሪክና አስገራሚው የኢማም አሕመድ ዜና መዋዕል ለምዕተ ዓመታት ተጠብቀው የተገኙት ከሐረሪ ኩተሚ መንግሥት ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር ከኢትዮጵያ ረጅምና ውስብስብ የእስላም መንግሥታዊ ታሪክ አኳያ በተለይ፥ ከኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብና መንግሥት ታሪክ አኳያ በአጠቃላይ በምስራቅ ኢትዮጵያ ደጋአምባም አገር ሴማዊ፥ እስላማዊ፥ ጥንታዊ፥ ስልጡንና አናሳ የሐረሪ ሕዝብና ኩተሚ መንግሥት (ኤሚሬት) ራሳቸው በራሳቸው አንድ ሕያውና አንጸባራቂ የታሪክ ምንጭ፥ መረጃ፥ ማስረጃና ሐውልት ናቸው።

በኢትዮጵያ ታሪክ የዚህን የሐረሪ ሕዝብና ኤሚሬት ታሪካዊ መነሻና ልዩ ሚና አስመልክቶ ደራሲው ካሁን በፊት የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በተሰኘው ጥናቱ አጠቃሎ እንዳ ስቀመጠው፥

> እስከ ዛሬ ድረስ በተጠቀሱ የሸዋ ማኸዙማዊና የይፋት ዋላስማ ተከታታይ ሥርወ መንግሥታት ሰነዶችና በአካባቢው የትውፊት መረጃዎች ላይ የተደረጉ ምሁራዊ የምርምር ጥናቶችና አስተያየቶች እንደሚያመለክቱ፥ በማምት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ ከአረቢያ በአመዛኙ በኤደን ባሕረሰላጤ-በዜይላ ቦር በግልና በቡድን በጥቂ እስላማዊ ነጋዲዎችና የሃይማኖት ሰባኪዎች ትምህርት በአፍሪካ ቀንድ በተለይ በኤደን ባሕረሰላጤና በዓባይ-ጊቤ መካከል በብዙ የአካባቢ ሱልጣኔቶች ወይም እስላማዊ መንግሥታት የተደራጁ ብዙ

ነጋሪና ተዛማጅ ሕዝቦች በዘር ኩሻዊና ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ነበሩ።

ከእዝህ በማኸዙማዊ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኖች ሰነድ ላይ የተካሄደው የዶክተር ኢንሪኮ ቼሩሊ ጥናት እንደሚያመለክተው፥ የሸዋ ሱልጣኔት ቋንቋ የኢትዮጵያ ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ ክፍል ማለትም ከኢትዮጵያ የግዕዝ፥ የትግሬ፥ የትግሬ፥ የአማራ፥ የጋፋት፥ የጉራጌ፥ የአርጎባና የሐረሪ ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ተመሳሳይ ነው።

በዚህ አኳያ በአካባቢው ከተጠቀሱ ሱልጣኔቶች በተለይ ከ896 እስከ 1577 ድረስ በሰባት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የሸዋ፥ ያይፋት፥ የአዳልና የሐረር ሕዝቦች ሥርወ መንግሥታትና ሱልጣኔቶች በተለይ በኤደን ባሕረሰላጤና በአዋሽ ጨርጨር መካከል በአንድ በተመሰነ የመሬት ክልል በጊዜ፥ በሥርዓት፥ በኢኮኖሚ፥ በሃይማኖትና በባህል እርስበርሳቸው እንዲት በቅርብ እንደተያያዙና እንደተወራረሱ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ታይቷል። በተጨማሪም በዚህ ጥናት በሐረር ታሪካዊ ግምብ ውስጥ የአደሬ ሴማዊ የቋንቋ ማኅበረሰብ በሥፍራና በጊዜ በሃይማኖትና በባህል የጥንታዊ ሸዋ፥ ይፋት፥ ኢፃልና ሐረር ሱልጣኔት ተከታይና ወራሽ እንደሆነ ከሰነድ መረጃ ታውቋል።
(ከገጽ152-53)

ክፍል ሁለት

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ

1. የታሪክ መረጃ፥ ትርጉምና ትምህርት

የቅድመ ታሪክና የዘመነ ታሪክ ልዩነትና ግንኙነት

በኢትዮጵያውያን ታሪክ በጥንቱ ግሪኮች ሂስቶሪ፥ በዘመናዊ አውሮፓውያኖች ሂስትሪ ተብሎ የሚታወቀው መሠረተ ሀሳብና ትምህርት ሁለት ተዛማጅነት ያላቸው ትርጉሞችን ያዘለ ፅንሰ ሀሳብ ነው። በአንደኛው ትርጉሙ የሰው ልጅ ያለፈው ዘመን ሥራ አጠቃላይ ትምህርት ነው። በሌላ ትርጉሙ ደግሞ የሰው ልጅ የዚያ ያለፈው ዘመን ሥራ በመረጃ መሰረትና ሚዛን በሥፍራና በጊዜ ቀመር የሚታወቅበት ሥልተ ትምህርት ወይም የምርምር ዘዴ ነው።

ከሁሉ በፊት የተፈጥሮን፥ የሰውን፥ የአእምሮን፥ የዕውቀትን፥ የባህልንና የማኅበራዊ ሥርዓትን ተዛማጅ መነሻ፥ መስተጋብርና መወራረስ በሚመለከት የሰው ልጅ ማዕከላዊ ተግባርና ሚና በትክክል መታወቅ ይኖርበታል። ከዚህ አኳያ የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን በራሱ ማህበራዊ የአእምሮ መሣሪያ በተወሰነ የሥፍራና የጊዜ ቀመር ውስጥ የሚያውቅና የሚለውጥ፥ በማህበራዊ ሥራው ራሱንና ባህሉን የሚፈጥር አንድ ልዩ አካል ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅ ዘመን፥ ማህበራዊ ሥራና ባህል *ቅድመ-ታሪክና ዘመኑ-ታሪክ*[1] ተብሎ በሁለት ከፍለ ዘመናት ይከፈላል። የሁለቱ ከፍለ ዘመናት መለያ የታሪክ መረጃ ነው። በመሆኑም የታሪክ መረጃ የሰው ልጅ የሥራ አሻራ ነው። ቅድመ-ታሪክ የሰው ልጅን የዕድሜ ዘመን፥ ሥራ፥ ሕይወትና ባህል በትክክል ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ሰብአዊ የድርጅት፥ የምርት፥ የባህል፥ የቅርጽ፥ የጽሑፍ፥ የቋንቋ፥ የትውፊት ምልክቶች እና አሻራዎች፥ መሣሪያዎችና መረጃዎች የማይገኙበት የጨለማ ከፍለ ዘመን ነው ለማለት ይቻላል።

ዘመኑ-ታሪክ ደግሞ በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅን የማህበራዊ አኗኗር ዘዴና ሥርዓት በሥፍራና በጊዜ ቀመር ውስጥ በተግባር

[1] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ (አዲስ አበባ፥ ንግድ ማተሚያ ቤት 1982) ገፅ 17-20።

መስፈርት ለይቶ ለማወቅ የሚረዱ ሰብአዊ የባህል፥ የምርት፥ የቅርጽ፥ የጽሑፍ፥ የቋንቋ፥ የትውፊት ምልክቶችና አሻራዎች፥ መሣሪያዎችና መረጃዎች የሚገኙበት የዕውቀትና የትምህርት ክፍለ ዘመን ነው።

የታሪክ መረጃ ዓይነቶች

ዛሬ በዓለማችን ዘመናዊ የሳይንስ ጥበብና የአሠራር ዘዴ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ መሠረታዊ የታሪክ መረጃ ዓይነቶችና ምንጮች በአራት ተዛማጅ ዘርፎች ይመደባሉ። እነርሱም፦

1) የፓሌአንቶሎጂ (Paleontology) ማለትም ሰብአዊ የአጥንትና የድንጋይ መረጃ I
2) የሰነድ (የጽሑፍ፥ የቅርፅ፥ የሥዕል) መረጃ I
3) የሊንጉዊስቲክስ ማለትም የሥነልሳን (የቋንቋ ሳይንስ) መረጃ I
4) የትውፊት (የኪነቃል፥ የአፈታሪክ) መረጃ ናቸው።

የኢትዮጵያ የፓሌአንቶሎጂ መረጃ

ባጭርና በጥቅል ለማስቀመጥ፥ ታሪክ የሰው ልጅን የያለፈ ዘመን ሥራ፥ ሕይወትና ባህል በሚመለከት ከተጨባጭ የሥራ መረጃ በመነሳት የእንሰሳት እርባታ፥ የእርሻ፥ የግጦር፥ የከተማ፥ የንግድና የዕደጥበብ ተግባራትን የሳይንስና የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችንና ምርቶችን ጨምሮ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ የጎበረተሰብን ማህበራዊ ድርጅትና ሥርዓት፥ የሥራ ዓይነት፥ ብዛትና ክፍፍል የሚገልፅ አንድ ልዩ ማህበራዊ ሳይንስ ወይም ጥበብ ነው። በሌላ ባሕሪው ደግሞ ታሪክ አንድ የማህበራዊ ትምህርት ዘዴ፥ የዕውቀትና የጥበብ መከፈቻ ነው። በሌላ ቃል የታሪክ መሻውና ምንጩ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ በተጨባጭ መረጃ በትክክል የሚገለፅ ተጨባጭ የሰው ሥራ ነው። በመሆኑም ማንኛውም በታሪክ መረጃ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመርና መስፈርት የማይታወቅና የማይገለፅ የሰው ልጅ ሥራና ሕይወት የማይጨበጥ ተረት ነው።

ከታሪክ መረጃ አኳያ፥ የቅድመ-ታሪክ የመታወቂያ ገፅታዎች በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ሳይንስ ከከርሰ ምድር በቁፋሮ የሚገኙ ሰብአዊና ጥንታዊ የአጥንትና የድንጋይ መሣሪያዎች ማለትም የፓሌአንቶሎጂ መረጃዎች በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ እንደሚያስረዱት፥ በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካልና በአእምሮ ዳብሮ የተከሰተው ከዛሬ አራትና አምስት ሚሊዮን ዓመታት በፊት በለሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በታላቁ

የስምጥ ሸለቆ[2] ውስጥ ነው። እንዲያውም ከሀዳር፥ ከመልካ ቁንጥሬና ከአሞ ፖሌአንቶሎጂያዊ ሥፍራዎች በቁፋሮ የተገኙ ሰብዓዊና ጥንታዊ የአጥንትና የድንጋይ መረጃዎች በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ እንደሚያረጋግጡት፥ በከፍለ አህጉሩ የሰው ልጅ ምንጭና መነሻ የሆነው ሥፍራ በሁለት የተራራ ሰንሰለቶች መካከል የኢትዮጵያ የአዋሽ-አሞ ወንዞች[3] ለም፥ ውሃማና ሚዳማ ምድር ነው።

ሠንጠረዥ 4

የኢትዮጵያ የፓሌአንቶሎጂና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች ግኝት

መረጃው የተገኘበት ሥፍራ	የመረጃው ዕድሜ በዓመት	የግኝቱ ዘመን
1.የሀዳር ሰው አጽም	ከ4,000,000 ዓመት በላይ	1973
2.የአሞ ሰው አጽምና የድንጋይ መሣሪያ	ከ2,000,000 ዓመት በላይ	1967-1968
3. የመልካ ቁንጥሬ ሰውና የድንጋይ መሣሪያ	ከ1,500,000 ዓመት በላይ	1965-1976
4.የሊጋአዳ ዋሻ እንሰሳት ሥዕል	4,000 ዓመት	1970-1978
5.የሻቤ ዋሻ እንሰሳት ሥዕል	3,000 ዓመት	በ1920ዎቹ
6.የሸዋ፥ የአርሲ፥ የሐረር፥ የሲዳሞ ትክል ድንጋይ ሐውልቶች	የብዙ ሺህ ዓመታት	በ1920ዎቹ
7.የደአማት-አክሱም የድንጋይ ላይ ጽሑፎች	2,500 ዓመታት	1959-1973

Source: UNESCO, History of Africa I; R. Jousssaume, Megalithisme du Harar (1974); Annales d'Ethiopie (AE), Vols. 3, 5, 6, 7, 9, 12.

የኢትዮጵያ ታሪክ የሰነድ መረጃ

የፐንት-ኢትዮጵያ ታሪካዊ ክስተትና ዕድገት

ማህበራዊ የሥራ ዓይነት፥ ክፍፍልና ድርጅት፥ የቅርጽና የጽሑፍ መረጃዎች የዘመንና የያልጣን መለኪያ መስፈርቶችና መግለጫዎች ናቸው በተባለው መሠረትና ሚዛን፥ በዘመነ ታሪክ ከዛሬ ዘጠኝ - አሥር ሺህ[4] ዓመታት በፊት የሰው ልጆች በሰፊራ፥ በእርሻ፥ በንግድ፥ በቤት፥ በከተማ ተግባራትና ድርጅቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥትና የሥልጣኔ ሥራዎችንና ሥርዓቶችን ከጀመሩባቸው ታሪካዊ ሥፍራዎች አንዱ በአፍሪካ አህጉር፥ በታችኛው የዓባይ ወንዝ ሸለቆ የሚገኘው የጥንቱ ፊርአናዊ ግብፅ እንደሆነ ከ1799[5] ጀምሮ ባለፉት 200 ዓመታት

[2] UNESCO, General History of Africa I; Methedology and African Prehistory (1981), I, pp. 300-301.

[3] Ibid., pp. 412-419, 438-448.

[4] General History of Africa, II.

[5] M. F. Unger, The New Unger's Bible Handbook, (Chicago: Moody Press, 1984), p. 66.

በአርኪኦሎጂ ሳይንስ ከከርሰ ምድር በቁፋሮ ከተገኙ ጥንታዊ የሃይሮ ግላፊክስ ቋንቋና ጽሑፎች በስፍራና በጊዜ መስፈርት ተረጋግጧል።

በጥንታዊ ግብፅና በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በፑንት-ኢትዮጵያ መካከል በንግድ፥ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና ዘርፎች ከ2800 እስከ 1000 ዓመተ ዓለም ድረስ ለ1800 ዓመታት የቆየ የመስተጋብርና የመወራረስ ሥርዓትና ሂደት እንደነበር ከተጠቀሱ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ መረጃዎች ታውቋል።

ከታሪክ መረጃና ከጎብረተሰብ ዕድገት አኳያ፥ በ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ የግብፅና የፑንት ጥንታዊ ግንኙነት በትከክል ባልታወቁ ምክንያቶች ከተቋረጠ በኋላ፥ በግምት ከ1000 እስከ 500 ዓመተ ዓለም ባለው ዘመን ውስጥ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የኢትዮጵያ የደአማት[6] ዘውዳዊ መንግሥት በአጎራባቹ ደቡብ አረቢያ ደግሞ በዕጣን፥ በሙጫ፥ በከርቤና በቀረፋ ቅመማ ቅመም ምርትና ዓለም አቀፍ ንግድ የተሰማሩና ሚና፥ ሳባ፥ ቀጣጣንና ሃድራማዊ የተባሉ አናሳ የአረብ መንግሥታት በየፊናቸው እንደ ተከሰቱ ከታሪክ መረጃ እና ጥናት ይታወቃል።[7]

ምንም እንኳን በዓመተ ዓለም፥ በአምስተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በደጋማው ክልል በዘውዳዊ ሥርዓት ተደራጅቶ በስነዳዊ መረጃ በታወቀው በደአማታ ውያን መንግሥትና በጥንታዊ ፑንት መካከል በሥፍራ፥ በጊዜ፥ በቋንቋና በባህል የነበረውን ግንኙነት የሚያስረዳ ተጨባጭ ታሪካዊ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ባይገኝም በሚከተሉት አያሌ የውስጥና የውጭ ተዛማጅ ምክንያቶችና ማስረጃዎች ሁለቱም የፑንትና የደአማት ሕዝቦች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ባንድ አካባቢ የአንዱ አዳጊ የዘውድ ሥርዓት ተከታታይ የዕድገት ደረጃዎችና ምዕራፎች እንደሆኑ መገመት ይቻላል። ምክንያቱም፤

አንደኛ፥ ከሁሉ በፊት ጥንታዊ የፑንትና የደአማት አገሮች በቅደም ተከተል የተገኙበት የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አንድ አካባቢ ነው።

ሁለተኛ፥ ከዘመነ ፑንት እስከ ዘመነ ደአማት ድረስ በአካባቢው የፑንት-ኢትዮጵያን ጥንታዊ የመንግሥት ዕድገት እንቅስቃሴና

[6] A. J. Drewes, Inscriptions de L'Ethiopie Antique, (Leiden: Brill, 1962); Roger Scheinder, "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne", Documents Histoire Civilisation Ethiopienne, RCP 230, CNRS, FASC. 7 (1976).

[7] J. Doresse, Histoire Sommaire de la Corne Orientale de L'Afrique, (Paris, 1971), pp. 49, 58, 66, 84; "History of Arabia", The New Encyclopaedia Britanica, Vol. 1, pp. 1043-44; ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገፅ 28-29።

አቅጣጫ የሚያደናቅፍ ውጫዊ ግፊት ሆነ ውስጣዊ ተፅዕኖ መከሰቱን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ምክንያት ወይም መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።

ሦስተኛ፥ የደአማታውያን መንግሥትና ሥልጣኔ በዓመተ ዓለም በአምስተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታውቆ በስነድ መረጃ የተገኘበት ወቅትና ሁኔታ የመንግሥቱ ታሪካዊ መነሻ መቼና እንዴት እንደነበር በዝርዝር ስለማያመለክትና አንድ መንግሥት በባህላዊና በማህበራዊ ዕድገት በራሱ ፊደልና ጽሕፈት በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የታወቀበት ጊዜ ገና የተፈጠረበት ዘመን ነው ተብሎ በዘልማድ ስለማይታሰብ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ ክፍለ አህጉር ረጅም ታሪክ፥ የዘመነ ፑንት ፍጻሜና የዘመነ ደአማት መባቻ ቢያንስ ከ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ ጀምሮ እንደሆነ መገመት ከአግባብ ውጭ አይሆንም።

አራተኛ፥ በዚህ ጥናት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ሁሉ የሚጠቀሰው ዘመናዊ የአፍሮ-እስያ ሊንጉስቲክስ ጥናት ማለትም የሥነ ልሳን ወይም የቋንቋ ሳይንስ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርና በዓባይ ሸለቆ በጥንቱ ተዛማጅ የግብፅና የፑንቱ ብሎም በዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ቋንቋዎች መካከል ለረጅም ዘመን የኖረውን የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት በአጠቃላይ መንገድና መልክ ስለሚያመለክት በክፍለ አህጉሩ በፑንትና በደአማት ሕዝቦችና ቋንቋዎች መካከል ዘላቂ መስተጋብርና መወራረስ እንደ ተካሄደ መገመትም ይቻላል።

የኢትዮጵያ ረጅም የሰነድ መረጃ ታሪክ

በአንፃራዊ አባባል በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በዓለም ላይ ለረጅም ዘመን የጽሑፍ መረጃና ታሪክ ካላቸው ጥቂት ጥንታዊ ሕዝቦች አንዱ ነው። ከአገር ውጭና በአገር ውስጥ የተገኙ የኢትዮጵያ የስነድ መረጃዎች ከጥንቱ ፈርኦናዊ ግብፅ ማለትም በዓመተ ዓለም ከ2800 ገደማ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በ5000 ዓመታት የሚቆጠር ዘመን እንዳላቸው ከላይ ባጭርና በጥቅል ተመልክቷል።

ከሁሉ በፊት የህልውናውና የሕይወት መሠረታዊ ጥያቄን በሚመለከት ሥፍራና ጊዜ የመሆንና የመኖር ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በመሆኑም የአንድ አገርና ታሪክም በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የተካበተ ጥቅል የሥራ፥ የልምድ፥ የድርጅት፥ የትዳርና የቤተሰብ የመንግሥትና የሃይማኖት ተቋማት፥ የትምህርት፥ የዕደ ጥበብ፥ የቴክኖሎጂ የሥልተ ምርትና የሥርዓተ ማህበር፥ የባህልና

የእምነት ድምር ውጤት ነው። ስለሆነም ታሪክ የዕውቀትና የግጎ በራዊ ልምዶች ከምችት፥ ምንጭና ግንዛቤ ነው ለማለት ይቻላል።

ዛሬ በዘመነ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የአንድ ሕዝብን ታሪክ በጥናት እና ምርምር ሚዛን በተመሰነ የሥፍራ፥ የጊዜ፣ የተግባር መስፈርት በትክክል አገናዝቦ ለመማር ለማሳወቅ፥ ለመጻፍና ለማስተማር፥ ለማንም ግለሰብ ከታላቅ ትዕግሥት ጋር በቅድሚያ የሚያስፈልጉ መሠ ረታዊ ነገሮችና ቅድመ ዝግጅቶች (1) ትክክለኛ የሆነ የታሪክ መረጃ፥ (2) የታሪክ ዓይነተኛ ትምህርት፥ ሙያና ፍቅር (3) የሰውና የታሪክ ተዛማጅ ፍልስፍና ናቸው።

በመሆኑም ዛሬ በድህረ አብዮት የኢትዮጵያን ረጅምና ውስብስብ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ታሪክ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሳይንሳዊ ምርምርና ሚዛን ከሥልተ ምርትና ሥርዓተ ማህበር አኳያ በትክክል ለማጥናት፥ ለማወቅና ለማሳወቅ ከአገር ውጭና ከአገር ውስጥ የሚያስፈልጉ የታሪክ መረጃዎች ብዙ ናቸው። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፦

1. ከአገር ውስጥ በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1050 ዓመታት ውስጥ በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች የተጻፉ የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንዲሁም ከወርቅ፥ ከነሐስና ከመዳብ የተሠሩ ጥንታዊ የአክሱማውያን ገንዘቦች፤
2. ከአገር ውጭ ደግሞ በግምት ከ2800-1000 ዓዓ ድረስ በ1800 ዓመታት ውስጥ የጥንታዊ ግብፃውያን ሥዕላዊ የሃይሮግላፊክስ (Hieroglyphics) ቋንቋና ጽሑፍ መረጃዎች እንዲሁም ብዙ ጥንታዊ የግሪክ፥ የሮማው ያንና የአረብ ጸሐፊዎች የቀረፁዋቸው የጽሑፍ መረጃዎች፤
3. በቅርቡ ከፍለ ዘመን በግምት ከ1270 እስከ 1855 ድረስ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች በግዕዝ ቋንቋ በብራና የተጻፉ የክብረ ነገሥት፥ የፍትሐ ነገሥት፥ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የቅዱሳን ገድሎች፤
4. ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በየጊዜው በአውሮፓ የዲፕሎማሲ መልእክተኞች፥ ሚሲዮናውያን፥ አገር ጎብኝዎችና ተመራማሪ ምሁራን ስለ ኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በብዙ ዘመናዊ የአውሮፓ ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሕፍት፤
5. ከአጼ ቴምድሮስ ዘመነ መንግሥት (1855-1868) ጀምሮ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች፥ የሕግ መዛግብት፥ እንዲሁም የመሥርያ ቤት ሰነዶች፤
6. የትውፊትና ዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎች በድምር የኢትዮ ጵያ መሠረታዊ የታሪክ፥ የትምህርት፥ የባህልና የእውቀት ምን ጮችና መሣሪያዎች ናቸው።

የአርኪኦሎጂ ሳይንስና የኢትዮጵያ ታሪክ ማኝት

በኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ ጉዳይ ላይ የጥንታዊ ግብፃውያንን መረጃ በሚመለከት፥ በዓመተ ዓለም ከ2800 እስከ 1000 ድረስ ለ1800 ዓመታት ገደማ በሁለቱም በባሕርና በምድር ማለትም በቀይ ባሕርና በዓባይ ሸለቆ የንግድ መስመሮች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር ከጥንታዊው የፑንት አገር ጋር ፈርኦናዊ የግብፅ ነገሥታትና ኑጋዴዎች ለረጅም ዘመን የንግድ፥ የባህልና የሃይማኖት ግንኙነቶች እንደነበሩዋቸው የክፍለ አህጉሩንም ሕዝብ፥ እንስሳት፥ እፅዋት፥ አዝዕርት፥ የአርሻ፥ የዱርና የንግድ ምርቶችን በሥዕልና በጽሑፍ የሚገልጹ ብዙ ጥንታዊ መረጃዎችን በሃይሮግላፊክስ ቋንቋና ፊደል ቀርጸው ለትውልድና ለታሪክ አቆይተዋል።

በአገር ውስጥ ደግሞ በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1050 ዓመታት ውስጥ የተፃፉና በ500 የሚቆጠሩ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ከ1804 ጀምሮ ባለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ አጎራባች አገሮች ከ50 በሚበልጡ ታሪካዊ ሥፍራዎች በ30 በሚቆጠሩ ተመራማሪዎች ጥናት ከክርስ ምድር በቁፋሮ ወጥተው አሁን በብዙ ዘመናዊ ቋንቋዎች ትርጉም የታሪክ መረጃዎች ሆነዋል።[8]

ሠንጠረዥ 5

በ522-1981 የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ያጠኑ ምሁራን፥

ያጠናው ምሁር	የተገኘበት አገር	የጽሑፉ ቋንቋ	የጽሑፍ ብዛት	የጥናቱ ዘመን
1.Cosmas	Ethiopia	GR	1	522
2.Schweinfurth	Ethiopia	GE	13	1894
3.C. Rossini	Ethiopia	SA, DA	7	1897-1905
4.Paribeni	Ethiopia	GR	8	1905
5.E. Littmann	Ethiopia	GR,SA, DA	97	1906
6.Franchini	Ethiopia	SA, DA	32	1953-56
7.Drewes	Ethiopia	SA, GE	105	1955
8.Schneider	Ethiopia	SA, DA	3	1970
9.Archaeology	Ethiopia	GE, SA, DA	160	1955-81
10.25 Others	ETH;ARB;SUD.,	SA, GE, GR	51	1804-1981
Total			471	

SOURCE: Bernand et al, Inscriptions. GR= GreekGE= Geez DA= Daamat SA= Saba

[8] E. Bernand, A. J. Drewes, R. Schneider, et F. Anfray, trs. and eds.; Recueil des Inscriptions de L'Ethiopie Periods Pre-Axoumite et Axoumite, (Forthcoming).

ሠንጠረዥ 6
በ1893-1981 የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን
የተረጎሙ ምሁራን

ተ ቁ	የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን ወደ ዘመናዊ ቋንቋ የተረጎሙ ምሁራን	የጽሑፍ ብዛት
1	E. Littmann	105
2	A. J. Drewes	103
3	R. Schneider	38
4	Drewes & Schneider	51
5	C. Rossini	9
6	10 Others	78
	Total	384

SOURCE: Bernand et al, Inscriptions.

ከእነዚህ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች፥ ባለፉት አሥርታት (1955-1981) ከአንራባች ኤርትራና ትግራይ ታሪካዊ የየሀ፥ የመጠራ፥ የክስክሴ፥ የሐውልቲ፥ የአዲቀይሀ፥ የአዲጋለሞ፥ የእንዳ ጨርቆስ፥ የዳክሀናሞ፥ የዘበንሞሮሮ፥ የሰሮ፥ የሰፍራ፥ የፊቅያ ወዘተ ሥፍራዎች[9] በአርኪኦሎጂ ጥናት የተገኙና በዓመተ ዓለም ከ430 እስከ 330 ድረስ ባለው በአንድ ምዕተ ዓመት ውስጥ በሁለቱም የደአማታውያንና የሳባውያን ቋንቋዎችና ፊደሎች የተፃፉ አሥራ ሦስት የንጉሥታት ዜና መዋዕሎች[10] እንዲሁም በዘመነ ክርስትና መጀመሪያ ላይ በ300 አካባቢ በአንድ የአክሱም አዋማዊ ንጉሥ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ተጽፎ በአዱሊስ ወደብ ከቆመ ሀውልት ላይ በ525 በግሪኩ-ግብፃዊ ጸሐፊ ኮስማስ ተገልብጦ በቅጅ የተገኘውና በኢትዮጵያ፥ በዓባይ ሸለቆና በአረቢያ በ30 በሚቆጠሩ አገሮች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄዱ የወረራ ጦርነቶችን የሚዘረዝር አንድ ታሪካዊ ሰነድ፥ የአፄ ነገሥታት ኢዛናና ካሌብ በግዕዝ እና በግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች የተጻፉ ዜና መዋዕሎች በአንድነት የኢትዮጵያን ጥንታዊ የመነሻ ታሪክ በሚመለከት ቁልፍና ወሳኝ የመረጃ ምንጮች ናቸው።

[9] E. Littmann, Sabaische, Griechische, und Altabessinische Inschriften, Deutsche Aksum Expedition Book IV (DAE) (Berlin, 1913), Inscriptions Nos. 4-11, pp. 4-35; A. Kammerer, Essai Sur L'Histoire Antique d'Abyssinie, de Royaume d'Aksm et Ses Voisines d'Arabie et de Merce (Paris, 1926), pp. 89-97; "Christian Inscriptions of Ezana"; S. H. Sellassie, Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270 (Addis Ababa, 1972); p. 103; R. Schneider, "L'Inscription Chretienne d'Ezana en Ecriture Sudarabie", AE, Vol. 10 (1976), pp. 109-117.

[10] Ibid., Schneider, "Histoire", pp. 51-54.

2. የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ

ከጥንታዊ ግብፃውያን፥ ግሪኮች፥ ሮማውያን፥ አረቦችና ከአገር ውስጥም በተገኙ የሃይሮግላፊክስ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግሪክ፥ የግዕዝ፥ የላቲንና የአረብኛ ጽሑፎች መሠረት፥ ከጥንት አንስቶ በዘመነ ክርስቶስና እስከ መጀመሪያው አሥር ምዕተ ዓመታት ድረስ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይ በሰሜኑና በምሥራቁ የጠረፍ ክልሎችና በደጋማው መሀል ክልል የኢትዮጵያ ተከታታይ የጥንታውያን፥ የደአማታውያን፥ የአክሱማውያንና የአገው ሕዝቦችን እና መንግሥታትን አካባቢያዊ ክስተትና ዕድገት በሚመለከት ሰነዳዊ የግንዛቤ መረጃዎችና መርሐ አሳቦች በዚህ ጥናት ለውይይት ቀርበዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በተለይም የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ውያንን የመነሻና የማንነት ጥያቄዎች በሚመለከት ከላይ የቀረቡ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የደአማታውያን ጽሑፎች በመነሻ፥ በዓይነትና በዕድገት ደረጃ በተለያዩ ሁለት ቋንቋዎችና ሁለት የጽሕፈት ሥርዓቶች (monumental writing and cursive writing) ማለትም በቁም የጌጥና በስድ የተራ ጽሕፈት ሥርዓቶች የተጻፉ ታሪካዊ ሰነዶች ናቸው።[11]

ከሁለቱ ቋንቋዎች አንዱ ከሥልተ ጽሕፈቱ በዘመኑ በደቡብ አረቢያ ከነበረው ከሳባ ጥንታዊ ቋንቋና የቁም ጽሕፈት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነና በኢትዮጵያ በአንድ ምዕተ ዓመት (430-330 ዓመተ ዓለም) ጊዜ ውስጥ ተገኝቶ በትክክል ባልታወቀ ምክንያትና መንገድ ከአገሪቱ የጠፋ ፊደልና ጽሕፈት መሆኑን በኢትዮጵያ የዘመኑ ታሪክና ጽሕፈት ዛሬ ታዋቂና መሪ በሆኑ ፕሮፌሰር ምሁራን ድሬዌስና[12] ሽናይደር[13] ከፍተኛ የጥናት ሥራዎች ተረጋግጧል።

ሁለተኛው ቋንቋ ግን ከሥልተ ጽሕፈቱ በዘመኑ ሆነ ከዚያም በፊት ወይም በኋላ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያልተገኘና በዓይነት አዲስና ልዩ ከመሆኑም በላይ በዕድሜ አኳያ ከሳባውያን ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት የጊዜም ቅድሚያ ያለው የአገሩ የደአማታውያን ብሔራዊ ቋንቋና ሥርዓተ-ጽሕፈት እንደሆነ አሁንም ከምሁራኑ ድሬዌስና ሽናይደር ጥናቶች ታውቋል።

[11] Drewes, Inscriptions., pp. 71-88.

[12] Ibid., pp. 6, 89, 107.

[13] Schneider, "Histoire", pp. 49, 51; Ibid., "On the Evolution of the Ethiopian Writing", Lecture Text (Addis Ababa, 1982), p. 5; Ibid., "On the Daamatite State, Kings, and Gods"; Written Note to the Writer (Addis Ababa, 1982).

በተጨማሪም፥ በጎላ በዘመነ አክሱም የኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት በታሪካዊ የዕድገት ሂደት ከዚሁ ከደአማታውያን ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት እንደተገኘ በተጠቀሱ ከፍተኛ ምሁራን በአሳማኝ መረጃና ትንተና ተገልጿል።[14] ከዝህ ከዘመነ ደአማት ጽሑፎች መካከል፥

1) ወአረነወተ፥ ረደአመ፥ ረበሀና ለመነ የተሰኙ የአራት ነገሥታትን ስሞች፥
2) ሰመአተመአከተነ የተባለች የአንዲት ንግሥትን ስም፥
3) ነረመ፥ ጸደቀነ፥ ሸመነ፥ ረበ እና አበከወደመ ተብለው የሚታወቁ የአምስት ያገር ወለድ አዋማዊ አማልክትን ስሞች፥
4) አስተርሀ፥ ሀወከለ፥ አለመቀሀ፥ ደተሀመየመ፥ እና ደተብአደነ ተብለው የሚጠሩ አምስት በዘመኑ በመካከላኛው ምስራቅና በአረቢያ የታወቁ የውጭ አማልክትን ስሞች የያዙ በድምሩ አሥራ ሦስት በደአማትኛ ቋንቋ የተጻፉ ታሪካዊ የደአማት ነገሥታት ዜና መዋዕሎች በተለይ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክና ጂኦ-ፖለቲካ እንዲሁም መነሻና ማንነት በተመለከተ በጣም ታላቅ ዋጋ ያላቸው መሠረታዊ ሰነዶች[15] ናቸው።

በእዝህ የታሪክ መረጃዎች መሠረት፥ በደአማት አገርና መንግሥት ሰለመመፈተረነ እና ወረሃደነ የተባሉ ሁለት ተከታታይ ሥርወ መንግሥታት ወይም የነገሥታት ወገኖች ነበሩ። ከላይ ከተጠቀሱ የደአማት ነገሥታት ወአረነወተ እና ረደአመ ከመጀመሪያው ሥርወ መንግሥት እንደሆኑ በዜና መዋዕሎቹ ተመልክቷል።[16] ይህም ሁኔታ በቅድመ አክሱም የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ጎብረተሰብ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች አገርና መንግሥት እንደሆነ ያመለክታል።

በአጉሉ መንግሥታዊ ሰነዶች ማለትም በነገሥታት ዜና መዋዕሎች ከደአማታውያን ብሔራዊ ቋንቋ፥ ጽሕፈትና አማልክት ጋር የውጭ አገር አማልክት፥ ቋንቋና ጽሕፈት አብሮ መገኘት የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ሕዝብና መንግሥት ከአካባቢው ዓለም ጋር በተለይም በአረቢያ ከሳባውያን ጋር በንግድ፥ በሃይማኖት፥ በቋንቋና በባህል የቀረበ ታሪካዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ መስተጋብርና መወራረስ

[14] Ibid., "Ethiopian Writings".

[15] R. Schneider, "Deux Inscriptions Sudaribique du Tigre", Biblothetica Orientalist, vol. 30, Nos. 516 (1973), pp. 387-89; Anfray, "Recherches Archaelogique en Ethiopia", Academic des Inscriptions et Belles- Lettres (1978), p. 715.

[16] Ibid., "Deux Inscriptions", p. 389.

እንደነበረው በተጨባጭ ያሳያል።

በዚህ ጉዳይ እንዲያውም ከደአማት ነገሥታት አንዱ የረዘመ ልጅ "ድል አድራጊው" ንጉሥ ለመነ በዜና መዋዕሉ ራሱን «የደአማታውያንን፥ የሳባውያንን፥ የአበራውያን የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ»፥ አጉሉን ደግሞ «ከምስራቅ እስከ ምዕራብ»፥ በማለት እንዲሁም «አስተርሃ ሀወከለ፥ አለመቀሀ፥ ደተሀመየመ፥ ደተብአደነ»[17] የተሰኙ አዋማዊ አማልክቱን ዘርዝሮ በማሳወቅ በዘመኑ የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥትን የሕዝቦች፥ የቋንቋዎች፥ የባህሎችና የሃይማኖቶች ብዛትና አንድነት ጥርና በጥቅል አስረድቷል።

በዜና መዋዕሉ «የደአማታውያንን፥ የሳባውያንን፥ የአበራውያንን፥ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ»[18] የሚለው የንጉሥ ለመነ የዙፋን ስም የደአማት መንግሥትና ጎብረተሰብ በእርግጥ እንደዛሬው ኢትዮጵያ ከመነሻው በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች አገር እንደሆነ በግልፅ ያስረዳል።

በአዲስ የጥናት ዘዴ፥ በዘመናችን የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማታውያንን ታሪክ፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ከከርሰ ምድር አግኝተው ለትውልድና ለዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳወቁ ሁለቱ ከፍተኛ የኢፕግራፊ ምሁራን (epigraphists) ማለትም የጥንታዊ ጽሑፍ ተመራማሪዎች የሆላንዱ ፕሮፌሰር አብርሃም ጆሃን ድሬዌስና ሉክሰምበርጋዊው ፕሮፌሰር ሮዤ ሽናይደር ናቸው።

በፕሮፌሰር ሽናይደር እንደተተረጎመው፥ ከላይ በደአማቱ «ድል አድራጊ» ንጉሥ ለመነ ዜና መዋዕል የተጠቀሱ «ሳባውያን» በዓመተ ዓለም በ4ኛው ምዕተ ዓመት በግምት ከ430 እስከ 330 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ ከአጎራባቹ የሳባ አገር ማለትም ከአረቢያ በሰፊው ይሁን ወይም በዜና መዋዕሉ በግልፅና በይፋ ባልታወቁ መንገዶችና ምክንያቶች መጥተው በሉአላዊ የደአማት መንግሥት ሕግ ሥር የሚኖሩ የውጭ አገር ዜጎች ወይም ባዕዳን ሠራተኞች፥ ገባሮች፥ ቅጥር ሙያተኞች ሊሆኑ ይችላሉ።

[17] Ibid., p.387

[18] Ibid.,

3. የኅብረተሰብና የሃይማኖት ግንኙነት

የሃይማኖት ማኅበራዊ ትምህርትና ተግባር

አራቱ የአሞግዊዝም፥ የክርስትና፥ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦችና ባህሎች ታሪክ ገላጭ ማህበራዊ ኃይሎችና ሥርዓቶች ናቸው። በዚህ ረገድና ተግባር እስከ ዛሬው ዘመናዊ ሳይንስና ብሔረ እስቴት (ብሔረ መንግሥት) ክስተትና ዕድገት ድረስ በዓለም ታሪክ ሃይማኖት በተለይ የሰው ልጅን መሠረታዊ የመነሻ፥ የሕይወትና የዕውቀት፥ የሥርዓትና የሥልጣን ጥያቄዎችን በሚመለከት ለረጅም ዘመን የትምህርትና የእምነት ምንጭና መሠረት እንደነበር ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።

የመነሻና የባሕርይ መሠረታዊ ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ የማንኛውም ሃይማኖት መሠረትና ምክንያት የተፈጥሮና የሕይወት ምሥጢር ነው ለማለት ይቻላል። ከዚህ አኳያ በአጠቃላይ መንገድ ሁሉም ሃይማኖቶች ከተፈጥሮና ከሰው በፊትና በላይ የሆነ ብሎም በውስኑና በጠባቡ የሰው ልጅ አእምሮና አሳብ በትክክል የማይታ ወቅና የማይገለፅ አንድ ኃይል ለሁሉም ነገሮችና ሁኔታዎች የመነሻ ምንጭና ምክንያት ነው ይላሉ። አንድ ዓይነት ምሥጢራዊና ፈጠሪ ኃይል እንዳለ ያስተምራሉ። ይህ ምሥጢራዊና ፈጣሪ ኃይል በሰው ልጅ አእምሮ በሥፍራና በጊዜ ቀመር ተወስኖ የማይገለጽና የማይታወቅ ረቂቅ አካል ነው። በመሆኑም ሃይማኖት በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ አንድ ምሥጢራዊ እምነት ነው። ባጭሩ ሃይማኖት በባሕሪው በሰብአዊ አእምሮ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር መስፈርትና ቀመር ተወስኖ የሚገልጽ እውቀት ሳይሆን ረቂቅ እምነት ነው። አንድ ልዩዓይነት ውስጣዊ የሕይወት ስሜትና ኃይል ነው።

እንዲሁም ከትምህርትና ከተግባር አኳያ ሁሉም ሃይማኖቶች በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች የተፈጥሮ፥ የሰው፥ የሕይወት፥ የእውቀት፥ የሥርዓትና የመንግሥት መነሻና መሠረት ከሁለቱም ማለትም ከተፈጥሮና ከሰው ውጭና በላይ የሆነ አንድ ዓይነት ፈጣሪ ኃይል እንደሆነ ያስተምራሉ። በመሆኑም

ሃይማኖት በባሕሪውም በተግባሩም ከሰው፥ ከታሪክና ከሳይንስ ውጭና በላይ የሆነ እምነት ነው ለማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል የሳይንስ ትምህርትና ጥበብ እንደሚያስተምረው፥ በአንድ በኩል ሁለቱም ማለትም የሰው አእምሮና ተፈጥሮ ተዛማጅ፥ ሕያውና አዳጊ ነገሮች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የሰው ልጅ የዕውቀት ምንጭና መሣሪያ የሆነው የሰው አእምሮ በሥፍራ፥ በጊዜና

በተግባር ቀመር የተወሰነ ነገር ስለሆነ በዓለም ላይ የነበረውን፥ ያለፈውንና የሚሆነውን የሕይወት ነገርና ሂደት አገናዝቦ ሁሉንም በአንድ ጊዜ የማያውቅ አንድ ውስን አካል ነው። በመሆኑም እምነትና ተስፋ የሰው ልጅ የሕይወት አካልና ውስጣዊ ሞተር ነው።

የሃይማኖት ድርጅትና ተግባር በጥንቱ አሞግዊ ግብፅ

የሰው ልጅ እምነትና ሥራ በቅርብና በጥብቅ የተያያዙ ተዛማጅ የሕይወት እንቅስቃሴዎች እንደሆኑ የሰው ልጅ የሥልጣኔ ታሪክ በሥፍራና በጊዜ መስፈርት ያስተምራሉ። በዚህ ረገድና ተግባር የሃይማኖት ተረቶች፥ እምነቶችና ትምህርቶች ሁሉ ለሰው ልጆች በየዘመናቸው የፈጠራ፥ የእምነት፥ የተስፋ፥ የትምህርት፥ የሥራ፥ የድርጅት፥ የሥርዓት፥ የሥልጣን ምንጮችና መሣሪያዎች ሲሆኑ እንደሚችሉ ረጅም የሰውና የሥልጣኔ ታሪክ በግልፅና በዝርዝር ያስተምራል። ለዚህ አባባል አንድ ጥሩ ታሪካዊ ምሳሌና ማስረጃ በታላቁ የዓባይ ሸለቆ የጥንታዊው ግብፅ ሥልጣኔ ነው።

በአንድ ምሁር ጥናት መሠረት የታላቁ ጥንታዊ ግብፅ ሥልጣኔ ሁለት መሠረታዊ መግለጫዎች፥ ተዛማጅ የሃይማኖትና የአርት ተቋማትና ሥራዎች ናቸው።[19] በዚህ ረገድና ተግባር የግብፅ ታላላቅ ፈርኦኖች በዓለም የሥልጣኔ ሥራና ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ የሚታወሱት ራሥ አሲሪስ፥ ኢሲስ፥ ሆራስ፥ ሴት፥ ኔፍታይስ፥ ኑት፥ አሞን፥ ማአት፥ ሙት፥ ቾንሱ፥ ፕታ፥ ሴፍሜት፥ ቶት፥ ሃቶር፥ አምቢስ፥ ባስት፥ ሃፒ፥ ኢምሆቴፕ፥ እና አቶን ተብለው በልዩ ልዩ ስሞች ለሚታወቁ አያሌ ብሔራዊና አካባቢያዊ አማልክት ክብርና ምሥጋና ባሰሩዋቸው ታላላቅ የመቅደስ፥ የመቃብር (ፒራሚድ) እና የቤተ መንግሥት ሕንፃዎችና የአርት ሥራዎች ነው።

የእነዚህ ታላላቅ የግብፅ አማልክትንና መቅደሶችን ድርጅታዊ ሀብት፥ ኃይልና የጥበብ ሥራዎች በሚመለከት ለምሳሌ አሞን የተባለው ታላቁ የሃይማኖት፥ የመቅደስና የካህናት ተቋም፥ ቴብስ፥ ሂሊኦፖሊስና መምፊስ በተባሉ ሦስት ታላላቅ የግብፅ መዲናዎችና የሃይማኖት ማዕከላት በአንድ በተወሰነ ዘመን በድምር 206,364 የመቅደስ ካህናት፥ ምሁራን፥ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች፥ 476,953 ልዩ ልዩ እንሰሳት፥ 1,094 ካሬ ኪሎ ሜትር የመሬት ይዞታ፥ 502 ልዩ ልዩ የአበባና የአትክልት ሥፍራዎች፥ 51 ልዩ ልዩ የእርሻ ማሳዎች፥ 88 ጀልባዎችና 169 ግብርና ቀረጥ የሚከፍሉ የከተማ ዝቢያዎች ነበሩት።

---

[19] Serge Saunron, The Priests of Ancient Egypt (New York: Grove Press, 1960) Preface.

የሃይማኖት ምሥጢራዊ ባሕሪውና ግልጽ ማኅበራዊ ፋይዳ

ባጭርና በጥቅል አነጋገር ማንኛውም ሃይማኖት በአንድ በኩል የነሳ፥ የቋንቋ፥ የህብት፥ የባህል፥ የመደብ ምርጫና ልዩነት ሳያደርግ ሰዎችን በአንድ ምሥጢራዊ የጋራ እምነት ሥር ያስተባብራል። በሌላ በኩል ደግሞ ሕይወት፥ የሰው ልጅን ዕውቀትና የመንግሥትን ሥልጣን ጨምሮ፥ በዓይን ከሚታየውና በእጅ ከሚዳሰሰው ሰውና ተፈጥሮ ውጭና በላይ ከሆነው ከአንድ ምስጢራዊና ከኃሊ ኃይል ይመጫል ብሎ ያስተምራል። ይህ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት እና እምነት በሰዎች ሕይወትና ተግባር ላይ መሠረታዊ የባሕርይና የአመለካከት ልዩነትና ለውጥ እንደሚያስከትል ረጅም የሰው ልጅ ታሪክ ያስተ ምራል። በሌላ ቃል የሃይማኖት ፋይዳ የሚለካው በሰው ልጅ የአእምሮ ሚዛን ሳይሆን በማህበራዊ ድርጅትና ተግባር ነው ለማለት ይቻላል።

በመሆኑም ዛሬ በድህረ አብዮት በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ታሪክ ላይ በሚካሄደው ጥናትና ምርምር የአገሪቱን ሃይማኖቶች መነሻና ማህበራዊ ፋይዳ በሚመለከት ሚዛናዊ ግምትና ትኩረት ሰጥቶ ማጥናትና ማወቅ በምንም መንገድና ምክንያት የማይታለፍ የእውነትም፥ የእውቀትም፥ የሕዝብም፥ የአገርም አንድ መሠረታዊ ጉዳይና ተግባር ነው።

ከዚህ አኳያ ከደአማት-የህ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ባለፉት 2500 ዓመታት ውስጥ በድንጋይ፥ በብራናና በወረቀት ላይ በአምስቱ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክና የአማርኛ ቋንቋዎች የተጻፉ የኢትዮጵያ መንግሥታዊ የታሪክ መረጃዎች፥ በሙሉ ለማለት ይቻላል፥ የአማልክት፥ የሃይማኖት፥ የነገሥታት፥ የካህናትና የጦርነት ዘገባዎች ናቸው። ጽሑፎቹ የሕዝቦችን ታሪክና ባህል በግልፅ ስለማያሳዩ ከሰነዶቹ በጥናትና ምርምር ፈልፍሎ የሕዝቡንና የነብረተሰቡን አጠቃላይ ታሪክና ባህል ማወቅ ቀላል ትግል የማይጠይቅ ታላቅ ሙያዊ ተግባር ነው።

ክፍል ሦስት

የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት

1. የአዋጣዊ ሃይማኖት ቀዳሚ መነሻና ሚና

አሰቢኑስ የትሮጅሎዳውያን የፀሐይ አምላክ

በጥንታዊ የግብፃውያኑ የሃይሮግላፊክስ ቋንቋና ጽሑፍ እንደ ተመለከተው፥ በታላቁ የስሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጥንት-ኢትዮጵያ ዘመነ ታሪክ የተከለተው ቢያንስ ቢያንስ ከዛሬ አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ ነው ተብሏል።

በጥንቱ አዋጣዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ ቋንቋና ጽሑፍ አነራባቹ የጥንት-ኢትዮጵያ ምድር የአማልክትና የቅመማ ቅመም፥ ግለትም የዕጣን፥ የከርቤ፥ የመጫ፥ የቀረፋና የዝንጅብል አገር ተብሎ ይታወቃል።[20] በተጨማሪም የጥንቱ ግብፃውያን በታላቁ የስሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጥንት-ኢትዮጵያ አገር የዘራቸውና[21] የሃይማኖታቸው[22] ምንጭና መነሻ እንደሆነ ሊድርገው ያምኑበት እንደ ነበር ተመልክቷል። በዚህ ረገድና ተግባር በጥንታዊ የግብፅ ታላላቅ አማልክት ሂቶር የሰማይ እመቤት፥ ሚን የምድረበዳው አምላክ፥ ሆራስ የጥንቱ አንበሳ እንዲሁም ቶት የጽሕፈትና የጥበብ ፈጣሪ ከምድረ ጥንት-ኢትዮጵያ የመጡ አማልክት ናቸው ተብሏል።[23]

በዓመተ ዓለም በግምት ከ2800 እስከ 1000 ድረስ በንግድ፥ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና ጉዳዮች በጥንታዊ ግብፅና በጥንት-ኢትዮጵያ መካከል ቢያንስ ለ1800 ዓመታት የነበረው ታሪካዊ መስተጋብርና መወራረስ በትክክል በማይታወቅ ሁኔታ ከተቋረጠ በኋላ በሚቀጥለው ሚሊኒየም ውስጥ በክፍለ አህጉሩ የኢትዮጵያ አዋጣዊው የደአማት መንግሥትና ሥልጣኔ ቀጥሎ እንደተከሰተ ከላይ ተገልጿል።

በዚህ ዓይነት ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት፥ በዓመተ ዓለም ከ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ በዘመነ ክርስትና እስከ 7ኛው ምዕተ

[20] Doress, Histoire Sommaire, pp. 47-68; J. Leclant, "L'Exploration des Cotse de la Mer Rough: A la Queste de Pount et Secretes de la Mer-Erythree" , AE: Vol. II (1978, pp. 69-78.

[21] E. A. W. Budge, A History of Ethiopia, (1966), p.7

[22] Doresse, Histoire Sommaire, p.48.

[23] Ibid.,

ዓመት መጀመሪያ ድረስ በአንድ ሚሊኒየም ውስጥ (ከ332 ዓዓ እስከ 642 ዓም) ግብፅን በተከታታይ ይዘው በድምሩ ለ974 ዓመታት የገዙ የአውሮፓ ግሪኮችና ሮማውያን በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በቀይ ባሕር፥ በአረቢያ፥ በመካከለኛው ምስራቅ፥ በግብፅና በሜዲትራኒያን ባሕር አገሮችና ሕዝቦች መካከል በንግድ፥ በቋንቋ፥ በባህልና በሃይማኖት መስኩችና መንገዶች የመጀመሪያውን ታሪካዊ የመስተጋብርና የመወራረስ ሥርዓትና ዘመን መሠረቱ።[24]

በተጠቀሰው የአፍሪካ፥ የእስያና የአውሮፓ አህጉራት የመጀመሪያ መስተጋብርና መወራረስ ሚሊኒየም ክፍለ ዘመን፥ በግሪኩ-ሮማውያን ጸሐፊዎች የተጻፉ መረጃዎች በአንድ በኩል በአፍሪካ አህጉር በዓባይ ሸለቆ በሁለቱ ኩሻዊ የግብፅና የኑቢያ ሕዝቦች፥ መንግሥታትና ሥልጣኔዎች መካከል በሥፍራ፥ በኢኮኖሚ፥ በዘር፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በሃይማኖትና በሥርዓት በጣም የቀረበ ግንኙነትና ትስስር ያሳያሉ።[25]

በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከሰሜንና ከምስራቅ የጠረፍ ክልሎች ጀምሮ በሰሜኑ ደጋማና ተራራማ ቀበሌ የትሮጅሎዳውያንን (የአፋር)፥ የአክሱማውያንንና የበር በራውያንን እንዲሁም በደቡብ ምሥራቁ ክፍል በረጅሙ የሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ቀበሌ የአዛኒያውያንን የተሊያዩ ነባርና አዋማዊ ሕዝቦችን በሥፍራና በባህል ለይተው ይገልጻሉ።[26]

በዚህ ረገድና ተግባር በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት በ80 ገደማ በክፍለ አህጉሩ በስም የተጠቀሱ የአክሱማውያንን፥ የትሮጅሎዳውያንን፥ የበርበራውያንንና የአዛኒያውያንን መልክዓምድር፥ ኢኮኖሚ፥ ባህልና አዋማዊ ሃይማኖት ለይቶ በመግለጽ በጻፈው ትምህርታዊ መጽሐፍ፥ ሮማዊው ጸሐፊ ፕላኔ በዘመኑ በአገራቸው በዕማን፥ በክርቤ፥ በዝንጅብልና በቀረፋ ቅመማ ቅመም ምርትና ንግድ ተሰማርተው የሚኖሩ የትሮጅሎድ ቆለኛ ሕዝቦች በተለይ ከአክሱም ደገኞችና እንዲሁም በአረቢያ ከሚኖሩ፥ ከሳባ፥ ከቀጣጣንና ከሃድራማዊ አጎራባች አገሮች ጋር በንግድ፥ በባህል፥ በሥርዓትና በሃይማኖት የነበራቸውን የቀረበ መስተጋብር፥ ትስስርና መወራረስ በዝርዝር ያስረዳል።[27]

[24] Ibid., Chap. 3, pp. 63-103: Lapiso G. Dilebo, The Italo- Ethiopian War of 1887-1896: From Dogali to Adwa, (1996), pp. 1-2.
[25] Doresse, Histoire Sommaire , pp. 63-70.
[26] Ibid., pp. 70-103
[27] Ibid., pp. 72-86.

በተጨማሪም ፕላኔ በመጽሐፉ በትሮጅሎዳውያኑ አገር ከቀረፋ ምርትና ንግድ ጋር የተያያዘውን አሰቢኑስ ተብሎ የሚታወቅ የፀሐይ አምላክን[28] ሃይማኖታዊ ባህልና ሥርዓት እንደሚከተለው ይገልፃል። በፕላኔ ዘገባ መሠረት፥ በትሮጅሎዳውያን አገር የቀረፋ ቅመም ምርትና ንግድ በአግባቡ የሚከናወነው በአሰቢኑስ የፀሐይ አምላክ ካህን ልዩ ትዕዛዝ፥ ፈቃድና አመራር ነው። በቅመሙ ምርት ዋዜማ ለአሰቢኑስ የፀሐይ አምላክ በአርባ የሚቆጠሩ በሬዎች፥ ፍየሎችና በጎች ለመስዋዕት ሥነስርዓት በአምላኩ ካህን አማካይነት ይቀርባሉ።

ከመስዋዕቱ ክብረ በዓል በኋላ የሚሰበሰበው የቀረፋ ምርት፥ በካህኑ እጅ በሁለት ተከፍሎ የተወሰነው ድርሻ ለአሰቢኑስ አምላክ ይሆናል። የተቀረውን ምርት አምራቾቹ ለነጋዴዎች በመሸጥ እንደ ሚጠቀሙ ፕላኔ ጨምሮ ገልጿል።[29] በዘመኑ የትሮጅሎዳውያኑን የቅመማቅመም ምርቶች የሚገዙ ዋና ደምበኞች በአረቢያ የሚኖሩ የሳባ፥ የቀጣጣንና የሃይድራማዊ አጎራባች አገሮች እንደ ነበሩም በፕላኔው ዘገባ ተመልክቷል።[30]

የደአማታውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት

ከላይ እንደተገለጸው በደአማት ዘውዳዊ አገርና መንግሥት ነረመ፥ ጸደቀነ፥ ሸመነ፥ ረበ እና አበከወደመ የተሰኙ የአገር ውስጥና አስተር፥ ህወበሰ፥ አለመቀሀ፥ ደተሀመየመ እና ደተበአደነ የተባሉ የውጭ አገር በድምሩ አሥር በስም የታወቁ መንግሥታዊ አማልክት ነበሩ። በዘመኑ በሁለቱ የደአማትና የሳባ ቋንቋዎችና ፊደሎች ተጽፈው በቅርቡ ከክርሰ ምድር በአርኪኦሎጂ ጥናት የተገኙ የኢትዮጵያ ቁልፍ የታሪክ ሰነዶች ለተጠቀሱ አማልክት ክብርና መታሰቢያ በዘመኑ ነገሥታት በድንጋይ ላይ የተቀረፁ ዝክረ ነገሮች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ የኢትዮጵያ የጥንቱ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖቶች የአገሪቱ የጥንታዊ ሥልጣኔ አንድ መሳሪና መገለጫ ናቸው ለማለት ይቻላል።

የአክሱማውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት

በ330 ዓመተ ምህረት አካባቢ መለኩታዊና አህዳዊ የክርስትና ሃይማኖት ወደ አገሩ ከመግባቱ በፊት በአክሱማውያን አገርና ቤተ መንግሥት አስተር፥ ብሔር፥ ምድር፥ መሕረም፥ ዘዩስ፥ አሬስና

[28] Ibid., pp. 74-85.
[29] Ibid., p. 74
[30] Ibid., p. 73-84.

ፓሴዶን የተባሉ ስባት አዋማዊ አማልክት ነበሩ። ከእነዚህ አስተር በዓሙተ ዓለም ከ5ኛው ምዓ ጀምሮ ለረጅም ዘመን በደአማታውያን አገርና መንግሥት የነበረ አምላክ ነው። ዘዩስ፥ አሬስና ፓሴዶን በአካባቢው የግሪክ ንግድ፥ ቋንቋ፥ ባህልና ሃይማኖት ከተስፋፉ በኋላ የገቡ የግሪክ አዋማዊ አማልክት ናቸው።

ከረጅም የሰውና የሥልጣኔ ታሪክ አኳያ ሲታይ፥ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ አራት ምዕት ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ በሦስቱ የግዕዝ፥ የሳባና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች በድንጋይ ሐውልቶች ላይ ተጽፈው ከክርሰ ምድር በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ጥበብና ጥናት የተገኙና ከላይ በሠንጠረዥ 4-5 የቀረቡ የታሪክ መረጃዎች በዘመኑ ነገሥታት ለእነዚህ አዋማዊ አማልክት ክብርና መታሰቢያ የተቀረፁ የጽሑፍና የሐውልት መረጃዎች የኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ ቁልፍ መገለጫዎች ናቸው።

የደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊ ሃይማኖቶችና የታሪክ መረጃዎች

በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በጥንታዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክ፥ የላቲንና የአረብ ቋንቋዎችና ፊደሎች ተቀርፀው በተገኙ የሰነድ መረጃዎች መሠረት በተለይም በክፍለ አህጉሩ የምስራቅና የሰሜን ጠረፍና ደጋማ ክልሎች ጥንታዊ የፑንታውያንን፥ የደአማታውያንን፥ የትሮጅሎዳውያንን የበርበራውያንን የአክሱማውያንን አዋማዊ ሃይማኖቶች ታሪካዊ መነሻና ዕድገት በሚመለከት ከላይ የታሪክ መዛኒያ ቢጋር ቀርቧል።

ነገር ግን በክፍለ አህጉሩ የደቡብና የመሀል ደጋማና ጤናማ ክልሎች ጥንታዊ የሐርላ፥ የህዲያ፥ የዳሞት-ጎንጋ፥ የጋሞ-ወላይታ ... ሕዝቦችና መንግሥታት በቅርቡ ሦስቱ መለኮታዊና አህጉራዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ አካባቢው ከመግባታቸው ቢፊት ከላይ በቀረቡ የግብፅ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክና የላቲን ጥንታዊ ሰነዶች በምንም ሥፍራና ጊዜ ተጠቅሰው አልተገኙም።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል በሐረርጌ ደጋማው ክፍል ከለጋአደ ዋሻ፥ በሲዳሞ ከሻቤ ዋሻ በድንጋይ ላይ ተስለው የተገኙ ጥንታዊ የእንሰሳትና የሰዎች እንዲሁም በደቡብ ሸዋ፥ በአርሲና በሐረርጌ ደጋ በብዙ ሥፍራዎች የሚገኙ ተክል የመቃብር ድንጋይ ሐውልቶች በጥንታዊ ግብፃውያን፥ ግሪኮች፥ ሮማውያንና አረቦች ሆነ በአክሱማውያን በቀጥታ ባልተደረሱ የደቡብና የመሀል ኢትዮጵያ ክልሎች ቢያንስ ገና ከዛሬ አራትና አምስት ሺህ ዓመታት በፊት ገደማ ጀምሮ

በእንሰሳት እርባታ፥ በእርሻና በዕደጥበብ ተግባራት የተሰማሩና በአዋማዊ ሃይማኖቶች የተደራጁ ብዙ ጥንታዊ የሐርላና የህዲያ ተዛማጅና አጎራባች ሕዝቦች ይኖሩባቸው እንደነበር በግልፅ ያሳያሉ።[31]

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የተጠቀሱ የቀሻ ድንጋይ ላይ ሥዕሎችንና የመቃብር ላይ ሐውልቶችን የሠሩ ጥንታዊ ሕዝቦችን መነሻ፥ ማንነትና ታሪካዊ ዕድገት በተመለከተ እስከ ዛሬ ድረስ በደቡብ ምስራቅ በተለይም በሐረርጌ የአካባቢው ነዋሪዎች በትውፊ ታዊ ግንዛቤያቸው የጥንቱ የሐርላ ሕዝቦች በሚል ጥቅል ስያሜ እንደሚጠሩዋቸው ታውቋል።[32]

ከቅርብ ጊዜ ታሪክ አኳያ ደግሞ ከ16ኛው ምዕት ዓመት ወዲህ በአካባቢው በዛሬው የሱማሌ፥ የኦሮሞና የአፋር ማህበረሰቦች እስኪወረስ ድረስ በምስራቅ ኢትዮጵያ ዛሙራሀ፥ ባርዛራሀ፥ ያቆላይ፥ ጃዛር፥ አረብ፥ ታክላና አልታ በተባሉ በራሱ አያሌ ጎሣዎችና ማኅበረሰቦች የተከፈለ በእንሰሳት እርባታ፥ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማራ ብሎም በመንግሥታዊ ሥርዓት የሚኖር አንድ «ሐርላ» የተባለ አገርና ሕዝብ እንደነበር ከዘመኑ ሰነዳዊ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ይቻላል።[33]

በመሆኑም በእዚህ በተጠቀሱ የአርኪኦሎጂ፥ የትውፊትና የታሪክ መረጃዎች መሠረት፥ ከደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕዝቦች አንዱ በዘር በቋንቋና በሃይማኖት በደቡብ ምስራቅ ከዛሬው የሐረሪ (አደሬ) ሕዝብ ጋር የቀረበ ታሪካዊ አንድነት ያለው የሐርላ ሕዝብ ነው። አንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ፤

1) በጣም በምስራቅ ከዋቤ ወንዝ አንስቶ በምዕራብ እስከ ጊቤ ወንዝ ድረስ ጥንታዊ የተክል ድንጋይ ሐውልቶች እስከ ዛሬ በሚገኙበት ምድር በ15ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ገዳይቾ፥ ጉዶሬ፥ ዲሾ፥ ሀይባ፥ ገንዛ፥ ሲጋ፥ ገላ፥ ቀቤና፥ ጎጋለና አላባ በተባሉ አሥር የነበሩ የክልል ማኅበረሰቦችና መስተዳድሮች ተከፍሎ የነበረው የህዲያ-ሲዳማ ሕዝብና[34] መንግሥት፤

---

[31] F. Anfray, "Les Stelse du Sudshoa et Sidamo", AE, Vol. 12 (1982): R. Joussoume, Legalithisme en Ethiopie: Monuments funeraires Protostorique du Harar (1974), pp. 101-103).

[32] U. Braukamper, "Islamic Principalities in South- Eastern Ethiopia between the 13th and 15th Centuries", Part I and II, Ethiopianist Notes, No. 1 (1977).

[33] G. W. B. Huntingford, tr. and ed., The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia (1965), p. 74: Arabfaqih, Histoire de la Conquete de L'Abyssinie, tr. and ed., R. Basset, (1897), pp. 111, 124, 130, 150, 170, 171,

[34] Huntingford, Amda Seyon, pp. 19-23: Ibn Fadl A. Umari: Masalik El Absar F:

2) በደቡብ ምዕራብ ከአባያ ሐይቅ እስከ ጎጀብ ወንዝ በሚኖረው የአሞ ሸለቆ ክልል የተለያዩ የጋሞ-ወላይታ ሕዝቦች[35]

3) በመሀል ምዕራብ በአዋሽ፥ በሙገር፥ በጊቤ፥ በዓባይ፥ በአንገር፥ በዲዴሳና በጎጀብ ወንዞች አካባቢ ዳሞት፥ ሂናሮ (እናርያ)፥ ቦሻ፥ ከፋ፥ ሸኸቾ (ሞቻ)፥ ቢዛሞ፥ ሺናሻና አንፊሎ ተብለው በልዩ ልዩ የማህበረሰብ ስሞች ለሚታወቁ አያሌ ተዛማጅ አገሮችና መንግሥታት የጋራ መነሻ የሆነው የጎንጋ ሕዝብ[36] ከላይ ከተጠቀሱ የሐርላ፥ የሀዲያ፥ የወላይታ፥ የጋሞ ወዘተ ማህበረሰቦችና መንግሥታት ጋር በጥንታዊ የታሪክ ሰነዶች የታወቁ ዋና ዋና የደቡብ ኢትዮጵያ ኑባር ሕዝቦች ናቸው።

በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ሚሊኒየም መጨረሻ ላይ ከእነ ዚህ የክልሉ ሕዝቦች በደቡብ ምስራቅ የሐርላ-ሸዋና የሀዲያ-ሲዳማ አጎራባችና ተዛማጅ ማኅበረሰቦች በመሀል-ምዕራብ ደግሞ የዳሞት-ጎንጋ ማኅበረሰቦች በየአካባቢያቸው ሉአላዊ አገሮችና መንግሥታት እንደ ነበሩ እስከ ዛሬ ድረስ የተፃፉ የሰነድ፥ የትውፊትና የቋንቋ መረጃዎችና ጥናቶች ያሳያሉ።[37]

ከእነዚህ ኑባርና አዋማዊ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችና መንግሥታት በዘመነ ክርስትና በማምት ከመጀመሪያ ሚሊኒየም ፍጻሜ ጀምሮ ሁለቱ መለኮታዊና አህዳዊ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶች[38] ከምስራቅና ከሰሜን ወደ መሀል አገር ከመግባታቸው በፊት በተለይ በጎንጋ ማኅበረሰቦች ዘንድ የአዋማዊ ሃይማኖት፥ ባህልና ሥርዓት በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ እንደነበር በ13ኛው ምዕተ ዓመት በዳሞቱ አዋማዊ ንጉሥ ሞተሎሚና በአማራ መንኩሴ አቡነ ተክለሃይማኖት (1215-1313) መካከል ለረጅም ጊዜ የተካሄደው ታላቅ የሃይማኖት ትግል[39] አንድ ታሪካዊ ማስረጃ ነው። ዛሬ በደቡብ ምዕራብ

Masalik El Masar, tr. and ed., G. Demombynes, (1927), pp. 14-18: J. Perruchon, tr. and ed., Les Chroniques de Zara Yaeqob et Baeda Maryam, (1893), pp. 16-18: U. Braukamper, Geschichte der Hadiya Sud-Athiopiens, (1980): Maps 6-18.

[35] C. F. Beckinham and G. W. B. Huntingford, trs and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646, (1954), pp. IXV-LXVII.

[36] Huntingford, Amda Syon, p. 45: O. G. S. Crawford, ed., Ethiopian Itineraries 1400-1524, (1958), pp. 78-84: Tekleselassie, Susenyos 1605-1632 (unpublished) Chronicle), W. Lange, History of the Southern Conga: Southern Ethiopia, (1982).


[37] Ibid., Ethiopia Itineraries, pp. 80-82: Braukamper, "Islamic Principalities", pp. 19-32.

[38] J. S. Trimingham, Islam in Ethiopia, (1966), pp. 48-76.

[39] Ibid., p.65:

ኢትዮጵያ የከፊቾና የሻክቾ የቋንቋ ማህበረሰቦች በአካባቢው ጥንታዊ የጎንጋ፥ የዳሞት፥ የእናርያ፥ የቦሻ፥ የቢዛሞ፥ የአንፊሎ፥ የሺናሻ ... ሕዝቦችና መንግሥታት ቀጥተኛ ተወላጆች ናቸው።[40]

የኢትዮጵያ የ1524 – 1543 የኢማም አህመድ ጦርነት ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።

[40] Weiner J. Lange, History of the Southern Gongo (Southern Ethiopia) (1982).

2. የክርስትና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

የክብረ ነገሥቱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ትምህርት

በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344)፥ በ1320 ገደማ፥ ከአረብኛ ቋንቋ ረቂቅ በአክሱም ከተማ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞ የኢትዮጵያ የክርስትያን ሃይማኖት፥ መንግሥትና ኅብረተሰብ መሪ የፖለቲካ ሰነድ በተደረገው የክብረ ነገሥት መፅሐፍ እንደተባለው፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በአሪት ሃይማኖትና ሕግ መሠረት ማክዳ ወይም ሳባ ከተባለች ከኢትዮጵያ አዋማዊት ንግሥትና ከይሁዳውያኑ ንጉሥ ሰለሞን ተወለደ በተባለው በቀዳማዊ ምኒልክ አመራር የተመሠረተው ከዛሬ 3000 ዓመታት በፊት በዓመተ ዓለም በ970-931 ባለው ዘመን ውስጥ ነው።[41]

በዚህ የፖለቲካ እምነትና ትምህርት መሠረት የኢትዮጵያ አዋማዊ የአክሱም ሕዝብና ቤተ መንግሥት በዘመነ ክርስትና በ330 ዓም በአፄ ኢዛና መሪነት ወደ አዲሱ መለኮታዊና አህጉራዊ የክርስትና ሃይማኖት በገባ ጊዜ በዓመተ ዓለም ከ931 ጀምሮ በዘመነ ክርስትና እስከ 330 ዓመተ ምህረት ድረስ ቢያንስ ለ1260 ዓመታት በጥንቱ መለኮታዊ አሪት ወይም በፅላተ መሴ እየተመራ ይኖር ነበር ተብሏል።

ይህንን የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያንን የመነሻና የማንነት ታሪክ በሚመለከት፥ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ አለቃ ታዬ ገብረ ማርያም (1860-1924)፥ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ* በተሰኘው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘርና ትውልድ በሚል ርዕስ ዘርዝረው እንዳስቀመጡት፥

> *የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በዋናው ሃገር በአራት ክፍል ይከፈላል። ነገደ አሪት፥ ነገደ ካም፥ ነገደ ሴም (ነገደ ዮቅጣን) ነገደ እሥራኤል ናቸው።*
>
> *ይህን ስለአልን የሕዝቡንና የመንግሥቱን ዋና ዋና የሆነ ዓይነት ኖውን ክፍል መናገራችን ነው እንጂ በዝርዝር ግን በየዘመኑ ከእስያ እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕዝቦች እጅግ ብዙዎች ናቸው።*
>
> *ከሁሉ በፊት አስቀድመው በመጀመሪያ ከእስያ ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አገሪቱንም ይዘው የኖሩ ነገደ አሪት የተባሉ ናቸው። የእነዚህም አባት በክብረ ነገሥት ከገፅ 40 እስከ 50 እንደአሳየን*

[41] E. A. B. Budge, tr. and ed., The Queen of Sheba and Her Only Son Menyelek I, (London: OUP, 1922).

> *ከአዳም ልጆች አንዱ ኦሪ ወይም አራም የተባለው ነው። እርሱ ... ከነልጅ ልጆቹ 21 ነገሥታት በኢትዮጵያ ነገሡ። በመጨረሻው ንጉሣቸው በሰሊማን ታረ ጊዜ በናህ ዘመን በጥፋት ውሃ ተደመሰሱ። አለቁም። የዚህን ሕዝብና ነገሥታት ታሪክ በአዲሱ ክብረ ነገሥት ከገፅ 317 እስከ 333 ተመልከት።*
>
> *እዚህ ሕዝቦች በማየ አይህ ከጠፉ ወዲህ የኢትዮጵያ አገርና ምድርም ሁሉ ከጥፋት ውሃ እስከ ባቢሎን ማማ መፍረስ በቋንቋ ተለያይተው እስከ ሰዎች መባታተን 531 ዓመት ከሥር ኢትዮጵያ ሰው የሌለባት ባዶ ነበረች። ከዚህ በኋላ ነገደ ካም መጡና ወረሰዋት።*[42]
>
> *ካም ከአሲያ በባብአልመንደብ ተሻግሮ መጥቶ በኢትዮጵያ ገባ። ይህም የሆነው በ2787 ዓመተ ዓለም 2713 ዓመት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት ነው።*
>
> *ካም በኢትዮጵያ 78 ዓመት ገዝቶ እንደገና ወደ እሲያ ሂዶ ሶርያንም እይዛለሁ ብሎ ከሌም ልጆች ጋር ተዋግቶ በጦር ሞተ። ልጆቹ ግን ታላቅ ወንድማቸው ኩሽን በላያቸው አንግሠው ኢትዮጵያን ወረሱ። ነገደ ካም እስከ የልጅ ልጆቻቸው 25 ነገሥታት ከ2787-3515 [?] ዓመተ ዓለም 743 ዓመት ነገሡ። ኢትዮጵያንም ገዙ። ከብረ ነገሥት ከገፅ 333-348 አይ።*
>
> *በነገደ ካም ዘመን ሦስት ነገዶች በዮጊዘው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። እነርሱም ነገደ ሻንቅላ፥ ነገደ ቅማንት፥ ነገደ ወይጠ ናቸው።*[43]

በዚህ በአለቃ ታዬ የታሪክ ትምህርትና ትንተና መሠረት፥ በነገደ ካም ሕዝቦች ላይ በመጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ሕዝቦች «ምርጥ» ሴማዊ የዮቅጣንና የእሥራኤል ነገዶች ናቸው። በአለቃው ቃልና ትምህርት መሠረት፥

> *ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ባላባቶች የሴም ዘሮች ሰድስት ወገን ናቸው። እነርሱም አማራ፥ ትግሬ፥ አገው፥ በደው፥ አስገዴ፥ በቅላ፥ ሐባብ ናቸው። በደው አስገዴ፥ በቅላ፥ ሐባብ እዚህ ሦስቱ ነገድ ወደ እስላም ሃይማኖት ገብተው ከወንድሞቻቸው ተለይተው ልዩ ወገኖች ሁነዋል።*
>
> *አማራ፥ ትግሬ፥ አገው ግን በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በሕገ አሪት ያመኑ በኋላ በክርስትና ያመኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የጸኑ ከጥንት ጀምሮ መንግሥት ያልጠፋባቸው ባዕድ ግዛ ያልገባባቸው የእዝአብሔር ሪዴት ያልራቀባቸው ሕዝብ ናቸው።*
>
> *ከዚህም ሁሉ ጋር አማሮች፥ ትግሮች የኢትዮጵያ ዓይነተኛ ባላገሮችና ባላባቶች ከሆኑ የሴም ዘር ከነገደ ዮቋጣን ልጆች ከእሥራኤልም ዘሮች እንደሆኑ የሚያስረዳ ብዙ ምስክር አላቸው።*[44]

[42] አለቃ ታዬ፥ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ*፥ (አዲስ አበባ፥ 1958)፥ 6ኛ እትም ገጽ 11-12

[43] Ibid., p. 12

በክብረ ነገሥት ባሕረ መዝገብ መሠረትነት በጥንቱ አዋማዊ የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ላይ ከዛሬ 3000 ዓመታት በፊት የኦሪትን ሃይማኖትና ሕግ ምሥረታ በሚመለከት «የነገደ እሥራኤል መምጣት» በሚል መነሻ በአሊቃ ታዱ መጽሐፍ እንደተባለው[1]

> *በእሥራኤል ንጉሥ በሰለሞን ዘመን ማኩዳ የኢትዮጵያ ንግሥት በመጽሐፍ ቅዱስ የሳባ የአዜብ ንግሥት የተባለች ... የሰለሞንን ጥበብ ወሬውን ሰምታ እርሱን ሊማየትና ጥበቡን ለመስማት ከብዙ ጓዝ ጋር ወረደች። ከሰለሞን ቀጻማዊ ምኒልክን ጸንሳ ወደ አገርዋ ተመለሰች። ካገርዋም ሱትደርስ ወለደችው። ሰሙንም የብልሃተኛ ልጅ ሱትል እብኒ እልሐኪም አሰኘው። ከእናቱ ጋር አደጎ 22 ዓመት ሲሆነው አባቱን ሰለሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ። በዚያ ሕገ አሪትንና ሕገ መንሥግትን የዕብራዊስጥን ቋንቋም እየተማረ ሦስት ዓመት ተቀመጠ። ከዚህ በኋላ አባቱ ንጉሥ ሰለሞን በኢትዮጵያ እንዲነግሥ ከእሥራ ሁለት ነገደ እሥራኤል 12000 የበኩር ልጆቻቸውን ብልሆችና አዋቂዎች የሆኑትን መርጦ ከተማሩት ከካህናት ልጆችና ከመኳንንት ልጆች 22 ታላላቆች ሹመ ልጁ ቀዳማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ልብሰ መንግሥት አሰፍቶ ቅብአ መንግሥት በሲቀ ካህናቱ እጅ አስቀብቶ ሕገ አሪትን ሥርዓተ መንግሥት ሰጥቶ ወደ ኢትዮጵያ መልሶ ሰደደው። ክብረ ነገሥት ገጽ 188-189 እይ።*[45]

በኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የኦሪት መገኘት ጥያቄ

የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ አለቃ ታዱ በኢትዮጵያ የፊላሻ ኦሪትንና የክርስትና ሃይማኖትን መነሻና መስተጋብር በተመለከተ የሚከተለውን ማብራሪያ አቅርበዋል።

> *ሰለ ፈላሾች ነባር ታሪክ ሦስት የታመነ ነው ያልነው እንዲህ ነው። በኢትዮጵያ ያሉ ፈላሾች ሥራቸውና ምንጫቸው ያለ ጥርጣሬ ከእሥራኤል ዘር ናቸው። ከፖለስቲና ከእሥራኤል አገር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ግን ሰዋዘመኑ ሦስት ጊዜ ነው።*
>
> *መጀመሪያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከእሥራኤል ሕዝብ አብረው የመጡ ናቸው። በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የኢትዮጵያ ሕዝብና ነገሥታት የመንግሥትም ዘር ሁሉ በወንጌል ቃል አምነው ክርስትና ሲዝ እዚሉ ግን ከወንድሞቻቸው ከሕዝባቸውም ተለይተው በወንጌል ቃል አናምንም ክርስትና አንገባም ሕገ አሪትን አንለቅም ብለው ተለይተው የቀሩ ናቸው።*
>
> *ሁለተኛ፥ አስብያኖስና ጢጦስ የሮም ነገሥታት ኢየሩሳሌምን ባፈረሰዋት ቤተ መቅደስንም ባቃጠሉና እሥራኤልንም በፈጁዋቸው ጊዜ ከሞት የተረፉ እሥራኤል በያገሩ ሲበታተኑ አንድ ክፍል ከፖለስቲና ተነደው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ።*
>
> *ሦስተኛ በጉዲት ዘመን ከሶር ንጉሥ ሸሽተው ከጉዲት ጋር ኢትዮጵያ ገብተው የክርስቲያንን መንግሥት የገለበጡና ያፈርሱ የአክሱምንም ቤተ ክርስቲያን ያቃጠሉና ክርስቲያንን ያረከሱ ናቸው። እነዚህም የፊተኞች ፈላሾች ኩለኞች ጋር ተቀላቅለው ጉዲትን ረድተው መንግሥትን ቢያፈርሱ በክርስቲያን ላይም ሞፍ እየሰሩ ሃይማኖተ መንጌል ቢያረክሱ ጉዲት በሞተች ጊዜ የክርስቲያን ንጉሥ አንሰላ ውድም በነገሠ ጊዜ እነዚህን ፈላሾች ፈጃቸውና የክርስቲያንን ደም ብድር መለሰ።*
>
> *ከዚህ በኋላ ጥቂት ከሞት የተረፉ በጹር በገደል የነበሩ ፈላሾች ሁሉ ማረን ሰለ እግዚአብሔር ብለህ ይቅር በለን ብለው ደንጊያ እየተሸከሙ ... ገብተው ቢለምኑት ንጉሡም ነፍሳችሁን ምሬአች ኋለሁ ከርስት ከጉልት ግን ነቅያችኋለሁ ብሎ ነቀላቸው። በዚህም ከጉልት ተነቅለው ሰደተኞች የክርስቲያን ዜጎች ጥገኞችና ጢሰኞች ሁነው ኖሩ። ሰለዚህም ፈላሰያን ተባሉ። ፈላሰያን ማለትም ሰደተኞች ማለት ነው። በዘመኑ ብዛትም ፈላሻ ተባሉ።*
>
> *እዚህ ሕዝቦች እሰከ አጼ ዓምደ ፅዮን ዘመን (1313-1344) ከዚያም ወዲህ እሰከ አጼ ሠርፀድንግል ዘመን (1563-1597) ድረስ በክርስቲያን መንግሥት እየሸፈቱ ያውኩ ነበር። በዚያም ምክንያት ነገሥታት ቀጠቀጥዋቸው። አደከምዋቸው። ያለ ምህረት አጠፍዋቸው። አጠቁዋቸው። ዛሬ ግን የቀሩት ጥቅቶቹ በክርስቲያን ላይ ራሳቸውን የማያቀኑ የተጠቁ ሆኑ። በያሉ ጥቂት ጥቂት አሉ። የሚበዙ ግን በጭልጋ፥ በጋባ፥ በአርማጭሆ፥ በወልቃይት፥ በጠገዴ፥ በቆላ ወገራ፥ በሳንደር ከተማ ዙርያ ይኖራሉ።*
>
> *እነዚህ ሕዝቦች ጊታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመሰቀል ከመግደላቸውና ለወንጌል ሃይማኖት ካለመታዘዛቸው በላይ ደሙ በእኛ በልጆቻችንም ላይ ይሁን ያሉት መርገም ደርሶባቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመባል ፈንታ በዓለም ላይ ተበታትነው ነበር። እንደዚሁም ብዙ ችግርና መከራ ደርሶባቸው በብዙዎች ዘንድ ተጠልተውና ተንቀው ይኖሩ ነበር። ... ሰለ ነገደ ፈላሻ ታሪክ በክብረ ነገሥት በገፅ 195-197 ተመልከት።*[46]

በአለቃ ታዱ የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የቀረበ ሂስ

በትንሹ፥ ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት ውስጥ በታላቁ የሰሜን ምሰራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይ በጥንቱ የግብፅ ቸይሮግላፊክስ፥ በደአማት፥ በሳባ፥ በግዕዝ፥ በግሪክ፥ በላቲንና

[44] Ibid., p. 21
[45] Ibid., p. 27

[46] Ibid., p. 34-35

በአረብኛ ቋንቋዎች በልዩ ልዩ ሥፍራዎች፥ ጊዜያት፥ መንገዶች፥ መጓጓዣዎችና ምክንያቶች ተቀርጸው የሚገኙትን የኢትዮጵያ ጥንታዊ የታሪክ መረጃዎችን የማያውቁ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ከ1270 ወዲህ የአገሪቱን ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በመካ ከለኛው ምስራቅ ከጥንታዊ ይሁዲውያኑ የሃይማኖት ትምህርትና ትውፊት ጋር በቅርብ አዛምደው በማቅረቡ ከላይ በከበረ ነገሥትና በአለቃ ታዱ የቀረበውን የተረት ቅኝት አድርገውታል።

በዚህ በከበረ ነገሥትና በአለቃ ታዱ የኢትዮጵያ ታሪክ ግድፈት ላይ በ1984 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር መጽሔት ውይይት ቅፅ 1 ቁጥር 2 «ተረትና ታሪክ በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የሚከተለው ሂስ ቀርቧል። በፕሮፌሰሩ ሂስ እንደተባለው፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ታሪክን ከሃይማኖት ጋር አያይዘው በማቅረብ ተግባር ዕውቅ ባለሙያዎች ናቸው። በፕሮፌሰሩ ቃል፦

... በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የጥንት ጸሐፊዎች በጣም የታወቁ ናቸው። ለምሳሌ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ከሀገራችን ታሪክ ጋር በቅርብ ያዛምዱታል። ሕዝቡ ሳይቀር ከጥንት እሥራኤል አገር የመጣ ነው እያሉ ይተርታሉ። የንግሥት ሳባና የቀዳማዊ ምኒልክ ተረት ይህንን ነው የሚያስተምረው። ካህናቱ እንደእውነት አድርገው ተቀብለውታል። በየመድረኩም ይሰብኩታል። በካህናት እንደበት የሚነገር ደግሞ እንደሃይማኖት አጥብቆ ስለሚያዝ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ትውፊትና አፈታሪክ ውስጥ በጣም ዘልቆ ገብቷል። ነገሥታቱ መኳንንቱ ካህናቱና ተራው ሕዝብ እንኳ ሳይቀርቱ ዘር ሲቆጥሩ ወይም ከንግሥት ሳባና ከልጇ ከቀዳማዊ ምኒልክ ወይም ከምኒልክ ጋር የእሥራኤልን ታቦት ሠርቀው መጡ ከሚባሉት ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ካንደኛው ነው የሚጀምሩት። ሰለሞናዊ የሚባለው ሥርወ መንግሥት መነሻው ከዚሁ ተረት ነው፥ የፈላሻ ሕዝብም እንደዚሁ።

ይህ ተረት ከየብራና መጻሕፍቱ ሲገለባበጥ፥ በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በሃያኛው መጀመሪያ ላይ እስከተነሱት የታሪክ ጸሐፊዎቻችን ድረስ ደርሷል። በተለይ አለቃ ታዱ የጻፉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በዚህ ነገር እጅግ ተብከሏል።...

አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእሥራኤል ወይም ከሰነዓን እንደመጣ አድርገው ነው የጻፉት። ይህ ነገር አሁን እኛ ለምና ደርገው የታሪክ ምርምር አንዳንድ ችግር እየፈጠረ ነው። ብዙ ጊዜ ቃለመጠይቅ የምናቀርብላቸው አዛውንት በዚህ ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ የታተመውን የአለቃ ታዱ መጽሐፍ ያነበቡ ናቸው። ታዲያ እንደሕዝባቸው ታሪክ አድርገው መልሰው የሚነግሩን ከአለቃ ታዱ ያገኙትን ይሆንብናል። ሌላው የታሪክ

ጸሐፊያችን አቶ አጽሜ ግን ለዚ ንግሥት ሳባና ቀዳማዊ ምኒልክ ተረት የተለየ አስተያየት አላቸው። ከቀደሞ ጀምሮ የሚነገረውን ይመዘግቡና ሲጨርሱ እንዲህ ሲሉ በፈገግታ ይደመድሙታል። 'ይህ ነገር እንትፋት፥ ጥፋት ነው አውነቱ ከውሸት ስለአልተለየ። በዘንዶ መቅደስ ጽላተ ሙሴ ገቸበት።'

ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከእሥራኤል ጋር የማያያዝ ነገር ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃ የለውም። እንዲያውም ያሉን አስተማማኝ የታሪክ ቅሪቶች በቱጥታ ይቃወሙታል። ቀዳማዊ ምኒልክና ጓደኞቹ የእሥራኤል መጣቶች ከኢየሩሳሌም ታቦት ሰርቀው አክሱም ኩተማ ቤተ መቅደስ አናሩት በሚባልበት ጊዜ አክሱም ገና አልተቆረቆረችም። አክሱም ከተማና የታሪክ ዘመን የሚጀምረው የቀዳማዊ ምኒልክ አባት ነው ከሚባለው ከንጉሥ ለለሞን 800 ዓመታት ያህል ቆይቶ ነው። የአይሁዶችም ሃይማኖት በዚያን ጊዜ ተመሥርቶ፥ ንጉሡ ተከታዮችና ሕዝቡ ሁሉ ተቀብለውት፥ በዚያ ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከአብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ ሃገር የሚባለውም እንዲያው የሃይማኖት ተረት ነው እንጂ የታሪክ መሠረት የለውም። ግዕዝ የመጻፊያ ቋንቋ የሆነው ከለለሞን በኋላ 1150 ዓመታት ያህል ቆይቶ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል። የአክሱናውያንም ሆነ የቅድመ አክሱም ነገሥታት፥ የክርስትና ሃይማኖት በ350 ዓም አካባቢ ከመመ ሥረቱ በፊት የገዙት በሙሉ በአምልኮ ጣኦት ይኖሩ ነበር እንጂ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች እንዳልነበሩ በሚገባ ታውቋል። ቡተለይ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ነው አቶ አጽሜ በኢትዮጵያ ያለውን ሃይማኖት «በአሪት ቅመም የተቀመመ፥ በአረመኔ ቅቤ የተጣፈጠ ክርስትና ነው» ብለው በረቀቀ አንደበት ሂስ ያቀረቡት።

ተረቱ መቸ እንደጀመረ ቁርጥ ያለ መረጃ ገና የለንም። ግን ከአክሱም ዘመነ መንግሥት የመጡልን አስተማማኝ ሰነዶች አይጠቅሱትም። ይህም በዚያን ዘመን ተረቱ ገና እንዳልተፈጠረ ያመለክተናል። ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገሩ ከኢትዮጵያ ጋራ ተያይዞ የምናገኘው በ350 ዓም አካባቢ ባንድ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጽሐፍ ነው፥ ግለትም የአክሱም መንግሥት ከወደቀ በኋላ፥ 'የጨለማ ዘመን' ተብሎ በሚጠራው ዘመን። ይህም መሆኑ አያስደንቅም። ምክንያቱም እንደዚሂ ያሉ ተረቶች የሚያዘጋጉት ተጨባጭ የታሪክ መረጃ በማይኖርበት 'በጨለማ ዘመን' ነው። በሀገር ውስጥ የመንግሥት ኃይል ወድቆ የሥነ ጽሑፍ ሥራ ተዳክሞ የትምህርት ተቋሞች ተበታትነው፥ የታሪክ ቅርስ ለማቆየት በማይቻልበት ጊዜ ነው በተለይ አፈታሪክ የሚስፋፋው። ከዓመታት በኋላ በጽሑፍ ይሰፍርና ይተሳሰፋል፥ ሥር ይሰዳል። የንግሥተ ሳባና የቀዳማዊ ምኒልክ ተረት መልክ ይዞ በመጽሐፍነት ተቀናብሮ፥ ከብረ ነገሥት በሚል አርዕስት የተዛፈው በአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመን

(1313-44) መሆኑ ተረጋግጧል። ያጻጻፉም ዋና ሂደት በአደፋ/ላሊበላ መንግሥትና በጎላ ሰለሞናዊ ነኝ ብሎ በሚኖረው አዲስ ሥርወ መንግሥት መካከል ከነበረው የሥልጣን ትግል ጋር የተያያዘ መሆኑን ብዙ ነጥቦች ያመላክቱናል። የሰለሞናዊያን ንግሥና ከተቋቋመ በጎላ የሕገ መንግሥትነት ባሕርይ አግኝቶ እጼ ኃይለ ሥላሴ (1930-74) ከሥልጣን እስኪወርዱ ድረስ ይቆያል።

ሌሎችም በተመሳሳይ ዓይነት የተፈጠሩ ተረቶች በታሪካችን ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ያላቸው ሞልተዋል። የፈላሻች ጥንታዊ አይሁድነት ጉዳይ እንደኛው ነው። በየመጽሐፉ ጉዲት እየተባለች የምትጠራዋ ሴትም በሚነገርላት ታሪክ አንባር እንዲያው የተረት ፈጠራ ናት። በዚያው 'የጨለማ ዘመን' በተባለው ጊዜ ነው የተፈጠረችው። የአክሱምን ትልቅ ኃይል አውዳደቅ በተጨባጭ ታሪክ ማስረዳት ሲያውክ አንድ የታወቀች ሴት ከሌላ ዘመን ከሌላ ሕዝብ ከሌላ አህጉር ተወስዳ በአክሱም ታሪክ ላይ የተወረወረች ዝገዝ መሪ ናት።

ስለዝህ ትረታዎች ይዘት መሠረታዊ ችግር ትከክለኛውን መሰመር የሚያመለክቱ አንዳንድ የታሪክ ጽሑፎች ቀርበዋል። ነገር ግን የእምነት ኃይል ጠንካራ ስለሆነ ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ አክሱማዊነት የዘውድ ሥርዓት ደጋፊ ከሆኑ ግለሰቦች ጀምሮ እስከ ተራ ቤተሰቦች ድረስ ይነገራል። ካህኑም ይተርተዋል። በጎና ደርዳሪ ውም ሥነጥበቡ ከዚያ የተገኘው ነው እያለ ያወሳናል። የጉዲትም ተረት መነገር ቀጥሏል። እዚህ ላይ ማንሳት የተፈለገው ዋና ነጥብ ከአባቶች የሚነገሩን አፈ ታሪኮች ሁሉ እንዳሉ እንደታሪክ መወሰድ እንደሌለባቸው፥ በታሪክ ምርምር ዘዴ አስተማማኝነታቸው መለካት እንደሚችልና ትክክለኛ ሥፍራቸውን ማግኘት እንደሚገባቸው ነው። ይልቁንም አሁን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የሚወስኑበት ሥርዓት በተዘረጋበት ጊዜ የየብሔረሰቡ ምሁራን የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ያልተጣሩ ተረቶችና አፈታሪኮች ይዞ መሯሯጥ ለሕዝቡ የዘለቄታ ታሪክ ይዘት ጥፋት እንደሚያመጣ መገንዘብ ያሻል።

የክርስትና ታሪካዊ መነሻና ትምህርት

ከዚህ በላይ በቀረቡ የጥናት ርዕሶችና ትችቶች በአንድ ብኩል በ330 የክርስትና ሃይማኖት ወደ አክሱማውያን አገርና ቤተ መንግሥት ከመግባቱ በፊት ለ1260 ዓመታት በኢትዮጵያ መለኮታዊ የአሪት ሃይማኖትና ሕግ ኦር የሚለው የክብረ ነገሥትና የእነአለቃ ታዬ ተዛማጅ መጻሕፍት ትምህርት ላለፉት ሰባት ምዕተ ዓመታት (1270-1974) በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጅጉ ተስፋፍቷል።

በሌላ በኩል በተጠቀሰው ረጅም የታሪክ ዘመን በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክና የላቲን ቋንቋዎች በልዩ ልዩ

ስፍራዎች፥ ጊዜያት፥ መንገዶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች የተቀ ረጹ የታሪክ መረጃዎች የኢትዮጵያ ጥንታዊ ደአማታውያን፥ ትሮጅ ሎዳውያን፥ አክሱማውያን፥ የሐርላ፥ የሀዲያ፥ የጎንጋ ሕዝቦችና መንግሥታት ሁሉም በየአካባ ቢያቸውና በየዘመናቸው ገና አቀማዊ አማልክትንና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ሕዝቦች እንደሆኑ ያሳያሉ።

በመሆኑም ከመካከለኛው ምስራቅ በአውሮፓዊ ግሪኮ-ሮማውያን ፍሬምናጦስና አደሰዩስ አማካይነት መለኮታዊ የክርስትና ሃይማኖት በ330 ዓም ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ቀጥሎም በ5ኛው ምዕተ ዓመት አረጋዊ፥ ጳንጠሌዎንን፥ ገሪማ፥ ሊቃኖስ፥ ይምአታ፥ ፅሕማን፥ ጉባ፥ አፍጼና፥ አሌፍ የተሰኙ ጻድቃን በአክሱም ከተማ መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ከመተርጎማቸው በፊት የአሪት ሃይማ ኖትና ሕግ በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት መገኘቱን የሚያመ ለክት የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ገና አልተገኘም።

በዚህ ረገድና ተግባር በዓመተ ዓለም ከ2100 አካባቢ ጀምሮ ለ2000 ዓመታት ግለትም ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ድረስ በመካከለ ኛው ምስራቅና በግብፅ በረሀብና በጠርነት ችግሮች ዘወትር ከአገር ወደ አገር ሲሰደድና ሲጓዝ እንደኖረ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚነገርለት ሴማዊ የይሁዳውያኑ አናሳ ዘላን ሕዝብ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጥንታዊ የጡንት-ኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጋር በጎንድ ሆነ በባህል ወይም በሃይማኖት በምንም መልክና መንገድ ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረጉን የሚያሳይ አንዳችም የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ የለንም።

በሌላ በኩል በእስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጡንት-ኢትዮጵያ ነባር ሕዝብና መንግሥት በዓመተ ዓለም ከ2800 አካባቢ ጀምሮ እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በድምሩ ቢያንስ ለ3440 ዓመታት ከሦስቱ ታላላቅና ተከታታይ የግብፅ፥ የግሪክና የሮማ ውያን መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ጋር በጎንድ፥ በባህልና በሃይማኖት በየዘመኑ የቀረበ መስተጋብርና መወራረስ እንደነበረው በዚህ ጥናት ከላይ በተጠቀሱ የሃይሮግላፊክስ፥ የግሪክና የላቲን መረጃዎች በሥፍራ፥ በጊዜና ተግባር ቀመር ውስጥ በትክክል ተረጋግጧል።

ከላይ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው በዓመተ ዓለም ከ2800 እስከ 1000 ድረስ ለ1800 ዓመታት በመር ከብና በሲራራ የንግድ ጉዞዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጡንት-ኢትዮጵያ ምድር ወደ ግብፅ በሚወሰዱ ብዙ ዓይነት የግዕድን፥ የእንሰሳት፥ የአዝዕርት፥ የእፅዋት፥ የአፅዋፍና የአራዊት ምርቶች ዝርዝር ልዩ ልዩ የብረታ ብረት፥ የወርቅ፥ የብር፥ የነሐስ፥ የመድሐኒትና የጌጣ ጌጥ ዕቃዎችና

ቀለሞች፥ የመጫ፥ የዕጣን፥ የከርቤ፥ የቀረፋና የዝንጅብል ቅመማ ቅመም፥ የዝሆን ጥርስ፥ የአውራሪስ ቀንድ፥ የሰንን ላባና እንቁላል፥ ድብና የድብ ቆዳ፥ ቀጭኔ፥ ቀበሮ፥ ዝንጀሮ፥ ሱሳግ ውሻ፥ አህያ፥ በሬ፥ ጥጃ፥ ልዩ ልዩ የእንጨት ምርቶች ለዓይነት የሚጠቀሱ የከፍለ አህጉሩ የተፈጥሮና የእርሻ ሀብቶችና ምርቶች ናቸው።[47]

በዓመተ ዓለም ከ332 እስከ 30 ድረስ ግብፅን በቀጥታ ይዘው ለ300 ዓመታት የገዙ ግሪኮች ቸከፍለ አህጉሩ በቀይ ባሕር፥ በኤደን ባሕረ ሰላጤና በሕንድ ውቅያኖስ ጠረፎች ላይ ቋሚ የንግድ ኬላዎችን፥ ከተሞችንና ገዘያዎችን መስርተው በንግድ በባህልና በሃይማኖት ከግብፅ፥ ከመካከለኛው ምስራቅና ከሜዲትራኒያን ባሕር ሕዝቦችና ሥል ጣኔዎች ጋር በቅርብ በማገናኘት በተጠቀሱ ጥንታዊ የአፍሪካ፥ የእስያና የአውሮፓ ሕዝቦችና በኢትዮጵያ አዳጊ የአክሱም መንግሥት መካከል በንግድ፥ በባህልና በሃይማኖት የመጀመሪያ ግንኙነቶችን ፈጠሩ።

ቀጥሎም ከ30 ዓመተ ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በግሪኮች እግር ተተክተው ግብፅንና አካባቢውን እስከ እስላማዊ የአረቦች ዓለማቀፋዊ እንቅስቃሴ ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት የገዙ ሮማውያን በአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ እስትራቴጂያዊ አካባቢዎች ላይ ለአክሱም መንግሥት እና ሥልጣኔ ዕድገትና መስፋፋት ብሎም ለሶስቱ መለኮታዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ምቹ ሁኔታዎችንና መንገዶችን ፈጠሩ።

ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል ለቀረቡት የጥንታዊ ግብፃውያን፥ ግሪኮችና ሮማውያን ተጨባጭ ግንኙነቶች በኢትዮጵያ ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ተገቢ ግምትና ዋጋ አልተሰጠም። በሌላ በኩል ግን በግሪኮ-ሮማውያን ምዕመናን ትምህርትና አመራር ሁለቱ የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊትም ሆነ በኋላ ከኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ጋር በምንም ሥፍራ፥ ጊዜና መንገድ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ግንኙነት ላልነበረው የይሁዳውያኑ ዘላን ሕዝብና ታሪክ በዘመነ ክርስትና ከ1270 ወዲህ ከዚህ በላይ በተዛግጅ የክብረ ነገሥትና የአለቃ ታዬ መጽሐፍት የቀረበውና ከኢትዮጵያ የታሪክ እውነታና እውቀት ጋር በፍጹም አብሮ የማይሄድ ታላቅ ሃይማኖታዊ ግምት ተሰጥቷል።

በዘመነ ክርስትና በ4ኛው ምዕተ ዓመት በሶሪያ እገር የጢሮስ ከተማው ሩፊኑስ የተባለው የሃይማኖት አስተማሪ ከእገሩ ፍሬምና ሮስና አደስዩስ የተባሉ ሁለት ግሪኮ-ሮማዊ ስደተኛ ነጋዴዎች በ330

[47] ላለ ጌ ድሊቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገጽ 58።

አካባቢ የአክሱምን አዋማዊ ቤተ መንግሥት ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንደለወጡና በኋላ ከሁለቱ ስደተኞች አንዱ ማለትም ፍሬምናጦስ በአስከንድርያ ከተማ በግብፁ ቤተ ክርስቲያን መሪ በፓትርያርክ አጥናቴዎስ (328-356) የአክሱማውያን ቤተ ክርስቲያን አስተማሪና መሪ ተደርጎ እንደ ተሾመ በትክክል ጽፏል።[48] በፍሬምናጦስ-አደስዩስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተለወጠው የአክሱም የመጨረሻው አዋማዊና የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሥ አጼ ኢዛና እንደሆነ ንጉሡ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊትና ከገባ በኋላ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች ከጻፋቸው ዜና መዋዕሎች በትክክል ታውቋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ እስከ ዛሬ ድረስ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ሐውልቶች ላይ የተፃፉና የንጉሡን ወታደራዊ ዘመቻዎች የሚገልፁ ብዙ ታሪካዊ የአጼ ኢዛና ዜና መዋዕሎች ተገኝ ተዋል።[49] ከ330 ዓም በፊት ጉና አዋማዊ በነበረ ዘመን በተጻፉ ዜና መዋዕሎቹ አጼ ኢዛና «አባቶቼ» ለሚላቸውና *ኣርስቱ መሕርምቱ ኣስተር፥ ብሔርና ምድር* ተብለው በአገርና በዓለም ደረጃ ለሚታወቁ አምስት አዋማዊ አማልክት ክብርና ምስጋና አምስት የወርቅ፥ የብርና የመዳብ ሐውልቶችን እንዳቆመላቸው በጽሑፎቹ ተገልጿል።

ነገር ግን በመጨረሻ አጼ ኢዛና ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከገባ በኋላ በሁለቱ የግዕዝና የግሪክ መንግሥታዊ ቋንቋዎች ተጽፎ በቅርቡ (1969) በአክሱም ከተማ በተገኘ በአንድ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ በግሪኩ ቅጅ በፊት «አባቶቼ» የሚላቸውን ከላይ የተጠቀሱ አዋማዊ አማልክትን ትቶ አሁን «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ... በእግዚአብሔር ልጅ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ»[50] በተሰኘ አዋጁ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሥ መሆኑን ለትውልድና ለታሪክ በይፋ አሳውቋል።

ከዘመኑ የታሪክ መረጃዎች እንደሚታወቀው፥ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአንድ በኩል በአገሪቱ ጥንታዊና አዋማዊ መንግሥት ምርጫ፥ ፈቃድና አመራር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በህብረተሰቡ ነባር ሥልተ ምርትና ሥርዓተ ማኅበር ላይ አዲስ ማህበራዊ የለውጥ ሁኔታና ሂደት አላመጣም።

[48] A. H. M. Jones and E. Monroe, A History of Ethiopia, (London L OUP, 1966), pp. 26-27.

[49] Littmann, DAE, Inscriptions Nos. 4, 6-11; Kammerer, Essai sur L' Histoire, pp. 89-97; "Christian Inscription of Ezana", S. Hablesellassie, History, p. 103.

[50] Ibid., "Christian Inscription".

በመሆኑም የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ነባሩ አዋማዊ ሀብረተሰብና መንግሥት ዘንድ በባህል ሆነ በእምነት ወይም በፖለቲካ ሥርዓት ተጓዳኝና ተዛማጅ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ፥ ለውጥና ውድ ቀት አላስከተለም። እንዲያውም በተቃራኒው ራሱን ከአገሪቱ ነባር አዋማዊ ሃይማኖት፥ ባህልና ሥርዓት ጋር በማቀናጀትና በማዋሃድ ከላይ በተጠቀሰው በአቶ አፅሜ ጥናት እንደተባለው «በአሪት ቅመም የተቀመመ በአረመኔ ቅቤ የተጣፈጠ» የኢዎማዊዝም፥ የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች፥ ባህሎችና ትምህርቶች ቅይጥ ሥርዓት ይሆናል።

በኢትዮጵያ የክርስትና አባት አስተማሪዎች

በኢትዮጵያ ለአዋማዊዝም፥ ለክርስትናና ለአሪት አማልክት፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ሥርዓታዊ መስተጋብር፥ መወራረስና ውህደት ብሎም ለኢትዮጵያ ጥንታዊና ዘውዳዊ የፖለቲካ ሥርዓት ቀጣይ ህልውና፥ ዕድገትና መስፋፋት በ5ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመታት በግምት ከ470 እስከ 550 ድረስ ባለው የስምንት አሥርታት ዘመን ውስጥ ታላቅ ድርጅታዊ፥ ትምህርታዊና ባህላዊ አስተዋጽኦ ያደረጉ ብሎም የኢትዮጵያ የሕዝብና ያገር ባለውለታዎች የሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ግሪኮ-ሮማዊ ጻድቃን ናቸው።

አንደኛ፥ የተጠቀሱት ጻድቃን መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተረጎሙ። የጻድቃኑ የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ለሁለቱም የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ዕድገት ትምህርታዊ፥ ባህላዊና ድርጅታዊ መሠረትና መሣሪያ ይሆናል።

ሁለተኛ፥ የተጠቀሱ ግሪኮ-ሮማዊ የሃይማኖት ምሁራን የግዕዝ ቋንቋን ታላቅ የሥነጽሑፍ መሣሪያ አድርገው በመግባት በኢትዮጵያ ለመንግሥትና ለሃይማኖት ሥርዓቶች ዕድገት እና መስፋፋት ብሎም ለአገሪቱ የባህልና የሥነ ጽሑፍ ድርጅታዊ ህልውና ወሳኝ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ እሙን ነው።

ሦስተኛ፥ በምሥጢረ ሥላሴ እምነታቸውና ትምህርታቸው ምክንያት ከአገራቸው መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መከራና ሥቃይ ደርሶባቸው በሽሽት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኛ ምሁራን በተጨማሪ በአገሪቱ የገዳምና የምንኩስና ሥራና የአሪት ሥርዓት በማቋቋም ለተዛማጅ የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ዕድገትና መስፋፋት ሌላ ድርጅታዊ መሠረት፥ መንገድና መዋቅር ፈጠሩ። በዚህ ረገድና ተግባር በአክሱምና አካባቢው እስከ ዛሬ ድረስ ለኢትዮጵያ የክርስትና ትምህርትና ባህል መሠረቶችና ማዕከላት የሆኑ ደብረዳሞ፥ አባ ገሪማና የመሳሰሉ ታሪካዊ የገዳም ተቋማትን መሠረቱ።

በዚህ የኢትዮጵያን ታላቅ የክርስትና ሃይማኖትና ባህል ግምባታ ተግባር በሚመለከት በግምት ከ330 እስከ 550 ድረስ በመጀመሪያ 220 ዓመታት ዘመን ከላይ በስም ከተጠቀሱት ግሪኮሮማዊ አስተማሪዎች ጋር የኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት ኢዛና (320-44)፥ አላአሜዳ (478-86)፥ ታዜና (486-93)፥ ካሌብ (493-534) እና ገብረ መስቀል (534-548) ከታላቁ የሃይማኖት ምሁር ያሬድ ጋር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሥራችና ገምቢ አባቶች እንደሆኑ ለምን ጊዜም በትውልድና በታሪክ ዘንድ ሙሉ እውቅና የማይነፈግ የታሪክ እውነታና እውቀት ነው።

የኢትዮጵያ የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን

በግምት ከአክሱሙ ንጉሥ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (534-548) እስከ ሰለሞናዊ ንጉሥ አምደፅዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344) ድረስ በስምንት ምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ሆነ ቤተ ክህነት በወቅቱ የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የጻድቃን ገድሎች ማለትም የታሪክ መረጃዎች የማይገኙ በት ረጅም «የጨለማ[51] ዘመን» ነው።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ በአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ቃል «አሁን ያለው የአክሱሙም የዛጉየውም ታሪክ መዘጋጀት የጀመረው በ14ኛው መቶ ዓመተ ምህረት ላይ በአጼ አምደፅዮን ጊዜ ነው። ታሪክ ነገሥታት የምንለው በየበኩሉ ወይም በየዘመኑ አንዳንድ የዘመኑ ሊቅ ያዘጋጀው»[52] ዜና መዋዕል ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎችን አጠቃላይ የታሪክ መረጃ፥ ሥልትና ትምህርት በሚመለከት ከአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በቀረበው ሂስ እንደተባለው፥

> *ከርስትና ከገባ ወዲህ በአክሱምም በላስታም በሸዋም በጎንደርም የነበሩ የኛ ሊቃውንትና ጸሐፊዎች ከቤተ ክህነት መንፈሳዊና ከቤተ መንግሥት ዘመናዊ አገልግሎት ወይም የነገሥታቱን ዜና መዋዕል ከመጻፍ በቀር ይልቅኑም ከጽርዕ (ከግሪክ) ከዕብራይስጥ ከአረብና ከሶፕት እንደስንክሳር እንደ ሃይማኖተ አበው እንደግዝት የመሳሰለውን መንፈሳዊ ጽሑፍ ከመተርጎምና ከመገልበጥ በቀር በታሪክ ረገድ መመርመርና መጻፍ መሰብሰብ እየሰበሰቡም በቀድሞው ላይ መጨመር ምንም ያህል አስፈላጊነቱ በዚያን ጊዜ የተሰማቸው አይመስልም። ያለውን ቡቂ አድርጎ በመመልከት በአክሱምና በዙሪያው በአዱሊስ በክስክሲ በየሀ በቆሃሂት ታሪካዊ ጽሑፍ ተሸክመ ቆሞ*

[51] Budge, History, pp. X-XI, 204, 563

[52] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም ዛጉዬ፥ (አዲስ አበባ፥ 1966) ገጽ 344።

ይኖር የነበረው ልዩ ልዩ ሐውልትና ዙፋን በዘመን ብዛት የቆመው ሲወድቅ የወደቀው ከነጽሕፈቱ ለመበለሽ ሲደርስ የንጉን ቁም ነገረኛነት ተመልክቶ የሐውልቱን ሥዕል ለማንሣት ጽሑፉን ለማስገልበጥና ለመገልበጥ ለመተርጎም በፊተኛው ዘመን የሞከረ ከኛ ወገን የለም።[53]

በተጠቀሰው ረጅም የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን በውቅቱ በአጎራባቹ የአረብ ዓለምና ሕዝቦች ዘንድ በዘልማድ «ሀበሻ» ብሎም በኋላ በአውሮፓውያኑ ትርጉም «አቢሲኒያ» ተብሎ በሚጠራው በዛሬው የሰሜን ኢትዮጵያ ተራራማ ክልል የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት፥ «የፈላሻ» ሕዝብ የአሪት ሃይማኖት፥ ክስተትና ዕድገት፥ የአገው ክርስቲያን መንግሥትና የገዥው መደብ ዕድገትና ውድቀት እንዲሁም በመጨረሻ በ1270 በሁለት የአማራ መሳፍንቶች ኢየሱስ ሞዓ እና አቡነ ተክለሃይማኖት ትምህርት ይኩኖ አምላክ በተሰኘው የጦር አበጋዝ መሪነት በክሳን ከጥንት ይሁዳውያኑ «ምርጥ» የአብርሃም፥ የሙሴ፥ የዳዊት፥ የሰለሞን ዘር በመሆኔ የአገው ዘውድና ዙፋን ሕጋዊ ወራሽ ነኝ ብሎ ራሱን የሰየመው አዲስ «ሰለሞናዊ» መንግሥትና የገዥው መደብ ክስተትና ዕድገት የመሳሰሉ ታላላቅ የፖለቲካ ሁኔታዎች፥ ኃይሎች፥ ሂደቶችና እንቅስቃሴዎች እንደተካሄዱ፥ እንደ ተፈጸሙ፥ ቦተረት መልክና መንገድ ይታወቃል። የተጠቀሱ ሁኔታ ዎችንና እንቅስቃሴዎችን መሳሳ፥ ተዋንያን፥ ክስተትና ዕድገት እስመ ልክቶ በወቅቱ የተመዘገቡ ተጨባጭ የታሪክ መረጃዎች እስከዛሬ ድረስ ስላልተገኙ የዘመኑ ታሪክ በሙሉ የተረት ቅኝት ሆኖ ቀርቷል።

የክርስትና የዕድገትና የመስፋፋት ዘመን 1270-1524

በ470-550 ዘጠኙ ጻድቃን በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በመተርጎም፥ በሌላ በኩል ደግሞ የገዳምና የምንኩስና ሥርዓት በማቋቋም ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በአክሱም ከተማና አካባቢው በጠንካራ መሠረትና መንገድ እንደጎበት ይታውሳል።

አሁን ደግሞ ከላይ ከተመለከተው የጨለማ ምዕተ ዓመታት ዘመን በኋላ በ1270 በመህል ሰሜን በምድረ አማራ (በቤተ አማራ) ማለትም በዛሬው የወሎ ክልል የአገውን የክርስቲያን መንግሥትና የገዥው መደብ አጥፍተው የመንግሥት ሥልጣን የያዙ ሰለሞናዊ ነገሥታትና ካህናት በብዙ አዳዲስ የወንጌል፥ የድርጅት፥ የፖለቲካ፥ የትጥቅና የሥነጽሑፍ ሥራዎች በመህል የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የአቀማመዝም፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶችን

[53] Ibid., pp. 102-103

ከሚከተሉ ብዙ ነባር ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር ዘውትር እየተዋጉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁለተኛውንና ታላቁን የዕድገትና የመስፋፋት ዘመን (1270-1524) ፈጠሩ።[54]

በዚህ ረገድና ተግባር አንደኛ፥ በተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት ዘመን መባቻ ላይ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ያዝ ተወላጅ የሃይማኖት መምህራን ማለትም የሐይቁ ገዳም መምህር ኢየሱስ ሞዓ (1211-1292) በመህል ሰሜን፥ የደብረሊባኖሱ ገዳም መሥራች አቡነ ተክለሃይማኖት (1215-1313) በደቡብ፥ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ሲንበት[55] መሥራች መነኩሴ አዎስጣጤዎስ (1273-1352) በሰሜኑ ክልል፥ በየአካባቢያቸውና በየዘመ ናቸው የቤተ ክርስቲያኑ ጠንካራ አስተማሪዎች ሆነው ተነሱ።

እነዚህ የብዙ ክርስቲያኑ ብርቱ አስተማሪዎች ከብዙ ተማሪዎቻ ቸውና ተከታዮቻቸው ጋር በጥንቱ ዘጠኝ ጻድቃን ጅምር የወንጌል፥ የገዳምና የግዕዝ ሥነጽሑፍ ሥራዎች መሠረትና ሞዴል መመሪያ በከፍለ አህጉሩ መህል አካባቢዎች በየክልላቸው የየራሳቸውን ብዙ አዳዲስ የወንጌል፥ የገዳምና የግዕዝ ብራና ጽሑፍ ሥራዎችን እንቅስ ቃሴዎችና የአሠራር ሥልቶች አዳብረው በመጠቀም በተጠቀ ሰው ዘመን የክርስትና ሃይማኖትን በሰሜን ከምፅዋ-ሐማሴን በምዕራብ እስከ ጎጃም፥ ዳሞትና እናርያ ገዳማትን እንደመሠረቱ በዘመኑ በብዙ የኢትዮጵያ፥ የአረብና የአውሮፓ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ ሥፍራዎችና ጊዜያት የተጻፉ የታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ።[56]

ሁለተኛ፥ በዚህ የክርስትና ሃይማኖት ዕድገት እና መስፋፋት ጉዳይ፥ በወደቀው የአገው መንግሥትና የገዥው መደብ ላይ ከቤተ ክርስቲያኑ አመራር ጋር የፖለቲካ ጥቅምና ትብብር የነበራቸው፥ ራሳቸውን «ምርጥ» የሰለሞን ዘርና የዘውድ ወራሽ ነጋሢያን ነን ብለው የሰየሙ አዬ ነገሥታት በተለይ ይኩኖ አምላክ (1270-1285)፥

[54] Taddesse Tamrat, "The Abbots of Dabra-Hayq", 1248-1535", JES? Vol. 8, No. 1 (1970), pp. 87-117; ibid., Church and State in Ethiopia 1270-1527 (London: OUP, 1972).

[55] Ibid., Church and State, pp. 206-207.

[56] Ibid., Champs. 5, 6; Ibn Fadl A. Umari, Masalik El Absar fi Mamalik El Masar, tr. and ed., G. Demombynes, (Paris, 1927); Maqrizi, The Book of the few knowledge of the Moslem Kings in Abyssinia, tr. by G. W. B. Huntingford (Typescript, 1955); Crawford, Itineraries; Arabfaqih, Conquete; F. Alvarez, The Prester John of Indies, 2 Vols., trs and ed., C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford (1961); Bahrey, History of the Galla, C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford, trs. and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646, (London: 1954).

ዓምደፅዮን (1314-1344)፥ ዳዊት (1372-1413)፥ ይስሐቅ (1414-29)፥ ዘርዓያዕቆብ (1434-68) እና በዕደማርያም (1468-78) በክፍለ አህጉሩ የአዋጣዊዝም፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ነባር ሕዝቦችንና መንግሥታትን በክርስቲያኑ ግዛት ሥር በማምጣት ለክርስትና ሃይማኖት ዕድገትና መስፋፋት የበለጠ አመቺ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ፈጠሩ።

ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል የቀረበውና ከዘመነ አክሱም ጀምሮ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እኽክ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ ግራኙ የአመፅ ጦርነት ድረስ ለረጅም ዘመን በክፍለ አህጉሩ ከሰሜን ወደ ደቡብ፥ ወደ ምዕራብና ወደ ምስራቅ አካባቢዎች የተካሀደው የክርስቲያን ሃይማኖትና መንግሥት የዕድገትና የመስፋፋት አንቅስቃሴ በታላቁ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለዛሬው የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ጎብረ ተሰብና መንግሥት ዕድገት ታሪካዊ መነሻዎችና መሣሪያዎች ከሆኑ ብዙ ታላላቅ ሕዝባዊ የፍለሳ፥ የጦርነት እና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች አንዱና የመጀመሪያው ሆነ።

3. የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻ፥ ዕድገትና ውድቀት

የሰሜን/ፈላሻ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪካዊ ፋይዳ

ራሱን «አይሁድ» እና «ቤተ እሥራኤል»[57] ብሎ በተለዋጭ ስሞች የሚጠራውና በሌላ በኩል ደግሞ ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት መዛግብት ብሎም በውጭ ሰዎች «ፈላሻ»[58] ማለትም ስደተኛ፥ መጤ፥ ባዕድ ተብሎ የሚታወቀው የኢትዮጵያ አንድ የጎንደር አማራ ማኅበረሰብ ሲሆን አሁን በቅርቡ በመካከለኛው ምስራቅ የጥንት አገሬና ሕዝቤ ወደሚለው ወደ እሥራኤል አገር ከሞላ ጎደል ጠቅልሎ በፍለሳ ገብቷል።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የጥንቱ ታሪክ የማህበረሰቡ እውነተኛ ስምና አገሩ አይሁድም፥ ቤተ እሥራኤልም፥ ፈላሻም፥ አማራም፥ ሳይሆን «ሰሜን» እንደሆነ የታሪክ መረጃና ትምህርት በሥፍራና በጊዜ መስፈርት ያሳያል። በዚህ ረገድና ተግባር በዘመነ ክርስትና በቅደም ተከተል በ300ዎቹና በ320ዎቹ አሥርታት አካባቢ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው በተገኙ የአክሱም አዋጣዊ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች መሠረት የማህበረሰቡ እውነተኛ ስምና አገር «ሰሜን» ነበር። አገሩም በዛሬው ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜና በዓባይ ወንዞች የመነሻ ክልል ታላቁ የሰሜን ተራራ በሚገኝበት በዘመኑ የአክሱም መንግሥትን በምዕራብና በደቡብ ከመህል አገር ሕዝቦችና ገዢዎች ጋር የሚያገናኝ አንድ ቁልፍ እስትራ ቴጂያዊ የጂኦፖለቲካ ምድር ነበር።

ከዚህ አኳያ በ300ዎቹ በአዱሊሱ የቀይ ባሕር ወደብ ከተማ ላይ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈበትን የድል ሀውልት «አባቶቹ» ለሚላቸው የግሪክ አማልክት አርስ፥ ዘዩስና ፖሴዶን መታሰቢያ ያቆመው አንድ አዋጣዊ የአክሱም ንጉሥ በነገሠ በ27ኛ ዓመት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በላይኛው የዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ በአራት መታደራዊ እርምጃዎች የግዕዝን፥ የአጋሜን (የአጋዚን)፥ የአገው[59] (የአታገውስን)፥ የስሬን (የዛጋሬን)፥ የአድዋን፥ የሰሜንን[60]

[57] Wolf Leslau, Falasha Anthology: The Black Jews of Ethiopia, (New York, 1951); pp. IV-X

[58] Huntingford, Amba Seyon, pp. 61-62.

[59] Cosmas, Christian Topography of Cosmas, tr. & ed., J. W. MaCrindle (London, 1897); p. 61.

[60] Ibid.,

(የፈላሻን) የቤጃን፥ በምዕራባዊ አረቢያ ጠረፍ በለኡህመና በኤደን የወደብ ከተሞች መካከል ደግሞ የአራቱንና የኪናይዞይልፕቴን አገሮች ጨምሮ በአራቱ አጎራባች አካባቢዎች በድምር በ30 የሚቆጠሩ አሮችንና ሕዝቦችን ባጉሩ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በምድርና በመርከብ ዘመቻዎች እንዴት እንዳስገበራቸው ቤሐውልቱ ሰነድ ይተርካል።

የአክሱምን ሥዩተ አፄ በሁለቱ አጎራባች የአፍሪካና የእስያ አህጉራት ላይ መሥራች እንደሆነ የሚነገርለት ይህ የአክሱም ንጉሥ በአክሱምና በላስታ አካባቢዎች የግዕዝን፥ የኢጋሚን፥ የአድዋንና የአገውን አገሮች ጨምሮ ብዙ ሉአላዊ መንግሥታትን ካስገበራቸው በኋላ ከአክሱም ከተማ በደቡባዊ ምዕራብ አቅጣጫ የተከዜን ወንዝ በጦር ተሻግሮ፥ ዓሙቱን በሙሉ ዝናብ፥ ብርድ፥ ውርጭና በረዶ በማይጠፋባቸውና ለመውጣትም በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ከፍተኛ ተራሮች ላይ በሚኖረውና «ሰሜን» በሚል የአገርና የሕዝብ ስያሜ በሚታወቀው በአንድ ሉአላዊ ሕዝብና መንግሥት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ያካሄደውን የወረራ ጦርነት በአንክሮ ይገልጻል።

ይህ በአዱሊስ ሐውልት ላይ በንጉሡ ተጽፎ በኋላ በ522 በግሪኩ መነኩሴ ኮስማስ ተገልብጦ ለትውልድና ለታሪክ የተላለፈው የጦርነት ዘገባ በሁለቱ አጎራባች የአክሱምና የሰሜን ሕዝቦችና መንግሥታት መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት ታሪካዊ መግለጫ ነው።

ይህ በጥንቱ አጎራባች የአክሱም ሕዝብና ታሪክ «ሰሜን» በሚል የሕዝብና የአገር ስም የሚታወቅ አንድ ነባር ኩሻዊ መንግሥት ከጥንት ጀምሮ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እስከ አጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት (1605-1632) ድረስ በአክሱማውያኑ የደቡብ ምዕራብ ጂኦ-ፖለቲካ ወሰን ላይ በተከዜና በአባይ ወንዞች መካከል የዛሬውን የሰሜን፥ የወልቃይት፥ የፀለምት፥ የወገራ፥ የአርማጭሆ፥ የጭልጋ፥ የደምቢያና የቋራ አውራጃዎችን[61] አጠቃሎ በሰሜን ተራራና በጣና አስትራቴጂያዊ ክልል የነበረ አንድ ሉአላዊ አገርና መንግሥት ነው።

በዘመነ ክርስትና በ300ዎቹ በአዱሊስ የወደብ ከተማ ላይ የድል መታሰቢያ ሐውልት ያቆመው የአክሱም ንጉሥ በተከዜ-ዓባይ ወንዞች አስትራቴጂያዊ ምድር ላይ ጦርነት ከከፈተበት ጊዜ ጀምሮ

[61] Teklesellassie, Susnyos 1605-1632, Champs. 41-44; R. Hess, "An Outline of Falasha", Proceedings of the 3rd International Conference of Ethiopia Studies, (1966), pp. 99-112; Ibid., "Chapter 4: Toward A History of the Falasha", Deneil F. McCaall, ed., Eastern African History, (1969); pp. 107-132; Taddasse Tamrat, Church and State, pp. 196-201.

አስከ 1632 ድረስ ለ14 ምዕተ ዓመታት የሰሜን ሕዝብና መንግሥት ከተከታታይ የአክሱም፥ የአገውና የአማራ ነገሥታት ጋር የመከላከል ጦርነት ሲያካሄድ እንደኖረ በድንጋይና በብራና ላይ የተጻፉ የዘመናቱ የታሪክ መዛግብት በግልጽ ያሳያሉ።

በዚህ ረገድና ተግባር በ300ዎቹ በአዱሊሱ የወደብ ከተማ የድል መታሰቢያ ሐውልትን የተከለው የአክሱም ንጉሥ በሁለቱ የአፍሪካና የእስያ አጎራባች አህጉራት ላይ የጀመረውን የአጼ መንግሥት ግምባታ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ በሁለአቀፍ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የትምህርት ፖሊሲዎችና እርምጃዎች ወደ ከፍተኛ የዕድገትና የመስፋፋት ደረጃ ያደረሰው የአሌአሜዳ ልጅ አጼ ኢዛና ነው።[62]

የአጼ ኢዛና ታሪክ ዋና ዋና የመረጃ ምንጮች በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ ብዙ የንጉሡ ዜና መዋዕሎች እንዲሁም በኢትዮጵያ አና በአረቢያ ከወርቅ ተሰርተው በግሪክ ቋንቋ የተጻፈባቸው ፕንዘቦች ናቸው። ንጉሡ በ330 ዓመተ ምህረት ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ጉና አዋማዊ በነበረበት ጊዜ በተሠሩ ፕንዘቦች ላይ የጨረቃ ምልክቶች፥ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ በተሠሩ ፕንዘቦች ላይ ደግሞ የመስቀል ምልክቶች ተቀርፀው ይታያሉ። በመሆኑም አጼ ኢዛና የአክሱም የመጨረሻ አዋማዊና የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ነው።

በዜና መዋዕሎቹ ከአጼ ኢዛና የዙፋን ስም ጋር በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በላይኛው የአባይ ሸለቆና በአረቢያ በድምሩ አክሱም፥ ሕሜር፥ ራይዳን፥ ኢትዮጵያ፥ ሀበሻ፥ ሳባ፥ ሰልሔን፥ ጽያሞ፥ ቤጃ፥ ካሱ (ሚሮዌ) የተሰኙ የሕዝብና የአገር ስሞች፥ አርስ፥ መሕርም፥ አስተር፥ ብሔር፥ እግዚአ ሰማይ፥ (የሰማዩ ጌታ) አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰኙ አዋማዊና መለኮታዊ የአማልክት ስሞች ጋር በተለያዩ ሥፍራዎችና ጊዜያት በይፋ ተጽፈው ተገኝተዋል።

ባጭሩ ንጉሡ «ሰምቼ» እያለ የሚጠራቸው መሐዛ፥ ሐራ፥ ደመወ፥ ፊልሐ፥ ፅራእ፥ ሐሌን፥ ምጤን፥ ዳኬን፥ ለኬንና ሰብራት የተባሉ መታደራዊ ድርጅቶችና «አባቶቼ» የሚላቸው አርስ፥ መሕርም፥ አስተር፥ ብሔርና ምድር የተሰኙ አማልክት በአጼ ኢዛና ዜና መዋዕሎች የመንግሥቱ፥ የዘመኑና የሥርዓቱ ማዕከላዊ ተዋንያን፥ መሣሪያዎችና መግለጫዎች ናቸው።

አጼ ኢዛና በ330 ዓመተ ምህረት የክርስትና ሃይማኖት ከመቀበሉ በፊት ጉና አዋማዊ ሳለ የአዱሊስን የድል መታሰቢያ ሐውልት የተከለው ንጉሥ ያገር ግምባታ ፖሊሲና ፕሮግራም በመከተል

[62] Kammerer, Essai Sur L' Histoire. p. 86.

በ320ዎቹ ከላይ የተጠቀሱ የጦር ኃይሎችን አስከትሎ አጉዘት በተባለው በአንድ አመፀኛ የአከባቢ አገርና መንግሥት ላይ ያካሄደው ታላቅ የቅጣት ዘመቻ በሚገልፀው የግዕዝ ቋንቋ ዜና መዋዕሉ ላይ ራሱንI «ኢዛና የአሌአሜዳ ልጅ የነገደ ሐሌን የአክሱም፥ የሕሜር፥ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሔን፥ የጽያሞ፥ የቤጃና የካሱ (የሚሮዌ) ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕረም ልጅ» ብሎ ይጠራል።[63]

ለሚታዘዙለት ምህረት ማድረግ፥ ሥልጣንና ትዕዙን የማይቀበሉትን ደግሞ ያለምሕረት መቀደል ፖሊሲውና ተግባሩ የሆነው የአማል ክት ልጅ ንጉሠ ነገሥት ኢዛና በ320ዎቹ በአጉዘት አገር ላይ ዘመቻ ባካሄደ ጊዜ የአዱሊስን የድል መታሰቢያ ሐውልት ከተከለው ንጉሥ ቀጥሎ ለሁለተኛ ጊዜ የተከዜን ወንዝ በመታደራዊ ዘመቻ ተሻግሮ በሰሜንና በወልቃይት ተዛማጅ አገሮች[64] ላይ የቅጣት ጦርነት እንዳካሄደ በዜና መዋዕሎቹ ይነባበል።

ከጊዜ፥ ከተባባርና ከታሪክ አኳያ፥ በ300ዎቹ በአዱሊስ ከተማ የድል መታሰቢያ ሐውልት ባቆመው ንጉሥና በ1913 በጀርመኑ የቋንቋ ምሁር በፕሮፌሰር ኢኖ ሊትማን (1875-1958) ቁጥር 8 እና ቁጥር 9 ተብለው የተተረጎሙ የግዕዝ ዜና መዋዕሎቹን[65] በዓፈው በአጼ ኢዛና በ320ዎቹ በሰሜንና በወልቃይት አገሮች ላይ በተከታታይ የተካሄዱ ጂኦ-ፖለቲካዊ ጦርነቶች ገና በቅድመ ክርስትና ዘመን አዋጣዊ የአክሱም ነገሥታት በተጠቀሱት የአካባቢ አገሮች ላይ የነበራቸውን ቋሚ የመስፋፋት ፖሊሲና ፕሮግራም በግልፅ ያሳያሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በኢትዮጵያ በዘመነ ክርስትና በግምት ከ330 እስከ 1316 ድረስ ማለትም እሰከ አጼ አምደጽዮን ጊዜ ድረስ የሰሜን/ፈላሻ ስም፥ ሕዝብና አገር በታሪክ ሰነድ ላይ በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ ተጽፎ አልተገኘም።

በሌላ በኩል በዚህ ወቅት በተለይም ከ330-577 ድረስ የአክሱም ክርስቲያን አገርና መንግሥት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በላይኛው የዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አጎራባች አገሮችና አካባቢዎች ላይ ለገቢያና ለኃይል ሚዛን ከዘመኑ ኃያላን የሮማውያንና የፋርሳውያን የአጼ መንግሥታት ጋር የሚወዳደር አንድ ጠንካራ የዓለም ኃይል ሆኖ እንዳደገ ይታወቃል።[66] በመሆኑም በዚህ የሦስት

[63] Ibid., p. 89
[64] Ibid.,
[65] Ibid., pp. 89-90
[66] Y. M. Kobishchanov, Axum, (1979).

ምዕተ ዓመታት የሽግግር ዘመን የአክሱም መንግሥትና ነገሥታት በሰሜን/ፈላሻ አጎራባች አገር ላይ የመስፋፋት ግፊት አሳደረጉም።

ይሁን እንጂ በ577 የአረብ የነሻት ኃይሎች ከአጎራባቹ የፋርሳውያን ባላንጣ መንግሥት ጋር በጎብረት በአረቢያ የአክሱማውያንን የባሕር ማዶ ግዛት ደመሰሱ።[67] ቀጥሎም ከዚህ በታች በዝርዝር እንደ ሚታየው፥ ከ632 እስከ 642 ድረስ አዲሱ የአረቦች እስላማዊ ዓለም አቀፍ ኃይልና እንቅስቃሴ በአንድ በኩል በአረቢያ፥ በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ የሮማውያንንና የፋርሳውያንን መንግሥታት ደመሰሰ።[68]

በሌላ በኩል ደግሞ አክሱማውያን በቀይ ባሕርና በላይኛው የዓባይ ሸለቆ በሮችና ጠረፎች በኩል ከጥንት ጀምሮ ከውጭ ዓለም ጋር በቀጥታ የነበራቸውን የንግድና የባህል ግንኙነት በማዳከም በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለአክሱማውያኑ መንግሥትና ነገሥታት ከሰሜን ወደ መህል፥ ደቡብ፥ ምዕራብና ምስራቅ አቅጣጫዎች በተለይም በአገው፥ በሰሜን/ፈላሻና በወልቃይት የቅርብ አካባቢዎችና አገሮች ላይ ለመስፋፋት አስገዳጅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታዎችንና ግፊቶችን ፈጠረ።

አሪታዊ የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት

የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀትና የመንግሥቱ የመስፋፋት ታሪክ

በቲዮሪም በተግባርም መንግሥትና ሥልጣኔ ሁለት በቅርብ ዮተያያዙ ነገሮች ናቸው። መንግሥት በሰፊ ትርጉሙ በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የአንድ የተወሰነ መሬት፥ ሕዝብና የፖለቲካ ሥርዓት ድርጅታዊና ሕጋዊ ትስስር ነው። ከሦስቱ መሠረታዊና አስፈላጊ አካላት አንዱ እንኳን ባይኖር በቲዮሪም በተግባርም መንግሥት ዮሚባል የፖለቲካ አሳብና ድርጅት አይኖርም። በሌላ በኩል ደግሞ ብመሬት፥ በሕዝብና በፖለቲካ ሥልጣን ቅንጅት የሚፈጠረው የመንግሥት ድርጅት የሰለጠነም ያልሰለጠነም ሊሆን ይችላል። ከትርጉምና ከግንዛቤ አኳያ የመንግሥት መሠረታዊ መገለጫ የፖለቲካ ሥልጣን ሲሆን የሥልጣኔ መገለጫ ደግሞ የባህል ዕድገት ደረጃ ሚዛን ነው።

በተግባራዊ ትርጉሙ ሥልጣኔ የከተማና የገጠር ተግባራት ዕድገትና ክፍፍል፥ የእርሻና የንግድ ተግባራት፥ የግል መሬት ይዞታ፥

[67] S. Hablessllassie, History, p. 155.
[68] J. Cuoq, L'Islam en Ethiopie des Origines Au XVI Siecle, (1981), pp. 35-36.

የጽሕፈትና የገንዘብ አገልግሎት ያሉት አንድ ባህላዊ የህብረተሰብ ሥርዓት ወይም የዕድገት ደረጃ ነው። ከዚህ አጭር ትርጉም እንደ ምንረዳው መንግሥት የሥልጣኔ መሠረትና ቅድመ ሁኔታ ነው። ሥልጣኔ ግን የመንግሥት ገላጭ ባህርይ አይደለም። መንግሥት የአንድ በሥፍራና በጊዜ የተሰመነ መሬት፥ ሕዝብና የፖለቲካ ሥርዓት ቅንጅት ሲሆን፥ ሥልጣኔ ግን የአንድ የባህላዊና የማህበራዊ ድርጅት የዕድገት አንፃራዊ ደረጃ ነው። የመንግሥት መግለጫና የመለያ ሚዛን የፖለቲካ ኃይል ነው።

በመሆኑም፥ የተጠቀሱ ባህላዊ የሥልጣኔ ገጽታዎች ቢኖሩም ባይኖሩም በአንድ በተወሰነ መሬት ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ቅንጅት የሚፈጠር የመንግሥት ድርጅትና ሥርዓት በእርግጥ ሊኖርና ሊሠራ ይችላል። ስለዚህ የሥልጣኔ አለመኖር ወይም ለውጥ የመንግሥት አለመኖር እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ሥልጣኔ ሲወድቅ፥ መንግሥቱ ግን በሌላ አቅጣጫ ከሰሜን ወደ ደቡብ በአጎራባች የአገው፥ የሰሜን/ፈላሻና የወልቃይት ምድር ከዚያም ባሻገር በሥፍራና በጊዜ እያደገና እየተሰፋፋ መሄዱ አንድ ትምህርታዊ የታሪክ ሂደት ግንዛቤ ነው ለማለት ይቻላል።

ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ኅብረተሰብ በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ታሪካዊ ወቅት የአንድ የተወሰነ መሬት፥ ሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ድርጅትና መግለጫ በመሆኑ አንድ ሉአላዊ መንግሥት፥ እንዲሁም ባህላዊ የአርሻ፥ የከተማ፥ የጽሕፈት እና የገንዘብ ገፅታዎችና አገልግሎቶች ያሉት የሰለጠነ ማህበረሰብ ድርጅት በመሆኑ ደግሞ አንድ ሥልጣኔ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ የሚለው አባባል ትክክልኛ ሀሳብና አባባል ነው።

ነገር ግን በመጨረሻ ከ7ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ በአንድ በኩል በብዙ ተግራሪ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች፥ ሂደቶችና ኃይሎች ክስተትና ግፊት የሥልጣኔ ባህላዊ መሠረቶች፥ መሻሻያችና መግለጫዎች ናቸው የተባሉ የአክሱማውያኑ የከተማ፥ የንግድ፥ የትምህርት፥ የዕደጥበብ፥ የኪነ ጥበብ፥ የሥነጥበብ፥ የገንዘብ መሠረቶች፥ መሣሪዎች፥ ገፅታዎች፥ ምልክቶችና ሥራዎች በከፊል ወይም በሙሉ እየፈረሱ ሄዱ።

በሌላ በኩል ግን በአንድ በሥፍራና በጊዜ ቀመር ውስጥ በተወሰነ የመሬት፥ የሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ግንኙነትና ቅንጅት ለረጅም ዘመን የተመሠረተው የአክሱማውያኑ የመንግሥት ሥርዓት በራሱ ውስጣዊና ጥንታዊ የዘውድ፥ የክርስትና ሃይማኖትና የገባር

ኢኮኖሚ ድርጅቶችና ሥርዓቶች በልዩ መንገድና የዕድገት ደረጃ ተጠናክሮ በአዲስ የአገው፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የወልቃይትና የአማራ አጎራባች ሕዝቦችና አገሮች ላይ እያደገና እየተስፋፋ ሄዶ በመጨረሻም ለኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች ኅብረተሰብና መንግሥት ምሥረታና ዕድገት አንድ ታሪካዊ መሠረትና መሣሪያ ይሆናል።

የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ትምህርት መነሻና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ

ከጊዜ፥ ከተማርና ከታሪክ መረጃ አኳያ በእስትራቴጂያዊው የተከዜ-ዓባይ ወንዞች የመነሻ ክልል በመሬትና በሥልጣን ጥያቄዎች በአጎሩ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና በክርስቲያን የአክሱም፥ የአገውና የአማራ ተከታታይ መንግሥታት መካከል ረጅምና ተከታታይ ጦርነቶች የተካሄዱበት ጊዜ በአመዛኙ የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት የ550-1300 'ጨለማ' ክፍለ ዘመን ነው። በመሆኑም አሁን የአካባቢውን ጥንታዊ ታሪክ በሥፍራና በጊዜ መስፈርት አገናዝቦ በትክክል ለማወቅና ለማስተማር ቀላል ጥረትና ተግባር እንደማይጠይቅ ግልፅ ነው።

በመሰረቱ ባለፈው ሚሊኒየም ማለትም በአንድ ሺህ ዓመታት ዘመን ውስጥ የሰሜን/ፈላሻ አካባቢ ታሪክን በተለይ የኢትዮጵያ ታሪክን በአጠቃላይ በእጅጉ ውስብስብና አስቸጋሪ ያደረጉ ነገሮች በሚሊኒየሙ መጀመሪያ ላይ የሁለቱን የአገውና የአማራ መንግሥታት ታሪካዊ መሻሻና ሕጋዊነት በሚመለከት ከግብጹ ቤተ ክርስቲያን በአረብኛ ቋንቋ ተዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የገቡ *ክብረ ነገሥትና ፍትሐ ነገሥት* የተሰኙ የፖለቲካ ባሕረ መፃሕፍት ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በ12ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ በግብፁ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ በጳጳሚ ገብርኤል ዘመን (1131-1145) የኢትዮጵያ የአገው አመጸኛ ንጉሥ ሀርቤ[69] የአገሪቱን ቤተ ክርስቲያን ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ሞግዚትነት ነፃ ለማውጣት የወሰደውን የፖሊሲ እርምጃ ለማጥፋት የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ምሁራን ሁለቱንም የክብረ ነገሥትና[70] የፍትሐ ነገሥት[71] መዛግብት አዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ እንዳስገቡ አሁን በታሪክ መረጃና ጥናት በትክክል ተረጋግጧል።

ከሁለቱ ባሕረ መዛግብት የክብረ ነገሥት ረቂቅ መጀመሪያ በእስክንድርያ ግብፅ በኮፕቲክ ቋንቋ ከተዘጋጀ በኋላ በ1225 የረቂቁ

[69] S. Hablesellassie, History, pp. 251-254.

[70] Budge, The Queen of Sheba, p. 228.

[71] Paulos Tzadau, tr. The Fetha Nagast: The Law of The Kings (1968), pp. XV, 1-4, 18.

የአረብኛ ቋንቋ ትርጉም በጥብቅ ምሥጢር ወደ ኢትዮጵያ እንደገባና በመጨረሻ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314-44) በ1320 ገደማ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተር ጉሞ የኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥትና ሃይማኖት ባሕረ ሕግ ሆነ።

በዚህ ጥናት ከላይ እንደተባለው የክብረ ነገሥት ባሕረ ሕግ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ የጥንቱ የአክሱም መንግሥት ከአሪት ሃይማኖት ጋር በ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ የተመሠረተው በኢየሩሳሌም ከሰለሞን ቤተ መቅደስ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ሕገ-አሪትን ሰርቀው ባመጡ የይሁዳውያኑ የመሳፍንትና የካህናት ልጆች ነው ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ የአገው ነገሥታትም በዘር ይሁዳውያን አይደሉም ይላል። በመሆኑም የአገው ነገሥታት በአገሪቱ ውስጥ በሰለሞናዊ ዙፋን ላይ መቀመጥ የማይገባቸው ሰርጎ ገብ ወንበዴዎች ናቸው ብሎ ይከሳል።

ፍትሐ ነገሥት ደግሞ የአገው ነገሥታት የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለማስወገድ የፖሊሲ እርምጃ በወሰዱበትና ሳልሳዊ ቀርሌዎስ (1235-1243) የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ በነበረበት ዘመን በግብፅ ኮፕቲክ ጸሐፊ አሳል ከልዩ ልዩ የብሉይ ኪዳን፥ የአዲስ ኪዳን፥ የቤተ ክርስቲያን፥ የግሪክ፥ የሮማውያን፥ የቁራንና የአረብ ምንጮች የተሰበሰቡ የመን ግሥትና የሃይማኖት ሕግጋት ጥምር ባሕረ መዝገብ ነው።

በመጨረሻም በ15ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1434-68)፥ ፍትሐ ነገሥት በግዕዝ ቋንቋ ትርጉም ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ከክብረ ነገሥት ጋር በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ እስከ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የ1931 ሕገ መንግሥት ድረስ ቢያንስ ለ400 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ መሠረታዊ የመንግሥትና የሃይማኖት ጥምር ሕግ ሆኖ ኖረ።

ከጊዜና ከታሪክ አኳያ፥ ከአንድ ሚሊኒየም በኋላ በ1230ዎቹ በግብፁ ጸሐፊ አሳል በፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግ እንደተባለው፥ አርዮስ ግብፃዊው የሃይማኖት ምሁር የክርስቶስን መለኮታዊና ሰብአዊ ጥምርና ረቂቅ ባሕርያት በሚመለከት የምሥጢረ ሥላሴ ጥያቄ ላይ ባስነሳው ታላቅ ክርክር ምክንያት፥ ዜና የክርስትና ሃይማኖት በ330 ዓመተ ምህረት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ አምስት ዓመታት አስቀድሞ፥ በ325 በታላቁ የኒቅያ ጉባኤ ከሮማውያኑ አጼ ቆስጠንጢኖስ (306-337) ጋር ለውሳኔ በተቀመጡ 318 የዓለም አህጉራዊ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን ከግብፃዊው አቡን በስተቀር ማንም የኢትዮጵያ ተወላጅ

በምንም ጊዜና መንገድ የአገሩ ቤተ ክርስቲያን የበላይ መሪና አስተማሪ ለመሆን አይችልም ተብሎ ተወስኗል ይላል።[72]

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከ330 አስከ 1950 ድረስ ማለትም ለ1620 ዓመታት፥ ከመነሻው ጀምሮ ለሮማውያን፥ ለአረብና ለቱርክ ጌቶቿ በባርነት ስትገዛና ስትገብር የኖረችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ራሷ ከጥገኝነት ሳትላቀቅ የአገሪቱን ቋንቋና ባህል በማያውቁ በ110 ወኪል አቡኖቿ አማካይነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በተንኮል ስትገዛና ስትዘርፍ እንደኖረች አይረሳም።[73]

ባጭርና በጥቅል አነጋገር ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያ የመንግሥትና የሃይማኖት መሪ ሕጎች ተደርገው የኖሩ ሁሉቱ የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግ ጋት የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ሊቃውንት የሞዝላትነት ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን በኢትዮጵያ ጥንኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ የበለጠ አጠናክረው ለማቆየት የፈጠሩአቸው የሕግ፥ የፖለቲካ፥ የሃይማኖትና የታሪክ ቅይጥ ሥራዎች እንደሆኑ ከላይ ከቀረቡ የታሪክ መረጃዎች ለማንም አስተዋይ ግለሰብ በጣም ግልፅ ነገር ነው።

ከዚህ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ከላይ በቀረቡ የፖለቲካ ምክንያቶችና መንገዶች ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት በገባው የክብረ ነገሥት ባሕረ ሕግና ትምህርት መሠረት፥ ባለፉት ስባት ምዕተ ዓመታት የኢትዮጵያ የዘመኑ ነገሥታትና የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች የአገሪቱን ጥንታዊ፥ ሉአላዊና በህውርታዊ ታሪክ ወስደው በመካከለኛው ምስራቅ የጥንቱ ይሁዳውያን የሃይማኖት ታሪክ አካል አድርገው አቅርበውታል። በመሆኑም በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ጎብረ ተሰብ መንግሥትና ታሪክ ላይ ታላቅ ግድፈት ፈጥረዋል።

በአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት የሰሜን/ፈላሻ ሚና ጥያቄ

በዚህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ ጥናት፥ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ በዘመነ ክርስትና (1)፥ በ4-5ኛ ምዕተ ዓመታት ውስጥ የክርስትና ሃይምኖት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ወደ አገሪቱ ከመግባቱ በፊት የይሁዳውያኑ የአሪት ሃይማኖትና ሕግ በኢትዮጵያ አለመገኘቱን፤ (2)፥ በ13-15ኛ ምዕተ ዓመታት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱ የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግጋት ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ከመግኢታቸው በፊት ሰለሞናዊ የተሰኘው

[72] Ibid.,, p. 18.

[73] ግሁተመ ሥላሴ ወ/መ፥ ዝክረ ነገር፥ (1962) ገጽ 891-894።

የፖለቲካ ተረት ሆነ የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት እንዳልአበረና (3)ቱ በ5ኛው ምዕተ ዓመት ዘጠኙ ግሪኩ-ሮማዊ ጸድቃን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ የተረጎሙት መጽሐፍ ቅዱስ በአክሱምና በአካባቢው አጠናክረው ከመሠረቱት የገዳም ሥርዓትና ከግዕዝ ቋንቋ ጋር በጎላ በሁለተኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ ምዕተ ዓመታት በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ በአራቱ የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ አገሮች ለሁለቱም ተዛማጅ የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ዕድገትና መስፋፋት የጋራ መሻና መሣሪያ እንደሆነ[74] የሚያስገነዝቡ አዳዲስ የውይይት ሀሳቦችና አስተያየቶች ወይም ቲሲሶች ቀርበዋል።

በሌላ በኩል፥ በ550-1300 የሰፍድ መረጃ ባልተገኘበት የጨለማ ዘመን ውስጥ በአካባቢው በተጠቀሱ አራት የፖለቲካና የሃይማኖት ማኅበረሰቦች መካከል፥ ለምሳሌ የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት፥ የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት ክስተት፥ የጉዲትን ፖለቲካ ተረት ጨምሮ፥ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች፥ ጊዜያት፥ መስኮችና መንገዶች የተካሄዱ ብዙ የግንኙነት ሁኔታዎችን፥ ሂደቶችንና ተዋንያንን በሥፍራ፥ በጊዜ፥ በቁጥርና በተግባር መሰፈርት ተንትኖ ለማወቅ የታሪክ መረጃ ስላልተገኘ ሁሉም የተረት ቅኝቶች ሆነው ቀርበዋል ወይም ቀርተዋል ለማለት ይቻላል።

ይህም ብቻ አይደለም። በታሪክ፥ በፖለቲካ፥ በሃይማኖትና በመንግሥት ሥልጣን ስም በተዛማጅ የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ መዛግብት የግዕዝ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች፥ መምህራንና ጸሐፊዎች በኢትዮጵያ ለረጅም የጠረጉትና የጥፋት መቅሰፍት፥ መሻና መሣሪያ የሚሆን ዘረኛ ትምህርት አስተምረዋል። በተጠቀሰው የተንኮል ሥራና ሥርዓት የኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻና የአገው ነባር ሕዝቦች የዚህ የግዕዝ ቤተ ክርስቲያን ዘረኛ ትምህርት የመጀመሪያ ሰለባዎች ሆነዋል።

ከዚህ አኳያ ነባሩ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ የአክሱሙን ሥልጣኔ በወረራ ያጠፋው ባዕድ ጠላት ነው ተብሎ ይወነጀላል። በመሆኑም ውሎ ሳያድር ከቤቱ፥ ከንብረቱ፥ ከመሬቱና ከአገሩ ይፈናቀላል። በገዛ አገሩ መጤ (ፈላሻ) ተብሎ ይፈረጃል። የዜግነት መብትና ክብር እንዲያጣ ይደረጋል። እንዲሁም የአገው ሕዝብና መንግሥት በአገሩ መንበረ ሥልጣን ላይ መቀመጥ የማይገባው ባዕድ ሕዝብና መንግሥት ነው ተብሎ ይኮነናል። በመሆኑም ከሥልጣኑ እንዲወርድ ከአገሩም እንዲሰደድ ይደረጋል። ታሪኩም ይፋቃል።

[74] Leslau, The Black Jews of Ethiopia, p. XIII; Taddasse Tamrat, Church and State. Chaps. 5-6.

የጉዲት ተረትና የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ቅጣት

የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብን የጥፋትና የቅጣት ታሪክ በሚመለከት አቶ ተከለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም ዘገዬ በተሰኘ መጽሐፋቸው «የፈላሻና የነገደ አዝዮ ወገኖች ተቀስቅሰው የአክሱሙን መንግሥት ጥለው ለየራሳቸው መንግሥት ለማቆምና ባሳቡቶቻቸውን ለማንገሥ»[75] በአመፅ ተነሱ የሚል አስተያየታቸውን ይደግፋሉ ብለው የሚገምቱአቸውን «የውጭዎቹም ያገራችንም ደራሲዎች እነ ብላቴን ጌታ ኅሩይ፥ እነ አለቃ ታዬ» የጻፉአቸውን ተመሳሳይ ሀሳቦችና አስተያየቶች አሰባስበውና አገናዝበው እንደ ሚከተለው አቅርበዋል። በአቶ ተከለ ጻድቅ መኩሪያ ቃል፥

> *በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ብዙ የእሥራኤል ወገኖች ካህናቶችም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሕዝቡን ሕገ አሪት እያስተማሩ በእውነተኛ በእዝለብሔር እንዲያምን አደረጉት። ከእነርሱም ውሰጥ ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እየተጋቡ እየተዋለዱ ብዙ ዘመን ኖሩ። በአብርሃና በአጽብሐ ጊዜ አባ ሰላማ (ፍሬሚናጦስ) በአክሱም መንግ ሥት ክርስትናን ከአመጣ በኋላ የአክሱም ሕዝብ ክርስትናን ተቀብሎ ሲኖር የእሥራኤል ወገን የሆኑት አዲሱን ሃይማኖት ክርስትናን አንቀበልም ብለው በዚያው በቀድሞው ሃይማኖትና በአሪት ሕግ ጸንተው ተቀመጡ። በዚህም የተነሳ ክርስቲ ያኖቹ ቢጨቁኗቸው ከአክሱምና ከዙሪያው እየተሰደዱ በሰሜንና በወገራ በወልቃይት ቦላስታም ተቀመጡ። እነዚህም ፈላሾች የሚባሉ ናቸው። ፈላሲ አገሩን ትቶ ሒያጅ ማለት ስለሆነ እነዚህም ጥንት ከኢየሩሳሌም ወደ አክሱም፥ አሁን ደግሞ ከአክሱም ወደ ሰሜንና ወደ ወገራ ሰለ ተሰደዱ ፈላስያን (ፈላሾች) ተባሉ ይባላል። ይህ በመጨረሻ የተሰደዱበት የሰሜን አገር ተራራማ ስለሆነ በዚህ ሥፍራ ሆነው በፍጥረቱ ምሽጉት እየተጠቀሙ ሊወጋቸው የሚመጣውን ሁሉ እየተከላከሉ ይመልሱት ነበር። ቁጥራቸው እየበዛ ኃይላቸው እየበረታ ሲሔድ ከመካከላቸው ጊዴዎን የሚባለውን እንደንጉሥ ሾሙት።*
>
> *ለጊዴዎን ቦጣም የተዋበች ልጅ ነበረችው። እርሷም ዮዲት አንዳንድ ጊዜ አሰቴር የምትባለው ነች። ዮዲትንም ዘርዓያዕቆብ የሚባል የቡግና (ላስታ) ገዥ ክርስቲያን ፈላሻንታን ሳይመረምር የመልኳን ውበትና ቁንጅናዎን አይቶ አገባት። እርሷም በውብታና በፍቅሯ በቱን ብዛት እየሳበች በርሷ ሃይማኖት (በይሁዲ) አገባትውና ሰሙንም ሰለዋን አሰንቻው።*
>
> *በዚህ ዘመን በአክሱም ዙፋን የተቀመጠው የኢትዮጵያ ንጉሥ ድኅንገን ነበር። ነገር ግን እርሱ ስለሞተ አንበሳ ውድም የሚባለው ሕጻን ልጁ ነገሠ። የንገሡው ሕጻን ለማስተዳደር አለመቻሉን ዮዲት ባወቀች ጊዜ ሰሰሜንና በሰላታ አውራጃ የሚኖሩትን ፈላሾች ወገኖቿን ደዛ ወደ አክሱም ገሠገሠች። የአክሱም መኳንንትም ሕጻኑን ንጉሣቸውን እንደያዙ እርሷን ፈርተው ከትግሬ ወደ*

[75] ተከለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ፥ አክሱም ዘገዬ፥ ገጽ 328።

ሸዋ ሸሸ። ከዚህ በኋላ (ክ.ል42 ዓም) ነገሥትና በእከሱምና በዙሪያው ያሉትን ሐውልቶች እያስፈረሰች አብያተ ክርስቲያናቱን ሁሉ አቃጠለች። እንደዘመኑ ልማድ የውሰጥ ጦርነት እንዳይቀሰቅሱ ተብሎ በደብረዳሞ ተራራ ላይ በዘገና ይጠበቁ የነበሩትን ከነገሥታት የሚወለዱትን መሳፍንትንት ሁሉ አሳረደቻቸው። በዚህ ሞካኔዋ ዮዲት የተባለው ሰሚ ተለውጠ ጉዲት፥ አስቴር የተባለውም ቀርቶ እሳቶ ተባለች ይባላል።

አንበሳ ውድም ወደ ሸዋ ሸሸቶ በመጣ ጊዜ የሸዋ ሕዝብ በደስታ ተቀበለው። ዮዲት ይሽን በሰማች ጊዜ በነገሠች በ23ኛው ዓመት ብዙ ሠራዊት ስብስባ ወደ ሸዋ ላከች። አንበሳ ውድምም የመንዝን ባላገር ይዞ የዮዲትን ጦር ተዋግቶ መለሰው። ከዚህ በኋላ ራሷ ዮዲት የቀረውን ጦርን ሰብስባ ራሷ እየመራች ወደ ሸዋ መጣች። አንበሳ ውድምም መመጣቷን ሲሰማ ከመንዝ ወደ መራቤቴ ወረደ። እርስዋም እስከ መራቤቴ ለመከታተል ምክራ ሳለ በመካከል የአህያ ፈድና የደባ መንገድ ገደላ ገደል ስላስቸገራት በዚህም ላይ አንበሳ ውድምን የሚረዳው የሸዋ ሕዝብ በሚያውቀው አገር ላይ እያደፈጠም ፊት ለፊትም እየወጋ ላደጋ እየጣለ ሰለ ለወከት ከሸዋ ወደ አክሱም ተመልሳ 17 ዓመት ያህል ኖራ በሙሉ 40 ዓመት ነግሣ ሞተች።

አንበሳ ውድም ዮዲትን ሞት በሰማ ጊዜ ከሸዋ በማሥጋሜ ወደ አክሱም ሔደ። የትግሬ ሕዝብም በደስታ ተቀበለውና ባባቶቹ አልጋ አስቀመጠው። ሀያ ዓመት ያህልም እንደገዛ ሞተና ልጁ ድል ነጓድ ነገሠ። ቢሆንም በዮዲት ጊዜ የተቀሰቀሰው የሰሜንና የላስታ ሕዝብ በዮጊዘው እየተነሳ አላስገዛ ብሎት ሲኖር በመጨረሻ መራ ተክለ ሃይማኖት የሚባል ትርዳአ ገበዝ የምትባለዋን (ልጅ) ይዞ ከላስታ ተነሥቶ ድልነጓድን ይወጋው ጀመር። አሁንም ድልነጓድ አቅም ስላጣ እንዳባቱ እንደአንበሳ ውድም ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሸ። መራ ተክለሃይማኖት ድልነጓድን ከአባረረ በኋላ በኢትዮጵያ ነገሡና የዛጉዬ መንግሥት መሠረተ።[76]

የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦች የጋራ መነሻና ዕድገት

በዚህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ ጥናት ተደጋግመው የሚነሱና ሰለሞን፥ ሳባ፥ ምኒልክ፥ አይሁድ፥ እሥራኤል፥ ቤተ እሥራኤል፥ ፈላሻ፥ ጌዴኦን፥ ጉዲት፥ ዘርዓያዕቆብ፥ ድግናግን፥ አንበሳ ውድም፥ ድልነጓድ፥ ትርዳአ ገበዝና መራ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ከላይ በምንባብ የቀረቡ ገፀባሕርያት በሰሜን ኢትዮጵያ በድህረ አክሱም ሥልጣኔ ከአራቱ ነባርና ተሳታፊ የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦች ታሪካዊ ከስተትና ዕድገት ጋር በቅርብና በጥብቅ በተያያዘ ሁኔታ ከ550-1300 የጨለማ ዘመን ወዲህ በምዕራፅ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች የተፈጠሩ የፖለቲካ ገፀ ባሕርያት ናቸው።

[76] Ibid., pp. 329-331.

ከሁለቱም ከደዘብትና ከቅርፅ አኳያ የገፀ ባሕርያቱ ድርሰት በተጠቀሱ ተሳታፊ የአካባቢ ሕዝቦች መካከል ኢታሪካዊ የሆነ ቅራኔ፥ ልዩነትና ጠላትነት ይፈጥራል። የተረቱ ድርሰትና ትምህርት በተጨማሪ በህብረተሰቡ ዘንድ «ምርጥ» በተባለው መጤ ሰለሞናዊ የንሸ መደብና በአብሩ አምራች ሕዝብ መካከል በዘርና በሃይማኖት ምርጫና ልዩነት ያደርጋል። ኢትዮጵያውያንን «ሕዝብ» እና «አሕዛብ» ማለትም «ወገን» እና «ጠላት» በማለት በሁለት ተግራሪ ሠፈሮችና ማኅበሮች ይመድባል።

«ሕዝብ» ተብሎ የተፈረጀውን «ምርጥ» የሕዝብ ወገን በአዲሱ የክብረ ነገሥት ፖለቲካ ትምህርት መሠረት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ሴማዊ ዘር ነው ከተሰኘው የይሁዲ። እሥራኤል ሕዝብ የሃይማኖት ታሪክ ጋር በቅርብ ያዛምዳል። «አሕዛብ» የተባለውን ወገን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ «የምርጡ» የይሁዲ። እሥራኤል ሕዝብ የሃይማኖት ጠላቶች ናቸው ከተባሉ አሞጣዊ የከነዓን፥ የግብፅ፥ የአሶሪያ፥ የባቢሎን፥ የአረብ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ጋር እያዛመደ በጥቁር ቀለም ያሳያል። ጥላሸት ይቀባል።

ከሁሉም በላይ በ550-1300 የሰነድ መረጃ አልባ ዘመን በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ ከተነሱ አራቱ የአካባቢ የፖለቲካ ማኅበረሰቦች ሁለቱን የሰሜን/ፈላሻና የአገው ሕዝቦችን ለይተው የተረቱ ፈጣሪዎች «የአክሱሙን መንግሥት» ያጠፉ ጠላቶች ናቸው በማለት ይወነጅሉዋ ቸዋል። በመሆኑም በአጋጣሚ በአካባቢው ታላቅ የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት የሆኑ የሰሜን/ፈላሻና የአገው ሕዝቦችን ሰቅጣት፥ ለጦርነትና ለዘረፋ የተፈጠሩ ጠላቶች አድርገው ያቀርቡአቸዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በሌላ በኩል፥ በድህረ አክሱም ሥልጣኔ በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ የአራቱን የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦችን ታሪካዊ ከስተትና ዕድገት በተለይ፥ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የኢትዮጵያን ሁለአቀፍ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ጎብረተ ሰብ ከስተትና ዕድገት በአጠቃላይ አለቅራኔ የሚገለፁ ሁለቱ ታሪካዊ ኃይሎች በእርግጥ የኢትዮጵያ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ ተቋማት ናቸው። ባጭሩ የኢትዮጵያን የታሪክ ይዘት፥ ዕድገትና ሂደት በተጨባጭ መንገድና ሚዛን የሚገልፁ የእነዚህ ሁለት ኃይሎች የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ ድርጅቶችና መዋቅሮች ናቸው።

ከዚህ አኳያ፥ በዓለም ታሪክ የክርስትና ሃይማኖትን የጎብረ ተሰብ ግምባታ ተባብርና ሚና በሚመለከት ዕውቁ የብሪቲሽ ምሁር

ኤድዋርድ ጊቦን (1737-1794) *The Decline and Fall of the Roman Empire (1788)* ዘዲክላይን ኤንድ ፎል ኦፍ ዘ ሮማን ኢምፓየር በተሰኘው መጽሐፉ ክርስትና ማኅበራዊና ሥርዓታዊ ግጭት በመፍጠር ለታላቁ የሮማውያን ኢምፓየር ድክመትና ውድቀት ዓይነተኛ መነሻና ምክንያት ሆነ የሚል ቲሲስ አቅርቧል። በሮማውያን ኢምፓየር ክርስትናን መጀመሪያ የተቀበሉ የገባርና የባርያ ወገኖች ነበሩ። ይህም በኅብረተሰቡ ዘንድ የሥርዓት ግጭት እንዳስከተለ አይረሳም።

የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ በተቃራኒው በአገሩ ነባር መንግሥት አመራር ራሱን ከአከሉም አዋማዊ የፖለቲካና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ጋር በማዋሃድ ለነባሩ ዘውዳዊ መንግሥት ቀጣይ ዕድገትና መስፋፋት አዲስ መንገድና መሣሪያ ሆነ። ማለትም በአካባቢው በቅይጥ የአዋማዊነም፥ የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች መሠረት በተለይ ለትግሬ፥ ለሰሜን/ፈላሻ፥ ለአገውና ለአማራ ሕዝቦች በህውርታዊ ኅብረ ተሰብና መንግሥት ዕድገት የድርጅት ላዕላይ መዋቅር ሆነ። በመሆኑም ሃይማኖቱ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሥርዓት ቀውስ አላስከተለም።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከሁሉ በፊት በ330 የክርስትና ሃይማኖትና ትምህርት በሰላማዊ መንገድ ወደ አዋማዊ የአክሱም ምድርና ቤተ መንግሥት የገባው በአገሩ መንግሥትና ሕዝብ ነፃ ፍላጎትና ምርጫ ነው። በመሆኑም፥ በአክሱሙ ኅብረተሰብ ዘንድ በአዲሱ ሃይማኖትና ትምህርት ምክንያት በሮማውያኑ ኅብረተሰብና መንግሥት ላይ የደረሰው ማኅበራዊና ሥርዓታዊ ግጭትና ውድቀት አላደረሰም። በኅብረተሰቡና በዘመኑ የኢኮኖሚ ታህታይ መዋቅር ላይም ሆነ የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅር ላይ ፈጣንና መሠረታዊ ለውጥ አልተካሄደም።

በተጨማሪም በኋላ በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በ6ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ (470-550) ላይ በአክሱም ከተማ መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በመተርጎም፥ በአዋማዊው አገር የገዳም ሥርዓትና ተቋም በማቋቋም፥ እንዲሁም የግዕዝ ቋንቋን የትምህርት፥ የሥነ ጽሑፍና የቅዳሴ መሣሪያና መገለጫ በማድረግ፥ የአክሱም ቤተ ክርስቲያንን በጠንካራ ባህላዊና ድርጅታዊ መሠረት ላይ የጸሙ ዘጠኙ ግሪኮ-ሮማዊ ጻድቃን፥ በዘመኑ የቤተ ክርስቲያኑን የመዝሙርና የቅዳሴ ሥርዓቶችን ከፈጠረው ምሁር ያሬድ ጋር፥ የአክሱም ነገሥታት አልአሜዳ፥ ታዛና፥ ካሌብና ገብረመስቀል አስተማሪዎችና አማካሪዎች በመሆን፥ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል በፍሬምናጦስ የተጀመረውን ሰላማዊና ተግባራዊ አንድነት የበለጠ እንዳጠናከሩ ከቤተ ክርስቲያኑ ታሪክና ትውፊት በትክክል ይታወቃል።

በ330-550 የክርስትና መነሻ ዘመን ፍሬምናጦ ስና ዘጠኙ ጻድቃን በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል የፈጠሩት ሰላማዊ ግንኙነት በ550-1300 የጨለማ ዘመንም ቢሆን የበለጠ እያደገና እየጠነከረ እንደሄደ የሚያመለክቱ አንዳንድ የታሪክ መረጃ ፍንጮችና ምንጮች አሉ። ለምሳሌ አንደኛ፥ በተጠቀሰው ዘመን መጀመሪያ በ610ዎቹ ከአረቢያ እስላማዊ ስደተኞች ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት በመጡ ጊዜ በአገሩ በክርስቲያን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መካከል ሰላማዊ ሕይወትና ሥራ እንደነበረ የስደተኞቹ ታሪክ ያሳያል።

ሁለተኛ፥ በዘመኑ ሁሉም የአክሱምና የአገው ነገሥታት የመንግሥትም የቤተ ክርስቲያንም የበላይ መሪዎች እንደሆኑ በጣዕፁ አቡን ሹመት ጉዳይ ላይ በኢትዮጵያና በግብፅ ባለሥልጣኖች መካከል የተካሄዱ የሥራ ግንኙነቶች ታሪክ ይገልጻል።

ሦስተኛ፥ በአገው ነገሥታት ከላስታ ቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍለው የተሰሩ አብያተ ክርስቲያናት በዘመኑ በኅብረተሰቡ ዘንድ የነበረው የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን አንድነት ታሪካዊ መገለጫዎች ናቸው።

የሥርዓተ አሪት ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ መምህራን ተግባር በሰሜን/ፈላሻ አገር

በ550-1300 የጨለማ ዘመንም ሆነ ከዚያም በፊት በአካባቢው የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት መከሰቱንና መኖሩን የሚጠቁም አንድም አሳማኝ የታሪክ መረጃ ፍንጭና ምንጭ ከአገር ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።

በመሆኑም ከታሪክ አኳያ የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት ከክርስትና እንቅስቃሴ የተጀመረው በ13ኛው ምዕተ ዓመት ከክብረ ነገሥት ትምህርትና ከሰለሞናውያኑ አገር አቀፍና ሁለአቀፍ የወንጌል፥ የገዳም፥ የግዕዝ ብራና ሥነጽሑፍ፥ የፖለቲካ፥ የግዛትና የመስፋፋት ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች[77] ጋር በቅርብ በተያያዘ ሁኔታና መንገድ ነው ለማለት ይቻላል።

ከ550-1300 ከፍለ ዘመን በኋላ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ በ15ኛው ምዕተ ዓመት እስከ አጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1434-68) ድረስ በጥንቱ ዘጠኝ ግሪኮ-ሮማዊ ጻድቃን የክርስትና ትምህርትና በአዲሱ የክብረ ነገሥት የፖለቲካ ፍልስፍና ጥምር መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርቡ የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ መሰክነትና

[77] Huntingford, Amda Seyon; Taddese Tamrat, Church and State.

መምህራን በቀይ ባሕርና በጎጃም-ሸዋ መካከል ከአሪት ሃይማኖት ጋር አጣምረው እያስተማሩ ብዙ አዳዲስ የወንጌል፥ የቤተ ክርስቲያን፥ የገዳም፥ የግዕዝ ብራና ሥነጽሑፍ ሥራዎችን፥ ተቋማትንና እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት በአካባቢው ለሁለቱም የክርስቲያንና የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ማኅበረሰቦች የፖለቲካ ዕድገት፥ መስተጋብርና መወራረስ ሁኔታዎችን፥ መንገዶችን፥ መሣሪያዎችንና መዋቅሮችን ፈጠሩ። ባጭሩ የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖት ታሪካዊ ምንጩና መሻሻው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነው።

በዘመኑና በአካባቢው ለተመለከተው የክርስትና እና የሰሜን/ፈላሻ የአሪት ሃይማኖቶች ጥምር ዕድገት፥ መስተጋብርና መወራረስ የትምህርትና የድርጅት ሁኔታዎችን ከፈጠሩ ከፍተኛ የገዳም መነሳሳትና መምህራን፥[78]

1. በቤተ አማራ የደብረሐይቅ ገዳም መሥራች አቃቤ ሰዓት ኢየሱስሞዓ (1211-1292)፥
2. በሸዋ የደብረሊባኖስ ገዳም መሥራች አቡነ ተክለ ሃይማኖት (1215-1313)፥
3. በትግራይ የሥርዓተ አሪት እንቅስቃሴ መሥራች መነኩሴ እምስጣጢዎስ (1273-1352)፥
4. በሰራየ የእምስጣጢዎስ ደቀመዝሙርና የደብረማርያም ገዳም መሥራች አባ አብሳዲ፥
5. በእንፍራንዝ ደምቢያ የእምስጣጢዎስ ደቀ መዝሙርና የደብረሰን ገዳም መሥራች አባ ገብረኢየሱስ፥
6. መነኩሴ ቆዝሞስ በደምቢያ ከደብረወይና ገዳም በአጼ ዳዊት ዘመን (1382-1412) ለሰሜን/ፈላሾች የሥርዓተ አሪት አስተማሪ፥
7. በሐማሴን የእምስጣጢዎስ የሥርዓተ አሪት ትምህርትና እንቅስቃሴ መሪና የደብረቢዘን ገዳም መሥራች መነኩሴ ፊልጶስ (1323-1406)፥
8. በ15ኛው ምዕተ ዓመት የአጼ ዘርዓያዕቆብ (1434-68) ምሁርና አመጸኛው ልጅ ሰብራ፥
9. በ15ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአ ጋሜ የጉንዳጉንዲ ገዳም መሥራች መነኩሴ አስጢፋኖስ ከነተከታዮቻቸው በመጀመሪያ ደረጃ የሚታወሱ ታላላቅ አባቶች ናቸው።

ባጭሩ እነዚህ መምህራን በጥንቱ ዘጠኝ ጻድቃን የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥራ መሠረት ከአዲሱ ሰለሞናዊ ነገሥታት ጎን ተሰልፈው በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን ግምባታ ፖሊሲና ተግባር

[78] Ibid., Church and State, Chaps. 5, 6.

ከድርጅትና በትምህርት መስኮች ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የገዳም መምህራንና መነኩሳት ናቸው። የተጠቀሱ መምህራንና ገዳማት፥ በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና አመራር ጉዳዮች፥ ከ1337 እስከ 1450 ድረስ በአንድ ምዕተ ዓመት ዘመን ውስጥ በሁለት ተፃራሪ አንጃዎች ተከፍለው እንደነበር ታውቋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በ1270 የአማራ የጦር አበጋዝ ይኩኖ አምላክ የአገውን ክርስቲያን መንግሥት ደምስሶ አዲስ ሰለሞናዊ መንግሥት በመሠረተ ጊዜ ሁለቱ ታዋቂ የገዳም መምህራን ማለትም የደብረሐይቁ ገዳም አቃቤ ሰዓት ኢየሱስሞዓና የደብረሊባኖሱ ገዳም አቡነ ተክለሃይማኖት ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ጋር የይኩኖአምላክ (1270-1285) መንግሥት ደጋፊዎች እንደነበሩ ተረጋግጧል። ለዚሁ ወሮታ ከሰለሞናዊያኑ መንግሥት መሪዎች፥

አንደኛ፥ ለደብረሐይቁ ገዳም መሪ ኢየሱስ ሞዓና ለተከታዮቹ በአዲሱ ቤተ መንግሥት ከንጉሡ ዙፋን ቀጥሎ ከፍተኛው የሆነ የአቃቤ ሰዓት ሥልጣንና ሹመት በውርስ መብት ተሰጠ።[79] በዚሁ ውሳኔ መሠረት ለምሳሌ ከ1270 እስከ 1535 ድረስ በ265 ዓመታት ውስጥ የመንግሥታቱ ከሃያ በላይ የሚቆጥሩ የአቃቤ ሰዓት ባለሥልጣኖች[80] በሙሉ የደብረሐይቅ ገዳም መሪዎችና መምህራን ነበሩ።

ሁለተኛ፥ ለደብረሊባኖስ ገዳም መሪ ለአቡነ ተክለሃይማኖትና ለተከታዮቹ በቤተ ክርስቲያን ስም ከመንግሥቱ መሬት ሲሰው ተሰጠ።[81]

ሦስተኛ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእምነ ትና የትምህርት አመራር ቀደም ብሎ በ1238 በግብፅ አገርና ደራሲ በተጻፈው የፍትሐ ነገሥት ሕግ መሠረት ለዘለዓለም በግብፁ ሞጢት ቤተ ክርስቲያን እንደራሴ አቡን እጅ በውርስ መብት እንዲሆን ሰለሞናዊ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተስማሙ።[82]

የእምስጣጢዎሳውያኑ የ1337-1450 የአሪት አመፅና ድል

በ1337-1450 በቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ትምህርትና ሥራ ጉዳዮች ላይ ከላይ በተጠቀሱ ታላላቅ መነኩሳትና ገዳማት መካከል ተፈጠሩ ሁለት ተፃራሪ ኃይሎችና ቡድኖች አንዱ በሰሜን ኢትዮጵያ «እምስጣጢዎስን የአሪት እምነት፥ ትምህርትና ሥርዓት ከክርስትና

[79] Ibid., "The Abbots of Debra Hayq 1248-1535", p.90.
[80] Ibid., pp. 88-117.
[81] ገድለ ተክለ ሃይማኖት ገጽ 74-80
[82] J. Bruce, Travels To Discover the Source of the Nile, 5 Vols., (1790), I, pp. 533-34.

ሃይማኖት ጋር አጣምሮና አዛምዶ የሚከተል በአመዛኙ በሰሜን የትግሬ[83] መኰሳትና ገዳማት አንጃ ነበር።

ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ማለትም በሸዋና በቤተ አማራ ከላይ ከቀረበው ከአገው-አማራ የመንግሥት ለውጥ ፖለቲካ አኳያ ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮችና ከሰለሞናዊ ነገሥታት ጋር የቀረበና የጠበቀ አንድነት የነበራቸው የደብረ ሐይቅና የደብረ ሊባኖስ[84] ገዳማትና መኰሳት አንጃ ነበር።

የዚህ የትግሬ-አማራ መኰሳትና ገዳማት አንጃዊ ትምህርትና ፖለቲካ መሻው በሥርዓተ አሪት ጉዳይ ላይ የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣ ኖች የወሰዱት አዲስ የእምነት አቋም ነው። ከዚህ አኳያ፥ በ1230ዎቹ የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ኮፕቲክ ጸሐፊ አሳል በ325 ዓም በኒቅያ ጉባኤ የተቀመጡ 318 የዓለም አህጉሯዊው ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን ከግብፁ ወኪል አቡን በስተቀር ኢትዮጵያዊ ተወላጅ በአገሩ ቤተ ክርስቲያን በእምነትና በሃይማኖት ጉዳይ ላይ የበላይ መሪና አስተማሪ ለመሆን አይችልም ብለው ደንግገዋል የሚለ ውን ፍትሐ ነገሥት ካዘጋጀ ወዲህ የአሪትን የሥርዓተ ሰንበት አምልኮ በሚመለከት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ማዕቀብ እንዳ ደረጉበት ታውቋል፣[85]

የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና አቡን ወኪሎቻቸው ይህንኑ የአሪት ሃይማኖት ማዕቀብ በኢትዮጵያ ጥንኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ ስመጫን ብዙ ጊዜ ያልተሳካ ሙከራ እንዳደረጉ ተረጋግጧል። በዚህ ሁኔታና ሂደት በ1337 መኰሳው እምስጣጢዎስ በኢትዮጵያ ለሁለቱም የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ጥምር ነፃነት፥ እኩልነትና ዕድገት መጀመሪያ በኢትዮጵያ ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ወኪል ከአቡነ ያዕቆብ ጋር በይፋ ተከራከረ። ቀጥሎም በዚያው ዓመት በግብፅ ከሞዝሊት ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ቤንጃሚን (1327-39) ጋር በይፋ ተከራክሮ በአያሌ የመከለኛው ምስራቅ አገሮች ለ15 ዓመታት በስደት ኖሮ፥ በመጨረሻ በ1352 በአርመን አገር ሞተ።[86]

ይሁን እንጂ ከ1352 እስከ 1450 ድረስ ከላይ የተጠቀሱ የእምስጣጢዎስ ተከታይ መኰሳትና መምህራን አብዛኛ፥ ገብረኢየሱስ፥ ቆዝሞስና ፊልጶስ በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩ ሌላ የገዳምና የቤተ ክርስቲያን መምህራን ጋር የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ግዝት፥ የመንግሥትን ቅጣትና

[83] Taddasse Tamrat, Church and State, pp. 206-212.
[84] Ibid., pp. 213-219.
[85] Ibid., p. 209.
[86] Ibid., p.207.

የደብረ ሐይቅ ገዳም አቃቤ ሰዓቶችን ግፊት ተቋቁመው በመላው ሰሜን ኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻን አገር ጨምሮ በቀይ ባሕርና በጎጃም መካከል በሚገኘው ክልል ከክርስትና ጎን የአሪት ሃይማኖትን አስፋፍተው መሠረቱ።

በተጠቀሰው ዘመን አመፀኛ እምስጣጢዎሳ ውያን መኰሳት፥ ገዳማትና ምዕመናን በአንድ በኩል የክርስትና ሃይማኖትና ትምህርት በሚመለከት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያንና ከኢትዮጵያ ሰለሞናዊ መንግሥት እንዲሁም ከደብረ ሐይቅና ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙነት አቋረጡ።

በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ በቀይ ባሕር ለግብፅ መንግሥት ገባር ከነበረውና በኢትዮጵያውያን ሥዩመ ባሕር ተብሎ ከሚጠራው አስላማዊ የዳህላክ ደሴት መንግሥት ሱልጣን ጋር ጠንካራ የንግድና የወዳጅነት ስምምነቶች ፈጠሩ።[87] በዚህ ወቅትና ጉዳይ በሐማሴን የደብረ ቢዘኑ ገዳም መሥራች መኰሳው ፊልጶስ በአካባቢው የእምስጣ ጤሳውያኑ የአሪት አመፅ ግምባር መምህርና መሪ ሆነ።

እንደዚህ በሥፍራቱ በጊዜና በትምህርት በፍጥነት እያደገና እየተስፋፋ የመጣውን የእምስጣጢዎሳውያንን የአሪት አመፅ በኃያል እርምጃ ለማጥፋት፥ በግብፁ አቡነ በርተሎሚዎስ (1399-1431) እና በደብረ ሐይቁ ገዳም አቃቤ ሰዓት ሠረቀብርሃን ጥምር ግፊት በ1400 አጼ ዳዊት (1382-1412) የአመፁ ግምባር መሪዎችና መምህራን ከየአ ከባቢያቸውና ከየገዳማቸው በቤተ አማራ በጉባኤ ላይ ተገኝተው ከአ ቡኑና ከአማራ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በጉዳዩ ላይ በይፋ እንዲ ከራከሩበት አዘዘ።[88]

በንጉሡ ትዕዛዝ መሠረት እምስጣጢዎሳውያኑ አመፀኛ መኰ ሳትና መምህራን በደብረቢዘኑ መኰሳ ፊልጶስ መሪነት በጉባኤው ላይ ቀርበው በግብፁ አቡነ በርተሎሚዎስና በደብረ ሐይቁ ገዳም አቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ከተመሩ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ ኃይሎች የአሪት አመፃቸውን ትተው ወደ ግብፃውያኑ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት በይፋ እንዲመለሱ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ውድቅ አድርገው በአመፃቸው የበለጠ ጸኑበት። በመሆኑም ተቃዋሚ ኃይሎች የግዝት እና የሞት ቅጣት ወሰኑባቸው። በዚሁ መሠረትና ምክንያት የአማፅያኑ መሪ መኰሳው ፊልጶስ ለአራት ዓመታት በቤተ

[87] S. Tadeschi. "Note Storiche Salle Isole Dahlack," Proceedings of The Third International Conference of Ethiopian Studies. 3 Vols., (Addis Ababa, 1966), I, p. 61.
[88] Taddasse Tamrat, The Abbots of Dabra- Hyq 1248-1535", pp. 103-4; Church and State, pp. 213-14.

አማራ በማዙት ኖረ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ለግብፃውያኑ ማዕትና ጥቅም ጥብቅና የቆመውና የካህናቱ የነፍሱ አመፅ ቀንደኛው ጠላት የሆነው አቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ከሞተ በኋላ፥ በ1404 ፊልጶስ በጎብረተሰቡ ግፊት ከማዙት በኃላ ተለቀቀ። ከሁለት ዓመታት በኋላ በ1406 በ79 ዕድሜው ሞተ። አመፁ ግን ከእርሱ ጋር አልሞተም።

ከተግባርና ከታሪክ አኳያ በ1400 በቤተ አማራ ጉባኤ ላይ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን፥ እምነትና ትምህርት ላይ በሃይማኖት ስም በይፋ ባካሄዱ ብሔራዊ የነፍሱ አመፅ እምስጣ ጤምሳውያኑ መነኩሳትና መምህራን በሁለቱ የግብፅና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አንጻ ላይ የክርስቲያን ሕዝቡንና ጎብረተሰቡን አጠቃላይ ቁጣ ቀሰቀሱ። የሕዝበ ክርስቲያኑን የአገር ክብርና ነፍሱ ሰሜት አጋጋሉ።[89] ሁለቱንም ማለትም ክርስትናንና ሥርዓተ አሪትን የኢትዮጵያ ጥምርና ነፃ ሃይማኖቶች አደረጉ። በመሆኑ በኢትዮጵያ በግብፁ ምንደኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ የመጀመሪያውን የእምነት፥ የርዕዮተዓለም እና የትም ህርት ሽንፈት፥ ኪሣራና ውድቀት አደረሱ። በተጨማሪም በሚቀጥሉት እምስት አሥርታት የገዳማትንና የአብያተ-ክርስቲያናትን ማምባታና ትምህርት በመላው ሰሜን ኢትዮጵያ የበለጠ አስፋፉ።[90]

ባጭሩ ቄሶቹ በአካባቢው አራቱን አጎራባችና ተዛማጅ የትግሬ፥ የስሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦችንና ማኅበረሰቦችን በግዕዝ ቋን ቋና በጥምር የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች መሠረት እንድ በህውር ታዊ ጎብረተሰብ አደረጉ። ለማኅበረሰቦቹም ማኅበራዊና ባህላዊ መስተጋ ብርና መወራረስ መሠረትና መሣሪያ የሚሆኑ ብዙ የገዳም ድርጅቶ ችንና ማዕከላትን ከግዕዝ ብራና ሥነ ፅሑፍ ጋር ገነቡ። በውጭ ግንኙ ነት በኩልም በቀይ ባሕር ከዳህላክና ከምፅዋ ሥዬመ ባሕሮች ማለትም ሱልጣኖች ጋር ነፃ የንግድና የወዳጅነት ግንኙነቶችን የበለጠ አስፋፉ።

በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት የኢትዮጵያ ሰለሞናዊ መንግ ሥትና ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት ጉዳይ በሁለት እንዳይከፈል ከፍተኛ ሥጋትና ፍርሃት ያደረበት አጼ ዘርዓያዕቆብ (1434-68) በ1450 በሸዋ ክፍለ ሀገር በምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን በሰየመው ጉባኤ በግብፁ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን፥ እምነትና ትምህርት ላይ ሁለቱንም የክርስትናና የአሪት እምነቶችንና ሥርዓተ በዓላትን ነፃ፥ እኩልና ሕጋዊ የመንግሥቱ እምነቶች እንዲሆኑ በመወሰን ለችግሩ በፖለቲካ ጥበብ የጥገና መፍትሔ አገኘ።[91]

[89] Ibid., Church and State. pp. 216-17.
[90] Ibid., pp. 211.
[91] Ibid., pp. 219-220.

የ1332-1632 የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት ጦርነቶች

የደቡብ ኢትዮጵያውያን አመፅ ተጽዕኖ በሰሜን/ፈላሻ ታሪክ ላይ

በ330 ዓመተ ምህረት የክርስትና ሃይማኖት ወደ አዋማዊ የአ ክሱም አገርና ቤተ መንግሥት ከመግባቱ በፊት በግሪክና በግዕዝ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ በተጻፉ የአክሱም መንግሥታዊ የዜና መዋዕል ሰነዶች ግዕዝ፥ አጋሜ፥ አድዋ፥ አገው፥ ሰሜን፥ አክሱም፥ ወልቃይት፥ ዳሞ፥ ሐማሴን... ሁሉም በአካባቢው በሥፍራና በስም የታወቁ ጥንታዊ ሕዝቦችና አገሮች ናቸው።

ዛሬ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ኢትዮጵያና ኢትዮ ጵያውያን የተሰኙ የአገርና የሕዝብ ስሞች ታሪካዊ መነሻና ትርጉም በሚመለከት በጥንት ይሁዳውያኑ መፅሐፈ አሪት (ብሉይ ኪዳን) በአፍሪካ አህጉር በላይኛው የአባይ ሸለቆ ኩሽ (ጉቢያ) የተሰኘ አንድ ጥንታዊ የጥቁር ሕዝብና አገር ስም መጽሐፉ ከ280 ዓመተ ዓለም በኋላ በግብፁ የእስክንድርያ ከተማ ከይሁዳውያኑ ቋንቋ ወደ ግሪክ ሲተረጎም ኢትዮጵያ (ጥቁር) ተብሎ እንደተተረጎመ ታውቋል። ከስባት ምዕተ ዓመታት በኋላ በዘመነ ክርስትና በ470-550 በአክሱም ኩተማ በዘጠኙ ጻድቃን የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግዕዝ ሲተረጎም አሁንም ኢትዮ ጵያ ተብሎ ተገለበጠ።

በመጨረሻም በ550-1300 'የጨለማ' ክፍለ ዘመን ፍጻሜ ገደማ ማለትም በ1225 በአረብኛ ትርጉም ሀበሻ (አቢሲኒያ) በተሰኘ የአገር ስም ተጽፎ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ክብረ ነገሥት ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ በአጼ ጸምደፅዮን ዘመን (1314-44) በ1320 ገደማ በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ይስሐቅና በአምስት ወዳጆቹ ወደ ግዕዝ ቋንቋ በተተረጎመ ጊዜ ሀበሻ የተባለው የአረብኛ ስም አሁን ኢትዮጵያ ተብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የአንድ ሕዝብና አገር መንግሥታዊ ስም ተደርጎ ተወሰደ።

ከዚያ ወዲህ ሁለቱም የግዕዝ ቋንቋ ሕገ አሪትና ክብረ ነገሥት መጻሕፍት ለኢትዮጵያ ሰለሞናዊ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ባለሥ ልጣኖችና ምሁራን ብቻ ሳይሆን ልአጎራባቹ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መን ግሥትም የሃይማኖትና የመንግሥት ሰነዶች ሆኑ። የሁለቱም ሰለሞናዊ የአማራና የሰሜን/ፈላሻ ተግራሪ ነገሥታትና ካህናት በአንድ በኩል ራሳቸውን በኢትዮጵያ እንደመጡ ይሁዳውያን እንዲሁም የሕገ-አሪትና የክብረ ነገሥት መጻሕፍትን እንደየራሳቸው ታሪክና ሕግ አድርገው በመውሰድ «ምርጥ» የአብርሃም፥ የይሴሐቅ፥ የዳዊትና የሰለሞን ዘርና

ልጆች ማለትም እሥራኤላውያን ነን ብለው አወጁ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ነባር ባህል፥ ሃይማኖትና ታሪክ የአረመኔዎች ጣዖትና ባህል ነው በማለት ማጥፋት ጀመሩ። በፖለቲካና በእምነት ግፊት የዘርና የስም ለውጥ አደረጉ።

ለሁለቱም ሰለሞናውያን ነን ለሚሉ ተግራሪ ኃይሎች ሁለቱንም የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች አጣምረውና አዛምደው በግዕዝ ሕገ አሪትና ክብረ ነገሥት መጻሕፍት የሚያስተምሩና የሚተረጉሙ ከላይ የቀረቡ የኢትዮጵያ የትግራ-አማራ መነሻዎችና ገዳማት ናቸው። ነገር ግን በመካከላቸው እንደዚህ በተረት፥ በዘር፥ በቋንቋ፥ በሥፍራ፥ በገዜ፥ በታሪክና በሃይማኖት የተፈጠረው የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት የአማራና የሰሜን/ፈላሻ አጎራባች ነገሥታትና መንግሥታት በመሬት፥ በገበያ፥ በፖለቲካና በማኅት ጉዳዮችና መስኮች ለነበራቸው ጂኦ-ፖለቲካዊ ጦርነት የሰላም እማራጭ ወይም መፍትሔ አልሰጣቸውም።

ከዚህ አኳያ በአካባቢው በግምት በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል ሰሜን፥ ወልቃይት፥ ፀለምት፥ ፀገዴ፥ ወገራ፥ አርማጭሆ፥ በጌምድር፥ ጭልጋ፥ ደምቢያ፥ ቋራ የተሰኙ አገሮችን አጠቃሎ የሚይዘው እስትራቴጂያዊ ምድር፥ በዚህ ጥናት ተደጋግሞ በሰነዳዊ መረጃ እንደተገለፀው፥ ከጥንት ጀምሮ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ አገር ነው። ይህንኑ አንጡራ ያባት አገር ተጠቃሹ ሕዝብና መንግሥት በ300ዎቹና በ320ዎቹ ከአጎራባቹ የአክሱም መንግሥት ወረራ ለመከላከል ያካሄደው ታሪካዊ ትግል ከዘመኑ የግሪክና የግዕዝ ዜና መዋዕሎች ከላይ ተገልጿል።

ከዚያ ከ300ዎቹ የአክሱም-ሰሜን/ፈላሻ የመጀመሪያው የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት ሚሊኒየም በኋላ በ1332 አጼ አምደፅዮን ከክርስትና ሃይማኖት ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገቡ አማፅያን ናቸው የሚላቸውን አራት የሰሜን፥ የወገራ፥ የፀለምትና የፀገዴ ማኅበረ ሰቦችን (የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና አገር) ቤኃይል ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዲመለሱ ከዳሞት፥ ከሰቀልት፥ ከሃንደርና ከሀዲያ አገሮች የተመለመሉ ምርጥና ታዋቂ የፈረሰና የአግር ጦር ሠራዊቶችን በአንድ ፀጋ ክርስቶስ በተሰኘ የበጌምድር ገዥ አዝማችነት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ አዘመተ ባቸው በቃሉ ይመሰክራል።[92]

[92] Huntingford, Amda Seyon, pp. 11-2; J. Perruchon, tr. and ed., Histoires des Guerres d' Amba Syon, Roi D' Ethiopie, Journal Asiatique, Ser. 8, Vol. 14 (1889). pp. 339-340.

ባጭር አነጋገር ከሁለቱ የ300ዎቹና የ320ዎቹ የአክሱም-ሰሜን/ፈላሻ ጦርነቶች ጀምሮ በአንድ ሚሊኒየም ከፍለ ዘመን ውስጥ በአጼ አምደ ፅዮን ዜና መዋዕል ነው የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና ምድር ለሦስተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ የመንግሥት ሰነድ ተጽፎ የተገኘው። በመሆኑም ከእውነትና ከእውቀት አኳያ፥ በ550-1270 ክፍለ ዘመን የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት የአክሱሙን መንግሥት ያፈረሰና ያጠፋ ባዕድ ጠላት ነው የሚለው የኢትዮጵያ የሰለሞናውያን ክስ የታሪክ መሠረት የሌለው ተረት ነው። በመሆኑም ከዚህ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ ውጭና ውድቅ የሆነ ተረት ነው።

በሌላ በኩል ከታሪክ አኳያ፥ በተጠቀሰው የተከዜ-ዓባይ እስት ራቴጂያዊ ምድር ላይ በተጨባጭ የመሬት፥ የገበያ፥ የማዘትና የእስት ራቴጂ ጉዳዮችና ምክንያቶች በነባሩ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና በአዲሱ ሰለሞናዊ የአማራ መንግሥት መካከል ከ1332 እስከ 1632 ድረስ ለ300 ዓመታት ረጅም የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት እንደተካሄደና በመጨረሻ ተጠቃሹ ነባር ሕዝብ ከአገሩ እንደተነቀለ ሃይማኖቱም እንደተሰረዘ ቋንቋውና ባህሉም እንደጠፋ በድል አድራጊ ሰለሞናዊ የአማራ አጼ ነገሥታት አምደፅዮን፥ ዳዊት፥ ይስሐቅ፥ ዘርዓያዕቆብ፥ በዕደ ማርያም፥ እስክንድር፥[93] ናኦድ፥ ልብነድንግል፥ ገላውዲዮስ፥ ሚናስ፥ ሠርጸድንግልና ሱስንዮስ ዘመናት፥ ጸሐፊዎችና ዜና መዋዕሎች ተመዝግቦ ለትውልድና ለታሪክ በይፋ ተላልፈዋል።

ታሪኩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ከእነዚህ ነገሥታት፥ አጼ ይስሐቅ (1414-1429) ተጠቃሹን ሕዝብ በክርስትና ሃይማኖት ባይጠመቅና ለክርስቲያኑ ንጉሥም ባይገብር ከአገሩ ንቅል ስደተኛ፥ ሒያጅ፥ ፈላሲ (ፈላሻ) የሚያደረግ ሕግ አወጀ።[94] ሕጉም «ፈላሻ» ለሚለው የሰሜን ሕዝብ አዲስ የስድብና የጭቆና ስም መነሻ ሆነ። አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ደግሞ የሰሜን/ ፈላሻ ሕዝብ ከሕገ አሪት ተመልሶ በክርስትና ሃይማኖት ባይጠመቅ በሙሉ እንዲገደል የሚያደርግ የሃይማኖት ሕግ አውጥቶ በጦር ኃይል በተግባር ላይ ለማዋል ሞከረ። ይሁን እንጂ በሁለት የሕዝብ መሪዎች ማለትም በፀለምቱ አምባ ነሐድና በሰሜኑ ፀጋይ አመሯር ሰሜን/ፈላሾች ንጉሡን በአፀፋ ጦርነት አሸንፈው መለሱት።[95] እንዲሁም የሰሜን/ፈላሻ መሪዎች

[93] Arab Faqih, Conquete, p. 458 Note 1; Conti Rossini, Sarsa Dengel p. 107.

[94] Taddasse Tamrat, Church and State, p. 201.

[95] J. Perruchon, ed., Les Chroniques de Zarayaqoeb et de Baeda Maryam, (Paris, 1893), pp. 96-97.

የንጉሡን ጦርና ሹማምንቶች እንደደመሰሱ፥ በዘጌምድር በክርስቲያኖች ሕይወትና ንብረት ላይም ታላቅ ጥቃትና ጥፋት እንዳደረሱ፥ ብዙ ክርስቲያኖችን በኃይል ወደ ኦሪት ሃይማኖት እንደመለሱ በንጉሡ ዜና መዋዕል ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ፥ መነኩሴው የንጉሡ ልጅ አባ ሰብራ በአመጽ ወደ ኦሪት ሃይማኖት ገብቶ በሰሜን/ፈላሻ አገር የገዳም ትምህርትና ሥርዓት እንደአስፋፋ ተገልጿል።[96]

ሰሜን/ፈላሾች በአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመን በክርስቲያኑ መንግሥትና ጦር ላይ የከፈቱትን የማጥቃት ዘመቻ በልጁና በአልጋ ወራሹ በዕደግርያም ዘመንም (1468-78) በአምባሐድ አዝማችነት ለሰባት ዓመታት የበለጠ አጠናክረው እንዳስፋፉና በመጨረሻ ግን የንጉሡ የበጌምድር ገዥ አዝማች ማርቆስ በፖለቲካ ተንኮል ብዙዎቹን ሰብስቦ የሙያ፥ የዕድሜና የጾታ ልዩነት ሳያደርግ በብዛት እንደገደላቸው ታውቋል።[97]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በመጨረሻ፥ ከተማ ባር፥ ከታክቲክ፥ ከእስትራቴጂና ከውጤት አኳያ በ1332-1632 ክፍለ ዘመን በክርስቲያን ነገሥታትና በሰሜን/ፈላሻ ነባር ሕዝብ መካከል የተካሄደው ረጅም የጂአፖለቲካና የሃይማኖት ጦርነት በሁለት ርዕሶችና ክፍለ ጊዜያት ተከፍሎ ሊቀርብ ይችላል።

አንደኛ፥ ከ1332 እስከ 1524 ድረስ ክርስቲያን ነገሥታቱ ከሸዋ ማዕከላቸው በደቡብ ኢትዮጵያ ነባር አዋማዊና እስላማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ዘውትር የንግድ፥ የግዛትና የሃይማኖት ጦርነቶች በማካሄድ ላይ ስለነበሩ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ቡተከዜ-ዓባይ እስት ራቴጂያዊ ክልል የሰሜን/ፈላሻን ሕዝብና አገር በተመሳሳይ የትጥቅ ፖሊሲና ተግባር ለመያዝና ለመዝለት ጊዜም አቅምም አልነበራቸውም።

በሌላ በኩል የ1337-1450 የእምስጣጢዎሳውያኑ የኦሪት እምነት፥ ትምህርትና አመፅ በአካባቢው በአራቱ የትግሬ፥ የሰሜን/ ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ማኅበረሰቦች መካከል በሃይማኖት፥ በትምህርት፥ በባህልና በማዕዝ ሥነጽሑፍ አማካይነት መሠረታዊና ዘላቂ የሆነ የመስተጋ ብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት ፈጠረ። በመሆኑም በአራቱ የአካባቢው ሕዝቦችና ማኅበረሰቦች ዘንድ የነገሥታቱ የጠረኝነትና የዘረኛነት ፖሊሲና ተግባር ሕዝባዊ መሠረት፥ ተቀባይነትና ድጋፍ አልነበረውም።

[96] Hess, "Falasha History", p.113.

[97] Conti Rossini (tr. & ed.), History Regi d'Sarsa Dengle, (1907), p. 111; Budge, History, p. 316.

ሁለተኛ፥ በመጨረሻ ሁለቱ ታላላቅና ተዛማጅ የ1524-1543 የአዳሉ ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (1506-1543) የአመፅ ጦርነትና የ1520-1660 ታላቁ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ በአንድነት ክርስቲያን ነገሥታትንና ሰፋሪ ኃይሎችን ከመላው ደቡብ ኢትዮጵያ ቦግለውጣት በአንድ በኩል በታላቁ የተከዜ-ዓባይ እስትራቴጂያዊ ምድር ለሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት ውድቀት፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለአዲሱ የጎንደር አካባቢ መንግሥት (1577-1855) ክስተትና ዕድገት ሁለአቀፍ የአካባቢ፥ የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካ፥ የእስትራቴጂ፥ የኅሳና የሃይማኖት ግፊቶችንና ቅድመ ሁኔታዎችን ፈጠሩ።[98]

በሰሜን/ፈላሻ አገር የጎንደር መንግሥት ታሪካዊ መነሻና ውጤት

ከ1524 እስከ 1535 ድረስ ኢማም አሕመድ ግራኙ የአጼ ልብነ ድንግልን መንግሥትና ጦር ደምስሶ መላ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርን በቀይ ባሕር አስላማዊ የዳህላክና የምፅዋ ደሴቶችን ጨምሮ ከሥሩ አዋለ።[99] ከ1535 እስከ 1543 ድረስ ለዘጠኝ ዓመታት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሜን/ፈላሻ ምድር የደምቢያን ለምና ሀብታም አገር የሱልጣኔቱ (የመንግሥቱ) መሠረትና ማዕከል አድርጎ ቆረቆረ።[100] በዚህ ወቅትና ሁኔታ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በአጼ ልብነ ድንግል መንግሥትና ጦር ላይ ከኢማም አሕመድ ግራኙ ግምባር በጎበረት ተሰለፈ።[101] ይሁን እንጂ በ1543 የንጉሡን ክርስቲያን መንግሥትና ጦር ለመርዳት ክሕንድ የመጣው የፖርቱጋል የነፍጠኞች ግብረ ኃይል የኢማም አሕመድ ግራኙን ክፍለ አህጉራዊ ሱልጣኔት ደመሰሰ።

በየካቲት 1543 በደምቢያ ክፍለ ሀገር በጣና ሐይቅ አጠገብ በወይናደጋ ጦር ሜዳ በጥምር የፖርቱጋል ነፍጠኞች ግብረኃይልና የአጼ ገላውዲዎስ ሠራዊት ጎብረት የኢማም አሕመድ ግራኙ ጦርና ሱልጣኔት ተደመሰሱ። ከዚያ በኋላ ከ1543 እስከ 1597 ድረስ ለስድስት አሥርታት ሦስቱ አጼ ነገሥታት ገላውዲዎስ፥ ሚናስና ሠርፀድንግል በክፍለ አህጉሩ በ1524-1543 የኢማም አሕመድ ግራኙ አመፅና በታላቁ የ1520-1660 የሕዝቦች እንቅስቃሴ ጥምር ግፊት የፈረሰውን የሰለሞና

[98] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ፥ ም 3-4

[99] Arabfaqih, Conquete, pp. 456-59.

[100] Ibid., p. 461.

[101] Ibid., pp. 458-59

ውያንን መንግሥትና ጦር በክፍለ አህጉሩ እስላማዊ፥ አሞሃዊና አሪ ታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ መልሰው ለመቋ ቋም ያካሄዱ የትጥቅና የሃይማኖት ጥረቶች[102] ሁሉ ላይሳኩ ቀሩ። ነገር ግን በተለይ ሁለቱ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስና ሠርፀድንግል በፊት ለሰለሞናውያኑ መንግሥት ለሦስት ምዕተ ዓመታት ሁለት ታላላቅ የጂኦ-ፖለቲካ ጠላ ቶች የነበሩትን የአዳል ሱልጣኔትና የሰሜን/ ፈላሻ መንግሥት ለመጨረሻ ጊዜ በጦር ኃይል አጠፉ።[103]

ከዚህ አኳያ ከኢማም አሕመድ ግራኙ ሞት በኋላ ከየካቲት እስከ መስከረም 1543 ድረስ፥ አጼ ገላውዴዎስ ጊዜያዊ ጦር ሠፈሩን በደምቢያ አድርጎ የደምቢያ የጎጃም፥ የበጌምድር፥ የላስታ፥ የሰሜን/ ፈላሻ፥ የትግሬ ሕዝቦችንና አገሮችን ከሥሩ በሹም ሽር አደራጃቸው።

በዚህ ወቅት በሌላ ግምባር እንዲሁም የሚቹ ኢማም አሕመድ ግራኙ የወንድም ልጅና አልጋወራሹ ወዚር ዓባስ አቡን ከበጌምድር የቀድሞ ግዛቱ ከኢማሙ ዝነኛዋ ሚስት ከባእትያ ድል ወንበራ ማሕፉዝ ጋር በሽሽት አምልጦ በደቡብ ምስራቅ ሦስቱን የፈጠጋር የደዋሮና የባሌ አጎራባች አስላማዊ አገሮችን በአንድነት ከሥሩ አደራጃቸው።

በደቡብ ምስራቅ በወዚር አባስ አቡን ወደሚመራው አዲሱ የአዳል መንግሥት ግምባር ከመመልሱ በፊት አጼ ገላውዴዎስ በፖርቱ ጋል ነፍጠኞች እርዳታ በደቡብ፥ በደቡብ ምስራቅና በመሀል ምዕራብ ኢትዮጵያ የሸዋ፥ የዳሞት፥ የጋፋት፥ የእናርያ፥ የቦሻ፥ የጉራጌ፥ የቀጅና የሀዲያ ሕዝቦችንና አገሮችን ከሥሩ ለማምጣት ያልተሳኩ ወታደራዊ ዘመቻዎችን በማካሄድ በአገሮቹ ላይ በሕይወ ትና በንብረት ታላቅ ጥቃታና ጥፋት አደረሰ።

በተጨማሪም በ1543 መጨረሻ በዝዋይ አዋሽ ክልል የቀጅን አገር የመንግሥቱ አዲስ ማዕከል አደረጎ ያዘ። ከ1543 እስከ 1559 ድረስ የንጉሡ የቀጅ ጦር ሠፈር በአዳልና በኦሮሞ እንቅስቃሴዎች ግምባር የአገሪቱ ዋናው የፖለቲካና የጦርነት ዞን ሆነ።

በጥቅምት 1544 አጼ ገላውዴዎስ ወዚር አባስ አቡንን በቀጅ ጦርነት ገደለ። ከዚህ ከወዚር አባስ አቡን ሞት በኋላ ከቀጅ ማዕከሉ አጼ ገላውዴዎስ በተከታታይ በሀዲያ፥ በጉራጌ፥ በዳሞት፥ በጋፋትና በእናርያ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ብዙ የቅጣት የዘረፋ፥ የፀጥታና የግብር ዘመቻዎችን አካሄደ። በተጨማሪም በቢፎሌ ሉባ ዘመን (1546-1554)

[102] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ም 5.

[103] Ibid.,

ከአዋጅ ሠፈሩ ተነስቶ ከኦሮሞዎች ጋር በባሌ አካባቢ በአገሩ ታሪክ የመጀመሪያውን ጦርነት አካሄደ።

ከ1540ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ እስከ 1550ዎቹ ድረስ አጼ ገላውዴዎስ ከዋጅ የጦር ሠፈሩ ከአዳሎች፥ ከኦሮሞዎች፥ ከሀዲያዎች፥ ከፖርቱጋሎችና ቱርኮች ጋር በትጥቅ፥ በፖለቲካና በሃይማኖት ሲዋጋ ዘመኑን በጦር ሜዳ ሞት ፈጸመ።

ከዚህ አኳያ ከ1547 እስከ 1550 ድረስ አጼ ገላውዴዎስና ሁለቱ ታላላቅ የጦር አበጋዞች ራስ ፋኑኤልና ራስ ሐመልግል ከሐረር እስከ ዜይላ «ከባር ሰዕደዲን እስከ ባር አጀም ድረስ» ግለትም ከአዋሽ እስከ ኤደን ባሕረሰላጤና እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ድረስ በታላቁ የአዳል አገርና መንግሥት ላይ ብዙ ተከታታይ የቅጣት ዘመቻዎችን በማካሄድ በሕይወትና በንብረት ታላቅ ጥቃትና ጥፋት አደረሱ። መንደሮችን፥ ከተሞችንና መስጊዶችን አፈራረሱ። አቃጠሉ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ አጼ ገላውዴ ዎስና የጦር አበጋዞቹ እንደዚህ የበቀልና የጥፋት ዘመቻዎች ሲያካ ሄዱ፥ በሌላ በኩል በ1555-57 ቱርኮች በሰሜኑ ጠረፍ የዳህላክና የምፅዋ ደሴቶችን በጦር ያዙ። በሚቀጥሉት ዓመታትና አሥርታት ቱርኮች ከምፅዋና ከሰዋኪን ተነስተው በአርኪኮ፥ በሐማሴን፥ በሰራዬ፥ በደባርዋ፥ በአከለገዛይ፥ በቡር፥ በትግሬና በመዘጋ ከተሞች፥ ቀበሌ ዎችና አውራጃዎች ላይ ረጅም የወረራ ጦርነት ከፈቱ።

ቱርኮች በሰሜን ኢትዮጵያ ላይ የወረራ ጦርነት በከፈቱበት ዘመን አጼ ገላውዴዎስ በደቡብ ምስራቅ፥ በአዋሽ-ዝዋይ ክልል፥ በፈጠጋርና በደዋሮ አካባቢ ከኦሮሞ የምችሌ ሉባ (1554-1562) ጋር በጦርነት ላይ ነበር። በውሆኑም በ1558 በሰሜን ባሕረነጋሽ ይስሐቅን ከደባርዋ ከተማ በቱርኮች ላይ አዘመተ። በ1558 አጼውና ባሕረነጋሹ በየግምባራቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድል ከተቀዳጁ በኋላ በመጋቢት 1559 በዋጅ ከአዳሉ ኤሚር ኑር፥ የሐረር ግመብ መሥራች፥ ጋር ሲዋጋ አጼ ገላውዴዎስ ራሱ ተገደለ።[104]

በአጼ ገላውዴዎስ ሞት ወንድሙ አጼ ሚናስ (1559-1563) ነገሠ። የአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት አጭር የውጥረት ወቅት ነበር። መንግሥቱ በደቡብ በአዳል፥ በሀዲያና በኦሮሞ የፍለሳና የሰፊራ እንቅስቃሴዎች፥ በሰሜን ደግሞ በሰሜን/ፈላሻና በባሕረ ነጋሽ ይስሐቅ አመፅ እንዲሁም በፖርቱጋሎችና ቱርኮች ግፊት እንደተወጠረ አጼ ሚናስ ራሱ በየካቲት 1563 በዋግ የዘረፋና የቅጣት ዘመቻ በማካሄድ ላይ

[104] W. Conzelman tr. and ed., Chronique de Galawdewos (Paris, 1895).

ሳለ በድንገተኛ ሕመም ሞተ። ከዚያ በፊት በሰሜን/ፈላሻ ላይ ወረራ አካሂዶ በሽንፈት እንደተመለሰም ታውቋል።

ከአጼ ሚናስ ሞት በኋላ፥ ከ1563 እስከ 1568 ድረስ፥ በክርስቲያኑ ቤተ መንግሥት አካባቢ ረጅም የሥልጣን ባላንጣዎችና አንጃዎች ጦርነት ተካሄደ። ከዚህ አኳያ የአጼ ሚናስ ሞት እንደተሰማ በቤተ መንግሥቱ አደባባይ አንድ የባለሥልጣኖች አንጃ የሚቹን የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ሠርፀ ድንግልን (1563-97) መለከሰገድ በሚል የዙፋን ስም በአክሱም ከተማ እንገሠ። በራስ ሐመልማል የተመራ አንድ ሌላ የሥልጣን አንጃ በበኩሉ በደቡብ ማለትም በሸዋ አንድ ሌላ ባላንጣ መስፍን አነገሠ። ፋሲል የተሰኘ አንድ ሌላ የጦር አበጋዝ ደግሞ በምዕራብ ማለትም በዳሞት ሦስተኛውን መስፍን አነገሠ። ይሁን እንጂ የሠርፀድንግል አንጃ መለሳይ ተብለው የሚጠሩ እስላማዊ የአዳል ምንደኛ ወታደሮችን በቅጥር በመጠቀም የሐመልማልንና የፋሲልን አንጃዎች ደምስሶ የአጼውን በትረ ሥልጣን በእጁ አደረገ።[105] እነዚህ መለሳይ የተሰኙ የአዳል ወታደሮች በፊት የኢማም አሕመድ ግራኙ ወታደሮች ነበሩ።

በአዳሉ የመለሳይ ምንደኛ ወታደሮች ድጋፍ በሥልጣን ባላንጣዎቹ ላይ ፍጹም የኃይል ሚዛን ካገኘ በኋላ፥ አጼ ሠርፀ ድንግል በ1597 እስኪ ሞት ድረስ በሦስት አሥርታት ዘመን በውስጥና በውጭ ጠላቶቹ ላይ ማለትም በደቡብ በሀዲያዎች፥ በጉራጌዎች፥ በአሮሞዎችና በአዳሎች ላይ፥ በሰሜን በባሕረነጋሽ ይስሐቅ፥ በቱርኮችና በሰሜን/ፈላሾች ላይ፥ በሰሜን ምዕራብ በአገዎችና በጉሙዞች ላይ፥ በመሀል ምዕራብ በዳሞቶች፥ በጋፋቶች፥ በእናርያ፥ በቢዛሞ፥ በቦሻና በጎንጋ ላይ ብዙ የማት፥ የቅጣትና የዘረፋ ጦርነቶች አካሄደ። ለንጉሡ በእነዚህ የወረራና የቅጣት ጦርነቶች ድል፥ ሀብትና ኃይል ያስገኙለት መለሳይ፥ ቁርባን፥ አቄትዝር፥ ጨረቃ፥ ገዮርጊስ ኃይሌ፥ ቱርክ፥ አፍሮአይገባ፥ ኮከብ ተብለው በልዩ ልዩ ስሞች የሚጠሩ በከፍተኛ የጦር አበጋዞች የሚመሩና በአርሶ አደሮች ምርት፥ ንብረትና ጉልበት በዘረፋ የሚኖሩ የጨዋ ማለትም የወታደር ድርጅቶችና ኃይሎች ነበሩ።[106]

ከ1569 እስከ 1577 ድረስ እነዚህን በወረራና በዘረፋ የሚኖሩ የጦር ኃይሎችን አስከትሎ አጼ ሠርፀ ድንግል ከዋጅና ከግንደበረት የጦር ሠፈሮች በደቡብ በተጠቀሱ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ብዙ ጦርነቶችን አካሄደ። በዚህ ወቅት በመጋቢት 1577 በዋቤ ሸለቆ ጦርነት በመለሳይ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች ድጋፍ የአዳሉን የመጨረሻ

[105] Conti Rossini, Sarsa Dengel, Chaps. 1-4.

[106] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ም 84-85.

ሱልጣን መሐመድ አራተኛን ከቀድሞ የኢማም አሕመድ ግራኙ የጦር አለቆችና ከሦስት የሐረሩ ኤሚር ኑር ልጆች ጋር በመግደል የአዳልን መንግሥት ወደ ዘመነ ፍጻሜው አደረሰ።

በመጋቢት 1577 የዋቤ ሸለቆ ጦርነት የአዳልን መንግሥት ከደመሰሰ በኋላ ለአጼ ሠርፀ ድንግል በደቡብ ኢትዮጵያ በአራት የነባ አካባቢዎችና ግምባሮች ተከፋፍለው በፍለሳ ስምሪት ከእንሰሳት መንጋ ዎቻቸው ጋር የሚንቀሳቀሱ የከረዩ፥ የወሎ፥ የቱለማና የሜጫ አሮሞ ግጎበረሰቦች፥ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የአገው፥ የሰሜን/ፈላሻና የጉሙዝ ሕዝቦች እንዲሁም በሰሜኑ ጠረፍ ከምፅዋ የቱርክ ወራሪዎች ከአካባቢው አማፅያን ጋር በትጥቅ የሚፋለማቸው የውስጥና የውጭ ዋና ዋና ጠላቶች ሆኑ።

በዚህ ሁኔታና ወቅት ከመጋቢት 1577 የዋቤ ሸበሌ ጦርነት በኋላ አጼ ሠርፀድንግል በድቡብ ኢትዮጵያ የአሮሞዎችን ግምባር ከፍት ትቶ ከአሠራዊቱ ጋር በሰሜን ምዕራብ በሰሜን/ፈላሻ ምድር በፊት የኢማም አሕመድ ግራኙ ዋና ማዕከል የነበረውን የደምቢያ ሰምና ሰፊ የእርሻ አገር የጠሩና የመንግሥቱ ቋሚ ማዕከል አድርጎ ያዘ። ማለትም በአካባቢው የጎንደር ዘመነ መንግሥት (1577-1855) ግም ቢታ ተግባር ጉባኤ በተባለ መንደር በንጉሡ የጦር ሠፈር ተጀመረ።

የሠርፀ ድንግልና የሰሜን/ፈላሻ ጦርነቶች (1580-1595)

የቱርክ ኃፍጠኞችና መድፎች በሰሜን/ፈላሻ ተራሮች

በ1578 አጼ ሠርፀ ድንግል በደምቢያ ከጉባኤ የጦር ሠፈሩ የአዳልን መለሳይና የአሮሞን ሉባ የተባሉ ወታደሮችን ጨምሮ ከልዩ ልዩ አገሮችና ሕዝቦች በኩታት አዋጅ የተጠራ ግዙፍ ሠራዊት አስከትሎ ከሚያዝያ እስከ ታኅሣሥ በሰሜን ኢትዮጵያ በባሕረነጋሽ ክፍለ ግዛት በቱርክ ወራሪዎችና ከ1563-1568 የሥልጣን ጦርነት ዘመን ጀምሮ የቱርኮች ተባባሪ በሆነው ባሕረነጋሽ ይስሐቅ ላይ ዘመተ። በጦርነቱ ሁለቱም ባሕረነጋሽና የቱርኩ ጦር አዛዥ በንጉሡ ወታደሮች ተገደሉ። ሠራዊታቸውም በንጉሡ ጦር ተደመሰሰ። የደባርዋ የጦር ምሽጋቸውም ፈረሰ። በተጨማሪም ብዙ የቱርክ ኃፍጠች፥ መድፎችና ወታደሮች በንጉሡ ምርኮ ተወሰዱ። እነዚህ የቱርክ ኃፍጠኞች፥ መድፎችና ወታደሮች በሚቀጥለው የሰሜን/ፈላሻ ረጅምና አስቸጋሪ የ1580-1595 ጦርነት ለንጉሡ የድል ሚዛን ወሳኝ መሣሪያዎች ሆኑ። በመሆኑም በመጋቢት 1579 ድል አድራጊው ሠርፀድንግል ከሰሜኑ ጦር ግምባር ከአሠራዊቱ በአክሱም በኩል አድርጎ በደምቢያ ወደ ጉባኤ የጦር ሠፈር ተመልሶ ገባ።

የ1580 የካሌፍ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት

በ300ዎቹ አሥርት በሰሜን/ፈላሻ አገር ላይ የመጀመሪያ ወረራ ያካሄደው የአክሱም አዋማዊ ንጉሥ በግሪክ ዜና መዋዕሉ አጉሩን «ዓመቱን በሙሉ ዝናብ፥ ብርድ፥ ውርጭና በረዶ» የማይጠፋበት በጣም አስቸጋሪ ተራራማ አገር ነው ብሎ እንደገለጸው ይታወቃል። ከ1280 ዓመታት በኋላ በጥቅምት 30 ቀን 1580 በሰሜን ተራራ «ካሌፍ አምባ» ላይ በአጼ ሠርፀ ድንግልና በሰሜን/ፈላሻው መሪ ካሌፍ ወታደሮች መካከል በቋመድፍና በመርግ (በድንጋይ ናዳ) የተካሄደውን ጦርነት በአይኑ አይቶ የመዘገበው ወልደ ሃይማኖት የአጼው ዜና መዋዕል ጸሐፊ፥ «የሰሜን ምድር ክፉት»[107] በሚል ርዕስ እንደ ሚከተለው ይገልጻል።

> *ሊንደኛ፥ የአገሩ መንገድ ሁሉ ገደላማ ነው። ፈረሶች በቅሎችና አህዮች በሰሜን ተራሮች መንገድ ላይ አይሄዱም።*
>
> *ሁለተኛ፥ የተራሮቹ ኃይለኛ ውርጭና ብርድ ያልለመደውን የውጭ ሰው አያኖሩም።*
>
> *ሦስተኛ፥ በተራራው አምባዎች ላይ ሁልጊዜ በረዶ ይወርዳል። ለምሳሌ፥ በጥቅምት 30 ቀን 1580 የአገሩ መሪ ካሌፍ በአምባው ላይ በአጼ ሠርፀድንግል ጦር በተከበበ ቀን ሌሊቱን በረዶ ሲወርድ አደረ። ሲነጋም በንጉሡ ድንኳንና በጦሩ ሠፈር ዙሪያ ሙሉ የበረዶ ከምር ነበር። የሠፈሩ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ሲንቀሳቀሱ በበረዶ ላይ መሄድ ጀመሩ።*[108]

ዘመናዊ የኑፍጥና የመድፍ መሣሪያዎች በፖርቱ ጋሎችና በቱርኮች አማካይነት ወደ አገሩ እስኪገቡ ድረስ ከአጎራባች የአክሱም፥ የአገውና የአማራ ተከታታይ መንግሥታትና ነገሥታት ግፊት የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብን ብሔራዊ ነፃነት ለዘመናት ጠብቀው ካኖሩት ብዙ ሁኔታዎች እና ኃይሎች አንዱ ይኸው የአካባቢ ልዩ የተፈጥሮ ገፅታ ነው ሰማለት ይቻላል።

ከዚህ ከተፈጥሮ ሁኔታ አንድ ሌላ የሰሜን/ ፈላሻ ሕዝብና አገርን ለረጅም ዘመን በሉአላዊ ነፃነት ያኖረው የራሱ የሕዝቡ አስገራሚ የመርግ ማለትም ከተራራ አናት በጠላት ላይ የሚወርደው የድንጋይ ናዳ መሣሪያ ነው። በከፍተኛ የሰሜን ተራራ አምባዎች ዙሪያ ከላይ ከገደል አፋፍ ወደታች በጠላቶች ላይ የሚለቀቁ መርጎች በመጫኛ ታሥረው ይኖራሉ።

ከዚህ አኳያ ለምሳሌ በታኅሳስ 1580 በረድ ኤት አምባ ላይ የንጉሡ የቱርክ ኑፍጠኞችና መድፈኞች በአዲሱ የጦር መሣሪያና ሥልት ወረራ ባካሄዱበት ጊዜ በተጠቀሰው አምባ ዙሪያ ከአጼ

[107] Conti Rossini, Sarsa Dengel, p. 112.
[108] Ibid., p. 112.

ነገሥታት በዕደግርያም፥ እስክንድርና ናአድ[109] ዘመናት ጀምሮ በመጫኛ የታሰሩና ብርሃን፥ ሀሳብና ባዋ ተብለው የሚጠሩ የመርግ መሣሪያዎች ከጠባቂዎች ጋር ተጠምደው እንደተገኙ የንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ወልደ ሃይማኖት አስታውቋል። በተጨማሪም ከአሱ የሚወለደው የቋራው ካሣ-ቴዎድሮስ በኋላ እንደሚያደርገው ሰሜን/ ፈላሾች በጠላት እጅ ምርኮኛ ሆነው ከመዋረድ በገደል ውስጥ በመውደቅና እርስ በርሳቸው በጉራዴ ስለት በመሰያየፍ ራሳቸውን በቅድሚያ መግደል እምነታቸውም ባህላቸውም ነበር።

እነዚህን ልዩ የተራራ ጦር መሣሪያዎችን፥ ሥልቶችንና ልምዶችን በመጠቀም አምባ ነሐድና ፀጋይ የተባሉ የሰሜን/ፈላሻ የጦር መሪዎች አፄ ዘርአያ ዕቆብንና ጦሩን ከአገራቸው በሽንፈት እንደመለሱ፥ እንደገና አምባሐዶና ተከታዮቹ ከአፄ በዕደግርያም ጋር ለሰባት ዓመታት እንደተዋጉ በ1559 ደግሞ ሪድኤት የተባለ ያገር መሪ የአፄ ሠርፀድንግልን አባት የአጼ ሚናስን ወራሪ ጦር ከምድረ ሰሜን/ፈላሻ አሸንፎ እንደ መለሰው ይታወሳል።

በመጨረሻ በጥቅምት 1580 አጼ ሠርፀድንግል ራሱ ከደምቢያ ጦር ሠፈር የቱርክ ኑፍጠኞችንና መድፈኞችን ጨምሮ ከትግራ፥ ከአግራ፥ ከአገውና ከኦሮሞ ወታደሮች የተሰባሰበ በ1578 በሰሜን ጦር ግምባር የቱርክንና የባሕረነጋሽ ይስሐቅን ሕብረ ሠራዊት በደመሰሱ የጦር አበጋዞች ሐሊቦ፥ ደሀርጎት፥ ዮናኤል፥ ተክለ ጊዮርጊስ፥ ዕቁበ ሚካኤልና አባ ንዋይ በሚባል የግምባር ጦር አዛዥ መነኩሴ በሕብረት የሚመራ ግዙፍ ሠራዊት አስከትሎ የሰሜን/ፈላሻ ጠረኛ መሪ «ረድኤት የእህል፥ የግር፥ የላምና የበግ ግብር» አልከፈለም በሚል የጠብ መቀስቀሻ በወገራና በሰሜን አጎራባች አውራጃዎች ላይ ታላቅ የዘረፋ ጦርነት በራሱ የበላይ አመራርና ቁጥጥር ከፈተ።

በመሆኑም ረድኤትና ወንድሙ ካሌፍ ባልተለመደ አዲስ የኑፍጥና የመድፍ መብረቃዊ መሣሪያዎች ታጥቆ ከመጣው ጠላት ጋር በታወቀው የሰሜን/ፈላሻ የመርግ መሣሪያ በግምባር ለመጋጠም በየአምባቸው ተንቀሳቅሱ። የንጉሡ ጦር በወገራና በሰሜን አውራጃዎች «የእሰላሞችንና[110] የፈላሾችን እህልና እንሰሳት» በመዝረፍ ጦርነቱን ጀመረ። ካሌፍ በበኩሉ የጠላቱን እንቅስቃሴና የወረራ እርምጃ ለማሰናከል የአገሩን መንገዶች ማፍረስ፥ ቤቶችና የእህል ማሳዎች በቅድሚያ ማቃጠል ጀመረ። ቀጥሎም ካሌፍና ጦሩ ከአምባ ምሽጋቸው ሆነው ከሦስት አቅጣጫዎች አምባውን ለመያዝ የመጣ

[109] Ibid., p. 103.
[110] Ibid., p. 97.

ውን የንጉሡን ሠራዊት በመርግ ናዳ ገጠሙት። በንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በወልደ ሃይማኖት እንደ ተገለጸው «በሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች መካከል መሻገር የማይቻል አንድ ትልቅ ገደል አለ። በዚህ ጊዜ በንጉሡ ሠራዊትና በፈላሻው ጦር መካከል ጠንካራ ውጊያ ተጀመረ። የካሌፍ ሠራዊት ከተራራው አምባ ላይ ሆኖ የንጉሡ ጦር ከታች ወደ አምባው እንዳይወጣ በመርግ ናዳ ከለከለ።»[111]

በዚህ ሁኔታና ጊዜ ንጉሡ የካሌፍን አምባ እንዲደበድቡ የቱርክ መድፈኞቹን አዘዘ። በዚህ «በድንቁጥኛ የመድፍ ቱኩስ ካሌፍ ታወከ። ወታደሮቹም ታወኩ። በሙሉ ተበተኑ። በላያቸው ላይ ከሰማይ መብረቅ የወረደባቸው መሰላቸው። የንጉሡ ወታደሮች ከፊትና ከኋላ ከግራና ከቀኝ ሽምቀው የመውጫ መንገዶችን ስለዘጉባቸው ካሌፍና የጦር አለቆቹ ቢታሳቅ ጭንቅ አምልጠው ወደ አንድ ከፍተኛ የገደል ጫፍ ላይ ወጡ። ከካሌፍ ወታደሮች ግማሾቹ በንጉሡ ወታደሮች ተገደሉ። ብዙዎቹ ከመግረክ በገደል ወድቀው አለቁ። በእግር የሚሄዱ ሁሉ እንዲገደሉ መኮሩሴው አባ ንዋይ በግዘት አዝዞ ስለነበር በካሌፍ አምባ ጦርነት የንጉሡ ወታደሮች የስሜን/ፈላሸ ሰውንና እንስሳትን በሙሉ ገደሉ»[112] በጦርነቱ የተሸነፉ ሰሜን/ፈላሾች በበኩላቸው በክርስቲያን ጠላቶቻቸው እጅ ከመግረክ በገደል ይውድቁ እንደነበር፥ በአንድ የክርስቲያን ወታደር የተማረከች እስረኛ ሴት ወታደሩን ይዛ ገደል እንደገባችና ብዙዎቹም በጠላት ከመማረክ እርስ በርሳቸው በስለት ተራርደው እንዳለቁ ጸሐፊው ወልደ ሃይማኖት ጨምሮ ገልጿል።[113]

የ1580 የረድኤት አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት

ከታሪክና ከጊዜ አኳያ አጼ ሠርፀድንግል በጥቅምት 1580 የካሌፍን አምባ ምሽግ በናፍጥና በመድፍ መሣሪያዎች በደመሰሰው ጊዜ የሰሜን/ፈላሻ የተራራና የመርግ ያገር መከላከያ ሥርዓት ብሎም የአገሩ ፖለቲካዊ ህልውና ወደ ፍፃሜው ዋዜማ ደረሰ። በዚህ ረገድና ተግባር፥ መድፈኛው አጼ ሠርፀ ድንግል ከጎንደር 20 ቀን እስከ ታህሣሥ 4 ቀን 1580 ድረስ መካሻ በተሰኘ ወንዝ አጠገብ የረድኤትን የአምባ ምሽግ በሁለት ሣምንታት የናፍጥና የመድፍ ከበባና ድብደባ ሰበረ። በጥንታዊ የመርግ፥ የጋሻ፥ የቀስትና የጎራዴ መሣሪያዎች በሚከለከሉ የሰሜን/ፈላሻ አምባ ምሽጎች ላይ በዘመናዊ የቱርክ ናፍጥና መድፍ መሣሪያዎች ታጥቆ የመጣበትን ያገር ጠላት

[111] Ibid.,
[112] Ibid., p. 101.
[113] Ibid.,

መመከት እንደማይችል ከወንድሙ ካሌፍ ሽንፈት የተረዳው ረድኤት በመኮሩሴው አባ ንዋይ አማካይነት ከአጼ ሠርፀድንግል ጋር በኡሪትና በወንጌል ቃለ መሃላ በሰላም ስምምነት ተደራድሮና «በራሱ ላይ አመድ ነስንሶ» ማለትም ሽንፈቱን በመሃላ ቃል ተቀብሎና ምህረት ጠይቆ በታኅሣሥ 6 ቀን 1580 ለንጉሡ እጁን ሰጠ።

የ1587 የጉሸን መርቅ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት

በ1587 ጉሸንና ጌዴኦን በተሰኙ ያገር መሪዎች ጥምር አመራር በሰሜንና በወገራ አውራጃዎች በታላቁ የወርቅ አምባ ምሽግ አንድ ሌላ የሰሜን/ፈላሻ አመፅና ጦርነት ተቀሰቀሰ።[114] የወርቅ አምባ ምሽግን ከጉሸን-ጌዴኦን አማፅያን ለማለቀቅ አጼ ሠርፀ ድንግል ከትግሬ፥ ከአማራ፥ ከአገው፥ ከኦሮሞና ከቱርክ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች የተዝለ አንድ ግዙፍ የጦር ሠራዊት በስመ ጥር አዛዦች ደሀርትት፥ የኑኤል፥ እቁበ ሚካኤል፥ አባ ንዋይና በሌሎችም አዝማችነት በአራት ግምባሮች ከፍሎ አምባውን አስከበበ። በከበባው መጀመሪያ በ1578 የቱርኮች ወረራ ጊዜ ታላቅ የጀብድ ሥራ የሠራ አርበኛው እቁበ ሚካኤል ከነጠሩ በተሰማራበት በሸሀና ግምባር በጉሸን አማፅያን በመገደሉ ንጉሡ በኃይል ተናዶ በተጠቀለው አምባ የሚኖሩ ሰሜን/ ፈላሾች ከአምባው አጠገብ ካለው ምንጭ ውሃ እንዳያገኙ ምንጩን በሀይለኛ የኦሮሞ ወታደሮች አስጠበቀ። የሸሀና አምባ ነዋሪዎች በውሃ ጥም ተሸንፈው በአጭር ጊዜ ውስጥ የንጉሡን ምህረት ጠይቀው እጃቸውን ሰጡ። ነገር ግን ምርኮኞቹ በምሕረት ክገቡ በኋላ ለማምለጥ ሲሞክሩ ተይዘው በሙሉ ተገደሉ።

ጉሸንና ጌዴኦን ከጦራቸውና ከተከታዮቻቸው ጋር የመሸጉበት የወርቅ አምባ በጣም ረጅምና አስቸጋሪ ሥፍራ በመሆኑ የንጉሡ ኦፍጠኞችና መድፈኖች በቀጥተኛ ተኩስ መስበር ስለአቃታቸው ንጉሡ ግታ በጨለማ በመጫኛ መሰላል ወደ ተራራው ወጥተው የሚሰብሩ የአገውና የቱርክ ምንደኞችን በቅጥር አሰማራቸው። በዚሁ መሠረትና ቁጣር ንፍታሌምና ገብረ ኢየሱስ የተባሉ ሁለት አገሮች በታላቅ ችግር ወደ ወርቅ አምባ አናት ላይ ወጥተው ጠላቂውን ገደሉት። ከዚያም የንጉሡ ጨዋዎች (ወታደሮች) ከቱርክ ምንደኞች ጋር ወደ አምባው አናት ላይ ወጥተው በድንገት ጦርነት ከፈቱ። በአምባው ቤቶችና የእህል ማሳዎች ላይም እሳት ለኮሱ። በዚህ ሁኔታና ጊዜ ጉሸን በ60 ከሚቆጠሩ ተከታዮቹ ጋር በአምባው ገደል ወድቆ ሞተ። ጌዴኦን ግን ከ15 ጦርና ጋሻ ከያዙ ተከታዮች ጋር በጨለማ ሽፋን

[114] Ibid., p. 115-123.

ከአምባው ወርዶና ከታች ዙሪያውን በከበቡ የንጉሡ ወታደሮች ሳይታይ ለጊዜው አመለጠ። ነገር ግን በኋላ ሲሸሹ በንጉሡ ጦር በተከበቡ ጊዜ ጌዴኦንና ተከታዮቹ በጠላት እጅ ከመማረክ አርስ በርሳቸው በስለት ተራርደው[115] ሞቱ። በተጨማሪም፥ ከ300 ዓመታት በኋላ በ1868 የዚህ ኩሩና ቆራጥ የሰሜን/ፈላሻ ወገን ተወላጅ የቋራው ካሳ ቴዎድሮስ በታላቁ የመቅደላ ጦር ሜዳ እንደሚያደርገው የአርበኛው ጉሸን እናትና ሚስት ባገር ጠላት እጅ ከመውደቅ ራሳቸውን በስለት ገደሉ።[116]

አጼ ሠርጸ ድንግልና ጠፊኛው መነኩሴ አባ ንዋይ ከ1580 እስከ 1587 የሰሜን/ፈላሻን የአምባ ሕዝብና መንግሥት በኑጥና በመድፍ ካስገበሩ በኋላ በሦስቱ የካሌፍ፥ የረድኤትና የጉሸን አምባዎች ላይ አብያተ-ክርስቲያናት መሠረቱ። በመጨረሻ በ1594 አጼ ሠርፀድንግል ከደምቢያ በስተምዕራብ የሚገኘውን የሰሜን/ፈላሻ የቋራ ጠረፍ አገር አስገበረ።[117] ይሁን እንጂ ከዚህ በታች እንደሚታየው፥ «የሰሙት አምባው» ጌዴኦን ወይም ዳግማዊ ጌዴኦን ከ1590 አካባቢ ጀምሮ እስከ 1624 ድረስ በአራቱ የጎንደር አጼ ነገሥታት ሠርፀ ድንግል፥ ያዕቆብ፥ ዘድንግልና ሱስንዮስ ላይ ታላቁንና የመጨረሻውን የሰሜን/ፈላሻ አመፅ ለሦስት አሥርታት ያካሂዳል።[118]

የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ውድቀት

የ1603-1632 የሃይማኖት ጦርነት

የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ተግባር በኢትዮጵያ

በ1597 አጼ ሠርፀድንግል በሩቅ ምዕራብ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝና በአናርያ መካከል በሚገኘው የዳሞት አገር በፍለሳ ጦርነት በሚንቀሳቀሰው የሚጫ አሮሞ ጎሳ ላይ የቅጣትና የዘረፋ ዘመቻ እያካሄደ እያለ መርዛማ ዓሣ በልቶ በድንገት ሲሞት በቤተ መንግሥቱ በሰባት ዓመት ልጁ ያዕቆብ፥ በወንድሙ ጎልማሳ ልጅ ዘድንግል ልሳነክርስቶስና በአጎቱ ልጅ ሱስንዮስ ፋሲል መካከል ከ1597 እስከ 1607 ድረስ ለአሥር ዓመታት የሚቆይ ረጅም የሥልጣን ጦርነት ተቀሰቀሰ።

የጦርነቱና የዘመኑ አንቀሳቃሽ የውስጥና የውጭ መሪ

[115] Hess, "Falasha History", p. 116.

[116] Conti Rossini, Sarsa Dengel, p. 123.

[117] Hess, 'Falasha History", p. 116,

[118] ተክለ ሥላሴ (ጸሐፊ ተዕዝዝ)፥ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605-1632 ያልታተመ ዜና መዋዕል፥ በብሄራዊ ቤተ መጽሐፍት፥ አዲስ አበባ) ም. 43፥ 73።

ተዋንያን[119] (1) በሦስቱ ታላላቅ የጦር አበጋዞች ራስ አጥናቴዎስ፥ ራስ ክፍለዋህድና ራስ ዘሥላሴ የሚመሩ የሚቹ የአጼ ሠርፀድንግል ቁርባን፥ አቴትዝር፥ ጨረቃ፥ ጊዮርጊስ ኃይሌ፥ ቱርክ፥ ኑፍጥ (ናራ)፥ አፍሮአይገባ፥ ኮከብ የተባሉ ኃይለኛ የጦር ድርጅቶችና ሹማምንቶች፥ (2) «እሥራኤላውያን» ተብለው የሚጠሩና በሻሸን አምባ ሙት የሚኖሩ የአማራ መሳፍንት፥ (3) በሸሜን ኢትዮጵያ የአማራ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የትግሬ ደጋአምባ አገሮችንና ሕዝቦችን ለመያዝ ወይም አልፎ ለመሄድ በፍለሳና በሰፈራ አንትስቃሴ ከምስራቅ፥ ከደቡብና ከምዕራብ ኢትዮጵያ የዘውትር ጦርነት የሚካሄዱ የከረዩ፥ የወሎ፥ የቱለማና የሚጫ አሮሞ ጎሳዎች፥ (4) ኢየሱሳውያን የተባሉ የእስፓኝ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን፥ (5) በዳግማዊ «ጌዴኦን» ማለትም «በሰሙት አምባው ጌዴኦን» መሪነት በሻሸን አምባ ላይ «እሥራኤላውያን» የተሰኙ የአማራ መሳፍንትን ከነናቸው አሰልፈው አዲሱን የጎንደር መንግሥት ለማጥፋት የሚዋጉ ሰሜን/ፈላሾች ነበሩ።

በዚህ ረገድና ተግባር በ1597 አጼ ሠርፀድንግል እንደሞተ በሚቹ ንጉሥ አማች በራስ አጥናቴዎስ የሚመራውና አገሩን የሚጠላው የሶስት ራሶች ጁንታ ከሦስቱ የዘውድ ባላንጣ ልዑላን ጎልማሳ ዘድንግልን አስሮ በራሱ ቁጥጥር ሥር ሕፃን ያዕቆብን አነገሠ። ሱስንዮስ ግን የነገሥታትን ሹም ሽር ከሚያደርገው የራሶች ጁንታ እጅ በሽሽት አምልጦ ወደ አጎራባቹ የኦሮሞ ወዳጆቹ ሄደ።

ከዚህ አኳያ የአጼ ልብነድንግል የልጅ ልጅ ሱስንዮስ ፋሲል በ1565 ገደማ ተወለደ። በ1580 አካባቢ በምርኮ ተወስዶ አንድ ቦኩ ለተባለ የቦረና አሮሞ የጉዲፈቻ ልጅ ተደረገ። በምርኮ ዘመኑ ሱስንዮስ የአሮሞን ቋንቋ፥ የገዳን ሥርዓት፥ የሉባን የጦር ድርጅትና ሥልት አጠናቅቆ አወቀ። እንዲሁም በ1586 ገደማ በአሮሞና በአማራ ምርኮኞች ልውውጥ ወደ ሠርፀድንግል ቤተ መንግሥት ከተመለሰ[120] በኋላ ሱስንዮስ የመንግሥትና የቤተ መንግሥት ወግ፥ አሠራርና ሥርዓት ጨምሮ ተማረ።

ከላይ እንደተመለከተው፥ በ1597 አጼ ሠርፀድንግል ሲሞት ባልጋወራሾቹና በጦር አበጋዞቹ መካከል የሥልጣንና የእርስ በርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ራስ ዘሥላሴ፥ ራስ አትናቴዎስ፥ ራስ ክፍለዋህድ፥ ዮልየስ፥ የኑኤል፥ ክፍሎም፥ ተክለ ጊዮርጊስ፥ ሠርፀ ክርስቶስ ...የተባሉ የዘመኑና የሥርዓቱ ከፍተኛ የጦር አበጋዞችና አገረገዥዎች

[119] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ይህ በ98 ምዕራፍ በተክለ ሥላሴ የተጻፈው ታላቅ መጽሐፍ ሁለተኛው አስፈላጊና ዋናው የዘመኑ ታሪክ ምንጭ ነው።

[120] Bahrey, History of The Galla, p. 121.

ከላይ የተጠቀሱ የጦር ድርጅቶችን ይዘው ከ1597 እስከ 1607 ድረስ በአንድ አሥርት ዘመን ውስጥ በዙፋን ላይ ሦስቱን የጎንደር አጼ ነገሥታት ያዕቆብን ዘድንግልንና ሱስንዮስን ሹም ሽር አደረጉ።[121]

በዚህ ወቅት ከ1597 እስከ 1603 ድረስ ገዥው የራሶች ጁንታ ሐፂን ያዕቆብን አነገሠ። ከ1603 እስከ 1604 ድረስ ደግሞ ያዕቆብን ሻረና ጎልማሳ ዘድንግልን ኮሸቱ አምጥቶ አነገሠ። በ1605-1607 ዘድንግልን ሽሮና ገድሎ ያዕቆብን ለሁለተኛ ጊዜ አነገሠ። በዚሁ ዓመት የጦር አበጋዞቹ አለቃ ራስ አትናቴዎስ የኦሮሞ ወታደሮችንና ተከታዮችን ይዞ በሽፍትነት የሚኖረውን ሱስንዮስን በራሱ ውሳኔ አነገሠ። በመሆኑ ከ1605 እስከ 1607 ድረስ አጼ ያዕቆብና አጼ ሱስንዮስ በአንድ ጊዜ በአንድ የኢትዮጵያ አገርና ሕዝብ ላይ ሁለት ባላንጣ አጼዎች ሆኑ።

በመጨረሻ በመጋቢት 10 ቀን 1607 በጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረዘይት በተሰኘ ሥፍራ ጎል በተባለ ተራራ ሥር በተካሄደ ጦርነት አጼ ሱስንዮስ 400 የኦሮሞ ወታደሮቹን ይዞ የአጼ ያዕቆብን ግዙፍ ሠራዊት ደመሰሰ። በጦርነቱ ሁለቱም አጼ ያዕቆብና ግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ ተገደሉ። በመሆኑም አጼ ሱስንዮስ የጎንደር መንግሥት ብቸኛው መሪና አዝማች ሆነ።

በዘመኑ በጎንደር መንግሥት የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርት እና ተግባር በሚመለከት፥ በ17ኛው ምዕተ ዓመት በመጀመሪያ ሦስት አሥርታት ውስጥ የእስፓኝ ኢየሱሳውያንን ዘመናዊ ትምህርት፥ የሙያ ጥበብ፥ አዲስ የቤት፥ የከተማ፥ የመንገድና የድልድይ ሥራዎችን በማየት የኢትዮጵያ ሦስቱ ነገሥታት ያዕቆብ፥ ዘድንግልና ሱስንዮስ በየበኩላቸውና በየዘመናቸው በባላንጣዎቻቸው ላይ ዘውዳዊ ሥልጣናቸውን የበለጠ ለማጠናከር በሚሲዮናውያኑ አማካይነት ከአውሮፓ ዘመናዊ የጦር መሥሪያ፥ የዕደጥበብ ሙያ፥ የዕድገትና የለውጥ ሀሳቦችን ፈላጊዎች መስለው ቀረቡ።

በሌላ በኩል ማዕከላዊ ጠንካራ የዘውድ ሥርዓት በእኦርሱ ላይ አፍራሽ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተፅእኖ የሚያስከትል ኃይል እንደ ሚሆን በመገመት የጦርና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ጴጥሮስና ስምኦን በተባሉ ግብፃውያን አቡኖች መሪነት የተጠቀሰውን የሚሲዮን ትምህርት "የጸረማርያሞች" ሃይማኖት ነው በሚል ስብከት በነገሥታቱ ላይ የዝሪዎችን፥ የቄሶችንና የወታደሮችን አጠቃላይ አመፅ ቀሰቀሱ።

በዚህ ሁኔታና ተግባር ከ1603 እስከ 1622 ድረስ በኢትዮጵያና በአካባቢው አገሮች የግዕዝ፥ የአማርኛ፥ የአረብኛና የቱርክ ቋንቋ ምችን በሚናገር በሙያው አስተማሪ፥ ሰባኪ፥ ግምበኛና አናጢ በሆነ

[121] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 1-21።

በአንድ አዋቂ ሚሲዮናዊ ቄስ ፔትሮ ፖያዝ (1564-1622) መሪነት የእስፓኝ ኢየሱሳውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ለሦስቱ አጼ ነገሥታት ያዕቆብ (1603)፥ ዘድንግል (1604) እና ሱስንዮን (1605-1632) ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ገብታችሁ ለሮማው ፖፖና ለእስፓኝ ንጉሥ ታዛዥ ተከታዮች ብትሆኑ በአገራችሁ የሥልጣንና የሹመት ጠላት የሆኑ የአካባቢ ጦር አበጋዞችንና የኦሮሞ ሰፋሪዎችን ለማስገበርና ለመሾመት ከእስፓኝ መንግሥት ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን እርዳታ ለማግኘት ትችላላችሁ ብለው ስለደለሉዋቸው ሦስቱም የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ ነገሥታት ከላይ እንደተጠቀሰው ወደ ሮማው ካቶሊክ ሃይማኖት ተለወጡ።[122]

በመጨረሻ በእስፓኝ ኢየሱሳውያን ትምህርትና ግፊት፥ አጼ ሱስንዮስ ሁለቱንም የሰሜን/ፈላሻ ኦሪትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖቶችን በአዋጅ ሰረዛቸው።[123] ሥርዓተ ሰንበትንም ሻረው። በዚህ ተግባሩም አጼ ሱስንዮስ በአንድ በኩል የሰሜን/ፈላሻ መንግሥትን ደመሰሰ። በሌላ በኩል ደግሞ በራሱና በመንግሥቱም ላይ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ገበሬዎችንና ቄሶችን የ1616-1632 የአመፅ ጦርነት ቀሰቀሰ።[124]

የ1609-1624 የዳግማዊ ጌዴኦን አመፅና የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ፍፃሜ

በ17ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አሥርታት የኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥት፥ ሃይማኖትና ጦር መሪዎች ከጉተከታዮቻቸው በሥልጣን፥ በሃይማኖትና በእርስ በርስ ጦርነቶች በሚገዳደሉበት ዘመን አጎራባቹ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በሰንሰት አምባው ዳግማዊ ጌዴኦን መሪነት በተጠቀሱ የክርስቲያን ኃይሎች ላይ ጎና የፈራሱን የነፃነት ትግል በማካሄድ ላይ ነበር።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ የአጼ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ተክለ ሥላሴ በዝርዝር እንደዘገበው፥[125] ከ1587 የወርቅ አምባ ጦርነት በኋላ፥ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በሰንሰት አምባው ዳግማዊ ጌዴኦን መሪነት፥ በ1594-1624 በአራቱ የጎንደር ነገሥታት ሠርፀ ድንግል፥ ያዕቅብ፥ ዘድንግልና ሱስንዮስ ላይ በሰሜን፥ በወገራ፥ በፀለምት፥ በአበርገሌና በበጌምድር ቆላዎችና አምባዎች የመጨረሻ

[122] Getahun Delibo, "Early Portuguese Imperialism in Ethiopia, 1490-1632: Origins, Responses, and Consequences", MA. Thesis (Howard University, 1971).
[123] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 44 ፋ. 62።
[124] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 62-98።
[125] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 33፥ 43፥ 68-73።

አመፅ ጦርነት ሲካሄድ ኖረ። በዚህ የነፃነት ጦርነት ሂደት ዳግማዊ ጌዴዎን በ1609፥ በ1613-1623 እና በ1623-1624 በአጼ ሱስንዮስ መንግሥትና ጦር ላይ በተከታታይ ተከላይ (አምዶ)፥ ክፍለማርያምና የአርዘ ልጅ የተባሉ የዘውድ ባላንጣ «እሥራኤላውያን» የአመፅ ኃይሎችንና እንቅስቃሴዎችን በማደራጀትና በመምራት፥ በ1624 እስኪገደል ድረስ፥ ለአዲሱ የነጋደር መንግሥትና ነባሥታት ታላቅ የሰላምና የፀጥታ ችግር እንደጅጠረ በተጠቀሰው ዜና መዋዕል በሥፍራና በጊዜ ተገልጿል።

በመሆኑም በ1616 አጼ ሱስንዮስ ቀደም ብሎ በሰሜን/ፈላሻ አገር ላይ የሾማቸው አገረ ገዥዎችና የጦር አበጋዞች በጣና ሐይቅና በተከዜ ወንዝ መካከል በየክፍለ ግዛታቸው የሚኖሩ ፈላሻዎችን የጸታ፥ የዕድሜና የሙያ ምርጫና ልዩነት ሳያደርጉ በሙሉ እንዲገሏቸው አዘዘ። ራሱም ንጉሡ የፈላሻ ሴቶችንና ልጆችን ባሮቹ አደረጋቸው። ሰወደደውም ሰጣቸው። እንዲሁም ንጉሡ በደምቢያ በነገሠበት አገር የሚኖሩ ፈላሾች ወደ ክርስትና እንዲገቡ ወይም በሙሉ እንዲገደሉ አዘዘ። የአይሁድን የኦሪት ሃይማኖት ለመከዳቸው ማስረጃ እንዲሆን በቅዳሚት ስንበት ቀን ሥራ እንዲሠሩበት፥ እንዲያርሱበት በአዋጅ አስገደዳቸው። ፈላሾቹም ከገፀምድር በሞት ከመጥፋት ይልቅ በንጉሡ ሕግ መሠረት በክርስትና መጠመቅ ጀመሩ።[126]

የጦርነቱ ታሪካዊ መነሻና ውጤት

አጼ ሱስንዮስ ኢየሱሳውያን በተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ግፊት በ1616 የሰሜን/ፈላሻ ጥንታዊ መንግሥትና የኦሪት ሃይማኖት ከደመሰሰ በኋላ በተጨማሪ በ1620-1622 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የቅዳሚት ስንበት ከረቡዕና ከአርብ ጾም ጋር በአዋጅ ሽሮ ራሱም በመጋቢት 1622 በይፋ ካቶሊክ ሆነ። የሽረት አዋጁንም በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ በኃይል ተግባራዊ ያደርግ ዘንድ ካቶሊክ ወንድሙን ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስን ከ7000 ወታደሮች ጋር ወደ ዳሞት ከፍለ ሀገር ላከ። ሕዝቡም ሕጉን በትጥቅ አመፅ በመቃወሙ በኦሪት ሃይማኖት ጥያቄ በኢትዮጵያ ክርስቲያን ሕዝብና መንግሥት መካከል የመጀመሪያው የሃይማኖት ጦርነት ተቀሰቀሰ።

የዘመኑን የሕዝብ እምነትና አመለካከት የአመፁንም ዓይነትና ስፋት የጦርነቱንም ሥልትና ውጤት በግልፅ የሚያሳይ አንድ ልዩ ታሪካዊ ሰነድ ስለሆነ የ1621 የዳሞት ጦርነት ዘገባ በጸሐፌ ትእዛዝ

[126] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 44።

ተክለ ሥላሴ እንደበት እንደሚከተለው ቀርቧል።

የአይሁድን ሰንበት ከረቡዕና ከዓርብ ጾም ጋር የሚሽር ሕግ አውጥቶ ሕጉንም እንዲያስፈጽም ራስ ሥዕለክርስቶስን ወደ ዳሞት ላከ። ራስ ሥዕለክርስቶስም ንጉሡ በአይሁድ ሰንበት ቀን ሥራ እንዲሠራበት ሕግ ማውጣቱን ለዳሞት ሰዎች ነገራቸው። የዳሞት ሰዎች ግን አዋጁን ሰሙተው የአይሁድ ሰንበት አይሻርም አሉ። ማን ሰው ነው ደፍሮ የሚሽረው በማለት ተቃወሙ። የድፍረት ቃልም ጨምረው አሰሙ። ራስ ሥዕለክርስቶስ በበኩሉ ለንጉሡ ሕግ ይታዘዙ ዘንድ አንድ የመልእክተኞች ቡድን ቢልክላቸውም እነርሱ ግን በድፍረት ተነሣሥተው በሰልፍ ወደ በርበሬ ሣፍና ለረንዝ ወጡ። በተጨማሪም የደልግ፥ የሰናና የእርብዝና የነጻም ሰዎች ጊዮርጊስ ኃይሌ ከተባሉ ጨዋዎች ጋር በንጉሡ ጦር ላይ ከዳሞት ሕዝብ ጎን ተሰለፉ። ከራስ ሥዕለ ክርስቶስ ሉሊያችም ጭምሮቹ ከዳሞት ሰዎች ወገን ሆኑ። የኪላና የሕሣጭ ጭፍሮች ብቻ አልደገፉአቸውም። ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ከራስ ሥዕለክርስቶስ ሠፈር ይልቅ በሕዝቡ ወገን በለረንዝ ተሰለፉ። ራስ ሥዕለክርስቶስ ሐመኖሚት በተባለው ቦታ ከሰፈረበት ለዳሞት ሰዎች «ለንጉሡ ሕግ ታዘዙ፥ የአይሁድን ሰንበት ሻሩ»፥ ብሎ አሁንም መልዕክተኞች ላከባቸው።

እነርሱም ለራስ ሥዕለክርስቶስ በሰጡት መልስ፥ ንጉሡ በእውነትም የአይሁድን ሰንበት ሻሩ ብሎ ማዘዙን ራሳችን ሂደን እንጠይቀው ዘንድ አንተ ግን መንገዱን ልቀቅልን ብለው ጠየቁት።

እሱም ይሆን ብሎ ከሐመኖሚት ተነሳ። በኤዳውሬ ሰፈረ። ከኤዳውሬ ተነስቶ በእንዞንድም ሰፈረ። ከዚያም አዛዥ አመሃኑ፥ አዛዥ ምርጫን፥ የጸሐፊላም ሠርጸን ልጅ ገብረ ክርስቶስንና ወፍር አጽቆን ከሁለት የንጉሡ ሉሊዎችና አዳምና ወርጡ ከተባሉ ሁለት የየሀብታ ሰዎች ጋር ላከባቸው። በላከው መልእክት በቂስ እያተገዘታችሁ እኔን ለመግደል የምትተባበሩ ምን ሰለ አደረኩአችሁ ነው። ተዉ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ። በንጉሡ ሕግ መሠረትም የአይሁድን ሰንበት ሻሩ። እኔንም ሰለ በደላችሁኝ ካሣ ሰጡኝ። ከእናንተ ጋር ያሉ ሉሊዎቼንም መልሳችሁ ላኩልኝ። እምቢ ብትሉ ግን ሰግይ ይሰግችሁ። ምድርም ታድምጣችሁ። እሜአብዝር ይፍረድ። ሴት ልጅ ሳይለዩ በሚገድሉ የየሀብታና የወረንጪኖ ሰዎች እንዳያገኙአችሁ። ተጠንቀቁ። በእኔና በእናንተ መካከል በተፈጠረው ጠብ ምክንያት ለሚፈሰው ደም ተጠያቂዎች እናንተ ናችሁ አለ።

የዳሞት ወታደሮች ግን ይህንን ከመልእክተኞች ሰምተው የበለጠ ለጦርነት ተነሣሡ። የተከታዮቻቸውን ብዛትና፥ አንድነትና ጥንካሬ በማየት በሠላቸው ጸኑ ትምክህት አዘሉ። ለራስ ሥዕለክርስቶስ በላኩት መልስ የቅዳሚት ስንበት እናከብራለን አንሽርም። ከእኛ ዘንድ የተማጸኑ ሉሊዎችንም አሳልፈን አንሰጥም ለአንተም በእኛ ላይ ምንም ካሣ የለብንም አሉ።

ራስ ሥዕለክርስቶስም ይህንን የድፍረት ቃል ከመልእክተኞቹ አፍ ሰምቶ ከእንዞንድም ተነሳ። በአረፋ የሚኖሩትን የዳሞት ሰዎች ወጋ። ላሞቻቸውንም በምርኮ ወሰደ። ቤቶቻቸውንም አቃጠለ። መሐሳት ዊምር ከአመጸኞች ጋር ከተባበሩ

ሰዎች ብዙዎቹ ተገደሉ። የአረፋን ሰዎች ከወጋ በኋላ ራስ ሥዕለክርስቶስ በየሰንበት ዝያ ሰፈረ።

በማግሥቱ ሰኞ ሰምን በስንቱ ትጠሉኛላችሁ። ከድተው ወደ እናንተ የሄዱ ሉሊዎቼን ላኩልኝ። ስለ በደላችሁኝ ካሉኝ። በንጉሥ አዋጅ መሠረት የአይሁድን ሰንበት ሻሩ በማለት ወደ ዳሞት ሰዎች በፊት የላክላቸውን አስታራቂዎች እንደገና መልሶ ላከላቸው። መልእክተኞቹም የዳሞት ሰዎች ተሰልፈው በሚገኙበት ሥፍራ ሄደው ነገሩአቸው። ሰዎቹም የራስ ሥዕለክርስቶስን መልእክት እንደገና ሰምተው እርሱ እርቅና ሰላም ከፈለገ ሰንበትን የሚሽረውን ሕግ ያንሳ። አባቶቻችንና እኛም ለብዙ ዘመናት ስናከብረው የኖረውን ሰንበት አንሽርም። ከእኛ ዘንድ የተማሩኑ ሉሊዎችንም አሳልፈን አንሰጠውም የሚል መልስ ሰጡ።

ራስ ሥዕለክርስቶስና አማካሪዎቹ ይህን መልስ ሰምተው የጦርነት ነገር ሲመክሩ አደሩ። በማግሥቱ ማክሰኞ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ በግለኛ ተነሱ። ሞፍርቹንም በየሥፍራቸው አሰለፉ። ለጦርነት ምቹ የሆነ ሰፍራ ያዘ። የዳሞት ወታደሮች ከብዙ የጎጃም ሠራዊት ጋር በሁለት የኢገሪኖና በአንድ የፈረሰኛ ሞባሮች ማለትም በሶስት ክፍሎች ተሰለፉ። የራስ ሥዕለ ክርስቶስ ሠራዊት የሚያልፍበትን መንገድ ዘጉ። ራስ ሥዕለ ክርስቶስ በቀስትና በሽጥ ለመዋጋት የሚያመች ቦታ ይዞ በማግሥቱ ውጊያ ለማደረግ በጠላት ሞባር ፊታውራሪ ሞፍራ አስቀመጠ። ነገር ግን የዳሞት ጦር ቀድሞ ውጊያውን ጀመረ።

ውጊያውን በጀመሩ ጊዜ ራስ ሥዕለክርስቶስ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ፊት በጉልበቱ ተንበርክኩ ሰገደ። ጌታዬ ሆይ በመንፈል እንደተጻፈው አንተን በእውነተኛ መንገድ በትክክል የማላምንህ ከሆነ ሰውነቴን ለእዚህ ጠላቶቼ ስጥ። በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት አንተን በትክክል በእውነተኛ መንገድ የማመልክህ ከሆነ ግን በስንቱ የሚጠሉኝን እዝህን ወንጀለኞች ስጠኝ አለ።

እንዲሁም በውሸት እንደሚጠረጥሩኝ ልጅሽን በእውነት የማላመልክው ከሆነ ለእዝህ ጠላቶቼ ራሴን ሰጥአቸው። በእውነት የማልወድሽ ከሆነ ልጅሽንም በትክክል የማላመልክው ከሆነ ሃይማኖቴም የቀና ካልሆነ ስለ ክብሬ ቀንተው ለሚጠሉኝ ለእዝህ ጠላቶቼ ራሴን ሰጥአቸው። ብሎ ወደ አመቤታችን ወደ እግዚአትነግርያም ጸለየ።

እንደዚህ ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ በፈረሱ ላይ ወጣ። ከፈረሰኛው ጋር የጦሩን አኩሌታ በደጃዝማች ቡሀ መሪነት ወደ ፊት ላከ። እርሱም ሕናጭ ከሚባለው የምርጥ ወታደሮች ሞፍራ ጋር ወደ እግረኛው ሞፍራ ሄደ። ጠላቶቹ ከፊቱ አልቆሙም። ሰራስ ሥዕለክርስቶስ ሠራዊት ጀርባቸውን ሰጡ። ብዙዎቹ ሞቱ። እንደደረቅ ቅጠል ረገፉ። በባሕር ላይ እንደረገፈ አንበጣ ረገፉ። የራስ ሥዕለክርስቶስ ሠራዊት እስከ ያምና እስከ ደብረጊዮርጊስ እስከ ብር ወንዝና እስከ ዘንደአምባ ድረስ ገደላቸው። ላሞቻቸውንም ፈረሶቻቸውንም በምርኮ ወሰደ። በዚያን ቃን ከራስ ሥዕለክርስቶስ ሠራዊት የጋላና የአማራ ወታደሮች አሥርቱ አምስት፥ ሀለት ያልገደለ ያልሰለበ የፈረሰና የላም ምርኮ ያልወሰደ አልነበረም።

ንጉሡም መሳለባቸውን ሰምቶ አዛዥ አሳናን፥ አዛዥ ጢናን፥ አዛዥ ሰንቡልን ያስታርቋቸው ዘንድ ላከ። እነርሱም ሄደው አስታረቁ። ያን ጊዜ ንጉሥ ነገሥቱ ሥልጣን ሰገደ በራስ

ሥዕለክርስቶስ ከተማ በሎዶቅያ የተሰበሰቡ ሰዎችን ሉዲስ ቆጸላትን እንዲያወጡ አዘዘ። የቅዳሚት ሰንበትን ያልሻረ ሁሉ ገንዘቡ ይወረሰ፥ ቤቱም ይቃርበር ብሎ አዋጅ አስነገረ።[127]

በኢየሱሳውያን ዘገባ መሠረት በታላቁ የሰንበት ጦርነት በሕዝቡ ወገን የተሰለፉ 14,000 የእገሬው ሕዝብና 400 ቄሶች ሲሆኑ የመንግሥቱ ወታደሮች ብዛት ደግሞ 7,000 ነበር። በመንግሥቱ ጦር ከተገደሉት መካከል 118 መኳሳት ነበሩ።[128]

በዚህ የሰንበት ጦርነት በአመፀኛው ሕዝብ ላይ ድል ከተጎናፀፈ በኋላ አጼ ሱስንዮስ በመጋቢት 1622 በቄስ ፔትሮ ፓዮዝ እጅ በይፋ በካቶሊክ ሃይማኖት ተጠመቀ። በማንቦት 23 ቀን 1622 ቄስ ፔትሮ ፓዮዝ ሞተ። በምትኩ በእስፓኝ ንጉሥና በሮማው ፓፓ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ተደርጎ የተላከው የእስፓኝ ተወላጅ አልፎንሶ መንዴዝ ከአሥራ ዘጠኝ ተከታዮቹ ጋር በ1625 በቤይሉል በር ወደ ኢትዮጵያ ደረሰ።

በየካቲት 11 ቀን 1626፥ አጼ ሱስንዮስ አልጋወራሽ ፋሲለደስንና ወንድሞቹን ጨምሮ በጎርጎራ ቤተ መንግሥት የእገሩ ከፍተኛ የመንግሥትና የሃይማኖት ባለሥልጣናች በተቀመጡበት ታሪካዊ ንግግሩ በፓትሪያርክ አልፎንሶ መንዴዝ በኢትዮጵያ የሮማው ፓፓ እንደራሴ ፊት በጉልበቱ ተንበርክኩ በራሱ፥ በመንግሥቱና በሕዝቡ ሁሉ የሮማ ፓፓውን መንፈሳዊ በላይነት በመቀበል የመሀላ ሥነ ሥርዓት ፈጸመ። ከንጉሡ ቀጥለው ልጁ ፋሲለደስ፥ ወንድሞቹ፥ ቀኽፍለ ሀገር እንደራሴዎች፥ መኳንንቶች፥ ካህናትና መነኮሳት በሙሉ እንዲሁም የሮማ ፓፓውን ሃይማኖታዊ በላይነትና መንፈሳዊ አመራር በመቀበል የታማኝነት ቃል ገቡ።

በዚህ ወቅትና ሁኔታ አጼ ሱስንዮስ ከ330 ጀምሮ እስከ 1626 ድረስ ለ1290 ዓመታት የመንግስቱ ሃይማኖት የነበረውን የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት በይፋ ሻረው። ፓትሪያርክ አልፎንሶ መንዴዝ ቀጥሎ በግብፁ አቡን ይመራ የነበረውን የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ትምህርት፥ ጸምና በዓላት በሙሉ አገደ። ካህናትና መኳሳትም በአዲሱ የካቶሊክ እምነትና ትምህርት መሠረት እንደገና እንዲጠመቁ ታዘዙ። በአገሩ የቀድሞ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሀብት በኢየሱሳውያን አስተዳዳሪነት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ እንዲሆን ተደረገ። በጎጃም፥ በደምቢያ፥ በዛጌምድርና በትግራይ በ21 ኢየሱሳውያን ቄሶች መሪነት 13 የእምነት፥ የትምህርትና የሥራ ማዕከላት ተመሠረቱ።

---

[127] ተክለ ሥላሴ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 63 ቁ. 273 275።

[128] Getahun Dilebo "The Portuguese in Ethiopia", p, 135.73

ከ1626 እስከ 1632 ድረስ ቢፖትርያርክ አልፎንሶ መንዴዝ ሥር ኑቀል ፖሊሲና የተሻሸ እርምጃዎች ሥልጣናቸውንና የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን የተነጠቁ የኢትዮጵያ የመንግሥት ባለሥልጣናች፥ የክፍለ ሀገር እንደራሴዎች የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን በኢየሱሳውያንና በንጉሡና በራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ ላይ በየአካባቢያቸው በአመፅ እንቅስቃሴ ተነሱ። በዚህ ታላቅ የመከራና የስቃይ ዘመን በንጉሡ፥ በራስ ቢትወደድ ወንድሙና በአልጋ ወራሽ ልጁ መካከል ብርቱ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። በተጨማሪም በየክፍለ ሀገሩ የንጉሡ እንደራሴዎችና የአካባቢው መሳፍንቶች በተለመደው የሥልጣን አመፅና ጦርነት ተነሱ። ባጭሩ በኢትዮጵያ ካቶሊኮችና እርቶዶክሶች መካከል ታላቅ የፖለቲካ ሽብርና የእርስ በርስ መገዳደል ዘመንና ሥርዓት ተጀመረ።

የ1629-1632 የአገው አመፅና የኢትዮጵያ የካቶሊክ መንግሥት ውድቀት

የመንግሥትን መሳሪ ሥልጣን ከጦር ጋር በእጁ የያዘው የኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተ መንግሥትና ኢየሱሳውያን የተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን እንጂ በ1629-1632 በላስታ-ዋግ ተራሮች በአገው ጦረኛ መስፍን መልክአ ክርስቶስ የተመራውን ሁለአቀፍ የአካባቢ መሳፍን ቶችን፥ የጦር አበጋዞችን፥ የቄሶችንና የገዘራዎችን ሕዝባዊና ብሔራዊ ፀረ-ካቶሊክ አመፅ መቆጣጠርና መግታት አቃታቸው። ይህ ጹሑፉ በሌላ ሥፍራና ሥራው በጥቅል እንዳስቀ መጠው፥[129]

በዚህ ሁኔታ በአንድ በኩል በቤተ መንግሥት በአሰንዮስ ወንድሞችና ልጆች መካከል ከፍተኛ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ አጠራር በጹሐፌ ትእዛዝ ተከለ ሥላሴ «ቦለድ» (ጅንደር) ወይም ወግበዴ ተብሎ የሚጠራው መልክአ ክርስቶስ የአገው አመፅ መሪ ራሱን እንደንጉሥ በመቁጠር የባለሥልጣናች ሹምሽር ማድረግ ጀመረ። ከንጉሡ በታች የካቶሊክ ሃይማኖትና የኢየሱሳውያን ዋናው ተከታይና ደጋፊ ስለነበር በጠረፍው ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ ላይ ብዙ ተቃዋሚዎች ተነሱ። በተለይም በራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስና በአልጋ ወራሹ ፋሲለደስ መካከል ብርቱ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። አልጋወራሹ የአባቱ እንደራሴ ሆኖ ዘመቻ ሲመራ ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ የአልጋወራሹን አመራር መቀበል እምቢ አለ። በመሆኑም ንጉሡ ራስ ቢትወደዱን ከነጸጸም ሹመት አወረደ። ሀብቱንና ጦሩን በከፊል ለአልጋወራሹ ፋሲለደስ ሰጠ። የአገው አመፅ ደግሞ በጎጊዘው እየተጠናከረ ሄደ። በዚህ ሁኔታና ወቅት አዲሱን የካቶሊክ ሃይማኖት ሰርዝ ጥንታዊውን የእርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መልሶ እንዲያደስ በንጉሡ ላይ ከአማካሪዎቹ፥

[129] ላእሶ ጌ. ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ፥ ገጽ 232-234፥ 237።

ከባላሥልጣኖቹና ከጦሩ ግፊት እየበዛ ሄደ።

በዚህ ሁኔታ በጥቅምት 1632 ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ ከ20,000 ወታደሮች ጋር ከባሉዱ መልክአ ክርስቶስ ጋር በምባር ተጋጥሞ በሽንፈት ተመለሰ። ከዚያ በኋላ ንጉሡ በራሱ አመራር የአርሞ ወታደሮች አደራጅቶ ከደምቢያ ወደ ላስታ በመዝመት በሰኔ 2 ቀን 1632 በድንገት ከተራራው ወርዶ በሜዳ ላይ ውጊያ በገጠመው የመልክአ ክርስቶስ ጦር ላይ ብርቱ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ በመውሰድ 8,000 ሰዎችን ገደለ። ቢሆንም መልክአ ክርስቶስ ሸሽቶ በሕይወቱ አመለጠ።

ከዚህ የመጨረሻ ድል በኋላ በሰኔ 25 ቀን 1632 አጼ ሱስንዮስ የእርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በአዋጅ አድሶ ራሱ በመስከረም 7 ቀን 1632 በካቶሊክ ሃይማኖቱ እንደጸና በ61 ዓመቱ ሞተ። ነገር ግን ልጁና ተከታዩ አጼ ፋሲለደስ የካቶሊክ እምነቱን ክዶ ወደ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተመለሰ። ኢየሱሳውያንንም በ1633 ከአገር አስወጣ። ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስን ጨምሮ ብዙ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ባለሥልጣኖችንና ምዕመናንን በሞት ቀጣቸው። በመጨረሻም አጼ ፋሲለደስ አውሮፓውያንና ሥልጣኔ አቸው ሁለተኛ ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ የመገቢያ በሩን እንዲዘጉ ባቸው በቀይ ባሕር ላይ ከእስላማዊ የቱርክ ባለሥልጣኖች ጋር ስምምነት አደረገ።

የቤተ እሥራኤል/ፈላሻ ሥቃይና የስደት ፍጻሜ

በስሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል በሚገኘው አገሩ ላይ በመሬቱ፥ በሃጥቱ፥ በመብቱ ጥያቄ በ15ኛው ምዕተ ዓመት ከአጼ ይስሐቅ (1414-29) ጋር ከተዋጋ ወዲህ ከፖለቲካና ከመሬት ጠላቶቹ «ፈላሻ» ማለትም ስደተኛ፥ መጤ፥ ባዕድ፥ የሚል ስም የተሰጠውና ከጊዜ በኋላ እርሱ ራሱን «አይሁድ» እና «ቤተ እሥራኤል» ነኝ ብሎ በሁለት ተለዋጭ የይሁዳውያኑ ስሞች መጠራት የጀመረው፥ ነገር ግን በአካባቢው በጥንቱ ዘመን ጊና የክርስትና ሃይማኖት በ330 ወደ ኢትዮጵያ ከመጣቱ በፊት በግሪክና በግዕዝ ቋንቋዎች በተጻፉ የአክሱም ሰነዶች «ሰሜን» በሚል የሕዝብ፥ የአገርና የመንግሥት ስም የታወቀ ነባርና ሉአላዊ ሰሜን/ፈላሻ በማምት ከ300 እስከ 1632 ድረስ ለ1300 ዓመታት ከአጎራባቹ መንግሥታትና ነገሥታት ጋር ሲዋጋ እንደኖረ ከላይ ተረጋግጧል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በዚህ ረጅም ዘመን ከ320 ገደማ እስከ 1332 ድረስ ለአንድ ሺህ ዓመታት ዘመን ሰሜን/ፈላሻ በምንም ሥፍራና ጊዜ ቢታሪክ ስነድ እንደገና ተጽፎ አልተገኘም። በዚህ ረጅም የሚሊኒየም ዘመን ውስጥ በአንድ በኩል በግሪኮ-ሮማውያን አማካይነት ከይሁዳውያኑ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የገባ

የክርስትና ሃይማኖት በሰሜኑ ደጋአምባ አካባቢ በተለይ በአራቱ ነባር፥ አዋማዊ፥ አጎራባችና ተዛማጅ የአክሱም-ትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦች ዘንድ በሃይማኖትና በባህል ታሪካዊ መስተጋብርና መወራረስ በማስከተሉ አራቱም ማኅበረሰቦች በተዛማጅ የክብረ ነገሥትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት በመካከለኛው ምስራቅ የይሁዳውያኑን ሕዝብ ጥንታዊ ታሪክና ባህል ከአሪት ሃይማኖት ጋር በእምነት ግፊት የራሳቸው አድርገው እንደወሰዱ ይታወሳል። በሌላ በኩል ደግሞ በተጠቀሰው የሚሊኒየም ክፍለ ጊዜ በተለይ በ550-1270 ክፍለ ዘመን በሰሜኑ ደጋአምባ የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀትና «ዛጉዬ». ቸብሎ የሚጠራው የአገው (በዘመኑ የግዕዝ ስያሜ ዘአገው) መንግሥት ክስተትና የዕድገት ሂደት ከታሪክ አኳያ እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል አይታወቅም።

የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ጥንተ ኢትዮጵያዊነት ታሪክ ከፍ ብሎ በየደረጃው ከየሰነዱ በተጻፈው መረጃ መሠረት እንደተጠቀሰው ሆኖ ሳለ እስከ ዛሬ ድረስ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጸሐፊዎች የኢትዮጵያን የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ስምና ታሪክ የሚያሉት[130] (1) በክብረ ነገሥት ትውፊት መሠረት ከክርስትና ሃይማኖት በፊት በኢትዮጵያ የአሪት ሃይማኖት ከይሁዳዊ የፈላሻ ሕዝብ ጋር ነበር የሚለውን ተረት ለማጠናከር፥ (2) ጉዲት የምትባል አንዲት ጨካኝ የፈላሻ ሴት የአክሱምን መንግሥት አጠፋች የሚለውን ክስ ለማስረዳትና፥ (3) የአክሱም መንግሥት በተጠቀሰችው የፈላሻ ሴት ከተደመሰሰ በኋላ በአካባቢው የአገው መንግሥት እንዴት፥ መቼና በማን ተፈጠረ የሚለውን ሌላ የታሪክ ጥያቄ ለመመለስ ሲፈልጉ ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ አሁን ከ1950ዎቹ ወዲህ በጥንቱ የደአማት-አክሱም ታሪካዊ ሥፍራዎች ላይ በተካሄደው ከፍተኛ የአርኪኦሎጂ ጥናት መሠረት አንደኛ፥ በ330 የክርስትና ሃይማኖት በግሪኮ-ሮማውያን አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት በአዋማዊ የደአማት-አክሱም አገርና ቤተ መንግሥት መለኮታዊና አህጉራዊ የአሪት ሃይማኖትና ትምህርት አልነበረም።

ሁለተኛ፥ ሁለቱም የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ከ330 ወዲህ በግሪኮ-ሮማውያን አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በግሪክ-ግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ሚዲያ አማካይነት ነው።

ሦስተኛ፥ ከጊዜና ከታሪክ አኳያ ሲታይ፥ በሰሜኑ ደጋአምባ አካባቢ ሰሜን/ፈላሻ የተባለ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕዝብና መንግሥት

[130] Hess, "Falasha History", pp. 125-126.

ከ550-1270 ክፍለ ዘመን በኋላ የአሪትን ሃይማኖት በግዕዝ ቋንቋ ሚዲያ አማካይነት ከአዲሱ የክብረ ነገሥት መጽሐፍና እምስጣጤዎ ሳውያን ከተባሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መምህራንና ገዳማት እንደተቀበለ ከዘመኑ የታሪክ መረጃና ትምህርት ለማንም አስተዋይ ግለሰብ ግልፅ ነገር ነው።

አራተኛ፥ በ1616-1632 የጦርነት ዘመን የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብን ከአሪት ሃይማኖት ጋር ከአጼ ሱስንዮስና ከኢየሱሳውያን የመጨረሻ ጥፋት ያዳነው ከላይ የተገለፀው የዳሞት፥ የአገው፥ የትግሬና የአማራ ክርስቲያን ሕዝቦች የአመፅ ትግልና ድል ነው። ይህም በዘመኑ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በንሳ፥ በአካባቢ፥ በፖለቲካና በሃይማኖት ልዩነት ምክንያቶች ጠላትነትና ጦርነት ላለመኖሩ አንድ ታሪካዊ ማስረጃና ምሳሌ ነው።

አምስተኛ፥ በ1616-1632 የጦርነት ዘመን አጼ ሱስንዮስ ያሰሜን/ፈላሻን መንግሥት አሸንፎ ሕዝቡን የንጉሡ ባሪያና ገባር ካደረገ በኋላ በተከዜና በዓባይ ወንዞች ክልል የሚገኘው የሕዝቡ ጥንታዊና አስትራቴጂያዊ ምድር ለአዲሱ የጎንደር መንግሥት የኢኮኖሚ መቲረትና የፖለቲካ ማዕከል ሆነ። በመሆኑም በኢትዮጵያ ለዛርው የአማራ ማዋበረሰብ ዕድገት የጥንቱ የሰሜን/ፈላሻ ምድርና ሕዝብ አንድ ታላቅ ምንጭና መሠረት ሆነ።

ስድስተኛ፥ በ1616 አጼ ሱስንዮስ ለሰሜን/ፈላሻ አሪታዊ ሕዝብ በሞትና በክርስትና ሃይማኖት መካከል ያንዱን ምርጫ በሰጠ ጊዜ ብዙዎቹ «በፍጥነት በክርስትና እየተጠመቁ»[131] ሕዝበ-ክርስቲያን እንደሆኑ በንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በተከለ ሥላሴ ተጽፏል። በዚህ በታወቀ የሰለሞናውያኑ የአገዛዝ ሥርዓት ብዙ አሪታዊ ሰሜን/ፈላሾች ስማቸውን ሃይማኖታቸውንና ቋንቋቸውን በመለወጥ ከጊዜ በኋላ ክርስቲያን የጎንደር ሕዝብ ሆኑ። ሌሎች ደግሞ በመሬት በባህልና በሃይማኖት ከአገው፥ ከትግሬና ከአማራ አጎራባችና ተዛማጅ የቋንቋ ማህበረሰቦች ጋር ተቀላቀሉ።

ሰባተኛ፥ የአጼ ሱስንዮስን የ1616 የኃይል ጥምቀት በመቃወም በአሪት ሃይማኖታቸው ጸንተው የቆሙ ሰሜን/ፈላሾች ከመሬታቸው ተነቀሉ። ተጋዙ። እነዚህ አሁን ራሳቸውን «ቤተ እሥራኤል» ብለው የሚጠሩ ንቅል፥ ተፈናቃይ ሰሜን/ፈላሾች በግምት ከ1616 እስከ 1990 ድረስ ለአራት ምዕተ ዓመታት በተወሰኑ መንደሮችና አካባቢዎች በእርሻ፥ በሸክላ፥ በእንጨት፥ በብረት፥ በቆዳና በልብስ ያራዎች

[131] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 44 ቁ. 209።

ተሰግርተው ኖሩ። በመሆኑም በጎብረተሰቡ ዘንድ ጠይብ፥ ቡዳና አስማተኛ ተብለው በስድብ ስም የሚጠሩ የኢትዮጵያ አንድ ልዩ የሃይማኖትና የዕደጥበብ ካስት ማዋበረሰብ ሆኑ።

በመጨረሻ በ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ የኢትዮጵያ ቤተ እሥራኤል/ፈላሾች በሥርዓትና በሃይማኖት ግፊት የጥንቱ አገራችን ወደ ሚሉት ወደ እሥራኤል ፈለሱ።

ይህ ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል የቀረበው የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ረጅም የቁጡዙሁ ዓመታት የመከራና የጦርነት ታሪክ በኢትዮጵያ ዘውዳዊ የሥርዓት ፥ የሕዝቦች መከራ አንድ ምሳልና መግለጫ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር የቅርቡ በ60000 የሚቆጠሩ ቤተ እሥራኤሎች የአገረ እሥራኤል ፍለሳ የኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻ ረጅም ታሪክ ፍጻሜ አይደለም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ልዩ የሕዝቦች፥ የቋንቋዎች፥ የባህሎችና የሃይማኖቶች መስተጋብርና መወራረስ ልምድና ታሪክ መሠረት በተጠቀሰው ረጅም ዘመን ሰሜን/ፈላሾች በመሬት፥ በጊዜ፥ በቋንቋ፥ በደም፥ በባህልና በእምነት በአካባቢው የአገው፥ የአማራና የትግሬ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች አካል ሆኗልና። እቴጌ ምንትዋብ፥ ዳኛች ውቤ፥ አጼ ቴዎድሮስና እቴጌ ጣይቱ የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ታላላቅ የአገርና የመንግሥት መሪዎች የወለደ አንድ የአገሪቱ ነባር ዘርና ሕዝብ ነውና።

4. የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

ከእስልምና በፊት የኢትዮጵያና የአረቦች ታሪካዊ ግንኙነት

የኢትዮጵያና የሮማውያን የፖሊሲ ስምምነት በአረቢያ

በ610-632 በአረቢያ በነቢዩ ሙሐመድ አብደላ የተመራው ታላቁ የአረቦች እስላማዊ አብዮት ታሪካዊ መነሻዎችና ዓለማቀፋዊ ውጤቶች በአካባቢው በሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል ለረጅም ዘመን ከተካሄዱ ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዙ ናቸው።

ከታሪክ እንደሚታወቀው፥ ሮማውያን በ30 ዓመተ ዓለም ግብፅን ለሦስት ምዕተ ዓመታት (332-30) ከገዙት ግሪኮች ያዙ። በዚህ የግሪኮ-ሮማውያን ዓለማቀፋዊ የሽግግር ዘመን በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ሞንታዊ የኑቢያ-ሚሮዌ መንግሥት እንዲሁም በአጎራባቹ አረቢያ ሚና፥ ሳባ፥ ቀጣብን፥ ሃድራማዊ፥ ሂሚያሪትና ሃምዳና የተሰኙ አናሳ የአረብ መንግሥታት በየበኩላቸው በራሳቸው ውስጣዊና አካባቢያዊ ምክንያቶችና ግፊቶች ሁሉም በፈጣን የውድቀት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ነበሩ።[1]

እነዚህ የዘመኑ ታላላቅ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ክስተቶች፥ ሁኔታዎችና ሂደቶች የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕር፥ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ እስትራቴጂያዊ አገሮችን ለሦስቱ የሮም፥ የፋርስና የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥታት ክፍት የማትና የተፅዕኖ አካባቢዎች አደረጉ።[2]

ይሁን እንጂ በአካባቢው ከሦስቱ ተጠቃሽ መንግሥታት፥ በእስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በደጋማው ክልል የሚገኘው የኢትዮጵያውያኑ መንግሥት በተጠቀሱት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ለዓባይ ሸለቆ፥ ለቀይ ባሕርና ለኤደን ባሕረሰላጤ ጠረፍ ንግድ፥ ሰላምና ፀጥታ ዋስትና ለመስጠት ብቃት ያለው ኃይል

[1] Kobishchanov, Axum, p. 36.
[2] Ibid., p.37.

ተሰማርተው ኖሩ። በመሆኑም በጎብረተሰቡ ዘንድ ጠይብ፥ ቡዳና አስማተኛ ተብለው በስድብ ስም የሚጠሩ የኢትዮጵያ አንድ ልዩ የሃይማኖትና የዕደ ጥበብ ክህት ማዋበረሰብ ሆኑ።

በመጨረሻ በ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ የኢትዮጵያ ቤተ እሥራኤል/ፈላሾች በሥርዓትና በሃይማኖት ግፊት የጥንቱ አገራችን ወደ ሚሉት ወደ እሥራኤል ፈለሱ።

ይህ ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል የቀረበው የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ረጅም የቁጡዙዙ ዓመታት የመከራና የጦርነት ታሪክ በኢትዮጵያ ዘውዳዊ የሥርዓት የሕዝቦች መከራ አንድ ምሳልና መግለጫ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር የቅርቡ በ60000 የሚቆጠሩ ቤተ እሥራኤሎች የአገረ እሥራኤል ፍለሳ የኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻ ረጅም ታሪክ ፍጻሜ አይደለም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ልዩ የሕዝቦች፥ የቋንቋዎች፥ የባህሎችና የሃይማኖቶች መስተጋብርና መወራረስ ልምድና ታሪክ መሠረት በተጠቀሰው ረጅም ዘመን ሰሜን/ፈላሾች በመሬት፥ በጊዜ፥ በቋንቋ፥ በደም፥ በባህልና በእምነት በአካባቢው የአገው፥ የአማራና የትግሬ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች አካል ሆኗልና። እቴጌ ምንትዋብ፥ ዳኛች ውቤ፥ አጼ ቴዎድሮስና እቴጌ ጣይቱ የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ታላላቅ የአገርና የመንግሥት መሪዎች የወለደ አንድ የአገሪቱ ነባር ዘርና ሕዝብ ነውና።

4. የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

ከእስልምና በፊት የኢትዮጵያና የአረቦች ታሪካዊ ግንኙነት

የኢትዮጵያና የሮማውያን የፖሊሲ ስምምነት በአረቢያ

በ610-632 በአረቢያ በነቢዩ ሙሐመድ አብደላ የተመራው ታላቁ የአረቦች እስላማዊ አብዮት ታሪካዊ መነሻዎችና ዓለማቀፋዊ ውጤቶች በአካባቢው በሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል ለረጅም ዘመን ከተካሄዱ ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዙ ናቸው።

ከታሪክ እንደሚታወቀው፥ ሮማውያን በ30 ዓመተ ዓለም ግብፅን ለሦስት ምዕተ ዓመታት (332-30) ከገዙት ግሪኮች ያዙ። በዚህ የግሪኮ-ሮማውያን ዓለማቀፋዊ የሽግግር ዘመን በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ጥንታዊ የኑቢያ-ሚሮዌ መንግሥት እንዲሁም በአጎራባቹ አረቢያ ሚና፥ ሰባ፥ ቀጣሪን፥ ሃድራማዊ፥ ሂሚያሪትና ሃምዳና የተሰኙ አናሳ የአረብ መንግሥታት በየበኩላቸው በራሳቸው ውስጣዊና አካባቢያዊ ምክንያቶችና ግፊቶች ሁሉም በፈጣን የውድቀት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ነበሩ።[1]

እነዚህ የዘመኑ ታላላቅ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ክስተቶች፥ ሁኔታዎችና ሂደቶች የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕር፥ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ እስትራቴጂያዊ አገሮችን ለሦስቱ የሮም፥ የፋርስና የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥታት ክፍት የማትና የተፅዕኖ አካባቢዎች አደረጉ።[2]

ይሁን እንጂ በአካባቢው ከሦስቱ ተጠቃሽ መንግሥታት፥ በእስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በደጋማው ክልል የሚገኘው የኢትዮጵያውያኑ መንግሥት በተጠቀሱት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ለዓባይ ሸለቆ፥ ለቀይ ባሕርና ለኤደን ባሕረሰላጤ ጠረፍ ንግድ፥ ሰላምና ፀጥታ ዋስትና ለመስጠት ብቃት ያለው ኃይል

[1] Kobishchanov, Axum, p. 36.
[2] Ibid., p.37.

መሆኑን አረጋገጠ።[3] ይህም ሁኔታ በኢትዮጵያና በሮማውያን መንግሥታት መካከል የጂኦፖለቲካና የፖሊሲ ስምምነት ለመፍጠር ምቹ መንገድና ምክንያት ሆነ። ባንግሩ፥ ሁለቱም በኋላ በአረቦቹ እስላማዊ አብዮት እስኪደመሰሱ ድረስ የሮማውያንና የፋርሳውያን መንግሥታት በአካባቢው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የንግድና የኃይል ሚዛን ባላንጣ ኃይሎች ሆኑ።

ኢትዮጵያ በአረቢያ ላይ የነበራት ፖሊሲ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

በ24 ዓመተ ዓለም ሮማውያን ከግብፅ ተነስተው በአረቢያ ላይ የመጀመሪያ ወረራ አካሂዱ።[4] በዘመነ ክርስትና በ105-108 ደግሞ የሮማውያኑ የአረቢያ አውራጃ ተመሠረተ።[5] በመሆኑም አረቢያ በአፍሪካ፥ በአውሮፓና በሩቅ እስያ አገሮች መካከል እስትራትጂያዊ የዓለም ንግድ መንገድና ድልድይ ሆነ። ስለሆነም ከላይ እንደተባለው ሁለቱ ኃያላን የሮምና የፋርስ መንግሥታት በአካባቢው በንግድ፥ በእስትራቴጂና በኃይል ሚዛን ጉዳዮች ላይ ለረጅም ዘመን ባላንጣ ኃይሎች ሆኑ።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የዘመኑ አረቦች በአጎራባቹ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር «ሀበሻት» እና «አክሱማውያን» በማለት በሁለት ተወራራሽ ስሞች የሚጠሩዋቸው ኢትዮጵያውያን ቀይ ባሕርን ተሻግረው በምዕራብ፥ በማዕከላዊና በደቡብ አረቢያ ምድር በግምት በሰሜን ምዕራቡ ጫፍ ከዛሬው የሳውዲ አረቢያ የሂጃዝና የአሲር ክፍላተ ሀገር አንስቶ በደቡብ ምስራቅ እስከ የመን ድረስ በሚገኘው ረጅም የቀይ ባሕር ምሥራቃዊ ጠረፍ ክልል በጥንታዊ ሰነዶች ቲሃማት፥ ሚና፥ ሃምዳና፥ ሳባ፥ ሂሚያሪት፥ አራብቴ፥ ኪናይዶኬንቴ፥ ሀበሻ፥ ረይዳን፥ የመን፥ ቀጣባንና ሃድራማዊ ተብለው በልዩ ልዩ የጎሳና የአካባቢ ስሞች ከሚታወቁ ብዙ የአረብ አገሮችና አናሳ የጠረፍ መንግሥታት ጋር ረጅም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን መቼና እንዴት እንደጀመሩ እስከ ዛሬ ድረስ ከተገኙ የጽሑፍና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ገና አልተቻለም።[6]

[3] Ibid., p. 41.

[4] G. W. B. Huntingford (tr. & ed.,) The Periplus of the Erythrean Sea (1980), pp. 3-4.

[5] Sergew Hablesellassie, History, p.72.

[6] Conti Rossini, "Expeditions et Posssessions en Arabie", Journal Asiatique, Ser. 18 (1921), pp. 5-36.

ይህን የኢትዮ-አረብ ግንኙነት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት አስመልክቶ ኢጣልያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ (1872-1949) እንደዘገበው፥ በዘመነ ክርስትና በ130 አንድ ረቢ አቂባ የተባለ ይሁዳዊ ጸሐፊ ደቡብ አረቢያን ጎብኝቶ ታልመድ በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ ከነባሩ የአረብ ሕዝቦች በመልክ፥ በቀለምና በባህል ልዩ የሆኑና ኢትዮጵያዊ ነኝ ያለ አንድ ጥቁር ንጉሥ የአገሩ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ሆኖ እንደእሱም ጥቁር ከሆኑች እቴጌዪቱ ጋር አረቢያን ያስተዳድር ነበር።[7]

ከዚህ በ130 ዓመተ ምህረት በአረቢያ በረቢ አቂባ ከተጠቀሰው ጥቁር ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በኋላ በግምት ከ2ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ እስከ 3ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ማለትም ከ175 እስከ 225 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተጽፈው በየመን አገር ከማሪብ ጥንታዊ የሳባ ከተማ ቤተኖ ብዙ የአረብ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች «የሀበሾችና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደሪት፥ ዋዜባና አድባ የተባሉና ደቡብ አረቢያን ይገዙ የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ አሁን በዘመናችን በአርኪኦሎጂ ጥናትና ምርምር ታውቋል።[8]

ቡተጨግሪም፥ በሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ኢማሽ አክቢ በኢትዮጵያ በመዳብ ዘንግ ላይ በግዕዝ ቋንቋና ፊደል የተጻፈና «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» የሚል አንድ ታሪካዊ ጽሑፍ በትርቡ በሰሜን ምስራቅ ትግራይ ከአንድ ጥንታዊ ሥፍራ ተቆፍሯል።[9]

አሁን ዋናው ነጥቡ በደቡብ አረቢያ በነባ ጽሑፍ «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» እና በኢትዮጵያ በግዕዝ ጽሑፍ ደግሞ «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» ተብለው የቀረቡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ሳይሆኑ በአንድ ወቅት በሁለት በተለያዩ ሥፍራዎች፥ ቋንቋዎችና ፊደላት በሁለት በተለያዩ የሰም አጠራር ዘይቤዎች የቀረቡ የአንድ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሁለት የተለያዩ ስሞች እንደሆኑ በዘመኑ ቋንቋና ታሪክ ታዋቂ የሆኑ ምሁራን አስረድተዋል።[10]

ከዚህ የታሪክ ትንተና አኳያ፥ የአረቦቹ «ሀበሻ» የሚለው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ስም በታሪክ ለነዱ ለመጀመሪያ ጊዜ

[7] Ibid., "Expeditions et Possessions", p. 18.

[8] Ibid., pp. 18-36; Kobishchanov, Axum, pp. 48-54; Sergew Hablesellassie, History, pp. 75-80; W. F. Jamme (tr., and ed.,), Sabaean Inscriptions from Mahram Bilqis (Marih), Baltimore, 1962.

[9] A Caquot et A. J. Drewes, "Les Momuments Recueillis A Maqalle", Annales D' Ethiopie, Vol. 1 (1955), pp. 35-39.

[10] Ibid., p. 39.

ተጽፎ የተገኘው ከዚህ «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» ተብሎ በተጠቀሰውና ለመጀመሪያው ጊዜ በ183 ዓመተ ምሕረት[11] በአረቢያ በሳባ ቋንቋና ፊደል በተጻፈ በአንድ የሃምዳኑ አረብ መስፍን ዜና መዋዕል ነው። ባጭሩ ሀበሻ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የአረቦች ስያሜ ነው።

በግምት ከ175 እስከ 225 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በአረቢያ እርስ በርሳቸው የማትና የሥልጣን ጠላት በሆኑ የሃምዳናቱ የሳባቱ የሂሚያራትና የቀጣቦንና የሃድራማዊ አረብ መንግሥታትና የጦር አበጋዞች መካከል በተካሄደው ረጅም ጦርነት አገሮቹ በሳና በሥልጣን አንጃዎች ተለያይተው እየተዋጉ ብዙ ጊዜ በየግምባራቸው «የሀበሻት እና የአክሱማውያን ነገሥታት» ከሚሉዋቸው ገደረት ዋዜባና አድባ አንድ ጊዜ የፖለቲካና የመሣሪያ እርዳታ ሲፈልጉ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጊዜያዊ የአረብ ጎብረት ፈጥረው ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ሲዋጉ ይታያሉ።[12]

በመጨረሻ በ220ዎቹ የሂሚያራት አናሳ መንግሥት የተቀሩ የአረብ ባላንጣ መንግሥታትን በውልም በውጊያም ተቆጣጥሮ ከዛፋር መዲናው በኢትዮጵያውያኑ የማትና የተፅዕኖ ሥር አንድ ጠንካራ የሂሚያራት-ሳባ ጥምር የአረብ ኃይል መሠረተ።

በሌላ በኩል «የሀበሻትና የአክሱማውያን» መንግሥት በአረቢያ የቀይ ባሕርን ምሥራቃዊ ጠርፍ ከልል በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ፥ ከአሲር እና ከቲሃማት ከልል ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ የኤደን ወደብ ድረስ ማለትም የሂጃዝ-የመን ጠረፎችን በሙሉ በመቆጣጠር በምድርም በባሕርም ለሚቀጥሉት ብዙ ምዕተ ዓመታት የደቡብ አረቢያ የበላይ ኃይልና ሥርዓት ሆነ።[13]

በተጠቀሰው ዘመን የአክሱሙ የአጼ መንግሥት የአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አጎራባች ሕዝቦችና አገሮች የበላይ ኃይል ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ታሪክ ላይ የታወቀው በታላቁ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ነው። ከላይ እንደተገለፀው፥ የዚህ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ የጻፈው ንጉሥ ስም ሆነ የተጻፈበት ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል አልተረጋገጠም።

ይሁን እንጂ ጽሑፉ የተጻፈበት ዘመን በ2ኛው ምዕተ ዓመት «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» አረቢያን ከገዛበት ጊዜ

[11] Conti Rossini, "Expedition et Possessions", p. 11; Kobishchanov, Axum, p. 50.
[12] Ibid., Axum, pp. 52-54.
[13] Ibid., 54.

በኋላና በ4ኛው ምዕተ ዓመት በ330 ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን በፊት (በ300ዎቹ?) እንደሚሆን በኢትዮጵያ የዘመኑ ታሪክ ታዋቂ የሆኑ ምሁራን ይገምታሉ።[14]

የዚህ የአዱሊስ ጽሑፍ ግኝትና ቅጅ አስመልክቶ የግሪኩ-ግብፅ ጸሐፊ ኮስማስ ከ525 የአዱሊስና የአክሱም ከተሞች ጉብኝቱ መልስ እንደጻፈው፥ በተጠቀሰው ዓመት ከአክሱሙ አጼ ካሌብ የጽሑፉን ቅጅ አስገልብጠ እንዲልክለት አባስ ሰተብለ የአዱሊስ ገዥ ትእዛዝ ይሰጣል። በታሪክ አጋጣሚ በዚህ ጊዜ ጸሐፊ መንገደኛው ኮስማስ ሚናስ ከተሰኘ ጓደኛው ጋር በንግድ ሥራ ምክንያት በአዱሊስ ከተማ ነበር።

በመሆኑም አገረ ገዥው አባስ የግሪኩ-ግብፅ ጸሐፊዎቹን ከሐውልቱ ጽሑፍ ለአጼ ካሌብ የሚልክውን ቅጅ እንዲያዘጋጁለት ጠየቃቸው። ጸሐፊዎቹም የጽሑፉን ሦስት ቅጆች አዘጋጅተው አንዱን ለአገረገዥው ሰጡ። የተቀሩ ሁለቱን ቅጅዎች ለራሳቸው አንዳንድ ወሰዱ። ኮስማስ የራሱን ቅጅ *የኮስማስ የክርስቲያን ቶፖግራፍ* በተሰኘ መጽሐፉ ገልብጠ ለትውልድና ለታሪክ መረጃ አስተላለፈ።[15] ነገር ግን ኮስማስ የጽሑፉን ደራሲ ሆነ የተጻፈበትን ዘመን ባለመጻፉ ሰነዱ መቼና በማን ተጻፈ የሚለው ቁልፍ የታሪክና የጊዜ ጥያቄ እስከ ዛሬ ድረስ አልተመለሰም።

ባጭሩ የታላቁ የአዱሊስ ጽሑፍ ርዕሰ ነገሮች ከጽሑፉ ገፅ ሆነ ይዘት በትክክል በማይታወቅ ዘመን በአንድ ስሙ በማይታወቅ የአክሱም ንጉሥ በአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አካባቢዎች በድምር በ30 በሚቆጠሩ አገሮች ላይ በምድርና በመርከብ ያካሄዳቸው ጦርነቶች[16] ናቸው። ከዚህ አኳያ፥ በመጀመሪያ ዘመቻ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋአምባ ክልል በግምት በመረብ ወንዝና በጣና ሐይቅ መካከል በሚገኘው ምድር ንጉሡ ግዕዝ፥ አጋሚ፥ ስግዱ፥ አድዋ፥ ቲአሞ፥ ጋምቤላ፥ ዚንጋበን፥ አንዝ፥ ትአማ፥ አገው (አታገው) ከሰና ሰሜን የሚላቸውን አሥራ ሁለት አዋማዊ አገሮችና መንግሥታት አስገበራቸው።

በሁለተኛው ዘመቻ በግምት በቀይ ባሕር፥ በአትበራ ወንዝ፥ በኑቢያ-ሚሮዌና በግብፅ መካከል ለዘን፥ ዘአ፥ ገበለ፥ አታልሞ፥ ቤጃና ተንገናይቴ (ታካ) የሚላቸውን ስድስት የተለያዩ የቤጃ አገሮች

[14] Ibid., pp. 41-43.
[15] Cosmas, Topography, pp. 55-56.
[16] Ibid., pp. 59-66; Kammerer, Essai Sur L'Histoire, pp. 57, 90.

ንና ማኅበረሰቦችን በማስገበር የመንግሥቱን የስሜን ምዕራብ ወሰን በላይኛው የዓባይ ሸለቆ እስከ የግብፅ ጠረፎች ድረስ አስፋፉ።

በሦስተኛው ዘመቻ ጠረኛው ንጉሥ በክፍለ አህጉሩ ከትግራይ ደጋአምባ በደቡብ ምስራቅ በማምት ከአዋሽ ሸለቆ እስከ ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ድረስ ባለው ቆላማና በጥንቱ ዓለም በዕጣን ምርትና ንግድ በታወቀ የትሮጅሎዳውያንና የበርበራውያን ምድር አነን፥ ምጤን፥ ሰለአ፥ ሮሳይና ሶስቱ የተሰኙ አምስት የቆላ ሕዝቦች ንና አገሮችን አስገበራቸው።

በአራተኛውና በመጨረሻው ዘመቻ የንጉሡ ጦር በመርከብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በአረቢያ ረጅም ምዕራባዊ ጠረፍ ዳርቻ ላይ በስሜን ምዕራብ ክልል በሚገኘው በሂጃዝ-አሲር አገር በዘመኑ የሮማውያን ይዞታ ከነበረ ከለኡኮመ ወደብ ጀምሮ በመሀል፥ በምስራቅና በደቡብ አረቢያ እስከ ሳባ-ሂሚያሪት ጠረፎችና እስከ ባብአልመንደብ ሰርጥ አካባቢ ድረስ ሙሉ ዘመቻ በማካሄድ በዘመኑ በሂጃዝ-አሲር ጠረፍ ኪናይዶኮልፕቴና በሂሚያሪት ጠረፍ አራብቱ የተሰኙ ሁለት እስትራቴጂያዊ አገሮችን የመንግሥቱ የባሕር ማዶ ግዛቶች አድርጎ በቀጥታ ያዘ። በዚህ ረገድና ተግባር ከዚህ በፊት «በሀበሾችና በአክሱማውያን ነገሥታት» ገደረት፥ ዋዜባና አድባ ዘመን በደቡብ አረቢያ በየመን ጠረፍ ሀበሻ የተባለ የኢትዮጵያውያን ግዛት እንደነበር አይዘነጋም።

የአዱሊስን ታሪካዊ ጽሑፍ ከጻፈው ንጉሥ ቀጥሎ በስሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አኅጉራት አካባቢዎች የኢትዮጵያን መንግሥት በ4ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመታት በኢኮኖሚ፥ በድርጅት፥ በክህሎት፥ በሃይማኖት፥ በዲፕሎማሲና በትጥቅ ከጥንቱ ኩሻዊ የግብፅና የኑቢያ መንግሥታት ቀጥሎ የአፍሪካ ታላቁ ዓለማቀፋዊ ሥርዓት አድርገው የገነቡት ሁለት አጼ ነገሥታት ኢዛና (320-344) እና ካሌብ (493-534) ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር የኢትዮጵያ የመጨረሻ አዋማዊና የመጀመሪያ ክርስቲያን መሪ የሆነው አጼ ኢዛና በኢትዮጵያና በአረቢያ በግሪክ፥ በግዕዝና በሳባ ጥንታዊ ቋንቋዎች በተጻፉ ዜና መዋዕሎቹ (1) «ሰምቼ» አያለ የሚጠራቸው መሀዛ፥ ሀራ፥ ደመወ፥ ፊልሀ፥ ፅራእ፥ ሀሌን፥ ምጤን፥ ዳኬን፥ ለኬንና ሰብራት የተባሉ የጦር ድርጅቶች፥ (2) «አባቶቼ» የሚላቸው አርስ፥ መሕርም፥ አስተር፥ ብሔር፥ ምድር፥ የሰማዩ አምላክ፥ ክርስቶስ፥ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብለው በልዩ ልዩ ስሞችና ቋንቋዎች የሚታወቁ የውጭና የአገር ውስጥ አማልክት እንደነበሩት፥ (3) እንዲሁም «ግዕዝ»፥ «ካዕብ»፥ «ሳልስ»፥ «ራብዕ»፥

«ሐምስ»፥ «ሳድስ» እና «ሳብዕ»፥ የተሰኙ የኢትዮጵያ ልዩ የቋንቋ ድምፅ፥ ንግግርና ንባብ ሥዕላዊ የፊደል ምልክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመነ መንግሥቱ እንደተገኙ የስነዶቹ ጥናት ያሳያል።[17]

ቡተጨማሪም ቡትጠቀሱት የድንጋይ ላይ ጽሑፎች «የአክሱም፥ የሚያርፅ፥ የረይዳን፥ የኢትዮጵያ፥ የሀበሻት (የሀበሾች)፥ የሳባ፥ የሰልሂን፥ የፅያሞ፥ የቤጃ፥ የካሱ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ»[18] የሚለው የአጼ ኢዛና የአገርና የመንግሥት ስም ንጉሡ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በ330ዎቹ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የአራቱ አኅጉራት የስሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አገሮች ሉአላዊ የበላይ ኃይልና ሥርዓት እንደሆነ ያመለክታል።

ከእነዚህ ከኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ግዛቶች ሂሚያር፥ ረይዳን፥ ሀበሻ፥ ሳቦና ሰልሂን የመንግሥቱ አምስት የአረቢያ ግዛቶች፥ እንዲሁም ፅያሞ፥ ቤጃና ካሱ የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ግዛቶች፥ አክሱምና ኢትዮጵያ ደግሞ በስሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በስሜኑ ደጋአምባ ላይ የአጼው መንግሥት ማዕከላዊ ኩተሳና አገር ናቸው።

ከአጼ ኢዛና ዘመን 200 ዓመታት በኋላ በ6ኛው ምዕተ ዓመት በ530ዎቹ «የአክሱም፥ የካሱ፥ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሂን፥ የትአሞ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የራብመ፥ የቤጃ፥ የናባ፥ የአራብት፥ ንጉሥ»[19] የሚለው የአጼ ካሌብ የአገርና የመንግሥት ስም በሁለቱም የአፍሪካና የእስያ አኅጉራት አህጉራት የኢትዮጵያ መንግሥት ከአጼ ኢዛና ዘመን የበለጠ እንደተስፋፋ በግልጽ ያሳያል።

በአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ከተጠቀሱት ግዛቶች ረይዳን፥ ሳባ፥ ሰልሂን፥ የመን፥ ቲሃማት፥ ራብመና አራብት ሰባት የኢትዮጵያ መንግሥት የአረቢያ ግዛቶች ናቸው። በዘመኑ ቲሃማት[20] በስሜን ምዕራብ ጠረፍ ከሂጃዝ በደቡብ ምስራቅ ጠረፍ እስከ የመንና ከዚያም ባሻገር ያለው ረጅም የደቡብ አረቢያ ምዕራባዊ ጠረፍ አጠቃላይ ስያሜ ነው። ካሱ፥ ትአሞ፥ ቤጃና ናባ ጅማሮ፥ ከሦስቱ ተከታታይ የአዱሊስ ሐውልት፥ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንደ

[17] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገጽ 78-84

[18] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገጽ 68

[19] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገጽ 68

[20] H. T. Norris, "The Himyaritic Tihama: Evidence for a Multi-Racial Society in Pre-Islamic and Early Islamic Arabia," Abbay, No. 9 (1978), pp. 101,116; Kamal Salibi, The Bible Came From Arabia (London Jonathan Cape, 1985), pp. 38-39.

ሚታወቀው፥ በቢጃና በሚሮዋ ሕዝቦችና አገሮች ላይ እየሰፉ የመጡ የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ክፍቶች ናቸው።

ዮ517-525 የይሁዳውያኑ አመፅ በአረቢያ

በአረቢያ የኦሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች ጦርነትና ውድቀት

በዘመነ ክርስትና በሚጀመሪያ ሰድስት ምዕተ ዓመታት የኢትዮ-አረብ ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት፥ በ130 ዓመተ ምህረት ደቡብ አረቢያ ከአፍሪካ በአንድ ጥቁር ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ይገ እንደዝር ረቢ አቂባ የተባለ ይሁዳዊ ጸሐፊ በዓይኑ አይቶ በመጽሐፉ አረጋግጧል። ቀጥሎም በ170-220ዎቹ ሦስቱ «የሀበሾችና የእክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፥ ዋዜባና አደባ በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ-አሲር በደቡብ ምስራቅ እስከ ኤደን የመን ድረስ የደቡብ አረቢያን ረጅም ምዕራባዊ ጠረፎችን ከሁለቱም ከምድርና ከባሕር በቀጥታ ይቆጣጠሩ እንደዝር በየመን ከጥንታዊ የግሪብ ኩጦግ በሳባ ቋንቋና ፊደል ተጽ ፈው በተገኙ ብዙ የአረብ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች በስፋትና በዝርዝር ተገልጿል።

በተጨማሪም በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ የአዱሊስ ሐውልትን የግሪክ ጽሑፍ የጻፈው የእክሱሙ ንጉሥ በአረቢያ የቀይ ባሕር ጠረፍ ከልል ከሂጃዝ እስከ ሳባ የመን ድረስ በሚገኘው ምድር ኪናይዶክልፕቴና አረብቱ በተሰኙ ሁለት እስትራቴጂያዊ ቀበሌዎች ላይ የፀጥታ ዘመቻ እንዳከሄደ በጽሑፉ በግልፅ ተቀምጧል።

በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአጼ ኢዛና (320-344) ዜና መዋዕል አምስቱ የሚያርፉ የረይዳን፥ የሀበሻ፥ የሳባና የሰልሄን ሕዝቦችና አገሮች በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ክፍቶች እንደሆኑ ተመልክቷል። እንዲሁም ከአጼ ኢዛና ዘመን 200 ዓመታት በኋላ በ6ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአጼ ካሌብ (493-534) ዜና መዋዕል ስባቱ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሄን፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የአራባውና የአራባት ሕዝቦችና አገሮች በዘመኑ የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር ማዶ ክፍቶች ሆነው ቀርበዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በ170-220ዎቹ ከላይ በስምና በተግባር ዝርዝር በተገለፁ አያሌ የደቡብ አረቢያ መንግሥታትና ማኅበረሰቦች መካከል ለረጅም ዘመን በተካሄዱ የጎሳ፥ የመሬት፥ የክብትና የሥልጣን ጦርነቶች መጨረሻ ላይ የሚያርሳባውያኑ ጥምር መንግሥት በሚ ያሩ መሳፍንትና የጦር አበጋዞች አመራር በኢትዮጵያውያኑ የውጭ ተፅእኖ ሥር የደቡብ አረቢያ ጠንካራው የአረብ ኃይል ሆኖ እንደተነሳ

በአጠቃላይ መንግድና መልክ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ከዘርዝር የታሪክ መረጃና እውቀት አኳያ፥ ከላይ ከተጠቀሱ የአዱሊስ ሐውልት፥ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ ሰነዶችም ሆነ ከሌላ የመረጃ ምንጮች የተጠቀሰው የሚሚያርሳባ ጥምር አገርና መንግሥት ታሪካዊ ዕድገትና ሂደት ሁኔታ እስከ የይሁዳውያኑ የ517-525 ፀረ-ክርስቲያን አመፅ ድረስ ለ325 ዓመታት በትክክል አይታወቅም።

በሌላ በኩል፥ በተባለው ዘመን ከአፍሪካ ኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች በደቡብ አረቢያ በሚያርሳባ አገር ግለትም በየመን በሥፍራ፥ በገዜና በቁጥር ተስፋፍተው እንደኖሩበት በዚህ ጥናት ከዚህ በላይና በታች የቀረቡ የታሪክ መረጃዎችና ትንተናዎች ያሳያሉ። በተጨማሪም ቦምት ከ115 ዓመተ ዓለም እስከ 517-525 ዓም ድረስ ባለው የሰባት ምዕተ ዓመታት ዘመን ውስጥ ብዙ ይሁዳውያን[21] በፍለሳ መጥተው በየመን እንደሰፈሩ ታውቋል። እንዲሁም ከ4ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያውያንና በሮማውያን አማካይነት ገብቶ በየመን አረቦችና በኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች ዘንድ እንደተስፋፋ የታሪክ መረጃና ጥናት ያሳያል።[22]

ከተግባር፥ ከታሪኮና ከሥርዓት አኳያ፥ በ6ኛው ምዕተ ዓመት በደቡብ አረቢያ በሮማውያንና፥ በፋርሳውያንና በኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል ለንግድና ለኃይል ሚዛን በተካሄደው ጂኦ-ፖለቲካዊ ትግል ሁለቱም የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች በተፋለሚ ዎች ዘንድ የፖለቲካ መሣሪያዎች እንደተደረጉ ታውቋል። በአጼ መንግ ሥታቱ መካከል በተፈጠረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግፊትና ግጭት የአገሩ የክርስትና ተከታይ አረቦችና የውጭ ሰፋሪ ክርስቲያኖች ከሮማ ውያንና ከኢትዮጵያውያን መንግሥታት[23] ወገን ተሰለፉ። ይሁዳዊ ሰፋሪዎችና አቀማዊ አረቦች ደግሞ ከሚያርሳባውያን አማፅያን ጋር ከፋርሳውያኑ የአጼ መንግሥት ወገን ሆኑ።

በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ከዚህ ቢታች እንደሚታየው፥ በአካባቢው በሦስቱ የአጼ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው የገቢና የኃይል ሚዛን ትግል እንዲሁም በሁለቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች መካከል የተከሰተው ግጭት በአንድነት ባጭር

---

[21] Ibid., p. 22.

[22] Sergew Hablesellassie, History, pp. 126-27; Vassilios Christides, "The Himyarite-Ethiopian War and the Ethiopian Occupation of South Arabia in the Acts of Gregentius, Ca. 530 A. D.; Annales D' Ethiopie, Vol. 9 (1972), pp. 130-131.

[23] Ibid., The Acts of Gregentius, p. 119.

ጊዜ ውስጥ በአረቢያ ለሦስተኛው መለኮታዊና አህዳዊ የእስልምና ሃይማኖት ክስተትና ዕድገት የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

ከዚህ አኳያ በ517 በየመን አረቢያ አንድ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ዩሱስ እና ፊንሃስ ተብሎ በልዩ ልዩ ስሞች የሚታወቅ ይሁዳዊ[24] የጦር አበጋዝ ግዕአድክርብ የተባለ የሚሚያርሳባ ንጉሥን ገልብጦ በምትኩ በራሱ መሪነት ይሁዳዊ የሂሚያር መንግሥት ለስምንት ዓመታት (517-525) በደቡብ አረቢያ መሠረተ።[25]

የይሁዳውያኑ የጦር አበጋዝ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ የሂሚያርን በትረ መንግሥት እንደያዝ በደቡብ አረቢያ በኢትዮጵያውያን፥ በሮማ ውያንና በአረብ ክርስቲያኖች ላይ የዘር፥ የቀለም፥ የቋንቋ፥ የጸታ፥ የዕድሜና የሙያ ምርጫና ልዩነት ሳያደርግ አጠቃላይ ግድያ ጀመረ። ለምሳሌም ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት የዛፋር ከተማ ውስጥ በአንድ የእልቂት ዘመቻ ብቻ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ 13,000 ሰዎችን ገደለ። 9,500 ሰዎችን ከ280,000 ግመሎች ጋር በምርኮ ወሰደ። የምዕመናንን ቤቶችና ቤተ ክርስቲያኖች በመደዳ አቃጠለ ተብሎ ተጽፏል።[26]

የ517-525 የአረብ ስደተኞች በኢትዮጵያ

በ517 ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ በአረቢያ በሕዝበ ክርስቲያን ላይ የጭፍጨፋ ዘመቻ እንደከፈተ የአረቢያ ክርስቲያኖች መሪና አስተማሪ አቡነ ቶማስ[27] ከናግራን ከተማ አምልጠ የአደጋውን ዜና በአክሱም ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች በማድረስ አስቸኳይ የነፍስ አድን እርዳታ ጠየቀ።

በመሆኑም በግንቦት-ሰኔ 517 በንጉሥ የሚመራ ፈጣን የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ቀይ ባሕርን በሰሜን ምዕራብ ጠረፍ ተሻግሮ የቲሃማትን ጠረፍ ያዘ።[28] ከቲሃማት ጠረፍ አገሩን ሲቆጣጠር ንጉሥ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ግን በሽሽት አምልጠ ወደ አንድ ተራራ ገባ። የኢትዮጵያ መንግሥት ጦር ከቲሃማት ጠረፍ ተንስቶ የሚሚያርሳባ መንግሥትን የዛፋር መዲና በመያዝ ደቡብ አረቢያን በቀጥታ የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር ማዶ ግዛት አደረገ። ይሁን እንጂ በዓመቱ መጨረሻ ከፊሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት ተመልሶ ወደ አገሩ ገባ።[29]

[24] Ibid., p. 136.
[25] Kobishchanov, Axum, p. 91.
[26] Sergew Hablesellassie, History, pp. 130-131.
[27] Kobishchanov, Axum, p. 91.
[28] Ibid.,
[29] Ibid., p. 92

ከኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት ከፊሉ ከደቡብ አረቢያ እንደ ዚህ በችኮላ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ከሸሸበት ተራራ ተመልሶ ከታህሳስ 517 እስከ ህዳር 518 ድረስ ሸሪክህል ያክቡል ከተሰኘው የጦር አበጋዙ ጋር በአገሩ በየአከባቢው ማለትም በሙሃ፥ በዘፋር፥ በናግራን፥ በማሪብና በሃድራማዊ ከተሞችና ከልሎች ክርስቲያኖችን በእሳትና በጎራዴ ስለት በመፍጀት እስከ 525 ድረስ አገሩን ለሰባት ዓመታት ተቆጣጠረ።[30]

ከ518 እስከ 525 ድረስ የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ካሌብ በአገሩ ውስጥ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በአረቢያ በይሁዳውያኑ እጅ የሚሰቃዩ ክርስቲያኖችን በዘመቻ ሄዶ ለመርዳት አልቻለም።[31] በዚህ ጊዜ በአረቢያ ከንጉሥ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ መከራና ስቃይ በመሸሽ የዘርና የሃይማኖት ልዩነት ሳያግዳቸው ከአረቢያ ብዙ አረቦች፥ ሮማውያንና ኢትዮጵያውያን ስፋሪዎች ወደ አክሱም በስደት እንደመጡ ተመዝግቧል።[32]

የንጉሥ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ የጦር አበጋዝ ሸሪክህል ያክቡል አዋማዊ ወንድምና የታዋቂው ያዛን ጎሳ ተወላጅ ሱማፋ አሸዋን በኢትዮጵያ የስደተኞቹ ጉዳይ ኃላፊ ሆነ።[33] በ517 አዋማዊ የአረብ መስፍን ሱማፋ አሸዋን ከጦር አበጋዝ ወንድሙ ሸሪክህል ጋር በማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ወገን ሆኖ በክርስቲያኖቹ ላይ ጦርነት እንዳካሄደ ታውቋል።[34] ነገር ግን ከ517 በኋላ የማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ጦርነት በአዋማዊ አረቦችም ላይ ጥቃትና ጥፋት ስለአደረሰ ሱማፋ አሸዋን ከሌላ ብዙ የአረብ ስደተኞች ጋር ወደ ኢትዮጵያ በስደት መጣ።[35]

የይሁዳውያኑ የአረቢያ አመፅና ውድቀት

የኢትዮጵያ ንጉሥና ጦር በአገር ቤት በተፈጠረው የፖለቲካና የፀጥታ ችግር ምክንያት ከግንቦት እስከ ሰኔ 517 የአረቢያ ዘመቻ በፍጥነት ወደ አገሩ እንደተመለሰ ታውቋል። አጼ ካሌብ በአገር ቤት የተፈጠረውን ችግር እስከ 523 ድረስ ተቆጣጠረ።[36] በመሆኑም በ524-525 በደቡብ አረቢያ በይሁዳውያኑ አማፅያን መንግሥት ላይ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን የቅጣት ዘመቻ ለማካሄድ ተዘጋጀ።

[30] Ibid., pp. 92-94
[31] Ibid., pp. 95-96
[32] Ibid., pp. 99-100
[33] Ibid.,
[34] Ibid., pp. 99-100
[35] Ibid., p. 100
[36] Ibid., p. 96

በዚህ ረገድና ተግባር፣ በቅድሚያ በሚያዝያ-ብኔ 524 አጼ ካሌብ በሂሚያሩ መስፍን ሱማፋ አሸዋን መሪነት በኢትዮጵያ የሚኖሩ የአረቢያ ስደተኞችን አስታጥቆ ወደ አገራቸው በመመለስ በይሁዳ ውያኑ አማፅያን ላይ አዘመታቸው።[37] በመጨረሻም በሰኔ-ሐምሌ 525[38] አጼ ካሌብ በራሱ መሪነትና አዝማችነት ሠራዊቱን በ70 መርከቦች አደራጅቶ በአዱሊስ ወደብ አጠገብ ከሚገኘውና ዝዘ ከተሰኘው ወደብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በየመን የይሁዳውያኑን የአመፅ መንግሥትና ጦር በአንድ የግምባር ውጊያ ደመሰሰ።

ድል አድራጊው አጼ ካሌብ፣ የመን አረቢያን እንደገና የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት አደረገው። ግዛቱንም እንዲመራ የሂሚያሩን ስደተኛ መስፍን ሱማፋን የክርስትና ልጁና በአረቢያ የመንግሥቱ እንደራሴ ንጉሥ (525-535) አድርጎ አነገሠ።[39] በተጨማሪም አጼ ካሌብ በንጉሥ ሱማፋ ሥር በጦርነቱ የፈረሰውን የአረቢያ ቤተ ክርስቲያን መልሶ እንዲያቋቁመው ከግብጹ ቤተ ክርስቲያን አንድ አቡነ ግረገን ቲዩስ የተሰኘ የሃይማኖት መሪና አስተማሪ አስመጣ።[40]

የኢትዮጵያ ከ525-577 የደቡብ አረቢያ መንግሥት ዕድገትና ውድቀት

በ525 አጼ ካሌብ በአንድ በኩል የአረብ መስፍን ሱማፋን በደቡብ አረቢያ የመንግሥቱ እንደራሴ ንጉሥ አድርጎ አነገሰ። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ የጦር አበጋዞች ጉባኤና ትእዛዝ የሚመራ ሠራዊት በአገሩ አሰፈረ።[41] በዚህ ጉዳይ በምንም ሥፍራና ጊዜ የአገሩን የተደራጀ ጦር የማይዝ መንግሥት በሁኔታው ደካማ የፖለቲካ ሥርዓት ነው። ከሕግና ከጎብረተሰብ በላይ የሆነ የጦር ኃይል ደግሞ ውሎ ሳያድር ለመንግሥቱም ለጎብረተሰቡም የሰላምና የፀጥታ ጠንቅ እንደሚሆን የሥልጣኔ ታሪክና ልምድ ያስተምራል።

በመሆኑም በአረቢያ አጼ ካሌብ የፈጠረው የደካማ መንግሥት እና የጠንካራ ጦር ጥምር የፖለቲካ ሥርዓት ባጭር ጊዜ ውስጥ መጀመሪያ በራሱ በአረቢያ የሥርዓት ቀውስና ውድቀት ያስከትላል። ቀጥሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሶስቱ የሮማውያን፣ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል የኃይል ሚዛን ያዛባል። በመጨረሻም በአካባቢው ለተጠቀሱ የአጼ መንግሥታትና ለክርስትና

[37] Ibid., p. 100
[38] Ibid., pp. 78, 100-101; Sergew Hablesellassie, History, pp. 133-136.
[39] Ibid., Axum, pp. 102-103, 105.
[40] Christides, "The Himyarite-Ethiopian War", p. 137.
[41] Kobishchanov, Axum, pp. 102-1-3.

ሃይማኖት ውድቀት በአንድ በኩል፣ ለምዕተ ዓመታት በመንግሥታቱ ሲጨቆኑ ለኖሩ የአረብ ነገዶች እስላማዊ አመፅና ዓለማቀፋዊ እንቅስቃሴ በሌላ በኩል የራሱን አስተዋጽኦ እንደ ሚያደርግ ከዚህ በታች አጭብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል።

በዚህ ረገድና ተግባር በ517-525 በአረቢያ የይሁዳውያኑን ፀረ-ክርስቲያን አመፅ በማጥፋት ጦርነት ኢትዮጵያውያንና ሮማውያን የጋራ ስምምነት እንደነበራቸው ይታወሳል። በሌላ በኩል በዘመኑ በተለይ በ529-531 በመካከለኛው ምስራቅ የሮማውያንና የፋርሳውያን መንግሥታት በጦርነት ላይ እንደነበሩና በጦርነቱም ፋርሳውያኑ አሸናፊዎች እንደሆኑ ታውቋል።[42]

በዚህም ምክንያት በ531 እና በ533 የሮማውያን መንግሥት ባለሥልጣኖች ከቁስጥንጥንያ መዲናቸው በቅደም ተከተል ዩሊያንና ናናሱስ በተሰኙ አምባሳደሮች የተመሩ ሁለት ተከታታይ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን በአክሱም ወደ አጼ ካሌብ፣ በዛፋር የመን ደግሞ ወደ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴው ንጉሥ ሱማፋ አሸዋን በመላክ በፋርሳውያኑ መንግሥት ላይ የሦስቱንም መንግሥታት አጠቃላይ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ጦርነት ለመክፈት ያልተሳኩ ሀሳቦችንና ዕቅዶችን አቀረቡ።[43]

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ግን በፋርሳውያኑ ላይ ከሮማውያኑ ጋር የጦርነት ግምባር ለመፍጠር ምንም አስፈላጊና በቂ ምክንያት አልነበራቸውም። ይልቁንም በደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ጦር ባለሥልጣኖች የሮማውያን መንግሥት ባለሥልጣኖች በተንኮል ከኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋን ጋር በቀጥታ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ማድረጋቸውን በአንድ ሉአላዊ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንደመግባት አድርገው የወሰዱት ይመስላል።[44]

በዚሁ ዓለማቀፋዊ ሁኔታና ሂደት በ535 በደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰፋሪ ጦር አዛዥ አብርሃ፣ እንደራሴ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋንን በኩዲታ ገልብጠ በምትኩ ራሱን (535-558) አነገሠ።[45] በአመፁ ምክንያት ለቅጣት ከአክሱም የተላኩ ሁለት ወታደራዊ ዘመቻዎችን ንጉሥ አብርሃ አሸንፎ መለሳቸው። ነገር ግን በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ አላመፀም።

[42] Ibid., p. 103.
[43] Ibid., pp., 103-105,
[44] Ibid., pp. 105-106.
[45] Ibid.,

በ543ቱ በየመን ደቡብ አረቢያ በጥንታዊው የግሪብ ከተማ ውሃ ግድብ ላይ በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተጽፎ የተገኘ በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴና የጦር አበጋዝ ንጉሥ አብርሃ ዙፋናዊ የአገርና የመንግሥት ስም[46] «የሳባ፥ የዲሁረይዳን፥ የሃድራማዊ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የደጋና ቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅና አዝማች 'Rumahis Zabiyaman'»[47] ተብሎ በውርስ የአማርኛ ትርጉም ይነበባል።

ከእሙ ጋር ከቀረበ የአረብ አገሮች ዝርዝር፥ ከሰንዓ መዲናና ቤተ ክርስቲያን ግምባታ፥ ከ543 የግሪብ ከተማ ውሃ ግድብ ላይ ጽሑፉ፥ ከንግድ ፖሊሲውና እንቅስቃሴው፥ እንዲሁም በ547 ወደ መካ ካካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ በግልፅ እንደሚታየው፥ ንጉሥ አብርሃ በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴና የጦር አበጋዝ በሰንዓ መዲናው ማዕከልነትና በክርስትና ሃይማኖት መሠረት መላ ምድረ አረቢያን በአንድ የአረብ መንግሥት ሥር የማድረግ ዓላማና ፖሊሲ ነበረው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ የመንግሥትን ሥልጣን በኃይሉ እንደያዘ የደቡብ አረቢያ መዲናን ከጥንቱ የሚሚያርሳባውያኑ የዛፋር ከተማ በስተሰሜን የግሪብ ውሃ ግድብ አጠገብ ወደ አዲሱ የሰንዓ ከተማ አዛወረ። እንዲሁም በአቡነ ግረጎንቲዩስ ጠንካራ ትምህርትና ምክር በዛፋር፥ በሰንዓ፥ በግሪብ፥ በናግራንና በተለያዩ ሌላ የአገሩ ከተሞችና አካባቢዎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሰራ። የግሪብን ጥንታዊ የውሃ ግድብ ብዙ የአረብ ነገዶችንና የህገር መሪዎችን አስተባብሮ በከፍተኛ የሰው ጉልበትና የንብረት ወጭ አደሰ። የዕደሳው ሥራ በሁለት ወራት ሲጠናቀቅ ንጉሡ ለሠራተኞቹ ቀለብ 5,806 የዱቄትና 26,000 የተምር ጆንያ ዎችን፥ 3,000 ከብቶችንና 300 ግመሎችን ከ11,000 ዶሮዎች ጋር እንደሰጠ በሳባ ቋንቋ በድንጋይ ላይ በተጻፈ የግድቡ ረጅም ታሪክ ተገልጿል።[48]

የአገሩን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ዕድገት በሚመለከት፥ ንጉሥ

[46] Sergew Hablesellassie, History, p. 48.

[47] ከንጉሥ አብረሃ የአገርና የመንግሥት ስም ጋር "Rumahis Zabiyaman" ተብሎ የተጻፈውን ታል/ሐረግ ዕውቁ የቋንቋና የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር (A. J. Drewes, Inscriptions, p. 108), "la lance dans sa main drite"? ብሎ በፈረንሳይኛ ሲያስተምር ፕሮፌሰር (Kobishchanov, Axum, p. 107), ደግሞ "Spear of the Right Hand" በግለት ወደ እንግሊዝኛ መልሶታል። ይህን የምሁራኑን ትርጉም መሠረት በማድረግ "እዝማች" በሚል ውርስ ትርጉም ወደ አማርኛ መልሻለሁ። ላጌድ።

[48] Sergew Hablesellassie, History, p. 149.

አብርሃ በደቡብ ምስራቅ አረቢያ የመንን በመካከለኛው ምስራቅ ከፍልስጤምና ከሶርያ ጋር በኤደን፥ በሰንዓ፥ በናግራን፥ በጣይፍ፥ በመካ፥ በየትሪብ (የዛሬው መዲና) አገር አቋራጭ የሲራራ ንግድ መንገድና ሥርዓት አጠናክሮ አገናኘ። እንዲሁም በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የንግድ መስመር በእስያ፥ በአፍሪካና በአውሮፓ አህጉራት መካከል የሚካሄደውን የዓለም ንግድ እንቅስቃሴና ምንጭ ከኤደን ወደብ ተቆጣጣሪ ኪለኛ ንጉሥ ሆነ።

በተጨማሪም በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በአቡነ ግረጎንቲዩስ ጠንካራ ትምህርትና ስብከት የአገሩን አዋጣዊ አረቦችንና ይሁዳውያን ሰፋሪዎችን በኃይል ግፊትና በኢኮኖሚ ተፅእኖ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለማስገባት ብርቱ የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎችን ወሰደ።[49]

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ንጉሥ አብርሃ በሰንዓ መዲናው በአገሩ የሃይማኖት፥ የኢኮኖሚና የባህል ማዕከልና መሳቢያ የሚሆን አረቦች ቃሊስ ብለው የሚጠሩትን ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ከቁጥጥንጥንያ በመጡ ሮማውያን ሙያተኞች[50] እርዳታ በፅብኝ በረድ፥ በወርቅ፥ በብር፥ በዝ ሆን ጥርስና በውድ እንጨት አስጊጦ ከሠራ በኋላ በአገሩ የሚኖሩ ሕዝ ቦች ሁሉ ከየአካባቢያቸው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የስግደትና የስለት ገዙና ጉብኝት እንዲያደርጉ የሚያስገድድ የፖሊሲ ሕግና ትዕዛዝ አወጀ።[51]

ነገር ግን እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በአረቢያ ይህን ቅይጥ የሃይ ማኖት፥ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመተግበር ሲጀምር በእስትራ ቴጂያዊው የመንሶራያ አገር አቋራጭ የሲራራ ንግድ መንገድ ላይ ማዕከላዊ ኬላ በሆነ የመካ የንግድና የሃይማኖት ከተማ በመጽሐፍ ቅዱስ የአብርሃምና የኢስማኤል መቅደስ እንደሆነ የሚነገርለትና ለሕዝበ አረቡ ሁለአቀፍ የእምነት፥ የስግደት፥ የስለት፥ የገበያ፥ የትምህርትና የባህል መሠረትና ማዕከል የሆነ የከዕባ ጥንታዊ መቅደስ አንድ ታላቅ የፖለቲካ እና የባህል ችግር ፈጠረበት።

በመሆኑም፥ በ547[52] አረቦች በተረት የገዘፈ ዓመት (ዓመልፈል) ብለው በሚያስታውሱት ዘመን፥ ንጉሥ አብርሃ የከዕባን መቅደስ ለማጥፋት በመካ አካባቢና በማዕከላዊ አረቢያ ላይ አንድ 60,000 ወታደሮችን ያቀፈና በዝሆን የሚጓዝ ታላቅ ሠራዊት አስከትሎ ያካሄደው ዘመቻ በመንገድ ላይ በተከሰተ የፈንጣጣ በሽታ ምክንያት

[49] Ibid., pp. 150-153.

[50] Kobishchanov, Axum, p. 106.

[51] Sergew Hablesellassie, History, pp. 150-151.

[52] Kobishchanov, Axum, p. 107.

ሳይሳካ ቀረ ተብሏል።[53]

ከዚህ በላይ በቀረቡ ልዩ ልዩ መንገዶችና መገለጫዎች ደቡብ አረቢያን ከሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን አጼ መንግሥታት ተፅእኖ ውጭ አንድ ጠንካራ የአካዚ መንግሥት አድርጎ ለ23 ዓመታት ከገዛ በኋላ፥ እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በ558[54] ሞተ።

እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ ዙ ያዛን የተባለ የሚሚያሩ መስፍንን ሬንሃባ የተባለች ቆንጆ ሚስትና ሲይፍ የተባለ የሁለት ዓመት ሕፃን እናት በሥልጣን ተፅእኖ የራሱ ሚስት አደረጋት። ሬንሃባ ለንጉሥ አብረሃም ያከሱምና ማዝሩቅ የተባሉ ሁለት ልጆች ወለደችለት። ሦስቱም የሴቲቱ ልጆች ሲይፍ፥ የአክሱምና ማዝሩቅ በአንድነት አብረው በቤተ መንግሥቱ እንዳደጉ ታውቋል።[55]

ከሬንሃባ ሦስቱ ልጆች፥ በአባቱ ወገን ይሁን በእናቱ መሆኑን ለይቶ በግልፅ ባያስቀምጥም፥ ፕሮፌሰር ካቢሽናቭ አክሱም በተሰኘ ጥናቱ፥ ሲይፍ ዙ ያዛን የእንደራሴ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋን የልጅ ልጅና የሚሚያር መስፍን እንደሆነ ገልጿል።[56] ውድ ሚስቱን ከሕፃን ልጁ ጋር በግፍ ከተቀማ በኋላ፥ ዙ ያዛን ከአገሩ ተሰዶ በሮማውያንና በፋርሳውያን መንግሥታት ዘንድ በአገሩ ላይ በሚካሄደው «የሀበሾች» እገዛ ላይ ለአሥር ዓመታት የእመፅ ፕሮፖጋንዳና ሴራ ሲያካሂድ ኖሮ በፋርሳውያኑ ቤተ መንግሥት በስደት እንደሞተ ታውቋል።[57] እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ እስኪሞት ድረስ ሲይፍ አብርሃን እንደአባቱ፥ ያከሱምንና ማዝሩቅንም ደግሞ እንደወንድሞቹ ቆጥሮ ይኖር ነበር። በ558 ንጉሥ አብርሃ በሞተ ጊዜ ትልቁ ልጅ ያከሱም ነገሠ። እርሱም በ562 ሞተ። ከንጉሥ ያከሱም ሞት በኋላ በማዝሩቅና በሲይፍ መካከል የከረረ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። በዚህ ወቅት ሲይፍ በማዝሩቅ የት አባክ ተብሎ ከተሰደበ በኋላ ከእናቱ አንደበት የዙ ያዛን ልጅ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማ። አባቱ ከአገሩ ተሰዶ እንዴት በፋርሳውያኑ ቤተ መንግሥት እንደሞተም አወቀ። በዚህ ጊዜ ሲይፍ ራሱ በስደት ወደ ፋርሳውያኑ ቤተ መንግሥት ሄደ። የአገሩን ነፃነት በሚመለከት በኢትዮጵያውያን ሰፋሪ ኃይሎች ላይ ከፋርሳውያን ባለሥልጣኖች ጋር የፖለቲካ ውልና ውሳኔ አደረገ።[58]

[53] Sergew Hableselassie, History, pp. 151-153.
[54] Kobishchanov, Axum, p. 107.
[55] Sergew Hablesellassie, History, p. 153; Norris, "The Himyaritic Tihama," p. 105.
[56] Kobishchanov, Axum, pp. 1110-111.
[57] Norris, "The Himyaritic Tihamma", p. 105.
[58] Ibid., pp. 105-106; Kobishchanov, Axum, 111.

በውሉም መሠረት በ577 ሲይፍ ዙ ያዛን ዋህራስ በተሰኘ የፋርሳውያን ጦር አበጋዝ የሚመራ የ800 ምንደኞች ጦር በ8 መርከቦች አስከትሎ በኤደን ወደብ በር በየመን አረቢያ በኢትዮጵያ ሰፋሪዎች ላይ ወሳኝ ጦርነት ከፈተ። የፋርሳውያኑ ጦር የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ ማዝሩቅን ገደለ። ጦሩንም ደመሰሰ። አገሩንም ያዘ። ሲይፍ ዙ ያዛንንም የፋርሳውያን መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አድርጎ በሰንዓ መዲና አነገሠ።[59] ንጉሥ ሲይፍ ዙ ያዛን በ517 ዙ ኑዋስ እንዳደረገው ሁሉ፥ የጸታ፥ የዕድሜ፥ የእምነትና የሙያ ምርጫና ልዩነት ሳያደርግ፥ የእሱ የክብር ዘብ ከሚሆኑ ጥቂት ወታደሮች ሌላ፥ በየመን አረቢያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በያለበት ሁሉ እንዲገደሉ አደረገ።

በየመን አረቢያ የኢትዮጵያውያንን ጦርና መንግሥት ደምስሶ በምትኩ ሲይፍ ዙ ያዛንን ካነገሠ በኋላ የፋርሳውያኑ ጦር አበጋዝ ዋህራስ በድል ወደ አገሩ ተመለሰ። ዋህራስ ወደ አገሩ እንደተመለሰ በ599 ገደማ ሲይፍ ዙ ያዛንም በኢትዮጵያውያን የክብር ዘበኞቹ ተገደለ። ይህ የኢትዮጵያ ወታደሮች አመፅ እንደተሰማ የፋርሳውያን ባለሥልጣናት የጦር አበጋዝ ዋህራስን ከ4,000 ወታደሮች ጋር የየመን አረቢያ ነዋሪ ገዥ አድርገው ላኩት። ከአገሩ መንግሥት በተሰጠው የፖሊሲ መመሪያ መሠረት፥ አገረ ገዥው ዋህራስ ኢትዮጵያውያን ከአረብ ደጋፊዎቻቸው ጋር ከአገር በሞት እንዲጠፉ የምንጊዜም ዘመቻ አካሄደ።

በዚህ ወቅትና ሁኔታ ከፋርሳውያኑ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ካመለጡ ኢትዮጵያውያን ከፊሎቹ ባሕሩን ተሻግረው ወደ አገራቸው ገቡ። ከፊሎቹ ወደ አጎራባች የመካና የሚጃዝ አረብ አገሮች በመሰደድ ከአካባቢው የቁረይሽ አረብ ሕዝብ ጋር ወደኋላ የሚታየውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍና ዘመን ይጀምራሉ።

የኢትዮጵያና የቁረይሽ አረብ ግንኙነት መነሻና ዕድገት (577-610)

የኢትዮጵያውያኑ የሂጃዝ አረቢያ ሰደትና ሰፈራ

የእስልምና ሃይማኖት መሥራች ነቢዩ ሙሐመድና የቁረይሽ አረብ ተከታዮቹ የኢትዮጵያ መንግሥትና ዜጎች ከነፍተው በመሰለፍ በተግራሪ ኃይሎች ላይ ለሃይማኖቱ ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት በፖለቲካ፥ ለስደተኞች ጥገኝነት በመስጠት፥ በትጥቅ፥ በሥራ፥ በድር ጅት፥ በትምህርትና በእምነት ሁለአቀፍ ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ለዓለምና ለታሪክ በይፋ አስታውቋል።

[59] Ibid., "The Himiyaritic Tihama",

በተጨማሪም በቅዱስ ቁርአን - ቤት፥ ደም፥ ነፍስ፥ አፈር፥ አንዛላ፥ መጽሐፍ፥ ድግምት፥ ፀሐይ፥ ዲያብሎስ፥ ሐዋርያ፥ የዋሀ፥ ማዕድ፥ መናፍቅ፥ ብላሌ፥ ታቦት፥ ብርሃን፥ ጣኦት፥ ምኩራብ፥ መሰኮት፥ ክፍል፥ ፈጠረና ደመደመ የተሰኙ የኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋ ቃላት ከአረብኛ ጋር የሃይማኖቱ ትምህርት ባህላዊ መግለጫና መሣሪያ ሆነው አገልግለዋል።[60]

ይህ ልዩና ጠቃሚ የሆነ ታሪክ ከሁሉ በፊትና በላይ በሁለቱ አጎራባች የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በቀይ ባሕር በርና ድልድይ አማካይነት ለረጅም ዘመን በመልክአ ምድር፥ በኢኮኖሚ፥ በጋብቻ፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በእምነትና በሥርዓት የተፈጠረ ጥልቅና ጥብቅ ግንኙነት ተግባራዊ ማሰረጃና መግለጫ ነው።

ከታሪክና ከጊዜ አኳያ ይህ የኢትዮ-አረብ የቀረበ ግንኙነት ከዘመነ ክርስትና መባቻ ጀምሮ እስከ 577 ድረስ ለብዙ ምዕተ ዓመታት የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱም መንግሥት ከአቻ የሮማውያንና የፋርሳውያን የአጼ መንግሥታት ጋር በአካባቢው አንድ ዓለማቀፋዊ ኃይልና ሥርዓት በነበረበት ዘመን በየመን ደቡብ አረቢያ በሁለቱ አጎራባች የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል እንዴት ተፈጥሮና አድጎ እንደ ዳበረ ከላይ በቀረበው ጥናታዊ ቢጋር ባጭሩ ተገልጿል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በ577 የመን ደቡብ አረቢያ በፋርሳውያን እጅ ከወደቀ በኋላ በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በተጠቀሰው ረጅም የኢትዮ-አረብ ግንኙነት ታሪክ ላይ አዲስና ከፍተኛ የዕድገት አቅጣጫ፥ መንገድና ምዕራፍ ተከፈተ። በዚህ ረገድና ተግባር ከየመን ደቡብ አረቢያ በ577-600 በፋርሳውያን ከተባረሩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹ ወዳገራቸው ተመለሱ። ከፊሎቹ ደግሞ በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በሂጃዝ ግዛቶችና ከተሞች በተለይም በመዕል ሀገር በሚገኘው የመካ የንግድና የ360 ጣኦቶች ከተማ እንዲሁም ከመካ ከተማ በ70 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከዛሬ የጅዳ ወደብ ከተማ በስተደቡብ በነበረውና ሹአይባ[61] በተሰኘው የሂጃዝ የቀይ ባሕር ወደብ ላይ በሰዋሪነት ሰፍረው ከነበር የቁረይሽ አረብ ነገድ ጋር አዲስና ዘላቂ የሆነ ሁለአቀፍ የኢኮኖሚ፥ የባህልና ማኅበራዊ ግንኙነት ጀመሩ። ይህ በኢትዮጵያውያንና በአረቦች መካከል በሹአይባና በመካ የሂጃዝ ከተሞች የተፈጠረው አዲስ ግንኙነት በእስልምና ሃይማኖት ክስተት ዋዜማ ላይ በተለይም በንግድና በባህል መስኮችና መንገዶች በኃይል አድጎና ዳብሮ

[60] ቅዱስ ቁርአን ያማርኛ ትርጉም «አዲስ አበባ 1961» መቅድም ገጽ 8፥11።

[61] S. Hablesellassie, History, p; 154; R. Pankhurst, An Introduction to the Economic History of Ethiopia, (1961), pp. 49. 54.

ለሃይማኖቱ ዓለማቀፋዊ ዕድገትና መስፋፋት የሚያደርገው ልዩ የድል አስተዋፅኦ[62] ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል።

በእስልምና ክስተት ዋዜማ በሂጃዝ የኢትዮጵያና የቁረይሽ አረቦች ታሪካዊ ግንኙነት

በ535-558 በአስትራቴጂያዊው የመን አረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በአዲሱ የሰንዓ መዲናው ማዕከልነትና በክርስትና ሃይማኖት መሠረት የተለያዩ የአረብ ማህበረሰቦችን፥ ነገዶችን፥ ክልሎችንና ባላባታዊ ግዛቶችን ባጎራባች የፋርሳውያን ተፃራሪ ኃይሎች ላይ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማደራጀት በ547 በማዕከላዊና በሰሜናዊ አረቢያ በፋርሳውያኑ የአረብ ወኪሎች ላይና በመካ አካባቢ በሮማውያኑ የፖለቲካ ድጋፍ ያካሄዳቸውን ተከታታይ ወታደራዊ ዘመቻዎች ጨምሮ ብዙ የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎችን እንደወሰደባቸው ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።[63]

ነገር ግን ንጉሥ አብርሃ ከሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት በተለይም ከፋርሳውያኑ የፖለቲካ ተፅእኖ ነፃ የሆነ አንድ ጠንካራ የአረብ አገርና መንግሥት ለመገንባት የነበረው ዓላማና ፖሊሲ በመጨረሻ በ577-600 የፋርሳውያኑ ጦር የመንን በያዘ ጊዜ ተደመሰሰ።[64] በዚህ ረገድና ተግባር፥ የፋርሳውያኑ ጦር ኢትዮጵያውያንን አሸንፎ ከየመን ደቡብ አረቢያ አባረረ። እንዲሁም የኢትዮ-ሂሚያር ጥንታዊ መንግሥትንና የንግድ ሥርዓትን አፈረሰ። በተጨማሪም እስከ 630 ድረስ የመን ደቡብ አረቢያ ራሱ የፋርሳውያኑ መንግሥት አንድ የጠረፍ አውራጃ (ማርዝፖኒት) እንዲሆን ተደረገ።

በመጨረሻም ፋርሳውያኑ በሕንድ ውቅያኖስና በቀይ ባሕር ዓለማቀፋዊ የንግድ መስመር በሦስቱ የእስያ፥ የአፍሪካና የአውሮፓ አህጉራትና ሕዝቦች መካከል በሚካሄደው ዓለማቀፋዊ የንግድ ሥርዓትና እንቅስቃሴ ላይ ማዕቀብ አደረጉ። ይህ የፋርሳውያኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ተግባር በደቡብ አረቢያ ላይ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በሦስቱ የፋርሳውያን፥ የኢትዮጵያውያንና የሮማውያን የአጼ መንግሥታቱም ላይ አፍራሽ የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካና የፀጥታ ተጽዕኖ ያሳድራል። በዚህ ሁኔታና ሂደት የደቡብ አረቢያ ነባር የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካ፥ የንግድና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ሁሉ ፈረሱ። ይህ አካባቢያዊና ዓለም

[62] Cuoq, Islam en Ethiopia, pp. 23-32; Kobishchanov, Axum,, pp. 113-114; Erlinch, Ethiopia and the Middle East, pp. 5-10; Norris, "The Himaritic Tihama", pp. 107-116.

[63] Ibid., Axum, pp. 106-107; Doresse, Historoire Sommaire, pp. 101-102, 113-114.

[64] Ibid., Histoire Sommaire.

አቀፋዊ ድርብ ሁኔታና ሂደት በ7ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ በሦስቱ ተጠቃሽ የአጼ መንግሥታት ላይ ታላቁን የአረቦች አብዮታዊ ኃይል እንዴት እንደሚያስከትል ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በስፋትና በዝርዝር ይታያል።[65]

በሌላ በኩል፥ ይህን መሰሉ የደቡብ አረቢያ ሁለንትናዊ ውድቀት ባንፃሩ በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በተለያዩ የምድርና የባሕር አቋራጭ የንግድ ሥርዓቶችና እንቅስቃሴዎች በሚኖሩ የቁረይሽ አረቦችና በተለያዩ የኢትዮጵያ ሰፋሪ ማኅበረሰብ ክፍሎች - ነጋዴዎች፥ ወታደሮችና ባሮች - መካከል በንግድ፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በጋብቻና በሃይማኖት አዲስ የማንነት ሁኔታዎችን፥ ሂደቶችንና ኃይሎችን ይፈጥራል።[66]

በዚህ ወቅትና ሁኔታ በሁለቱ ማለትም የበረሃ አቋራጭ የየመን-ሶሪያ የሲራራ ንግድ መስመርና በቀይ ባሕሩ የአዱሊስና የሹአይባ አጎራባች ወደቦች በኩል የሚያልፈው ድንበር-ዘለል የኢትዮ-ኢራቅ ዓለማቀፋዊ የንግድ መንገድ የመገናኛ ኬላ ላይ የሚገኘው የቁረይሽ አረቦች[67] የመካ ከተሜ-መንግሥት በፍጥነት አደገ። ይህ ትንሹ የመካ የንግድ ከተማና መንግሥት ባጭር ጊዜ ውስጥ ለምዕተ ዓመታት በሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል የጂኦ-ፖለቲካ ትግል መድረክ በሆነው የአረብ ምድር ላይ የአረቦቹ ጠንካራ የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካ፥ የባህልና የትምህርት ማዕከል ቀጥሎም የታላቁ የእስልምና ሃይማኖት መነሻ ልደት እንዴት እንደ ሚሆን ከዚህ በታች ይታያል።

በተጨማሪም በትንሹ የመካ የንግድና የሃይማኖት ከተማ ከየአካባቢው አዋጣዊ የአረብ ነገዶችና ጎሳዎች ለስግደት፥ ለሥለትና ለንግድ የሚመጡበትና 360 ጣኦቶች የሚገኙበት ታላቁ የከዕባ[68] መቅደስ ተቋም ከኢስማኤል ምንጭ ጋር ለአዳጊ የቁረይሽ ነጋዴዎችና ባለሥልጣኖች አንድ ታላቅ የሀብትና የኃይል መሠረት፥ ማዕከልና መሣሪያ ይሆናል።

በአረቦቹ ትውፊታዊ እምነት መሠረት፥ በመካ ከተማ የከዕባ መነሻ መቅደስ ከዛሬ 4000 ዓመታት በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ለአብርሃም[69] የተሰጠ ቅዱስ የስግደትና የሰላት ቦታ

[65] Ibid., p. 114.
[66] Erlich, Ethiopia and the Middle East, p. 5.
[67] W. M. Watt, Muhammad et Mecca (1952), p. 3.
[68] Ibid., pp. 4-5.
[69] S. Hablesellassie, History, p. 152.

ነው። በዚህ ቅዱስ የከዕባ መነሻ መቅደስ በዘመነ ክርስትና በ5ኛው ምዕተ ዓመት አንድ ቁሰይ የተሰኘ የቁረይሽ አረብ ባላባት የመካን ከተማ ለሕዝበ አረብ የሃይማኖት፥ የፖለቲካና የንበያ መሠረትና ማዕከል አድርጎ እንደቆረቆረው ታውቋል።[70]

የመካ ከተማ መሥራች ባላባት ቁሰይ - አብድቁሰይ፥ አብድ አዳር፥ አብድሜናፍና አብድአልኡዛ የተባሉ 4 ወንድ ልጆች ይወል ዳል። ከአራቱ የቁሰይ ልጆች አንዱ ማለትም አብድመናፍ በበኩሉ አብድሸምስ፥ ነውፈል፥ ሀሺምና አልሙጠሊብ የተባሉ አራት የኋይዩ ሙሐመድ አብደላህ (570-632) ቅድመ አያቶችንና በ6ኛው ምዕተ ዓመት በተለይም የመን ደቡብ አረቢያ በኢትዮጵያውያን አስተዳደር ሥር በከፍተኛ የዕድገት ደረጃና እንቅስቃሴ ሂደት ላይ በነበረበት ዘመን (525-577) የመካ ከተሜ-ጎብረተሰብንና መንግሥትን በንግድ፥ በሥራ፥ በሃይማኖትና በፖለቲካ ሥርዓት በከፍተኛ ደረጃ እንደገነቡ የሚነገርላቸውን የቁረይሽ አረብ ታዋቂ መሰፍንታዊ ጎሳዎችን መሠረተ።[71]

ከእነዚህ አራቱ የመካ ቁረይሽ መሰፍንታዊ ጎሳዎች (1) የአብድሸምስ ተወላጆች ከመካ ከተማ በደቡብ ግምባርና የሲራራ ንግድ መንገድ ከየመን የዕጣን ምርትና ንግድ አገር ጋር፥ (2) የአልሙጠሊብ ተወላጆች በምዕራብ ግምባር በሲራራና በባሕር ንግድ መስመሮች በቀይ ባሕሩ የአረብ ሹአይባና የኢትዮጵያ አዱሊስ አጎራባች ወደቦች በኩል በአፍሪካ አህጉር ከኢትዮጵያ ታላቅ የሰውና የተፈጥሮ ሀብት አገር ጋር፥ (3) የነውፈል ተወላጆች በምስራቅ ግምባርና የሲራራ ንግድ መስመር ከኢራቅና ከፋርስ አገሮች ጋር፥ (4) የሀሺም ተወላጆች ደግሞ በሰሜን ግምባርና የሲራራ ንግድ መንገድ በዘመኑ የሮማውያን ግዛቶች ከነበሩ የፍልስጤምና የሶርያ አገሮች ጋር ለመነው የቁረይሽ አረብ ከተሜ-ጎብረተሰብና መንግሥት ህልውናዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የሆኑ የንግድ ዝነያዎችን፥ ፖሊሲ ዎችን፥ ስምምነቶችንና እንቅስቃሴዎችን በየበኩላቸው መሠረቱ።[72] በእስልምና ክስተት ዋዜማ እነዚህ አራቱ ዓለማቀፋዊ የንግድ መንገ ዶችና ዝነያዎች የመካ ከተሜ-ጎብረተሰብና መንግሥት የኢኮኖሚ መሠረቶችና መሣሪያዎች እንደነበሩ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

[70] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 5. 30.
[71] Ibid., p. 7,
[72] Ibid., pp. 13, 30

ከማኅበራዊ ዕድገት መርህ አኳያ፥ በምንም ሥፍራና ጊዜ የዕድገት ደረጃ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የአንድ የፖለቲካ ሥርዓትና ኅብረተሰብ ሁለት የተያያዙ መሠረቶችና መለጫዎች የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅሮችና ድርጅቶች ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር ከዛሬ 1400 ዓመታት በፊት በምድረ አረቢያ በአመዛኙ በእንሰሳት እርባታ ተሰማርተው በዘላንነት በሚኖሩ የአረብ ነገዶች አገር ውስጥ በትንሹ የመካ የንግድና የጣአት ከተሜ-ኅብረተሰብና መንግሥት ለታላቁ የእስልምና ሃይማኖት ክስተትና ዕድገት ታሪካዊ መነሻ የሆነው ነገደ ቁረይሽ ከላይ ባጭሩ በተገለጸው ቅይጥ የሲራራ ንግድ ኢኮኖሚ፥ የመቅደስ አገልግሎትና የባሪያ ጉልበት የሚኖር አንድ አናሳ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ነበር።[73] ባንፃሩ በተባለው የመካ ቁረይሽ አናሳ አገርና መንግሥት የዘላንም ሆነ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ ለዓይነት አልነበረም።[74]

በዘመኑ በተቀሩት የአረቢያ ክልሎች ከእንሰሳት እርባታ ጎን ለምሳሌ በየመን ደቡብ አረቢያ የመስኖ እርሻና የዕጣን ምርት፥ ቢያትሪብ ግለትም በመዲና በአአሲስ ምንጮች ሥፍራ የተምር ዛፍ ምርትና ንግድ እንዲሁም ከመካ የንግድና የጣአት «ደሴት» አጠገብ ጣይፍ በተሰኘው ተራራማ ቀበሌ ከንግድና ከጣአት ሥራዎች ጎን የተለያዩ የምግብና የንግድ ሰብሎች በዓይነትና በመጠን ይመረቱበት ነበር።[75] ነገር ግን በነቢዩ መሐመድ ዘመን በትንሹ የመካ አገርና መንግሥት እነዚህ በምድረ አረቢያ የታወቁ የእንሰሳት እርባታና የእርሻ ሥራዎች አልነበሩም።

ባጭሩ በዚህ በመካ ልዩ የንግድ፥ የጣአትና የባሪያ ጎብረተሰብና መንግሥት ከንግድ ኢኮኖሚና ባህል ጋር አብሮ የሚፈጠረው የፋይናንስ አገልግሎት እንዲሁም የገንዘብ ወለድና የአራጣ ብድር ሥርዓት በሌላ ተመሳሳይ የከተማና የንግድ ጎብረተሰብ ዘንድ እንደ ሚያደርገው ሁሉ ባጭር ጊዜ ውስጥ በነቢዩ መሐመድ ትምህርት መሠረት ታላቅ ማኅበራዊ የሥርዓት ቀውስና ለውጥ ያስከትላል።[76]

በነቢዩ መሐመድ ዘመን (570-632) የትንሹ መካ ከተማ ነዋሪዎችን የዘር፥ የቋንቋ፥ የባህልና የሃይማኖት ይዘት፥ ጥንቅርና ተግባር በሚመለከት ደግሞ ከተማው ከሞላ ጎደል የሁለት ልዩ ሕዝቦች ማለትም የቁረይሽ አረብ ነገድና የኢትዮጵያ ሰፋሪ ነጋዴዎች፥

[73] Ibid.,
[74] Ibid.,
[75] Ibid.,
[76] Ibid., pp. 3, 16-19.

ሙያተኞች፥ አስተማሪዎች፥ ወታደሮችና ባሮች መኖሪያ እንደነበር የነቢዩና የሃይማኖቱ መነሻ ታሪክ ያሳያል።[77]

በዚህ ረገድና ተግባር ለምሳሌ በ6ኛው ምዕተ ዓመት በየመን ደቡብ አረቢያ የአዋማዊዝም፥ የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ነባር አረቦች ከሰፋሪ ኢትዮጵያውያን፥ ይሁዳውያን፥ ሮማውያን፥ ፋርሳውያን፥ አርመናውያንና ግሪኮች ጋር አብረው የሚኖሩበት አንድ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች አገር እንደነበር ከላይ በቀረበው የ517-535 የይሁዳውያን ጦርነት ታሪክ ተመልክቷል። እንዲሁም በዘመኑ ከመካ በስተሰሜን በሚገኘው የየትሪብ (የመዲና) የአአሲስ ተምር ዛፍ ምርትና ንግድ አገር አዋማዊ አረቦችና የአሪት ሃይማኖት የሚከተሉ ይሁዳውያን ሰፋሪዎች በእርሻ ኢኮኖሚ ተሰማርተው በአንድነት ይኖሩበት እንደነበር የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሰተምራል።

በተጠቀሰው ዘመንና ሥርዓት በመካው የቁረይሽ አረቦች የንግድ፥ የጣአትና የባሪያ አሳዳሪው ጎብረተሰብና ከተሜ-መንግሥት ግን ከኢትዮጵያውያን ሰፋሪ ነጋዴዎች፥ ሙያተኞች፥ አስተማሪዎች፥ ወታደሮችና ባሮች በስተቀር ሌላ የታወቁ የውጭ አገር ሕዝቦችና ሃይማኖቶች እንደነበሩ በግልፅ የሚያሳይ የታሪክ መረጃና ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።[78]

በሌላ በኩል አረቦች ከጥንት ጀምሮ በዘልማድ «አልሀበሻ» ብለው በወል የሚጠሩዋቸው ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ መስኮች፥ መንገዶችና ደረጃዎች የመካው ከተሜ-ጎብረተሰብና መንግሥት ውስጣዊ አባላትና አካላት እንደነበሩ በዝርዝር የሚያሳዩ ብዙ የሰው፥ የቋንቋ፥ የሰነድና የባህል መረጃዎችና ማስረጃዎች አሉ።

ከሁሉም በላይና በፊት በዚህ ወቅትና ጉዳይ ከ610 እስከ 632 ድረስ በ23 ዓመታት ውስጥ በመካና በመዲና ከፈጣሪው አላህ በመልአኩ ጅብሪል «ቅዱስ ገብርኤል» አንደበት ለነቢዩ መሐመድ በአረብኛ ቋንቋ የተገለጸው ቅዱስ ቁርአን የዘመኑን ታላላቅ የይሁዳዊ፥ የግሪክ፥ የፋርስና የላቲን ዓለማቀፋዊ ቋንቋዎችን ጨምሮ ከየትኛውም ሌላ ቋንቋ የበለጠ በኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋ ተገልጿል።[79] ይህም ነቢዩ መሐመድ ከአረብኛ የእናት ቋንቋው ቀጥሎ በመካ ከተማው ከኢትዮጵያውያን ሰፋሪ ነጋዴዎች፥ ሙያተኞች፥ ወታደሮችና ባሮች

[77] Trimingaham, Islam in Ethiopia, p.44.
[78] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 3, 5, 8-9.
[79] ቅዱስ ቁርአን ያመርኛ ትርጉም ገጽ 11።

ጋር አብሮ በመኖርና በመነጋገር የኢትዮጵያን የግዕዝ ቋንቋ ደህና አድርጎ ያውቅ እንደነበር ይጠቁማል።

በእስልምና ምሥረታና ግስጋሴ የኢትዮጵያውያን ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ

የታሪክ መረጃ ምንጮች

በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በታላቁ የእስልምና ሃይማኖት ክስተት፥ ዕድገትና መስፋፋት ዘመን በሃይማኖቱ መሥራች ነቢዩ ሙሐመድና በኢትዮጵያውያን ደጋጌዎቹ መካከል በእምነት፥ በባህል፥ በቋንቋ፥ በሃይማኖትና በተግባር የተፈጠረውን የትብብር ታሪክ ለዓለምና ለትውልድ መዝግቦው በማቆየት ባለውለታ የሆኑት የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች በከፊል የሚከተሉት ናቸው፥[80]

ከእነዚህ ባለውለታ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች አንዱና የመጀመሪያው በ712 የሞተ፥ የነቢዩ ሙሐመድ ቤተዘመድና የካሊፋ አቡበክር (632-634) እህት አስማ ልጅ ኡርዋህ ዙቤይር (Urwah Zubayr) ለኡማያዱ ካሊፋ ለአብድ አልማሊክ (685-705) በጻፈው ደብዳቤ ነቢዩ ሙሐመድ የመጀመሪያ ሙስሊም ተከታዮቹ በእምነት ምክንያት በመካ የቁረይሽ ባለሥልጣኖች እጅ መከራና ሥቃይ ስለደረሰባቸው ሰላምና ፍትሕ ወዳለበት ወደ ኢትዮጵያዊው (ሀበሻው) ንጉሥ ነጃሺ አገር በጊዜያዊ ስደት ሂዱ ብሎ እንዳዘዛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፉ አረጋግጧል።[81] በተጠቀሰው ደብዳቤ፥ ኡርዋህ በዘመኑ የኢትዮጵያ አገር ለቁረይሽ አረቦች ታላቅ ሀብት፥ ሰላምና የሥራ ዕድል ያለበት ገነት አንደነበር ጨምሮ አስታውቋል።

በ768 የሞተው ኢብን ኢስሓቅ የነቢዩ ሙሐመድን የሕይወት ታሪክ፥ በ822 የሞተው አልዋቂዲ የነቢዩ ሙሐመድን ዘመቻዎች ታሪክ፥ በ833 የሞተው ኢብን ሂሻም የነቢዩ ሙሐመድን የሕይወት ታሪክ፥ በ845 የሞተው ኢብን ሰይድ የነቢዩን ተከታዮች የሕይወት ታሪክ፥ በ870 የሞተው አልቡኻሪ የነቢዩን ሀዲሶች ማለትም ምርጥ ትውፊታዊ ንግግሮችና አባባሎች፥ በ922 የሞተው አልጣባሪ የነቢዩን ዜና መዋዕሎች፥ በ1234 የሞተው ኢብን አልአጢሂር የነቢዩን ተከታዮች የሕይወት ታሪክ፥ እንዲሁም በ1449 የሞተው የግብፁ የእስላም ሼኽና የካይሮ ዋና ቃዲ ኢብን ሐጀር የነቢዩን ተከታዮች የሕይወት ታሪክ አስመልክተው በየበኩላቸውና በየዘመናቸው ባቀረቧ

[80] Watt, Muhammad at Mecca, pp. XI-XXI; Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 107-116.

[81] Ibis., Muhammad at Mecca, pp. 100-101.

ቸው ዘገባዎች፥ በ610-661 የእስልምና ሃይማኖት ክስተት፥ ዕድገትና መስፋፋት ዘመን ከአረቢያ እስከ ንጉሠ ነገሥት ድረስ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ መደቦችና ደረጃዎች የነበሩ ኢትዮጵያውያን የበታቸ፥ የጸታቸ፥ የዕድሜ፥ የቋንቋና የሙያ ልዩነት ሳያግዳቸው በመካ፥ በአክሱም፥ በመዲና፥ በፍልስጤም፥ በሶርያ፥ በግብፅ፥ በአርመን፥ በኢራቅና በፋርስ በነቢዩ ሙሐመድና በመጀመሪያ አራት ወራሽ ካሊፋዎቹ አቡበክር (632-634)፥ ዑመር፥ (634-644)፥ ዑስማን (644- 656) እና ዓሊ (656-661) ትምህርትና አመራር በተግራሪ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ላይ ለሃይማኖቱ ፈጣን ማዕከላዊ ድልና ዕድገት በፖለቲካ፥ በዲፕሎማሲ፥ በትምህርት፥ በሥራ፥ በድርጅትና በትጥቅ ከፍተኛ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ አንዳደረጉ በታላቅ አድናቆት መዝግበዋል።

በተጨማሪም በኋላ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከተነሱ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች በተለይ ኢብን አልጀውዚ (1116-1200)፥ አልሱዩጢ (1402-1515) እና በ1583 የሞተው ሙሐመድ አልባቂ በአንድ ላይ በአራት ምዕተ ዓመታት ዘመን ውስጥ (1116-1583) ከላይ የተጠቀሱ ቀዳሚ የመረጃ ምንጮችን መሠረት አድርገው (1) *Ibn al-Jawzi, Tanwir al Gabash fi fadl al Sudan wal Habash, (2) Al Suyati, Rafshain, and (3) Al Bukhari, al-Tiraz al-Manqush fi Mahasin al-Hubush* በተሰኙ ርዕሶች ባዘጋጁት መጻሕፍት ከነቢዩ ሙሐመድና ከመጀመሪያ አራት ወራሽ ካሊፋዎቹ ጋር ተሰልፈው ለእስልምና ሃይማኖት ድልና ዓለማዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉትና በሙስሊሙ ዓለም ታሪክ በታላቅ ክብር ከሚታወሱ ዕውቅ ኢትዮጵያውያን መካከል ከዚህ በታች ዝቅ ብሎ የሚቀርቡ ብዙ ባለታሪኮችን ስምና ታሪክ በወግ መዝግበዋል።[82]

የእስልምና ዓለም አቀፋዊ ክስተትና ዕድገት (610-661)

በ610 በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በመካ ጥንታዊ የእስማኤል ምንጭ፥ የአብርሃም መቅደስና የግዳጅ ከተማ፥ የቁረይሽ አረብ ተወላጅና የአርባ ዓመት ጎልማሳው ሙሐመድ አብደላ ከፈጣሪው አምላክ - አላህ በወረደ ቅዱስ ቁርዓንና በመልአክ ገብርኤል አንደበት በተገለፀው መለኮታዊ ራዕይ ለሰው ልጆች አዲስ ሃይማኖት ከአንዱ እግዚአብሔር ተቀብያለሁ በማለት የከተማ ነዋሪዎቹን አዋማዊ ሃይማኖትና በአረጣና በወለድ ትርፍ የተመሠረተ የንግድ ኢኮኖሚ ሥርዓት በማውገዝ ስብከቱን ጀመረ። የሃይማኖቱ መሠረተ ትምህርት I «የአላህ አንድነትንና የመሐመድ መልእክተኝነትን ማመን፥ ጸሎት

[82] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 107-116

(ሰላት) መስገድ፥ ምጽዋት (ዘካት) መስጠት፥ የረመዳንን ወር መጾም፥ ሐጅ መድረስ አቅም ካለ» የሚል ነው። ይህ ታላቅ የነቢዩ ሙሐመድ መለኮታዊ ትምህርትና ስብከት በመካ ኃይለኛ ባለሥልጣኖችና ከበርቴ ነጋዴዎች ዘንድ በነቢዩና በተከታዮቹ ላይ ብርቱ ቁጣ፥ ተቃውሞና መከራ ስላስከተለ ነቢዩ በ615-16 በሁለት ተከታታይ ቡድኖች በድምሩ በ150 የሚቆጠሩና «ሙስሊሞች» ማለትም «እውነተኛ አማኞች» ተብለው የሚጠሩ ተከታዮቹን በአማቹ ዑትማን ቢን አፋንና በወንድሙ ልጅ ጀዕፈር አቡጣሊብ መሪነት «ጌሳችንን ለመከላከል አላህ ብርታቱን እስከሰጠን ድረስ ወደ ሀበሻ አገር ሄዳችሁ እዚያው ቆዩ። የሀቀኞችና የጻድቃን አገር ናት። ንጉሷም ፍርድና ፍትሕ አዋቂና አስተዋይ ስለሆነ በእርሱ ዘንድ ማንም አይበደልምና አትሰጉ»[83] በማለት በአፍሪካ ምድር ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ አስሓማ (600-630) ቤተ መንግሥት በስደት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲሄዱ አዘዛቸው።

የነቢዩ ሙሐመድ አሳዳጊ ሞዝሊት የነበረችው በረካ ኡም አይማንን ጨምሮ ከስደተኛ ሙስሊሞቹ ሀያ አንዱ የመጀመሪያ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ነበሩ።[84] በአጼ አስሓማ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥት ለሁሉም ስደተኛ ሙስሊሞች የጥገኝነት መብት እንዲሁም ለነቢዩ ሃይማኖትና ትምህርት በዓለም ላይ የመጀመሪያውን እውቅና ሰጠ። በመሆኑም በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ የእስልምና ሃይማኖት ከመካ መካነ ልደቱ ቀጥሎ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ አገርና ቤተ መንግሥት በይፋ ተሰበከ። ከስደተኛ ሙስሊሞቹ አብዛኞቹ በጀዕፈር አቡጣሊብ መሪነት እስከ 631 ድረስ ለ15 ዓመታት በኢትዮጵያ ከንብረተሰቡ ጋር በባህልና በሃይማኖት ተቀላቅለው ኖሩ። ዑትማን ቢን አፋንን ጨምሮ ብዙዎቹ ደግሞ በፈቃዳቸው ወደ አገራቸው ተመልሰው ከነቢዩ ጋር በተግራራ ኃይሎች ላይ በመካና በመዲና የተሳካ የፖለቲካና የትጥቅ ትግል በማካሄድ ሃይማኖቱን በአገር ውስጥ አጠናክሩ። ከውድቀትና ከመጥፋት አደጋ በቆራጥነት አዳኑ።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮቹን በ615-616 በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከላካቸው በኋላ ራሱ ከመካ በደቡብ ምስራቅ በ110 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘውና ጣይፍ በተሰኘው ታዋቂ የንግድና የወይን እርሻ አገር ሃይማኖቱን ለማስፋፋት ያልተሳካ ሙከራ አደረገ። በወይን ምርትና ንግድ የታወቁ የጣይፍ አዋማዊ

[83] ሐሰን ዑመር አብደ «ሐበሻ ማንው?» ፥ ጣቢያ ቅ 5 ቁ 4 (1989)፥ ገጽ 32

[84] Earlich, Ethiopia and the Middle East, p. 10.

አረቦች የነቢዩን መለኮታዊ ሃይማኖት ውግዘና ውድቅ አደረጉ። ራሱንም ከአገራቸው አባረሩት።[85]

በመጨረሻ፥ በመስከረም 622 ነቢዩ ሙሐመድ በመካ ከቁረይሽ ተግራሪ ኃይሎች በድብቅ የግመል ገዛ አምልጦ ከመካ በስተሰሜን በ430 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘውና አረቦችና ይሁዳውያን በጉርብትና ወደሚኖሩበትና የትሪብ ተብሎ ወደሚጠራው የተምር እርሻ አገር በስደት ገባ።[86] የትሪብ አረቦችና ይሁዳውያን ስደተኛውን ነቢይ አስተማሪና መሪ አድርገው በሰልፍ በደስታ ተቀበሉት። የትሪብ የሚለው የአገራቸው ስም አሁን «መዲና» ማለትም «የነቢይ ከተማ» ተብሎ ተለወጠ። ቡጢጫማሪም ነቢዩ ሙሐመድ ከመካ በስደት ወደ የትሪብ-መዲና የገባበት መስከረም 22 ቀን የሙስሊሙ ታሪክ መነሻ ዘመን «ሂጅራ» ተብሎ ተሰየመ።

ነቢዩ ሙሐመድ በስደት ከመካ ወደ መዲና እንደደረሰ ተከታዮቹ የሚተዳደሩበትን ባለ47 አንቀጽ «የመዲና ሕገ መንግሥት» መሠረተ።[87] በሕገ መንግሥቱም መሠረት ነቢዩ ሙሐመድ በመዲና ከተማ የሙስሊምና የይሁዲ ተከታዮቹን በጎበረት አስተባብሮ በ624[88] ገደማ «ኡማ» የተሰኘውን የሙስሊሞች መንግሥትና ጎብረተሰብ በይፋ በማቋቋም የመንግሥትን ሥልጣን በቀጥታ ያዘ። ነገር ግን በኋላ የመዲና ይሁዳውያን የነቢዩ ሙሐመድን ነብይነት ውድቅ ስለአደረጉ እርሱም በአጸፋ እርምጃ ከአገር አስወጣቸው።

በቅዱስ ቁርኣንና በ624 የኡማ ሕገ መንግሥት ጥምር መሠረቶችና መሣሪያዎች፥ ነቢዩ ሙሐመድ በመካና በመዲና ተግራሪ ኃይሎች ላይ ሁለአቀፍ የሃይማኖት፥ የዲፕሎማሲ፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የትጥቅ ግፊቶችንና እርምጃዎችን በመጠቀም በጥር 630 መካንና መዲናን የመንግሥቱ መንትያ ከተሞችና ክፍለ ግዛቶች አደረጋቸው።[89] የመካን ጥንታዊና አዋማዊ የጣኦት መቅደስንም ደግሞ ቀድሶ ወደ ታላቁ የመካ መስጊድ[90] ቀየረው።

ከሥርዓት፥ ከፖሊሲ፥ ከተሞርና ከጊዜ አንፃር ሲታይ፥ ነቢዩ ሙሐመድ በመካና በመዲና ከተሞችና አካባቢዎች የአረብና የይሁዲ ተግራሪ ኃይሎችን በልዩ ልዩ መስክች፥ መንገዶችና መሣሪያዎች

[85] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 138-140.

[86] Ibid., p. ነ5ነ.

[87] Ibid., Muhammad at Medina, (1956), pp. 221-28.

[88] Ibid., 225-228.

[89] Ibid., pp. 40-69.

[90] Ibid., p. 69.

ሁሉንም አንድ በአንድ ተቆጣጥሮ በጥር 630 በአንድ እስላማዊ የኡማ መንግሥትና ጎብረተሰብ ሥር ባዋላቸው ጊዜ በቅዱስ ቁርአን ትምህርት መሠረት በ610 የጀመረው እስላማዊ የሃይማኖት፥ የመንግሥትና ማኅበራዊ አመፅና ለውጥ ወደ አንድ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ደረሰ ለማለት ይቻላል።

በዚህ አኳያ ነቢዩ ሙሐመድ ከ610 እስከ 632 ድረስ በ23 ዓመታት ውስጥ በመካና በመዲና በሁለቱ የአረብና የይሁዲ ማኅበረ ሰቦች ዘንድ በቅዱስ ቁርአን ትምህርት መሠረት ያስተማረውንና ያደራጀውን ሁለአቀፍ እስላማዊ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የባህል፥ የሕግና ማኅበራዊ ሥርዓት ከ632 እስከ 661 ድረስ በሦስት አሥርታት የነቢዩ አራቱ ቤተዘመድና ወራሽ ካሊፋዎች አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑትማንና ዓሊ በሁለቱ አኅጉራት የእስያና የአፍሪካ አህጉራት የዘመኑ ኃያላን የነበሩ የፋርሳውያንና የሮማውያን የአፄ መንግሥታትን ደምስሰው በምትካቸው አንድ እስላማዊ የዓለም መንግሥትና ሃይማኖት መሠረቱ።

በዚህ ታላቅ ዓለማቀፋዊ የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት ግምባታ ፖሊሲና ተግባር በዓለም ላይ ከቁረይሽ አረብ መሪዎችና አስተማሪዎች ጎንና ግምባር የቆሙ ደጋፊዎች የኢትዮጵያ መንግሥትና ተወላጆች ብቻ እንደሆኑ የታሪኩ ባለቤት የሆኑት አረቦች ራሳቸው ለታሪክና ለትውልድ በይፋ አስታውቀዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ነቢዩ ሙሐመድ ራሱ ለተከታዮቹ «ኢትዮጵያውያንን ሳይነኩዋችሁ አትንኩዋቸው፥ በግድ የማስለም ዘመቻ አታውጁባቸው» ብሎ የፖሊሲና የተግባር መመሪያ እንደ ሰጣቸው ተከታዮቹ ጨምረው አስታውቀዋል። እንዲያውም የተጠቀሱ ተከታዮች ከነቢዩና ከወራሽ ካሊፋዎቹ ጎን ተሰልፈው ከ610 እስከ 661 ድረስ ለሃይማኖቱ ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት ታሪካዊ አስተዋፅኦ ያደረጉ ኢትዮጵያውያንን ስምና ሥራ በወግ ጽፈው ለታሪክና ለትውልድ እንደሚከተለው አቆይተዋል።

የኢትዮጵያውያን ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ በእስልምና ምሥረታ

አረቦች «የሀበሾችና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፥ ዋዜባና አድባ የሚሉዋቸው የኢትዮጵያ የጦንቱ አዋማዊ ያገር መሪዎች በዘመነ ክርስትና በግምት ከሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ እስከ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በየመን ደቡብ አረቢያ የነበራቸውን የባሕር ማዶ ግዛት ታሪክ የሳባ-ሂሚያር አረቦች በቋንቋቸው በድንጋይ ላይ ዜና መዋዕሎች ቀርፀው ለታሪክና

ለትውልድ እንዳቆዩ በዚህ ጥናት ከላይ ተመልክቷል።

አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ የጽሑፍ መረጃ ባልተገኘበት የ550-1300 ዘመን፥ በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ የቁረይሽ አረቦች የኢትዮጵያ መንግሥትና ተወላጆች በግምት ከ610 እስከ 661 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ ከነቢዩ ሙሐመድና ካልጋወራሽ ካሊፋዎቹ አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑትማንና ዓሊ ጎን ተሰልፈው ለታላቁ የእስልምና ሃይማኖት ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት ጉልህ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ በማድረግ ሌላ ታሪክ በዓለም ደረጃ እንደሠሩ በሰነድ ቀርፀው ለታሪክና ለትውልድ እንደሚከተው አስታውቀዋል።

ከዚህ በታች በስም የቀረቡ ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች ከነቢዩ ሙሐመድና ከወራሽ ካሊፋዎቹ ጋር ተሰልፈው በእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ዘመን (610- 661) ለሃይማኖቱ ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት ተግባራዊ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ ያደረጉ ሰዎች ናቸው። የስማቸውና የታሪካቸው ዝርዝር የተገኘው ከላይ ከተጠቀሱ ጥንታዊ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ኡርዋህ ዘቤይር፥ ኢብን ኢስሓቅ፥ አልዋቂዲ፥ ኢብን ሂሻም፥ ኢብን ሰይድ፥ አጢታብን፥ አልአጢሂር፥ ኢብን ሐጀር፥ ኢብን አልጀውዚ፥ አልሱዩጢ፥ መሐመድ አልባቂና ሌሎችም በልዩ ልዩ ወቅቶችና መንገዶች ከቆዩዋቸው ሰነዶች በልዩ ልዩ ምሁራን ተለቅሞ ነው።

1. Baraka Umm Ayman በረካ ኡም አይማን የሐፃኑ ሙሐመድ አብደላ ኢትዮጵያዊት አሳዳጊ ሞግዚትና በኋላም የነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖት ተከታይ ሙስሊም ነበረች። በቅደም ተከተል በ875፥ በ989፥ በ1234፥ እና በ1277 የሞቱ ሙስሊም ኢብን ቁጠይባ፥ አጢሂርና ነዋዊ የተሰኙ የአረብ ታሪክ ጸሐፊዎች በየዘመናቸው እንዳረጋገጡት፥ በረካ ኡም አይማን ኢትዮጵያዊት ባሪያ ነበረች። ሌላ የታሪክ ምሁራን ደግሞ የነቢዩ ሙሐመድ አያት አብድአልሙጠሊብ በ543 ከየመን በመካ አካባቢ ዘመቻ ካካሄደው ከንጉሥ አብርሃ ክርስቲያን ሠራዊት በረካ ኡም አይማንን በምርኮ ይሁን በሌላ መንገድ እንደወሰዳት ጽፈዋል።[91]

ሐፃኑ ሙሐመድ ከነጋዴ አባቱ አብደላ አብድሙጣሊብና ከእናቱ አሚና ወህብ በ570 ተወለደ። ሙሐመድ ከመወለዱ በፊት ነጋዴ አባቱ ከሶሪያ ሲመጣ በመንገድ እያለ በመዲና ሞተ። በመሆኑም ሐፃኑ ሙሐመድ ለመጀመሪያ ስምንት ዓመታት በተጠቃሹ አያት ዘንድ አደገ። የስድስት ዓመት ሕፃን ሳለ በ576 እናቱም ሞተች። ከሁለት ዓመታት በኋላ አያቱም ሞተ። አሁን ወላጅ አልባው ሙሐመድ በነጋዴ አጎቱ አቡጣሊብ አብድአልሙጠሊብ ዘንድ አደገ። እናቱ አሚና

[91] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 107- 116; Erlich, Ethiopia and the Middle East, pp. 5- 10.

ሰትሞት የቤተሰቡ ኢትዮጵያዊት ባሪያ በረካ ኡም አይማን የሙሐመድ አሳዳጊ ሞግዚት ሆነች። በኋላ ባለውለታው ሙሐመድ ሞግዚት እናቱን ከባርነት አርነት አውጥቶ ዘይድ ለተባለው አበልጁ ዳራት።[92]

በ595 ሙሐመድ ራሱ በ25 ዓመቱ በመካ የአርባ ዓመት ዕድሜ ባልቴትና የራሱም ቀጣሪ የነበረችውን ነጋዴ ወይዘሮ ከድጃን አግብቶ ከሷም ዘይነብ፥ ሩቅያ፥ ኡም ኩልቱማና ፋጢማ የተሰኙ አራት ሴትና ቃሲም፥ አብደላና ጣሂር የተባሉ ሦስት ወንድ ልጆቹን ወለደ። በረካ ኡም አይማን ለሙሐመድ ሚስት ከድጃ አገልጋይ እንዲሁም ለተጠቃሽ ልጆቹም አሳዳጊ ሞግዚት ሆነች። በተጨማሪም በረካ ኡም አይማን የነቢዩ ሙሐመድን የእስልምና ሃይማኖት መጀመሪያ ከተቀበሉ ሙስሊሞች አንዲ ነበረች።

በመሆኑም፥ በ615-16 ከመካ ወደ ኢትዮጵያ ከተሰደዱ የነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች መካከል በረካ ኡም አይማንና ልጁ ሩቅያ አብረው ነበሩ። የነቢዩ አብዛኛዎቹ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ ከተሰደዱ በኋላ በ620 በመካ ሚስቱ ከድጃና አጎቱ አቡጣሊብ ተከታትለው በሞት ተለዩት። በ622፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ በመካ ከቁረይሽ ጠላቶቹ በሽሽት አምልጦ ራሱም ወደ መዲና ገባ። በረካ ኡም አይማን ከኢትዮጵያ ስደት ከተመለሰች በኋላ በመዲና ከነቢዩ ጋር እንደገና አብራ መኖር ጀመረች። በዚህ ጊዜ ሁሉ ነቢዩ በረካ ኡም አይማንን እንደወላጅ እናቱ አድርጎ ይወዳትና ይጠራት ነበር። ከነቢዩ ሞት በኋላ አልጋወራሽ ካሊፋዎቹ አቡበከርና ዑመር ለበረካ ኡም አይማን ተመሳሳይ እንክብካቤ ያደር ጉላት ነበር። እሷም የነቢዩን ብዙ ሀዲሶች ማለትም ምርጥ ትውፊታዊ ንግግሮች ለተከታዮቹ ታስረዳ እንደነበር ተጽፏል።

2. Bilal ibn Ribah <u>የሪባሕ ልጅ ቢላል</u> መዓዚኑ (610-644)፥ የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊዎች እንዳስታወቁት ሁሉ፥ በ610 በራዕይ የተገለፀለትን የነቢዩ ሙሐመድን መለኮታዊ የእስልምና ሃይማኖት የመጀመሪያው ደጋፊና ተከታይ ሚስቱ ከድጃ ስትሆን፥ ሁለተኛው አቡበከር የነቢዩ ሦስተኛይቱ ሚስት አይሻ አባትና የመጀመሪያው አልጋወራሽ ካሊፋ (632-634) እንደሆነ ተገልጿል። በአቡበከር አማካይነት የነቢዩ መሐመድ ትምህርትና ሃይማኖት ተከታይ ከሆኑ ሰዎች አንዱ ኢትዮጵያዊው ባሪያ የሪባሕ ልጅ ቢላል መዓዚኑ እንደሆነ ታውቋል።[93] በእነዚሁ ታሪክ ጸሐፊዎች ቃል መሠረት፥ ቢላል በመካ የአንድ የቁረይሽ ክበርቴ ባሪያ ነበር። ቢላል የነቢዩን እስላማዊ ትምህርትና ሃይማኖት መከተሉን በመቃወም አሳዳሪ ጌታው በክፉኛ እንደ ሚያሰቃየው የነቢዩ ተከታይ እዛውንቱ አቡበከር ይሰማል። ከዚያ በኋላ አቡበከር ቢላልን ከጌታው ገዝቶና አርነት አውጥቶ

[92] <u>Ibid</u>., "The Himyaritic Tihama", p. 114.
[93] Earlich, <u>Ethiopia and the Middle East</u>, p. 6.

ወደ ነቢዩ ይወሰደዋል። የእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ዘመንና ተግባር፥ «ቢላል አል-ሀበሻ» ማለትም ኢትዮጵያዊው ቢላል ከነቢዩ ታላላቅ የሃይማኖትና የጦር ባለሥልጣኖች አንዱ ሆነ። በመጀመሪያ ደረጃ ከሩቅ የሚሰማ ከፍተኛ ድምፅ ያለው ሰው ስለሆነ፥ ቢላል አል-ሀበሻ የመጀመሪያው የሙስሊሞች ሙዓዚን (አቃቤ ፀሎት) ለምዕመናን የስዓተ ስግደትን ጥሪ በድምፅ የሚያሰማ ታላፊ ሆነ። በተጨማሪም ሙዓዚኑ ቢላል ታላቅ የሃይማኖት ጦር አበጋዝ ሆነ። በዚህ ረገድና ተግባር ቢላል አል-ሀበሻ በካሊፋ ዑመር ዘመንና አመራር (634-644) እስልምናን በመላው መካከለኛው ምሥራቅና በግብፅ ያስፋፋው የሙስሊም ጦር ሠራዊት አንድ አርበኛ ወታደር በመሆን ሲዋጋና ሲያዋጋ በ642 በደማስቆ ሶርያ ሞተ። መካነ መቃብሩም እስከ ዛሬ ድረስ በደማስቆ የሙስሊሙ ዓለም አንድ ቅዱስ ሥፍራ ሆኖ እንደሚገኝ ታውቋል።[94]

3. The Negash: <u>አጼ ነጃሺ አስሓማ</u> የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፥ ከላይ እንደተጠቀሰው፥ አጼ ነጃሺ አስሓማ (600-630) በነቢዩ ሙሐመድ ፈቃድና ትእዛዝ በ615-616 ከመካ አረቢያ በስደት ወደ አገሩ ለገቡ የመጀመሪያ ሙስሊም ስደተኞች የጥገኝነትና የሃይማኖት ነፃነት መብት እንዲሁም ለእስልምና ሃይማኖት በዓለም ላይ የመጀመሪያውን የእምነትና የፖለቲካ እውቅና የሰጠው ኢትዮጵያዊ አስተዋይ የአገርና የመንግሥት መሪ ነው። የዘመኑ የአረብ ጸሐፊዎች በ628 በነቢዩ የደብዳቤ ጥሪ መሠረት አጼ አስሓማ ወደ እስልምና ሃይማኖት መግባቱንና በ630 በሞተም ጊዜ ነቢዩ ሰምቶ ለሙስሊም ሙታን የሚደረገውን ፀሎተ ቅዳሴ በመዲና እንዳደረገለት ጽፈዋል።

4. Luqman the Wise: <u>ጠቢቡ ሉቅማን</u> በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን (610-632) በመካ አረቢያ አንድ ወደ ከፍተኛ የትምህርትና የጥበብ ደረጃ የደረሰ ብሎም ለእስልምና ሃይማኖት ድልና ዕድገት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እንደሆነ ተገልጿል።[95]

ነቢዩ ሙሐመድ በሀዲስ ቃሉ ማለትም በትውፊታዊ ቃሉ፥ ሦስቱ ማለትም ጠቢቡ ሉቅማን፥ ነጃሺ አስሓማና ቢላል ሙአዚኑ ከእኛ ጋር መንግሥተ ሰማያት የሚወርሱ «ሱዳኖች» ማለትም ሀበሾች (ኢትዮጵያውያን) ስለሆኑ እንደወንድሞቻችሁ አድርጋችሁ ተቀበሉዋቸው ብሎ ለአረብ ሙስሊም ወገኖቹ እንዳስተማራቸው የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊ ኢብን አባስ[96] ጽፏል።

የነቢዩ ሙሐመድን «ሱዳን» የሚለውን ቃል ግንዛቤና ትርጉም በሚመለከት፥ ታዋቂ የጥንቱ አረብ ሙስሊም ምሁራን እንደሚያስተ

[94] <u>Ibid</u>., p. 10.
[95] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 108-109, 117.
[96] <u>Ibid</u>., p. 108.

ምሩት፥ «ሱዳን» እና «ሀበሻ» ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የአረቦቹ ሁለት ተለዋጭ ስሞች ናቸው።[97] ለምሳሌ በ1450 የሞተው የግብፁ ታዋቂ ምሁር ኢብን ሀጀር የእስልምና ሼክና የካይሮ ዋና ቃዲ ከእሱ በፊት በ870 በሞተው አልቡኻሪ የተጻፈውን የአቢዩ ሙሐመድን የትውፊት ቃልና ትምህርት ሲያስረዳ እንዳለው፥ በዘመኑ የኢትዮጵያውያን ምድር በአረቢያ ከየመን በደቡባዊ ምዕራብ በኩል የሚገኝ አገርና መንግሥት ነበር። የአገሩም ሕዝቦች የተለያዩ «የሱዳን» ዘሮች ናቸው። በአገሩ የሚኖሩ ሁሉም የሱዳን ሕዝቦች ለሀበሾቹ ንጉሥ ተገዢ ነበሉ። ንጉሡም በጥንት ዘመን «ነጃሺ» በ15ኛው ምዕተ ዓመት በሼኽ ቃዲ ኢብን ሀጀር ጊዜ ግን «ሐጼ» ተብሎ ይጠራ እንደነበር በታሪካዊ መረጃና ትንተና አስረድቷል።[98]

5. Mihja ibn Saleh: የሳልህ ልጅ ሚህጃ፥ በ610 ነቢዩ ሙሐመድ ከአላህ የእስልምና ሃይማኖት ራዕይ ከተቀበለ በኋላ ዑመር ኢብን አልኸጣብ ዳግማዊ ካሊፋ (634-644) እርነት ያወጣው ኢትዮጵያዊ ባሪያና ከነቢዩ መጀመሪያ ሙስሊም ተከታዮቹ አንዱ ነበር። ሚህጃ በ615-16 ነቢዩ ሙሐመድ በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከላካቸው ሙስሊሞች አንዱ ሲሆን በ624 በበድር ጦር ሜዳ ላይ በአዋጣዊ ቁረይሾችና በነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደውና ሙስሊሞቹ የመጀመሪያ ድል በተቀዳጁበት ታሪካዊ ጦርነት የመጀመሪያው ሙስሊም ሰማዕት ሆነ።[99]

6. Saleh Shukran ibn Ali: የዐሊ ልጅ ሳልህ ሹቅራን፥ ሳልህ ሹቅራን ኢብን ዐሊ ነቢዩ ሙሐመድ ከአንድ የቁረይሽ ከበርቴ ገዝቶ አርነት ያወጣው ኢትዮጵያዊ ባሪያ ነበር። በ624 የበድር ጦርነት ጊዜ ሳልህ ሹቅራን የጠላት ምርኮኞችና ንብረት ጠባቂ ሹም ሆነ።

7. Nafi Abu Bakra ibn Masruh: የማዝሩህ ልጅ ናፌ አቡበክራ፥ ናፌ አቡበክራ ማዝሩህ አርነት ወጥተው የነቢዩ ሙሐመድ ከፍተኛ ተከታዮችና ባለሟሎች ከሆኑ ብዙ የቀድሞ ኢትዮጵያዊ ባሮች አንዱ ነበር። አርጅቶ በ675 ከመሞቱ በፊት ናፌ አቡበክራ ከነቢዩ ሀዲሶች ማለትም ትውፊታዊ ንግግሮችና አባባሎች 132ቱን ለታሪክና ለትውልድ በቃሉ ያሳለፈ ባለውለታ ነው።

8. Aslum al-Habashi: አስሉም አል-ሀበሺ (ሀበሻው አስሉም) አስሉም አልሀበሽ በመዲና ለአንድ ይሁዳዊ ባሪያ የነበረ ኢትዮጵያዊ ነው። የነቢዩ ሙሐመድ ተከታይ ወታደር ከሆነ በኋላ በ629 በከይበር በይሁዳውያንና በነቢዩ ተከታይ ሙስሊሞች መካከል በተካሄደው ጦርነት ሞቷል።

[97] Ibid., p. 109.
[98] Ibid., pp. 108-109.
[99] Ibid., p. 111.

9. Khalid ibn Alhawari al Sabachi: ካልድ ኢብን አልሀዋሪ አልሰበኪ፥ ከነቢዩ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ነበር።

10. Alaswas al Habash: አልአስዋስ አልሀበሽ ከነቢዩ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ እንደነበር ተመልክቷል።

11. Dhu Mihdem, Dhu Muhammas, Dhu Mukhbir, Dhu Dawjayn, and Dhu Munahib: ዙ ሚህደም፥ ዙ ሙሐመስ፥ ዙ ሙክቢር፥ ዙ ዘውጃይንና ዙ ሙናህብ፥ ዙ የተሰኘ የአረብ ማዕረግ ያላቸው አምስት የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሹማምንቶች ነበሩ።

12. Asim al-Habashi: አሲም አልሀበሽ፥ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ነበር።

13. Nayil al-Habashi: ናይል አልሀበሽ፥ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ።

14. Abu 'lQit al-Habashi: አቡ ልቂጥ አልሃበሽ፥ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታይ ነበር።

15. Yassar al-Habashi: ያሣር አልሀበሽ፥ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታይና የመስጊድ ፅዳት ሠራተኛ ነበር።

16. Wahshi al-Habashi: ዋሕሽ አልሀበሽ፥ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታይና በጦር ውርወራና ውጊያ ዕውቅ ወታደር ነበር።

17. Bulaha al-Habashiya: ቡለህ አልሀበሺያ፥ የነቢዩ ሙሐመድ ሚስት የኡም ሀቢባ ኢትዮጵያዊት ሙስሊም ሠራተኛ ነበረች። ኡም ሀቢባ ነቢዩ ሙሐመድንና የእስልምና ሃይማኖቱን ለማጥፋት ያልተሳካ ሙከራ ያደረገ የቁረይሽ መንግሥት መሪ አቡሱፍያን ልጅ ናት። ከአዋጣዊ አባቷ አቡሱፍያ ተለይታ የነቢዩ ሙሐመድን የእስልምና ትምህርትና ሃይማኖት ከተቀበለች በኋላ ኡም ሀቢባ በታዋቂ መስፍንና ሙስሊም ባልዋ ዑበይ ዑብደላ ጃህሽ ጋር በ615-16 በስደት ወደ ኢትዮጵያ ሄደች። ነገር ግን በኢትዮጵያ ባልዋ ዑበይ ዑብደላ ጃህሽ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የእስልምና ሃይማኖቱን ትቶ በፊቃዱ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ገባ። በመሆኑም ኡም ሀቢባ ከዑበይ ዑብደላ ጃህሽ ጋር ለረጅም ጊዜ የመሠረተችውን የጋብቻ ትዳር አፍርሳ የእስልምና ሃይማኖት ስደተኛ እንደሆነች ቆየች።

በመዲና ነቢዩ ሙሐመድ በኡም ሀቢባ የአቡሱፍያን ልጅ በሃይማኖት ልዩነት ከመስፍን ባልዋ ጋር የመሠረተችውን የረጅም ጊዜ ጋብቻ አፍርሳ መለያየቷን እንደሰማ በአክሱም የአጎቱ ልጅና የስደተኛ ተከታዮቹ መሪ ጃዕፈር አቡጣሊብንና የኢትዮጵያ አፄ አስሓማን በእርሱና በባልቴቷ ሀቢባ መካከል ሥርዓተ ጋብቻ ለመፈጸም አማላጆች እንዲ ሆኑለት ጠየቃቸው።[100] ኡም ሀቢባም በአማርኛቹ አስተባባሪነት ከነቢዩ

[100] Earlich, Ethiopian and the Middle East, p. 80.

የቀረበላትን የጋብቻ ጥያቄ በደስታ ተቀበለችው። ንጉሡም ነቢዩ በጠየቀው መሠረት ኡም ሀቢባን እንደአገሩ ባህል 400 ዲናር ጥሎሽ ከፍሎ ዳራት።[101]

በመሆኑም በ628 በመዲና አረቢያ ነቢዩ ሙሐመድና ኡም ሀቢባ አቡ ሱፍያን ሥርዓተ ጋብቻ ፈጸሙ።[102] ስደተኛዋ ኡም ሀቢብ አቡሱፍያን ከኢትዮጵያ ወደ መዲና ለጋብቻ ስትሄድ ኢትዮጵያዊት ቡለህ አልሀበሺያን እንደሠራተኛዋ ይዛ ሄደች።[103] በዚህ መንገድ ቡለህ አልሀበሺያ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ታዋቂ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ሆነች።

በተጨማሪም በዚህ በሙሐመድና ኡም ሀቢባ የፖለቲካ ጋብቻ ምክንያት በወቅቱ (624-630) የቁረይሽ አዋማዊ መንግሥት መሪ የነበረው የኡም ሀቢባ አዋማዊና ተቃዋሚ አባት አቡሱፍያን በልጁ ብርቱ ግፊት በአዋማዊ የቁረይሽ ሕዝብና መንግሥት ላይ በምሥጢር ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር ሆኖ ተገኘ።[104] በመሆኑም በመጨረሻም በጥር 630 ነቢዩ ሙሐመድ መካን አለውጊያ ያዘ።[105] መካ በተያዘ ቀን አቡሱፍያን በመዲና በነቢዩ ሠፈር ነበር።

18. Barira al-Habashiya: በረራ አልሀበሺያ፥ በነቢዩ ሙሐመድ ሦስተኛይቱ ሚስትና የቀዳማዊ ካሊፍ አቡበከር ልጅ አይሻ ብርቱ ድጋፍ ራሷን ከአንድ የቁረይሽ አሳዳሪ ጌታዋ አርነት አውጥታ ከዕውቅ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንድዋ ሆነች።

19. Shagira al-Habashiya: ሸግራ አልሀበሺያ፥ ከአንድ የቁረይሽ አሳዳሪ ጌታዋ አርነት ወጥታ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ሆነች።

20. Nabgha al-Habashiya: ነብጋ አልሀበሺያ፥ የነቢዩ ሙሐመድ አጎት አቡጣሊብ ልጅ ኡም ሀኒ ባሪያ የነበረችና አርነት ወጥታ ከነቢዩ ዕውቅ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ለመሆን የበቃች ሴት ናት።

21. Aslum al-Bujawi: አስሉም አልቡጃዊ፥ ዳግማዊ ካሊፋ ዑመር (634-644) ከባርነት አርነት አውጥቶት በ114 ዓመት ዕድሜው በ702 የሞተ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው።

22. Ayman al-Habashi al-Makki: አይማን አልሀበሺ አልመኪ፥ አንድ ከባርነት አርነት የወጣ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው።

23. Ata ibn Abi Ribah Aslum al Nakki: አጣ ኢብን አቢ ረባህ

[101] Ibid.,
[102] Watt, Muhammad at Medina, p. 396,
[103] Norris, "The Himyaritic Tihama", p. 115.
[104] Watt, Muhammad at Medina, pp. 63-64.
[105] Ibid., pp. 65-70.

አስሉም አልናቂቂ አንድ ሌላ ከባርነት የወጣ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው።

በኢትዮጵያ የ615-631 የነቢዩ ሙሐመድን የሙስሊም ስደተኞች ሕይወትና ሥራ በሚመለከት፥ በመጋቢት 1904 በአዲስ አበባ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የቱርክ የመጀመሪያ ልዑካን ቡድን መሪ የመጣው ሌ/ጄ ስድቅ አልሙአየዩ አልዐዝም በዓመቱ *Habesh Siyahetnamehsi* በሚል ርዕስ በቱርክኛ ቋንቋ ጽፎ በ1908 *Rihlat al Habasha (The Ethiopian Voyage)* ገዙ በሚል ስም ወደ አረብኛ ቋንቋ በተተረጎመው ተወዳጅ መጽሐፍ የጥንት አረብ ሙስሊም ጸሐፊዎችን ሰነዶች በስፋትና ጥልቀት መርምሮ ብዙ አዲስና ጠቃሚ መረጃዎችን እንዳቀረበ በቅርቡ በአንድ ምሁራዊ ጥናት ተገልጿል።[106]

የቱርኩ ጄኔራል በአዲስ አበባ ቆይታው ውቅት ከሁሉ በላይ የአገራቸውን ታሪክ በወግ ለማያውቁ ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የአገራቸው የጥንት መንግሥትና ሕዝብ ነቢዩ ሙሐመድን በእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ተግባር እንዴት በልዩ ልዩ ሥራዎች፥ መንገዶችና መሣሪያዎች እንደረዱት ለመጀመሪያ ጊዜ በማሳወቅ በእጅጉ አስደነቃቸው።[107]

ሁለተኛ፥ የጄኔራል አልዐዝም ጥናት በ615-631 በኢትዮጵያ ከነበሩና በድምሩ በ150 ከሚቆጠሩ የነቢዩ ሙሐመድ ሙስሊም ስደተኞች ከበረካ ኡም አይማን ጋር አምስት ሴቶችን ጨምሮ ሃያ አንድ በዘርና በትውልድ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ያሳያል። በተጨማሪም የተባሉ ኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በ615-631 በኢትዮጵያ በነበሩበት ዘመን ብዙ ኢትዮጵያውያንን ወደ እስልምና ሃይማኖት እንደመለሱ የጄኔራሉ ጥናት ጨምሮ ያመለክታል።[108]

ሦስተኛ፥ በዚህ ረገድና ተግባር በ631 በነቢዩ ሙሐመድ ወንድም ልጅ በጻዕፈር ሙጠሊብ መሪነት ስደተኞቹ ወደ አረቢያ በተመለሱ ጊዜ ከተጠቀሱት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ነቢዩን ለመርዳት 72 ወዶ ዘማቶች በአጼ አስሓማ ወንድም ልጅ በዙ ማህጃር አልሀበሽ፥ የቀድሞ ኢትዮጵያዊ የአረቢያ ንጉሥ አብርሃ (535-558) የልጅ ልጅ አብርሃ ቢን ሰባህ አልሀበሽና በአንድ ዕውቅ የታሪክና የቅኔ ባለሙያ በዙ ማህጃር አልሀበሽ አዝማችነት ከስደት ተመላሾች ጋር አብረው እንደሄዱ ተገልጿል።[109]

[106] Earlich, Ethiopia and The Middle East, pp. 10, 79-82.
[107] Ibid., p. 81.
[108] Ibid., p. 10.
[109] Ibid.,

ከእነዚህ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥትና የጦር ሹማምንቶች አንዱ በዙ ማህጀር አልሀበሽ ለነቢዩ ሙሐመድ የኢትዮ-አረብ ጥንታዊ ታሪክ ያስተምር ነበር ተብሏል።[110]

በቁረይሽ አረቦች ጦርነት የኢትዮጵያ ሀበሾች ማንነትና ሚና

የእንግሊዙ ታሪክ ጸሐፊ ሞንትጎማሪ ዋት ጥንታዊ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ኡርዋህ ዙቤይር፥ ኢብን ኢስሓቅ፥ አልወቂዲ፥ ኢብን ሂሻም፥ ኢብን ሰይድ፥ አጠታባሪና ብዙ ሌሎችም ያቆዩዋቸውን የጽሑፍ መረጃዎች ብቻ አጥንቶ ማለትም ዘመናዊ የአርኪኦሎጂና የሊንጉዊስቲክስ (የሥነልሳን) ማጠናከሪያ መረጃዎችን ሳይጨምር የነቢዩ ሙሐመድን የሕይወት፥ የሃይማኖት፥ የትምህርትና የሥራ ታሪክ በሚመለከት ሙሐመድ በመካ፥ ሙሐመድ በመዲና በተሰኙ ርዕሶች በ1950ዎቹ ባዘጋጃቸው መጻሕፍት (W. M. Watt, Muhammad at Mecca, 1953; Muhammad at Medina, 1956), በ624-630 በመካና በመዲና ከተሞች በአዋማዊና በእስላማዊ የቁረይሽ አረብ ኅብ መካከል በተካሄደው የሃይማኖትና የአርስ በርስ ጦርነት[111] ወገንና ጠላት ሆነው በራሳቸው ጦር፥ ድርጅት፥ ትጥቅና ስንቅ የተዋጉትንና በአረቦች ሀበሻ፥ አልሀበሽ፥ አህብሽ[112] አልአህብሽ፥ ሀበሻትና አልህብሻት ተብለው በነጠላና በብዙ ስሞች የሚጠሩ ሰፋሪ ኢትዮጵያውያንን እንደአንድ «ምሥጢራዊ አህብሽ» (the mysterious Ahabish)[113] የተሰኘ አንድ የአረብ ማኅበረሰብ (tribeless people) አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል።[114]

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል በ1966 በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው የኢትዮጵያ ዓለማቀፋዊ ጥናት ሦስተኛ ጉባኤ «ደቡብ አረቢያና ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ የፊረንሳዩ ምሁር ፕሮፌሰር ስርጄ፥ (R. B. Serjeant "South Arabia and Ethiopia") የተለያዩ ጥንታዊና ዘመናዊ የመረጃ ምንጮችን አገናዝቦ ባቀረበው ሚዛናዊ ጥናት እንዳለው፥ ከላይ በአረቦቹ የተጠቀሱ የአገርና የሕዝብ ስሞች ቢያንስ በዓመተ ዓለም ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ከምድረ አፍሪካ በወታደራዊ ዘመቻና ሰፈራ ገብተው በደቡብና በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በቲሃማት ጠረፍ ክልል ማለትም በየመንና በሂጃዝ ጠረፎች አካባቢ በሰፈራ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተሰጡ ስያሜዎች

[110] Ibid.,
[111] Watt, Muhammad at Medina, pp. 10-77.
[112] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 10-11.
[113] Ibid., p. 156.
[114] Ibid., pp. 154-157.

ናቸው።[115]

የአረቦቹ በነጠላ ሀበሻ፥ አል-ሀበሽ፥ በብዙ ሀበሻት፥ ሁብሻት የተሰኙ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ስሞች ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ ተጽፈው የተገኙበት ዘመን፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ በዘመነ ክርስትና በ2ኛው ምዕተ ዓመት በ183 በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተቀርጸው በየመን ደቡብ አረቢያ ከማሪብ ጥንታዊ የሳባ ከተማ በተገኙ የአረብ ዜና መዋዕሎች «የሀበሻት እና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፥ ዋዜባና አድባ በተባሉና አረቢያን ይገዙ በነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ነው። ቀጥሎም፥ (1) በ320-344 በግዕዝ፥ በግሪክና በሳባ ቋንቋዎችና ፊደሎች ተጽፈው «የአክሱም፥ የሂሚያር፥ የረይዳን፥ የኢትዮጵያ፥ የሀበሻት[116] የሳባ፥ የሰልሂን፥ የፅያሞ፥ የቤጃ፥ የካሱ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ» የሚሉ ብዙ የአፄ ኢዛና ዜና መዋዕሎች፥ (2) በ493-534 በግዕዝ ቋንቋና በሳባ ፊደል ተጽፎ «የአክሱም፥ የካሱ፥ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሂን፥ የቲአሞ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የራቦም፥ የቤጃ፥ የኖባ፥ የአራባት ንጉሥ» የሚለው የአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል፥ (3) በ535-558 በደቡብ አረቢያ በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተጽፎ ከማሪብ ጥንታዊ ከተማ የተገኘውና «የሳባ፥ የዲሁረይዳን፥ የሃድራማዊ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የደጋና የቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅና አዝማች» የሚለው በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴና የጦር አበጋዝ ንጉሥ አብርሃ መንግሥታዊ ስምና ሥልጣን በአንድነት ከላይ ከተጠቀሰው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ነገሥታት ገደረት፥ ዋዜባና አድባ ታሪክ ጋር በዘመኑ በኢትዮጵያውያንና በአረቡ አጎራባች ሕዝቦች መካከል በኢኮኖሚ፥ በቋንቋ፥ በፖለቲካና በባህል ለምዕተ ዓመታት ለነበረው ግንኙነት ታሪካዊ መረጃዎች ናቸው።

በሁለቱ የአጼ ካሌብና የንጉሥ አብርሃ ዜና መዋዕሎች የተጠቀሰው የቲሃማት አረቢያ የጠረፍ አውራጃ በዘመኑ በሰሜን ምዕራብ አረቢያ ከሂጃዝ ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ ሳባ፥ ሰሃርት፥ ሂሚያር፥ ሀበሻ፥ የመን ጠረፍ ወሰኖችን የሚሸፍን አንድ እስትራቴጂያዊ ክልል ነበር።[117]

[115] R. B. Sergeant, "South Arabia and Ethiopia: African Elements in the South Arabian Population", Proceedings of the 3rd International Conference of Ethiopian Studies, 3 Vols. (Addis Ababa: HSIU, 1966), I, pp. 25-26.
[116] J. T. Bent, The Sacred City of The Ethiopians (London) 1896),pp. 240, 246-47.
[117] Salibi, The Bible Came from Arabia, pp. 38-39, 76-78; Norris, "The Himayaritic Tihama", p. 116; Kobishchanov, Axum, Map 1, pp. X, 50, 54; Serjeant, "South Arabia and Ethiopia", pp. 25-28.

በዘመነ ክርስትና ለመጀመሪያ ሰባት ምዕተ ዓመታት ማለትም በግምት እስከ 700 ድረስ ይህ የአረቢያው የቲሃማት ጠረፍ አውራጃ በዘመኑ የሦስቱ አኅጉራት የለሚን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የቀይ ባሕርና የላይኛው አባይ ሸለቆ ዓለማቀፋዊ የበላይ ሥርዓት ለነበረው የኢትዮጵያ ያጼ መንግሥት አንድ ዋና የማዝት፥ የገበያና የተፅእኖ ክልል ነበር።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በ570ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ኢትዮጵያ ውያን በፋርሳውያን ጦር ከየመን ደቡብ አረቢያ ግዛታቸው ከተባረሩ በኋላ እስከ ነቢዩ ሙሐመድ መነሳት ድረስ ለአራት አሥርታት በለሚን ምዕራብ አረቢያ የቲሃማት ጠረፍ አውራጃና በመሀል አገር የመካ የንግድና የሃይማኖት ከተማ በመላው ምድረ አረቢያ ለኢትዮጵያዊ ህበሾች ዋና የለፊራና የንግድ ማዕከላት ሆኑ።[118]

በተጠቀሰው የሽግግር ዘመን መጨረሻ ላይ በነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖታዊ ትምህርትና አመፅ በቁረይሽ አረብ ጎሳዎች መካከል በተከሰተው የእርስ በርስ ጦርነት በሂጃዝ አረቢያ በልዩ ልዩ መንገዶችና ምክንያቶች ሰፍረው የሚኖሩ የኢትዮጵያ የተለያዩ ማኅበራዊ ክፍሎችና ኃይሎች ማለትም ወታደሮች፥ ነጋዴዎች፥ የዕደጥበብ ባለሙያዎች፥ ባሮችና አስተማሪዎች በየፊናቸው በሁለቱ ተፋላሚ የአዋጣውያንና የሙስሊም ማኅበሮች ተሰልፈው እንደተዋጉ ታውቋል።

ከዚህ አኳያ በሙስሊሞች ማኅበር ተሰልፈው የተዋጉት ኢትዮጵያውያን በአንፃራዊ አነጋገር በአመዛኙ ጥቂት ግለሰብ ባሮችና ባለሙያዎች ነበሩ። በሌላ በኩል በሂጃዝ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የህበሻ ማኅበረሰብ በጥቅል መልኩ በራሱ ወታደራዊ አመራር፥ ትጥቅና ስንቅ የተሰለፈው በነቢዩ ወገን ሳይሆን በቁረይሽ አዋጣዊ መንግሥት ማኅበር ነበር። የዚህ የአዋጣውያንና የሙስሊም ቁረይሽ ችን ጦርነት ታሪካዊ መነሻና ውጤት በሚመለከት፥ በ622 ነቢዩ ሙሐመድ በስደት የመዲና ማዕከሉን ከመሠረተ በኋላ በመካና በሶሪያ መካከል በሊራራ ንግድ መንገድ በሚንቀሳቀሱ የመካ ቁረይሽ ነጋዴዎችና በነቢዩ ተከታይ መስሊሞች መካከል ጦርነት ተፈጠረ።[119]

በመሆኑም በመጋቢት 624 በድር በተሰኘው ሥፍራ በነቢዩ ሙሐመድ 324 የሙስሊም ተከታዮችና በቁረይሽ መንግሥት መሪ አቡ ጃህል በተመሩ 950 አዋጣዊ የመካ መንግሥት ተዋጊዎች መካከል በተካሄደው ጦርነት አዋጣውያኑ ከአዝማች መሪያቸው ጋር በሙስሊ

[118] Ibid., "South Arabia and Ethiopia", p. 26, Cited from Ibn Duraid, Al-Ishtiqaq, (Cairo, 1958), p. 193.

[119] Watt, Muhammad at Medina, pp. 2-3.

ሞቹ እጅ ተደመሰሱ።[120] በዚህ በበድር ጦርነት ታላቅ ሽንፈትና ውድቀት የደረሰባቸው የመካ ቁረይሽ አዋጣዊ ባለሥልጣኖችና ነጋዴዎች በሚቹ አቡ ጃህል ምትክ በተመረጠው መሪያቸው በአቡ ሱፍያን አመራር በመዲና ሙስሊሞች ላይ ከመካና ከቲሃማት የኪናና አረብ ነገድንና ኢትዮጵያዊ የህበሻ ማኅበረሰብን ጨምሮ ብዙ የአጎራባች ሕዝቦችን ወታደራዊ እርዳታ መጠየቅ ግዴታ ሆነባቸው።[121]

በዚሁ የፖሊሲና የተግባር እርምጃ መሠረት የመካ ቁረይሽ አናሳ መንግሥት መሪና አዝማች አቡ ሱፍያን ከመካ ማዕከሉ በመጋቢት 625 እና በመጋቢት 627 ከሰፋሪ የህበሻ ማኅበረሰብ፥ ከአረቡ የኪናና ነገድና ከቲሃማት አውራጃ ነዋሪዎች የተውጣጡ ብዙ ሺህ ወታደሮችን አስከትሎ በመዲና ከተማ ሙስሊሞች ላይ በቅደም ተከተል ኡሑድና ኸንደቅ በተሰኙ ሁለት የጦር ሜዳዎች ያልተሳኩ ተከታታይ ዘመቻዎችን አካሂዶ በሽንፈት ወደ መጣበት ተመለሰ።[122] ኸንደቅ በሁለቱ የቁረይሽ ተፋላሚ ኃይሎች መካከል በመዲና የተካሄደው የምሽግ ጦርነት ሥፍራ ስም ነው።

እንግሊዛዊው ምንትጎመሪ ዋት የመረጃ ምንጭ ጠቅሶ እንደ ዘገበው፥ በጦርነቱ በአዋጣዊ ቁረይሾች ግምባር የዘመቱ የህበሻ ወታደሮችን ቁጥር በሚመለከት፥ በኡሁዱ ጦርነት 3,000፥[123] በኸንደቁ ጦርነት ደግሞ 10,000[124] ነበር። እንዲሁም በመጨረሻ፥ በጥር 630 የመካ ከተማና መንግሥት በነቢዩ ሙሐመድ እጅ አለመውደቅ በወደቀ ጊዜ ነቢዩን በትጥቅ ከተቃወሙ ጥቂት ሰዎች መካከል ኢትዮጵያዊ ህበሾች አብረው እንደነበሩ ተመልክቷል።[125]

የእነዚህ አልህበሽ/ህበሻት ተብለው በ624-630 የቁረይሽ አረብ ጎሳዎች የእርስ በርስ ጦርነት በአዋጣዊ አንጃው ግምባር የተሰለፉ ኢትዮጵያውያንን ማንነትና ተግባር በሚመለከት ብዙ የዘመናችን አውሮፓውያን የታሪክ ጸሐፊዎች የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። ለምሳሌ ኤች ላሚንስ የተሰኘ አንድ ጸሐፊ «አህበሾችና የመካ ወታደራዊ ድርጅት በሂጅራ ዘመን» በሚል ርዕስ በ1916 ባዘጋጀው ጽሑፍ የመካ አዋጣዊ ቁረይሾችን ወደ ሽንፈትና ውድቀት ያደረሱት አህበሾች የተባሉ ኢትዮጵያዊ ባሪያ ወታደሮች ናቸው በማለት

[120] Ibid., pp. 10-13.

[121] Ibid., p. 20; Ibid., Muhammad at Mecca, pp. 154-155.

[122] Ibid., Muhammad at Medina, pp. 21, 35.

[123] Ibid., Muhammad at Mecca, p.155, Passage F.

[124] Ibid., Passage F.

[125] Ibid., Passage F.

ተችቷል።[126]

ነገር ግን የእንግሊዙ ታሪክ ጸሐፊ ዋት በበኩሉ አህበሾች የተባሉና በአዋማዊ ቁረይሾች ግምባር የተዋጉ ምንደኛ ወታደሮች ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ «አህበሽ»[127] እና «አልሁብሽ»[128] (Ahbash and Al-Hubshi) በተሰኙ ቦታዎች የተቋቋመ አንድ «ልዩ» የአረብ ማኅበረሰብ ወይም የድርጅት ምንደኛ ወታደሮች ናቸው በማለት በብርቱ ተከራክሯል።[129]

ይሁን እንጂ ከታሪክ መረጃና ትምህርት አኳያ፥ ሁለቱም ጸሐፊዎች ላሜንስና ዋት ረጅም የኢትዮ-አረብ ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት ኢታሪካዊ ግድፈት ፈፅመዋል። ምክንያቱም በአጎራባቹ የአረቢያ ምድር በአረቦቹ አል-አህበሽ፥ አል-ሀበሽ፥ ሀበሻት፥ ሁብሻት ተብሰው በተለያዩ የነጠላና የብዙ ስሞች የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን ሆነ ከዚያም በፊት ወይም በኋላ ባሮችም አረቦችም አልነበሩም። ይህ ግን በተጠቀሰው ጊዜ ሆነ በሌላ ከፍለ ዘመን በአረብ ምድርና ታሪክ እንደነቢዩ ሙሐመድ አሳዳጊ ሞግዚት በረካ ኡም አይማን፥ የነቢዩ ሙሐመድ የትግል አጋርና የሃይማኖት ወዳጅ ቢላል ሪባሕ ሙዓዚንና ሌሎችም ብዙ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ባሮች አልነበሩም ማለት አይደለም።

ታሪክ ጸሐፊው ላሜንስ ከቁረይሹ አዋጣውያን ጋር በጦር ሜዳ የተሰለፉ ሀበሾችን ኢትዮጵያዊ ባሮች ናቸው በማለቱ የእንግሊዙ አቻው ዋት በብርቱ ነቅፎታል።[130] ይሁን እንጂ ጸሐፊው ዋት ራሱ በሌላ በኩል የተጠቀሱ ሀበሾች ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ አህበሽና ሁብሽ በተሰኙ የወንዝና የተራራ ስሞች የተሰየሙ ያንድ ልዩ የአረብ ማኅበረሰብ ወይም ማኅበር ምንደኛ ወታደሮች ናቸው የሚለውን የግል ግምትና እምነት ለማሳመን «ሁብሻት/ሀበሻት»[131] (Hubashat/ Habashat) ማለትም በአረብኛ ቋንቋ «አህበሾች/ሀበሾች» የተሰኙ የሕዝብ ስሞችን በታሪክ ሳይሆን በሰዋስዋዊ የቃላት ትርጉም የሥፍራ ስያሜዎች[132] አድርጎ አቅርቦአቸዋል።

[126] Ibid., p. 154, Cited from H. Lemmens, "The Ahabish et l'Organisation Militire de la Mecque, au Siche de 'hejire", Journal Asiatique, Vol. 8, (1916), 425-82.
[127] Watt, Muhammad at Mecca, p. 154, Passage B.
[128] Ibid., p. 156, Passage L.
[129] Ibid., pp. 11, 156.
[130] Ibid., pp. 154, 157
[131] Serjeant, "South Arabia and Ethiopia", p. 26.
[132] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 154, 156.

ባሮርና በጥቅል አነጋገር በአጎራባቹ አረቢያ በአረቦቹ አል-አህበሽ፥ አል-ሀበሽ፥ ሀበሻት፥ ሁብሻት ተብለው በልዩ ልዩ የነጠላና የብዙ ስሞች የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች ለረጅም ዘመን በሁለቱ የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በቋንቋ፥ በሃይማኖት፥ በባህልና በዘር ዘላቂ የመገናኛ መንገድና ድልድይ መሥራት ሕዝቦች ናቸው። በመልካም ሥነምግባር፥ በአካል፥ በመንፈስና በጠባይ ጥንካሬ፥ በትዳር ፍቅርና ፅናት፥ በወታደራዊ ጥበብ ችሎታና ወኔ፥ በአእምሮ ንቃትና በማንዛቤ ጥራት፥ በአስተዳደርና በአመራር ብቃት፥ በጠንካራ እምነትና ታማኝነት በአረቡ ኅብረተሰብና መንግሥታት ዘንድ የታወቁና የተወደዱ ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ብዙ ታዋቂ የአረብ ሙስሊም ታሪክ ምሁራንና ጸሐፊዎች በየዘመኑ መስክረላቸዋል።[133] በመሆኑም የሀበሻን ማንነትና ታሪክ ለማወቅና ለማሳወቅ እንዎትን መሰል የሰዋሰውና የጂኦግራፊያ አስተማሪዎች የሚሰጡት ትምህርታዊ ግምገቤ የለም። ምክንያቱም የህበሾቹ መነሻና ማንነት ከተገባራቸው ጋር በገዘናና በታሪክ የታወቀ ነውና።

በአረቡ ዓለምና ታሪክ ከቅድመ እስልምና ጀምሮ ይህ ዓይነቱ ሕዝባዊና ማኅበራዊ አመለካከትና እምነት ኢትዮጵያዊ ሴቶችን፥ ባሮች ንና ወታደሮችን በተለይ በጣም ተፈላጊና ተወዳጅ ማኅበራዊ አካላትና ኃይሎች እንዳደረጋቸው የራሳቸው የአረቦች የታሪክና የትውፊት መረጃዎች ያስተምራሉ።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ለምሳሌ ከነቢዩ ሙሐመድ የቁረይሽ ከፍተኛ የመንግሥትና የጦር መሪዎች መካከል ዳግማዊ ካሊፋ ዑመር[134] (634-644) እና በ641 ግብፅን በጦር ኃይል ያስገበረው አምሩ አልአስ[135] በአንድ ወገን ኢትዮጵያዊ ተወላጆች እንደነበሩ ታውቋል። ከሁለቱ ኢትዮ-አረብ ሙስሊም መሪዎች በሴት አያቱ ወገን ኢትዮጵያዊ የነበረው ካሊፋ ዑመር በአዲሱ እስላማዊ ሕግ መሠረት በመዲና የሚኖሩ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያንን ክብድ የሃይማኖት ግብር ማስከፈሉን በተቃወመና አቡ ሉሉ በተባለ በአንድ ኢትዮጵያዊ ሀብታም የዕደጥበብ ባለሙያ እጅ በ644 በጎራዴ ሰለት እንደተገደለ የአረቡ ታዋቂ የታሪክ ጸሐፊ አጢታባሪ አስታውቋል።[136]

[133] Erlich, Ethiopia and the Middle East, p. 5; Couq, Islam En Ethiopie, p. 27; Ibn Fadl Umari, Masalik El Absar, pp. 19-21, 30-31.
[134] Ibid., Ethiopia and the Middle East, p. 5
[135] Ibid., p. 7.
[136] Sergew H. Sellassie, History, p. 192.

ሀበሻ መንግሥት መነሻና ውድቀት በየመን አረቢያ (1021-1159)

በሂጃዝ አረቢያ የሀበሾችን ፍጻሜ በሚመለከት፥ የ632-661 የአራቱ የመዲና ካሊፋዎች አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ የእስልምና ዘመንና ግዛት በ661 ባላንጣቸው ካሊፋ ሞአዊያ (661-680) በደማስቆ ሶሪያ የኡማያድን መሳፍንታዊ ዘመንና ግዛት (661-750) በመሠረተ ጊዜ በመካ፥ በአክሱምና በመዲና በቁረይሽ አረብ ሙስሊሞችና በኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቻቸው መካከል ከ610 ጀምሮ ለግማሽ ምዕተ ዓመት የነበረው ታሪካዊ የቀረበ ግንኙነት ወደ መጨረሻው ደረሰ ለማለት ይቻላል።

በተጠቀሰው ረጅም የእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ዘመን (610-750) በቀይ ባሕር የሁለቱን ማለትም የኢትዮጵያ ጥንታዊ የክርስቲያንና የአዲሱ የአረብ እስላማዊ መንግሥታትን ብሔራዊ ጥቅምና የኃይል ሚዛን በሚመለከት፥ የዳህላክ ደሴትንና የአዱሊስ ወደብን ጨምሮ የባሕሩ ንግድ፥ ወደቦችና ደሴቶች በሙሉ ገና በኢትዮጵያውያኑ ባሕር ኃይል[137] ቁጥጥር ሥር ነበሩ። በአንፃሩ በማመልና በፊረስ ጦር በምድረ በዳ የፋርሳውያንንና የሮማውያንን ያጼ መንግሥታት የማስገበር ትግል ያካሄዱ የነበሩ አረቦች ከኢትዮጵያኑ ጋር የሚወዳደራቸው የንግድም ሆነ የጦር መርከብ መሣሪያና ድርጅት ገና አልነበራቸውም።[138] የሀብትም ሆነ የስው ኃይል ሚዛንም ቢሆን በኢትዮጵያውያኑ በኩል ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በ610ዎቹ በሂጃዝ አረቢያ በቁረይሽ አረቦች መካከል በተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት ኢትዮጵያውያን ጣልቃ በመግባት ከውስጥም ከውጭም በአካባቢው የአገራቸውን የገዘያ ሆነ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘትና ለማስፋፋት በ616 በቁረይሾቹ መንግሥት በኩል በይፋ የቀረበውን የጎበረት ጥሪ ውድቅ እንዳደረጉ ይታውሳል። ነገር ግን የቁረይሽ ሙስሊም አረቦች አገራቸውን ከተቆጣጠሩ በኋላ በ630፥ በ640፥ በ702 ኢትዮጵያውያን ከቀይ ባሕሩ የአዱሊስ ወደብና የዳህላክ ደሴት በቁረይሾቹ የሸፍይሀና የጅዳ ወደቦች ላይ ያልተሳኩ ተከታታይ የባሕር ወረራዎችን እንዳካሄዱ ታውቋል።[139]

በመሆኑም በ703 ከደማስቆ ሶሪያ ማዕከላቸው የአረቡ የኡማያድ ባለሥልጣኖች በአፀፋ እርምጃ የዳህላክ ደሴትን በሰፋሪ ጦር በመያዝ

[137] Erlich, Ethiopia and the Middle East, p. 11.
[138] Tedeschi, "Note Storiche sulle Isole Dahlak", p. 52.
[139] Erlich, Ethiopia and the Middle East, pp. 9-11; Couq, Islam En Ethiopie, pp. 35-36.

የፖለቲካ እስረኞቻቸው ግዞት አደረጉት።[140] በተጨማሪም የአረብ ሙስሊም ኃይሎች ከዳህላክ ደሴት በትክክል ባልታወቀ ወቅትና ሁኔታ የኢትዮጵያን የአዱሊስ ወደብ አጠፉት።

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የቀይ ባሕር ጂኦፖለቲካ ለውጥ በጥንታዊ የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በቆየው ታሪካዊ መስተጋብርና መወራረስ ሂደት ላይ ከአካባቢ፥ ከማዕከልና ከአሠራር ለውጥ ባሻገር አዲስ መሠረታዊ ለውጥ አላስከተለም። በዚህ ረገድና ተግባር፥ በአረቢያ የኢትዮጵያ ሀበሾች መሠረትና ማዕከል አሁን በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ፥ መካና ቲሃማት በደቡቡ ጠረፍ በጥንት ዘመን ከ577 በፊት እንደነበር በየመኑ ቲሃማት ሆነ። በመሆኑም አሁን በኢትዮጵያና በየመን አረቢያ መካከል የዳህላክ ደሴትና የዜይላ ወደብ አዲስ የንግድና የባህል ልውውጥ መንገዶችና በሮች ሆኑ።

እንደዚህ የኢትዮ-አረብ የንግድና የባህል ልውውጥ ማዕከልና መንገድ የሆነው የዳህላክ ደሴት ከአጎራባቹ የምፅዋ ወደብ ጋር ከ703 እስከ 1159 ድረስ ለ460 ዓመታት ከደማስቆ ሶሪያና ከባግዳድ ኢራቅ በቅደም ተከተል በአረቡ የኡማያድና የአባሲድ (750-1517) ተፃራሪ ባለሥልጣኖች፥ በግብፅ መንግሥታት፥ ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር በቤጃ መሳፍንታዊ ኃይሎችና በኢትዮጵያ ነገሥታት እንዲሁም በ1021-1159 የመንን ለ138 ዓመታት በገዙ ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ባኒናጃህ ባለሥልጣኖች መካከል ታላቅ የጂኦ-ፖለቲካ ትግል ደሴት እንደሆነ የታሪክ መረጃ ጥናት ያሳያል።[141]

ከዚህ አኳያ ከ703 እስከ 809 ድረስ[142] ለአንድ ምዕተ ዓመት የዳህላክ ደሴት ከሶሪያና ከኢራቅ ማዕከላት ለኡማያድና ለአባሲድ አረብ ባለሥልጣኖች፥ ከላይ እንደተጠቀሰው፥ የፖለቲካ እሥረኞች ግዞት ሆነ። ቀጥሎም በ831 በቤጃው የናቅስ አካባቢ መንግሥትና በግብፁ የአረብ መንግሥት መካከል በተፈጸመው የንግድና የወዳጅነት ውል የዳህላክ ደሴት ከምፅዋ ወደብ ጋር የናቅስ ቤጃ መንግሥት ግዛት መሆኑ ዕውቅና አገኘ።[143] በ872[144] ደግሞ የዳህላክ ደሴት የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት እንደነበር የአረቡ ታሪክ ጸሐፊ የዕቁቢ መዝግቧል። በዘመኑ የዳህላክና ፂምፅዋ እስላማዊ ገዥ ራሱን ሱልጣን

[140] Tedeschi, "Note Storiche sulle Isole Dahlak", pp. 52-53.
[141] Ibid., pp. 52-57.
[142] Ibid., pp. 52-53.
[143] Ibid., p. 53.
[144] Ibid., p. 54., Cuoq, Islam En Ethiopie, p. 42.

ወይም ንጉሥ ብሎ ሲጠራ ኢትዮጵያውያኑ ግን «ሥዩመ ባሕር»[145] በሚል የገባር ስም ይጠሩት ነበር።

በ935 ደግሞ አንድ ሌላ የአረብ ታሪክ ጸሓፊ መስዑዲ ዳህላክና ምፅዋ ከዜይላ ጋር የኢትዮጵያ መንግሥት[146] ግዛቶች እንደነበሩ አስታውቋል። በተጨማሪም በዘመኑ በኢትዮጵያና በየመን አጎራባች መንግሥታት መካከል ጥሩ የወዳጅነትና የንግድ ስምምነት እንደነበር መስዑዲ ጨምሮ መዝግቧል። በ977[147] አሁንም አንድ ሌላ የአረብ ታሪክ ጸሐፊ ኢብን ሃውቀል የዳህላኩ ሥዩመ ባሕር ለየመኑ መንግሥት ገባር እንደነበር ጽፏል። በሌላ ቃል በ10ኛው ምዕተ ዓመት የዳህላኩ ሥዩመ ባሕር የኢትዮጵያም የየመንም ጥምር ገባር ነበር ማለት ነው።

በተጠቀሰው ዘመን የዳህላክ ደሴት ዋናው የኢኮኖሚ መሠረት የባሪያ ንግድ ነበር። የባሮቹ ሁለት አጎራባች ምንጮች ደግሞ በአፍሪካ ኢትዮጵያና ኑቢያ ነበሩ። በወቅቱ የዳህላኩ ሥዩመ ባሕር ለየመኑ መንግሥት ግብር የሚከፍለውም በባሪያ ነበር። በዚህ ረገድና ተግባሩ ለምሳሌ አገሩን ለ80 ዓመታት ገዝቶ በ981 የሞተው የየመኑ ሱልጣን አቡጋይሽ ሚስቱን በደሴቱ ወኪል አድርጓት በማስቀመጥ ከዳህላኩ ሥዩመ ባሕር በዓመት በአንድ ሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያና የኑቢያ ባሮችን በግብር ስም ያገኝ እንደነበር አሁንም አንድ ሌላ የዘመኑ የአረብ ታሪክ ጸሐፊ አማሪህ[148] ጽፏል።

ከዚህ አኳያና ወቅት በ11ኛውና በ12ኛው ምዕተ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ባሮች በቀይ ባሕር አካባቢ አንድ ዋና የፖለቲካ ኃይል እንደነበሩ የዘመኑ ታሪክ ያስተምራል። ለምሳሌም ከ1021 እስከ 1159 ድረስ በየመንና በዳህላክ ደሴት አዲሱ ኢትዮጵያዊ የሀበሻ በኒ ነጃህ ሥርወ መንግሥትና ባለሥልጣኖች በየመኑ ቲሃማት የአረቡን ጥንታዊ የበኒ ዝያድ ሥርወ መንግሥት ደምስሰው ራሳቸውን የአገሩ መሪዎችና የግዥ መደብ አደረጉ።[149] በወቅቱ በየመኑ ቲሃማት ጃዛሊና ስህርት የተሰኙ ሁለት ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ነገዶች እንደነበሩና የተጠቀሰው የሀበሻ በኒ ነጃህ ሥርወ መንግሥትና የግዥው መደብ ከሁለቱም ማኅበረሰቦች እንደወጡ ታውቋል።[150]

145 Tadeschi, "Note Storiche Sulle Isole Dahlak" p. 58.
146 Ibid., p. 54; Cuoq, Islam En Ethiopie, pp. 44-45.
147 Ibid., "Dahlak" p. 55; Couq, Islam En Ethiopie, p. 46.
148 Ibid., "Dahlak", p. 55.
149 Ibid., pp. 55-57; Cuoq, Islam en Ethiopie, pp. 47-49.
150 Surjeant, "South Arabia and Ethiopia", p, 25.

የሀበሻ በኒ ነጃህ ሥርወ መንግሥትና የግዥው መደብ ከስተትና ተግባር በሚመለከት፥ በ981 የየመኑ ሱል[illegible] አቡጋይሽ ሲሞት በአገሩ ረጅም የሥልጣን ችግር ተፈጠረ።[151] በዚህ ወቅት ናጃህና ነፍስ የተባሉ ሁለት ኢትዮጵያዊ የቀድሞ ባሮችና አሁን ከፍተኛ የየመን ቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች ከነተከታዮቻቸው ጋር በ5,000 አና በ20,000[152] የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች አደራጅተውና እንዲሁም በዘርና በፖለቲካ ከዳህላኩና ከኢትዮጵያ መንግሥታት ባለሥልጣኖች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥረው ከ1021 እስከ 1159 ድረስ የመንን በሀበሻ መንግሥት ሕግና ጦር ሥር ለ138 ዓመታት በበላይነት አስተዳድረዋል።[153]

በመጨረሻ በ1159 ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ባኒናጃህ ሥርወ መንግሥት መሪዎች፥ ባለሥልጣኖችና ወታደሮች፥ ከ582 ዓመታት በፊት በ577 ቅድመ አያቶቻቸው ከየመን በፋርሳውያን እንደተባረሩ ሁሉ፥ አሁን እነሱም በየመን አረብ አመፅ ተሸንፈው ወደ እናት አገራቸው ተመለሱ። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ በ1173 ሁለቱም የመንና የዳህላክ ደሴት በግብፁ ባለሥልጣናት ተዕዕኖ ሥር ወደቁ። በዚህ ረገድና ወቅት፥ ግብፅ ከ1171 እስከ 1250 ድረስ አዩቢ ተብሎ በሚታወቀው የሰለሃዲን ሥርወ መንግሥት ሥር እንደነበር ይታወሳል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሙስሊሙ ዓለም ሚና

የአረቦችን እስላማዊ አመፅ ታሪካዊ መነሻና እንቅስቃሴ በሚመለከት፥ ነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖቱን ማስተማር በጀመረ ጊዜ በመካ ከተማ በንግድ ኢኮኖሚ የሚተዳደር የቁሬይሽ ነገድ፥ በየትሪብ ማለትም በመዲና የገበሬ መንደር በእርሻ ሥራ የሚተዳደር የቃላይ ነገድና ከሁለቱም ከመካና ከመዲና በምዕራብ፥ በምስራቅ፥ በሰሜንና በደቡብ አረቢያ ምድረ በዳ በእንስሳት እርባታ በዘላንነት የሚኖሩ ብዙ የአረብ ነገዶች አንድ ማዕከላዊ የጋራ መንግሥት፥ ሕግና ሥርዓት ሳይኖራቸው በተለያዩ ማኅበራዊ የሥራና የዕድገት መስኮችና ደረጃዎች ተሰማርተው የሚኖሩ አዋማዊ ማኅበረሰቦች ነበሩ።

በመጨረሻ በሰኔ 632 በ62 ዕድሜ ከመሞቱ በፊት ከ622 እስከ 630 ድረስ ነቢዩ ሙሐመድ ኪላይ በቀረበው ብርቱ ሥርዓታዊ ትግልና ድል በመካና በመዲና የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት መሠረተ። ከ630 እስከ 632 ድረስ በሁለት ዓመታት ውስጥ ከመካና

151 Tedeschi, "Dahlak", 56.
152 Cuoq, Islam En Ethiopie, p. 48.
153 Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 76.

ከመዲና ውጭ የተጠቀሱ የአረብ ዘላን ነገዶችና ጎሳዎች አንድ በአንድ በተወካዮቻቸው አማካይነት በመዲና ከተማ ለድል አድራጊው ነቢዩ ሙሐመድ ታማኝነታቸውን አረጋገጡ።[154]

ይሁን እንጂ በ632 የነቢዩ ሞት እንደታወቀ የተጠቀሱ የአረብ ነገዶች በየአካባቢያቸው በአዲሱ የሙስሊም መንግሥት ላይ አመፁ። ስለሆነም የነቢዩ አንጋፋው ተከታይና የመጀመሪያ አልጋወራሽ ካሊፋ አቡበከር (632-634) የዘላን ነገዶችን አመፅ በፈጣን ወታደራዊ እርምጃዎች በመቆጣጠር የነቢዩን የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት ከመጥፋት አደጋ አዳነ።

ቀጥሎም ዳግማዊ ዑመር (634-644) በአንድ አሥርት ውስጥ ከመዲና ማዕከል በተባበረ የአረብ እስላማዊ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ጦር በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ ጥንታዊ የፋርሳውያንንና የሮማውያንን የአጼ መንግሥታት ደምስሶ በምትካቸው ዓለማቀፋዊ የእስላም መንግሥትና ሃይማኖት ግምባታ አጠናከረ። በ644-661 ተከታይ ካሊፋዎች ዑስማንና ዓሊ የነቢዩን፥ የአቡበከርንና የዑመርን እስላማዊ የዓለም ሥርዓት ግምባታ ፖሊሲና ተግባር የበለጠ ተግባራዊ አደረጉ።

ከእነዚህ አምስቱ ታላላቅ የእስላም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ መሥራች መሪዎችና አዝማቾች ጎንና ግምባር አያሌ ኢትዮጵያውያን በተግባራዊ ትብብር አብረው እንደነበሩ ከላይ የቀረቡ የታሪክ መረጃዎችና ጥናቶች በሥፍራ፥ በጊዜና በቁጥር ዘርዝረው ያሳያሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ ከታሪክ አኳያ እንደዚህ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ተግባራዊ ድጋፍ የዓለም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ሆኖ የተነሳው እስልምና በኢትዮጵያ ሥልጣኔና ታሪክ ላይ በዲያሌክቲካዊ መንገዶች ሁለቱንም አሉታዊና አዎንታዊ ማለትም የተፅዕኖና የአስተዋፅኦ ሁኔታዎችንና ሂደቶችን አስከትሏል። ከአሉታዊ የተፅዕኖ ሚና አኳያ፥ ከካሊፋ ዑመር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በአካባቢው ዓለማቀፋዊ መንግሥት ሆኖ የተከሰተው የአረቦች እስላማዊ ኃይልና እንቅስቃሴ ከአረቢያና ከግብፅ እስትራቴጂያዊ ሥፍራዎች የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ የንግድ በሮችንና እንቅስቃሴዎችን የአዱሊስን ወደብ ጨምሮ ከመጫኢና ከመውጫ ኬላዎች በመቆጣጠር በ577 የፋርሳውያን ጦር ሰፋሪ ኢትዮጵያውያንን ከየመን አረቢያ ባባረራቸው ጊዜ የጀመረውን ኢትዮጵያውያንን ከውጭ ዓለም የመገለል ሁኔታና ሂደት የበለጠ አጠናከረ።

[154] Watt, Muhammad at Medina, Chap. 4.

ከአዎንታዊ የአስተዋፅኦ ሚና አኳያ ደግሞ በአካባቢው የአረቦች እስላማዊና ዓለማቀፋዊ ኃይል ራሱ በተለያዩ መንገዶችና መሣሪያዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር ለታላቁ የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ህብረተሰብና መንግሥት ዕድገት የራሱን ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳደረገ የታሪክ መረጃና ትምህርት በግልፅ ያስተምራል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከካሊፋ ዑመር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በሐርላና ሀዲያ ጥንታዊ፥ አጎራባችና ተዛማጅ ሕዝቦች ምድር ላይ ከሂጃዝ አረቢያ ቀይ ባሕርን ተሻግረው የገቡ የቁረይሽ አረብ ሙስሊም አስተማሪዎችና ነጋዴዎች የኢትዮጵያን ተከታታይ የማኽዙማይት (896-1285) እና የሃሽማይት-ዋላስማ (1285-1577) ሥርወ መንግሥታትና አያሌ ተዛማጅ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ማለትም መንግሥታት መሠረቱ።[155] የሸዋ፥ የሀዲያና የይፋት ሱልጣኔቶችን ጨምሮ እነዚህ የኢትዮጵያ እስላማዊ መንግሥታትና ማኅበረሰቦች በተጠቀሰው ጥንታዊ ከፍለ ዘመን በሃይምኖት፥ በንግድ፥ በቋንቋና በባህል በአካባቢው ከአረቡ የሙስሊም ዓለም ጋር የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራቸው በዚህ ጥናት ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በዝርዝር ይታያል።[156]


በተጨማሪም በ330 የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን ጀምሮ በግብፅና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያኖች መካከል የተፈጠረው ግንኙነት በ642 ግብፅ በአረብ ሙስሊሞች ከተያዘም በኋላ ለዘለቄታው በመቀጠል በተጠቀሰው የኢትዮጵያ ረጅም የገለልተኝነት ዘመን አገራቱን በመጠኑም ቢሆን ከውጭው ዓለም ጋር የሚያገናኝ አንድ ሌላ መንገድ ሆነ።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ታሪክ ከአገር ውስጥ የሰነድ መረጃ ባልተገኘበት የ550-1300 'ጨለማ' ከፍለ ዘመን የኢትዮጵያን የሙስሊም ሃይማኖት ታሪክ ጨምሮ በመጠኑም ቢሆን የዘመኑን ታሪክ ከውጭ በኩል በልዩ ልዩ ወቅቶች፥ ምክንያቶችና መንገዶች መዝግበው ለትውልድ በዓይነት ያቆዩት ብዙ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎችና የታሪክ ባለሙያዎች ናቸው። ባጭሩ በተጠቀሰው ዘመን ለኢትዮጵያ በህውርታዊ ኅብረተሰብና መንግሥት ከስተትና ዕድገት እስልምና አንድ ማኅበራዊ መሠረትና መሣሪያ እንደሆነ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

[155] Trimigham, Islam in Ethiopia, pp. 58-59.

[156] Umari, Masalik el Absar, Maqrizi, Moslem Kings in Abyssinia; Braukamper, "Islamic Principalities".

የኢትዮጵያ የ1520 – 1660 ታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።

ክፍል አራት

የእስልምና ሃይማኖትና መንግሥት መነሻና ዕድገት በኢትዮጵያ 615-1300

በዘመነ እስልምና የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር በሮችና መንገዶች

በ615-616 በአቢዩ ሙሐመድ መመሪያ መሠረት ከመካ በሁለቱ የቀይ ባሕር አጎራባች የሹአይባና የአዱሊስ ወደብ በሮች በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ የኢትዮ-አረብ የመጀመሪያ ሙስሊሞች በ631 ወደ መካ እስከተመለሱ ድረስ አብዛኞቹ በኢትዮጵያ ለአሥራ አምስት ዓመታት እንደኖሩና ከእነርሱም በሀያ የሚቆጠሩ በኢትዮጵያ ሞተው እንደተቀበሩ ታውቋል።

ዛሬ በሰሜን ኢትዮጵያ በዘልማድ «ጀበርቲ» ተብለው በወል ስያሜ የሚታወቁ የትግሬ፥ የአገውና የአማራ ሙስሊሞች በአክሱም አገርና ቤተ መንግሥት እስልምናን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማሩ ብሎም ቅድመ አባት አያቶቻቸውን ከዘመኑ የአክሱም ክርስቲያን ንጉሥ (ንጃሺ) አፄ አስሓማ ኢብን አብድጃር (600-630) ጋር ወደ እስልምና ሃይማኖት የመለሱ እነዚሁ ስደተኛ ሙስሊሞች ናቸው ብለው በጽኑ ያምናሉ። ያስተምራሉ። ለዚህ እምነታቸውና ትምህርታቸው በሰሜን ምስራቅ ትግራይ «ነጋሽ» ቡተሰኘው ቀበሌ የሚገኘውንና የአጼ አስሓማና ሌላም የዘመኑ ሙስሊሞች መካነ መቃብር ነው የሚሉትን እንደአንድ ታሪካዊ መረጃ ያቀርባሉ።[157]

በሰሜን ኢትዮጵያ ከ615-631 የመካ ስደተኛ ሙስሊሞች ትምህርትና ሥራ በጎላ ቀጣዩን የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴና ተግባር በሚመለከት ደግሞ፥ ከ981 እስከ 1154 ድረስ አሁንም በሰሜን ምስራቅ ትግራይ ከነጋሽ ቀበሌ በስተደቡብ በአምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በመቀሌ ከተማ አጠገብ በሚገኘው የኩሀ መንደር የቆሙና በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈባቸው ብዙ የአረብ መቃብር ሐውልቶች በሀኛው ምዕተ ዓመት በአርኪኦሎጂ ጥናት ተገኝተዋል።[158]

---

157 "Negash: The Second Mecca", Tigrai Culture, Tourism and Information Bureau (Mekelle, 1997).

158 M. Schneider, "Stelese Funeraires Arabes de Quiha", Annales D'Ethiopie, Vol. 7(1967), pp. 107-118; Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 63, No. 2.

እንዲሁም በ15ኛው ምዕተ ዓመት በበጌምድርና በደቡብ ትግራይ የተደራጁ የሙስሊም ማኅበረሰቦች እንደነበሩ በአጼ ነገሥታት ዘርዓያዕቆብና በዕደማርያም ዜና መዋዕሎች ተመልክቷል።[159] ቀጥሎም በ1520 የፖርቱጋል ልዑካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ በደቡብ ትግራይ በአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ ዶባ የተሰኘ አንድ ጠንካራ የሙስሊም የአካባቢ ሕዝብና አገር ነበር።[160] በመጨረሻም በ1533 ኢማም አሕመድ ግራኙ ከደቡብ ኢትዮጵያ በሰሜኑ ደጋማ አካባቢ ላይ ዘመቻ ባካሄደ ጊዜ በትግራይ በውቁሮ/ነጋሽ ቀበሌ ተከታዮቹ «አሕመድ ነጋሽ አስማሃ» መካነ መቃብርን እንደሰበኙና[161] እንዲሁም ወደ አክሱም ከተማ በደረሰ ጊዜ «በለው» የተሰኘ የሙስሊም ሕዝብ ተወካዮች መጥተው ኢማሙን በክብር እንደተቀበሉት በዜና መዋዕሉ ተጽፏል።[162] በኢማሙ የ1524-1543 የአመፅ ጦርነት ወቅትና በኋላ እስልምና በሰሜን ኢትዮጵያ በፍጥነት እንደተስፋፋ ታውቋል።

በሌላ በኩል፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ በ550-1300 'ጨለማ' ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የክርስቲያን ምድርና ታሪክ በድንጋይ ላይ ሆነ በብራና የተጻፈ የሰነድ መረጃ ባለመኖሩ ከኢማም አሕመድ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ በደጋው ክልል የተጠቀሱት ተከታታይ እስላማዊ ማኅበረሰቦች፥ ኃይሎችና እንቅስቃሴዎች በሹአይባ-አዱሊስ የወደብ በሮች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ የኢትዮ-አረብ ስደተኞች ጋር በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀጥተኛ ግንኙነት እንደነበራቸው በትክክል የሚታወቅበት መንገድና መሣሪያ የለም። በዚህ ሁኔታ ከስደተኞቹ የአረብ ሰነዳዊ ታሪክ ጋር በቅርብ የተያያዘው ሕዝባዊ ትውፊት እንደአንድ አንባራዊ የግንዛቤ መሠረትና መሣሪያ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል በዚህ ጥናት ከላይ የታሪክ መረጃ ዓይነት፥ ትርጉምና ትምህርት አስመልክቶ በቀረበው ትንታኔ ተገልጿል።

በመጨረሻም በዘመነ እስልምና የኢትዮጵያን የቀይ ባሕር በርና መንገድ በሚመለከት፥ በአንድ በኩል ከ700 ዓመተ ምህረት በኋላ ማዕከላቸውን በደማስቆ ሶሪያ ላይ ያደረጉት የአረብ ኡማያድ ባለሥልጣኖች በአረቢያ ላይ ከኢትዮጵያውያን ዘወትር ከባሕር የሚሰነዘረውን የዘረፋ ጥቃት ከምንጩ ለማቆም በቀይ ባሕር ጠረፍ ላይ የአገሪቱን ጥንታዊ የአዱሊስ ወደብ ከተማ ማጥፋትን አስቸኳይ የታክቲክም

[159] Cuoq, Islam En Ethiopie, pp. 157, 160.
[160] Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 81.
[161] Arabfaqih, Conquete, p. 419.
[162] Ibid., pp. 420-421.

የእስትራቴጂም ፖሊሲና ተግባር አድርገው ወሰዱት።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል የአረብና የፋርስ ሙስሊም ሰፋሪ ነጋዴዎችና አስተማሪዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በቀይ ባሕር፥ በኤደን ባሕረ ሰላጤና በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻዎችና ደሴቶች ዳህላክን፥ ምፅዋን፥ ሱዋኪንን፥ ዜይላንና ሞቃዲሾን ጨምሮ ብዙ እስላማዊ የሰፈራ፥ የንግድ፥ የሃይማኖትና የባህል ማዕከላትንና በሮችን መሠረቱ።[163]

ከእነዚህ ቁልፍ የቀይ ባሕርና የሕንድ ውቅያኖስ እስላማዊ የደሴትና የጠረፍ ማዕከላት ዳህላክ፥ ምፅዋና ሱዋኪን በሰሜን ክልል ለኢትዮጵያ የክርስቲያን አገር እንዲሁም ለቤጃና ለኑቢያ አገሮች፥[164] በኤደን ባሕረሰላጤ ላይ የዜይላ ወደብ ከተማ በምስራቅና በመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ ለጥንታዊ የሐርላና የሀዲያ ነገሮና አጎራባች አገሮችና መንግሥታት እንዲሁም በሰሜን መህል ደጋማው ክፍል ለኢትዮጵያ የክርስቲያን አገሮች፥[165] ሞቃዲሾ ደግሞ በደቡብ ምስራቅ ለአዛኒያና ለሱማሌ ሕዝቦችና አገሮች[166] አዲስ የእስላም፥ የንግድ፥ የሃይማኖትና የባህል ምንጮች፥ በሮችና መንገዶች ሆኑ።

የኢትዮጵያ እስላማዊ ሥልጣኔ ክስተትና ዕድገት (896-1300)

የታሪክ መረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው፥ በግምት ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 700 ዓመተ ምህረት ማለትም እስከ ዘመነ እስልምና ድረስ በ3500 ዓመታት ውስጥ በልዩ ልዩ ክፍለ ዘመናት በጥንታዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክ፥ የላቲንና የአረብ ቋንቋዎችና ፊደሎች በተቀረፁ የሰነድ መረጃዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይም በረጅሙ የቀይ ባሕር፥ የኤደን ባሕረሰላጤና የሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍና በሰሜኑ ደጋማው ክፍል የሚኖሩ ጥንታዊ የጉንት፥ የደአማት፥ የአክሱም፥ የቤጃ፥ የአገው፥ የሰሜን፥ የትሮጅሎዲት፥ የበርበርና የአዛኒያ ነባር ሕዝቦችና አገሮች በሥፍራ፥ በጊዜና በስም ተጽፈው በታሪክ በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች ታውቀዋል።

[163] Cuoq, Islam En Ethiopie, Chap. 3; Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 61; Doresse, Histoire Sommaire, Chap. 5
[164] Ibid., Islam En Ethiopie, pp. 42-53.
[165] Ibid., pp. 54-64.
[166] Doresse, Histoire Sommaire, pp. 116-150.

ነገር ግን እነዚህ የተጠቀሱ ጥንታዊ የግብፅ፥ የግሪክ፥ የሮም፥ የአክሱምና የአረብ ሕዝቦች፥ ነጋዴዎችና ጸሐፊዎች ከዘመነ እስል ምና በፊት ከክፍለ አህጉሩ የሰሜንና የምስራቅ ባሕር ጠረፎች እንዲሁም የዘመኑ ግሪኮ-ሮማውያን «ትሮጅሎዳውያን» እና «በርበራውያን» ብለው የሚጠሩዋቸው ብዙ ዘላንና አዳኝ የቆላ ማኅበረሰቦች በእንቅስቃሴ የሚኖሩባቸውን የቆላና የበረሀ ክልሎች ተሻግረው ደጋማና ውሃማ ለምና ሰፊ በሆነው መህል ደቡብ ኢትዮጵያ ሰፍረው ብሎም በእርሻና በእንሰሳት እርባታ ተግባራትና ባህል ተሰማርተው ከሚኖሩ የተለያዩ ሴማዊ፥ ኩሻዊና አሞአዊ የሐርላ፥ የሀዲያ፥ የጎንጋና የጋሞ-ወላይታ ሕዝቦች፥ ማኅበረሰቦችና መንግሥታት ጋር ግንኙነት አላደረጉም።

ከእነዚህ በውጭው የዓለም ክፍሎች ዘንድ እስከ ዘመነ እስልምና ድረስ በሥፍራና በጊዜ ሳይታወቁ ከኖሩ ብዙ ጥንታዊ የመህል ደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በግምት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በዚይላ የንግድ በርና መንገድ ወደ ተጠቀሰው ለምና ሰፊ መህል አገር በገቡ የአረብ ሙስሊም ነጋዴዎችና አስተማሪዎች አማካይነት ለመጀ መሪያ ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት በመቀበል በክፍለ አህጉሩ ቀዳሚ የእስላም አገሮችና መንግሥታት የሆኑ ማኅበረሰቦች ከምሥራቁ ቆላማ የጠረፍ ክልሎች አንስቶ በምዕራቡ መህል አገር እስከ ዓባይና ጊቤ ወንዞች ድረስ እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ እስከ ዋቤና ገናሌ ወንዞች ድረስ በሚገኘው በክፍለ አህጉሩ የታላላቅ ወንዞችና ሐይቆች ምድር ላይ በሰፊራ የሚኖሩ ሴማዊና ኩሻዊ የሐርላና የሀዲያ አጎራባችና ተዛማጅ ሕዝቦችና መንግሥታት ናቸው።

በመህል ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ፥ የእነዚህ ሙስሊም አገሮ ችንና መንግሥታትን የታሪክ ምንጭና መነሻ በሚመለከት፥ አንደኛ፥ በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ታዋቂ የኢጣሊያ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ዶክተር ኢንሪኮ ቼሩሊ የ896-1285 የማኽዙማይትና የ1285-1577 የሃሽማይት-ዋልስማ ማለትም ተከታታይ የሸዋና የይፋት እስላማዊ ሥርወ መንግሥታትን፥ ሱልጣኔቶችንና ሱልጣኖችን ከስተት እና ዕድገት በተመለከተ በአረብኛ ቋንቋ ተጽፈው ከሐረር ጥንታዊ ከተማ የተገኙ የዜና መዋዕል ሰነዶችን መርምሮ *"The Chronological Repertory of Shoa"* እና *"The History of the Walasma"* በተሰኙ ጥናቶቹ የሱልጣኔቶቹን የስባት ምዕተ ዓመታት (896-1577) እውነተኛ ታሪክ ለዓለምና ለትውልድ ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል አሳውቋል።[167]

[167] E. Cerulli, Ethiopia's Relations with the Muslim World, UNESCO, History of Africa, Vol. III (1988), pp. 575-585; Trimingham, Islam In Ethiopia, pp. 58-61; Cuoq, Islam En Ethiopia, pp. 120-129, 151.

ሁለተኛ፥ ከኢትዮጵያ የ550-1300 «የጨለማ» ክፍለ ዘመን በኋላ በ14ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በሁለቱ ማለትም በአጼ አምደጽዮን (1314-1344) የግዕዝ ዜና መዋዕልና[168] በግብፁ ጸሐፊ አል-ዑማሪ[169] *Masalik al-Absar fi Mamalik al-Amsar* በሚል ርዕስ በተጻፈው የአረብኛ መጽሐፍ በክፍለ አህጉሩ ማለትም በደቡብ ኢትዮጵያ ከ896 እስከ 1344 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በግምት በምስራቅ ጠረፍ ከኤደን ባሕረ ሰላጤ ጀምሮ በመህል አገር አዋሽን ጨምሮና አልፎ እስከ ዋቤ፥ ጊቤና ዓባይ ወንዞች ድረስ በሚገኘው የታላላቅ ወንዞችና ሐይቆች ምድር ላይ የኢትዮጵያ ጥንታዊና እስላማዊ የሸዋ፥ የሀዲያ፥ የይፋት፥ የወርጅ፥ የገዳል፥ የአዳል፥ የሞራ፥ የለበከላ፥ የሀገራ፥ የፊድሴ፥ የግደድ፥ የንብ፥ የዚባ፥ የሐርላ፥ የሀብት፥ የተርሳ፥ የእይም፥ የእልብሮ፥ የዜይላ፥ የአስቴ፥ የደዋሮ፥ የመንዝ፥[170] የዜጋ፥ የኩልጉራ፥ የገደያ፥ የቀድሴ፥ የሐርጋዖ፥ የብቁልዘር፥ የፊጢጋር፥ የአርጎባ (የጁባ)፥ የሸርካ፥ የአረባኒኒ፥ የባሌ፥ የደራ፥ የሐረር፥[171] የጉራጌ፥[172] የስልጤና፥[173] የአውሳ[174] ወዘተ ሕዝቦች፥ አገሮች፥ ከተሞችና መንግሥታት፥ በድምሩ ከ200 በላይ በሚሆኑ የይፋት ሱልጣኔት የአስተዳደር ክልሎች[175] የሚገኙ 17 የአካባቢ ነገሥታትን፥[176] ከ2700 በላይ የጦር አበጋዞችንና[177] ከ12,000[178] በላይ መስጊዶችን ጨምሮ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ በስምና በቁጥር ተመዝግቦ ተገኝተዋል።

እነዚህ ሁለቱም የአምደጽዮን ዜና መዋዕልና የአልዑማሪ መጽሐፍ በአንድነትና በተናጠል የሚገለፁት በደቡብ ኢትዮጵያ ከ1270 እስከ 1577 ድረስ ለ300 ዓመታት በመሬት፥ በሞት፥ በንግድና በኃይል ሚዛን ምክንያቶችና ጥያቄዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ አዲስና ተስፋፊ የአማራ መንግሥትና ከደቡቡ ነባር የሙስሊም ሱልጣኔቶች መካከል

[168] Huntingford, Amda Seyon, p. 3.
[169] Al-Umari, Masalik El Absar, pp. 1-10.
[170] Huntingford, Amda Seyon, p. 57; Crawford, Itineraries, p. 81; Trimingham, Islam In Ethiopia, p.71.
[171] Ibid., Amda Seyon, p.78.
[172] Ibid..
[173] Ibid , p. 75.
[174] Ibid., p. 79.
[175] Ibid., pp. 73-79; Perruchon, Histoire des Guerres d'Amda Seyon, Roi d' Ethiopie, Journal Asiatique, Ser. 8, T. 14 (1889), pp. 323, 361.
[176] Ibid., Amda Seyon, p. 74.
[177] Ibid., Amda Seyon, p. 80.
[178] Ibid.,

የተካሄደውን ረጅም ጦርነት የመጀመሪያውን ምዕራፍ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ የአልዑማሪን መጽሐፍ ምንጭና ትምህርት በሚመለከት፥ ክርስቲያኑ የአማራ ንጉሥ አጼ አምደጽዮን በተጠቀሱት ነባር መሳሊም ሕዝቦች፥ አገሮችና መንግሥታት ላይ የ1316-1332 ወረራ ካካሄደ በኋላ፥ በ1332-1338 ይሆንኑ የአጼ ጦርነት ፖሊሲና ተግባር በመግለጽ የይፋት ሱልጣኔት ባለሥልጣኖች የሰላም አስተዋፅኦ ያደርጉ ዘንድ በአንድ የዜይላ ሼክ ጃማልዲን አብደላህ በተባለ የሕግና የሃይማኖት ምሁር የሚመራ አንድ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ መልዕክተኞች ቡድን ወደ ግብፅ መንግሥት ባለሥልጣኖች ላኩ።[179]

የይፋት ዲፕሎማቲክ ልዑካን ቡድን መሪ ሼክ ጃማልዲን አብደላህ በካይሮ ግብፅ ቆይታው ወቅት ለግብፁ አስተዋይ የቤተ መንግሥት ባለሚልና የታሪክ ባለሙያ ኢብን ፋድል አላህ አል-ዑማሪ የኢትዮጵያን የዘመኑን በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ጎብረተሰብና መንግሥት በሚመለከት ዝርዝር የታሪክ መረጃዎችን እንደሰጠው የግብፁ ጸሐፊ በመጽሐፉ ከመግለፁም በላይ ከሼኩ በተሰጡ መረጃዎች መሠረት የሰባቱን የይፋት፥ የዳዋሮ፥ የአረባቢኒ፥ የሀዲያ፥ የሸርካ፥ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለምና ለትውልድ በጽሑፍ አስታውቋል።

ሰንጠረዥ 7
በ14ኛው ምዕተ ዓመት በጀግለዲን-ዑማሪ ግምት
የኢትዮጵያ የሰባት ሡልጣኔቶች የመሬት ስፋትና የሠራዊት ብዛት

አገር	ያገር ስፋት በስኩር ኪሎሜትር			ሠራዊት በወታደር ዓይነትና ብዛት		
	ቁመት በኪሜ	ጎን በ ኪሜ	ስፋት በስኳር/ኪሜ	የእግር ጦር	የፈረስ ጦር	ድምር
ይፋት	288	384	111000	20000	15000	35000
ደዋሮ	96	38	3600	2000	15000	35000
አረባቢኒ	77	77	5900	10000	10000	20000
ሀዲያ	160	172	27500	80000	40000	120000
ሸርካ	58	96	5500	5000	3000	8000
ባሌ	384	120	46000	ብዙ ሺህ	18000	+18000
ደራ	57	57	3300	2000	2000	4000
ድምር	1120	144	203000	+137000	103000	+240000

Source: Umari, Masalik, pp. 5-16; Huntington, Amdaseyon, pp. 20-23.

[179] Umari, Masalik El Absar, pp. 35, 5, 29; Trimingham, Islam In Ethiopia, pp. 72-73.

ሦስተኛ፥ በኢትዮጵያ አጠቃላይ የመካከለኛው ዘመን ታሪክ ሁለት ቁልፍ የመረጃ ምንጮች የሆኑት የአጼ አምደጽዮን ዜና መዋዕልና የግብፁ አልዑማሪ መጽሐፍ በ1330ዎቹ በአንድ ጊዜ ከተፃፋበት ዘመን በኋላ አንድ መቶ ዓመት ቆይቶ ሌላ የግብፅ አረብ ታሪክ ጸሐፊ አሕመድ ማክሪዚ[180] (1366-1442) በኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ በአንድ በኩል የዑማሪን መጽሐፍ አንብቦ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱም ከአሳራባቹ የየመን አገር ተጨማሪና ወቅታዊ መረጃዎችን አሰባስቦ በ1430ዎቹ *በኢትዮጵያ የሙስሊም ነገሥታት አውኑኖና ታሪክ* መጽሐፍ በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ በተለይም የኢትዮጵያ የክርስቲያንና የሙስሊም ባላንጣ ነገሥታትን ረጅምና አውዳሚ ጦርነት በሚመለከት ብዙ አዳዲስና ቁልፍ መረጃዎችን ሰጥቷል።[181]

አራተኛ፥ በኢትዮጵያ የእስልምናና የሙስሊሞች ታሪክ አንድ ሌላ ቁልፍ የመረጃ ምንጭ በኢትዮጵያ ተወላጅ ሸሃቡዲን አሕመድ ቢን አብደልቃድር (አረብ ፋቂህ) <u>የሀበሻ ዘመቻ</u> (*Futuh al-Habasha*) በሚል ርዕስ በ1535 በአረብኛ ቋንቋ ተጽፎ በኋላ በ1897 በፊረንሳዩ ረኔ በሌት ወደ ፊረንሳይኛ ቋንቋ የተተረጎመው የኢማም አሕመድ ግራኙ የ1524-1543 ዜና መዋዕል ነው። ዜና መዋዕሉ ለምዕተ ዓመታት ተጠብቆ የኖረው በታላቁ የሐረር ከተማ መንግሥት ነው።

የኢትዮጵያ የማኽዙማይትና የሃሽማይት-ዋላስማ ሥርወ መንግሥታት ታሪካዊ መነሻ

በ1936 ከሐረር ከተማ በኢጣሊያዊ ምሁር *በዶክተር ቼሩሊ* በተገኘው የሸዋ እስላማዊ መንግሥት (896-1285) ለነድና በ1430ዎቹ በግብፁ ማክሪዚ በተፃፈው የይፋት ሱልጣኔት (1285-1577) ታሪክ መሠረት፥ ሁለቱንም የኢትዮጵያ የማኽዙማይትና የሃሽማይት-ዋላስማ ሥርወ መንግሥታትንና ሱልጣኔቶችን በደቡብ ኢትዮጵያ የመሠረቱት ከመካ የመጡ የቁረይሽ አረብ ነገድ በቅደም ተከተል ማኽዙማ ይትና[182] ሃሽማይት[183] የተሰኙ ሁለት ጎሳዎች ተወላጆች ናቸው። ከላይ በተጠቀሰው በዶክተር ቼሩሊ ጥናት እንደተባለው፥ ከመካ የተወሰኑ የማኽዙማዊ ጎሳ ተወላጆች በዳግማዊ ካሊፋ ዑመር ዘመን (634-644) ቀይ ባሕርን በፍለሳ ተሻግረና በዜይላ በር ወደ መህል

[180] Maqrizi, The Book of the True Knowledge of the History of the Moslem Kings in Abyssinia, Tr. by G. W. B. Huntingford, (Typescript, 1955).

[181] Ibid., pp. 1-29.

[182] Cuoq, Islam En Ethiopie, p. 121; Trimigham, Islam In Ethiopia, p. 58, No. 2.

[183] Maqrizi, Moslem Kings, p. 11.

ኢትዮጵያ ገብተው ከገዜ በኋላ በ896 በሐርላው ሴማዊ ምድር የኢትዮጵያን የመጀመሪያ እስላማዊ የሸዋ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኔት መስርተው እስከ 1285 ድረስ ለ400 ዓመታት እንዳስተዳደሩት ተረጋግጧል።[184]


በዚህ ረገድና ተግባር፥ ዝቢዩ ሙሐመድ አብድሽምስ፥ ነውፊል፥ ሃሺምና አልሙጠሊብ የተሰኙ አራት ቅድመ አያቶች እንደነበሩትና ዝቢዩ ራሱም የሀሺም የልጅ ልጅ እንደሆነ ይታወቋል። በማከሪዚ ዘገባ መሠረት፥ ከዚህ ከዝቢዩ ሙሐመድ የሃሽማይት ጎሳ የወጡ አባላት በአገው ዘመነ መንግሥት (1100-1270) ከሂጃዝ አረቢያ በዜይላ በር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው መጀመሪያ «ደበርቲ» ተብሎ በሚጠራው የዜይላ ቆላማ አገር ቀጥሎም በመሀል አገር በሐርላው ምድር በሸዋ ሱልጣኔት ሰፍረውና ተጠቃሹንም ሱልጣኔት ገልብጠው በ1285 የራሳቸውን አዲስ የዋላስማ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኔት በውመር ዋላስማ መሪነት መሠረቱ።[185]

በአጭርና በጥቅል አነጋገር፥ የእስልምና ሃይማኖት ከመካ በመጡ የቁረይሽ አረብ ሙስሊም ስደተኞች፥ ነጋዴዎችና አስተማሪዎች አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በሁለት በተለያዩ መንገዶችና ጊዜያት ነው። መጀመሪያ በ615-616 ከመካ በሹዓይባና በአዱሊስ የጠረፍ በሮች በስደት ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት የመጡ ኢትዮ-አረብ ሙስሊሞች በሰሜን ኢትዮጵያ ሃይማኖቱን በአክሱሙ የክርስቲያን አገርና ቤተ መንግሥት አስተማሩ። ሁለተኛ፥ ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ከሂጃዝ አረቢያ በዜይላ በር ወደ አዋማዊ መህል ደቡብ ኢትዮጵያ የገቡ የማኸዙ ማይትና የሃሽማይት አረብ ጎሳዎች በሐርላና በሀዲያ ሴማዊና ኩሻዊ አገሮች እስልምናን የሕዝብና የመንግሥት ሃይማኖት አድርገው አስተማሩ። መሠረቱ። የእነዚህ የኢትዮጵያ የሙስሊም ሕዝቦችና መንግሥታት ዝርዝር ታሪክ በሌላ መጽሐፍ (1300-1974) በስፋት ይጠናል።

[184] Cuoq, Islam En Ethiopie, p.121.

[185] Ibid., p. 124; Maqrizi, Moslem Kings, pp. 11-12.

የኢትዮጵያ ማኸዙማይትና የሃሽማይት ዋላስማ ሥርወ መንግሥታት የነገደ ቁረይሽ ሐረግ



Source: Watt, Muhammad (1953).

የኢትዮጵያ የሸዋ ቀዳሚ ሱልጣኔት ረጅም የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ (896-1991)

በመሀል-ደቡብ ኢትዮጵያ ቁልፍ ጂኦ-ፖለቲካዊ ምድር ላይ ከ896 እስከ 1991 ድረስ በ1100 ዓመታት ውስጥ «ሸዋ» የተሰኘው ጥንታዊና ማዕከላዊ የሐርላ አገር ተለዋዋጭ ስም በግምት፤

1. ከ896 እስከ 1316 ድረስ በሙገር፥ በአዋሽ፥ በከሰም፥ በጀማና በአባይ ወንዞች መካከል በጥንቱ ሴማዊ የሐርላ ምድር የኢትዮጵያ የመጀመሪያው እስላማዊ አገርና መንግሥት (ሱልጣኔት) ሰያሚ[186]
2. ከ1316 እስከ 1600 ድረስ በጥንቱ የሐርላ እስላማዊ ሱልጣኔት ምዕራባዊ ከፊል ላይ የአዲሱ ሰለሞናዊ ክርስቲያን የአማራ መንግሥት ያንድ ያስተዳደር ክልል ሰያሚ፤
3. ከ1600 እስከ 1889 ድረስ በኢትዮጵያ ረጅም የሕዝቦች እንቅስ ቃሴና ያካባቢ ጦር አበጋዞች ዘመን አሁንም በጥንቱ የሐርላ እስላማዊ ሱልጣኔት ከፊል ክልል በቱለማ፥ በሚጫ፥ በወሎና በከረዩ አሮሞ ሰፋሪዎች ዙሪያ መልስ ቀለበት ውስጥ የተንሹ የመንዝ አማራ ባላባታዊ መንግሥት ሰያሚ፤
4. ከ1889 እስከ 1936 ድረስ በወሎና በአዋሽ መካከል የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ማዕከላዊ የዘውድ አውራጃ ሰያሚ፤
5. ከ1936 እስከ 1941 ድረስ በአዲስ አበባና ዙሪያው የኢጣሊያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ማዕከላዊው የአስተዳደር ክልል ሰያሚ፤
6. ከ1941 እስከ 1974 ድረስ በወሎ÷ በአባይ÷ በጊቤ÷ በጥቁር ወንዝና በታችኛው የአዋሽ ሸለቆ መካከል የኢትዮጵያ የአጼ መጨረሻ መንግሥት የማዕከላዊ ጠቅላይ ግዛት ሰያሚ፤
7. ከ1975 እስከ 1986 ድረስ በወሎ፥ በዓባይ፥ በጊቤ፥ በጥቁር ወንዝና በታችኛው የአዋሽ ሸለቆ መካከል የኢትዮጵያ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የማዕከላዊ ክፍለ ሀገር ሰያሚ፤
8. ከ1987 እስከ 1991 ድረስ በወሎ፥ በጎጃም፥ በኢሉባቦር፥ በሲዳሞ፥ በአርሲ፥ በሐረርጌና በአስብ ክልሎች መካከል የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሰሜን ሸዋ፥ ምዕራብ ሸዋ፥ ደቡብ ሸዋና ምስራቅ ሸዋ የተሰኙ አራት ማዕከላዊ ያስተዳደር ክልሎች የወል ስያሜ እንደሆነ ይታወሳል።

በመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ በጥንቱ የሐርላ ምድር የሸዋ ቀዳሚ የእስላም አገርና መንግሥት የተከሰተበት ዘመን (896-1285) ባንፃሩ በሰሜኑ የክርስቲያን ኢትዮጵያ የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት


[186] Cuoq, Islam En Ethiopie, p.120-121, 145; Huntingford, pp. 2, 14-16, 22.

የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን እንደነበር አይረሳም። በመሆኑም ከ1300 በፊት በሸዋ ሱልጣኔት ማለትም በደቡብ ኢትዮጵያ ነባር ሕዝቦችና በሰሜኑ ተከታታይ የአክሱም፥ የአገውና የአማራ ክርስቲያን መንግሥታት መካከል የመጀመሪያ ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነት መቼና እንዴት እንደተጀመረ በሥፍራና በጊዜ ሚዛን በትክክል ለማወቅ ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ከሥፍራና ከጊዜ ቀመር ሚዛን ውጭ በተረትና በተአምር መልክ በየወቅቱ የተዘጋጁ ብዙ የትውፊትና የገድል ባሕረ መዛግብት እምብዛም የሚረዱ የታሪክ መረጃዎችና ማስረጃዎች አይደሉም። በዚህ ረገድና ተግባር፥ ለምሳሌ በቅርቡ ከአረብ ጥንታዊ የታሪክ መረጃዎች በትክክል እስከታወቀ ድረስ በተጠቀሱት የኢትዮጵያ የተረትና የገድል ድርሳናት በአካባቢው «ሸዋ» የሚባል ጥንታዊ የእስላም አገርና መንግሥት እንደነበር አልተገለጸም።

በመጨረሻ በ1285 ገደማ ጥንታዊ የሸዋ ሱልጣኔት አገር በሁለቱ አዳዲስ የይፋትና የአማራ ተፃራሪ ሥርወ መንግሥታትና መንግሥታት መካከል በምዕራብና በምስራቅ በሁለት የፖለቲካ ክልሎች ተከፈለ።[187] የምዕራቡ አጋማሽ ሸዋ፥ በ1531 ከመላው ደቡብ ኢትዮጵያ በኢማም አሕመድ ግራኙ አመጽ ተሸንፈው እስኪባረሩ ድረስ፥ ለሁለት ምዕተ ዓመታት ተኩል (1285-1531) በአካባቢው የሙስሊም ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ለክርስቲያን የአማራ ነገሥታት ዋናው የፖለቲካና የእስትራቴጂ መሠረትና ማዕከል ይሆናል።

[187] Huntingford, Amda Seyon, pp. 16, 22, 57.

የኢትዮጵያ የ1855 – 1900 ታላቁ ምዕክልና ታሪክ ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።

ክፍል አምስት

የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ረጅም የስያሜ ታሪክ

የሀበሻና የአጋዓዚያን ነገዶች ጥያቄ በኢትዮጵያ ታሪክ

የሀበሻ ታሪካዊ መነሻና ትርጉም በአረቡ ዓለም

በጥቢያ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 4፣ 1989 «ሐበሻ ማነው? ማንስ ነው ያልሆነው?» በሚል ጥያቄ በቀረበው ጽሑፉ፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በልምድ ከታወቁ ብዙ ውስብስብና ተዛማጅ የኋላ ቀርነት ማለትም የእውቀት፣ የትምህርት፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና አጠቃላይ ማኅበራዊ የዕድገት ደረጃ ችግሮች ጎን ያለው አንድ መሠረታዊ የጎላ ተሰብ፣ የታሪክና የማንነት ማዛቤ ችግር እንደሚከተለው ይነበባል። በመጽሔቱ አቀራረብ፣

ከሁለት ዓመት በፊት ገደማ እንደገና በአዲስ መልክ ከተዋቀረው የአቢሲኒያ ባንክ መሥራች አባላት መካከል የተወሰኑ ራሳቸውን ከባንኩ ባለድርሻነት ማግለላቸውን አስታወቁ። ዜና ሆኖ ያነጋገረው ራሳቸውን ማግለላቸው ላይሆን ለድርጊታቸው የሰጡት ምክንያት ነበር። አቢሲኒያ (ሐበሻ) የሚለው ሲያሜ በአረቦች ዘንድ አሉታዊ ትርጓሜ ስለሚሰጠው የባንኩ ስም ካልተቀየረ የለንበትም የሚል አቀራረብ ነበር ይፋ የወጣው።

ሐበሻ ማን ነው? በሚለው ጥያቄ ላይ እንድቆዝም ምክንያት የሆነኝ የባንኩ ባለአክሲዮኖች አባባል ብቻም አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ የቆየ የአገሪቷና የሕዝቧ አጠራር በተለያዩ ወገኖች፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተዘውትሯል። የኦሮሞ ብሔርተኞች አቢሲኒያና ሐበሻ የሚለውን አጠራር ለተወሰኑ የአገሪቷ ብሔረሰቦችና ክፍሎች ሲያሜ አድርገው ይጠቀመብታል። በኡርዚና ሲይፈ ነበልባል የሚወጡትን ጽሑፎች ማየቱ በቂ ይመስለኛል። በአውሮፓ መዲናዎች አዲስ የተፈጠረችው የኅረቤት አገር ኤርትራ ተወላጆችም የኢትዮጵያ ዜጎችን በአንድነት ለመጥራት ሀበሻ የሚለውን ቃል በጥቅም ላይ እያዋሉ ነው። «ወንድም ኢትዮጵያዊ ነህ ኤርትራዊ ላለማለት ተፈርቶ» ሐበሻ ነህ ወይ? የሚል ጥያቄ መልካም የማምለጫ ዘዴ ሆኖ ቀርቧል።

ለመሆኑ ሐበሻ ማነው? የሚለው ጥያቄ ለጥቢያ መጽሔት አንባቢያን ማቅረብ አፈልጋለሁ። ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ። እንደተባለው ስሙ በአረቦች ዘንድ ጸያፍ ይዘት አለው? ቢኖረውስ አጠራሩ የራሱ መታወቂያ ነው የሚል ወገን ካለ በሌላኛው አሉታዊ አመለካከት ምክንያት አድርጎ ስሙን የመሰለ ነገር እርግፍ

አድርጎ ይተዋል? ይህ ስም ለአገሪቷ መጠሪያ፥ ለሕዝቧ መታወቂያ ሆኖ ለብዙ ዘመናት መገልገሉ እየታወቀ ኢትዮጵያ የሚለው ሲያሚ የተመረጠበትን ምክንያት የሚያስረዱን ባለሙያዎች ከመካከላችን እንደማጠይቁ እርግጠኛ ነኝ። የባንኩ ባለአክሰሮኖች ዓይነት ምክንያት እንደማይሰጠኝ ተሰፋ አደርጋለሁ። ሌሎች ጥያቄዎችም ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ የቆየ ሲያሚ እንደገና ነፍስ እንዲዘራና እንዲያንሰራራ የሚፈልጉ ወይም የሚጉሉ ወገኖች አሉ? ለየትኛው ፖለቲካዊ ዓላማቸው? የሚል ጥያቄ የግድ ያስከትላል።

አረቦች «አልሐበሻ» የሚለው ስም ለአገራችን መቼ መጠቀም እንደጀመሩ በእርግጠኝነት መናገር ቢያዳግትም አሰያየሙ የቆየ መሆኑ አያጠያይቅም። እኔኑ «አልጃሂሲያ» የድንቁርና ዘመን በሚሉት ቅድመ እስልምና ወቅት ላይ የዛሬይቱ ኢትዮጵያን «አልሐበሻ» ብለው እንደሚጠሯት ብዙ ዋቢ መጥቀስ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ኢትዮጵያ በዚያ ጊዜ ገናና ከነበሩት ሮምና ፋርስ፥ ሕንድ ጎን ለጎን ደጋግማ የምትጠቀስ አገር ነች። እብርሃ የተባለው የአጼ ካሌብ የጦር አበጋዝና እንደራሴ በካዕባ የነበሩትን የዓረቦች ቅድመ እስልምና ማምለኪያ ቅዱሳን ሰፈሮች ለማፈራረስ በ571 ዓም ገደማ ያሰማራው በዝሆኖች የተጠናከረ ዘመቻ በዓረቦች ታሪክ እውቅ የጊዜ መለያ ታሪክ መጋጠሚያ ነው። ዓመቱ የዝሆኖች ዓመት ይባላል። ባለዝሆኖቹ ደግሞ አብርሃ አልሐበሻ (የሐበሻው አብርሃ) ይባላሉ።

ከሁሉ በላይ ግን ሐበሻ የሚለው ስም ከዓረቦች ሆነ በኋላ እስልምና ከተቀበሉ የአካባቢ ሕዝቦች ልቦና ጋር ያቆራኘው የመጀመሪያው መነሊሞች የሐበሻ አገር ፍልሰትና መለደድ ነበር። ነቢዩ ሙሐመድ 'ራሳችንን ለመከላከል አላህ ብርታቱን እስኪሰጠን ድረስ ወደ ሐበሻ አገር ሂዳችሁ እዚያው ቆዩ። የሐቀኞችና የፃድቃን አገር ናት። ንጉሱም ፍርድና ፍትሕ አዋቂና እስተዋይ ስለሆነ በእርሱ ዘንድ ማንም አይበደልምና አትሰደ' በማለት የሰጡትን መመሪያ በመቀበል የመጡት ሲደተኞች ናቸው ለዚች አገር እንግዳ ተቀባይነት፥ ለሕዝቧ ጨዋነት ምስክርነት የሰጡት በዚህ መሠረት ነው ነቢዩ 'ሐበሻን አትንኩ፥ ሐበሻ ላይ በግድ የማስለም ዘመቻ አታውጁ' ብለዋል የሚባለው። በዓረቦች ዘንድ 'ሐበሻ' የሚለው ስም በታላቅ አክብሮትና ባለውለታነት እንጂ በአሉታዊ አመለካከት የተንጸባረቀበት ጊዜ የለም።

ዓረቦች ሌሎች ሕዝቦችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱበት አንዱ መመዘኛ ከሰማያት የወረዱ የሚሉዋቸው ሦስቱን ባለመጽሐፍ ሃይማኖቶች ከመቀበልና ባለመቀበል ላይ የተመሠረተ ነው። 'ሐመጅ' በማለት እንደአሕዛብ የሚያንቋሽሿቸው ተራ ውስጥ «ሐበሻ» አልነበረችም። ምክንያቱም ግልፅ ነው። ከእነሱ በፊት አይሁዳዊነትን፥ ክርስትናንና እስልምናን የተቀበለ ሕዝብ አገር ናትና። እስልምናም ቢሆን መዲና ከመገባቱ በፊት አክሱም ላይ ተሰብኳል።

አቢሲኒያ የሚለው የሐበሻ የፈረንጅኛ አጠራር ዘዉው ምንጩ ይህ የዓረብኛ ቃል መሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። ፈረንጆች አገራችንን በዚህ ሲያሚ አማካኝነት ለቀረው ዓለም አስተዋውቀ ዋታል። አሁንም 'ሀበሻ' የሚለውን ስም ዓረቦች ከዮት አመጡ የሚለው ጥያቄ መልስ አላገኘም። ሊቃሉ አመጣጥ ብዙ መላ ምቶች ቢሰጡም ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን። አንደኛው ሐበሻ የሚለው ቃል መሠረቱ 'ሐቢሸ' ከሚለው የዓረብኛ ቃል ተገኝ የሚለው ነው። «ሀቢሸ» ትርጉሙ ቅይጥ ወይም የተደበላለቀ ማለት ነው።

ብዙ ሕዝቦች በአንድነት ተቀይጠው ስለሰፈሩባት ሲያሚው ተሰጣት የሚል ማብራሪያ እናገኛለን።

ሌላው ደግሞ 'ሐበሻ' የሚለው ቃል ከደቡብ ዓረቢያ ፊልሰው በደጋው ኢትዮጵያ ከፍል ከነበሩት ዋና ዓረብ ነገዶች አንዱ ከነበረው «ሐበሻ» ጋር ያቆራኙታል። ሁለተኛ ደግሞ 'አግዓዚ' የሚባል እንደነበረ በኢትዮጵያ የታሪክ ማስተማሪያ መጻሕፍት ሰንግረው የነበረው ነው። አጋዓዚያን ለግዕዝ ቋንቋ ስማቸውን ሲያበረክቱ 'ሐበሻ' ደግሞ ለዚህ ለቆመው የአገሪቱ መጠሪያ ምንጭ ነበረ ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱ ያስከፋ ይሆን? የታሪክ ባለሙያዎችን ምን ይላሉ?

በማለት መፅሐፉ ሊመለስ የሚገባ ጥያቄ ሰንዝሯል።

በኢትዮጵያ ታሪክ የሀበሻና የአጋዓዚያን ጥያቄ ማብራሪያ

ከሁሉ በፊት በዚህ ጥናት ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው «ሀበሻ» የተሰኘ ስም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰነድ ተጽፎ የተገኘው በዘመነ ክርስትና በ183[188] በደቡብ አረቢያ በጥንታዊ የግሪብ ከተማ በሳባ ቋንቋና ፊደል በተጻፈው በአንድ የአረብ መስፍን ረጅም ዜና መዋዕል «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት»[189] ተብሎ በአንቀጽ 13፥ 20፥ 28፥ 32 በሰፈረው ታሪክ ነው። «ግዕዝ» የተሰኘ የሕዝብና የአገር ስም ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ ተጽፎ የተገኘው በ300 ዓመተ ምህረት አካባቢ በቀይ ባሕሩ የአዱሊስ ወደብ በግሪክ ቋንቋና ፊደል በተፃፈው በአንድ የአክሱም ንጉሥ ዜና መዋዕል «የጋዝ፥ የአጋሜ፥ የአገው፥ የአድዋ፥ የሰሜን፥ የቤኝ ሕዝቦች»[190] ተብሎ በቀረበው ታሪክ ነው።

ሁለተኛ፥ የግዕዝ ቋንቋና ፊደል ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የተገኘበት ዘመን ደግሞ በዘመነ ክርስትና በ2ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ተጽፎ በቅርቡ በ1950ዎቹ በአርኪኦሎጂ ጥናት ከትግራይ ቡተገኘውና «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» በሚለው አጭር ታሪካዊ ዜና መዋዕል[191] ነው። በተጨማሪም፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ ለግዕዙ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ግዕዝ፥ ካዕብ፥ ሳልስ፥ ራዕብ፥ ሐምስ፥ ሳድስና ሳብዕ የተሰኘው የድምፅ፥ የንግግር፥ የጽሕፈትና የንባብ ሕግና ሥርዓት የተቀረጸለት በአጼ ኢዛና ዘመነ መንግሥት (320-344) ነው።[192]

[188] Kobishchanov, Axum, p. 50.
[189] S. Hablesellasie, History, p. 76.
[190] Cosmas, Christian Topography, pp. 60-61; Kammerer, Essai Sur L'Histoire, p. 90.
[191] Coquote et Drewes, "Les Monuments", p. 37.
[192] Littman, DAT, TV, Inscriptions, Nos. 9-11.

ይህ ሁሉ ከሆነና ከታወቀ በኋላ ኢጣሊያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ሙሴ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ (1872-1949) በጆርናል አሲአቲክ ቁጥር 18 ጁላይ/ሴፕቴምበር 1921 «የሐበሻት ዘመቻዎችና ግዛቶች በአረቢያ» «*Expeditions et Possessions Des Habashat En Arabie*» *Journal Asiatique, Ser. 18, 1921)* በሚል ርዕስ ባሳተመው ጽሑፍ ከላይ ከቀረቡ ሁለት ታሪካዊ ስነዶች ማለትም ከግሪኩ የ183 የሳባ ቋንቋ ዜና መዋዕል «ሀበሻት» የተሰኘውን ስም በመውሰድ ከአዱሊስ የ300 የግሪክ ቋንቋ ዜና መዋዕል «ጋዝ» ከተባለው ስም ጋር አቀናጅቶ በዓመተ ዓለም በግምት ከ7ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ «በኋላቀሩ» የአፍሪካ ዓለም የኢትዮጵያን ጥንታዊ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ኃይሎች ናቸው በማለት «ሀበሻ» እና «አጋዓዚያን» የሚላቸውን ሁለት «ምርጥ» ሴማዊ የአረብ ነገዶች ፈጥሮ ለዓለምና ለትውልድ ተረቱን በድፍረት አሳወቀ።[193]

ለማንም የሚገርመው ጉዳይ ግን በተጠቀሰው ጽሑፍ፥ ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት በአረቢያና በኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች በጥንታዊ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በተጻፉና ከላይ በቀረቡ የግሪክ፥ የአዱሊስ፥ የአጼ ኢዛና፥ የአጼ ካሌብና የንጉሥ አብርሃ ታሪካዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች መሠረት፥ የተለያዩ የአክሱም ነገሥታት ከኢትዮጵያ ቀይ ባሕርን ተሻግረው በአረቢያ ቢያንስ በአራት ልዩ ልዩ ክፍለ ዘመናት ያካሄዱዋቸውን መታደራዊ የእስትራቴጂ፥ የግዛትና የገበያ ዘመቻዎችን በትክክል ካስቀመጣቸው በኋላ ከጥናቱ ተጨባጭ ስነዳዊ መረጃዎችና ግኝቶች ውጭ የኢትዮጵያን አገር በቀል ባህል፥ ታሪክና ሥልጣኔ የሚያፈርስ ዘረኛ አስተያየቱን እንደሚከተለው ሰነዘረ።

በኢጣሊያኑ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ በሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ ብርቱ እምነትና ትምህርት መሠረት፥ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያው ስድስት ምዕተ ዓመታት ከኢትዮጵያ ተነስተው ከላይ የቀረቡትን የእስትራቴጂ፥ የግዛትና የገበያ ዘመቻዎች ያካሄዱ ኢትዮጵያውያን ነባርና ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች ሳይሆኑ አስቀድሞ በግምት ከ1000 ዓመታት በፊት ገደማ ማለትም በ700-500 ዓመተ ዓለም አካባቢ ከምድረ አረቢያ ቀይ ባሕርን በባቤልመንደብ ሰርጥ ተሻግረው ለመጀመሪያ ጊዜ «ኋላቀሩ» በተባለው የአፍሪካ ምድር በአብሩ ኩሻዊ ሕዝብ ላይ በኋላ «ለምርጥ» ሴማዊ የአክሱሙ መንግሥትና ሥልጣኔ መሠረትና መነሻ የሚሆነውን ሴማዊ አገርና ጎብረተሰብ በየህ

[193] Conti Rossini, "Expeditions et Possessions", pp. 5-36.

ደጋ አምባ ላይ የቆረቆሩና «ሀበሻት» እና «አጋዓዚያን»[194] የተሰኙ ሁለት ወራሪ የአረብ ነገዶችና ተወላጆች ናቸው።

ባጭሩ፥ ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒና ተባባሪዎቹ የጀርመን፥ የኢጣሊያ እና የይሁዲ ሴሚቲስት የቋንቋና የታሪክ ምሁራን ለምሳሌ አውጉስት ዲልማን (1823-1894)፥ ኢኖሲዮ ጉይዲ (1844-1935)፥ ኢኖ ሊትማን (1875-1958)፥ በኋላም ኤድዋርድ ኡለንዶርፍ፥ ምልፍ ሌስላውና ብዙ ሌሎችም ከተማሪዎቻቸውና ከተከታዮቻቸው ጋር የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ ፈጣሪ ባለቤቶች «ሀበሻት» እና «አጋዓዚያን» የተሰኙ ሁለት ሴማዊ የአረብ ነገዶች ናቸው የሚል ተረታቸውን በስመ ሳይንስ ለማሳመን «የሳባ ፊደል» ነው የሚሉትን የኢትዮጵያን አገር ወለድ የጽሕፈት ሥርዓትና «ሴማዊ» የተሰኙ ስምንት የግዕዝ፥ የትግረ፥ የትግሬ፥ የአማራ፥ የአርጎባ፥ የሐረሪ፥ የጉራጌና የጋፋት ቋንቋ ማኅበረሰቦችን እንደዋና መረጃዎች አድርገው ያቀርባሉ።[195]

ነገር ግን፥ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ባለፉት አምሳ ዓመታት ውስጥ በከፍተኛ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር በተገኙ ዘመናዊ የአርኪኦሎጂና የሊንጉዊስቲክስ ማለትም የሥነልሳን መረጃዎችና ግኝቶች መሠረት፥ እንደኛ፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት የተገኘው፥ የኢጣሊያን፥ የጀርመንና የይሁዲ ሴሚቲስት የቋንቋና የታሪክ ምሁራን እንደገመቱት፥ በአረቢያ ዛሬ ከገጸምድር ከጠፋው የሳባ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ሳይሆን ከራሱ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ነው።[196] ሁለተኛ፥ በጥንቱ ዓለም ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች በአረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ከአፍሪካ በፍለሳና በሰፊራ እንቅስቃሴ ከመገኘታቸው በፊት ቢያንስ ለ8,000-10,000 ዓመታት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ይኖሩ እንደነበር አሁንም የቋንቋ ሳይንቲስቶች ያስተምራሉ።[197]

[194] Ibid., pp. 6-20.

[195] Littmann, DAT, IV, Inscriptions; E. Ullendorff, The Semitic Languages of Ethiopia (1955); W. Leslau, "South-East Semitic: Ethiopic and south Abrbic", "South-East SemiticAmerican Oriental Society, Vol. 63 (1943), pp. 4-14; Budge, History, pp. 551-553,557.

[196] Drewes, Inscriptions; Schneider, "Deux Inscriptions".
_____, " Histoire".
_____, "Evolution of the Ethiopian Writing".
_____, " Daamatite State, Kings, and Gods".

[197] Murtonen, Early Semitic: A Diachronical Inquiry into the Relationship of Ethiopia to the Other so-called South-East Semitic Languages, (Leiden: Brill, 1967):
___, G. Hudson, "Language Classification and the Semitic Prehistory of Ethiopia", Folia Orientalia, Vol. 18 (1977), pp. 119-166.

ስለሆነም የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥት፥ ሥልጣኔና ታሪክ ከአረቢያ «ሀበሻ» እና «አጋዓዚያን» የተሰኙ ሴማዊ የአረብ ነገዶች ሥራ ነው የሚለው የእነኮንቲ ሮሲኒ ቲዮሪ በተጨባጭ የታሪክ መረጃ ላይ ያልተመሠርተ ተረት ነው። በሌላ በኩል ሀበሻ የተሰኘው ስም ግን አጎራባቹ አረቦች ለሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ጥቁር ሕዝቦች በሙሉ የሰጡት የመጠሪያ ስም ነው። በመሆኑም ስሙ የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ አንድ ሕያው አካልና መግለጫ ነው ለማለት ግን ይቻላል።

የአረቦቹ የአፍሪካውያን ግንዛቤና ስያሜ

የአፍሪካ ምድር ሕዝቦች ጥንታዊ ስያሜዎች ከሞላ ጎደል ሁሉም ከሦስቱ የይሁዲዊ፥ የግሪክና የአረብ ሕዝቦች የተሰጡ የሕዝብና የአገር መጠሪያ ስሞች ናቸው። ለምሳሌ በቅደም ተከተል በታችኛው የዓባይ ሸለቆ፥ በላይኛው የዓባይ ሸለቆና በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የካም-ኩሽ ልጆችና ዘሮች ናቸው ተብለው የተጠቀሱት ሦስቱ የጥቁር አፍሪካ የመጀመሪያ ሕዝቦችና መንግሥታት ግብፅ፥ ኩሽና ፑንት በዓለም ሥልጣኔ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የታወቁት ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በነቢዩ ሙሴ ተጻፈ በሚባለው በይሁዳውያኑ የፍጥረት ታሪክ መጽሐፍ ማለትም በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 10 ነው።

እንዲሁም በጊዜና በታሪክ ከሴማዊ ይሁዳውያኑ በኋላ የተነሱት ግሪኮች ኩሽ/ኑቢያን ጨምሮ ከምድረ ግብፅ በታች ለሚኖሩ መላ የጥቁር አፍሪካ ነባር ሕዝቦች «ኢትዮጵያ» የተሰኘ አንድ የወል ስም ሰጡ። የስሙም ገላጭ ትርጉም ጥቁር ሕዝብ/ሕዝቦች ማለት ነው። አረቦች ደግሞ በዘመናቸውና በቋንቋቸው፤

1) በአጠገባቸው በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለሚኖሩ ጥቁር ሕዝቦች «ሀበሻ» የተሰኘ የወል ስያሜ፤
2) በጥንታዊ የግሪክ፥ የሮማውያንና የአረብ ሰነዳዊ መረጃዎች መሠረት፥ በግምት ከ100 ዓመተ ዓለም እስከ 1400 ዓመተ ምህረት ገደማ ድረስ ለ1500 ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ ምሥራቃዊ ጠረፍ ግለትም በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በሰሜን ከጉአርዳፉይ ጫፍ አንስቶ በደቡብ ምስራቅ እስከ ዛንዚባርና ሞዛምቢክ ድረስ በሚገኘው ረጅም ክፍለ አህጉር ለነበሩና

___, "Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory", Abbay, Vol. (1978), pp. 71-85; Bernal, Black Athena, pp. XXIV-XXVI, 11-12.

አዛኒያ ተብለው ለሚታወቁ ጥቁር የባንቱ አፍሪካውያን «ዘንጅ»[198] የተሰኘ የወል ስያሜ፤

3) ኩሽ/ኑቢያን ጨምሮ በማዕከላዊና በምዕራብ አፍሪካ ክፍላተ አህጉር ለሚኖሩ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች ደግሞ «ሱዳን» የተሰኘ የወል ስያሜ ማለትም በሦስት በተለያዩ ክፍላተ አህጉር ለተሰራጩ አፍሪካውያን ሦስት ልዩ ልዩ የወል ስሞች እንደሰጡ ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል። በአረቦቹ ዘንድና አንደበት የሦስቱም ስያሜዎች ገላጭና ማዕከላዊ ትርጉም አረብ ያልሆነ ጥቁር ሰው ጥቁር ሕዝብ እንደማለት ነው።

በመሆኑም «ሀበሻ» አረቦች ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦችን ከሚጠሩባቸው ሦስት የወል ስሞች አንዱና የመጀመሪያ ስያሜ ነው። ነገር ግን «ሀበሻ» «ሀቢሽ» ከሚለው የአረብ ቅጽል የወጣ ቅይጥ፥ ድብልቅ ማለት ነው የሚለው ተረትና ትውፊት በዚህ ጥናት ከላይ ከቀረበው ከስሙ ውስብስብና ረጅም ታሪክ ጋር አብሮ የማይሄድ ኢታሪካዊ ትረካ ነው። ምክንያቱም ጥቁር ሰው ማለት ቅይጥ ወይም ድብልቅ ዕቃ፥ ነገር ነው ማለት አይደለምና።

የኢትዮጵያ የአገርና የመንግሥት ስያሜ ረጅም ታሪክ

ከጊዜና ከታሪክ አኳያ የአረቦቹ «ሀበሻ» የሚሰው ገላጭ የሕዝብና የአገር ስም በኢትዮጵያ ምድር፥ ቤተ መንግሥትና ታሪክ ከአፊሴላዊ ፕሮቶኮል አንፃር ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ በሰንድ ተጽፎ የተገኘው አረቢያ የኢትዮጵያ የባሕር ማዶ ግዛት በነበረበት ዘመን በሦስቱ የግሪክ፥ የሳባና የግዕዝ ቋንቋዎች የፀረኔ ጦርነት አስመልክቶ በድንጋይ ላይ በተቀረፀው በአጼ ኢዛና ዜና መዋዕል በሁለቱ የሳባና የግዕዝ ቋንቋ ቅጅዎች «ኢዛና የአክሱም፥ የሕሜር፥ የረይዳን፥ የሐበሡት፥ የሳባ፥ የሰልሐን፥ የፅያሞ፥ የካሱ፥ የቤጃ፥ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ»[199] ተብሎ በተገለፀው ታሪክ ነው። ከዚያ በፊትና በኋላ ኢትዮጵያውያን «ሀበሻ» የሚለውን ስም የአገራቸውና የመንግሥታቸው አፊሴላዊ ስያሜና መግለጫ አድርገው የተጠቀመበት ሥፍራና ጊዜ መኖሩ እስከ ዛሬ ድረስ ከታሪክ መረጃና ትምህርት አይታወቅም።[200]

በመሆኑም ከላይ በጠቢያ መጽሐት በቀረበው ጽሑፍ ሀበሻ የተባለው «ስም ለአገሪቱ መጠሪያ፥ ለሕዝብ መታወቂያ ሆኖ ለብዙ

---

[198] Doresse, Histoire Sommaire, pp. 116-134.
[199] Littmann, DAT, Vol. 4, Inscriptions, Nos. 6, 7, pp. 10-12.
[200] Schneider, "Histoire", p. 49.

ዘመናት ማገልገሉ እየታወቀ» ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ የተመረጠ በትን ምክንያት አስመልክቶ የተሳሳውን ትምህርታዊ የግንዛቤ ጥያቄ በሚመለከት፥ ከታሪክ አኳያ ከሁሉ በፊት «ኢትዮጵያ» የሚለው የግሪክ ስም በግምት ከ1500 ዓመተ ዓለም እስከ 63 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1563 ዓመታት ውስጥ በ13 ልዩ ልዩ ደራሲያን በተፃፉ በ15 ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በአርባ በሚቆጠሩ ሥፍራ ዎችና ጊዜያት ማለትም፤

በአሪት ዘፍጥረት 2:13፥ በአሪት ዘሀልቁ 12:1፥ 8:9፥ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 19:9፥ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 14:9፥ 16:8፥ 21:16፥ በመጽሐፈ አስቴር 1:1፥ 8:9፥ በመጽሐፈ ኢዮብ 28:19፥ በመዝሙረ ዳዊት 68:31፥ 87:4፥ በትንቢተ ኢሳያስ 11:11፥ 18:1፥ 20:3-5፥ 37:9፥ 43:3፥ 45:14፥ በትንቢተ ኤርምያስ 13:23፥ 38:7፥ 10፥ 12፥ 39:16፥ 46:9፥ በትንቢተ ሕዝቅኤል 29:10፥ 30:4:5:9፥ 38:5፥ በትንቢተ ዳንኤል 11:43፥ በትንቢተ አሞፅ 9:7፥ በትንቢተ ናሆም 319፥ በትንቢተ ሶፎንያስ 2:12፥ 3:10፥ በሐዋሪያት ሥራ 8:27I በተሰኙ ምዕራፎችና ቁጥሮች በላይኛው የዓባይ ሸለቆ በዘመኑ በግብፃውያኑ «ኑቢያ»፥ በይሁዳውያኑ ደግሞ «ኩሽ» ተብሎ ከላይ የቀረበ ያንድ ጥንታዊ የጥቁር አፍሪካ የሕዝብና የአገር ስም ትርጉም ነው።

የይሁድውያኑ ብሉይ ኪዳን (መጽሐፍ ቅዱስ) በ280-150 ዓመተ ዓለም በግብፁ የእስክንድሪያ ከተማ ከይሁዳውያኑ ቋንቋ ወደ ግሪክ በተተረጎመ ጊዜ በመጽሐፉ ኩሽ የተሰኘው የሕዝብና የአገር ስም «ኢትዮጵያ» ተብሎ ተተካ። እንዲሁም ከስምንት ምዕተ ዓመታት በኋላ በዘመነ ክርስትና በ5ኛው ምዕተ ዓመት በአክሱም ከተማ መጽሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በተተረጎመ ጊዜ አሁንም «ኢትዮጵያ» ተብሎ ተገለበጠ።

በመጽሐፍ ቅዱስ በይሁዳውያኑ «ኩሽ» በኋላ በግሪኮች «ኢትዮጵያ» የተሰኘው የዚህ የአንድ የጥቁር አፍሪካ ጥንታዊ የሕዝብ፥ የአገርና የመንግሥት ስም ታሪካዊ መነሻና መጨረሻ አስመልክቶ ይህ ጸሐፊ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* በተሰኘው ጥናቱ አሳጥሮ እንዳስቀመጠው፤

በጥንትና በመካከለኛ ዘመናት የዓለም ታሪክ *ኩሽ፥ ኑቢያ፥ ኢትዮጵያ፥ ናፓታ፥ ሚሮዌ፥ ናቡዩ፥ መኩሪያ፥ አልዋና ፋንጅ* ተብለው በብዙ ተከታታይ ስሞች በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የሚታወቁ ማኅበረሰቦች፥ ሕዝቦችና አገሮች በግምት ከ3000 ዓመተ ዓለም እስከ 1820 ዓመተ ምህረት ድረስ በ4820 ዓመታት ውስጥ በላይኛው የዓባይ

ሸለቆ በሰሜን ከዛሬው የአስዋን ግድብ አጠገብ፥ ከዓባይ ወንዝ የመጀመሪያው ፋኋቴ አንስቶ በደቡብና በምስራቅ እስከ አክሱማውያኑ ያልተወሰነ ጠረፍ ክልል ድረስ ባለው ምድር በየጊዜው በፈረቃ የተነሱ ተዛማጅ የጥቁር አፍሪካ ጥንታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ናቸው።

ከእነዚህ ስሞች ኩሽ፥ ኑቢያና ናፓታ ለተጠቀሱት ተዛማጅ ሕዝቦችና አገሮች የጥንታዊ ግብፃውያንና የሴማውያን ስያሜዎች ናቸው። ግሪኮች ግን የተጠቀሱትን ሕዝቦችና አገሮች ጨምሮ ከግብፅ በታች የሚገኙ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦችንና አገሮችን በሙሉ የኅሳ፥ የቋንቋ፥ የባህል፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳያደርጉ በጥቁር የቆዳ መስፈርት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሚል የወል ስያሜ ይጠሩ እንደነበር ተገልጿል። ሚሮዌ ለጥንታዊው ኑቢያ በኋላ የግሪኮች፥ የሮማውያንና የአክሱማውያን ስም ነው። ናቡዩ፥ መኩሪያ፥ አልዋና ፋንጅ ደግሞ በዘመነ ክርስትና በክልሉ የተነሱ አናሳ መንግሥታት ናቸው። የእነዚህ ጥንታዊ የላይኛው ዓባይ ሸለቆ ሕዝቦችና መንግሥታት ሥልጣኔና ቋንቋ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይገለፅና ሳይታወቅ በከርሰ ምድር ተቀብሮ ይኖራል።

ከጊዜ በኋላ በጦርነት፥ በሃይማኖትና በንግድ መንገዶችና ምክንያቶች ከ640ዎቹ ጀምሮ በአካባቢው የተስፋፉ አረቦች የተጠቀሱ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦችንና አገሮችን «ሱዳን» በሚል የአረቦች ስም መጥራት ጀመሩ። ከላይ እንደተባለው፥ «ሱዳን» (ቢላድ አል-ሱዳን) የሚለው ስም ራሱ ለጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች የአረቦቹ የወል ስያሜ ነው። ለምሳሌ ነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያውያን ወዳጆቹን «ሀበሾች» እና «ሱዳኖች»[201] እያለ በተለዋጭ ስሞች ይጠራቸው ነበር። ባጭሩ ኢትዮጵያ፥ ሱዳን፥ ሀበሻና ዝንጅ የተሰኙ ስያሜዎች ሁሉ ከሶስ ግሪኮችና አረቦች ለጥቁር አፍሪካውያን የተሰጡ ገላጭ የሕዝብና የአገር ስሞች ናቸው።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ጥንት በላይኛው ዓባይ ሸለቆ በመጽሐፍ ቅዱስና በዓለም ታሪክ ይይሁዳውያኑ «ኩሽ»፥ በግብፃውያኑ «ኑቢያ»፥ በግሪኮቹ «ኢትዮጵያ»፥ በአረቦቹ «ሱዳን» የተሰኘው የጥቁር አፍሪካ ሕዝብና መንግሥት በዘመኑ ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር ነባርና ሉአላዊ የቱንት፥ የደአማት፥ የአክሱም፥ የአገው፥ የሰሜን/ፈላሻ ተከታታይና ተዛማጅ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር ብሎም ከዛሬው የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያውያን ጋር በሥፍራ፥ በጊዜ፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በሃይማኖት፥ በሥርዓትና በታሪክ ቀጥተኛ

[201] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 108.

ግንኙነት መኖሩን በተጨባጭ መልክና መንገድ የሚያሳይ የሰነድ፥ የቋንቋ ወይም የአርኪኦሎጂ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ገና አልተገኘም።

በተጨማሪም የጥንት ይሁዳውያንንና ፑንታውያንን ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት፥ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለዛሬ ኢትዮጵያውያን ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት አንድ ታሪካዊ መነሻና ምንጭ የሆነው የጥንት ሕዝብና መንግሥት በግምት ከ1500 እስከ 400 ዓመተ ዓለም ድረስ በ1000 ዓመታት ውስጥ በይሁዳውያኑ መጽሐፍ ቅዱስ *በአሪት ዘፍጥረት ም. 10 ቁ 6፥ በትንቢተ ሔርምያስ ም. 46 ቁ 9፥ በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. 27 ቁ 10፥ ም. 30 ቁ 5፥ ም. 36 ቁ 5* በድምሩ በአምስት ልዩ ልዩ ሥፍራዎችና ጊዜያት ብቻ በጨረፍታ ተጠቅሷል።

በአጭርና በጥቅል አነጋገር፥ በዘመነ ክርስትና *በመጽሐፍ ቅዱስና በክብረ ነገሥት* ከመካከለኛው ምስራቅና ከግብፅ በግዕዝ ትርጉም ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ኩሽ-ኑቢያውያንና ይሁዳውያን የተሰኙ ጥንታዊ ሕዝቦች ከጥንቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካውያን ጋር በንግድ፥ በሃይማኖት፥ በባህል የጠራቸውን ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያሳይ ተጨባጭ የታሪክ መረጃና ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ ገና አልተገኘም።

በሌላ በኩል፥ በዚህ ጥናት ከላይ እንደተመለከተው፥ በዓመተ ዓለም ቦዝም ከ2800 እስከ 1000 ድረስ ለ1800 ዓመታት ገደማ በጥንታዊ የግብፅና የጥንት አገሮችና መንግሥታት መካከል በምድርና በባሕር መንገዶች በንግድ፥ በሃይማኖትና በባህል ረጅም የመስተጋብርና የመወራረስ ዘመናትና እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ከግብፃውያኑ የሃይሮግላፊክስ ዘገባዎችና ግኝቶች አሁን በሥፍራ፥ በጊዜና በታሪክ መስፈርት በትክክል ታውቋል።

ይህ በጥንታዊ የግብፅና የጥንት ሕዝቦች መካከል በንግድ፥ በሃይማኖትና በባህል የነበረው ረጅም ግንኙነት በብዙ የውስጥና የውጭ ግፊቶችና ምክንያቶች በ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ ከተቋረጠ በኋላ ቦሚቀጥሉት 1640 ዓመታት ውስጥ፤

አንደኛ፥ በ700-100 ዓመተ ዓለም አካባቢ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋ ክፍል የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማትና የአክሱም ሉአላዊ መንግሥታት በተከታታይ ተነሱ።

ሁለተኛ፥ በተመሳሳይ ዘመን እንዲሁም በአጎራባቹ ደቡብ አረቢያ በፅጣን፥ በመዒ፥ በክርቤና በቀረፋ ቅመማቅመም ምርትና ንግድ የተሰማሩ የሚና፥ የሳባ፥ የቀጣጥን፥ የሚያርና የሃድራማዊ አናሳ መንግሥታት ተከሰቱ።

ሦስተኛ፥ በዓመተ ዓለም በ6ኛው ምዕተ ዓመት በላይኛው የዓባይ ሸለቆ የሚርዌ[202] መንግሥት ተነሳ።

አራተኛ፥ ጥንታዊው የግብፅ መንግሥት በ525-404 በፋርሳ ውያን፥ በ332-30 በግሪኮች እጅ ወደቀ። ከ30 ዓመተ ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በሮማውያን ተገዛ። በ642 በሙር ተይዘ የአረቦች አገር ሆነ።

ባጭሩ እነዚህ የዘመኑ ታላላቅ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕር፥ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ ሕዝቦችና አገሮች የጂኦ-ፖለቲካ ክስተቶች፥ ኃይሎች፥ ለውጠችና እንቅስቃሴዎች ናቸው በተጠቀሰው ረጅም ዘመን በንግድ፥ በሃይማኖት፥ በቋንቋ፥ በባህልና በእስትራቴጂ ጉዳዮች፥ መስኮችና መንገዶች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ኢትዮጵያውያንን ከሰባር የቀይ ባሕር፥ የአረቢያ፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የመካከለኛው ምስራቅና የሜዲትራኒያን ጥንታዊ ሕዝቦች፥ መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች በቅርብ ያገናኙ ዋቸው። ለምሳሌ በዚሁ ዘመን ነበር ከውጭ ግሪኮች «ኢትዮጵያ» አረቦች ደግሞ «ሀበሻ» የተሰኙ የወል ስያሜዎችን ለሕዝቡና ለአገሩ የሰጡት።

ከሁሉም በላይ በዚሁ በተጠቀሰው ዘመንና መንገድ ነበር በአገሩ ነባርና ሉአላዊ የደአማት-አክሱም አዋማዊ ጎብረተሰብና መንግሥት የኢኮኖሚ ታህታይና የፖለቲካ ላዕላይ መሠረቶችና መዋቅሮች ላይ የተጠቀሱት የውጭ ኃይሎች የተለያዩ የንግድ፥ የባህል፥ የትምህርት፥ የፖለቲካና የእምነት ግፊቶች ከሦስቱ መለኮታዊና አህጉራዊ የክርስትና፥ የአረትና የእስልምና ሃይማኖቶች ጋር ለኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ጎብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ ክስተትና ዕድገት ሁሉም አንፃራዊ አስተዋፃአ ያደረጉት።

የዚህን የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ጎብረተሰብና መንግሥት ስያሜ በሚመለከት፥ ከታሪክ ትምህርትና ተግባራዊ ልምድ እንደሚታወቀው፥ በጥንት ዘመን በየትኛውም ክፍለ ዓለም የሕዝብና የአገር ስም ጥያቄ የሚነሳው በአመፃኞ ከአገር መሪ፥ መንግሥት ወይም ኩነማ ጋር በተያያዘ መንገድና መልክ ነው። ከዚህ አኳያ ለምሳሌ፥

1. በዓመተ ዓለም በ4ኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ በሳባ ፊደልና ቋንቋ የተፃፈ የአንድ የደአማት ንጉሥ የረበህ ልጅ ለመነ ዜና

[202] P. L. Shinnie, Meroe: A Civilization of the Sudan, (1967), p. 33.

መዋዕል የንጉሡን ስም ከአገሩ ስም ጋር አጣምሮ «ለመነ የረበሀ ልጅ የደአማታውያን፥ የሳባውያን፥ የአበራውያን፥ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ» ይላል።

2. በዘመነ ክርስትና በ183 በምድረ አረቢያ በሳባ ቋንቋና ፊደል በተጻፈ ዜና መዋዕል የዘመኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ ስም «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» ተብሎ ተጽፏል።
3. በአረቢያ በሳባ ዜና መዋዕል «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» በዚያው ዘመን በኢትዮጵያ በግዕዝ ቋንቋና ፊደል በተጻፈ ዜና መዋዕል «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» ተብሎ ቀርቧል።
4. በ4ኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ በሦስቱ የግዕዝ፥ የግሪክና የሳባ ቋንቋዎች የተጻፈው የአጼ ኢዛና ዜና መዋዕል «ኢዛና የአልአሜዳ ልጅ የንገደ ሐሌን፥ የአክሱም፥ የሀሜር፥ የረይዳን፥ የኢትዮጵያ፥ የሐበሠት፥ የሳባ፥ የሰልሐን፥ የጽያሞ፥ የካሱ፥ የቤጃ ንጉሠ ነገሥት» ይላል።
5. በ6ኛው ምዕተ ዓመት በአረቢያ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው የአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ደግሞ «ካሌብ የኢዛና ልጅ የአክሱም፥ የካሱ፥ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሐን፥ የትአሞ፥ የቲሃማት፥ የራባም፥ የኖባ፥ የአራባት፥ ንጉሥ» ብሎ ከንጉሡ ስም ጋር የብዙ ሕዝቦችንና አገሮችን ስም ይጠራል።
6. በ6ኛው ምዕተ ዓመት በሳባ ቋንቋና ፊደል የተጻፈው በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ አብርሃ ዜና መዋዕል «የሳባ፥ የዲሁረይዳን፥ የሃድራማዊ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የደጋና ቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የንገደ ግዕዝ ተወላጅ» ይላል።

እነዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ ቁልፍና ወሳኝ የሆኑ የሰነድ መረጃዎች የተጻፉት በማም ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በአንድ ሚሊኒየም ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ ረገድና ተግባር ከላይ በሠንጠረዥ 4 - 5 በቀረቡ መረጃዎች እንደተመለከተው፥ በአንድ በኩል እነዚህን ልዩ ዜና መዋዕሎች ጨምሮ ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በአንድ ሺህ ዓመታት ዘመን ውስጥ በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በጣዕመ በአምሳ በተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎች በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች በድንጋይ ላይ የተፃፉና በ500 የሚቆጠሩ ጽሑፎች በ1804-1981 ሰላሳ በሚሆኑ ተመራማሪ ምሁራን ጥናት ተገልጸው ለዓለምና ለትውልድ ለመጀመሪያ ጊዜ ታውቋል።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ ከላይ እንደተጠቆመው፥ በ550-1300 'ጨለማ' ዘመን በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት በድንጋይ ላይ ሆነ በብራና የተፃፈ አንድም የጽሑፍ ሰነድ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።[203] በመሆኑም በ550-1300 'ጨለማ' ዘመን ውስጥ የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት በሚመለከትም ሆነ የአገው መንግሥት ከክተትና ፍጻሜ ወይም የአጉኔና የመንግሥቱን ስያሜ በሚመለከት ምንም ተጨባጭ የታሪክ መረጃና ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። ይህን አስመልክቶ የእንግሊዙ ታዋቂ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ምሁር ዶክተር ዋሊስ ባጅ እንዳስቀመጠው፥

> *The truth is that Abyssinians know nothing about the true history of their country in pre-Christian times. They have always had a passionate desire to be considered a very ancient nation, and the vivid imagination of their scribes has borrowed the traditions of historical facts preserved by the Semites, i.e. Yamanites, Himyarites, Hebrews, etc., and modified them to suit the aspiration of their fellow-countrymen ... The first "King of the Kings of Ethiopia" known to us is Yekuno-Amlak (A. D. 1270-1285), who brought the whole country under his rule.*[204]
>
> *The history of Abyssinia during the Christian Era, as presented by chroniclers and scribes, until we come to the second half of the 13th century, is incomplete and, in some respects, is wholly untrustworthy ... It is the sad fact that no Ethiopic manuscript older than the 14th century is known to exist.*[205]
>
> *Contradictions, anacronisms and confounding of the names of persons and places are common in works dealing with history and chronology, and prove that their authors and copyists lacked the ability to write history as we understand it. Much confusion has been caused by the mistakes made in copying by ignorant and sleepy and careless scribes,*[206]

ይህ ሁሉ ከሆነና ከተባለ በኋላ በስሜን ምስራቅ አፍሪካ ከፍለ አህጉር አጎራባች አረቦች «ሀበሻ» ብለው ለሚጠሩት ለአንድ የጥቁር አፍሪካ ጥንታዊ ሕዝብና አገር «ኢትዮጵያ» የተሰኘው የግሪኮች ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የተሰጠው፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314- 1344) በ1320 ገደማ[207] በአክሱም ቤተ ክርስቲያን መነኩሳት ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ

---

203 Budge, History, p. XI.

204 Ibid., p. X.

205 Ibid., XI.

206 Ibid., p. XII.

207 Donald N. Levin, Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society, (1974), p. 100.

በተተረጎመው የክብረ ነገሥት መጽሐፍ ነው።[208] የሰነዱ የአረብኛው ረቂቅ የተጻፈው «ሀበሻ» በሚል ስም ነው። በኋላ በ17ኛው ምዕተ ዓመት በሃይማኖት ትምህርት ልዩነትና ግጭት ተሸንፈው ከኢትዮጵያ የተባረሩ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን «ሀበሻ» የተሰኘውን የአረብ ስያሜ «አቢሲኒያ» በሚል ላቲናዊ ትርጉም በምዕራቡ ዓለም እስከ ሀያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ በጽሑፍ አሰራጩ።

በሌላ በኩል በአገር ውስጥ በ1931 በአጼ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥት «ኢትዮጵያ» የሚለው የግሪኮች ስም በመጨረሻ የሕዝቡ የአገሩና የመንግሥቱ ሕገ መንግሥታዊ ስያሜ ተደርጎ ተደነገገ። በቀጣይ ሦስት የኢትዮጵያ የ1955፥ የ1987 እና የ1994 ሕገጋተ መንግሥትም እንዲሁ ተደነገገ። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ሁለቱም የአረቡ «ሀበሻ» እና የግሪኩ «ኢትዮጵያ» ነባር የጥቁር አፍሪካ ሕዝቦች የወል ስያሜዎች ናቸው።

[208] Budge, Queen of Sheba, p. 228.

መደምደሚያ

የውጭ አገር አስተማሪዎች ትምህርት ተጽዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ

የኢትዮጵያ የ1974 ሕዝባዊ አብዮት የቀድሞ ዘውዳዊ ሥርዓትን ከጉልተኛው የፖሽ መደብ ጋር በማስወገድ የአገሪቱን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ባዲስና ሁለአቀፍ የጥናት ዘዴ (ሜቶዶሎጂ) ከስልተ ምርትና ከሥርዓተ ማህበር አኳያ፥ ከአዳዲስ የመረጃ ምንጮች አኳያ፥ ከአዲስ የኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረተሰብ ግምባታ አኳያ ለማጥናትና ለማወቅ ብዙ አስፈላጊና ምቹ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን፥ ምክንያቶችንና መንገዶችን ፈጥሯል። ስለሆነም በዚህ ወቅትና ሁኔታ ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪካዊ መነሻና ማንነት በሚመለከት ባገር ውስጥ ባለፉት 2500 ዓመታት፤

1) በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1000 ዓመታት በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው ባለፉት 200 ዓመታት ከከርሰ ምድር የተገኙ ጥንታዊ ሰነዶች፤
2) በዘመነ ክርስትና በግምት ከ1270 እስከ 1855 ድረስ በ585 ዓመታት በግዕዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች፥ የካህናት ገድለ ቅዱሳንና ገድለ ሰማዕታት፤
3) ከ1855 እስከ 1974 ድረስ በ120 ዓመታት በአማርኛ ቋንቋ በቤተ መንግሥት ባለሟሎች የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች፥ ገድለ ካህናትና የመሥሪያ ቤት መዛግብት እስከ 1974 ሕዝባዊ አብዮት ድረስ የተለያዩና ቁልፍ የሆኑ የታሪክ መረጃ ዓይነቶችና ምንጮች ናቸው።

በመጀመሪያው ክፍል የተጠቀሱና በድንጋይ ላይ የተጻፉ ጥንታዊ ሰነዶች የኢትዮጵያን የጎብረተሰብ፥ የመንግሥትና የታሪክ መነሻ በሚመለከት ቁልፍና ወሳኝ የሆኑ የመረጃ ምንጮች ናቸው። በመሆኑም ይህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ጥናት በአመዛኙ የተመሠረተው በተጠቀሱ ጥንታዊ ቁልፍ ጽሑፎች ላይ ነው።

በሌላ በኩል በዘመነ ክርስትና በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ ለስምንት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ የክርስቲያን ቤተ መንግሥትና ምድር በድንጋይ ላይ ሆነ በብራና የተጻፈ አንድም ሰነዳዊ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። በዚህ ረጅም የታሪክ መረጃ ባልተገኘበት የጨለማ ዘመን በኢትዮጵያ ከአክሱም ቀጥሎ የተነሳው የአገው የክርስቲያን መንግሥት (1100-1270) ባለሥልጣኖች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ረጅም ግዛት ነፃ ለማውጣት ለመጀመሪያ ጊዜ ያልተሳካ የፖለቲካ እርምጃ እንደወሰዱ ተረጋግጧል።

ነገር ግን ይህንን የአገው መንግሥት የሻሩት ፖሊሲና እንቅስቃሴ ለማጥፋት እስከዚያ ድረስ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ላይ ለ1000 ዓመታት የነበራትን ከፍተኛ የሥልጣን መብትና የኢኮኖሚ ጥቅም የበለጠ ለማጠናከርና ለማስፋፋት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በአንድ በኩል በአገር ውስጥ፥ በራሱ በአገው ሥርወ መንግሥትና መንግሥት ላይ ተግራሪ የፖለቲካ ኃይሎችን በወኪል አቡኖቹዋ አማካይነት አደራጅታ በተሳካ የፖለቲካ ሴራ ከሸኩዋ አሰለፈች።[1] በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት በአስገቻቸውና ከብረ ነገሥት እና ፍትሐ ነገሥት በተሰኙ ባሕረ መፃብት[2] የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ ሰለሞናዊ የአይሁድ ተረት ቀየረች።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በከብረ ነገሥት ሰነድ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የእክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በ1000 ዓመተ ዓለም በሙሴው የአሪት ሕግና ሃይማኖት ትምህርት የመሠረቱ ከኢየሩሳሌም የመጡ የአይሁድ መሳፍንትና ካህናት ናቸው ብላ በይፋ አወጀች።[3] በ1300ዎቹ በተጻፈው የፍትሐ ነገሥት ሰነድ ደግሞ ከ1000 ዓመታት በፊት በ325 ዓመተ ምህረት በኒቅያ ጉባኤ የተቀመጡ 318 የዓለም አህጉራዊ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን (ማለትም ክርስትና ገና በ330 ዓመተ ምህረት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት) ከግብፃዊው ወኪል አቡን በስተቀር ማንም ኢትዮጵያዊ ተወላጅ በምንም ጊዜና መንገድ የአገሩ የኢትዮጵያ ቤተ

[1] ተክለጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ይኩኖ አምላክ እስከ አጼ ልብነድንግል (1951)፥ ምዕ 4 ፥ Tadesse Tamrat "The Abbots of Debre Hayq 1248-1535", Journal of Ethiopian Studies, Vol. 8, No. 1 (1970), pp. 89-90.

[2] E. A. W. Budge, tr. and ed; The Queen of Sheba and Her only Son Menyelek (1929); Paulos Tzadau, tr. The Fetha Nagest: The Law of the Kings (1918).

[3] Ibid., The Queen of Sheba, pp. 51-84.

ክርስቲያን የበላይ መሪና አስተማሪ እንዳይሆን ወሰነዋል[4] በማለት በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የዘረኝነት መርዛማ ትምህርት በመለከ ታዊው የክርስትና ሃይማኖት ስም መሠረተች።

ባጭሩ የኢትዮጵያን የሕዝብ፥ የመንግሥትና የታሪክ መሻና ማንነት በሚመለከት ጉዳይ ላይ የተጠቀሱ የከብረ ነገሥት እና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግጋት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን የቀረበው የዘረኝነት አስተምህሮ (ማለትም እምነትና ትምህርት) ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት፥ በኢትዮጵያ በሠውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብ፥ መንግሥት እና ታሪክ ላይ ሁለአቀፍ የፖለቲካ፥ የእምነት፥ የትምህርት፥ የባህል፥ የኢኮኖሚ፥ የሰላም፥ የዕድገትና የልማት ችግሮችን ያስከትላል። የጦርነትና የጥፋት መዘዝና መዓት ያደርሳል።

ከ1270 እስከ 1855 ድረስ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች በግዕዝ ቋንቋ በብራና የተፃፉ ዜና መዋዕሎች፥ ገድለ ቅዱሳንና ገድለ ሰማዕታት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን በከብረ ነገሥት እና በፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግጋት በገባ የፖለቲካ አስተምህሮ የሚመራው የኢትዮጵያ ጎብረተሰብና መንግሥት የፖለቲካ፥ የሃይማኖትና የጦርነት ዘገባዎች ናቸው።

ዘገባዎቹ የሚገልፁት ሁኔታዎችና ነገሮች በተጠቀሰው የጦርነት ዘመን ራሳቸውን ሰለሞናውያን ነን ብለው የሰየሙ የኢትዮጵያ ነገሥታት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አሞግዊ፥ አስላማዊና አሪታዊ ሕዝቦችንና መንግሥታትን ለመዝለት ለረጅም ዘመን ያካሄዱ ዋቸውን ወታደራዊና ወንጌላዊ ዘመቻዎችን ነው።

በተጠቀሱ የመንግሥትና የሃይማኖት ሰነዶች የክፍለ አህጉሩ አሪታዊ፥ አስላማዊና አሞግዊ ሕዝቦችና መንግሥታት፥ ሰምሳሌ የአገው፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የይፋት፥ የህዲያ፥ የዳሞት፥ የአዳል፥ የሶማሌ፥ የኦሮሞ... ሕዝቦች በሙሉ የኢትዮጵያ የክርስቲያን ሕዝብ፥ መንግሥትና ሃይማኖት ደመኛ ጠላቶች ናቸው ተብለው ተፈርጀዋል። የተጠቀሱ ሕዝቦች በአገራቸውና በመሬታቸው «ወራሪ» ጠላቶች ተብለው ለቅጣትና ለጥፋት ጠርጅት ተመድበዋል።

በመሆኑም የክፍለ አህጉሩ አሞግዊ፥ አስላማዊና አሪታዊ 'ጠላት' የተባሉ ሕዝቦችና መንግሥታት በተጠቀሱ የክርስቲያን ኃይሎች እና ሰነዶች ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተደርገው አልተወ ሰዱም። ምክንያቱም የክርስትና ሃይማኖት፥ በተጠቀሱ ኃይሎች ዘንድ፥

[4] Paulos Tzadau, The Fetha Nagest, pp. 17-18.

የኢትዮጵያዊነት ብቸኛው መሰረትና ቅድመ ሁኔታ ማተብና ማህተም እንደሆነ ተደርጎ ተወስዷልና።

በቅርቡም በ1855-1974 በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የኢትዮጵያ የአጼው መንግሥት ሰነዶች የአገሪቱን አሞግሟ፥ እስላማዊና አሪታዊ ሕዝቦች፥ መንግሥታትና ሃይማኖቶች በሚመለከት በ1270-1855 የግዕዝ ብራና ከተጻፉ መዛግብት በይዘትና በዓይነት የሚለዩ አይደሉም። ከዚህ አንፃር እንዲያውም በዘመኑ የተነሱ አጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ፥ ዮሐንስ፥ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ በክፍለ አህጉሩ አስላማዊና አሞግሟ ሕዝቦች ላይ የክርስትያን መንግሥትና ጎብረተሰብ ለመገንባት ለቀየሉትና ለተከተሉት ወታደራዊና ወንጌላዊ ፖሊሲና ፕሮግራም ታሪካዊ ሞዴልና መሠረት ተደርጎ የተወሰደው የጥንቱ ሰለሞናውያን ነገሥታት ይኩናአምላክ፥ አምደፅዮን፥ ዳዊት፥ ይስሐቅ፥ ዘርዓ ያዕቆብ፥ ልብነ ድንግልና ገላውዴዎስ ... በክፍለ አህጉሩ ነባር አስላማዊና አሪታዊ ሕዝቦች ላይ በጠንካራ የክርስቲያን ሃይማኖትና ጦር የተማከለ ዘውዳዊ መንግሥትና ሥርዓት ለመገንባት የተጠቀሙት ወታደራዊና ወንጌላዊ ፖሊሲና ፕሮግራም ነው።

ከ1855 እስከ 1935 ድረስ ለ80 ዓመታት የተጠቀሱ አጼዎችና ባለሥልጣኖቻቸው በተለይ በኢትዮጵያ እስላማዊና አሞግሟ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ በሰፋሪ የጦር አበጋዞች፥ ወታደሮችና ቄሶች አማካይነት አጼያዊ የክርስቲያን መንግሥት፥ ሃይማኖት፥ ሥርዓትና ባህል እንደመሠረቱ ሕዝቡንም እንደባዕድ ጠላት በአጉሩና በመሬቱ ላይ ሰብዓዊ የምርጫና የአንቅስቃሴ መብትና ነፃነት የሌለው የመንግሥትና የሰፋሪ ኃይሎች ቋሚ ገባርና ባሪያ አድርገው፥ በጦርና በፈረስ ኃይል የተሸነፈው ሰው የአሸናፊው ባሪያና ገባር ነው በሚለው የፍትሐ ነገሥት አሪታዊ ሕግና ሥርዓት መሠረት፥ እንደገዙት የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ በ1936 ዘውዳዊና አሪታዊ የነፍጠኛ፥ የባሪያና የገባር ሥርዓቶች በኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተደመሰሱ። በዚህ ወቅትና ሁኔታ መሰፍንታዊ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች ከአጼው ጋር ከአገር ተሰደዱ። በመሆኑም የኢትዮጵያ የሰለሞናውያኑ ባሮችና ገባሮች አርነት ወጡ።

በ1941 በእንግሊዝ ጦርና በኢትዮጵያ አርበኞች ጎብረት የኢጣሊያ ወራሪ ፋሽስቶች ከአገር ተባረሩ። የተሰደዱ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከተከታዮቻቸው ጋር ተመልሰው እንደገና የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሆኑ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ተመልሶ ለሚቀጥሉት 33 ዓመታት ወደ ዘውዳዊ ቀምበር ሥር ገባ።

በዚህ ወቅት ከ1941 እስከ 1974 ድረስ የምርጥ መሳፍንቶች፥ መኳንንቶች፥ ካህናት፥ ሚኒስትሮች፥ አገረገዥዎች፥ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች፥ ጉልተኞችና የከተማ ከበርቴዎች ጎብረት መንግሥት በአጼው መሪነትና አዝማችነት በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ጎብረተሰብ ላይ በአንድ በኩል የገዥውን መደብ ሃይማኖትና ቋንቋ ብሔራዊ ሃይማኖትና ቋንቋ አደረገ። በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን የተቀሩ ቋንቋዎችን ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ለማጥፋት የሚያስችል የኢኮኖሚ፥ የትምህርት፥ የባህልና የሃይማኖት ፖሊሲና ሥርዓት ቀይሶ ተግባራዊ በማድረግ ለኢትዮጵያ የ1974 ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታ የራሱን የጎላ አስተዋፅኦ አደረገ።

ከዚህ አኳያ፥ አንደኛ፥ በ1940ዎቹ፥ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ በ19ኛው ምዕተ ዓመት በደቡብ ኢትዮጵያ በመንግሥት ስምና ሥር የተያዘው የአገርና የሕዝብ መሬት በአጼው ፈቃድና ትእዛዝ ከላይ ለተጠቀሱ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች በስፋት በግል ይዞታ ተሰጠ። በዚህ አዲስ የመሬት ፖሊሲ ጉዳይ፥ በ1941-1974፥ «ለገዥው መደብ አባሎች በድምሩ 4,828,560 ሄክታር ማለትም ስፋቱ 4,636,716 ሄክታር ከሆነው ከቀድሞ የኢሉባቦር ክፍለ ሀገር የሚበልጥ ለም መሬት በአጼው ትእዛዝና ስጦታ በርስትነት እንደተሰጣቸው በሰነድ ተመልክቷል።»[5]

ይህ የአጼው የመሬት ፖሊሲና ተግባር በአብዮቱ ዋዜማ በአገሪቱ ውስጥ በአንድ በኩል በመንግሥቱ ላይ የገጠር አርሶ አደሮችንና ብሔረሰቦችን በየአካባቢያቸው በአመፅ አስነሳ። በሌላ በኩል ደግሞ በአዲሱ ጉልተኞች ከመሬታቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች ከገጠር ወደ ከተማና ኢንዱስትሪ አካባቢዎችና ማዕከላት እየተሰደዱ ለከተማና ለወዛደሩ መደብ ዕድገት አንዱና ዋናው ምንጭና ምክንያት ሆኑ። ባጭሩ በድህረ ጦርነት የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥት የመሬት ፖሊሲና ተግባር የገጠሩን አርሶ አደር ወደ ከተሜነት፥ ወዛደርነት፥ ኔጋዴነት፥ ወታደርነት፥ ተማሪነት፥ ቦዘኔነት፥ አሽከርነትና ኩሊነት ለወጠው። በተጨማሪም በገጠር ለብሔረሰብና ለአርሶአደር እንዲሁም በከተማ ለወዛደር፥ ለተማሪ፥ ለአስተማሪ፥ ለነጋዴ፥ ለቦዘኔ ፀረ መንግሥት አመፅ መንገድና ምክንያት ፈጠረ። በሌላ ቃል፥ በራሱ በኢትዮጵያ በህውርታዊ ጎብረ ተሰብና መንግሥት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ታሪካዊ መሰረት፥ ሂደትና ዘመን ተከሰቱ። በኢምፔሪያሊዝም ግፊት፥ በኢትዮጵያ ጥንታ

[5] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም (1983)፥ ገፅ 222።

ዊና ኋለቀር «ምሥራቃዊ» ሥልተምርትና ሥርዓተማኅበር ለአብዮ ታዊ የሥርዓት ለውጥ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎች፥ ኃይሎች እና ግፊቶች ተከሰቱ።

ሁለተኛ፥ በኅሐሴ 1944 በንጉሡ ሁለአቀፍ የቋንቋ፥ የሃይማ ኖት፥ የትምህርትና የባህል ፖሊሲ ድንጋጌ ቁጥር 3 በአገሪቱ ከአንዱ የገዥው መደብ ቋንቋ በስተቀር የተቀሩ ቋንቋዎች በሙሉ የጽሕፈት፥ የትምህርትና የሥራ መዛሪዎች ሆነው እንዳያድጉ በሕግ ተወሰነ።[6] የድንጋጌው መሠረታዊ ዓላማና ተግባር፥ የኢትዮጵያን በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ የአንድ ሕዝብ፥ ቋንቋ፥ ሃይማኖት፥ ባህል፥ ንጉሥ፥ መንግሥትና ሥርዓት አገር ማድረግ ነው።

ሦስተኛ፥ በጥቅምት 1955 በተሻሻለው ሕገ መንግሥት፥ በአንድ በኩል በአንቀጽ 38 እና 40 በይፋ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በሕግ ፊት የእኩልነት መብትና የሃይማኖት ነፃነት አላቸው ተባለ። ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ በአንቀጽ 125 እና 126 ሁለቱ የገዥው መደብ ቋንቋና ሃይማኖት ምርጥ ያገርና የመንግሥት መዛሪያዎችና መግለጫዎች ናቸው ተብለው ተደነገጉ።[7]

አራተኛ፥ በጥር 1956 በንጉሡ ትእዛዝና በጽሕፈት ሚኒስቴር ማለትም በንጉሡ ልዩ ጽሕፈት ቤት ጥብቅ ቁጥጥር ስር «የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር» በተቋቋመበትና በቅርቡ በመጋቢት 1993 ለሕዝብና ለታሪክ ይፋ በሆነ የምሥጢር ሰነድ[8] በአንድ በኩል የገዥ መደቡን ቋንቋና ሃይማኖት ምርጥ ያገርና የመንግሥት ብቸኛ ቋንቋና ሃይማኖት አድርጎ ለማሳደግ፥ በሌላ በኩል ግን የአገሪቱን የተቀሩ ቋንቋዎች በሙሉ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር በመንግሥታዊ ፖሊሲ እና አሠራር ለመጨቆን እስከ 1974ቱ አብዮት ድረስ በተግባር ላይ የሚቆይ የፖለቲካ ውሳኔና እርምጃ ተወሰደ።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከታወቀ በኋላ፥ ከ1855-1974 ድረስ ለ120 ዓመታት የኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ ላይ አህዳዊና ወንጌላዊ የዘውድ መንግሥትና ሥርዓት ለመገንባት

[6] የሚለዮናውያን የግዝር አቋቋም፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ ድንጋጌ ቁጥር 3 (ኅሐሴ 21 ቀን 1936)።

[7] የኢትዮጵያ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት (ጥቅምት 24 ቀን 1948) አንቀጽ 38፥ 40፥ 125፥ 156።

[8] የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር፥ ቤተ መዛግብት ቁጥር 146 (48) ሚያዝያ 8 ቀን 1948)፥ ፣የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጸር የሆነው መንግሥታዊ ሰነድ፥ ጋዜጣ፥ ቁጥር 3 (መጋቢት 1985)።

በተከታታይ ያካሄዱት የምዕክልና ፖሊሲና ፖለቲካ የየካቲት 1974 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በፈነዳ ጊዜ ፈረሰ።

የኢትዮጵያና የኢትዮያውያን ታሪካዊ መነሻና ማንነትን በሚመለከት በሰኔ 11 ቀን 1987 (1995) ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረግኩት ቃለምልልስ፥ «የትኛውም የኢትዮጵያ ዘር መጤ አይደለም፥ ያገራችንን ፖለቲካ ያበላሸው የታሪካችን መባላሸት ነው» በሚል ቲሲስ ያቀረብኩትን ትንታኔ የዚህ ተዛማጅና ቀጣይ ጥናት መደምደሚያ ላደርገው እወዳለሁ።

በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት በስፋትና በጥልቀት እንደተብራ ራው፥ ታሪክ ማለት የሰው ልጅ ያለፈው ዘመን ሥራ፥ ሕይወት፥ ድርጅት፥ ምርት፥ ባህል፥ አምነትና ትምህርት ድምር መግለጫ ነው። ካለፈው ዘመን፥ ሥራና ልምድ በጥናትና ምርምር የሚገኝ እውቀትና ትምህርት ነው። የሰው ልጅ በየዘመኑና በየትውልዱ የያለፈውን ዘመን ባህላዊ ቅርስና ውርስ ማለትም ተጨባጭ የሥራ መረጃና ልምድ በጥናትና ምርምር በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር መለፈርትና ሚዛን መርምሮና አናዝቦ የሚያገኘው ግንዛቤያዊ ልምድ፥ እውቀት፥ ትምህርት ነው። በሌላው ትርጉሙ ደግሞ፥ ታሪክ የማህበራዊ እውቀትና ትምህርት የሚገኝበት ሜቴዶሎጂ ማለትም ስልተ ጥናት ነው። ከተግባር አኳያ ደግሞ ታሪክ የሰው ልጅ ካለፈው ዘመን ልምዳዊ እውቀትና ትምህርት ተነስቶ የሚመጣውን ዘመን፥ ትውልድ፥ ኅብረተሰብ ከሁለቱም ከትላንትና ከዛሬው የተሻለና የበለጠ አድርጎ ለመገንባት የሚችልበት መንገድና መዛሪያ ነው። በዚህ የታሪክ ትርጉምና ትምህርት መሠረት፥ የታሪክ መነሻ ከሰው ልጅ ሥራና ልምድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የሚገኝ የታሪክ መረጃ ነው። በመሆኑም የታሪክ መረጃ በሌለበት ሥፍራና ጊዜ የታሪክ ሜቴዶሎጂም እውቀትም አይኖርም ማለት ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ የኢትዮጵያን በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ መነሻ፥ ይዘት፥ ጥናትና ትምህርት በሚመለከት ባለፉት 700 ዓመታት (1270-1974) ውስጥ ከአገር ውጭ የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን አስተማሪዎችና ጸሐፊዎች የተረትና የዘረኝነት ተፅእና በማሳደራቸው በአገራችን እስከ ዛሬ ድረስ ሳይንሳዊ የታሪክ ሜቴዶሎጂና ትምህርት ጎና አልዳበረም።

ከዚህ አኳያ፥ አንደኛ ከ330 እስከ 1950 ድረስ ለ1620 ዓመታት በ110 ወኪል አቡኖቹዋ አማካይነት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ስትመራ የኖረችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የአገሪቱን ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በ1000 ዓመተ ዓለም በእሪት ሕግና

ሃይማኖት ምህረት የፈጠሩ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ምርጥ የእይሁድ መሰፍንትና ካህናት ናቸው ብላ በከብረ ነገሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተማሪች። ሕዝቡም ራሱንና ታሪኩን ረስቶ ምርጥ የአይሁድ ዘር ነኝ ማለት ጀመረ። በዚህ የተረት እምነትና ትምህርት መሠረትም እንደአገውና እንደኦሮሞ ያሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ዜጎች የአይሁድ ዘር አይደላችሁም ተብለው በአገራቱ መንበረ-ሥልጣን ላይ እንዳይቀመጡ ተደረጉ። ለምሳሌ በዚህ መንገድ እና ምክንያት፥ በ1270 የአገው ተወላጅ አጼ ይትባረክ፥ እንዲሁም በ1916 የኦሮሞ ተወላጅ ልጅ ኢያሱ፥ ሁለቱም በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከተወገዙ በኋላ፥ በጦር ኃይል ከመንበረ ሥልጣን ተባረሩ። እንደእንሰላትም በስለት ታረዱ።

ሁለተኛ፥ ባለፉት ሦስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያን የግዕዝ ፊደል ከስምንቱ ሴማዊ የግዕዝ፥ የትግረ፥ የትግርኛ፥ የአርጎብኛ፥ የአማርኛ፥ የጉራግኛ፥ የሐረሪኛና የጋፋትኛ ቋንቋዎች ጋር አይተው የእውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁራን በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በነባር ኩሻዊና ናይሎቲካዊ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች ላይ ከ500 ዓመተ ዓለም ጀምሮ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ከአረቢያ ቀይ ባሕር ተሻግረው የገቡ «ሀበሻ» እና «እጋዓዚያን» የተባሉ ሁለት ሴማዊ ነጮና ምርጥ የአረብ ነገዶች ናቸው በማለት መላምት ፈጥረው በሳይንስና በታሪክ ስም ለኢትዮጵያውያንም ለዓለምም በስፋትና በዝርዝር አስተምረዋል።[9]

በእነዚህ የእውሮፓ ምሁራን እምነትና ትምህርት መሠረት፥ የኢትዮጵያ ነባር ኩሻዊና ናይሎቲካዊ ሕዝቦች የመንግሥትና የሥልጣኔ ሥርዓቶችን መገንባት የማይችሉ ኋላቀር ጥቁር ዘሮችና ሕዝቦች ናቸው። መጤ ነጭ ሴማውያን የተባሉ ሕዝቦች ደግሞ «ምርጥ» የሥልጣኔ ሐዋሪያት ናቸው። በመሆኑም መጤ ሴማውያን የተባሉ ኃይሎች በኢትዮጵያ ነባር ጥቁር ሕዝቦች ላይ ጭቆናዎችና ጌቶች ለመሆን በቅተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር ናቸው የተባሉ የኢትዮጵያ ጥቁር ሕዝቦች በቁጥር በመብዛታቸው ምክንያት በአናሳ መጤና «ምርጥ» ሴማውያን ቋንቋና ባህል ላይ ከባድ የብክለትና

[9] Job Ludolf, A New History of Ethiopia (1681); E. Littmann, tr. and ed., Saba sche, Greichische und Altabessinische Inschriften Book IV, Deusche Aksum-Expedition (DAT) (Berlin, 1913); Conti Rossini, "Expedition et Possessions des Habashat en Arabie", Journal Asiatique, Vol. 18 (1921); E. Ullendorf, The Semitic Languages of Ethiopia (1955); Ibid., The Ethiopians (1966).

የብልሽት ተፅዕኖ እንዳስከተሉ በተጠቀሱ ምሁራን ተገልጿል። በሌማውያኑ ምርጥ ቋንቋና የሥልጣኔ ባህል ላይ የተባለውን ብክለትና ብልሽት አድርሰዋል ተብለው ከተከሰሱ ነባር ኢትዮጵያውያን መካከል የቤጃ፥ የአገውና የኦሮሞ ኩሻዊ ሕዝቦች በመጀመሪያ ደረጃ ተወንጅለዋል።

ይህን የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ በሁለት የኩሽና የሴም «ጠላት» ዘሮችና ሕዝቦች መካከል የሚከፍለውን ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ (1) *The Semitic Languages of Ethiopia (1955)* እና (2) *The Ethiopians (1966)* በተሰኙ መጽሐፎቹ በ1960ዎችን በዓለም ላይ በዓይነትና በብዛት ያሰራጨው የእንግሊዙ ይሁዳዊ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁር ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ኡለንዶርፍ (Edward Ullendorf) ነው። ፕሮፌሰር ኡለንዶርፍ (The Ethiopians) ስለኢትዮጵያስ በተሰኘው መጽሐፉ በግልፅና በይፋ እንዳስተመጠው፥

1. "A glance at any linguistic map of Ethiopia will show almost dramatically, the small, yet compact, Semitic island stretching from northern Eritrea to Addis Ababa into the south surrounded on all sides by a vast Cushitic sea, with some Nilotic currents in the west and two tiny Semetic islets in the east (Harari) and the south (Gurage).

"For the reasons which already have been stated in previous chapters, we shall mainly confine ourselves in this survey to the Semitic languages of Ethiopia, since they express that "real" Abyssinia as we know it and are the virtually exclusive carriers of Ethiopian civilization, literature and intellectual prestige ... the impact of the Cushitic languages on their Semitic superstrata has in some cases been considerable, especially in the field of syntax, and will to that extent be touched upon in the following pages. The position has been well summed up by M. M. Moreno in the form of a general "law": the socially superior minority imposes its language by virtue of its prestige while the majority "deforms" that language by virtue of its large numbers."[10]

2. "The Gallas had nothing to contribute to the civilization of Ethiopia; they possesed no material or intellectual culture, and their social organization was at a far lower stage of development than that of the population among whom they settled. They were not the only cause of the depressed state into which the country now sank, but they helped to perpetuate a situation from which even a physically and spiritually exhausted

[10] Ibid., The Ethiopians, pp. 116-117.

Ethiopia might otherwise have been able to recover far more quickly."[11]

ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአግትና የአክሱም የድንጋይ ላይ ጽሑፎችና የአካባቢው ጥንታዊ የአረብ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት ከጻፉ ገነቢ ሰነዶች በስተቀር፥ ከ1270 እስከ 1974 ድረስ በኢትዮጵያውያንና በአውሮፓውያን ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የተጻፉ ሰነዶችና መጻሕፍት በሙሉ፥ በ1972 በሁለት የኢትዮጵያ ዘመናዊ የታሪክ ቀዳሚ ምሁራን ግለትም በዶክተር ሰርጉ ሀብለሥላሴና በፐሮፌሰር ታደሰ ታምራት በቅደም ተከተል *(Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270* እና *Church and State in Ethiopia 1270-1527)* በተሰኙ ርዕሶች የተጻፉትን መጻሕፍት ጨምሮ፥ ከላይ የተጠቀሱ የግብፅና የአውሮፓ ዘረኛ አስተማሪዎች፥ ምሁራንና ጸሐፊዎች እምነትና ትምህርት ነጸብራቆች፥ መግለጫዎች ማሰፋፊያዎች ብቻ ናቸው ለማለት ይቻላል።

ለምሳሌ በታዋቂ የኢትዮጵያ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሁርና ጸሐፊ በፐሮፌሰር ታደሰ ታምራት እምነትና ትምህርት መሠረት፥ ባለፉት 2500 ዓመታት በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ፥ ከአጎራባቹ አረቢያ ምድር በፍልሰ የገቡ «ምርጥ» እና «ሰልጡን» ሴማዊ ሕዝቦች ኑሮና «ኋላቀር» ኩሻዊ ሕዝቦችን በሚከተሉት አምስት ልዩ ልዩ ዘመናት ገዝተዋቸዋል። በፐሮፌሰሩ ታልና ትምህርት በግልፅና በይፋ እንደተባለው፤

1. "The ultimate origins of the Ethiopian State lie in the remote past, when Sabean settlements were established in northern Ethiopia."[12]

2. "South Arabian immigrants began to settle in the hinterland of Adulis as far inland as the surroundings of Aksum before the fifth century B.C."[13]

3. "From then on, their settlements became the spearhead of a long process of Semitization of the Ethiopian region."[14]

4. "The extensive area of north-east Africa, between the Red Sea and the Nile as far north as the First Cataract and including the whole of the Ethiopian region, is still predominantly inhabited by a large family of people known to anthropologists and linguists as the Kushites."[15]

5. "It is precisely in this characteristic pattern of a few South Arabian or Sabeanized individuals moving far into the interior and assuming political and cultural leadership among the Kushitic people of the Ethiopian region that one can best envisage the origin and the eventual expansion of the embryonic state organization long established in northern Ethiopia."[16]

6. "Thus both for its cultural inspiration and its economic development the Ethiopian region depended entirely on South Arabia."[17]

7. "As has already been suggested above, the slow penetration of social and cultural influences into these southern areas must have started in the pre-Aksumite period."[18]

8. "It is in fact apparent that the Aksumite conquests were only a second major wave of "Semitic" expansion into the interior of the Ethiopian highlands."[19]

9. "With the introduction of the Church into Aksum, this process of expansion got yet another dimension, and it continued throughout the early and the late medieval period."[20]

10. "One of the most characteristic aspects of the process of expansion was the establishment of military colonies in the newly conquered territories. It has been said above that the Agaw were the native inhabitants of the Ethiopian plateau north of the river Jama. The immigrants from South Arabia settled in the Northen part of this region and lived among the Agaw population, who gradually adopted the language of the settlers. These linguistically Semitized natives later constituted the dominant section of the peoples of Aksum. As the Kingdom acquired additional territories, large groups of these people were apparently recruited and settled in distant frontier stations. Here they intermarried with the local people and formed yet another Semitized zone in the interior of the Agaw country, which was gradually passing into the sphere of Aksumite political influence. It is apparent that all the Semitic linguistic groups South of the Tigre region had a similar origin. The Amhara tribal group is the most northerly of these communities and was probably the earliest to be established as such.

Traditional material on the Amhara is lacking and it is impossible here to give any specific dates for their origin."[21]

11. "Ethiopian history has a particular tendency to repeat itself. The military exploits of King Amda-Seyon strongly remind one of the great achievements of the Aksumite Kings Ezana and Kaleb on whom he seems to have modeled himself. More recently, in the nineteenth century, the extensive conquests and

[11] Ibid., p. 76.
[12] Tadesse Tamrat, Church and state in Ethiopia 1270-1527, (1972), p. 5.
[13] Ibid.,
[14] Ibid.,
[15] Ibid.,

[16] Ibid., p. 12.
[17] Ibid., p. 15.
[18] Ibid., p. 19.
[19] Ibid.,
[20] Ibid.,
[21] Ibid., p. 37.

expansion of Amda-Seyon were dramatically re-enacted by Emperor Minilik, who, just like his fourteenth-century predecessor, had the Shawan plateau as the centre of his military activities. It remains to be seen, however, whether Minilik and his successors have been more successful than their medieval counterparts in the essential task of building an Ethiopian nation.[22]

ሁለት ልዩ የኩሽና የሴም ተግራሪ ዘሮችና ሕዝቦች ናቸው «የተባሉ» ኃይሎች ላለፉት 2500 ዓመታት በኢትዮጵያ ምድር ላይ በመሬትና በሰፊራ ምክንያቶች በሥፍራና በጊዜ በማያቋርጥ ግጭትና ጦርነት ላይ እንደኖሩ ተደርጎ የቀረበው ይህ የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ትርጉም በሁሰንትናው የተወሰደው ከኢጣሊያዊ ጸሐፊ ከሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ መላምትና ከላይ ከተመለ ከተው ከፕሮፌሰር ኡለንዶርፍ ሐተታ ነው።[23]

አሁን እጭርና ዋናው ነገር፥ የሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ የኢትዮጵያ ታሪክ መላምት ሆነ የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ተዛማጅና ቀጣይ ትምህርት፥ ከመነሻውም ሆነ ከመረጃና ከይዘት ወይም ከታሪካዊ ዕድገትና ሂደት አኳያ፥ የአገሪቱን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጎብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ ከተጨባጭ ሳይንሳዊ መረጃና ሥልተ ጥናት በትክክል አልገለፀም። ሊገለፅም አይችልም። ምክንያቱም በእነኮንቲ ሮሲኒ እንደተባለው የኢትዮጵያ ታሪክ የንባር ኩሻውያንና የወራሪ ሴማውያን ጦርነት መግለጫ መሆኑን በሥፍራና በጊዜ መስፈርትና ሚዛን የሚያሳይ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። የታሪክ መረጃ ሳይኖር ታሪክም ሆነ የታሪክ ባለሙያ እንደማይኖር የታወቀ ነው።

በመሆኑም አሁን የኢትዮጵያን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ በአዲስ ሜቶዶሎጂ፥ መስፈርትና ሚዛን እንደገና ማጥናትና ለህሉም የአገሪቱ ዜጎች በሚገባና በሚጠቅም መንገድና ቋንቋ መግለፅና ማስተማር አማራጭ የሌለው የእውነትና የእውቀት ግዴታ ነው።

[22] Ibid., p. 302.
[23] Ibid., pp. 1-12.

የመረጃ ምንጮች
Bibliography

1. Alvarez, F. The Prester John of Indies, 2 Vols., trs and ed., C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford (1966).
2. Anfray, F., "Recherches Archaelogique en Ethiopie", Academic des Inscriptions et Belles-Lettres (Paris, 1978).
3. Anfray, F. "Les Steles du Sud Shoa et Sidamo", Annales D'Ethiopie. No. 12 (1982).
4. Arabfaqih, Histoire de la Conquete de L'Abyssinie, tr. and ed., R. Basset, (1897).
5. Aren, Evangelical Pioneers in Ethiopia: Origins of the Evangelical Church Mekane Yesus (1978).
6. Bahrey, History of the Galla, C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford, trs. and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646, (London: 1954).
7. Beckingham C. F., "A Note on the Topography of Ahmed Gragn's Campaign in 1542", Journal of Semitic Studies, Vol. 4 (1955).
8. Beckingham, C. F. and G. W. B. Huntingford (1966). trs. and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646 (1954).
9. Beke, C. T., The French and English in the Red Sea, (1862).
10. Bent, J. T., The Sacred City of The Ethiopians, (1896).
11. Bernal, M., Black Athena: The Afrosiatic Roots of Classical Civilization, Volume I: The Fabrication of Ancient Greece 1785-1985 (1997). Volume II: The Archaeological and Documentary Evidence (1991).
12. Bernand, E. A., Drewes, A. J., Schneider, R. et Anfray, F., trs. and eds., Recueil des Inscriptions de L'Ethiopie Periods Pre-Axoumite et Axoumite, (Forthcoming).
13. Braukamper, U., "Islamic Principalities in South- Eastern Ethiopia between the 13th and 15th Centuries", Part I and II, Ethiopianist Notes, No. 1 (1977).
14. Braukamper, U. Geschichte der Hadiya Sud-Athiopiens, (1980).
15. Bruce, J. Travels To Discover the Source of the Nile, 5 Vols., (1790).
16. Budge, E. A. W., A History of Ethiopia, (1966).
17. Budge, E. A. W., The Queen of Sheba and Her Only Son Menyelek, (1922).
18. Coquote A. et Drewes, A. J., "Les Monuments Recueillis a Maqale", Annales D'Ethiopie, No. 1 (1955).
19. Cerulli, E., Ethiopia's Relations with the Muslim World, UNESCO, History of Africa, Vol. III (1988).


20. Christides, Vassilios, "The Himyarite-Ethiopian War and the Ethiopian Occupation of South Arabia in the Acts of Gregentius, Ca. 530 A. D." AE. Vol. 9 (1972).
21. Conti Rossini, Historia Regis Sarsa Dengil, (1907).
22. Conti Rossini, "Expeditions et Possessions des Habashat en Arabie", Journal Asiatique, Ser. 18 (1921).
23. Conzelman, W. E. (tr. and ed.), Chronique de Galawdewos, Roi d' Ethiopie, (1895).
24. Cosmas, Christian Topography of Cosmas, tr. and ed. J. W. McCrimble (1897).
25. Crawford, O. G. S., Ethiopian Itineraries, Circa 1400-1524, (1958).
26. Crummey, D., Priests and Politicians: Protestants and Catholics Missions in Orthodox Ethiopia, 1830-1868 (1972).
27. Cuoq, J., L'Islam en Ethiopie des Origines Au XVI Siecle, (1981).
28. Drewes, A. J., Inscriptions de L'Ethiopie Antique (1962).
29. Doresse, J., Histoire Sommaire de la Corne Orientale de L'Afrique, (1971).
30. Erlich, H., Ethiopia and The Middle East, (1994).
31. The Fetha Nagast: The Law of The Kings, tr. and ed., Paulos Tzadau, (1968).
32. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo) "Early Portuguese Imperialism in Ethiopia, 1490-1632: Origins, Responses, and Consequences", MA. Thesis (Howard University, Wash. D. C., 1971).
33. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), "Emperor Menelik's Ethiopia, 1865-1916: National Unification OR Amhara Communal Domination", Ph.D. Dissertation (Howard University, Wash. DC, 1974).
34. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), "Historical Origins and Development of the Eritrean Problem 1889-1962", A Current Bibliography on African Affairs, Vol. 7, No. 3, (1974).
35. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), History and Historical Maps, National Atlas of Ethiopia, (1988).
36. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), Ethiopia: A Cradle of History, (1989).
37. Gobalt, S., Journal of a Three years' Residence in Abyssinia (1850).
38. Greenberg, J. H., African Linguistic Classification, UNESCO, African History, Vol. 1, (1981).
39. Hess, Robert, "Chapter 4: Toward A History of the Falasha", Deneil F. McCaall, ed., Eastern African History, (1969).
40. Hess, Robert, "An Outline of Falasha History", Proceeding of the 3rd International Conference of Ethiopian Studies, (1966).
41. Hudson, G., "Language Classification and the Semitic Pre-History of Ethiopia", Folia Orientalia, Vol. 18, (1977).

42. Hudson, G., "Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory", Abbay, Vol. 9, (1918).
43. Huntingford, G. W. B., tr. and ed., The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia, (1965).
44. Huntingford, G. W. B., tr. and ed., The Periplus of the Erythrean Sea (1980).
45. Ibn Fadl A. Umari, Masalik El Absar Fi Amalik El Masar, tr. and ed., G. Demombynes, (1927).
46. Isenberg C. W., and Krapf, J. L., Journals of Isenberg and Krapf (1843).
47. Jamme, W. F., tr. and ed., Sabaean Inscriptions from Mahram Bilqis (Marib), (1962).
48. Jones A. H. M., and Monroe, E., A History of Ethiopia, (1966).
49. Joussaume, R., Le Megalithisme En Ethiopie: Monuments Funeraries Protohistorique Du Harar (1974).
50. Kammerer, A., Essai sur L'Histoire Antique D'Abyssinie: Le Royaume D'Aksum Et Ses Voisins D'Arabe Et De Meroe, (1926).
51. Krapf, J. L., Travels and Researches in East Africa. (1860).
52. Kobishchanov, Y. M., Axum, (1979).
53. Lange, W., History of the Southern Conga: SouthwesternEthiopia, (1982).
54. Lapiso G. Dilebo, The Italo-Ethiopian War of 1887-1896 From Dogali to Adwa, (1996).
55. Leclant, J., "L'Exploration Des Cote Da Mer Rouge : A La Quete De Pount Et Des Secretes De Mer Erythree", AE, No. 11, (1978).
56. Leslau, W., "South-East Semitic: Ethiopic and South Arabic', Journal of the American Oriental Society, Vol. 63, (1943).
57. Leslau, W., Falasha Anthology: The Black Jews of Ethiopia, (1951).
58. Levin, D. N., Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society, (1974).
59. Littmann, E. tr. and ed., Sabaische Griechische, und Altabessinische Inschriften, Deutsche Aksum Expedition Book IV (DAE) Book IV (1913).
60. Ludolf, Job, A New History of Ethiopia (1681).
61. Maqrizi, The Book of the True Knowledge of the History of the Moslem Kings in Abyssinia, Tr. by G. W. B. Huntingford, (Typescript, 1955).
62. Murtonen, A., Early Semetic: A diachronical Inquiry into the Relationship of Ethiopic to the Other so-called South-East Semetic Languages, (Leiden: Brill, 1967).
63. "Negash: The Second Mecca", Tigrai Culture, Tourism and Information Bureau (Mekelle, 1997).
64. Norris, H. T., "The Himyaritic Tihama: Evidence for a Multi-Racial Society in Pre-Islamic and Early Islamic Arabia," Abbay, No. 9 (1978).

65. Pankhurst, R. An Introduction to the Economic History of Ethiopia, (1961).
66. Perruchon J., tr. and ed., Les Chroniques de Zara Yaeqob et de Baeada Mariam, (1893).
67. Perruchon, J. tr. and ed., "Histoires des Guerres d'Amba Syon, Roi D'Ethiopie", Journal Asiatique, Ser. 8, Vol. 14 (1889).
68. Rubenson, S., The Survival of Ethiopian Independence (1976).
69. Salibi, Kamal, The Bible Came from Arabia, (1985).
70. Sauneron, Serge, The Priests of Ancient Egypt, (1960).
71. Schneider, M., "Steles Funeraires Arabes de Quiha", Annales D'Ethiopie, Vol. 7 (1967).
72. Schneider, R. "Deux Inscriptions Sudaribique du Tigre", Biblothetica Orientalist, vol. 30, Nos. 516 (1973).
73. Schneider, R. "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne" Documents Histoire Civilisation Ehiopienne, RCP. 230, CNRS, FASC. 7 (1976).
74. Schneider, R., "On the Evolntion of the Ethiopian Writing", Lecture Text (Addis Ababa, 1982).
75. Schneider, R., "On the Daamatite State, Kings, and Gods", Written note to the author (Addis Ababa, 1982).
76. Schneider, R., "L'Inscription Chretienne d'Ezana en Ecriture Sudarabie", AE, Vol. 10 (1976).
77. Taddesse Tamrat, "The Abbots of Dabra-Hayq", 1248-1535", Journal of Ethiopian Studies, Vol. 8, No. 1 (1970).
78. Tadesse Tamerat, Church and State in Ethiopia 1270-1527, (1972).
79. Tadeschi, S. "Note Storiche Salle Isole Dahlack," Proceedings of The Third International Conference of Ethiopia Studies. 3 Vols., (Addis Ababa, 1966).
80. Sergew Habte Sellassie, Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270 (Addis Ababa, 1972).
81. Sergeant, R. A., "South Arabia and Ethiopia: African Elements in the South Arabian population", Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies, 3 Vols. (Addis Ababa: HSIU, 1966).
82. Shinnie, P. L., Meroe: A Civilization of the Sudan, (1967).
83. Trimingham, J. S., Islam in Ethiopia, (1966).
84. Ullendorff, E., The Semitic Languages of Ethiopia (1955).
85. Watt, W. A., Muhammad et Mecca, (1952).
86. Watt, Muhammad at Medina, (1956).
87. UNESCO, General History of Africa I; Methedology and African Prehistory, (1981).
88. Unger, M. F., The New Unger's Bible Handbook, (Chicago: Moody Press, 1984).

89. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ አዲስ አበባ፥ ንግድ ማተሚያ ቤት 1982)።
90. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ የገበር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም (1983)።
91. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ (1974)።
92. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የምርትና የገበል ዕድገት በከምባታና ሀዲያ (1975)።
93. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ (1985)።
94. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ «ብሄራዊ ስሜት ብቻውን የታሪክ ምሁር አያደርግም»፥ እፎይታ ቅ6 ቁ2 (1990)።
95. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ «ኢትዮጵያዊነት ትላንትና ዛሬ»፥ እፎይታ ቅ7 ቁ1 (1991)።
96. አጥሙ ጊዮርጊስ፥ የጋላ ታሪክ (ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ በሁለት ቅጾች) (1907)።
97. ገበረ ሥላሴ፥ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፥ 1959።
98. ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ፥ የታሪክ ማስታወሻ፥ 1901-1922 (ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ። የልጅ አያሱና የንግሥት ዘውዲቱ ዘመናት ዜና መዋዕል)።
99. ተክለ ሥላሴ (ጸሐፊ ተዕዛዝ)፥ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605-1632 (ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ)።
100. ማኅተመ ሥላሴ ወ/መ፥ ዝክረ ነገር፥ (1962)።
101. ገድለ ተክለ ሃይማኖት (1973)።
102. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ፥ አክሱም ዛጉዌ (1966)።
103. አለቃ ታዬ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፥ (1958)።
104. ቅዱስ ቁርአን ያማርኛ ትርጉም (1961)።
105. «አንድነት»፥ ብርሃንና ሰላም (ታኅሣሥ 19 ቀን 1926)
106. «ሰለሚሲዮናውያን ማህበር አቋቋም የወጣ ድንጋጌ» ነጋሪት ጋዜጣ ቅ.3 ቁ.3 (ነሐሴ 21 ቀን 1936)።
107. «የልጅ ኢያሱ ምሥጢራዊ አገዳደል» እፎይታ፥ ቅ.2 ቁ.5/6 (ሐምሌ ነሐሴ 1985)።
108. የ1948 የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ምሥጢራዊ የብሔረሰብና የሃይማኖት ሰነድ የመዝገብ ቁጥር 140/48 በ8/10/48 የተመዘገበ።

የውጭ ኃይሎች ግፊት፣ የኢትዮጵያ የትግልና የድል ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።



ይህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች በሰነድ፥ በትውፊት፥ በአርኪኦሎጂ፥ በሊንጉዊስቲክስና በፖሌኦንቶሎጂ መረጃዎች ላይ በዘመናዊ የጥናት ሜቶዶሎጂ በአገርኛ ቋንቋ የተካሄደና ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የተከሰተውን የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ የሚገልጽ የአገራቱ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ጥናት ነው። ቋንቋዎቹና ሃይማኖቶቹ የኢትዮጵያውያን የጋራ ህልውናና ማንነት ህያው መግለጫዎችና ማስረጃዎች ናቸው።

በመጽሐፉ እንደተገለደውና በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፥ የሳይንስና የባህል ድርጅት እንደተረጋገጠው ክፍለ አህጉሩ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተበት ብሎም ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ ለዛሬ የዓለም ሕዝቦችና ቋንቋዎች የፍለሳና የስርጭት አንቅስቅሴ መነሻ የሆነው ምድር ነው። በሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት መሠረት የኢትዮጵያ አራቱ ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ኦሞአዊና ናይሎቲካዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ሁሉም የክፍለ አህጉሩ ነባር ሕዝቦች ናቸው።

ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት የአካባቢው ነባር ሕዝቦችና መንግሥታት በአፍሪካ፥ በእስያና በአውሮፓ አጎራባች አህጉራት በተነሱ ጥንታዊ የግብፅ፥ የሚሮዌ፥ የሳባ፥ የግሪክ፥ የሮምና የአረብ አገሮች ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር በጂኦ-ፖለቲካ፥ በሃይማኖትና በባህል የቀረበ መስተጋብርና መወራረስ እንደነበራቸው ከታሪክ መረጃና ትምህርት ተረጋግጧል። በተጠቀሱት የመስተጋብርና የመወራረስ ምክንያቶች፥ መንገዶችና ሥርዓቶች ከመካከለኛው ምሥራቅና ከአረቢያ የገቡ የክርስትናና የእስላምና ሃይማኖቶች ከአገራቱ ነባር አዋማዊ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጋር ተዋህደው ለኢትዮጵያ የክርስቲያንና የእስላም መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ድርጅታዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ለመሆን እንዴት እንደበቁ መጽሐፉ በታሪካዊ መረጃና ትምህርት በዝርዝር ያሳያል።